
በዘፍጥረት ላይ የተሰጡ ስብከቶች (I)

ቅዱስ ስላሴ
ለ ሰዎች ያለው ፈቃድ



PAUL C. JONG

Worldwide websites of



The New Life Mission

The Official Website of The New Life Mission

www.nlmission.com or
www.bjnewlife.org

Please find your vernacular websites below.
You can download Christian e-books and request Christian books for free.
Feel free to visit our websites below right now!

A
www.nlmafghanistan.com
www.nlmafrikaans.com
www.nlmalbania.com
www.nlmamharic.com
www.nlmangola.com
www.nlmarabemirates.com
www.nlmarabic.com
www.nlmargentina.com
www.nlmarmenia.com
www.nlmaruba.com
www.nlmaustralia.com
www.nlmaustria.com

B
www.nlmbahamas.com
www.nlmbahrain.com
www.nlmbangladesh.com
www.nlmbelarus.com
www.nlmbelgium.com
www.nlmbengali.com
www.nlmbenin.com
www.nlmbhutan.com
www.nlmbolivia.com
www.nlmbotswana.com
www.nlmbrasil.com
www.nlmbriton.com
www.nlmbrunei.com
www.nlmbulgalia.com
www.nlmburkinafaso.com
www.nlmburundi.com

C
www.nlmcameroon.com
www.nlmcanada.com
www.nlmcebuano.com
www.nlmchichewa.com
www.nlmchile.com
www.nlmchin.com
www.nlmchina.com
www.nlmcolombia.com
www.nlmcongo.com
www.nlmcostarica.com
www.nlmcotedivoire.com
www.nlmcroatia.com
www.nlmczech.com

D
www.nlmdenmark.com
www.nlmdioula.com
www.nlmdominica.com
www.nlmdrcongo.com
www.nlmdutch.com

E
www.nlmecuador.com
www.nlmegypt.com
www.nlmelsalvador.com
www.nlmequatorialguinea.com
www.nlmethiopia.com

F
www.nlmfinland.com
www.nlmfrance.com
www.nlmfrench.com

G
www.nlmgabon.com
www.nlmgeorgian.com
www.nlmgerman.com
www.nlmgermany.com
www.nlmghana.com
www.nlmgreek.com
www.nlmgrenada.com
www.nlmguatemala.com
www.nlmgujarati.com

H
www.nlmhaiti.com
www.nlmhindi.com
www.nlmholland.com
www.nlmhonduras.com
www.nlmhungary.com

※ Some of these websites may not work because they are still under construction.

Worldwide websites of The New Life Mission

I
www.nlm-india.com
www.nlmindonesia.com
www.nlmiran.com
www.nlmiraq.com
www.nlmisrael.com
www.nlmitaly.com

J
www.nlmjamaica.com
www.nlmjapan.com
www.nlmjavanese.com

K
www.nlmkannada.com
www.nlmkazakhstan.com
www.nlmkenya.com
www.nlmkhmer.com
www.nlmkinyarwanda.com
www.nlmkirghiz.com
www.nlmkirundi.com
www.nlmkorea.com

L
www.nlmlatvia.com
www.nlmluganda.com
www.nlmluo.com

M
www.nlmmadi.com
www.nlmmalagasy.com
www.nlmmalayalam.com
www.nlmmalaysia.com
www.nlmmarathi.com
www.nlmmauritius.com
www.nlmmexico.com
www.nlmmindat.com
www.nlmmizo.com
www.nlmmoldova.com
www.nlmmongolia.com
www.nlmmyanmar.com

N
www.nlmnepal.com
www.nlmnewzealand.com
www.nlmnigeria.com
www.nlmnorthkorea.com
www.nlmnorway.com

P
www.nlmpakistan.com
www.nlmpanama.com
www.nlmperu.com
www.nlmphilippines.com
www.nlmpoland.com
www.nlmportugal.com
www.nlmportuguese.com
www.nlmprcongo.com

Q
www.nlmqatar.com

R
www.nlmromania.com
www.nlmrussia.com
www.nlmrwanda.com

S
www.nlmsaudiarabia.com
www.nlmserbian.com
www.nlmshona.com
www.nlmsingapore.com
www.nlmslovakia.com
www.nlmslovene.com
www.nlmsolomon.com
www.nlmsouthafrica.com
www.nlmspain.com
www.nlmspanish.com
www.nlmsrilanka.com
www.nlmsuriname.com
www.nlmswahili.com
www.nlmswaziland.com
www.nlmsweden.com
www.nlmswiss.com

T
www.nlmtagalog.com
www.nlmtaiwan.com
www.nlmtamil.com
www.nlmtanzania.com
www.nlmtelugu.com
www.nlmthailand.com
www.nlmtogo.com
www.nlmtonga.com
www.nlmturkey.com

U
www.nlmuganda.com
www.nlmukraine.com
www.nlmurdu.com
www.nlmusa.com

V
www.nlmvenezuela.com
www.nlmvietnam.com

Z
www.nlmzambia.com
www.nlmzimbabwe.com
www.nlmzou.com



በዘፍጥረት ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሄር አላማ

ቤት መስራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በመጀመሪያ ለዚያ የተለየ አላማ ገጣሚ የሆነ ንድፍ መንደፍ አለበት ከዚያም በዚያ ንድፍ መሰረት ቤቱን ይሰራል ልክ እንደዚሁም ጌታችን የሰውን ዘር ከሐጢያት ለማዳንና ሰዎችን የእግዚአብሄር ሕዝብ ለማድረግ ንድፍ አስፈለገው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሙሉ የእግዚአብሄርን ንድፍ ቢያሳየንም በተለይ የዘፍጥረት መጽሐፍ ዕቅዱን በስፋት ይገልጣል ከእግዚአብሄር የደህንነት ዕቅድ ውስጥ አላማውን እጅግ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚገልጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት ነው እኛም በእግዚአብሄር ቃል በማመን እርሱ ለእኛ ያለውን ፈቃድ መረዳት እንችላለን።

እግዚአብሄር እኛን የፈጠረበት አላማ ምን ነበር? ጌታ የፈጠረን የእግዚአብሄርን ጽድቅና ፈቃዱን እንድናመሰግን ነው የሰማይንም መንፈሳዊ በረከቶችም ይሰጠን ዘንድ ነው ይህ ሁሉ አግዚአብሄር ለእኛ ሊገልጠው የፈለገው አሳቡ ነበር።

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ፈቃዱን ገልጦዋል እግዚአብሄር በቤተክርስቲያኑ በኩል በገለጠው በዚህ አላማ በማመንም ይህንን ልንቀበልና ልንደሰትበት ችለናል እግዚአብሄር የሰጠን በረከቶች በሙሉ ሁሌም ከእኛው ጋር ናቸው ሐሌሉያ!

ቅዱስ ስላሴ
ለ ሰዎች ያለው ፈቃድ

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።

በዘፍጥረት ላይ የተሰጡ ስብከቶች (I)

ቅዱስ ስላሴ
ለ ሰዎች ያለው ፈቃድ

PAUL C. JONG

ሐፍዚባ ፕብሊሽንግ ሐውስ
የኒው ላይፍ ሚሽን አገልግሎት
ሴኡል፤ ኮርያ

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

በዘፍጥረት ላይ የተሰጡ ስብከቶች (I)
ቅዱስ ስላሴ ለ ሰዎች ያለው ፈቃድ

የታተመው © 2013 by The New Life Mission
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው የዚህ መጽሐፍ የትኛውም ክፍል ከባለቤቱ የጽሁፍ ፈቃድ ውጪ ፎቶ ኮፒ ማድረግን መቅዳትን ወይም ማንኛውንም መረጃ በሚይዝ ወይም ይዞ የሚያስቀር ሲስተምን ጨምሮ በማንኛውም መልክ በኤሌክትሮኒክ ወይም በመካኒካል ወይም በማንኛውም መንገድ ማባዛት ወይም ማሰራጨት ክልክል ነው።።
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት *ከ1954ቱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ* ነው

ISBN 978-89-282-3246-8

Website : http://www.nlmission.com
http://www.bjnewlife.org
http://www.nlmbookcafe.com
E-mail : newlife@bjnewlife.org

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።።

የማውጫ ሰሌዳ

መቅድም ---------- 10

ምዕራፍ 1

መጽሐፍ ቅዱስ የደህንነት መጽሐፍ እንጂ የሳይንስ መጽሐፍ አይደለም
(ዘፍጥረት 1:1-2) ---------- 20

በወንጌል እውነት ብርሃን ሆናችኋልን?
(ዘፍጥረት 1:2-3) ---------- 48

ከጨለማ ስልጣን ወደ ልጁ መንግስት
(ዘፍጥረት 1:2-5) ---------- 74

አንደኛ ቀን፡ በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ
(ዘፍጥረት 1:1-5) ---------- 134

ከጠፈር በላይ ያለው ውሃና ከጠፈር በታች ያለው ውሃ
(ዘፍጥረት 1:6-8) ---------- 172

እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ውሆችን ለየ
(ዘፍጥረት 1:6-8) ---------- 204

እግዚአብሄርን ፈቃድ ለመፈጸም
(ዘፍጥረት 1:9-13) ---------- 258

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።

በእግዚአብሄር ስራ ውስጥ ለመሳተፍ
(ዘፍጥረት 1:9-13) ---------- 292

ከሐጢያታችን ሁሉ መዳን የምንችለው ሐጢያታችንን በሙሉ ስናውቅ ብቻ ነው
(ዘፍጥረት 1:9-13) ---------- 332

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ የእግዚአብሄር አገልጋዮች ሊያደርጉት የሚገባቸው ነገር
(ዘፍጥረት 1:14-19) ---------- 348

እግዚአብሄር የክብር ዕቃዎች አድርጎናል
(ዘፍጥረት 1:16-19) ---------- 368

ጻድቅ በእምነት ብቻ ይኖራል
(ዘፍጥረት 1:20-23) ---------- 388

ልቦቻችሁን በእግዚአብሄር ፊት አጽኑ
(ዘፍጥረት 1:20-23) ---------- 418

ከልባቸው በእግዚአብሄር ቃል የሚያምኑ የእምነት ሰዎች ሕይወት
(ዘፍጥረት 1:20-23) ---------- 438

እግዚአብሄር እኛን በአምሳሉ የፈጠረበት ምክንያት
(ዘፍጥረት 1:24-31) ---------- 458

በእግዚአብሄር መልክ ተፈጥረናል
(ዘፍጥረት 1:24-31) ---------- 480

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) **በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::**



መቅድም

- ቅዱስ ስላሴ ለሰዎች ያለው ፈቃድ -

ኤፌሶን 1:9-10 እንዲህ ይላል *«በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደ እንደ አሳቡ የፈቃዱን ምስጢር አስታውቆናልና በዘመን ፍጻሜም ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው»* እግዚአብሄር በዘፍጥረት መጽሐፍ አማካይነት ለእኛ ያለውን በጎ አሳብ እንድንገነዘብ ይሻል እግዚአብሄር ለእኛ ያለው ፈቃዱ የተገለጠው የት ነው? ይህ የተገለጠው እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባከናወነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ውስጥ ነው እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ወደተገለጠው ወደዚህ የእግዚአብሄር አሳብ በእምነት መቅረብ አለብን ያንን ለማድረግ የእግዚአብሄርን ቃል በምናጤንበት ጊዜ አሁን ያሉንን ስጋዊ አስተሳሰቦቻችንን መጣልና በእግዚአብሄር ቃልም በትክክል እንደተጻፈው ማመን ያስፈልገናል ሁላችንም እስከ አሁን ደረስ የተጠራቀመውን የተሳሳተ እውቀታችንን መጣልና እምነታችንን በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ በማኖር መንፈሳዊ አይኖቻችንን መክፈት አለብን::

በእግዚአብሄር በትክክል ማመን የምንችለው በቃሉ ውስጥ የተገለጡትን የእርሱን በጎ አሳቦች በትክክል ስንረዳ ብቻ ነው እግዚአብሄር የሰማያትንና የምድርን ፍጥረት ቃል የጻፈልን እነዚህን አሳቦች ሊገልጥልንና ሊያሳየን ነው ስላሴ አምላክ ዩኒቨርስን ሲፈጥር ለሰው ዘር እንዴት ያለ አሳቦች እንደነበሩት መረዳት አለብን እግዚአብሄር እያንዳንዱን ሰው በራሱ አምሳል ሊፈጥረው ፈለገ::

እግዚአብሄር ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ሲፈጥር ሌሎች ፍጥረታቶችን ሁሉ ከመፍጠሩ በፊት በመጀመሪያ ሰውን ቢፈጥር ኖሮ ሰው ለእግዚአብሄር በጎ አሳቦች እንቅፋት እንደሚሆን ግልጽ ነው ሰዎች በራሳቸው አስተሳሰብ ደረጃ ሊያስተውሉት ያልቻሉትን ማንኛውንም ነገር አይቀበሉም ስለዚህ ሰው የራሱን አስተሳሰቦች እስካልጣለ ድረስ የእግዚአብሄርን ፈቃድ የሚቃወም ይሆናል ምክንያቱም በስጋዊ እሳቤው የእግዚአብሄርን አሳቦች መረዳት አይቻለውምና በርካታ ሰዎች የእግዚአብሄርን ጽድቅ ሳያውቁ የእርሱን እውነተኛ ፍቅር እየተቃወሙ አይደሉምን?

የእግዚአብሄር የእውነት ቃል ጽድቁን የሚያሳይ ንድፍን ይመስላል በጨለማ በተሞላው በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ እግዚአብሄር የእውነት ብርሃን ሆንዋል እግዚአብሄር በመጀመሪያው የፍጥረት ቀን ከጨለማ ውስጥ ብርሃን እንዲሆን አዘዘ በዚህም ገና ከመጀመሪያው በጎ አሳቦቹን አስታወቀን ይህም በመንፈሳዊ ሁኔታቸው ለጨለሙት ልቦቻችን እውነተኛውን የሐጢያት ስርየት መስጠት ነበር የስላሴ አምላክ አሳብ በሰይጣን ማታለያዎች ለሞት ታስረን ሳለ ወደ ደህንነት ጸጋው እንድንመጣ ጨለማን በእውነት ብርሃን ማሸነፍ ነበር።

ሰማያትና ምድር በተፈጠሩበት በሁለተኛው የፍጥረት ቀን እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየ በሁለተኛው ቀን የተገለጠው የእግዚአብሄር አሳብ ቃሉን ከዲያብሎስ ቃሎች በመለየት ሁላችንንም ከሰይጣን ቃሎች የሚያድነን መሆኑ ነበር ስለዚህ በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተመስርተን የእምነት ሕይወታችንን መኖር አለብን ያንን ለማድረግም በመጀመሪያ በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ በተገለጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል በማመን መዳን አለብን በሦስተኛው ቀን እግዚአብሄር ከሰማያት በታች ያሉት ውሆች በሙሉ

በአንድ ስፍራ እንዲሰበሰቡና የብሉ እንዲገለጥ አዘዘ እግዚአብሄርን ይህንን ሲያዝዝ አሳቡ ሐጢያተኝነታችንን መግለጥና የእርሱን ጽድቅ ብቻ እንድንከተል ማድረግ ነበር።

ሰማያትና ምድር በተፈጠሩ በአራተኛው የፍጥረት ቀን እግዚአብሄር ጸሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብቶችን ፈጠረ በአራተኛ ው ቀን የተገለጠው የእግዚአብሄር አሳብ እግዚአብሄር የደህንነትን ብርሃን ለዚህ አለም የሚያሰራጨውና ፈቃዱን የሚፈጽመው በእርሱ ጽድቅ በማመን ጨለማውን በሚያበሩት አገልጋዮቹ እንደሆነ ለማሳየት ነበር በጠፈር ላይ ባሉት ጸሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብቶች እግዚአብሄር የእርሱን ጽድቅ የእርሱን አገልገሰዮችና ልባችንን እየገለጠ ነበር እግዚአብሄር በአምስተኛ ው ቀን ወፎች በሰማይ ላይ እንዲበሩና ውሃውም እንደየወገኑ በአሶች እንዲሞላ ባዘዘ ጊዜ የእውነተኛ እምነት ትክክለኛ ባህርይ ምን እንደሆነ ለሁላችንም እያሳየን ነበር እግዚአብሄር በአምስተኛ ው ቀን በሰራው ስራ አማካይነት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ጽድቁን ማወቅ እንደምንችልና በዚህ ቃል በማመንም እንቅፋቶቻችንን በሙሉ ማሸነፍና ድል ማድረግ እንደምንችል ገልጦዋል።

እግዚአብሄር በስድስተኛው ቀን ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ እግዚአብሄር ሰውን የፈጠረው ጽድቁን ሊገልጥና በሁላችንም በመክበር ሰዎችን ልጆቹ ለማድረግ ነበር ስለዚህ እግዚአብሄር በሰጠው የውሃና የመንፈስ ወንጌል አማካይነት የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበልና ጻድቁን አምላካችንን ማመስገን ይገባናል።

በመጨረሻም እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን አረፈ ይህ ሰባተኛው ቀን እግዚአብሄር ብቻውን ሊከብር እንደወደደ ያሳያል ምክንያቱም ሁሉንም ነገር አቅዶ በአሳቦቹ መሰረት ፈጽሞአልና ይህ ማለት እግዚአብሄር ዩኒቨርስንና የሰውን ዘር እንዲህ በመፍጠር በፈቃዱ መሰረት

ሁሉንም አጠናቋል ማለት ነው እግዚአብሄር በሰባተኛው ቀን ያረፈው እውነተኛ የሐጢያት ስርየትን ሊሰጠን፣ የእርሱ ልጆች አድርጎ ሊባርከንና መንግስተ ሰማያትን ሊሰጠን ነው።

ከዘፍጥረት ጠቅላላ ቃል እግዚአብሄር ለሰው ዘር ያለውን አሳብ መረዳት፣ በእርሱ ማመንና ደህንነታችንን ማግኘት አለብን የእምነት ቀደምቶቻችን ሁሉ በእግዚአብሄር ቃል መሰረት አምነው ኖረዋል በክብር ለመኖርም ቀድመውን ወደ እግዚአብሄር ዕረፍት ገብተዋል።

በዚህ በመጨረሻው ዘመን ለመኖር የእግዚአብሄርን መልንም አሳብ በትክክል ማወቅና በእርሱም ማመን አለብን አሁን የጌታ ዳግም ምጽአት ወደ እኛ እንደቀረበ ግልጽ ነው ስለዚህ በእግዚአብሄር ጽድቅ የሚያምኑ ሰዎች ግልጽ ባልሆኑ አንዳንድ የክርስትና ትምህርቶች ውስጥ መውደቅና ክቡር የሆነውን ጊዜ ማባከን የለባቸውም ነገር ግን ይልቁኑ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የእግዚአብሄርን ጽድቅ ማስፋፋት አለባቸው እኛ እውነተኛውን ዕረፍት የምናጣጥመው የእግዚአብሄር ጽድቅ የተገለጠበትን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል በመታመን ስንኖር ነው በእግዚአብሄር ጽድቅ በመኖር በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት መሞላት አለብን እኛ እውነተኛ ተስፋን እውነተኛዕረፍትንና እውነተኛ የዘላለም ሕይወትን ማጣጣም የምንችለው የእግዚአብሄርን ጽድቅ በማወቅና በማመን ነው።

ከአሁን ጀምሮ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመላው አለም የሚሰብኩ እጅግ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ በተመሳሳይ ጊዜም የአለም ሰዎች የአለም ፍጻሜ እንደተቃረበ ቢናገሩም በራሳቸው ደህንነት ላይ ፍላጎቶችን የሚያሳዩ ጥቂቶች እንደሆኑ እናያለን በዚህ በአሁኑ ዘመን አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ምን ያህል የእግዚአብሄርን ጽድቅ እንደማያውቁና በክርስትና ውስጥም

ሐሰተኛ ትምህርቶችና አሳፋሪ ድርጊቶች ምን ያህል እንደገነኑ እናያለን በርንታ ክርስቲያኖች የሐጢያቶቻቸውን ችግር መፍታት ሳይችሉ ቀርተው በመንፈሳዊ ጥማት እየተሰቃዩና እየጠፉ ነው::

አሁን እኛ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመላው አለም የማሰራጨት ጥሪ አለን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የፍርዱ ቀን በተቃረበበት በዚህ ዘመን በሕይወታችን የእግዚአብሄርን አሳብ መረዳት አለብን ያን ጊዜ ምን ማወቅ እንደሚገባንና ምን ማመን እንደሚገባን እንረዳለን አሀንም ድረስ በሐጢያት ታስራችሁ በሐዘን እየኖራችሁ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት እግዚአብሄር በሰጣችሁ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እንድታምኑና እውነተኛውን ደህንነታችሁን እንድታገኙ እመክራችኋለሁ::

በዚህ ዘመን ሕይወታችሁን ስትኖሩ በምን አይነት እውነት ማመን እንደሚገባችሁ በጥንቃቄ ልትመረምሩ ይገባል በእግዚአብሄር ጽድቅ ውስጥ ባለው ተጨባጭ እውነት ልታምኑ ይገባል በእግዚአብሄር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ አምናችሁም ልትኖሩ ይገባችኋል እምነታቸው ገና ያልበሰሉ ሰዎች ካሉ የእግዚአብሄር ጽድቅ ምን እንደሚል በትክክል ልናስተምራቸው ያስፈልገናል በዚህ በመጨረሻው ዘመን አስቀድመው ዳግም እንደተወለዱ ሰዎች ራሳችንን አሳልፈን ልንሰጥለት የሚገባን ተግባር እንዲያመኑና የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዲቀበሉ የእግዚአብሄርን ጽድቅ የሚገልጠውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በትክክል ለሌሎች ማስተማር ነው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ለተቀበሉ ሰዎችም ተግባራችን የእግዚአብሄርን ጽድቅ ለሚያገለግለው የጽድቅ ስራ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን እንዲቀድሱ ማስተማር ነው ቀሪውን ሕይወታችንን በእግዚአብሄር ጽድቅ በመታመን ለመኖር በምናደርገው ውጥን

ሊሳካልንና ከዚያም በጌታ ሕልውና ፊት ልንቆም ይገባናል።

በመላው አለም ለተበተኑት ጓደኞቼ ሁሉ ሰላምታዩን አቀርባለሁ እነዚህ ስብከቶች የታቀዱት አስቀድመው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላመኑና እንደዚሁም ይህንን ጽድቅ የማወቅ በእርሱ የማመንና ለእርሱ የመኖር ናፍቆት ላላቸው ሰዎች ሁሉ ነው በዚህ መጽሐፍ አማካይነት ሁላችሁም እግዚአብሄር ለእኛ ለሰዎች ያተራቀመልንን ፈቃድ ወደ መረዳትና መከተል እንድትደርሱና በእግዚአብሄር ላይ ባላችሁ እምነት አማካይነትም ድል እንድታደርጉ ተስፋዬና ጸሎቴ ነው እግዚአብሄር ሁላችሁንም በበረከቶቹ እንዲቀባችሁ እጠይቀዋለሁ።

የእግዚአብሄር ጽድቅ እናንተንና እኔን እንደሚጠብቀንና ሁላችንንም እንደሚባርከን አምናለሁ ሁላችንም ወደ እግዚአብሄር መንግስት እስከምንገባበትና እስከምንገናኝበት ቀን ድረስ በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ባለን የጋራ እምነታችን እውነተኛ ሕብረትን በመጋራት እንድንቀጥል እጅግ ልባዊ ጸሎቴ ነው። ✉

Paul C. Jong

ምዕራፍ 1

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ የደህንነት መጽሐፍ እንጂ የሳይንስ መጽሐፍ አይደለም

« ዘፍጥረት 1:1-2 »

«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር።»

«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ይህ የዘፍጥረት 1:1 ምንባብ መጽሐፍ ቅዱስን ስንገልጥ የምናገኘው የመጀመሪያው ቁጥር ነው እግዚአብሄር «በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» አለ እዚህ ላይ «ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ» ሲል ይህ የሚያብራራው ዳግም ያልተወለዱትን ሰዎች ልቦች ሁኔታ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሳይንስ መጽሐፍ አይደለም መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱን ሰው ከሐጢያት የሚያድን የእውነት ቃል ነው ለሰው ዘር የሐጢያት ስርየትን የሚያመጣ ቃል ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እግዚአብሄር ለሰው የተናገረውና የፈጸመው የተባረከ ቃል ነው እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«እናንተ በመዳህፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ*

ይመሰላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው» (ዮሐንስ 5:39) መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ዘር ከሐጢያት ማዳንና የዘላለምን ሕይወት መስጠት የሚችል ቃል ነው ስለዚህ ሰው ከሐጢያቶቹ እንዲድን ከሁሉ በፊት በቅዱሳት መጽሐፍት ቃል አማካይነት የልቡን ሁኔታ መገንዘብ አለበት::

እዚህ ላይ እግዚአብሄር «ምድርም ባዶ ነበረች» ሲል የእያንዳንዱን ሰው የልብ ሁኔታ እያብራራ ነው የእግዚአብሄር የሰው ሁሉ ልብ ልክ እንደዚህ ባዶ እንደሆነ በፍጥረቱም ደግሞ በዋናነት ሐጢያትን የተሞላ ስለመሆኑ ይናገራል በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ እነዚህ ሦስቱ የቅርጽ አልባነት፣ የባዶነትና የጨለማ ሁኔታዎች ይገኛሉ በሌላ አነጋገር ቅርጽ አልባነት፣ ባዶነትና ሐጢያት በሰዎች ልቦች ውስጥ በአእምሮዋቸውና በአስተሳሰቦቻቸው ውስጥ በጥልቀት ተቀምጠዋል የሰው አስተሳሰቦች «ቅርጽ አልባ» መሆናቸው የሚመላክተው የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል በማያውቁና በዚህ የተነሳም ኢየሱስ ክርስቶስን ያልተገናኙትን ሰዎች ነው «ባዶ» የሚለው ቃል የሚያመላክተው እርካታ ያጡትን የሐጢያተኞች ልቦች ነው በሌላ በኩል በሰው ልብ ጥልቅ ውስጥ ጨለማ መንሰራፋቱ የሰው ዘር ሐጢያቶች በልቦቻቸው ጥልቅ ውስጥ ተደብቀዋል ማለት ነው::

ጌታ ከሰጠን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ጋር በትክክል ያልተገናኙ ሰዎች ልቦቻቸው ቅርጽ አልባ መሆናቸው ተገልጦዋል በሌላ አነጋገር እነርሱ የእግዚአብሄር እውነት ምን እንደሆነ አያውቁም ማለትም የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ምን እንደሆነ አያውቁም ስለዚህ በራሳቸው አስተሳሰቦች ተጠምደው ይባዝናሉ የዚህ አለም ሰዎች የጠፉበት ምክንያቱ አስተሳሰቦቻቸው በዋናነት ግራ የተጋቡ በመሆናቸው ነው ግራ

የተጋቡት አስተሳሰቦቻቸው የራሳቸውን ችግሮች በሙሉ እንዳይፈቱ አዳጋች አድርጎባቸዋል።

የእያንዳንዱ ሰው ልብ ባዶና ቅርጽ አልባ የሆነበት ምክንያት በሰው ልብ ውስጥ የኢየሱስ ቃል አለመኖሩ ነው በሌላ አነጋገር አእምሮዋቸው ባዶና ግራ የተጋባ የሆነው ሰዎች የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል በልቦቻቸው ውስጥ ማኖር ስለተሳናቸው ነው በልቦቻቸው ውስጥ ባዶነት የነገሰው ልቦቻቸው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የሰጣቸው ጌታ ሊኖርባቸው ባለመቻሉ ነው።

በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ «ጨለማ» የሚያመላክተው የሰውን ዘር ሐጢያት ነው ይህ የሚያመላክተው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት በትክክል መረዳት ስለተሳነው ከሐጢያቶቹ ያልነጻበትን ሁኔታ ነው ሰው ሐጢያቶች ካሉበት ለዚህ ምክንያቱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አለማመኑ ነው ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል እውነት መሆኑን በእግዚአብሄር ፈቃድ መሰረት መረዳትና ማመን አለበት ነገር ግን ብዙ ሰዎች አሁንም ድረስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለማያምኑ ሐጢያት እስከ ዛሬ ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ መኖሩን ቀጥሎዋል ለዚህ ምክንያቱ እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን መላውን ዩኒቨርስና በውስጡ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረ ጌታ እንደሆነና ኢየሱስም ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንደደመሰሰ እውነቱን ስለማይገነዘቡ ነው አሁንም እንኳን አብዛኛው ሕዝብ የራሳቸውን መልንም ምግባሮች ብቻ ይናገራሉ እንጂ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል አያውቁትም መጽሐፍ ቅዱስ የራሳቸውን ጽድቅ ለማቆም የሚሹ እንዲህ ያሉ ሰዎች ለእግዚአብሄር ጽድቅ እንደማይገዙ ይናገራል። (ሮሜ 10:2-3)

ታዲያ በእነዚህ ሐጢያተኞች ልቦች ውስጥ ምን

ይከሰታል? ልቦቻቸው ሐጢያተኞች ስለሆኑ የእግዚአብሄር የደህንነት እውነት ምን እንደሆነ ስለማያውቁ ግራ በመጋባት ይሰቃያሉ የእግዚአብሄርን ቃል እንደተጻፈው በትክክል የማይቀበሉ ሰዎች ሁሉ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት ምን እንደሆነ በትክክል ማጥናትና መገንዘብ አለባቸው በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የተገለጠውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማያውቅ ማንኛውም ሰው ግራ በተጋቡት አስተሳሰቦቹ ይሰቃያል እንዲህ አይነት ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች ናቸው።

እንደተጠቀሰው በዛሬው ምንባብ ውስጥ «ምድር» የምታመላክተው የሰውን ልብ ነው ምድር (የሰው ልብ) ባዶና አንዳች ያልነበረባት መሆንዋ በእግዚአብሄር ፊት ያሉት ሐጢያቶቻችን ከጌታ ጋር እንዳንገናኝ እንደሚከለክሉን ያመላክታል በዚህ ምክንያት ልቦቻችን ግራ በመጋባትና በባዶነት ይጠመዳሉ በሌላ አነጋገር በሰዎች አእምሮ ውስጥ ግራ መጋባት የሚመጣው በእግዚአብሄር እውነተኛ የደህንነት ቃል ሳያምኑ ከእግዚአብሄር ርቀው ሲቅበዘበዙና ከውሃው ከደሙና ከመንፈሱ እውነት ሲንሸራተቱ ነው አጋር ምዕመናኖቼ ሰው ሰማያትንና ምድርን የፈጠረውን እግዚአብሄርን አዳኙ አድርጎ አስንልተቀበለ ድረስ ትክክለኛውን እውነት ማወቅ አይችልም ሰው በግራ መጋባት የሚሰቃየው የእግዚአብሄር እውነት እውቀት ከሌለው ነው እርሱ በዚህ አለም ላይ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ማን እንደፈጠረውና እግዚአብሄርም ማን እንደሆነ ሊገነዘብ አይችልም በርካታ ሰዎች አምላክ አለት ይሁን ጨረቃ፣ ትልቅ ዛፍ ይሁን ወይም ዝሆን ምን እንደሆነ ሳያውቁ እንዲህ ባለው ግራ መጋባት ውስጥ ወድቀዋል እግዚአብሄር የሐጢያተኛ ልቦችን ሁኔታ አስመልክቶ ሲናገር «ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ» ያለው ለዚህ ነው።

ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻቸው የማይቀበሉ ከሆነ በውሸንብር ይሞላሉ ሁሉን የፈጠረው አምላክ ሌላ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን፣ ኢየሱስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር መምጣቱን፣ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀትም የሰውን ዘር ሐጢያቶች ለአንዱና ለመጨረሻ መውሰዱን፣ ክቡር ደሙን በመስቀል ላይ ማፍሰሱንና ዳግመኛም ከሙታን ተነስቶ ወደ ሰማይ ማረጉን በትክክል ካልተገነዘቡ ሕይወታቸውን በሙሉ በውሸንብር፣ በባዶነትና በጨለማ ውስጥ ታስረው ይኖራሉ በጣም ብዙ ሰዎች ለዘላለም በውሸንብር፣በባዶነትና በጨለማ ውስጥ እየተቅበዘበዙ ከሐጢያቶቻቸው መዳን የማይችሉት ለዚህ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሄር አብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ ዩኒቨርስን ፈጠረ ይህ እውነት ነው ወይስ አይደለም? በእርግጥም እውነት ነው ይህ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ የዩኒቨርስ ባለቤት ነው ማለት ነው የሰው ዘር ሐጢያት ሌላ ሳይሆን ከእግዚአብሄር እውነት ርቆ መባዘንና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በመጣው በዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከልብ አለማመን ነው (ዮሐንስ 16፡90) ሰዎች የፈጠራቸውን ጌታ ባለቤታቸው አድርገው አለማመናቸውና የመጀመሪያውን ፈጣሪያቸውን አለማወቀቸው ሐጢያት አይደለምን? በእርግጥም ሐጢያት ነው በሌላ አነጋገር ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኙ አድርጎ አለማመኑና ሐጢያቶቹንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እንደደመሰሰለት ከማመን መጉደሉ ሐጢያት ነው ሰው ከኢየሱስ ክርስቶስ ርቆ መቅበዝበዙ ጥፋት ውስጥ እንዲወድቅ የሚነዳው ሐጢያት ነው የሰውን ዘር ወደ ውሸንብር የሚመራው መንገድ ይህ ነው በእርሱ ሳያምኑ ከእግዚአብሄር የራቁ ሰዎች ጠፍተዋል ምክንያቱም በእውነት ቃል አያምኑምና።

በሰዎች ልቦች ውስጥ ያለው ባዶነትና ሐጢያት

ለእኛ ለሰዎች እውነተኛ እርካታን ሊሰጠን የሚችለው ሌላ ማንም ሳይሆን ኢየሱስ ብቻ ነው ነገር ግን ሰዎች አዳኛችን ኢየሱስ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ያደረገውን ስለማይቀበሉ ክርስቶስ ወደ ልባቸው ገብቶ ሊኖር አይችልም በልቦቻቸው ውስጥ ያለው ባዶነት ብቻ መሆኑ ለዚህ ነው።

ሰዎች ባዶ ልቦቻቸውን ለመሙላት በእውነት የተሞላውን የኢሱስን ቃል ወደ ልቦቻቸው ማስገባት አለባቸው ያንን ለማድረግ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ በነበረ ጊዜ ያደረገውን እያንዳንዱን ነገር በልቦቻችን ማመን አለብን ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመውሰድ እንደተጠመቀ፣ ደሙን አፍስሶ በመስቀል ላይ እንደሞተና ዳግመኛም ከሙታን እንደተነሳ በልቦቻችን መቀበል አለብን ኢየሱስ ያደረገላችሁን በልቦቻችሁ ተገንዝባችሁ ብትቀበሉ በልቦቻችሁ ውስጥ ያለው ባዶነት በእርግጥም ይወገዳል።

የሰው ልብ በጨለማም ተሞልቷል መጽሐፍ ቅዱስ «ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ» ሲል የሰው ሁሉ ሐጢያቶች በልቡ ውስጥ በጥልቀት በመከማቸታቸው እርሱ ራሱ ይህንን አያውቀውም ማለቱ ነው ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ሐጢያቶቻቸውን ለመደበቅ ይሞክራሉ ማለትም ነው አጋር ምዕመናኖቼ ሰው ሐጢያቶቹን ከደበቀና ሐጢያተኝነቱን ለመቀበል እምቢተኛ ከሆነ በጨለማ ውስጥ ታስሮ በመኖር ይቀጥላል እግዚአብሄርን የሚያስደስት ዳግም የተወለደ ሰው አይሆንም ሰው ምን ያህል ደካማና ክፉ እንደሆነ ካላወቀና ካልተቀበለ በመጨረሻ የምህረትን አምላክ ሊያውቀው አይችልም በቃሉ አማካይነትም ከደህንነት አምላክ ጋር መገናኘት ይሳነዋል።

ሰው የእግዚአብሄርን እውነት እስንልተቀበለ ድረስ እውነተኛ ማንነቱን ፈጽሞ ሊገነዘብ አይችልም ሰው እውነተኛ ማንነቱን ካላወቀ እግዚአብሄርን ይተወዋል ሰዎች ራሳቸውን መልካም ሰዎች አድርገው ለማቆምና በራሳቸው ጥረትም ራሳቸውን ለመጠበቅ በመሞከር ሐጢያቶቻቸውን ለመደበቅ የሚሞክሩት እግዚአብሄርን መቀበል ስለማይችሉ ነው ሰው የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል ካልተቀበለ የሚሆነው ይህ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ ይህ ሐጢያት ነው ከእግዚአብሄር የራቁና በቃሉ የማያምኑ ሰዎች ሁሉ ሐጢያተኞች ናቸው እግዚአብሄር ገና ከመጀመሪያው ልቦቻቸው ቅርጽ አልባና ባዶ እንደሆኑ ጨለማም በጥልቁ ላይ እንደሆነ በመንገር ለእነዚህ ሐጢያተኞች ሲነግራቸው ነበር።

እግዚአብሄር በእኛ ውስጥ የሚሰራው በቃሉ አማካይነት ብቻ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ እንደነበር ይናገራል እግዚአብሄር የሐጢያተኛውን መተላለፎች የሚያነጻው በምን አማካይነት ነው? እግዚአብሄር የሰዎችን ሁሉ ሐጢያቶች በሙሉ የሚያነጻው በቃሉ አማካይነት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ «ውሃ» የሚያመላክተው የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል ነው «ምድር» የምታመላክተው የሰውን ልብ ነው «ባህር» የሚያመላክተው አለምን ነው።

እዚህ ላይ ቃሉ «የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» ሲል የእግዚአብሄር መንፈስ የት እንደሚሰራ በመጠቆም መንፈስ ቅዱስ በተጻፈው ቃሉ ክልል ውስጥ እንደሚሰራ ያመላክታል ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል ሲይዙና

በዚህ ቃል ሲያምኑ እግዚአብሄር በቃሉ በልቦቻቸው ውስጥ ይሰራና በልቦቻቸው ውስጥ ያሉትን ሐጢያቶች በሙሉ ፈጽሞ በመደምሰስ ሁሉንም ያድናቸዋል እግዚአብሄር ዩኒቨርስን በቃሉ ፈጠረ የእያንዳንዱን ሐጢያተኛ ሐጢያቶች በሙሉ ያስወገደውም እንደዚሁ በቃሉ ነው።

ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ አምላክ የሆነው መንፈስ ቅዱስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ ማለት የተቀደሰው የእግዚአብሄር መንፈስ ማለትም መንፈስ ቅዱስ በሐጢያተኛ ልብ ውስጥ መግባት አይችልም ማለት ነው ይህ ምንባብ እግዚአብሄር በሰዎች ልቦች ውስጥ መኖርና አብሮዋቸው መሆን ቢፈልግም በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት እስካለ ድረስ ይህንን ማድረግ እንደማይችል ይነግረናል።

እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ ወደ እያንዳንዱ ሰው ልብ መግባት ይፈልጋል ነገር ግን እርሱ መግባት የሚችለው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ወደ ተቀበሉ ሰዎች ልቦች ውስጥ ብቻ ነው ሰው ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ማመንና በውሃና በመንፈስ የመጣውን የሐጢያት ስርየት በልቡ ውስጥ መቀበል ያለበት ለዚህ ነው ጌታ ወደ ውስጣችን ሊገባ የሚችለው ያን ጊዜ ነው።

ዩኒቨርስን የፈጠረው ማነው? ራሱ አምላክ የሆነው ኢየሱስ ነው ግልጽ በሆነ አነጋገር ኢየሱስ ራሱ እኛን የሰራንና ዩኒቨርስን የፈጠረ አምላክ ነው ኢየሱስ የሰውን ዘር ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ሊያድነን ወደዚህ ምድር የመጣ አዳኝ አምላክ ነው ኢየሱስ ተፈጥሮን ሁሉ የፈጠረ አምላክ ነው ታዲያ ይህንን ኢየሱስ ልንገናኘው የምንችለው እንዴት ነው? ኢየሱስን ልንገናኘው የምንችለው በእግዚአብሄር የእውነት ቃል አማካይነት ነው የሐጢያት ስርየትን በሚያስገኘው የወንጌል ቃል እውነት ስናምን በእርግጥም የሐጢያቶቻችንን ይቅርታ

መቀበልና እግዚአብሄርን መገናኘት እንችላለን ያን ጊዜ እግዚአብሄር ማን እንደሆነ፣ እግዚአብሄር የተናገረለት ሐጢያት ምን እንደሆነ፣ እግዚአብሄር የተናገረለት ደህንነት ማለትም የሐጢያት ስርየት ምን እንደሆነ፣ እግዚአብሄር የሰጠው የዘላለም ሕይወት ምን እንደሆነና እግዚአብሄር ምን አይነት በረከቶችን እንደሰጠን መረዳት እንችላለን እግዚአብሄርን በልቦቻችን ልናምነው የምንችለው በኢየሱስ በማመን ነው።

እግዚአብሄር በዚህ እውነተኛ የደህንነት ቃል በሚያምኑ ሰዎች ይሰራል እግዚአብሄር የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ሁሉ በመስጠት የሚያድናቸው በዚህ ቃል የሚያምኑትን አማኞች ነው እግዚአብሄር በአምላክ የደህንነት ቃል ለሚያምኑ ሰዎች የሐጢያት ስርየትን ሰጥቶዋል ነገር ግን ሰው የእውነትን ቃል ባይሰማም ሆነ ባያምንና በልቡ ውስጥ ሐጢያቶች ተቀምጠው ቢቀሩ እግዚአብሄር ወደ ልቡ ሊገባ አይችልም እግዚአብሄር በመጀመሪያ እርሱ ለእያንዳንዱ ሰው በነጻ የሚሰጠውን የሐጢያት ስርየት እንድንቀበል በመንገር በዙሪያችን የሚያንጎበበው ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስም «የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» የሚለው ለዚህ ነው።

የሰው ዘር ሐጢያት ምንድነው? በመጀመሪያ እውነተኛ የሐጢያት ስርየት የሚያመጣውን የእግዚአብሄርን የደህንነት ቃል አለመቀበልና እርሱን በልብ ለማመን እምቢተኛ መሆን ነው ሰው የእግዚአብሄርን የደህንነት እውነት የማያምን ከሆነ በእግዚአብሄር ላይ ትልቅ ሐጢያት ይሰራል ሰዎች ብዙውን ጊዜ ትልቅ ሐጢያት እንደሆነ የሚቆጥሩት ለየት ያለ የከፋ መተላለፍ ሲፈጽሙ ብቻ ነው ነገር ግን ሐጢያት ያ ብቻ አይደለም ራሱ ቃል በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አለማመንም ሐጢያት ነው ተጨባጩና እጅግ መሰረታዊው ሐጢያት

የእግዚአብሄርን ቃል አለመቀበልና አለማመን ነው።

ይህ ሆኖ እያለ ውሸቦንብር ውስጥ የወደቁ ሰዎች ይህ የምግባሮቻቸው ጉድለት ሐጢያት የሚሆነው የሆነ ስህተት ሲሰሩ ብቻ እንደሆነ በማመን ከእግዚአብሄር ውጭ በራሳቸው ያስባሉ በአንጻሩ እግዚአብሄር ስማያትንና ምድርን ሲፈጥር ለሰዎች ሐጢያት በእርሱ ኑባሬና በቃሉ አለማመን መሆኑን በመናገር የሐጢያት መጀመሪያ፣ መነሻና መሰረት ይህ እንደሆነ ግልጽ አድርጓል።

ሰዎች በእግዚአብሄርና በቃሉ ባለማመናቸው ምን አይነት ሐጢያተኞች ይሆናሉ? እግዚአብሄር ለአዳምና ለሔዋን እንዲህ አላቸው *«ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» (ዘፍጥረት 2:16-17)* አዳም በእግዚአብሄር ቢያምንም እርሱ የተናገረውን ቃል በሙሉ አላመነም ስለዚህ መልካምንና ክፉን የምታስታውቀውን ዛፍ በላ ሐጢያት የጀመረው ከዚህ ነው።

አዳምና ሔዋን በእግዚአብሄር ባለማመናቸው የዚህ ውጤት ምን ሆነ? ሰዎች በሰይጣን ፈተና ተታልለው እግዚአብሄር ከኋላቸው በመተው በፊቱም ሐጢያትን በመስራት ቃሉን ባለመቀበልና እንዲያውም ከዲያብሎስ ጋር በመወገን መጨረሻቸው ሐጢያተኞች መሆን ሆነ ሰዎች በእግዚአብሄር ቃል ባለማመን ራሳቸውን የተረገሙ ሐጢያተኞች አደረጉ ቃሉን በተሳሳተ መንገድ በማመን ከእግዚአብሄር የራቁ ሁሉ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች ሆነዋል የሰው ዘርም በእግዚአብሄር ሊኮነን የታጨ ርጉም ሆነ።

አንድ ሐጢያተኛ ከእግዚአብሄር ርግማን ሊድን ከፈለገ የእግዚአብሄር ጽድቅ በሆነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ማመን አለበት የሰው ዘር ወደ እግዚአብሄር መመለስ

የሚችለው በዚህ የእውነት ቃል ሲያምን ብቻ ነው ሰዎች የሆንን ሁላችን ወደ እውነተኛው የእግዚአብሄር ቃል መመለስ እርሱን መቀበልና በእርሱም ማመን አለብን አንድ ሐጢያተኛ ወደ እግዚአብሄር መመለስ ከፈለገ ከአለማመኑ በእግዚአብሄር የእውነት ቃል ከማመን እምቢተኝነቱ መመለስ አለበት።

ሁላችንም ከዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሄር የተናገረለት ሐጢያት ምን እንደሆነ እግዚአብሄር እንዴት ወደ ሐጢያተኞች እንደሚመጣና የደህንነት ስራውና በረከቶቹም እንዴት እንደተዘጋጁ መረዳት እንችላለን እኛ ሰዎች በሐጢያት ስንወድቅ ራሱ አምላክ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ የሐጢያተኞች አዳኝ ሆኖ ወደ እኛ በመምጣት የእያንዳንዱን ሐጢያተኛ ሐጢያቶች በሙሉ አነጻ እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው በቃሉ ነው ልክ እንደዚሁ የሐጢያቶቻችንን ስርየትና መንግስተ ሰማይን የሰጠን በቃሉ ነው።

እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ሲፈጥር የፈጠራቸው በቃሉ ነው።

እግዚአብሄር ሁሉን ነገር ከሰማይ በታችና በምድር ላይ በፈጠረ ጊዜ ያዘዘው በቃሉ ነው «ብርሃን ይሁን» «በውሆች መንከል ጠፈር ይሁን በውሃና በውሃ መካከልም ይከፈል» «ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍ ታብቅል» «ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ» «ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ ታስገኝ» አለ።

እግዚአብሄር ከአንደበቱ በወጣው ቃል ሁሉን ፈጠረ መላው

ዩኒቨርስና በውስጡ ያለው እያንዳንዱ ነገር ወደ ኑባሬ የመጣው በእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ ሁሉ የሰው ዘር የሐጢያት ስርየት ወደ እኛ የመጣውም በጌታ ቃል ነው ጌታችን የእግዚአብሄርን እውነተኛ ደህንነት ቃል ባለማመናችን በሐጢያት የወደቅነውን እኛን ለማዳን በእግዚአብሄር የጽድቅ ቃል እንደገና ሊፈልገን መጣ ጌታችን ወደ እኛ የመጣው በሕልሞቻችንም ሆነ በራዕዮቻችን አይደለም እርሱ ወደ እኛ የመጣው በጽድቅ ቃል ነው ጌታ በሆኑ ረቂቃዊ ልምምዶች አማንይነት አይገናኘንም::

እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ::» (ዘፍጥረት 1:1-3)*

ይህ ምንባብ እግዚአብሄር ይህንን መላውን ዩኒቨርስ በቃሉ እንደፈጠረ ሁሉ ሐጢያተኞች ወደ ሐጢያት በወደቁ ጊዜ በጽድቅ ቃል ወደ እነርሱ መጥቶዋል ማለት ነው ይህ ማለት ጌታ ሐጢያተኞችን ከበደሎቻቸው አድኖዋቸው እግዚአብሄር እንደተናገረው በትክክል የሐጢያታቸውን ስርየት አጠናቋል ማለትም ነው::

ኢየሱስ በሐጢያት የወደቁትን ሰዎች ሁሉ ለማዳን በጌታ የእውነት ቃል እነርሱን ፍለጋ መጣ አዳምና ሔዋን በሐጢያት በመውደቃቸው ሌላውም ሰው ሁሉ እንደዚሁ ሐጢያተኛ ሆነ ጌታችን እነዚህን ሰዎች ፍለጋ የመጣው እንዴት ነበር? እርሱ የመጣው በእውነትና በጸጋ ቃል ነበር እዚህ ላይ ወደ ኢሳይያስ **55:1-3** እንሂድ::

«እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ
ወደ ውሃ ኑ ገንዘብም የሌላችሁ
ኑና ግዙ ብሉም ኑ ያለ ገንዘብም

ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት
ግዙ ገንዘብን እንጀራ ላይደለ
የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ
ነገር ለምን ትመዝናላችሁ?
አድምጡኝ በረከትንም ብሉ
ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው
ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም
ቅረቡ ስሙ ሰውነታችሁም
በሕይወት ትኖራለች የታመነችይቱንም
የዳዊትን ምህረት የዘላለምን ቃል ኪዳን
ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ::»

የሰው ሁሉ አስተሳሰቦች በውሸጉብር ውስጥ ተጠምደውና ልብም በጥልቁ ላይ በነበረው ጨለማ ባዶ ሆኖ ሳለ ጌታችን በእውነተኛው የደህንነት ቃል እግዚአብሄርንና ቃሉን ትተውት ወደነበሩ ሐጢያተኞች መጣ እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ ስሙ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች የታመነችይቱንም የዳዊትን ምህረት የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ»* እግዚአብሄር ዳግመኛ ወደ እኛ የመጣው በጽድቅ ቃሉ ነው::

ወደ እግዚአብሄር ቃል መመለስ አለባችሁ

የእግዚአብሄር ቃል ሌላ ሳይሆን እናንተና እኔ የያዝነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የእግዚአብሄር ቃል ነው የእግዚአብሄርን ቃል ማወቅና በእምነት መቀበል አለብን ከሦስቱ የእግዚአብሄር ስብዕናዎች ማለትም ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል የሆነው ወልድ ነው አሁን

እኛ እያነበብነው ያለው ይህ ቃል ራሱ እግዚአብሄር ነው። (ዮሐንስ 1፡1)

ይህ እውነት ስለሆነ በጌታ የሚያምኑ ሰዎች የተጻፈውን የቅዱሳት መጽሐፍት ቃል የሚያምኑ ሰዎች ያንን የሚያደርጉት ይህ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ በማመን ነው በአንጻሩ በጌታ የማያምኑ ሐጢያተኞች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ አያምኑም ቃሉ ራሱ እግዚአብሄር እንደሆነም አያምኑም።

እግዚአብሄር መንፈስ ነው ነገር ግን እርሱ ሎጎስም ማለትም ራሱ ቃል ነው እውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የእግዚአብሄር ቃል ነው ቃሉም ራሱ እግዚአብሄር ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሐጢያተኞች ልቦች ውስጥ የመጣው በደህንነት ቃል ነው ምክንያቱም እርሱ የቃሉ አምላክ ነውና እግዚአብሄር በቃሉ ወደ ሐጢያተኞች በመምጣት እንዲህ አለ።

«እግዚአብሄርን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት
ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን
በደለኛም አሳቡን ይተው ወደ
እግዚአብሄርም ይመለስ እርሱም
ይምረዋል ይቅርታውም ብዙ ነውና
ወደ አምላካችን ይመለስ።» (ኢሳይያስ 55፡6-7)

እግዚአብሄር በተናገረን ቃል ባይሆን ኖሮ ጌታን እንዴት አዳኛችን አድርገን እናምነው ነበር? ጌታን እንዴት ልንገናኘው እንችል ነበር? ጌታ ስሞቻችንን ቢጠራና በራዕያችንም በሙሉ ክብሩ ተገልቶ «ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ እየወሰድሁ ነው» ቢለን ኖሮ ሁላችንም ራሳችንን ስተን በሞትን ነበር እግዚአብሄር እንደ እኛ አንል የለውም እርሱ የእውነት ቃል ሆኖ ወደ እኛ በመምጣት ተናገረን «እግዚአብሄርን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን

ይተው ወደ እግዚአብሄርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ» አለን፡፡

እግዚአብሄር በቃሉ አማካይነት ይቀርበናል ጌታ በዳኑት ልቦች ውስጥ ሲኖር ለማያምኑ ሰዎች ግን የእግዚአብሄር ቃል ሆኖ በጣም ይቀርባቸዋል ጌታ ቃል ሆኖ ሁሌም ለሐጢያተኞች ቅርብ ነው ሐጢያተኞች በሕይወት እያሉ እግዚአብሄርን ቢጠሩት በእርግጥ እርሱን ቢፈልጉት እግዚአብሄር በእርግጠኝነት በቃሉ አማካይነት ይገናኛቸዋል፡፡

ሐጢያተኞች እግዚአብሄርን ለማግኘት በመጀመሪያ መንገዳቸውን ክፉዎችም አሳባቸውን መተው አለባቸው እዚህ ላይ ሐጢያተኛ የሚለው ቃል የሚያመላክተው የእግዚአብሄርን የጽድቅ ቃል የማይቀበሉትን ሰዎች ነው ክፉዎች የእግዚአብሄርን ጽድቅ ከማያውቅ መንገዳቸው መመለስ አለባቸው በእግዚአብሄር ፊት አመጸኞች የሆኑ ሰዎች የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል የማይቀበሉና ሐጢያትን የሚሰሩ ሰዎች ናቸው እነርሱም ከሐጢያተኞች ጋር አብረው የማያምኑትን አሳቦቻቸውን መተውና ወደ እውነት አምላክ መመለስ አለባቸው ክፉዎችና አመጸኞች ሁሉም ሐጢያተኞች ናቸው እነዚህ ሐጢያተኞች ወደ እግዚአብሄር መመለስ ከፈለጉ የወደቁበት ሐጢያት ምንም ይሁን በእግዚአብሄር ጽድቅ በማመን ወደ ወንጌል መምጣት አለባቸው፡፡

ያንን ለማድረግም በመጀመሪያ የእግዚአብሄርን የጽድቅ ቃል ለማወቅ ምን ያህል እንደተሳናቸው መገንዘብ አለባቸው ሐጢያተኞች በሙሉ እግዚአብሄርን መገናኘትና በእርሱ ማመን የሚችሉት በውስጣቸው ያለውን ክፋት ሲያምኑ ውድቀታቸውን ሲገነዘቡ የእግዚአብሄርን ሕልውና ሲቀበሉና እግዚአብሄር ጌታቸውና አዳኛቸው መሆኑን ሲያምኑ ብቻ ነው እያንዳንዱ ሐጢያተኛ ወደ እግዚአብሄር መመለስ ይችላል ይህ የሚሆነው

ግን እግዚአብሄር የተናገረውን የእውነት ቃል ሲቀበልና ሲያምን ብቻ ነው።

ወደ እግዚአብሄር መመለስ የምንችለው በእርሱ በማመን የእግዚአብሄርን ቃል ስንቀበል ብቻ ነው ይህ ገብቶዋችኋልን? እግዚአብሄርን የተወው የሰው ዘር ወደ እርሱ የሚመለስበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው አንድ ሐጢያተኛ የሚታደሰውና ወደ እግዚአብሄር የሚመለሰው የእርሱን ሉአላዊነት ሲቀበልና እርሱ የተናገረውን ቃል ሲገነዘብ ብቻ ነው።

ወደ እግዚአብሄር ለመመለስ በመጀመሪያ አስተሳሰቦቻችሁን ጣሉ

ሰው «ጌታ ሆይ!» እያለ በመጮህ የጌታን ስም በመጥራት ወደ እግዚአብሄር ሊመለስ አይችልም አንዳንድ መጋቢዎች *«የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» (ሮሜ 10፡13)* የሚለውን ምንበብ ከሮሜ በመጥቀስ ይህንን ይላሉ ነገር ግን ሰው «አቤቱ አምናለሁ» በማለት ብቻ ወደ እግዚአብሄር መመለስ ፈጽሞ አይችልም ይህ የሰው አሳብ ነው እያንዳንዱ ሰው ወደ እግዚአብሄር መመለስና እርሱን መገናኘት የሚችለው የእግዚአብሄርን ቃል ሲገነዘብ ብቻ ነው ሐጢያተኞች ወደ እግዚአብሄር መመለስ የሚችሉት አሳባቸውን ሲተዉ ብቻ ነው።

እኛ የዳንን ጻድቃን ሰዎችና ያልዳኑትም ሐጢያተኞች እንደዚሁ በእግዚአብሄር ፊት ብዙ ስህተቶችን ሰርተናል ይህ ሆኖ ሳለ ግን እግዚአብሄር እነዚህን በደሎች በሙሉ በጽድቁ አማካይነት ወስዶዋቸዋል ከተሳሳቱት አስተሳሰቦቻችን፣ ከተሳሳቱት መረዳቶቻችንና ድካሞቻችን የተነሳ የምንሰራቸውን

ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ ወስዶዋል ሰዎች በድካሞቻቸውና በአለማወቃቸው ምክንያት የሚሰሩዋቸውን እነዚህን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል እኛ ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ምን ያህል መሃይሞች እንደሆንን ታውቃላችሁን? ምንም አስተውሎት ስለሌለን ብቻ በስህተት ያሰብነው፣ የተሳሳተ መረዳት የያዝነውና የተሳሳተ አስተውሎት ያስተናገድነው ስንት ጊዜ ነው? በዚህ አለም ላይ ሐጢያት በመስራት ያበቃነው ለዚህ ነው ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ኢየሱስ እነዚህን ሐጢያቶች በሙሉ አልወሰደምን? ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ተሸክሞ ሁሉንም እንዳስወገዳቸው እርግጥ ነው ኢየሱስ አዳኛችን ነው::

ከላይ በተጠቀሰው የኢሳይያስ ምንባብ ውስጥ እንዲህ ይላል::

«ክፉ ሰው መንገዱን
በደለኛም አሳቡን ይተው ወደ
እግዚአብሄርም ይመለስ እርሱም
ይምረዋል ይቅርታውም ብዙ ነውና
ወደ አምላካችን ይመለስ::»

እግዚአብሄር አሳቦቻችንን እንድንተውና ወደ የሆዋ እንድንመለስ ይነግረናል አጋር ምዕመናኖቼ አሳቦቻችን በእግዚአብሄር ፊት ምን ያህል ክፉ እንደሆኑ ታውቃላችሁን?

ጌታችን እነዚህንም የተሳሳቱ አስተሳሰቦች በሙሉ ማስወገዱ እርግጥ ነው ነገር ግን አሁንም ድረስ የእግዚአብሄርን ኑባሬ የሚክዱ በጣም ብዙ የተማሩ ፈላስፎች አሉ እነዚህ ሰዎች ልቦቻቸው በአሳቦቻቸው ደንድነዋል «እግዚአብሄር የታለ? ኢየሱስ እንዴት አምላክ ሊሆን ቻለ? እግዚአብሄር እንዲት የቃሉ አምላክ ሊሆን ይችላል? እርሱ መላውን ዩኒቨርስና የሰውን ዘር እንዴት ሊፈጥር ቻለ? ሁሉም ነገር ወደ ኑባሬ የመጣው በዝግመተ ለውጥ አማካይነት ነው» ይላሉ በዚህ

አለም ላይ የሚኖሩ በጣም ብዙ ሰዎች የሚያስቡት ልክ እንደዚህ ነው።

ነገር ግን እግዚአብሄር በደለኞች አሳቦቻቸውን እንዲተዉና ወደ የሆዋ እንዲመለሱ እየተናገረ ነው እግዚአብሄር ሐጢያተኞች ከሐጢያቶቻቸው እንዲነጹ ከፈለጉ በመጀመሪያ ክፉ አሳቦቻቸውን መተውና በእግዚአብሄር ጽድቅ ማመን እንዳለባቸው እየተናገረ ነው አስተሳሰቦቻችን ምን ያህል ክፉ እንደሆኑ መገንዘብ አለብን በእግዚአብሄርም ፊት በእግዚአብሄር ቃል የአለማመን ዕብሪት ትልቅ ሐጢያት እንደሆነ መገንዘብ አለብን።

ያም ቢሆን ጌታችን ከድካሞች የተነሳ ከተሰሩት ሐጢያቶች ጀምሮ ክፉ አሳቦቻችንንና ድርጊቶቻችንን ጨምሮ በጥምቀቱ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል በእምነት ወደ የሆዋ አምላክ መመለስ የምንችለው ለዚህ ነው እግዚአብሄር «በደለኛ ም አሳቡን ይተው ወደ እኔም ይመለስ» ይላል አስተሳሰቦቻችን በእግዚአብሄር ፊት እንደን አለባቸው ወይስ እንከን የለሽ ናቸው? አስተሳሰቦቻችሁ ትክክል ናቸው ወይስ ብልሹ? ከእግዚአብሄር ቃል ውጭ እግዚአብሄር በተናገረው ቃል ላይ ካለን እምነት ውጭ የያዝናቸው አስተሳሰቦችና ከዚህ እምነት የሚፈልቁ አስተሳሰቦች በሙሉ ክፉ መሆናቸውን መገንዘብ አለብን ሰው ሰራሽ አስተሳሰቦች በመሰረቱ የተሳሳቱ ናቸው ከእኛ አስተሳሰቦችና ከእግዚአብሄር ቃል ትክክለኛው የቱ ነው? ትክክለኛው የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ የታወቀ ነው።

የጀርመን የስነ ኑባሬ ፈላስፋ ፍሬድሪክ ኒቼ (1844-1900) እግዚአብሄር ሞቷል ብሎ ደመደመ «ክፉዎች በዚህ ምድር ላይ ብዙ ክፉ ነገሮችን እያደረጉ እንዲህ ብርቱ የሆኑት እግዚአብሄር ስለሞተ ነው! እግዚአብሄር የሞተው ለዚህ ነው!» ብሎ አሰበ ኒቼ በጉዞ ላይ ሳለ መርከቡ ተሰበረና በሕይወት አድን ጀልባ

ላይ ተሳፈረ ማዕበሉ ግን በጣም ከፍተኛ ስለነበር ሊሰምጥ ሆነ «እግዚአብሄር ሆይ እባክህ አድነኝ!» ብሎ በመለመን ወደ እግዚአብሄር እንደጸለየ ተነግሮዋል እግዚአብሄር እንደሞተ የተናገረው ኒቼ ያድነው ዘንድ እግዚአብሄርን ለመነ።

እግዚአብሄርም አዳነው እንደገናም እግሩ መሬትን እንዲረግጥ አደረገው ከጥቂት ቀናቶች በኋላ ኒቼ ንግግር ሲያደርግ እንደገና «እግዚአብሄር የለም እግዚአብሄር ሞቷል» አለ በንግግሩ ላይ ከኒቼ ጋር አብረው መርከብ የተሰበረባቸው መንገደኞች ነበሩ እነርሱም «ያ ኒቼ የተባለ ሰው እንግዳ የሆነ ሰው ነው በባህር ላይ ሳለ እግዚአብሄር ሕያው ነው አለ አሁን መሬት ላይ ሲሆን እግዚአብሄር ሞቷል ይላል ስለዚህ አስተሳሰቦቹ ውሸት መሆን አለባቸው» ሲሉ ተደምጠዋል።

ሰዎች ሁሉ የሚያስቡት እንደዚህ ነው የሆነ አስደንጋጭ አጋጣሚ ሲደርስባቸው ወደ እግዚአብሄር ይመለከታሉ ነገር ግን ከተመቻቸው በኋላ እግዚአብሄር ሞቷል ይላሉ ይህንን የሚያደርጉት ለምንድነው? ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሄር መማረክ ስለማይፈልጉ ነው በእግዚአብሄር ያለ ማመን ሐጢያት ሌላ ሳይሆን ይህ ነው እነዚህ ሰዎችም እግዚአብሄርን የተዉ እጅግ ክፉ ሐጢያተኞች ናቸው።

የእግዚአብሄር የእውነት ቃል ከሰው ዘር አሳቦች የተለየ ነው

ነፍሳችሁ ከሐጢያት እንድትድን የምትፈልጉ ከሆናችሁ ሰብአዊ አስተሳሰቦቻችሁን ጣሉት በእግዚአብሄር ቃል ስለመጣው የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና መስቀልም አስቡ የተሳሳቱት አስተሳሰቦቻችን የኢየሱስን ቃል እንዳንቀበል

ያደርጉናል ጌታ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ።» (ማቴዎስ 11:28)

ጌታ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ ወሰደ ስለዚህ ሐጢያተኞች እግዚአብሄርን መገናኘት ከፈለጉ የራሳቸውን አሳቦች መጣልና ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ አለባቸው ያን ጊዜ እግዚአብሄር «እንደሚምራቸው» መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ኢየሱስ ለሐጢያተኞች ካለው ርህራሄ የተነሳ ከ2,000 አመታት በፊት በዮሐንስ በተሰጠው ጥምቀት አማካይነት መተላለፎቻቸውን ሁሉ በስጋው ወስዶዋል።

እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል

«አሳቤ እንደ አሳባችሁ
መንገዳችሁም እንደ መንገዴ
አይደለምና ይላል እግዚአብሄር
ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል
እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ
አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው።» (ኢሳይያስ 55:8-9)

የእግዚአብሄር የጽድቅ አሳቦችና የእኛ የሰዎች አሳቦች በዋናነት የተለያዩ ናቸው የሚገኙትም ፈጽሞ በተለያ ደረጃ ላይ ነው እኛ ሰዎች በሰብአዊ አስተሳሰቦቻችን «እግዚአብሄር በዚህ አለም ላይ እንዲህ እንድሰቃይ በመጀመሪያ ደረጃ ለምን ፈጠረኝ? ለምን እንደዚህ እንደፈጠረኝ ለምን እንዲህ እንድወለድ እንዳደረገኝ አላውቅም» ብለን እናጉረመርማለን እግዚአብሄርን የሚወቅሱ ሰዎች ወላጆቻቸውንም ይወቅሳሉ «ወላጆቼ ለምን አንዳች ውርስ እንዳልተዉልኝ፣ እንዲህ ደሃ ሆነው ሳለ በመጀመሪያ ለምን እንደወለዱኝና በብዙ እየተሰቃየሁና በብዙዎች እየተናቅሁ እንዲህ እንድኖር ለምን እንደሚፈቅዱ ሊገባኝ አይችልም?» ብለው ያስባሉ ይህ በአሳባቸው ውስጥ ተቀብሮ ያለ ነገር ብቻ አይደለም ነገር ግን ይህንኑም በቀጥታ

ለወላጆቻቸው ይነግሩዋቸዋል።

ነገር ግን ጌታችን እግዚአብሄረን እንዲፈልጉና እንዲሹ እግዚአብሄርን የተዉትን ሐጢያተኞች በሙሉ ከሐጢያት ለማዳንና ክብሩን ለማልበስ መከራን እንደፈቀደ ይናገራል በዚህ ምድር ላይ መከራ ባይኖርና ሁሉም ነገር ሰላም ቢሆን ሰው እግዚአብሄርን አይፈልግም ነበር ሰዎች ጉድለቶች ወይም ድካሞች ባይኖርባቸው ኖሮ በኢየሱስ በማመን የእግዚአብሄር ልጆች አይሆኑም ነበር እግዚአብሄር ሰው በዚህ ምድር ላይ መከራ እንዲደርስበት የፈቀደው ለዚህ ነው ያ ግን ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው ይህ የሆነበት ምክንያት የሰው አስተሳሰቦችና የእግዚአብሄር አስተሳሰቦች ፈጽሞ የተለያዩ በመሆናቸው ነው።

ሰዎች «እግዚአብሄር ምናልባት ስለተሰላቸ ራሱን ለማዝናናት ሲል የእርሱ አሻንጉሊቶች አድርጎ ሳይፈጥረን አይቀርም» ይላሉ ብዙዎች እንደዚህ ለማሰብ ያዘነብላሉ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሄርን የሚረግሙትና ጣቶቻቸውን በእርሱ ላይ የሚቀስሩት ለዚህ ነው ነገር ግን የእግዚአብሄር አሳቦች ከእኛ አሳቦች የተለዩ ናቸው።

እግዚአብሄር እኛን ሰዎችን የፈጠረን በምድር ላይ በገነትና በመንግስተ ሰማይ በደስታ እንኖር ዘንድ ሕዝቡና ልጆቹ ሊያደርገን ነው እግዚአብሄር ሰውን የፈጠረው ልክ እንደ ራሱ እንደ እግዚአብሄር ዘላለማዊና ፈጽሞ ማለቂያ የሌለው ሕይወትን እንድናጣጥም ነው እግዚአብሄር እኛን የፈጠረን በዚህ ዕቅድ ነው እነዚህን አላማዎች በሙሉ ለመፈጸምም ኢየሱስ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ሞተ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ በዚህም ሁሉንም አከናወነ ይህ የእግዚአብሄር ችሮታ ነው።

እግዚአብሄርን ሰውን የፈጠረው ለእኛ ለሰዎች እውነተኛ ሐሴትንና በረከቶችን ለመስጠት ነው ነገር ግን ሰው ሰራሽ

በሆኑት አስተሳሰቦቻችን የምናስበው እንዲህ አይደለም በምትኩ አብዛኛውን ጊዜ «እግዚአብሄር ሰውን ከፈጠረ ክፉውን ወይም ዲያብሎስን መፍጠር አይገባውም ነበር» የሚሉ የስድብ ቃሎችን በመናገር እግዚአብሄርን እንወቅሳለን፡፡

እግዚአብሄር ዲያብሎስን ፈጥሮዋል? አልፈጠረም ሰይጣን ዲያብሎስ በመጀመሪያ መልአክ ነበር ይህ መልአክ ራሱን ከእግዚአብሄር በላይ ከፍ ለማድረግ በመሞከሩ ወደቀ መልአኩ ሰይጣን የሆነው ለዚህ ነው እግዚአብሄር የእስራኤል ሕዝብ እንዳይቀበሉት የፈቀደው በእርሱ ጽድቅ በማመን ከሐጢያት እንድንድን ለማስቻል የመሆኑን እውነታም መገንዘብ ይገባናል፡፡

የእግዚአብሄርን ፈቃድ ይበልጥ በቀላሉ ለማብራራት እዚህ ላይ በአምስት አመት ሕጻን ልጅና በወላጆቹ መካከል ያለውን ተዛምዶ ላቅርብ ጎልማሶች የሆነ ስራ ሊሰሩ ሲፈልጉ በትክክል ከመጀመራቸው በፊት አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶችን ሁሉ በጥንቃቄ ያደርጋሉ ልጅ ግን ምንም ያህል ለማብራራት ቢሞክርም ይህንን መረዳት አይችልም፡፡

እዚህ ላይ ከዱቄት የሚሰራ ሾርባ እየሰራን ነው እንበል ከዱቄት የሚሰራ ሾርባ ስንሰራ በመጀመሪያ በጎድጓዳ ሳህን ውስጥ ዱቄት እንጨምራለን በምሳሌያችን ላይ የጠቀስነው የአምስት አመት ልጅ ይህንን አይቶ «ዱቄት የምትጨምሩት ለምንድነው?» በማለት ይጠይቃል ከዚያም በሳህኑ ውስጥ ውሃ እንጨምራለን ልጁም እንደገና «ዚያ ውስጥ ውሃ የምትጨምሩት ለምንድነው?» በማለት ይጠይቃል ፈጽሞ ስለማይገባው ለምን ውሃ እንደሚጨመር ማስተዋል አይችልም ከዚያም ሊጡን ማቡካት እንጀምራለን ልጁ «ለምንድነው የምታቦኩት?» ብሎ ይጠይቃል ከዚያም ሊጡን በመዳመጫ እንዳምጠዋለን ያን ጊዜ ልጁ እንደገና «ለምንድነው የምትዳምጡት?» በማለት ይጠይቃል፡፡

ለልጅ እያንዳንዱ ነገር አጓጊና ጥያቄን የሚፈጥር ነው የተዳመጠውን ሊጥ ስንቀራርጥ ልጁ እንደገና «የምትቆርጡት ለምንድነው?» በማለት ይጠይቃል ውሃውን ስናፈላ «ውሃውን የምታፈሉት ለምንድነው?» ብሎ ይጠይቃል ከዱቄት የተሰራውን ሾርባ ወደሚፈላው ውሃ ውስጥ በምንጨምርበት ጊዜ እንደገና «ከዱቄት የሚሰራውን ሾርባ እዚያ ውስጥ የምትጨምሩት ለምንድነው? ለምንስ ታፈሉታላችሁ?» በማለት ይጠይቃል።

ልጁ ከጠየቃቸው ጥያቄዎች አንዳቸውም እስከ መጨረሻው ድረስ ሊመለሱ አይችሉም ነገር ግን ከዱቄት የሚሰራውን ሾርባ እንዲሞክረውና እንዲቀምሰው ብንፈቅድለት ያን ጊዜ «አሃ ለካ ከዱቄት የሚሰራ ሾርባ ማለት ይህ ነው» በማለት ግንዛቤን ያገኛል በመሃሉ ከዱቄት የሚሰራውን ሾርባ ለመስራት የተወሰዱት ደረጃዎች አይታወሱትም እርሱ የሚመለከተው ውጤቱን ብቻ ሲሆን እርሱም የቀመሰውን ከዱቄት የሚሰራ ሾርባ ነው ሊያስተውል የሚችለው ነገር ቢኖር «ኦ ለካ ከዱቄት የሚሰራ ሾርባ ማለት ይህ ነው ዋው! በጣም ጣፋጭ ነው!» የሚለውን ብቻ ነው።

ስለዚህ ወላጆቹ ከዱቄት የሚሰራውን ሾርባ ለመስራት የተጠቀሙባቸውን ደረጃዎች በሙሉ ማስተዋል አይችልም ልክ እንደዚሁ እግዚአብሄር እኛን ስለፈጠረበት አላማ ምንም ያህል ቢነገረንና እግዚአብሄር በደስታ እንኖር ዘንድ እኛን ልጆቹ ያደረገበት ይህ ግብና ሐሴት ቢብራራልንም ልክ እንደዚህ ልጅ ስለሆንን ሁሉንም ነገር ለመረዳት በጣም ያዳግተናል።

የእግዚአብሄርን ቃል ዘላለማዊነት መቀበል አለብን

ይህንን ማድረግ የእግዚአብሄርን በጎነት መቀበል ነው

እግዚአብሄር ሰውን የፈጠረው ሊባርከው ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ እንድንወለድ ያደረገን ሊባርከን ነው እግዚአብሄር የወይን ቦታውን አዘጋጅቶ እጅግ የተመረጠ የወይን ግንድ እንደተከለበትና መልካም የወይን ፍሬ ያፈራ ዘንድ እንደሚጠብቅ ተናግሮዋል (ኢሳይያስ 5:2) እግዚአብሄር እጅግ ምርጥ የወይን ፍሬዎችን ለማፍራት የሆነ ዕቅድ ካለውና እነርሱንም ካፈራ እኛም ደግሞ ደረጃዎቹን ሁሉ መቀበል አለብን::

ይህ ሆኖ ሳለ ሰዎች አሁንም ድረስ በእግዚአብሄር አያምኑም ወደ ሲያል የሚጣሉት በዚህ አለማመናቸው ነው ሰው እግዚአብሄርን እንደ እግዚአብሄርነቱ ካልተቀበለው የዚህ ሐጢያት ደመወዝ ለዘላለም ይሰቃይ ዘንድ ፈጽሞ ማለቂያ ወደሌለው የእሳት ባህር ውስጥ መጣል ብቻ ነው የማያምኑ ሰዎች ሲያል የመጣላቸው የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው::

አንዳንድ ሰዎች «እግዚአብሄር ሲያልን መፍጠር አልነበረበትም ለምን ፈጠረው?» ብለው ይጠይቁ ይሆናል አጋር ምዕመናኖቼ ፍጡር ፈጣሪውን አለማወቁ ተገቢ አይደለም መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ነጥብ በሸክላ ሰሪ ምሳሌ ያብራራዋል እኛ አንድ ዕቃ ብንሰራ፣ በሆነ ምክንያት በዕቃው ደስ ባንሰኝ፣ ብንሰብረውና ብንጥለው እዚህ ላይ የሰራነው ስህተት አለ? የለም የዕቃው ሰሪ ስለሆንን ምንም ስህተት አልሰራንም ይህንን ስናስተውል እኛ በፈጣሪያችን በእግዚአብሄር ፊት ተራ ፍጥረታት እንደመሆናችን ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር በእርሱ ማመንና እርሱ የሰጠንን መቀበል ብቻ ነው እግዚአብሄርን ልንወቅስበት የምንችልበት ምንም ነገር የለንም::

እኛ ፈጣሪ ነን? አይደለንም እኛ ፍጥረታቶች ነን በፍጥታት ላይ ምንም ነገር ቢደረግ ያ የፈጣሪው መብት ነው እግዚአብሄር በጥሩ ዕቅድ ለመልንም አላማ ፈጥሮን ሳለ ለዚህ

አለመገዛታችን በራሱ የተሳሳተና ክፉ ነገር ነው ይህ ከዲያብሎስ የፈለቀ ክፋት ነው እግዚአብሄርንም መገዳደር ነው እግዚአብሄር የሚመላለሰው በእውነት ቃል አማካይነት ነው በዚህ አምላክ አለማመናችንና በተናገረው ቃሉ አለማመናችን ሐጢያት ነው የእግዚአብሄር መንፈስ በውሃ ላይ እንደሰፈፈም መገንዘብ አለብን እግዚአብሄር በቃሉ አማካይነት ይሰራል ይህንን ቃል ስንቀበል በእርሱ ስናምንና እርሱን ስንከተል በእርግጠኝነት እግዚአብሄርን ልናገኘው እንችላለን፡፡

የእግዚአብሄር ቃል የሚሰራው በሰው ልብ ውስጥ ነው

በእግዚአብሄር ቃል ከማመን ይልቅ ረቂቀ ልምምዶችን ወይም ተፈጥሮአዊ መገለጦችን የምናምንና የምንሻ ከሆንን እግዚአብሄርን ልናገኘው አንችልም ይህ ገብቶዋችኋልን? እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፈፎ ነበር»* የእግዚአብሄር መንፈስ በውሃ ላይ ሲሰፍፍ የነበረው ስለተሰላች እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም እግዚአብሄር በምድር ላይ ማንጎበብ አይቻለውምን? እግዚአብሄር በምድር ላይ መመላለስ ያልቻለው ለምንድነው? ነገሩ ከዚህ የራቀ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምደር መጥቶ በእርስዋ ተመላልሶዋል ይህ ምንባብ መንፈስ ቅዱስ በሐጢያተኛ ልቦች ውስጥ መኖር አይችልም ማለት ነው፡፡

እግዚአብሄር እዚህ ላይ እያስተላለፈልን ያለው ልዩ መልዕክት ሐጢያተኞች እግዚአብሄርን ለማግኘት ወደ ቃሉ መመለስ እንዳለባቸው ነው ስለዚህ እግዚአብሄርን ያገኙትና ዳግም የተወለዱት ወደ ቃሉ የተመለሱ ሰዎች ብቻ ናቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ያስቀመጠው

ለዚህ ነው «እናንተ ከሐጢያት መዳን ከፈለጋችሁ በመጀመሪያ የሐጢያት ክምሮች መሆናችሁን መገንዘብ አለባችሁ ሁለተኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ዳግም መወለድ አለባችሁ» በሌላ አነጋገር ሰው ዳግም የሚወለደው በእግዚአብሄር ቃልና በእግዚአብሄር ማህተም በሚያትመው በመንፈስ ቅዱስ ነው::

በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት ምን እንደሆነና እግዚአብሄርም ማን እንደሆነ ማወቅ አለብን እግዚአብሄርን የተዉ ሰዎች ልቦች ግራ የተጋቡና ባዶ እንደሆኑ ጨለማም በጥልቁ ላይ እንዳለ መገንዘብ አለብን ሐጢያት ማለት ሌላ ሳይሆን በእግዚአብሄር ቃል አለማመን ነው እኛ ወደ እግዚአብሄር መመለስ ከፈለግን ወደ ቃሉ መመለስ አለብን እግዚአብሄርን ልናገኘው የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው ቃሉ ራሱ አምላክ ነው እግዚአብሄር የሚሰራውም በቃሉ አማካይነት ነው እኛም ይህንን በመገንዘብ ሁላችንም ወደ ቃሉ መመለስ አለብን::

እኛ ጻድቃኖችም እንደዚሁ አስተሳሰቦቻችንን መጣል አለብን እኛ ጻድቃኖች መባረክ የምንፈልግ ከሆነ የራሳችንን አስተሳሰቦች መጣል አለብን በእርሱ ማመን የምንችለው የእግዚአብሄርን ቃል ስናውቅ ነው ቃሉን ስንቀበል በእግዚአብሄር ማመን ወደ እርሱ መመለስና የእርሱን በረከቶች በሙሉ መቀበል እንችላለን በተለይም በቅርቡ የሐጢያት ስርየትን የተቀበሉ ሰዎችና አሁንም ድረስ ተጠራጣሪና ግራ የተጋቡ ሰዎች ወደ እግዚአብሄር ቃል መመለስ ይገባቸዋል ቃሉንም ማድመጥና ቃሉ በትክክል የሚለውን ማሰላሰል አለባቸው::

ይኸው ምክር ሐጢያተኞችንም ደግሞ ይመለከታል ሐጢያተኞች ወደዚህ ቃል ባይመለሱና የእግዚአብሄርን ቃልና

መንገዱን ባያውቁ እግዚአብሄርን እንዴት ሊያገኙት ይችላሉ እንዴትስ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ከኢየሱስ ሊቀበሉ ይችላሉ? እነዚህም ሐጢያተኞች ቢሆኑ ኢየሱስን ማግኘት እግዚአብሄርን ማግኘት ፈጣሪያቸውን ማግኘትና ከሐጢያቶቻቸው መዳን የሚችሉት ወደ ቃሉ ሲመለሱ ብቻ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ቀኖና ማለትም «የደህንነት መለኪያ ዘንግ እግዚአብሄርን እንድንገናኝ የሚያስችለን ባሮሜትርና የፍርድ ሁሉ መለኪያ ነው» የምንለው ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በሰው የተጻፈ ነገር አይደለም መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው እግዚአብሄር ራሱ ነው በዚህች ቅጽበትም እንኳን በርካታ ነፍሳቶችን በመለወጥ ቀጥሎዋል መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ በእርግጥም እግዚአብሄር እንዳለና እንደምናገኘው መረዳት እንችላለን በቃሉ ስናምንም ይህ ቃል ወደ ልቦቻችን ይገባና በሕይወታችን ውስጥ ይሰራል።

ቃሉ በሕይወታችን ውስጥ ለመስራት ወደ አእምሮዋችን ይገባል የተሳሳቱትን አስተሳሰቦቻችንንም ይሰባብራል ቃሉ የሐጢያቶቻችንን ስርየት እንድንቀበልና የእግዚአብሄርንም ፈቃድ እንድንከተል ያስችለናል ቃሉ ሕያው ስለሆነ በአማኞች ልብ ውስጥ በሐይል ይሰራል።

«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» እግዚአብሄር በሐጢያት የወደቅነውን እኛን ሰዎች የሚገናኘን እንዴት ነው? ከዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ እግዚአብሄር እንዴት ወደ እኛ እንደሚመጣና በሕይወታችን ውስጥ እንደሚሰራ ለዚህ ጥያቄ መልሱን አይተናል እግዚአብሄር እኛን ፍለጋ የመጣውና በዚህ አለም ላይ የሚሰራው በቃሉ አማካይነት ነው አሁን ይህንን ተገንዛባችኋልን?

እኔ ምስጋናዬን ሁሉ ለእግዚአብሄር እሰጣለሁ እኛ በእርግጥም ውሸንብርና ባዶነት ውስጥ ወድቀናል ጌታችን ግን

እኛን ፍለጋ መጥቶ በቃሉ አማካይነት ተገናኘን ገና በእምነታቸው ያልበሰሉና በቅርቡም ቃሉን ሰምተው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎች ቃሉን በተቻለ መጠን አዘውትረው ይሰሙ ዘንድ የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

በአምልኮና በጉባኤ ሰአታቶች ፈጽማችሁ እንዳትቀሩ ነገር ግን በሁሉም ላይ እንድትገኙ እመክራችኋለሁ ምክንያቱም *«እምነት ከመስማት መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነውና» (ሮሜ 10:17)* እግዚአብሄርን ማወቅ የምንችለውና ጥያቄዎቻችንም በሙሉ የሚመለሱት እውነተኛውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል ስንሰማ ነው።

የእግዚአብሄር ቃል የደህንነት ቃል እንጂ የሳይንስ መጽሐፍ አይደለም። ✉

በወንጌል እውነት ብርሃን ሆናችኋልን?

« ዘፍጥረት 1:2-3 »

«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ይሰፍፍ ነበረ እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ::»

እግዚአብሄር ዩኒቨርስንና በውስጡ ያሉትን ፍጥረታት በሙሉ በመፍጠር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ታላቁንና ክብራማ ዕቅዱን ገለጠ የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ 1 እግዚአብሄር ለሰው ዘር ያዘጋጀውን ክብራማ ዕቅድ ያሳየናል በሌላ አነጋገር የሰማያትና የምድር ፍጥረት እንደዚሁም የፍጥረታት ሁሉ መፈጠር፣ ሰው በእግዚአብሄር አምሳል መፈጠሩ፣ ሰው በሰይጣን ተታሎ መውደቁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ደህንነት፣ እኛም በእርሱ ችሮታ የእግዚአብሄር ልጆች መሆናችንና የእግዚአብሄር ዘላለማዊ ጸጋ በረከቶች እነዚህ ነገሮች ሁሉ በዚህ በዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ተገልጠዋል::

«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ተብሎ የተጻፈውና ይህንንም ተከትሎ *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» (ዘፍጥረት 1:2)* ተብሎ የተመዘገበው ለዚህ ነው እዚህ ላይ «ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ»

ሲል ይህ የሚያመላክተው በወደቀው መንፈሳዊ ፍጡር በሰይጣን ተታልሎ ውሸቱንብር ውስጥ የወደቀውንና በእግዚአብሄር የተፈጠረውን የሰውን የፍጥረትን ሁሉ ሁኔታ ነው በሌላ አነጋገር ይህ የሚያብራራው ሰው በሐጢያት መውደቁን ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ዩኒቨርስንና በውስጡ ያሉትን ፍጠራቶች በሙሉ የፈጠረውን የእግዚአብሄርን ፈቃድ በትክክል መረዳት አለብን እግዚአብሄር ፈቃድ የማናውቅ ከሆነ ወይም በተሳሳተ መንገድ የምንረዳው ከሆነ ትልቅ አደጋ ላይ ነን ከሰማያት በታች ያለ እያንዳንዱ ነገር የሚኖርበት አላማ አለው እግዚአብሄር ሲፈጥረን በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ አድርጎ ሊቀበለን ወስኖዋል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ከአለም ፍጥረት በፊት እንኳን እኛን የእርሱ ልጆች ሊያደርገንና በዚህም መለኮታዊ ፍጥረታቶች አድርጎ ከፍ ሊያደርገን በአእምሮው ውስጥ ዕቅድ ነበረው።

እግዚአብሄር በዕቅዱ መሰረት ፈጥሮን በዚህ ምድር ላይ ስንኖር መከራ እንዲገጥመን የፈቀደው እንዲህ ባሉ ችግሮች ውስጥም እርሱን እንድንሻው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነትም ሐጢያቶቻችንን የደመሰሰውን የወንጌል እውነት እንድናገኝ የፈቀደልን ለዚህ ነው እንዲህ በማድረግ እግዚአብሄር የእርሱ ልጆች አድርጎ ተቀበለን ውብ መንግስቱንም ሰጠን ስለዚህ እግዚአብሄር በእኛ ፈቃድ ላይ የተመረኮዘ ምንም ነገር እንደሌለ ነገር ግን ሁሉም ነገር የሆነው በእርሱ ፈቃድ ብቻ እንደሆነ አሳየን ስለዚህ በዚህ አለም ላይ ስንኖር እነዚህን ነገሮች ስናጣጥምና ስናሰላስል ልናደርገው የምንሻው ነገር በእኛ ፈቃድ የሚከወን ሳይሆን እግዚአብሄር አስቀድሞ በወሰነው መሰረት የሚከወን መሆኑን እኛው ራሳችን እንደርስበታለን እኛ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር ቃሉን በማመንና በመቀበል ወደ እግዚአብሄር ግዛት መግባትና ከዚያም እርሱን በእምነት

መከተል ነው ኢየሱስ «እኔ መንገድ ነኝ» (ዮሐንስ 14:6) ያለው ለዚህ ነው።

የእግዚአብሄርን ዕቅድ በሙላት መረዳት የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ነው እግዚአብሄር ለሰው ዘር ዕቅድ አለው ይህንን ዕቅዱንም ባቀደው መሰረት በቃሉ ውስጥ በመግለጥ አሳይቶናል ስለዚህ የእግዚአብሄርን ፈቃድ መረዳት የምንችለው በእግዚአብሄር ቃል ነው እግዚአብሄርን ማግኘት የምንችለውም በዚህ ቃል በማመንና ቃሉንም በመከተል ነው ስለዚህ በእግዚአብሄር ስናምን እግዚአብሄርን ማወቅና ማመን የሚገባን ተስፋ በሰጠው ቃሉ መሰረት ነው።

ለእግዚአብሄር የተስፋ ቃሎች ምንም ትኩረት ሳትሰቱ ስለራሳችሁ ብቻ የምታስቡ፣ በራሳችሁ ፈቃድ የምትወስኑና እግዚአብሄርንም በራሳችሁ ጥረት ለማግኘት የምትሞክሩ ከሆነ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ውሸቦንብር ውስጥ ትወድቃላችሁ ሰው እግዚአብሄርን ለማግኘት ተስፋ በሰጠው ቃል ማመንና እርሱን መከተል አለበት እግዚአብሄርን መገናኘት የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው እግዚአብሄር መጽሐፍ ቅዱስን የሰጠን ለዚህ ነው።

የእግዚአብሄር ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ እግዚአብሄርን ማግኘት አይቻለንም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል ነው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር የፈጸመውና እየፈጸመው የሚቀጥለው የኪዳን ቃል ነው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር በቃሉ ያቀደ በቃሉ ይህንን ዕቅድ ለእኛ የፈጸመ ወደ እኛ የመጣና በቃሉ አማካይነት የተገናኘን የቃሉ አምላክ እንደሆነ ጽፎዋል።

ቃሉ እግዚአብሄር ነው (ዮሐንስ 1:1) እግዚአብሄር ቃል ነው ራሱን በሰዎች ፊት ሲገልጥ ይህንን የሚያደርገው በተስፋው ቃል መሰረት ነው ሁላችንም እግዚአብሄር ቀድሞውኑም በቃሉ አማንይነት ራሱን እንደገለጠና እርሱም

በቃሉ አማካይነት የተገናነን የተስፋ አምላክ እንደሆነ በግልጽ መረዳት ይገባናል።

መጽሐፍ ቅዱስን ልብ ወለድን ወይም የታሪክ መጽሐፍን እንደምናነብ ልናነብበው አይገባንም ይልቁንም ይህ ቃል በራሱ እግዚአብሄር የተናገረው የተስፋ ቃል መሆኑን መረዳት አለብን እግዚአብሄር ራሱን ለእኛ የገለጠው በቃሉ ነው ስለዚህ እናንተና እኔ መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ ሁሉ በመጀመሪያ ይህ እግዚአብሄር ለእኛ ተስፋ የሰጠው ቃል መሆኑን መረዳት ይገባናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው የተሰጠ የደህንነት ብርሃን ነው

እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበረ እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ...እግዚአብሄርም ብርሃኑን ከጨለማው ለየ ብርሃኑንም ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው።»* *(ዘፍጥረት 1:2-5)*

እግዚአብሄር በዚህ ምንባብ ውስጥ ብርሃኑን ቀን ጨለማውንም ሌሊት ብሎ በመጥራት እግዚአብሄር ሐጢያትን በእርሱ ከተያዙ ነፍሳቶች ለማስወገድ ያለውን የማያወላውል ፈቃድ ያጸናል ቃሉ ይህንን ሐጢያት ይህንን ሁሉ ውሸጉበር ባዶነትና ጨለማ የሚያስወግደው ብርሃን እንደሆነ ይናገራል።

ታዲያ ይህ ብርሃን ማነው? አዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ቅርጽ አልባና ባዶ በጥልቁ ላይም ጨለማ ያለባቸው ሰዎች እነማን ናቸው? እነርሱ የሚያመላክቱት ሌላ ማንንም ሳይሆን እኛን ነው ይህ የሚያብራራው በእግዚአብሄር ብንፈጠርም

በክፉው ሰይጣን ተታልለን ውሸቦንብር ውስጥ የወደቅነውን እኛ ን ሰዎችን ነው እግዚአብሄር ገና ከመጀመሪያው የሚከተለውን ተስፋ ሲሰጥ ነበር «ውሸቦንብር ውስጥ ስትወድቁ በብርሃን አድናችኋለሁ ብርሃንን የሚቀበሉ ሰዎችም ብርሃን ይሆናሉ ነገር ግን ብርሃንን የማይቀበሉ ሰዎች ጨለማ ይሆናሉ።»

አንድን ነገር ስንፈጥር አስቀድመን የፈጠርንበት አንድ አላማ አለን ያለ አላማ የተፈጠረ ምንም ነገር የለም እግዚአብሄር በመጀመሪያ ሰማያትንና ምድርን እንዲሁም ሰውን በፈጠረ ጊዜ አላማ እኛን ልጆቹ አድርጎ ሊያሳድገንና ከእንግዲህ ወዲያ ተራ ፍጥረታቶች ብቻ ሆነን እንዳንኖር የእርሱ ልጆች በምንሆንበት በዚህ ክብር ሊያከብረን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም የሚለው ይህንኑ ነው በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ እርሱ እኛን ፍጡራኖቹን በፈጠረ ጊዜ አሻንጉሊቶች አድርጎ አልፈጠረንም ነገር ግን ለሁላችንም ነጻ ፈቃድን ሰጠን እግዚአብሄር «እያንዳንዳችሁ ጸጋዬንና በረከቶቼን ትቀበላላችሁ ወይም ትንቃላችሁ እኔ የምርጫ ነጻነት ያላችሁ ፍጡራኖች አድርጌ ፈጥሬአችኋለሁ» ይለናል።

ዮሐንስ 3:20-21 እንዲህ ይላል *«ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና ስራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሄር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።»*

እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎች ብርሃንን ከጨለማ በግልጽ መለየት እንችላለን ነገር ግን አሁንም ገና ከሐጢያት በታች ያሉ ግራ የተጋቡ ሰዎች ብርሃኑን ከጨለማ መሌት አይችሉም በፋንታው እነርሱ በጥቅሉ ብርሃንን ይጠላሉ ጨለማን ይወዳሉ የሆኖ ሆኖ ከእነዚህ ከሁለቱ የምንቀበለውን የመምረጥ መብት ሙሉ በሙሉ የእኛ ነው እግዚአብሄር ይህንን የመምረጥ መብት

ባይሰጠን ኖሮ ማለትም ነጻ ፈቃድን ባይሰጠን ኖሮ እግዚአብሄር ጻድቅ ነው ማለት ባልቻልንም ነበር።

በሌላ በኩል እግዚአብሄር ሰውን ሁሉ ወደ ሲያል እንዲወርድ ለብቻው ትቶት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሄር ቅዱስና ጻድቅ ነው ማለት አንችልም ነበር እግዚአብሄር «እኔ ሁሉን ቻይ ነኝ ነገር ግን ነጻ ፈቃድ ሰጥቻችኋለሁ ስለዚህ በእርግጥ በኃጎትን የምትወዱ ከሆነ ይህንን በኃጎት ተከተሉ በረከቶቼንም ሁሉ ተቀበሉ ነገር ግን ጨለማን ከመረጣችሁ ያንን ለማድረግ ነጻነት ይሰማችሁ» ይላል።

ስለዚህ ወደ እግዚአብሄር ብርሃን የመጡ ሰዎች እግዚአብሄርን መርጠዋል እርሱን ተቀብለውታል በእርሱም አምነዋል በዚህ ምርጫቸውም ሁሉም ከእግዚአብሄር ዘንድ የደህንነት በረከቶችን ተቀብለው ለዘላለም ይኖራሉ በሌላ በኩል ይህንን ማድረግ የተሳናቸው ሰዎች ወደ ሲያል ተጥለው ሊሰቃዩና ጥርሳቸውን ሊያፋዋጩ የተገባቸው ናቸው ምክንያቱም የራሳቸውን ሐጢያት መርጠዋልና የእግዚአብሄር ጻድቅ እውነት ይህ ነው የእግዚአብሄርን መለኮታዊነት የሚገልጠውም ይኸው ነው እግዚአብሄር ሙሉ በሙሉ ፍጹም መሆኑን የሚገልጠውም ይኸው ነው እግዚአብሄር ምንም ነገር እንድናደርግ አያስገድደንም ነገር ግን እርሱ ራሱን በኪዳኑ አማካይነት ገልጦዋል በጽድቅ እንድናመሰግነውም አድርጎናል።

እግዚአብሄር ጸጋውንና እውነቱን ለእኛ በመስጠት በሌሎች ፍጥረታቶች ሁሉ ላይ እንድንሰለጥንና በእነርሱም እንድንገለገል አዞናል እግዚአብሄር የሚባርካቸው በእግዚአብሄር ፊት ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማለትም ብርሃንን የመረጡ ሰዎችን ነው ክፋትን የሚመርጡትን ሰዎች ግን እግዚአብሄር በጽድቁ መሰረት ሐጢያቶቻቸውን ይፈርዳል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው አምላንችን ይህ ነው።

እግዚአብሄር የኪዳን አምላክ ነው ማንም ሰው እግዚአብሄር ጨካኝና የማያመዛዝን ነው ማለት አይችልም እግዚአብሄር ለሰው የመምረጥን መብት ሰጥቶዋል መጽሐፍ ቅዱስ ከበረከቶች ይልቅ እርግማኖችን የሚወድድ ሰው ካለ ያንኑ እንደሚያገኝ ይናገራል በአንጻሩ ብርሃንን የሚወዱና ይህንን ብርሃን ማለትም የእግዚአብሄርን ቃል በሕይወታቸው ለተቀበሉ ሰዎች እግዚአብሄር ተስፋ የሰጠውን በረከቶች በሙሉ ይሰጣቸዋል ሰማያትንና ምድርን በፈጠረው በእርሱ ሊባረክ ለሚወድ ሰው ሁሉ በጎነቱን እንዲመርጥና ደህንነትንና የዘላለም ሕይወትን በረከቶች እንዲቀበል ፈቅዶለታል።

ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው አምላክ እየተናገረን ነው እግዚአብሄር ፍጹም ነው እርሱ ብቻውን ጻድቅና ፍጹም ለፍጥረታቱም ሁሉ መለኮት ነው እርሱ ፈጣሪ ነው እርሱ ፍጹም አምላክ ነው ይህንን መቃወም የሚችል ማንም የለም።

እኛ በቃሉ አማካይነት በቃሉ ተስፋ የሰጠንንና ይህንን የተስፋ ቃል የፈጸመልንን የኪዳን አምላክ አይተነዋል እግዚአብሄር በመጀመሪያ ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ እግዚአብሄር ሁሉንም ጨለማንና ብርሃንንም ጨምሮ ፈጥሮዋል ይህንን ትቀበላላችሁን? የመምረጥ መብት ለሰዎች ሁሉ ተሰጥቶዋል የእግዚአብሄር ዳፊ የተሰጣቸውም በምርጫቸው መሰረት ነው።

በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ያለው «አዎ» እንጂ «አይሆንም» የሚል ቃል አይደለም በሌላ አነጋገር አንድ የማይሳሳት እውነት ብቻ አለ ያለው «አዎ» ብቻ ነው ማለት አሉታዊ ነገር የለም ማለት ነው።

እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን*

ሰለ ብርሃንም ሆነ» (ዘፍጥረት 1:2-3) መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሀር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ሲልና «ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም» በማለት ሲያክል ይህ የሚያመላክተው የእግዚአብሄር ዕቅድ ከአለም ፍጥረት በፊት እንኳን በሰይጣን ፈተና ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው።

የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ 1 እና 2 የሚገልጡት የእግዚአብሄርን ዕቅድ ከሆነ ከምዕራፍ 3 ጀምሮ ቀጣ የዚህ ዕቅድ ፍጻሜ ነው እግዚአብሄር ጠቅላላውን ዕቅዱን የተገበረው ደረጃ በደረጃ ነው ማለት እንችላለን በዚህ አለም ላይ ያሉ የሕንጻ ተቋራጮች አንድ ሕንጻ በሚሰሩበት ጊዜ የግንባታቸውን ንድፍ ብዙ ጊዜ ይለውጣሉ ነገር ግን እግዚአብሄር ዕቅዱን ከነደፈ በኋላ አንድም ጊዜ ለውጦት አያውቅም እርሱ በዕቅዱ መሰረት ሁሉንም ነገር ፈጽሞታል እግዚአብሄር የፈጠራቸውን ፍጥረታቶቹን ፍጡራኖች ብቻ አድርጎ አልተዋቸውም ነገር ግን እንደገና ተፈጥረው ዳግም እንዲወለዱ አቀደላቸው ሰውን ከሐጢያት ነጻ ያወጣው ብርሃን ነበር የእግዚአብሄር ቃል ሰዎች ከሐጢያት እንዲያመልቱ ያስቻላቸው መሳሪያ ነበር።

የሰው ዘር ቅርጽ አልባና ባዶ ባይሆን ኖሮ በጥልቁ ላይ ቸለማ ባልኖረ ነበር ማለትም የሰው ዘር በሰይጣን ባይታለል ኖሮ ሰዎች ከሐጢያት ነጻ የሚያወጣቸውን ጸጋ መልበስና የእግዚአብሄር ልጆች መሆን ባልቻሉም ነበር ሁላችንም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን የደህንነት ጸጋ እንድንለብስና የእግዚአብሄር ልጆች እንድንሆን የተፈቀደልን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመናችን ነው ክብራችን ቀድሞውኑም በእግዚአብሄር ችሮታ በዕቅዱ ውስጥ ተዘጋጅቶ ነበር።

የሰው ዘር የጋራ አያቶች የሆኑት አዳምና ሔዋን በሰይጣን ተታለሉ ነገር ግን ይህም ቢሆን በእግዚአብሄር ቅድመ ውሳኔ ውስጥ ተንቷል ኩብከባዎች በዕጭ ደረጃ ለብዙ አመታቶች

ያህል ከመሬት በታች ይኖራሉ ውለው አድረው ግን ክንፎቻቸውን ዘርግተው አንበጦች ይሆኑ ዘንድ በለውጥ ሒደት ውስጥ አልፈው ዛፍ ላይ ይወጣሉ አንበጦች ለመሆን ሁሉም ከጨለማው መሬት በታች ኩብኩባዎች ሆነው መኖር አለባቸው ልክ እንደዚሁ እኛ በሰይጣን ተፈትነን በሐጢያት የወደቅን ሰዎችም በእግዚአብሄር ክቡር ዕቅድ ውስጥ አስቀስቋን ተወስነናል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በሰይጣን እንድንፈተን የፈቀደው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን የምንለወጠው መጀመሪያ ሐጢያተኞች ስንሆን ብቻ ነው።

ሰዎች ቅርጽ አልባና ባዶ መሆናቸው ጨለማም በጥልቁ ላይ መሆኑ የእግዚአብሄርን ብርሃን ከመተው የመጣ ሁኔታ ነው ሰው ከፈጣሪው ከእግዚአብሄርና ከኪዳን ቃሉ ሲርቅ ልቡ በውሸንብርና በባዶነት ይጎበኛል የመጀመሪያው ሰው አዳም ከእግዚአብሄር ቃል በመራቅ ውሸንብር ውስጥ እንደወደቀ ሁሉ አሁንም ከአዳም ዘሮች መካከል ኢየሱስ ክርስቶስን በኪዳኑ ቃል አማንይነት መገናኘት የተሳናቸው ሰዎች በሙሉ ውሸንብር ውስጥ ወድቀዋል ለምን ውሸንብር ውስጥ ወደቁ? እግዚአብሄር የሰጠውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል ባለማወቃቸው ነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል አማካይነት የተገናኘንን አምላክ ማወቅ የማይችሉት ለዚህ ነው ይህ ከሆነ ሰዎች ከውሸንብራቸው ለማምለጥ ምን ማድረግ አለባቸው? ወደ እግዚአብሄር የእውነት ቃል ቢመጡ በእርግጥም እግዚአብሄርን ሊያገኙት ይችላሉ።

ከዚህም በላይ ሰው ሁሉ ባዶነት ውስጥ የወደቀው በሐጢያቶቹ ምክንያት ነው ስለዚህ ሰዎች እርካታ የላቸውም እኛ ሰዎች ከእውነት አምላክ ጋር እስካልተገናኘን ድረስ ባዶ ነን ሰዎች መጀመሪያ ሲፈጠሩም ፍጹማን አልነበሩም እግዚአብሄር ይህንን አለፍጽምና ቀድሞ የፈቀደው በዕቅዱ ፍጹማን

ሊያደርገን ነው እኛ የፈጠረን ፍጹም የሆነው አምላክ ስለሆነ እርሱ በውስጣችን እስከሌለ ድረስ ፍጹማን ያልሆኑ ሰዎች ሆነን እንቀራለን እውነተኛ እርካታም አይኖረንም ባዶነት ውስጥ እንወድቃለን ስለዚህ እግዚአብሄር ሲፈጥረን እኛን ሰዎችን በአምሳሉ ስለፈጠረን ሰው ሁሉ እውነተኛ እርካታን ማግኘት ከፈለገ ያለ ማመንታት ዳግም መወለድ አለበት በሌላ አነጋገር በሰዎች ልቦች ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት ሊኖር ይገባል እኛ ፍጹማን ልንሆን የምንችለው በውስጣችን መንፈስ ቅዱስ ሲኖር ብቻ ነው ሰው በእውነት የሚረካው ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያገኝ ብቻ ነው።

ሁላችንም በሰይጣን ክፉ ሴራዎች ተታልለናል በዚህ የተነሳ ሁላችንም ውሸቦንብር ውስጥ፣ ባዶነትና ሐጢያት ውስጥ ወደቅን እግዚአብሄርም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንደ እኛ ያሉ ሰዎችን እንደሚያድን ተናገረ ከምድን እንደሚያድነን ቃል ገባልን? ከውሸቦንብር፣ ከባዶነትና ከሐጢያት ሊያድነን ቃል ገባ ከሐጢያቶቻችን፣ ጥልቅ ከሆነው ባዶነታችንና ከማይረካው ቅብዝብዝነታችን ሊያድነን ቃል ገባ ይህ የደህንነት ተስፋ ቀድሞውኑም በኢየሱስ ክርስቶስ የታሰበ ነበር።

ፈጣሪው ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች አዳኝ ነው

የዩኒቨርስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ» ተብሎ ሲጻፍ እዚህ ላይ ብርሃኑ ሌላ ማንም ሳይሆን እናንተንና እኔን ከሐጢያቶቻችንን ያዳነን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ዩኒቨርስንና

በውስጡ ያሉትን ነገሮች በቃሉ የፈጠረው ማነው? ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አይኖቻችን የሚያዩትን እያንዳንዱን ነገር ከሰማያት እስከ ምድር፣ ከተራሮች እስከ ባህሮች፣ ከአበቦች እስከ ሁሉም አይነት የሕይወት መልኮች ድረስ ያለውን የፈጠረው ይኸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» (ዘፍጥረት 1:1) ይህንን ምድርና እነዚህን ሰማያት የፈጠረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሁላችንም ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ካለ እግዚአብሄር የራሱን ልጅ በመላክ ሐጢያቶቻችንን የደመሰሰ መሆኑ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላስ ማነው ይላል? ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር አብ ልጅ ነው ይላል *«ትዕዛዙን እናገራለሁ እግዚአብሄር አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ» (መዝሙረ ዳዊት 2:7)* ተብሎ እንደተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በአብ እንደተወለደ ይናገራል ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር አብ ልጅ ልክ እንደ አብ ያው እውነተኛ አምላክ እንደሆነም ይናገራል። **(1ኛ ዮሐንስ 5:20)**

ኢየሱስ ክርስቶስን በራሱ አይኖች ያየው በራሱ እጆች የዳሰሰውና ለሦስት አመታቶችም አብሮት የኖረው ሐዋርያው ዮሐንስ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሄር ነበረ» **(ዮሐንስ 1:1)** ያለው ለዚህ ነው በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ዩኒቨርስን የፈጠረ አምላክ ነው እግዚአብሄር አብ መንግስተ ሰማይን በልጁ አማካይነት ገነባ ኢየሱስ ክርስቶስም አሁን አይኖቻችን የሚያዩዋቸውን ሰማያትና ምድር ፈጠረ ሁላችንም ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አምላክ እንደሆነ በትክክል ልናውቀው ይገባናል።

ሌላስ እግዚአብሄር ምን አለ? ሐጢያት አልባ በሆነው ልጁ አማካይነት ከሐጢያቶቻችን ሁሉ እንደሚያድነን ተናግሮዋል እግዚአብሄር የእውነት አምላክ ነው የእግዚአብሄር አብ ልጅ

ይህንን አለም በፈጠረ ጊዜ እግዚአብሄር በብርሃን ያብረቀረቀውን አለም በማየቱ መልካም እንደሆነ ተናገረ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል *«ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ አለም ይመጣ ነበረ።» (ዮሐንስ 1:9)*

ይህ የእግዚአብሄር ዕቅድ የተገለጠው በስላሴ አምላክ ማለትም በእግዚአብሄር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል «ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበረ» በውሃ ላይ ሰፍፎ የነበረው ይህ መንፈስ ማነው? እዚህ ላይ መንፈስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው ይህንን ዩኒቨርስ የፈጠረው የአብ ልጅ ነው እግዚአብሄር አብም በልጁ አማካይነት ውሸጉንብርና ባዶነት ውስጥ የወደቁትን እነዚህን ሰዎች ሁሉ እንደሚያድን ቃል ገባ።

እግዚአብሄር የእግዚአብሄር ልጆች የሚያደርገንን መንፈስ ሊሰጠን ፈለገ ነገር ግን በውስጣችን ሐጢያት እስኃለ ድረስ ይህ መንፈስ ወደ ልባችን ሊገባ አልቻለም እግዚአብሄር አብ ከእኛ ከፍጥረታቶቹ ጋር ኪዳንን ያደረገውና ልጁን ወደዚህ ምድር ለመላክ ቃል የገባልን ለዚህ ነው እዚህ ላይ «የእግዚአብሄር መንፈስ» የሚያመላክተው መንፈስ ቅዱስን ነው ይህ መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሄርን የተስፋ ቃል ወደሚያምኑትና ወደሚከተሉት ሰዎች ይገባና አብሮዋቸው ይኖራል የእግዚአብሄር ዕቅድ ይህ ነው እዚህ ላይ ስላሴ አምላክ ተገልጦዋል እግዚአብሄር አለምን ከመፍጠሩ በፊት ለእኛ የተሟላ ዕቅድ ነበረው ይህንንም ዕቅድ ደረጃ በደረጃ ሲፈጽመው ቆይቶዋል እግዚአብሄር የምድርን ግዛትና የሰማያትን ግዛት በፈጠረ ጊዜ መልካም እንደሆነ ማየቱን የተናገረው ለዚህ እንደነበር መረዳት ያስፈልገናል።

እግዚአብሄር ልጁ ይህንን ዩኒቨርስ በፈጠረበት

በመጀመሪያው ቀን ብርሃንን በፈጠረ ጊዜ መልካም እንደሆነ ማየቱን ተናግሮዋል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የፈጠራቸውን ፍጥረታቶች የራሱ ልጆች ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመሳሳይ ልጆቹ በማድረጉ ተደሰተ ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሄርን የከበረ ዕቅድ ተገንዝቦ *«የእግዚአብሄር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው ፍርዱም እንዴት የማይመረመር ነው ለመንገዱም ፍለጋ የለውም» (ሮሜ 11:33)* በማለት ያመሰገነው ለዚህ ነው።

እንዲህም ተብሎ ተጽፎዋል *«ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን» (ሮሜ 11:36)* ታዲያ አንድ ተራ ፍጡር በፈጣሪው ላይ እንዴት ሊያምጽ ይችላል? አለመታዘዝ ራሱ ሐጢያት ነው እግዚአብሄር የተስፋ ቃሉን ነግሮናል እርሱ በቃሉ አማካይነት ልጆቹን ከዲያብሎስ ለጆች የሚለይ አምላክ ነው እግዚአብሄር የተናገረውን ቃል በልቦቻችሁ ውስጥ ከተቀበላችሁ እናንተም የእግዚአብሄር ሕዝብ ትሆናላችሁ ወደ እውነት ብርሃን ቅረቡ ያን ጊዜ እናንተም ደግሞ ብርሃን ትሆናላችሁ።

እግዚአብሄርም *«ብርሃን ይሁን»* አለ

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ሰውንና ዩኒቨርስን በፈጠረ ጊዜ ምድር ባዶ እንደነበረችና አንዳች እንዳልነበረባት ጨለማም በጥልቁ ላይ እንደነበረ ይናገራል መጽሐፍ ቅዱስ በሐጢያት የወደቁትን ሰዎች ሁኔታ የገለጠው እንዲህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ምድር ማለትም የሰው ልብ ምንም ባልነበረው ባዶ በነበረና በሐጢያት ጥልቅ ውስጥ በሆነ ጊዜ የእግዚአብሄር መንፈስ በውሃ ላይ ይሰፍፍ እንደነበር ይናገራል በሌላ አነጋገር ዩኒቨርስን

የፈጠረውና የሰውን ዘር ያዳነው እግዚአብሄር በሐጢያተኞች ልቦች ውስጥ ይሰራል።

እግዚአብሄር በቃሉ በመታመን በቃሉ አማካይነት ወደ እርሱ ለቀረቡ ሰዎች ይናገራል ከእነርሱም ጋር ሕብረትን ያደርጋል በቃሉ ስናምን እግዚአብሄር ይቀበለናል ነገር ግን በእግዚአብሄር ቃል የማናምን ከሆነ በመጨረሻ አስተሳሰቦቻችን ወደ ጥፋት ይነዱናል።

ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ የሰጠውና የሸጠው ይሁዳ ራሱን ለምን ሰቀለ? እርሱ በእግዚአብሄር ቃል በመታመን ይህንን ሐጢያት መፍታት ይችል ነበር ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ በቃሉ ከመታመን ይልቅ ተጸጽቶ ራሱን እንደሰቀለ ጽፎዋል ልቦቻቸው በእግዚአብሄር ቃል ላይ እምነት የሌላቸው ሰዎች መጨረሻቸው ራሳቸው ሐጢያቶቻቸውን መኮነን ይሆናል ስለዚህ ለዘላለም ከመሞት አያመልጡም ይሁዳ በራሱ መንገድ መጸጸቱ የሚያሳየው ለጥቂት ሳንቲሞች ሲል የገዛ ራሱን መምህር አሳልፎ በመስጠትና በመሸጥ ትልቅ ስህተት እንደሰራ በመገንዘቡ በሕሊናው መወቀሱን ነው።

የይሁዳ ምግባር በጣም የከፋ ነበር ነገር ግን ከዚህ የሚበልጠው መንፈሳዊ ስህተቱ ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ አድርጎ አለማመኑ ነበር በአዲስና በብሉይ ኪዳናት ቃል ላይ ተመስርተን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ምን እንዳደረገ ልናሰላስል ይገባናል ከዚህ ተነስተንም እርሱ ራሱ አምላክና የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መረዳትና ማመን አለብን ይሁዳ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነት አላመነም ስለዚህ «እውነተኛውን የእግዚአብሄር ልጅ አሳልፌ ሰጠሁ እርሱንም አዳኜ አድርጌ አልተቀበልሁትም» ብሎ ከመጸጸት ይልቅ በራሱ ሕሊና ተወቀሰ አስተማሪው የነበረውን ሰው አሳልፎ በመስጠቱ በጸጸት ስለተገረፈ ራሱን አጠፋ።

በእግዚአብሄር ፊት መቆም የምንችለው በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተመስርተን ስህተቶቻችንን ስናውቅና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ከሐጢያቶቻችን ንስሐ ስንገባ ብቻ ነው ከዚህ በተቃራኒ ምግባሮቻችንን በራሳችን መለኪያ መሰረት ብቻ የምንዳኝ ከሆንን ሕይወታችንን ከማጣታችንም በላይ ዘላለማዊ ወደሆነው የሲያል እሳትም እንጣላለን።

አንዳች የተሳሳተ ነገር ስናደርግ ብዙውን ጊዜ «ኦ ስህተት ሰራሁ» ብለን እናስባለን ነገር ግን እኛ መልካምንና ክፉን የምንለንበት መለኪያ በጣም አሻሚ ነው ከእኛ አመለካከት አንጻር ምግባሮቻችን በተለየ መንገድ ሊገመገሙ ይችላሉ ብዙውን ጊዜ በስጋ አይን መልካም መስሎ የሚታየው በመንፈሳዊ አመለካከት በጣም የከፋ ሆኖ ይታያል ስለዚህ ይሁዳ በእግዚአብሄር ፊት በተጸጸተ ጊዜ የተጸጸተው በሕሊናው እንጂ የእግዚአብሄርን ቃል በማመን አይደለም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አምላክና የእኛ የሰዎች አዳን መሆኑ ግልጽ ነው ይሁዳ በዚህ አዳኝ አለማመኑ እጅግ ትልቁ ስህተቱ ነበር ይሁዳ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ አድርጎ ስላላመነ አሳልፎ ሰጠው ይህ የራሱ ስህተት ነበር ይሁዳ ግን ይህንን አልተገነዘበም በሌላ አነጋገር ይሁዳ በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተመስርቶ ስህተቱን አላመነም በፋንታው ስህተቱን ያመነው በሕሊናው ብቻ ነበር ስለዚህ በእርግጠኝነት ሲያል እንደሚወርድ ስላሰበ ራሱን ገደለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁዳ በጭራሽ ባይወለድ ይሻለው እንደነበር በሐዘን የተናገረው ለዚህ ነበር። (ማርቆስ 14:21)

እግዚአብሄር የሚናገረንና በልቦቻችን ውስጥ የሚሰራው በቃሉ አማካይነት እንደሆነ ሁላችንም መገንዘብ አለብን እግዚአብሄር በዚህ የእውነት ቃል አማካይነት ግራ በተጋባነው፣ ባዶ በሆንነውና በሐጢያት ጥልቅ ውስጥ ባለነው በእኛ ላይ የደህንነትን ብርሃን እንዳበራልን ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባናል

እግዚአብሄር ብርሃኑን ስላበራልን ልቦቻችን ምን ያህል ባዶና ግራ የተጋቡ እንደሆኑና እኛም እንደምን በሐጢያት ጥልቅ ውስጥ እንዳለን በመጨረሻ መገንዘብ የምንችለው በዚህ የእውነት ብርሃን አማካይነት ነው ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሄር የደህንነትን ብርሃን በሁላችንም ላይ ስላበራ ነው እግዚአብሄር ይህንን ብርሃን ባያበራ ኖሮ ግራ መጋባታችን ስለማናውቅና ባዶ እንደሆንንና ጨለማ ውስጥ እንዳለን ስለማናስተውል ፈጽሞ ምንም ነገር መረዳት ባልቻልንም ነበር።

እግዚአብሄር እንደ እኛ ላሉ ሰዎች የደህንነትን ብርሃን አበራልን ብርሃኑንም ከጨለማው ለየ ስለዚህ ብርሃን ልናውቅ ይገባናል አንድ ነገር ስንሰራ ከእግዚአብሄር ቃል ምልከታ አንጻር ወይም በራሳችን ስጋዊ አስተሳሰብ ላይ ተመርኩዘን ያው ተመሳሳ ነገር በጣም በተለየ መንገድ ሊታይ ይችላል ተመሳሳይ የሆነ ነገርን በምንመለከትበት ጊዜም እንኳን ብርሃን በሆነው በእግዚአብሄር ቃል አማካይነት የምናየውና በራሳችን ስጋዊ አይኖች አማካይነት የምናየው ፈጽሞ የተለያየ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ ብርሃንን መከተል በእጅጉ አስፈላጊ ነው ልቦቻችንና አስተሳሰቦቻችን ይህንን ብርሃን መንከባከብና መውደድ አለባቸው እኛም ሁልጊዜ ምዚህ ብርሃን መሰረት መኖርና ሁሉንም ነገር ከእርሱ እይታ አንጻር መመልከት አለብን ይህ አስፈላጊ ነው እኛ ሁላችን በዚህ መንገድ በብርሃኑ መሰረት መኖር አለብን።

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ እንዲህ ብሎዋል *«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም» (ዮሐንስ 8:12)* በእግዚአብሄር ውስጥ ምንም አይነት ጨለማ የለም ያለው ብርሃን ብቻ ነው እኛም እግዚአብሄር የሰጠውን የደህንነት ብርሃን በመቀበል ጻድቃን ሰዎች ሆነናል በትክክል ድነን እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ሐጢያተኞች ሆነን ቀርተን እንደሆነ ወይም ጻድቃን

እንደሆንን ሁሉም የሚመረኮዘው ይህ የእውነት ብርሃን አለን ወይስ የለንም በሚለው ላይ ነው።

ስለዚህ ደህንነታችን ይህ ብርሃን እንዲኖረን ይጠይወናል ነገር ግን ከዚያ በኋላስ? ከዳንን በኋላ ልንኖር የሚገባን እንዴት ነው? የእውነትን ብርሃን መከተል አለብን ወንጌልን ስታሰራጩ «*እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ*» ተብሎ እንደተጻፈ ሌሎችን እግዚአብሄር በሰጠው የእውነት ብርሃን እያበራናቸው ነው ብርሃንን እየተከተላችሁና ብርሃንን እያበራችሁ ነው እኛ የዚህ ብርሃን ፈጣሪ አይደለንም ነገር ግን የምናደርገው ነገር ቢኖር ይህንን ብርሃን በልቦቻችን ውስጥ መቀበልና ለሌሎች ማብራት ነው ምክንያቱም ይህንን ወንጌል መስበክ ብርሃንን ማብራት ነውና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበንችን ብርሃንን ማስፋፋት ነው ያን ጊዜ ነፍሳቶች እኛ የሰበክነውን የብርሃን ቃል ሰምተው ይለወጣሉ።

ብርሃኑን ገና በጨለማ ውስጥ ላሉ ሰዎች የማናበራ ከሆነ ምንም ያህል በሚገባ ብናስተምራቸውና የልቦቻቸውንም መሬት በደንብ ብናርስ ሁሉም ነገር ዋጋ የለውም ጥረቶቻችን ሁሉ ዋጋ የላቸውም ሁላችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮችና ቅዱሳኖች እንደመሆናችን ሁላችንም ልናደርግ የሚገባን ነገር ቢኖር እውነተኛውን ብርሃን ማብራት ነው «የእምነት ሕይወታችን ብርሃንን የሚከተል ሕይወት ነው እኛ የእግዚአብሄርን ብርሃን እንከተላለን መመስከር ብርሃንን ማብራት ነው በዚህ አለም ላይ ብዙ ነገሮች አሉ በእግዚአብሄር ዘንድ ግን ብርሃን እንጂ ጨለማ የለም» በማለት አእምሮዋችንን ብናዘጋጅ ሕይወታችን ይበልጥ ብሩህ ይሆናል።

እኛ ይህ ብርሃን አብሮን አለ በዚህ አለም ላይ ብርሃንና ጨለማ አሉ እኛ የምንከተለው ግን ብርሃንን ነው እግዚአብሄር «ብርሃን ይሁን» ብሎ የእውነትን ብርሃን ሰጥቶናል ወንጌልን

በምንሰብክበት ጊዜ ይህንን ብርሃን እያበራን ነው የቀን ተቀን ሕይወታችንን ስንኖርም ይህንን ብርሃን እየተከተልን ነው።

እግዚአብሄር በሰጠን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ማለትም በእግዚአብሄር እውነት አማካይነት ድነናል ብርሃንም ሆነናል አሁን ብርሃን እንደሆንን እናምናለን ብርሃንን እንሰብካለን ይህንን ብርሃን እየተከተልንም ሕይወታችንን እንኖራለን በዚህ ምድር ላይ በብርሃኑ መሰረት የሚኖርና የስጋን ነገሮች የሚያስፋፋ ሳይሆን ብርሃንን የሚያሰራጭ የሕይወት አይነት ልንኖር እንፈልጋለን እግዚአብሄር እኛን የጠራን ለዚህ አላማ ነው በሕይወታችን ውስጥ ፈጽሞ ልንረሳው የማይገባን ነገር ቢኖር ይህንን ብርሃን መከተል ነው ይህ ማለት ግን በስጋዊ ፍጽምና መኖር አለብን ማለት አይደለም።

ብርሃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው እርሱም በብርሃኑ ልቦቻችንን አብርቷል እኛም ይህንን ብርሃን ተቀብለናል ስለዚህ ቀን ሆነናል ብርሃን ሆነናል ማለት በስጋ ፍጹማን ሆነን መኖር እንችላለን ማለት አይደለም ይልቁንም ይህ ማለት በእግዚአብሄር ጸጋ ችሮታ የሐጢያት ስርየትን ተቀብለናል ማለት ነው ሁላችንም ብርሃን ምን እንደሆነ በግልጽ ማወቅ አለብን።

ሕይወታችንን ስንኖር ብዙውን ጊዜ ስለ ወንጌል ብርሃን በቀላሉ እንረሳለን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ብርሃን ነው ነገር ግን ይህንን እንረሳለን የጠፋብንን ነገር ካገኘን በኋላ አግኝቶ የመለሰልንን ሰው ፈጥነን ልንረሳው እናዘነብላለን ልክ እንደዚሁ አእምሮዋችንም ብርሃንን ይረሳል ይህ ከበድ ያለ ችግር ነው።

እኛ ብርሃን አለን ይህም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይህ ብርሃን የውሃውና የመንፈሱም ወንጌል ነው ብርሃን ካለ የሰው ደመ ነፍስ ብርሃንን ይከተላል እነርሱ ብርሃንን ማገልገል ይፈልጋሉ ልቦቻችን ብርሃን ቢኖራቸው መልካም ነው

እግዚአብሄር ብርሃን መሆኑን አእምሮዋችን ቢያስታውስም መልካም ነው ወንጌልን መስበክ ብርሃንን ማሰራጨት ነው ብርሃንን የምናሰራጨው የራሳችንን አንዳች ነገር ስናደርግ ሳይሆን ከጌታ የተቀበልነውን ወንጌል ስንሰብክ ነው ብዙ የተለያዩ ነገሮችን እናደርግ ይሆናል እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተደረጉት ግን ወንጌልን ለመስበክ ነው የእምነት ሕይወታችንን የምንኖረው ብርሃንን ለመከተል ነው ሁሉን የምናደርገውና ሕይወታችንንም በሙሉ የምንኖረው በዚህ ብርሃን ነው።

እግዚአብሄር በመጀመሪያው የዮሐንስ መልዕክት ላይ በተደጋጋሚ ስለ ብርሃን ተናግሮዋል *«በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ አለ ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል ማሰናከያም የለበትም ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ በጨለማም ይመላለሳል የሚሄድበትንም አያውቅም ጨለማው አይኖቹን አሳውሮታልና።»* *(1ኛ ዮሐንስ 2:9-11)*

የምንኖረው በእግዚአብሄር ጸጋ ነው ወንጌልን መስበክና የእግዚአብሄርን ስራ መስራት በእርግጥም ብርሃንን የሚያሰራጭ ሕይወትን መኖር ነው ይህንን ሕይወት በጣም ውስብስብ አድርጋችሁ ከማሰብ ይልቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና የእርሱን የደህንነት ወንጌል እውነት መስበክ ብርሃንን የሚያስፋፋ ሕይወትን መኖር እንደሆነ በቀላሉ በግልጽና በትክክል ልትገነዘቡ ይገባል እናንተ ማድረግ የሚኖርባችሁ ነገር ቢኖር የብርሃን ሕይወት ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን ብርሃን አድርጎ ማመንና መስበክ መሆኑን በአእምሮዋችሁ መያዝ ነው።

ይህንን በአእምሮዋችሁ ውስጥ እስንልያዛችሁ ድረስ ለምን እንደምትኖሩ መገንዘብ አትችሉም ይህንን ያልሁበት ምክንያት በቅርቡ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎች በአእምሮዋቸው ውስጥ በጣም ብዙ ነገሮች ስላሉ ነው

የእግዚአብሄር አገልጋዮች እንዲሆኑና እንዲሰሩ ሲነገራቸው በሁሉም አይነት ማመንታት ይሞላሉ ነገሩ ለምን እንዲህ ሆነ? እነርሱ ስለ እግዚአብሄር ቃል ስለረሱ ነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የመዳናችን እውነታም ቢሆን ቀድሞውኑም የተደረሰበት ነገር ነው ስለዚህ የዚህን ክቡርነት ልንረሳ እንችላለን።

በየጊዜው ብርሃን የመሆናችንን እውነታ ማረጋገጥ የሚገባን ለዚህ ነው «እግዚአብሄር ብርሃን ነው እግዚአብሄር ብርሃን እንዲሆን አዘዘ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄር ብርሃኑን ከጨለማው ለየ ብርሃኑን ቀን ጨለማውንም ሌሊት ብሎ ጠራው እግዚአብሄር ቅርጽ አልባ ባዶና ጨለማ በሆነችው ምድር ላይ ብርሃኑን አበራ እግዚአብሄር ብርሃኑን በዚህች ምድር ላይ ባበራ ጊዜ እኔም ዳግም ተወለድሁ ግራ መጋባቴን፣ ባዶነቴንና የጨለማዬን ጥልቀት ተገነዘብሁ» ብለን በማሰላሰል እንደገና ቃሉን ማሰብ ያስፈልገናል።

አንድ ነፍስ ጻድቅ መሆኑ ወይም ሐጢያተኛ ሆኖ መቅረቱ በእግዚአብሄር ብርሃን የሚወሰን ቀላል ውጤት ነው እግዚአብሄር በደህንነት ብርሃን ማለትም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሲያበራን ይህንን የደህንነት ብርሃን የሚቀበሉ ሰዎች ጻድቃን ይሆናሉ ይህንን ብርሃን በልቦቻቸው የማይቀበሉ ሰዎችም ሐጢያተኞች ሆነው ይቀራሉ ጸሐይ በማለዳ ስትወጣ ብርሃንዋ መላውን አለም ያበራል ማንም ሰው ከሙቀትዋ ማምለጥና መደበቅ አይችልም። (መዝሙረ ዳዊት 19:6)

በሌላ አነጋገር እውነተኛውን ብርሃን ለመቀበል በጣም የሚርቅ ስፍራ የለም ሁሉም ነገር ይበራል ሁሉም ነገር ይህንን ብርሃን ያንጸባርቃል ያበራማል።

ጨረቃ ከጸሐይ የተቀበለችውን ብርሃን እንደምታንጸባርቅ ሁሉ እኛም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ቅዱሳን

የሆንን ሰዎች ወደ ብርሃኑ መመልከትና ይህንን ብርሃን ሁሌም ማብራት አለብን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ የአለም ብርሃን ነኝ» ቢልም እኛ የአለም ብርሃን ነን ማለት አንችልም በስጋችን ውስጥ የሚወደድ ወይም የሚያኮራ ምንም ነገር የለም እኛ ማንም አይደለንም በስጋችን ብርሃኑን ማብራት አንችልም መጽሐፍ ቅዱስ *«ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነው ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው» (ሮሜ ፰፡፮)* እንደሚል በቀን ተቀን ሕይወታችን ውስጥ ብርሃንና ጨለማ አብረው ይኖራሉ፡፡

የሐጢያቶቻችንን ስርየት የተቀበልን ሰዎች ብርሃን እንዳለን ስናውቅና በዚህ ብርሃን ላይ አተኩረን ይህንን ብርሃን እየተከተልን ወደፊት ስንገሰግስ ሁሌም ትክክለኛ ሕይወትን መኖር እንችላለን እኛ በእርግጥም ብርሃን እንዳለን ማሰባችን ያስደስታል ልቦቻችንን ሲጨልሙ ግራ ስንጋባና ምን እንደምናደርግ ሲጠፋን ብርሃኑን ብቻ ብንመለከት ወዲያውኑ ትክክለኛውን ነገር መወሰን እንችላለን ምን ማድረግ እንደሚገባንና እንዴት መኖር እንደሚገባን ለይተን ማወቅ የምንችለው በብርሃን ነው እኛ ሰዎች ስለሆንን ብዙውን ጊዜ ግራ እንጋባለን ብዙውን ጊዜ ባዶነት ይሰማናል ብዙውን ጊዜም ጨለማ በጥልቁ ላይ ነው ነገር ግን እንደዚያም ቢሆን እንዲህ ባሉ ወቅቶች ብርሃኑን መከተል እንችላለን ምክንያቱም ብርሃን አለንና፡፡

ብርሃን ስላለን ይህም ብርሃን በልቦቻችን ውስጥ ስላለና ይህ ብርሃን በመላው ዩኒቨርስ ውስጥ ስለሚገኝ በጣም አመስጋኝ ነኝ ብርሃንን የሰጠን አምላክ ስላለ በእርግጥም አመስጋኝ ነኝ ምንም አይነት ሁኔታዎች ቢገጥሙንም በውስጣችን ምንም አይነት ጉድለቶች ቢገለጡም ብርሃን ስላለን አሁንም እርሱን መከተል እንችላለን እኔ ለዚህ ምን ያህል አመስጋኝ እንደሆንሁ የምገልጥበት ቃላቶች የሉኝም ይህ ብርሃን እዚያ ባይገኝ ኖሮ

የሚጠብቀን ተስፋ ቢስነት ብቻ ይሆን ነበር።

ብርሃን ባለው ሰውና ብርሃን በሌለው ሰው መካከል ትልቅ ልዩነት አለ ብርሃን ያላቸው ሰዎች ለጥቂት ጊዜ ይጨልሙ ይሆናል ነገር ግን ብርሃን ስላላቸው እንደገና መዘውሩን ይዘው የብርሃኑን ምሪት ሊከተሉ፣ የሕይወታቸውን አቅጣጫ ሊወስኑና ብርሃኑን እየተከተሉ መጓዝ ይችላሉ።

በአንጻሩ ምንም ያህል ይህንን ቢመኙም ብርሃን የሌላቸው ሰዎች ይህንን ብርሃን ያልተቀበሉ ሰዎች የብርሃን ሕይወትን መኖር አይችሉም ይህ ትልቅ ልዩነት ያመጣል በስጋ አንጻር ሲታይ ብርሃንን በተቀበሉ ሰዎችና ባልተቀበሉ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት ጥቂት ነው ከስጋ አንጻር ከታየ አስተሳሰቦቻቸውም ቢሆኑ እርስ በርስ የተለያዩ አይደሉም በሁለቱ መካከል ያለ ማንኛውም ልዩነት በጣም ጠባብ ነው የሚነገርለት ትልቅ የሆነ ልዩነትም የለም ዳግም የተወለደ ሰው ወደ መታጠቢያ ክፍል እንደሚሄድ ሁሉ እኔም ወደ መታጠቢያ ክፍል እሄዳለሁ እርሱ ሲበላ እኔም ደግሞ እበላለሁ።

ብቸኛው ልዩነት ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት ተቀብሎዋል ወይስ አልተቀበለም የሚለው ነው ከዚህ ውጭ ሌላ ምንም ልዩነት የለም ይህ ትንሽ ልዩነት ይመስል ይሆናል ነገር ግን ግዙፍ የሆነ ልዩነት ነው እኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላለን በእርሱ ጸጋ እንኖራለን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለምናምንም የእግዚአብሄርን ስራ ሁሌም መስራት እንችላለን።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማንይነት ዳግም የተወለዱ ሰዎች ፈጽመው ጎዶሎዎች ይሆኑ ይሆናል ነገር ግን አሁንም ቢሆን ብርሃኑን መመልከትና ሁሌም እርሱን መከተል ይችላሉ በአንጻሩ ብርሃኑን ያልተቀበሉ ሰዎች ይህንን ለማድረግ ምንም ያህል ቢመኙም ጥሩ ሰዎች ሆነው መኖር አይችሉም እኔ ይህ ሁሌም በዙሪያ ሲከሰት አያለሁ የእግዚአብሄር አገልጋዮች

ተብለው የሚጠሩት እንኳን በውስጣቸው ብርሃን የላቸውም ስለዚህ ምንም ነገር ማስተማር አይችሉም ከእነርሱ ብዙዎቹ ንጥቀት መቼ እንደሚመጣ ከታላቁ መከራ በፊት፣ በኋላ ወይም በመካከል ስለመሆኑ ጉባኤያቸውን ማስተማር የማይችሉት እነርሱ ራሳቸው ይህንን በግልጽ ስለማያውቁ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን እንደሆነ የሚያውቁና ይህንን ብርሃን የተቀበሉ ከሆኑ አሁንም ድረስ በጨለማ ያሉት ለምንድነው? ወንጌሉና ብርሃኑ እዚያው እያሉ እንዴት ይህንን ማወቅ አልቻሉም? ጌታ የመጨረሻው መለከት ሲነፋ ተመልሶ እንደሚመጣ በግልጽ ተናግሮዋል ነገር ግን ይህ የመጨረሻው መለከት የሚነፋው መቼ ነው? ከታላቁ መከራ በፊት ነውን? ፈጽሞ አይደለም! ታዲያ ከታላቁ መከራ በኋላ ነውን? በፍጹም! ሁለቱም አመለካከቶች ትክክል አይደሉም ምክንያቱም ጌታችን ንጥቀት የሚሆነው ታላቁ መከራ ከጀመረ በኋላ ነገር ግን ከመጠናቀቁ በፊት የሰባቱ ጽዋዎች ቁጣ ከመውረዱ በፊት እንደሆነ ተናግሮዋል በዚያን ጊዜም ብዙ ቅዱሳኖች ሰማዕት ይሆናሉ እኛ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ካለ በዚህ መሰረት ማመን ነው በእርግጥ ብርሃን ያለው ሰው ይህንን ማወቅ ይሳነዋልን?

በአሁኑ ጊዜ ምኵርያ ያሉ ቤተክርስቲያኖች ትላልቅ የቤተክርስቲያን ሕንጻዎችን ለመስራት የሚፎካከሩ ይመስላሉ በአለም ላይ ካሉት አስር ታላላቅ ቤተክርስቲያኖች አምስቱ የሚገኙት በኮርያ ነው ይባላል የእነዚህ ቤተክርስቲያኖች አንዳንዶቹ መጋቢዎች ጉባኤያቸው ብድሮችን በመበደርና ቤቶቻቸውን በወለድ አግድ በማስያዝ የግንባታ ገንዘቦችን እንዲለግሱ ያደርጉዋቸዋል ይህ አይነቱ ባህርይ ብርሃንን የተቀበሉ ሰዎች ከሚኖሩት ሕይወት ጋር የሚጣጣም ነውን? እነርሱ እውነተኛውን ብርሃን አልተቀበሉም።

ብርሃንን የተቀበሉ ሰዎች በጸጋ ይመላለሳሉ እግዚአብሄር ስላዳነን በእግዚአብሄር የተሰጠውን የውሃና የመንፈስ ወንጌል የምንሰብከው በእርሱ ጸጋ ነው ሁሉን የምናደርገውም እግዚአብሄር በሰጠን ጉልበት መጠን መሰረት ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *«ሐይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» (ፊልጵስዩስ 4:13)* በማለት የመሰከረው ለዚህ ነው።

አንዳንድ ሰዎች በኋላ መጋቢ ለመሆን በቤቶቻቸው ውስጥ ሆነው በራሳቸው ጥረት መጽሐፍ ቅዱስን እያጠኑ እንደሆነ ይናገራሉ ነገር ግን አንድ ሰው መጋቢ ሆኖ ለማገልገል ከፈለገ በመጀመሪያ ስለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል መማርና በእርሱም ማመን አለበት በመጀመሪያ ብርሃኑን መቀበል አለበት በጨለማ ውስጥ ለተቀመጡ ለሌሎች ብርሃኑን ማብራት የሚችለው እርሱ ራሱ ብርሃን ሲሆን ብቻ ነው።

እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን በእግዚአብሄር ጸጋ ውስጥ ወደ መኖር መጥተናል እኛ እግዚአብሄር ያበራልንን ብርሃን እያበራን ያለነው በእግዚአብሄር የውሃና የመንፈስ ወንጌል አማካይነት የደህንነትን ስጦታ ስለተቀበልን ነው በጌታ ሆኜ እግዚአብሄር ምን አይነት ጸጋ እንደሰጠን በጸጥታ አሰላስላለሁ እግዚአብሄር ሥራውን በአደራ ሰጥቶናል እኛም እርሱ በሰጠን ሐይል ክልል ውስጥ ሆነን ይህንን ስራ በእምነት እንሰራለን እንዲህ በማመን ጌታን ስለምንከተል ሁሌም ሰላም አለን።

ሰው ደህንነቱን ካልተቀበለ እኛም በጉልበት በእርሱ ላይ አንጭንበትም እኛ አምላክ ነን? የለም አይደለንም እኛ እግዚአብሄር ብርሃን እንደሆነ እናምናለን ይህንንም ብርሃን እንከተላለን ልቦቻችን ድንሞችና ጨለማ ውስጥ ሊወድቅ ሲያዘነብል እንደገና ቀና ብለን ብርሃኑን ማየትና በእርሱ እንድንበራ ይህንን ብርሃን መከተል ይኖርብናል።

ወጥታችሁ ስትመሰክሩ ይህንን ከሚታወቀው በላይ በጣም አዳጋች አታድርጉት እኛ እያሰራጨን ያለነው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ብቻ ነው እያሰራጨን ያለነው የራሳችንን አንደበተ ርቱዕነት፣ የራሳችንን ስጦታ ወይም የራሳችንን ጥበብ አይደለም እኛ የምንመንበት ምንም ነገር የለንም ነገር ግን እያሰራጨን ያለነው ኢየሱስ ክርስቶስ ያጠናቀቀውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ብቻ ነው የምንኖረውም በብርሃኑ መሰረት ነው ዋናው ነገር አንድን ነገር በሚገባ መስራታችን ወይም አለመስራታችን አይደለም ነገር ግን ዋናው ነገር ለጌታ መኖርና እርሱን መከተል ነው።

እኛ ቀድሞውኑም ብርሃንን ተቀብለናል እኛ ቀድሞውኑም ይህንን ብርሃን የሚያስፋፉ ሰዎች ሆነናል በልቦቻችን ውስጥ እንዲህ ያለ አመኔታ ሊኖር ይገባል ይህ እምነት ራሱ ሁሌም ወንጌልን እንድናስፋፋ፣ የጽድቅን ስራ እንድንሰራና በብርሃኑ መሰረት እንድንኖር ያስችለናል ያን ጊዜ ሁሌም በትክክል እንኖራለን ፈጽሞም አንሰናከልም።

ከሌላው ሁሉ በላይ የደህንነትን ብርሃን ስለሰጠን እግዚአብሄርን አመሰግነዋለሁ ምንም እንኳን እኛ ከደህንነት ብርሃን በቀር ሌላ አንዳች ነገር ባንሆንም አሁንም ቢሆን ሁሌም በጌታ ሆነን ሕይወታችንን መኖር እንችላለን በእኛ ውስጥ ምንም መልካም ነገር ስለሌለ ብርሃን ያስፈልገናል እኛ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር በዚህ የደህንነት ብርሃን ማመንና በዚህ ጸጋም ሕይወታችንን መኖር እውነተኛውንም ወንጌል ለሰው ሁሉ ማስፋፋት ነው እኛ በደህንነት ብርሃን ስለምናምን አሁን በእግዚአብሄር ፊት ሁሌም የብርሃንን ሕይወት መኖር እንድንችል ተደርገናል። ✉

ከጨለማ ስልጣን ወደ ልጁ መንግስት

« ዘፍጥረት 1:2-5 »

«ምድረም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ እግዚአብሄርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው።።»

በውሃውና በመንፈሱ በመንፈሱ ወንጌል እውነት ስታምኑ የአእምሮ ውሸንብራችሁ ይጠፋል

እናንተና እኔ ከሐጢያቶች ሁሉ እጅግ ኢምንት የሆነች ሐጢያት ሰርተን ከሆነ በእግዚአብሄር ፊት ለዚህች ሐጢያት ተኮንነን እንሞታለን ያ የእግዚአብሄር ሕግ ነው ነገር ግን እንዲህ ያለውን ኩነኔ ለማራቅ እግዚአብሄር አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ምድር ላከው ከአጥማቂው ዮሐንስም ጥምቀትን እንዲቀበል አደረገ ስለዚህ እግዚአብሄር የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ልጁ በማስተላለፍና እርሱንም በመስቀል ላይ እንዲሰቀል በማድረግ ልጁ ለሰው ሁሉ በይፋ እንዲሞት አደረገ እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተደረጉት ሰው ሁሉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን እንዲድን ነው።።

ኢየሱስ እንዲህ አለ *«እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም*

ነኝ» (ዮሐንስ 14:6) ነገሩ እንዲህ ከሆነ ጌታችን የተናገረው የውሃና የመንፈስ ወንጌል እውነት መሆን አለበት።

እናንተና እኔ በእግዚአብሄር ላይ ሐጢያት በምንሰራበት ጊዜ ሁሉ ብንናዘዘው ይህ ሐጢያት ይቅር የሚባል ይመስላችኋልን? የኑዛዜ ጸሎቶችን በምናቀርብበት ጊዜ ሁሉ ሐጢያቶቻችን እንደሚነጹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው የት ቦታ ነው?

ብዙ ሰዎች 1ኛ ዮሐንስ 1:9ን የንስሐ ትምህርት መሰረት አድርገው ይጠቁሙታል 1ኛ ዮሐንስ 1:9 *«ለሐጢአታችን ብንናዘዝ ሐጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው»* ስለሚል አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ሐጢያቶቻቸውን በሚናዘዙበት ጊዜ ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው እንደነጹ ያምናሉ ነገር ግን እንደዚህ ያለው አተረጓጎም ትልቅ ስህተት ነው።

የዚህ ምንባብ ትክክለኛው ትርጉም በአሁኑ ጊዜ ያለ ማቋረጥ ሐጢያት ብንሰራም ጌታችን ቀድሞውኑም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ የደመሰሰ መሆኑ ነው እነርሱ የ1ኛ ዮሐንስ 1:9ን የመጀመሪያ ሐረግ ብቻ የሚያውቁትና በዚሁ ምንባብ ውስጥ ያሉትን ተከታይ ሐረጎች ችላ የሚሉት ለምንድነው? እዚህ ላይ እግዚአብሄር «የታመነና ጻድቅ ነው» ሲል ምን ማለቱ ነው? እዚህ ላይ እግዚአብሄር «የታመነና ጻድቅ ነው» ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ እናንተና እኔ ሐጢያት እንደምንሰራ ያውቅ ስለነበር ከ2,000 አመታት በፊት በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ ያለፉትን፣ የወደፊቶቹንና የአሁኖቹን ሐጢያቶች በሙሉ አስቀድሞ በመውሰድ ሁሉንም በእውነትና በታማኝነት አንጽቶዋቸዋል መጽሐፍ ቅዱስ በሐጢያቶቻችን ብንናዘዝ እግዚአብሄር ይቅር ሊለን የታመነና ጻድቅ ነው የሚለው ለዚህ

ነው በሌላ አነጋገር በአሁኑ ጊዜ ሐጢያት በመስራት ብንቀጥልና ሐጢያቶቻችንን ብንናዘዝም ጌታችን ቀደም ብሎ ከረጅም ጊዜ በፊት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በወሰደና ሁሉንም በደመሰሳቸው ጊዜ ያኔ ጥንት ሁሉን ነገር አጠናቋል።

ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን አስቀድሞ ዳግም እንደተወለደ ሰው በዚህ ምድር ላይ ሕይወታችንን በመኖር ስንቀጥል ሐጢያት በምንሰራ ጊዜ ሁሉ እምነታችንን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ በማኖር እንደሚከተለው ትክክለኛውን ኑዛዜ ማድረግ አለብን «አባት ሆይ ይህንን ሐጢያት ሰርቻለሁ ሐጢያት ከመስራት በቀር ምንም ማድረግ አልእችልም ነገር ግን አንተ አስቀድመህ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ ይህንንም ሐጢያት እንደደመሰስህ አምናለሁ አሁን የተሰሩት ሐጢያቶቼ በሙሉ እነዚህ ሐጢያቶች አንተ በተጠመቅህና በተሰቀልህ ጊዜ ከረጅም ጊዜ በፊት ተደምስሰዋል አንተ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የአለም ሐጢያቶቼን በሙሉ ያለፉትን ሐጢያቶቼን ብቻ ሳይሆን የአሁኑንና የወደፊት ሐጢያቶቼንም ጭምር አንጽተህ ደምስሰሃል ለሲዖል ታጭቼ ሳለሁ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመቀበሌ ሙሉ በሙሉ አድነኸኛልና አመሰግንሃለሁ ጌታ ሆይ የጽድቅ አገልጋይ ሆኜ እንድኖር የዚህን ጻድቅ ሰው ልብ ጠብቅ ክፉ ነገር ውስጥም እንዳልወድቅ ጠብቀኝ።»

እኛ ከሐጢያቶቻችንና ከግራ መጋባታችን ሁሉ መዳን ከፈለግን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት ማወቅና በእርሱም ማመን አለብን

ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ እውነተኛ የደህንነት ብርሃን ነው

ኢየሱስ ክርስቶስ የታመነ አዳኛችን ነው በውሃውና በደሙ አማካይነትም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በተጨባጭ ደምስሶዋል እርሱ ሐጢያቶቻችንን የደመሰሰው መቼ ነበር? የደመሰሳቸው ከረጅም ጊዜ በፊት ነው አንዳንዶቻችሁ ሐጢያት በምትሰሩበት ጊዜ ሁሉ «ጌታ ሆይ በጣም አዝናለሁ እባክህ ይህንን ሐጢያቴን ይቅር በለኝ» ትሉ ይሆናል ነገር ግን እንዲህ ያለ ኑዛዜ የምትናዘዙት ገና ፍጹም የሆነውን የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ስላልተቀበላችሁ ብቻ ነው በዚህ የሕሊና ኑዛዜ ወደ እግዚአብሄር ስታለቅሱ እውነቱ ግን ጌታ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ለአንዱና ለመጨረሻ የደመሰሰ መሆኑ ነው::

ጌታ የንስሐ ጸሎቶቻችንን ስናቀርብ በየቀኑ ሐጢያቶቻችንን ይቅር የሚል ቢሆን ኖሮ ጌታ ገናም በአብ ቀኝ መቀመጥ ባልቻለም ነበር አሁን እየተናገርን እንኳን በየቀኑ መጠመቅና በየቀኑ ተሰቅሎ መሞት ነበረበት ሐጢያቶቻችሁ በየቀኑ ይቅር እንደሚባል አሁንም ድረስ የምታምኑ ከሆነ እምነታችሁ በመንፈሳዊ ግራ መጋባት የተጨማለቀ ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ የደህንነት ብርሃን ሆኖ ወደዚህ ምድር የመጣው ከሐጢያት አዘቅት ሊያድነን ነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ወደ እኛ በመምጣትም እውነተኛ አዳኛችን ሆንዋል ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው፣ የአለምን ሐጢያቶች በመስቀል ላይ የተሸከመውና የተሰቀለው ለዚህ ነው «ተፈጸመ» በማለትም በመስቀል ላይ ሞተ ዳግመኛ ም ከሙታን ተነሳ ዕብራውያን 10:18 *«የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ሐጢአት ማቅረብ የለም»* እንደሚል ዳግመኛ ለሐጢያት የሚቀርብ ቁርባን እንዳይኖር ስጋውን የዘላለም መስዋዕት አድርጎ በማቅረብ ለአንዱና ለመጨረሻ ፈጽሞ አዳነን ስለዚህ ሁላችሁም በውሃውና

በመንፈሱ ወንጌል እንድታምኑና ከግራ መጋባታችሁ ነጻ እንድትወጡ እጠይቃችኋለሁ የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበል፣ ጻድቃን ሰዎች መሆንና ዳግም መወለድ የምንችለው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት በማወቅና በማመን ነው አሁኑኑ ከውሸቦንብር ነጻ እንድትወጡና ብዙ ሰዎችንም ከግራ መጋባት እንድትታደጉ ሁላችሁንም እመክራለሁ።

ብሉይ ኪዳንም እንደዚሁ የሰው ዘር የሐጢያት ክምሮች እንደሆነ ይናገራል

እግዚአብሄር በኢሳይያስ 59:1-8 ላይ ሁሉም ሰው በእጆቹ፣ በእግሮቹ፣ በከንፈሮቹና በስጋው ሐጢያት እንደሚሰራና ሁሌም ሐጢያትን ለመስራት እንደሚያቅድ በመናገር ስለ ሰው ዘር ሐጢያት ይናገራል እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል።

«እነሆ የእግዚአብሄር እጅ ከማዳን
አላጠረችም ጆሮውም ከመስማት
አልደነቆረችም ነገር ግን በደላችሁ
በእናንተና በአምላካችሁ መካከል
ለይታለች እንዲይሰማም ሐጢአታችሁ
ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል
እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል
ረክሳለች ከንፈራችሁም ሐሰትን
ተናግሮዋል ምላሳችሁም ሐጢአትን
አሰምቶአል በጽድቅ የሚጠራ
በእውነትም የሚፈርድ የለም
በምናምንቴ ነገር ታምነዋል
ሐሰትንም ተናግረዋል ጉዳትንም

ጸንሰዋል በደልንም ወልደዋል
የእባብን ዕንቁላል ቀፈቀፉ
የሸረሪትንም ድር አደሩ
እንቁላላቸውንም የሚበላ ሰው
ይሞታል እንቁላሉም ሲሰበር
እፉኝት ይወጣል ድሮቻቸውም
ልብስ አይሆኑላቸውም በሥራቸውም
አይሸፈኑም ሥራቸውም የበደል ስራ
ነው የግፍም ሥራ በእጃቸው ነው
እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ
ንጹሑን ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ
አሳባቸው የሐጢአት አሳብ ነው
ጉስቁልናና ቅጥቃጤ በመንገዳቸው አለ
የሰላምን መንገድ አያውቁም
በአካሄዳቸውም ፍርድ የለም
መንገዳቸውን አጣመዋል የሚሄድባትም
ሁሉ ሰላምን አያውቅም::»

ኢሳይያስ 59:1-2 እንዲህ ይላል *«እነሆ የእግዚአብሄር እጅ ከማዳን አላጠረችም ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም ነገር ግን በደላችሁ እናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች እንዳይሰማም ሐጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል::»*

እዚህ ላይ ቃሉ ሰዎች ከእግዚአብሄር ጋር መግባባት ያልቻሉበት ብቸኛው ምክንያት ሐጢያቶቻቸው እንደሆኑ ይናገራል ጸሎቶቻችን ወደ እግዚአብሄር ሊደርሱ የማይችሉት በሐጢያቶቻችን ምክንያት ነው እግዚአብሄርም ሊባርከንም ሆነ ወደ ዘላለማዊው መንግስተ ሰማይ እንድንገባ ሊፈቅድልን አይችልም በሌላ አነጋገር ሐጢያቶቻችን ከእግዚአብሄር እያገዱን ስለሆነ እግዚአብሄር ሊረዳን ቢፈልግም ሊረዳን አይችልም::

እግዚአብሄር በዚህ አለም ላይ የሚሰቃዩትንና የሚጨቆኑትን ሰዎች ጸሎቶች ሊመልስና ሊረዳቸው ይፈልጋል ነገር ግን ሰዎች ሐጢያተኞች ስለሆኑ ሊረዳቸው አይችልም አሁንም ገና በልቦቻችሁ ውስጥ ሐጢያት ካለ ምንም ያህል ራሳችሁን ሰጥታችሁ ብትጸልዩም እግዚአብሄር ጸሎቶቻችሁን ሊሰማ አይችልም እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት እንድንቀበል የሚነግረን ለዚህ ነው።

አሁን በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ምን አይነት ሐጢያት እንደምትሰሩ ከቃሉ እንመልከት እዚህ በኢሳይያስ 59:3 ላይ «እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል ረክሳለች» ሲል በእጆቻችን ሐጢያትን እንሰራለን ማለቱ ነው *«እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል ረክሳለች ከንፈራችሁም ሐሰትን ተናግሮዋል ምላሳችሁም ሐጢአትን አሰምቶአል በጽድቅ የሚጠራ በእውነትም የሚፈርድ የለም» (ኢሳይያስ 59:3-4)* ሲል በከንፈሮቻችን ሁሉንም አይነት ሐጢያቶች እንሰራለን ማለቱ ነው።

ኢሳይያስ 59:4-5 እንዲህ በማለት ይቀጥላል *«በምናምንቱ ነገር ታምነዋል ሐሰትንም ተናግረዋል ጉዳትንም ጸንሰዋል በደልንም ወልደዋል የእባብን ዕንቁላል ቀፈቀፉ»* ይህ ምንባብ ከድንጋይና ከእንጨት በተቀረጹ ምስሎች ፊት ፍጹም በሆነ ከንቱነት በመጎንበስ እንዴት ጣዖትን እንደምናመልክ ያሳያል ትንሽ ከተጎዳን፣ ከቆሰልን ወይም ከተሰደብን የመግደል ፍላጎቶች ያሉዋቸው ልቦቻችን ምን ያህል ክፉ እንደሆኑና የእባብን እንቁላል የሚቀፈቅፈውም ልብ በትክክል ይህ እንደሆነ ያሳየናል።

የሰው ተፈጥሮ በባህሪው መልካም ነው ወይስ ክፉ? በምስራቅና በምዕራብ የሚገኙ በርካታ ፈላስፎችና ባለ እውቀቶች ክርክሮቻቸውን በማብራራት አንዳንዶቹ የሰው

ተፈጥሮ መልንም ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ክፉ ነው ብለው ተናግረዋል።

ነገር ግን የእውነት ጌታ የሆነው ኢየሱስ በማርቆስ 7፡21-23 ላይ የሰዎችን ሐጢያተኛ ልቦች እንደሚከተለው አብራርቷል «ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ሰንፍና ናቸው ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል» የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እውነት ነው።

ሁሉም ሰው የተወለደው ከሐጢያት ጋር ነው ሁሉም ሰው ዕድሜውን በሙሉ የሚኖረው ሐጢያትን እየሰራ ነው በዚህ አለም ላይ እንደ ሰው ክፉ የሆነ ሌላ ዘር የለም በቅርቡ *ማሩታ* የሚል ርዕስ ያለው ፊልም በኮርያ ሲታይ ነበር ይህ ፊልም በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት በቻይና ላይ የተፈጸሙትን የጃፓን ጭካኔ የተሞሉ ግድያዎች የሚተርክ ታሪክ ነው ፊልሙ የጃፓን ወታደራዊ ክፍል ለኬሚካልና ለባዮሎጂካል የጦር መሳሪያዎች በሰው አካሎች ላይ በርካታ ሙከራዎችን ማድረጉን ይተርንል በዚህ ፊልም ላይ የጃፓን ጦር ሰራዊት በሕይወት ያሉ የሰው አካሎች በሰውነቶቻቸው ውስጥ ያሉ ውሃዎች ተመጠው አልቀው እስኪሞቱ ድረስ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድባቸው ለማወቅ በመሞከሪያ ክፍል ውስጥ በማስቀመጥ የሰው ሕይወት በተለያዩ የቅዝቃዜ መለኪያዎች ውስጥ ምን ያህል እንደሚቆዩ ለመሞከር ሲሉ በቻይናና በኮርያ ሕዝብ ላይ የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገዋል ለመሞት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድባቸው ለመሞከር ሲሉ የቡቦኒክ መቅሰፍት አምጪ ባክቴርያ ወግተዋቸዋል ስለዚህ የሰው ልብ ቋንቋ ከሚገልጠው በላይ ክፉ ነው ሰዎች በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ምን ያህል ጨካኝና አስፈሪ እንደሆኑ ማየት እንችላለን

በጣም ክፉ ከመሆናቸው የተነሳ በሕይወት ያሉ ሰዎችን የሙከራ መሳሪያዎች የማድረግ አቅም አላቸው ይህ ሁሉ እያንዳንዱ ሰው ፈጽሞ ራስ ወዳድ ልብ ያለው ለመሆኑ ማስረጃ ነው።።

በሰብአዊ ማህበረሰባችን ውስጥ አዘውትረን የምንመለከታቸው ሁለት ነገሮች ፉክክርና ግጭት ናቸው እርስ በርሳቸው ከተጠቃቀሙ በኋላ ዕቅዳቸው ከተጠናቀቀ በኋላ ሌሎችን ለመግደል የማያመነቱ በጣም ጨካኝ ሰዎች አሉ የራስን ኑሮ ከሁሉ በላይ የሚያስቀድመውና ለጥቅሙ ሲል ሌሎችን መስዋዕት ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነው እጅግ ራስ ወዳድ የሆነ ልብ ከሰው የልብ ክፋት የመነጨ ውጤት ነው።።

ሰዎች ምን ያህል ሐጢያቶችን ይሰራሉ? እኛ በእጆቻችን፣ በከንፈሮቻችንና በድርጊቶቻችን በርካታ ሐጢያቶችን እንሰራለን በሐጢያት ስለተወለድን ልናመልጥ የማንችልበት እውነታችን ይህ ነው *ሺንድለርስ ሊስት* በሚለው ፊልም ውስጥ ሺንድለር «ሁኔታዎች በፈቀዱ ጊዜ ሁሉ በሰዎች ልቦች ውስጥ ያለው ክፋት ይፈስሳል» ብሎዋል ስለዚህ ሰዎች በተፈጥሮ እንዲህ ያሉ ክፉ ሐጢያቶችን ይዘው በዚህ አለም ላይ ስለተወለዱ ሐጢያቶቻቸውን ለማፍሰስ ሁኔታዎች እንደተመቻቹላቸው ወዲያውኑ ሁሉም ሐጢያትን ይሰራሉ።።

ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው የሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ በሐይማኖታዊ ሕይወታቸው ለመደበቅ ይሞክራሉ የተገለጡትን ሐጢያቶቻቸውን እንደ መስዋዕት፣ የበጎ ፈቃድ ስራ፣ የብህትውና አኗኗር፣ ጸሎቶችና የወንጌል ስርጭት ጥረቶች ባሉ ነገሮች ለጊዜውም ቢሆን ለመሸፋፈን ይሞክራሉ በኮርያም እንደዚሁ ዘመናቸውን በሙሉ መስዋዕትነት በመክፈል የቀደሱ ብዙ ሰዎች ስላሉ ሕያዋን ቅዱሳን ተብለው ተጠርተዋል እነርሱ ሕሙማንን ሊፈውሱ፣

ቁሳዊ ሐብቶቻቸውን ከሌሎች ጋር ሊካፈሉ፣ የመስተንግዶ አገልግሎቶችን ሊያቀርቡና በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ለተገፉት ሰዎች ስጋዊ ሕይወት ጥቅሞችን ሊያመጡ ይችሉ ይሆናል ነገር ግን እነዚህን ሰዎች ከሐጢያት ሊታደጉዋቸውና ጻድቃን አድርገው ሊለውጡዋቸው አይችሉም ምክንያቱም እግዚአብሄር የሰውን ፊት አያይም እርሱ የሚመለከተው ልብን ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የሰዎችን ልቦች ማዕከል ሲመለከት መርዛማ በሆኑ ሐጢያቶች እንደተሞሉና ክፋትን እንደሚያደርጉ ይመለከታል እግዚአብሄር ይህንን ለማየት አጉሊ መነጽር አያስፈልገውም ምክንያቱም የፈጠረን እርሱ ነው ስለዚህ ስለ እኛ ሁሉንም ያውቃል።

አጋር ምዕመናኖቼ የሰው ልብ ምን ያህል እንደነደነ ታውቃላችሁን? ደካማ የሆኑ ሰዎችን መናቅ የሰው ተፈጥሮ ነው በመልኑም ምግባሮቻቸው በአለም ሁሉ የታወቁ ሰዎችን ስንመለከት ወይም የሰለጠኑትንና በከፍተኛ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ የሆኑ አገሮችን ስንመለከት ባህሪዎቻቸው ይበልጥ ሐይለኛ እንደሆኑ ማየት እንችላለን በጥንት ዘመን ታላላቅ መንግስታት ያለ ምንም ማመንታት ደካሞቹንና ትናንሽ የሆኑትን አገሮች መውረርና መዝረፍ ልማዳቸው ነበር።

ለምሳሌ ያህል ታላቋ ብሪታንያ ሆንግ ኮንግን ቅኝ ግዛቷ ባደረገች ጊዜ ቻይናን በአደንዛዥ ዕጽ አላደከመቻትምን? ሰው ሁሉ ለራሱ ጥቅም ሲል ከመጠን በላይ ጨካኝ ይሆናል የሰዎች ሁሉ እውነተኛው ስዕል ይህ ነው።

ሰዎች በጣም ጨካኞች ስለሆኑ ሌሎች ሰዎችን መግደል ቢያስፈልጋቸው እንኳን ሌላውን አገር ወርረው መሬቱን የራሳቸው አድርገው ለመውሰድ ፈቃደኞች ናቸው ሰዎች በተፈጥሮዋቸው እንደዚህ ናቸው ራሱ የሰው ዘር እንዲህ ያለ ክፉ ዘር ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን *«የክፉ አድራጊዎች ዘር»*

(ኢሳይያስ 1:4) በማለት ሐጢያተኞች አድርጎ የገለጣቸው ለዚህ ነው ኢሳይያስ 59:7ም እንዲህ ይላል «*እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ ንጹሑን ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ አሳባቸው የሐጢአት አሳብ ነው ጉስቁልናና ቅጥቃጤ በመንገዳቸው አለ*» በማለት የሰውን ዘር ሐጢያተኛ ተፈጥሮ በግልጽ የሚጠቁመው ለዚህ ነው ሰው ሁሉ በአሳብና በምግባር እንደዚህ ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው «ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ» «ክፉ አሳብ፣ ምንዝርና፣ ዝሙት፣ መግደል፣ ስርቆት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና» ብቻ ነው አጋር ምዕመናኖቼ እነዚህን ሐጢያቶች እያንዳንዳቸውን በጣቶቻችሁ ቁጠሩዋቸውና እነዚህ ክፉ ነገሮች በልቦቻችሁ ውስጥ እንዳሉ ወይም እንደሌሉ ራሳችሁን ጠይቁ በእግዚአብሄር ፊት እውነተኞች ከሆናችሁ ልቦቻችሁ እነዚህን ሁሉ በደሎች እንደያዙ ታምናላችሁ::

ይህ ሆኖ እያለ ሰዎች ሁሉ በልቦቻቸው ውስጥ እነዚህ ሐጢያቶች ቢኖሩባቸውም ሐጢያቶቻቸውን አያውቁም እግዚአብሄር ለእነዚህ ሰዎች እንዲህ ይላቸዋል «ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ» በሌላ አነጋገር በልቦቻቸው ውስጥ ሁሉም አይነት ሐጢያቶች ቢኖሩም ሰዎች በእርግጥ ማን እንደሆኑ አይገነዘቡም በርካታ ሰዎችም ያን ያህል ክፉ እንዳልሆኑ በማሰብ ተታልለዋል እኛ የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበል ከፈለግን በመጀመሪያ እውነተኛውን ማንነታችንን መገንዘብ አለብን ችግሩ ግን ይህንን አለመገንዘባችን ነው ሰው በጣም ክፉ ስለሆነ ለሲዖል የታጨ ስለመሆኑ ራሱን የማያውቅ ከሆነ ተራ የሆነ ግብዝ ሐይማኖተኛ ከመሆን ማምለጥ አይችልም ብዙ ፈሪሳውያን የደህንነትን ጸጋ መቀበል የተሳናቸው እውነተኛ ማንነታቸውን ባለመገንዘባቸውና ይህንን ለመቀበል እምቢተኞች በመሆናቸው ነው::

እግዚአብሄር ልቦቻችንን በእውነት ብርሃን ማብራት የነበረበት ለዚህ ነው በሌላ አነጋገር የሐጢያቶቻችንን ስርየት የመቀበሉን አስፈላጊነት መገንዘብ የምንችለው እግዚአብሄር ምን አይነት ሐጢያት እንዳለብንና ምን አይነት ሐጢያት እንደምንሰራ ሲያስተምረን ብቻ ነው እግዚአብሄር ስለ ሰዎች ሐጢያቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጻፈበት ምክንያት ይህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ቃል በማመን ከሐጢያት እንድንድን የሚያስችለን የደህንነት መጽሐፍ ቢሆንም በሌላ በኩል ራሳችንን ማየት የሚያስችለንም መስታወት ነው።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰው ልብ ውስጥ ክፉ አሳቦች እንደሚወጡ አስቀድሞ ተናግሮዋል በሌላ አነጋገር በልቦቻችን ውስጥ ክፉ አሳቦች አሉ ክፉ አሳቦች አሉባችሁ ወይስ የሉባችሁም? በእርግጥም አሉባችሁ የተበላሹ ምኞቶች አሉባችሁ ወይስ የሉባችሁም? እንዳሉባችሁ የታወቀ ነው ለመስረቅ የሚያነሳሱዋችሁ የስስት ፍላጎቶች አሉባችሁ ወይስ የሉባችሁም? እንዳሉባችሁ የታወቀ ነው የመግደል ፍላጎቶች አሉዋችሁ ወይስ የሉዋችሁም? እንዳሉዋችሁ የታወቀ ነው የማመንዘር ፍላጎት አላችሁ ወይስ የላችሁም? እንዳላችሁ የታወቀ ነው ልቦቻችሁ ስስታሞች አይደሉምን? በእርግጥም ናቸው ልቦቻችሁ ክፉ፣ ተንኮለኛና ተዳሪዎች አይደሉምን? በእርግጥም ናቸው በልቦቻችሁ ውስጥ ምቀኝነት፣ ትዕቢት፣ ስድብና ስንፍና አለ? በእርግጥም አለ እነዚህ ሁሉ ሐጢያተኛ ምኞቶች በእናንተ ልቦችና በእኔ ልብ ውስጥ፣ በዚህ ምድር ላይ በሚኖር በእያንዳንዱ ሰው በወንዶችና በሴቶች፣ በወጣቱና በሽማግሌው፣ በሐብታሙና በደሃው ልብ ውስጥ በጽናት ተተክለዋል።

ሆኖም ሰው ሁሉ በልቡ ውስጥ እነዚህ ሐጢያቶች እንዳሉበት አያውቅም እግዚአብሄር በእውነት ብርሃን ደህንነትን

በሰዎች ላይ ከማብራቱ በፊት የራሳቸውን እውነተኛ ማንነት እንኳን የሚያውቁበት መንገድ የለም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ከማወቃችን በፊት ብዙም እንዳልተበላሸን እናስባለን «አንዳች ትልቅ የሆነ ሐጢያት ሰርቼ አላውቅም ፈጽሞ ከማንም ሰው አንዳች ነገር አልሰረቅሁም አንዳች ትላልቅ መተላለፎችን አልሰራሁም መልካም ሰው ሆኜ ኖራለሁ» ይላሉ::

እግዚአብሄር ግን እንዲህ ይለናል «እናንተ ነፍሰ ገዳዮች፣ ሌቦች፣ አመንዝራ ሰዎች ናችሁ እናንተ የመጎምጀት፣ የክፋት፣ የመዳራት፣ የምቀኝነት፣ የመለያየት፣ የትዕቢትና የስንፍና ሐጢያቶችን የሰራችሁ ሰዎች ናችሁ» ያን ጊዜ ሰዎች «መቼ ገደልሁ ማንን ገደልሁ? እኔ በጭራሽ ማንንም አልገደልሁም የተዳራሁትስ እንዴት ነው? የሚዳሩት መሸታ ቤቶችን የሚያዘወትሩ ሰዎች እንጂ እኔ አይደለሁም እኔ በጭራሽ እንዲህ ያለ ቦታ ተገኝቼ አላውቅም ታዲያ እንዴት ተዳራህ ትለኛለህ? እንዴት እንዲህ ትሰድበኛለህ?» ይላሉ::

ሰዎች እውነተኛ ሐጢያቶቻቸውን የማይገነዘቡ ብቻ ሳይሆኑ እውነተኛውን ክፉ ማንነታቸውንም ፈጽመው አያውቁትም ከየት እንደመጡና ወዴት እንደሚገሰግሱ፣ ለምን እንደሚኖሩና ወዴት እንደሚሄዱ አያውቁም የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎችና የእግዚአብሄርን ጸጋ ያልተቀበሉ ሰዎች የመጨረሻ መዳረሻቸው ምን እንደሆነም አያውቁም::

ሰው በመጨረሻ ሐጢያቶቹን በግልጽ መረዳት የሚችለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ፍቅር የመጣውን አምላክ ሲያውቅ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሆዋን መፍራት የጥበብ መሰረት እንደሆነ ይናገራል በሌላ አነጋገር ራሱን ማወቅ፣ ወዴት እንደሚገሰግስ መገንዘብ፣ ሐጢያቶቹን ማወቅና እግዚአብሄር ለአለም ሁሉ ያለውን ዕቅዶቹን በሙሉ መረዳት የሚችለው እግዚአብሄርን ከልቡ የሚፈራ ሰው ነው ይህ እናንተንና እኔንም

ይመለከታል እግዚአብሄር እኛ ሰዎች ሁላችንም ክፉ አሳቦች እንዳሉን ቢናገርም እኛ ግን «ምን ክፉ አሳቦች አሉብኝ? እኔ በጭራሽ ምን ክፉ አሳቦች የሉብኝም!» ብለው በማሰብ ተታልለዋል።

የእግዚአብሄር ቃል እንዲህ ስለሚናገር ሐጢያተኝነታችንን ከማመን በስተቀር ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም እኛ በእግዚአብሄር ቃል ፊት ሐጢያተኞች መሆናችንን ለማመን የተገደድነው የእግዚአብሄር ቃል እውነት ስለሆነ ነው ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን ተአማኒነት ካልተቀበለ በማርቆስ 7:21-23 ላይ እንደተተቆመው እንዲህ ያሉ ክፉ ነገሮች እንዳሉበት አይቀበልም።

ለምሳሌ ያህል ሞት ወይም እድሜ ልክ የተፈረደባቸውን ወንጀለኞች ብትገናኙ በሁኔታዎቻቸው ምክንያት ትንሽ ስህተት እንዲሰሩ መገደዳቸውንና ጥፋተኞችም እንዳልሆኑ ሊነግሩዋችሁ ይችላሉ ስለዚህ አብዛኞቹ ወንጀለኞች የታሰሩት በአርባ ቀን ዕድላቸው ምክንያት እንደሆነ በመናገር ንጽህናቸውን ያጸድቃሉ።

ስለዚህ ሰዎች ሐጢያቶቻቸውን ፈጽመው አያውቁም እናንተና እኔ የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከመቀበላችን በፊት እንዲህ ያለን ክፉ ዘር የነበርን የመሆናችንን እውነታ ፈጽሞ አናውቅም ነበር እኔም ብሆን ባለፉት ጊዜያት ብዙ አስከፊ ነገሮችን አድርጌአለሁ ነገር ግን በውስጤ ወፈፌ የሆነ አእምሮ እንዳለኝ አላውቅም ነበር በሌላ አነጋገር በልቤ ጥልቅ ውስጥ እነዚህ ሐጢያቶች ነበሩ ውጫዊው ገጽታዬ ግን እነርሱን አልገለጣቸውም አልፎ አልፎ አንዳንድ የእብድ ውሳኔ እወስናለሁ አስከፊ ነገርንም አደርጋለሁ ከዚያ በኋላ ግን በሁኔታዎች አማካኝለሁ ራሴን አሰቃያለሁ ባደረግሁት ነገርም እተክዛለሁ።

ከዚያም በልቤ ራሴን ለማጽናናት እሞክራለሁ ተፈጥሮአዊ የሆኑት ሐጢያተኛ ፍላጎቶቼ በሚገለጡበት ጊዜ ሁሉ እንዲህ ያሉ ክፉ ምግባሮችን ፈጽሜአለሁ ይህ ሆኖ ሳለ በእርግጥ እንደዚህ ባደርግና ሰውን እስኪሞት ድረስ ብደበድብም ራሴን እንደ ነፍሰ ገዳይ አስቤው አላውቅም «ሰውን እስከ ሞት ድረስ የወጋሁት መቼ ነው?» እኔ በገሃድ ፈጽሞ ማንንም ገድዬ ስለማላውቅ ሁሌም ራሴን ንጹህ አድርጌ ጨዋ ሰው እንደሆንሁ እቆጥር ነበር።

የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ከማወቁ በፊት ራሴን ጨዋ «ክሐጢያት» በጣም የራቀ ሰው አድርጌ አስብ ነበር እኔም ብሆን ስለ ራሴ ፈጽሞ መሃይም ነበርሁ ምናልባት እናንተም ደግሞ ልክ እንደ እኔ ነበራችሁ ልጅ በነበርሁ ጊዜ ኮረዳ ልጃገረዶችን ሁሉ መልአክ እንደሆኑ አድርጌ አስብ ነበር ነጭ ቀሚሶችን የለበሱ ሴት መነኮሳትን ወይም ነርሶችን ባየሁ ጊዜ ሁሉ እነርሱም ደግሞ መላዕክቶች ናቸው ብዬ አስብ ነበር ነገር ግን ከጎረመስሁ በኋላ ቆንጆ ሴቶችን ባየሁ ጊዜ ሁሉ የብልግና ፍላጎቶችን የተሞሉ የመዳራት አሳቦች በውስጤ እንደ ነበልባል መንደድ ጀመረ ስለዚህ እንደ እኔ ያለ የረከሰ ሰው ከምድረ ገጽ መጥፋት እንዳለበት ስላመንሁ ተስፋ ቆረጥሁ ከጉርምስና ወደ ጉልምስና ስሻገር በመጨረሻ ሰዎች ሁሉ ግብዞች እንደሆኑና ሁሉም ሰው ተመሳሳይ እንደሆነ ተረዳሁ በሌላ አነጋገር ሰው ሁሉ ፈጽሞ ራሱን ስለማያውቅ ሕይወቱን በከንቱ እያባከነ ነው።

እግዚአብሄር «እናንተ ሌቦች ናችሁ» ብሎ የነገረን አንዳች ነገር ከመስረቃችን በፊት በልባችን ውስጥ ያለውን የመስረቅ ፍላጎት ስለተመለከተ ነው «እናንተ ነፍሰ ገዳዮች ናችሁ እናንተ ዕብሪተኞች ናችሁ እናንተ ወፈፌ ናችሁ» ይለናል እንደ እውነቱ ከሆነ የሌላውን ሰው ሐብት የማይመኝ ሰው አለ? ማንም የለም

እዚህ ላይ ዋናው ጉዳይ ሰው የሆነ ነገር ይሰርቃል ወይስ አይሰርቅም የሚለው ሳይሆን ሰው ሁሉ በተፈጥሮው ሐጢያተኛ ልብ ስላለው ሁኔታዎች በፈቀዱለት ጊዜ ሁሉ ፍላጎቶቹን የሚተገብራቸው መሆኑ ነው።

አበቦችን በምንተክልበት ጊዜ ወዲያውኑ መሬት ላይ አንተክላቸውም ነገር ግን በመጀመሪያ ዘሮችን እንተክላለን ውሃ እናጠጣቸዋለን እንዲበቅሉና እንዲያብቡም እናደርጋቸዋለን ልክ እንደዚሁ የሐጢያት ምግባሮችን የምናደርገው በልቦቻችን ውስጥ የሐጢያት ዘሮች ስላሉ ነው በሌላ አነጋገር በልቦቻችን ውስጥ አስራ ሁለት የሐጢያት ዘሮች አሉ ስለዚህ አንዱ ዘር ዛሬ ይበቅላል ሌላው ዘር ነገ ይበቅላል ሁኔታዎች በሚፈቅዱበት ጊዜ ሁሉ እነዚህ አስራ ሁለት ዘሮች በልቦቻችን ውስጥ መብቀላቸውን ማደጋቸውንና ማበባቸውን ይቀጥላሉ በሌላ አነጋገር እንተገብራቸዋለን ጨለማም በምድር ላይ ነበረ ማለት በሰዎች ልቦች ውስጥ ጠልቀው የተደበቁ ሐጢያቶች ስላሉ እነርሱ በጥረቶቻቸው አያውቁዋቸውም ማለት ነው።

ጨለማ የሚያመላክተው ሐጢያትን ነው በሰዎች ልቦች ውስጥ ሐጢያት አለ ማለት ነው እግዚአብሄር የሚለው ያንን ነው አጋር ምዕመናኖቼ ይህንን ልትቀበሉት ትችላላችሁን? እኛ እነዚህን በድርጊታችን አልሰራናቸው ይሆናል እግዚአብሄር ግን አሁንም እነዚህ ሐጢያቶች እንዳሉብን ይነግረናል ይህንን እውነት ትቀበላላችሁን? እውነቱ ሰው ሁሉ እንደዚህ መሆኑ ነው ለምሳሌ ያህል የዚህ ዘመን የታወቀች ቅዱስ ሰው እንደሆነች የምትቆጠረው ማዘር ቴሩዛ እንዲህ አልነበረችምን? ሌሎችን ብትረዳም ልብዋ ከማናቸውም የብልሹነት፣ የመግደል፣ የምንዝርናና የመጎምጀት ምኞቶች ሙሉ በሙሉ ነጻ ነበር? እርስዋ በእርግጥ ከእነዚህ የሐጢያት ምኞቶች ሙሉ በሙሉ ነጻ ወጥታ ቢሆን ኖሮ ወይ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋሽቷል ወይም

ማዘር ቴሬሳ «ሰብአዊ ፍጡር» አልነበረችም ነገር ግን ማዘር ቴሬሳም ሰው ስለነበረችና የኢየሱስ ክርስቶስም ቃል አንዲት ነጥብ እንኳን ስህተት የሌለበት ፍጹም እውነት ስለሆነ እርስዋ በጭራሽ ፍጹም አልነበረችም።

በክርስትና ታሪክ ውስጥ በይፋ የታወጀውን የዘመኑን ሐይማኖታዊ ትክክለኝነት በመቃወማቸው ብቻ በርካታ ሰዎች የተገደሉባቸው ፍጅቶች ምን ያህል ናቸው? ክርስቲያኖች በመካከለኛው ዘመን በርካታ ሰዎችን አርደዋል ይህ ለምን ሆነ? ሐይማኖታዊ ስልጣናቸውን ስለተቃወሙ ብዙ ሰዎችን ያለ ርህራሄ የገደሉት በልቦቻቸው ውስጥ የመግደል ፍላጎቶች ስለነበሩ ነው።

እንዲያውም የሐይማኖቶች ሁሉ ክልል የረከሰ ነው ዳግም ያልተወለደ የእያንዳንዱ ሐይማኖተኛ ሕግ አጥባቂ ሕይወት ልክ እንደ ተበላሸና እንደበሰበሰ አሳ ነው ስለዚህ በክርስትናም ውስጥ እንኳን ሰው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ካልተወለደ ይህ ሰው ለሌሎች እውነተኛ መሰጠትን ቢያሳይ እንኳን እግዚአብሄር በግልጽ «አንተ የሐጢያት ክምርና ሐጢያተኛ ነህ በኢየሱስ ክርስቶስ እስካላመንህ፣ ብርሃንን እስካልተቀበልህና የሐጢያቶችህን ስርየት እስካላገኘህ ድረስ ሲያል ትጣላለህ መጋቢ፣ ሽማግሌ ወይም ዲያቆን ብትሆንም እንኳን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ዳግም እስካልተወለድህ ድረስ ወደ ሲያል ትጣላለህ።»

ስለዚህ ሰው ለእግዚአብሄር ቃል መማረክ አለበት ይህ ሆኖ እያለ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት ችላ የሚሉ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ላይ እየተጓዙ ነው በሌላ አነጋገር በራሳቸው ሐይማኖታዊ ሕይወት በምግባሮቻቸው ልቀት ላይ ለመድረስና አካሎቻቸውን ለመግራት በመሞከር ከሐጢያቶቻቸው ለመንጻት ይሞክራሉ ነገር ግን ሐጢያተኛ

የሆነውን ማንነታቸውን ለማያውቁ ሰዎች ጌታ *«የሰላምን መንገድ አያውቁም በአካሄዳቸውም ፍርድ የለም መንገዳቸውን አጣምመዋል የሚሄድባትም ሁሉ ሰላምን አያውቅም» (ኢሳይያስ 59:8)* ይላል::

መጽሐፍ ቅዱስ *«ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው» (ምሳሌ 16:25)* በማለት ይህንን ግልጽ አድርጎታል ብዙ ሰዎች «መልካም ሕይወት ብኖር ሰማይ መግባት እችላለሁ» ብለው ያምናሉ ስለዚህ በራሳቸው ምናባዊ አስተሳሰቦች መሰረት የሐይማኖት ሕይወታቸውን ይኖራሉ ነገር ግን እግዚአብሄር እነዚህ ሰዎች ያለ ምንም አድልዎ እንደሚጠፉ ይናገራል እነዚህ ሰዎች ለሌሎች መልካም ቢሆኑና በድርጊቶቻቸውም ትጉህ ቢሆኑ አንድ ቀን ሰማይ እንደሚገቡ ምንም ያህል በራሳቸው አስተሳሰቦች ቢያምኑም መጨረሻቸው ጥፋት እንጂ ሌላ ምንም ቢሆንም እንዲህ የሚያስቡት የሰላምን መንገድ ስለማያውቁ ነው::

ሕግ አጥባቂዎች የሰላምን መንገድ ስለማያውቁ ሰዎችን ወደ ውሸንብር እየነዱዋቸው ነው

ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች በሳሎናቸው ውስጥ የተሰቀሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ስዕሎችና መስቀል አላቸው ጥሩ መስሎ በሚታያቸው በማንኛውም መንገድ ቢያምኑ ሰማይ እንደሚሄዱ ያስባሉ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚምኑት የሰላምን መንገድ ሳያውቁ ነው ሰማይ ለመግባት ማንኛውም ሰው በመጀመሪያ የሐጢያት ስርየትን መቀበል አለበት::

ጌታችን «ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም

ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ» ሲል ሰዎች ብዙ ሐጢያቶች ቢኖሩባቸውም ሐጢያቶቻቸውን አልተገነዘቡም ማለቱ ነው ነገር ግን በማርቆስ 7፡21 ውስጥ በሚገኘው ምንባብ አማካይነት በልቦቻችን ውስጥ አስራ ሁለት ሐጢያቶችን እንደያዝን፣ ሁላችንም እነዚህን ሐጢያቶች እንደምንተገብራቸውና በሕይወት ዘመናችን ሁሉ እነርሱን በመስራት እንደምንቀጥል ተረድተናል።

እያንዳንዳችን በስጋችን ሐጢያትን እንሰራለን በዚህ ጉዳይ ላይ ምርጫ የለንም ሰው ምንም ያህል መልካምና ጥሩ ቢሆን ይህ ሰው አሁንም ሐጢያትን ይሰራል ምክንያቱም በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንዳለ የተረጋገጠ ነውና።

ሁላችንም በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያትን እንሰራለን በድርጊቶቻችሁ ሐጢያት ባትሰሩም በልቦቻችሁ ግን አሁንም ሐጢያትን እየሰራችሁ ነው እዚህ ላይ በሆነ ድርጊት ወይም ምግባር አንድ የተለየ ሐጢያት ሰርታችኋል ማለቴ አይደለም እያልሁ ያለሁት እናንተና እኔ በተፈጥሮዋችን በልቦቻችን ውስጥ ያስቀመጥናቸው እነዚህ ሐጢያቶች አሉ ሁኔታዎች አመቺ በሚሆኑበት ጊዜ ሁላችንም በአስተሳሰቦቻችን፣ በቃሎቻችንና በምግባሮቻችን እንሰራቸዋለን ነው አሁን እኛ በተጻፈው የእግዚአብሄር ቃል አማካይነት ሁላችንም እንዴት ታላላቅ ሐጢያተኞች እንደሆንን ወደ መረዳት ደርሰናል መጽሐፍ ቅዱስ «ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ» ሲል ይህ የሚያመላክተው ከተወለድንበት ቀን ጀምሮ እስከምንሞትበት ቀን ድረስ በእግዚአብሄርም ፊት እስከምንቆም ድረስ እነዚህን ሐጢያቶች እንደሰራንና በመስራትም እንደምንቀጥል ነው አጋር ምዕመናኖቼ ይህንን ቃል በልቦቻችሁ ትቀበላላችሁን?

አሁን ወደ ዮሐንስ 8፡1-11 እንመለስ።

«ኢየሱስም ወደ ደብረ ዘይት ሄደ ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ ተቀምጦም

ያስተምራቸው ነበር ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርስዋን አቁመው መምህር ሆይ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን አንተ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በምድር ላይ ጻፈ መላልሰውም በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ ከእናንተ ሐጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው ደግሞም ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ እነርሱም ይህንን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ አንቺ ሴት እነዚያ ከሳሾችስ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት እርስዋም ጌታ ሆይ አንድ ሰንኳ አለች ኢየሱስም እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ሐጢአት አትሥሪ አላት::»

እዚህ በዮሐንስ 8:11 ላይ ኢየሱስ እጅ ከፍንጅ በምንዝር የተያዘችውን ሴት «እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ደግመሽ ሐጢአት አትስሪ» አላት ይህች ሴት የተያዘችው ከወንድ ጋር በማመንዘርዋ ነው ይህ መተላለፍ ከአስርቱ ትዕዛዛት ስለጣሰ እንዲህ ያለ ሰው ምስክሮች ከመሰከሩበት በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል ሕጉ ያዛል ታዲያ ጌታ በሐጢያትዋ እጅ ከፍንጅ ለተያዘችው ሴት እንዴት «እኔም አልፈርድብሽም» ሊላት ቻለ?

ይህች ሴት የተያዘችው በፈሪሳውያንና በጸሐፍቶች ነበር ጸሐፍቶች የችሎት ሹሞች ነበሩ በሌላ አነጋገር እነርሱ የመንግስት ሹመኞች ነበሩ በሌላ በኩል ፈሪሳውያን የዘመኑ የሐይማኖት መሪዎች የሕጉም አስተማሪዎች ነበሩ ሴቲቱ ሕጉን ስለጣሰች ከመሞት በስተቀር ከኩነኔ የምታመልጥበት

ምንም መንገድ እንደሌላት እነዚህ ሁለት ቡድኖች አምነዋል ሴቲቱን ስታመነዝር እጅ ከፍንጅ ስለያዙዋት እንደ ውሻ እየጎተቱ በኢየሱስ ክርስቶስ እግር ፊት ወረወሩዋት በዚያን ጊዜ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በአይኖቻቸው እሾህ የሆነባቸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሴቲቱ ጋር አብረው ይገድሉት ዘንድ ሊያስቆጡት እየሞከሩ ነበር።

«የሙሴ ሕግ በምንዝር የተያዘችውን ይህችን ሴት እንድንወግራት ያዘናል አንተ ግን ይህችን ሴት ምን ታደርጋታለህ?» በማለት ኢየሱስ ክርስቶስን አዋከቡት ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሌም ስለ ፍቅር ይናገር ስለነበር ኢየሱስ ክርስቶስን በሕጉ ሊፈትኑት እየሞከሩ ነበር በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ በጣቱ በመሬት ላይ መጻፍ ጀመረ ከዚያም «ከእናንተ ሐጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት» አላቸው።

በወቅቱ ሴቲቱ በሕጉ መሰረት ከመሞት ማምለጥ የማትችል ሰው ነበረች ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያት የሌለባቸው ሰዎች እንዲወግሩዋት በነገራቸው ጊዜ ሕዝቡ ይህንን ሰምተው «ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞቹ አንድ አንድ እያሉ ወጡ» ስለዚህ ሴቲቱን የኮነንዋት ብዙዎቹ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው አንድ ንግግር ጥለዋት ሄዱ በእግዚአብሄር ፊት ሁሉም እንደዚህ ነው።

አሁን የእግዚአብሄር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦዋል

አጋር ምዕመናኖቼ በዚህ አለም ላይ ሕጉን ፍጹም አድርጎ መጠበቅ የሚችል ማነው? ሕጉ የሚያመላክተው ምን ማድረግ እንደሚገባቸውና ምን ማድረግ እንደማይገባቸው የተደነገገውንና

እግዚአብሄር ለእስራኤል ሕዝብ የሰጠውን 613 ትዕዛዛት በሙሉ ነው በጥቅል አነጋገር ሕጉ በቀን ተቀን ሕይወት ውስጥ ሊጠበቁ የሚገባቸው አስር ዋና ዋና ትዕዛዛት እንደዚሁም ሌሎች ትዕዛዛት አሉት ነገር ግን እኛ እዚህ ላይ በግልጽ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ቢኖር በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሄርን ሕግ በሙሉ መጠበቅ የሚችል ሰው እንደሌለ ነው በእግዚአብሄር ሕግ ስርአቶች መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ ሴቲቱንና የእርስዋን ከሳሾች መግደል ነበረበት ነገር ግን ከፍቅር ሕግ አንጻር ሲታይ ሴቲቱን ማዳን ነበረበት ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አዳኝ መሆኑን መናገሩ እውነት ነው በቃሉም ሴቲቱን አድኖ ከሳሾችዋን አባረራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ «ከእናንተ ሐጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት» ማለቱን ሲሰሙ ከሽማግሌው ጀምሮ እስከ ልጁ ድረስ ሁሉም ሕሊናቸውን ወቀሳቸውና ከዚያ ሄዱ።

በእግዚአብሄር ሕግ ፊት ስንቆም ከመካከላችን ያለ አንዳች ሐፍረት ራሱን ቀና አድርጎ መቆም የሚችል ማነው? እግዚአብሄር ሕጉን በሙሉ መጠበቅ እንደማንችል አሳምሮ ያውቃል ሕጉን የደነገገውና ለእኛ የሰጠን ያድነን ዘንድ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሴቲቱን እንዲህ አላት «እኔም ሐጢያት አለብሽ አልልም» «እኔም አልፈርድብሽም አንቺ ሴት ተነስተሽ ቁሚ ዚጂ ደግመሽ ሐጢአት አትስሪ።»

ጌታችን እንዲህ ማለት የቻለው እንዴት ነው? ሴቲቱ እጅ ከፍንጅ ስታመነዝር መያዝዋና በእርግጠኝነትም ሐጢያት መስራትዋ እውነት ከሆነ ይህ ማለት ሐጢያትዋ ከፍቅር የተነሳ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ተሸፍኖላታል ማለት ነውን? እንደምናውቀው እግዚአብሄር እንዲህ ያለ ፍርደ ገምድል አምላክ አይደለም ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አንደዚያ ማለት ቻለ?

ያ የሆነበት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘር ወኪል ከሆነው ከአጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት የዚህችን ሴት ሐጢያት ጨምሮ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ አስቀድሞ ስለወሰደ ነው ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የዚህችን ሴት ሐጢያት ብቻ ሳይሆን የእኛን ሐጢያቶችና ሰዎች ባለፉት ጊዜ የሰሩዋቸውንና ወደፊት የሚሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ስለወሰደ ሴቲቱን ሐጢያት የለብሽም አላት በሌላ አነጋገር ጌታ ሴቲቱን «እንማይፈርድባት» የነገራት ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ አስቀድሞ የአለም ሐጢያቶችን ስለወሰደ ነበር።

ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህችን ሴት ሐጢያት በትክክል የወሰደው እንዴት ነው? መልሱን ለማግኘት ወደ ማቴዎስ 3:13-17 እንመለስ።

«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሄርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።»

እዚህ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ አጥማቂው ዮሐንስ በሚባል ሰው እንደተጠመቀ እናያለን መጀመሪያ ላይ ግን አጥማቂው ዮሐኝስ ኢየሱስን ለማጥመቅ አሻፈረኝ አለ «የለም! እኔ በአንተ ልጠመቅ የሚገባኝ ሆኜ ሳለሁ የእግዚአብሄር ልጅ የሆንከውን አንተን እንዴት አጠምቃለሁ?» ማለቱ ነበር።

ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ*

ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና» በማለት አጥማቂውን ዮሐንስን ሲያዘው መመልከት እንችላለን በዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ የእያንዳንዱን ሰው ሐጢያቶች ለመደምሰስ መጠመቅ እንደሚገባው መናገሩ ነበር ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በራሱ ላይ በመጫን በውሃው ውስጥ በማጥለምና ከውሃው ውስጥ በማውጣት ኢየሱስ ክርስቶስን አጠመቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላም የሰማይ በሮች ተከፈቱ እግዚአብሄር አብም «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» አለ።

«ጽድቅን ሁሉ» ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዱን ሰው ሐጢያት አልባ ለማድረግና ሁሉንም ሰማይ ለመውሰድ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል ማለት ነው ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ሐጢያት አልባ የሚያደርገውን ይህንን የጽድቅ ስራ ለመስራት ምን ማድረግ ነበረበት? በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቀቂው ዮሐንስ የተቀበለው ጥምቀት «መታጠብ፣ መቀበር፣ ማስተላለፍ ወይም ማሻገር» ማለት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዱና ለመጨረሻ ስለወሰደ በመስቀል ላይ ተሸከማቸው ተሰቅሎም ሞተ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ ነው እርሱ ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር የፈጠረ ፈጣሪ ነው እርሱ እናንተንና እኔን ከሐጢያቶቻችን ያዳነ አዳኝ ነው ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ከፍንጅ በምንዝር ከተያዘች ሴት ጋር ተገናኘ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህችን ሴት ሐጢያት አስቀድሞ ወሰደ ምክንያቱም እርስዋ በዚህ አለም ላይ ስትኖር ሐጢያት እንደምትሰራና እንደምታመነዝር አስቀድሞ ያውቅ ነበር።

የኢየሱስ ዘላለማዊ መስዋዕትነት በዘሌዋውያን ውስጥ ተገልጦዋል::

ዘሌዋውያን ምዕራፍ 16 «በስርየት ቀን» የሚሆኑትን ድንጋጌዎች ያብራራል አሮን የእስራኤል ሕዝብ ከአመታዊ ሐጢያቶቻቸው እንዲነጹ የሚያግዛቸው በዚህ ጊዜ ነበር::

በዘሌዋውያን 16:21-22 ላይ እንዲህ ይላል *«አሮንም ሁለቱን እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤልን ልጆች በደል ሁሉ፣ መተላለፋቸውንም ሁሉ፣ ሐጢአታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል በተዘጋጀው ሰውም እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰድደዋል ፍየሉም ሐጢአታቸውን ሁሉ ወደ በረሃ ይሸከማል ፍየሉንም በምድረ በዳ ውስጥ ይለቅቀዋል::»*

በዚህ ምንባብ ውስጥ ሊቀ ካህኑ አሮን ተጠቅሶዋል በእስራኤል ሕዝብ ፋንታ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ለእግዚአብሄር መስዋዕቶችን ከሚያቀርቡት ካህናቶች ሁሉ እርሱ እጅግ ታላቁ ካህን ነበር ይህ ወኪል የሆነው ካህን በሰባተኛው ወር በ10ኛው ቀን ለእስራኤል ሕዝብ ሁለት ፍየሎችን አቅርቦ ዕጣ ይጥልባቸዋል መጀመሪያ የተመረጠውን ፍየል ወደ መገናኛው ድንኳን ይወስደውና እጆቹን በራሱ ላይ በመጫን የእስራኤሎችን ሐጢያቶች በሙሉ ያስተላልፋል::

ከዚያም «እግዚአብሄር ሆይ! የእስራኤል ሕዝብ እያንዳንዱን ሐጢያት ሰርተዋል ገድለዋል አመንዝረዋል ሰርቀዋል ጣዖታትን አምልከዋል በሐሰት መስክረዋል ጎምጅተዋል ተሳድበዋል» በማለት የእስራኤሎችን ሐጢያቶች በሙሉ ይዘረዝራል ሲጸልይ በፍየሉ ላይ ጭኖዋቸው የነበሩትን እጆቹን ሲያወርድ እነዚህ ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ፍየሉ ተላልፈዋል እጆችን መጫን ማለት በመንፈሳዊ አነጋገር

«ማስተላለፍ» ማለት ነው ደግሞም «መቅበር» ማለትም ነው።።

አሮን የዚህን ፍየል ጉሮሮ ይቆርጥና ደሙን ያፈስሰዋል ይህንብም ደም ይረጨዋል በዚህም የስርየት መክደኛውን የመገናኛውን ድንኳንና የሚቃጠለውን መስዋዕት መሠውያ የማንጻት ስርአት ይፈጽማል አሮን የእግዚአብሄር ቤት በሆነው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ይህንን መስዋዕት በማቅረቡ እግዚአብሄር የመስዋዕቱን እንስሳ፣ በዚህ እንስሳ ላይ እጆችን በመጫን የተላለፉትን ሐጢያቶችና በይፋ የመኮነኑን ደም ከተመለከተ በኋላ የሕዝቡን ሐጢያቶች በሙሉ ያነጻል በአጭሩ የእግዚአብሄር ትክክለኛ የደህንነት ዘዴ ይህ ነበር።።

ኢየሱስ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ሁሉ ፈጸመ

እግዚአብሄር የማንንም ሰው ሐጢያቶች አይታገስም መጽሐፍ ቅዱስ *«የሐጢአት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6:23)* ስለሚል ሐጢያት በሞት መኮነን አለበት የእግዚአብሄር ፍትህ ይህ ነው ነገር ግን እግዚአብሄር የፍቅር አምላክም ነው ስለዚህ የፍቅሩንና የፍርዱን ሁለት ሁኔታዎች ለማሟላት የእስራኤል ሕዝብ ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እጆቻቸውን በራሱ ላይ በመጫን እንደ ፍየል ወይም በግ ባለ ነውር የሌለበት የመስዋዕት እንስሳ ላይ እንዲያስተላልፉ አደረገ የእስራኤል ሕዝብ ይህንን እንስሳ በራሳቸው ምትክ ሲገድሉት፣ ደሙንም በሚቃጠለው መስዋዕት መሰውያ ቀንዶች ላይ ሲቀቡትና በስርየት መክደኛው ላይ ሲረጩት እግዚአብሄር የዚህን እንስሳ ደም በማየቱ ቤዛነት ይገኝ ነበር ማለትም ይህ በእግዚአብሄር ጻድቅ የደህንነት ሕግ ፊት ትክክል ነበር እግዚአብሄር የሐጢያትን ስርየት የሰጣቸው ለዚህ ነበር እግዚአብሄር እንዲህ

ያለውን ትክክለኛ የደህንነት መስዋዕታዊ ስርአት የሰጠው የሰውን ዘር በመውደዱ ነበር።

ከዚያም አሮን ቀሪውን ፍየል በሕዝቡ ፊት ይወስድና እጆቹን በራሱ ላይ ይጭናል ዘሌዋውያን 16:21 «አሮንም ሁለቱን እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤልን ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ሐጢአታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል» እንደሚል አሮን እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ ይጭንና የእስራኤል ሕዝብ አመቱን ሙሉ የሰሩትን ሐጢያቶች በሙሉ ይናዘዛል እጆቹን ካነሳ በኋላም አሮን ሕያው የሆነውን ፍየል ለሌላ ሰው በአደራ ያስረክበዋል እርሱም በጣም ሩቅ ወደሆነ የፓለስቲን ምድረ በዳ ይወስደውና እዚያ ይለቅቀዋል ከዚያም ይህ ፍየል የእስራኤልን ሕዝብ ሐጢያቶች በሙሉ ተሸክሞ ውሃና ሳር በሌለበት ምድረ በዳ ይቅበዘበዛል በመጨረሻም በምትለበልበው ጸሐይ በጥማት ይሞታል።

የእስራኤል ሕዝብ አመቱን በሙሉ የሰሩዋቸውን ሐጢያቶች የደመሰሰውና «በስርየት ቀን» የቀረበው መስዋዕት ይህ ነበር እግዚአብሄር በዚህ የመስዋዕት እንስሳና ቁርባን አማካይነት በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረውን መላውን የሰው ዘር ለማዳን እያቀደ ነበር ይህ ምንባብ እንዲጸፍ ያደረገው ለዚህ ነው።

የእስራኤል ሕዝብ በዚህ ቃል መሰረት በየአመቱ ተመሳሳይ መስዋዕት ያቀርቡ ነበር ሊቀ ካህኑ ሲሞትም ልጁ 30 አመት ሲሆን ይተካዋል ይህ መስዋዕትም በተደጋገሚ ይቀርብ ነበር ነገር ግን ይህ መስዋዕት ሊመጣ ያለው መልካም ነገር ጥላ ብቻ ነበር የእስራኤል ሕዝብ በየአመቱ በተደጋጋሚ ያንኑ መስዋዕት የማቅረባቸው እውነታ በዚህ መስዋዕት አማካይነት ፍጹም የሆነውን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ለአንዱና ለመጨረሻ ሊቀበሉ እንደማይችሉ ማስረጃ ነው። (ዕብራውያን 10:1-4)

እግዚአብሄር ከ700 አመታት በፊት አንድያ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል ማህጸን ውስጥ እንደሚጸነስና የሰው ስጋ እንደሚለብስ የተነበየው ለዚህ ነው ልክ በተተነበየው በዚህ ተስፋ መሰረትም እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስንና አጥማቂውን ዮሐንስን ወደዚህ ምድር በመላክ ጽድቅን ሁሉ እንዲፈጽሙ ፈቀደላቸው በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደተገለጠው «ስለ ሐጢአት አንድን መስዋዕት ለዘላለም» ለማቅረብ ራሱ የእግዚአብሄር ልጅ ስጋ ለብሶ በዚህ ምድር ላይ ተወለደ።

ስለዚህ ኢየሱስ ሕዝቡን ከሐጢያቶች የሚያድን አምላክ ሆኖ መጣ 30 አመት ሲሆነውም የሰው ዘር ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ ሐጢያቶችን በሙሉ ተቀበለ ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው «ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም» (ማቴዎስ 3:15) ነበር መሞት በእግዚአብሄር መኮነንና ወደ ሲያል መጣል የሚገባኝ እኔ ነበርሁ ነገር ግን እግዚአብሄር ስለወደደኝ ልጁን ወደዚህ ምድር ላከው በእጆች መጫን አማካይነትም የሰው ዘር ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ አማካይነት በጥምቀት ሐጢያቶቼን በሙሉ አስተላለፈ ልጁን በመስቀልም ኮነነው በዚህም እናንተንና እኔን አዳነን።

ስለዚህ ጌታችን እንዲህ ማለትም እጆችን በመጫን የመቀበል ዘዴ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ሁሉ ፈጸመ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀውና የተሰቀለው እያንዳንዱን ሰው ሐጢያት አከልባ ለማድረግ ነበር ጥምቀት የሚለው ቃል «መታጠብ፣ ማስተላለፍ፣ መቅበር» ማለት ነው ይህም እግዚአብሄር በዚህ መንገድ በዚህ እጅግ ተገቢና ተስማሚ መንገድ ከአለም ሐጢያቶች እንዳዳነን ይነግረናል ስለዚህ እግዚአብሄር እዚህ በብሉይ ኪዳን ተስፋ በገባልን መሰረትና ሐጢያት በእጆች መጫኑ እንደሚተላለፍ በእግዚአብሄር በጸናው ሕግ መሰረት ጌታችን በጥምቀት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ተቀበለ።

ስለዚህ የሐጢያቶቻችንን ስርየት የተቀበልነው በዚህእውነት በማመን ነው የእግዚአብሄር በግ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ስለመጣ ሐጢያቶቻችንን ስለወሰደና ተሰቅሎ ስለሞተ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ አዳነን አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምን ሁሉ ወንድም፣ ሴትም፣ አይሁድም፣ አሕዛብም ያለ አድልዎ የሐጢያት ስርየትን መቀበል ይችላል

አጋር ምዕመናኖቼ ጌታችን ስታመነዝር እጅ ከፍንጅ ለተያዘችው ሴት «አንቺ ሴት እኔም አልፈርድብሽም» ያለው ጌታችን በዚህ ምድር ላይ ይህንን ስራ ስለሰራ ነው በሌላ አነጋገር «እኔም ሐጢያት አለብሽ አልልም ደግሞም አልፈርድብሽም ምክንያቱም ሐጢያቶችሽን በሙሉ በጥምቀቴ ስለተቀበልሁ በአንቺ ምትክ መሞት አለብኝ በአንቺ ፋንታም ሐፍረትን መቀበል አለብኝ በአንቺ ምትክም ቅጣቶችን ሁሉ መሸከም አለብኝ አንቺ በዚህ አለም ላይ የሰራሻቸው ሐጢያቶች በሙሉ አስቀድመው ወደ እኔ ስለተላለፉና አሁን እነርሱን የወሰድኋቸው እኔ ስለሆንሁ እንዲህ ልሰቃይ ይገባኛል» ማለቱ ነበር::

ጌታችን በዮሐንስ 8:12 ላይ እንዲህ ያለው ለዚህ ነው *«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም»* የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል የሚያምኑና የሚከተሉ ሰዎች የሕይወት ብርሃን ይሆናሉ በዘፍጥረት 1:2 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ»* ይህ ማለት በውስጣችን ጥልቀት ውስጥ ሐጢያት አለ ማለት ነው ጌታ ግን በመጠመቅ በመስቀል ላይም ደሙን በማፍሰስና የሐጢያትን ኩነኔ ሁሉ ተሸክሞ ዋጋውን ሁሉ በመክፈል ደህንነትን ሰጥቶናል::

አጋር ምዕመናኖቼ ጥልቅ ከሆኑ የጨለማ ሐጢያቶች

ምክንያት ሐጢያቶቻችንን መገንዘብ አልቻልንም ሁላችንም ለሞት የታጨን ነበርን ወደ ሲያል ከመጣል በቀር ምርጫ አልነበረንም ሐጢያቶቻችንን ብናውቅም እነዚህን ሐጢያቶች መፍታት አልቻልንም ነገር ግን ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይሁንለት እኛን የመሰሉ ሰዎች አሁን ከጨለማ ተለውጠው ብርሃን ሆነዋል በሐጢያቶቹ ከመሞት ማምለጥ የማይችል ሰው አሁን ጻድቅ ሰው ሆንዋል ምንም ያህል ብንሞክር ይህ በራሳችን ጥረት የሚቻል አልነበረም ነገር ግን በጌታችን በማመን አሁን ጻድቃን ሆነናል በእርግጥ እኛ ሁላችንም ሐጢያተኞች ነበርን ጌታ ግን ወደዚህ ምድር መጥቶ እናንተንና እኔን አዳነን ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሀንስ 8 ላይ ላለችው ለዚህች አመንዝራ ሴት *«እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ደግመሽ ሐጢአት አትስሪ»* አላት እንዲህ ደግሞ አለ *«የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም»* አጋር ምዕመናኖቼ አሁን ሐጢያተኞች ጻድቃን ሆነዋል የተኮነኑትም አሁን የዘላለምን ሕይወት ተቀብለዋል።

በዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ትፈልጋላችሁን? ይህንን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛችሁ አድርጋችሁ ታምናላችሁን? ጌታችን *«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» (ማቴዎስ 11:28)* ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን በተጨባጭ ስላስወገደና ስላዳነን ነው።

ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ በዚህ ምድር ላይ በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች ደህንነትን ተስፋ የሚሰጥ አንዳች ሌላ አማልክት አለ? ቡድሃ ሰውን ሁሉ ለራሱ ዕድቅ ትቶታል ኮንፊሺየስና ሜናሺየስም ጥሩና በስነ ምግባር የታነጹን ሰዎች ሆነን መኖር እንደሚገባን በማደፋፈር ይህንኑ አድርገዋል ለሲያል ለታጨነው ለእናንተና ለእኔ አብዝቶ እስኪራራልን ድረስ የገዛ ራሱን ሕይወት ለእኛ አሳልፎ የሚሰጥ ሰው

ከወደፊት ማግኘት እንችላለን? ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሰማይ ዙፋኑን ለእናንተና ለእኔ ትቶ ወደዚህ ምድር መጣ በመጠመቅም ሐጢያቶቻችንን በነሙለ ተቀብሎ ወሰደ በራሱ ሕይወትም የሐጢያቶቻችንን ዋጋ ከፈለ ያዳነን ሌላ ማንም ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ስለዚህ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን ነው ጌታ ለጋለሞታይቱ ሴት የተናገረውን የተናገረው ለዚህ ነው::

ከእግዚአብሄር ዘንድ የሐጢያቶቻችንን ስርየት እንድንቀበል የሚያስችለንን እምነት ማንሳት አለብን

በሮሜ 8:1-2 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከሐጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና::»*

እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመሞት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በመውሰዱ ጌታ ሐጢያት አልባ እንዳደረገን ይናገራል አጋር ምዕመናኖቹ እኛ ሁላችን በዚህ አለም ላይ ሐጢያትን አንሰራምን? በእርግጥም እንሰራለን ነገር ግን በዮሐንስ 1:29 ላይ አጥማቂው ዮሐንስ እርሱን ባጠመቀው ማግስት «የአለምን ሐጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሄር በግ» መሆኑ አወጀለት ይህ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እየሰራናቸው ያለነውንና መቼም የምንሰራቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ተሸክሞዋል ማለት ነው እርሱ በተጠመቀ ጊዜ ሁሉንም ተቀብሎ ወደ መስቀል ወሰዳቸው ስለ እነርሱም ተኮነነ::

ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉ ሰዎች ኩነኔ

እንደሌለባቸው የተናገረው ለዚህ ነው በሌላ አነጋገር በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ደሙ ከልባቸው የሚያምኑ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑ ሰዎች ምንም ሐጢያት ሊኖርባቸው አይችልም ይህ ማለት እነርሱ ሐጢያተኞች ሊሆኑ አይችሉም ከምንሰራቸው ሐጢያቶች የተነሳ ሐጢያተኞች ከመሆንና ወደ ሲያል ከመጣል ማምለጥ አንችልም ነገር ግን ወደዚህ ምድር በመምጣት፣ በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመሞት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የደመሰሰው ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ እንደሆነ ብታምኑና ከሙሉ ልቦቻችሁም በትክክል ይህንን ብታምኑመጽሐፍ ቅዱስ ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ኩነኔ እንደሌለባችሁ ይናገራል ይህ ምንባብ «ፈጽሞ ሐጢያት እንዳለባችሁ መናገር አትችሉም» ብሎ የሚያውጅ የተባረከ አዋጅ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ ይህ ሆኖ ሳለ በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም ሐጢያተኞች እንደሆኑ የሚናገሩ ብዙ ሰዎች አሉ ብዙ ክርስቲያኖች ጉባኤውን ወክለው በሚጸልዩበት ጊዜ «ቅዱስ አባታችን ተመስገን ባለፈው ሳምንት ብዙ ሐጢያቶችን ሰርተናል እባክህ እነዚህን ሐጢያቶች አንጻቸው» ይላሉ ጸሎቶቻቸውን የሚያተናቅቁት እንዴት ነው? «ይህ ምስኪን ሐጢያተኛ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጸልያል» ይላሉ።

ሐጢያተኛ እንዴት ወደ እግዚአብሄር ሊጸልይ ይችላል? ሐጢያተኛ ወደ እግዚአብሄር ቢቀርብ ወዲያውኑ ይጠፋል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሄር የሐጢያተኛውን ጸሎቶች እንደማይሰማ ተጽፎዋል ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን ለመደምሰስ ወደዚህ ምድር መጥቶ ሳለ በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመኮነንም የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ተሸክሞና ወስዶ ሳለ በዚህ አለም ላይ የቀረ አንዳች ሐጢያት እንዴት ሊኖር ይችላል? ምንም ያህል ጎዶሎ ብንሆን ኢየሱስ ክርስቶስ

ሐጢያቶቻችንን በበቂ ሁኔታ በግልጽና በተትረፈረፈ መልኩ ደምስሶዋል ታዲያ ምን አይነት ሐጢያት ሊኖርባችሁ ይችላል?

ለምሳሌ ያህል የመጋዘን ዕዳ አለባችሁ እንበል አባታችሁ ትክክለኛ ከሆነ የዕዳ መጠን በላይ በሚሊዮኖችና በቢሊዮኖች መጠን አስቀድሞ ዕዳችሁን ከከፈለ ከዚያ በኋላ ምንም ያህል ብዙ ዕዳ ቢኖርባችሁም አንዳች የገንዘብ ዕዳ የለባችሁም ደህንነትም ይኸው ነው::

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8:1) ኢየሱስ ክርስቶስን በትክክል ባመኑ ሰዎች መካከል ፈጽሞ ሐጢያተኛ የለም ሁሉም ጻድቃን ናቸው ለምን? ምክንያቱም *«በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከሐጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና» (ሮሜ 8:2)* በሕጉ መሰረት ወደ ሲያል ከመጣል በቀር ምርጫ የለንም ነገር ግን ያዳነንን የሕይወት መንፈስ ሕግ ይህንን የፍቅር ሕግ በሚመለከትስ? ጌታ ሐጢያተኞችን ለማዳን ወደዚህ ምድር መጣ በመጠመቅም ሐጢያቶቻችንን የአለምን ሐጢያቶች ወሰደ በእኛ ፋንታም ተሰቅሎ ሞተ እኛን ወደ ሕይወት መልሶ ለማምጣትም ዳግመኛ ከሙታን ተነሳ በዚህም እውነተኛ አዳኛችን ሆነ::

«በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከሐጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና» (ሮሜ 8:2) እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ምዕመናን የሆንነውን እናንተንና እኔን ከሐጢያትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶናል የኮርያ ሕዝብ በ2ኛው የአለም ጦርነት ወቅት በጃፓናውያን አገዛዝ ስር ነው ነገር ግን ነሐሴ 15፡ 1945 ኢ.ም የነጻነቱ ቀን ከመጣ በኋላ ኮርያ ዳግመኛ የጃፓናውያን ቅኝ ግዛት አልሆነችም ልክ እንደዚሁ እኛ ከእንግዲህ ወዲህ ሐጢያተኞች አይደለንም በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ እንደሆነ የምታምኑ ከሆነ

ሐጢያተኞች አይደላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም ራሳቸውን ሐጢያተኞች አድርገው የሚገልጡ ሰዎች ካሉ ለዚህ ምክንያቱ በውሸታሞች መታለላቸውና ሐሰተኛ ወንጌል ማመናቸው ነው።

ሮሜ 8:3 እንዲህ ይላል *«ክሥጋ የተነሳ ስለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን እግዚአብሄር የገዛ ልጁን በሐጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በሐጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና ሐጢአትን በሥጋ ኮነነ» (ሮሜ 8:3)* ሕጉን ለመጠበቅ ሥጋችን በጣም ደንማ ነው ሕጉን መጠበቅ እንችላለን? ሕጉ ሌሎች አማልክቶች እንዳይሆኑልን፣ እንዳንገድል፣ እንዳናመነዝር፣ እንዳንሰርቅና በሐሰት እንዳንመሰክር አዞናል ነገር ግን እንደማትገድሉ እርግጠኞች ናችሁ? እንደማትሰርቁ እርግጠኞች ናችሁ? በሐሰት እንደማትመሰክሩ እርግጠኞች ናችሁ? ትንሽ ኪሳራ ብትደርስባችሁ ትዋሻላችሁ ታጭበረብራላችሁ።

አለማመንዘር ትችላላችሁን? ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎዋል *«አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል» (ማቴዎስ 5:27-28)* እንዳታመነዝሩ የሚያዛችሁን የሕግ ስርአት በእርግጥ መጠበቅ ትችላላችሁን? እንደማትችሉ የታወቀ ነው ሕጉን ሁሉ መጠበቅ ትችላላችሁን? እንደማትችሉ የታወቀ ነው እኛ የሕጉን እያንዳንዱን ትዕዛዝ እንጥሳለን የምንጥሰው እንዴት ነው?

ሕጉን እንተወውና ማህበራዊ ድንጋጌዎችን እንኳን መጠበቅ እንችላለን? የትራፊክ ሕጎችን ሁሉ እንጠብቃለን? በጣም ባተሌ በምንሆንበት ጊዜ ማቋረጫ መንገድን ወይም መጠምዘዣን የምንጠቀመው እንዴት ነው? ሌሎች የማያዩን ከሆነ ጥሰን እንራመዳለን ሕጉን እንዲህ አንድ ጊዜ ብቻ የጣሰ ማንኛውም ሰው የማህበረሰቡን ሕጎችና መመሪያዎች መጠበቅ አቅቶታል።

አጋር ምዕመናኖቼ ሰዎች በዚህ ምድር ላይ የራሳቸውን ሰው ሰራሽ ሕግ መጠበቅ የማይችሉ ሆነው ሳለ የእግዚአብሄርን ሕግ እንዴት መጠበቅ ይችላሉ? ከእግዚአብሄር ሕግ ውስጥ አንዲቷን ትዕዛዝ እንኳን ጥሰን ከሆነ በሁሉም በደለኞች ነን እግዚአብሄር ውጥናችንን በሙሉ ዋጋ ያሳጣዋል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *«ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል አታመንዝር ያለው ደግሞ አትግደል ብሎአልና ባታመነዝርም ነገር ግን ብትገድል ሕግን ተላላፊ ሆነሃል» (ያዕቆብ 2:10-11)* ስለዚህ በእኛ መካከል ሕጉን በእግዚአብሄር ፊት ያለ እንከን የጠበቀ ሰው የለም ስለዚህ ሁላችንም ለሲያል የታጨን ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ ስጋችን ደካማ ስለሆነ ሕጉን መጠበቅ አንችልም ልቦቻችን ሕጉን መጠበቅ ቢፈልጉም ስጋችን ያንን ለማድረግ በጣም ደካማ ነው ስለዚህ እግዚአብሄር ምን አደረገ? *«ከሥጋ የተነሳ ሰለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን እግዚአብሄር የገዛ ልጁን በሐጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በሐጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትዕዛዝ ይፈጸም ዘንድ ሐጢአትን በሥጋ ኮነነ።» (ሮሜ 8:3-4)*

ስጋችን ሕጉን ለመጠበቅ በጣም ደንማ ነው እግዚአብሄር ግን የሕጉን ትዕዛዝ ፈጸመ በሕጉ መሰረት ሐጢያት ያለበት ማንኛውም ሰው መሞት ነበረበት ነገር ግን የእግዚአብሄር ልጅ ወደዚህ ምድር ስለመጣ፣ በጥምቀቱም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስለተቀበለና በእኛ ፋንታ ተኮንኖ ስለሞተ ሕጉ የጠየቀውን መጠይቅ አሟላ የሕጉንም መጠይቆች በሙሉ ፈጽሞ ደህንነትን አጠናቀቀ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሕጉን አረካ ኢየሱስ ክርስቶስ የሐጢያት ደመወዝ ሞት መሆኑን የሚያውጀውን የሕግ ትዕዛዝ

በጥምቀቱና ባፈሰሰው ደሙ በመፈጸም እርሱን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑትን ሰዎች አዳናቸው እዚህ ላይ እግዚአብሄር አብ «የገዛ ልጁን በሐጢአተኛ ስጋ ምሳሌ በሐጢያትም ምክንያት አድርጎ ልኮታልና ሐጢአትን በሥጋ ኮነነ» ሲል ለሲያል የታጨነውን እኛን ለማዳን እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችንን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተላልፎ በስጋው ላይ አሸከመው ማለት ነው ይህ ገብቶዋችኋል? የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ምስጢር ሌላ ሳይሆን ይህ ነው።

እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትዕዛዝ ይፈጸም ዘንድ ሐጢአትን በሥጋ ኮነነ እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሰላምና ሕይወት ነው።»* *(ሮሜ 8፡4-6)*

አጋር ምዕመናኖቼ ከስጋዊ አመለካከት አንጻር ብቻ ከታየ በዚህ አለም ላይ በየቀኑ ሐጢያትን በመስራት እየቀጠልን እንዴት ሐጢያት የለብንም ማለት እንችላለን? በኢየሱስ ክርስቶስ ብናምንም እንዴት ሐጢያት አለክባ ነን ማለት እንችላለን? ነገር ግን እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚመላለሱ ሰዎች የሚያመላክቱት እግዚአብሄር በውሃውና በደሙ ወንጌል ፈጽሞ እንዳዳነን የሚያምኑ ሰዎችን ነው።

የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን የምናምን ከሆነ በእርግጥ በተጻፈው ቃል የምናምን ከሆነ ታዲያ እንዴት ሐጢያት የለብንም ማለት እንችላለን? ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ መደምሰሱ አያጠራጥርም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ማድረጉን በግልጽ መዝግቦዋል እግዚአብሄርም የዚህ ማስረጃ አድርጎ ቅዱሳት መጽሐፍትን እንዲህ ትልቅ ጥራዝ አድርጎ ጻፋቸው መጽሐፍ ቅዱስን ያለ ምንም ለውጥ ለሺህ አመታቶች

ያህል ጠብቆ አቆየው ሁሌም እንደነበረው አድርጎም ሰጠን ይህ ሆኖ ሳለ በእርግጥ በዚህ ቃል የምናምን ከሆንን አሁንም ድረስ እንዴት ሐጢያት አለብን ማለት እንችላለን? እዚህ ላይ ዋናው ጉዳይ ይህ ነው ማመን የሚገባን በስጋዊ አስተሳሰቦቻችን ነው ወይስ ማመን የሚገባን በመንፈስ ማለትም በእግዚአብሄር ቃል ነው? በተጻፈው የእግዚአብሄር ቃል መሰረት እናምን እንደሆነ ወይም በራሳችን አስተሳሰቦችና ስሜቶች እናምን እንደሆነ መወሰን አለብን::

በተጻፈው የእግዚአብሄር ቃል ከማመን ይልቅ በስሜቶቻቸው የሚያምኑ ሰዎች እምነታቸው ሁሉ ከንቱ ነው እግዚአብሄርን ማመን የሚገባን በቃሉ መሰረት ነው በተጻፈው ቃል መሰረትም ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን መሆኑን ማወቅና ማመን አለብን ጌታችን ተስፋን የሰጠንና ተስፋዎችን የፈጸመ የቃል ኪዳን አምላክ ነው ጌታችን ተስፋዎቹን ሁሉ በቃሉ መሰረት በትክክል የሚጠብቅ አምላክ ነው ለመድገም ያህል በብሉይ ኪዳን እግዚአብሄር የእስራኤልን ሕዝብ ሐጢያቶች እጆቹን በራሱ ላይ በሚጭነው በሊቀ ካህኑ አማካይነት ለመስዋዕት ወደቀረበው እንስሳቸው በማስተላለፍ የእንስሳውን ጉሮሮ እንዲቆርጡ፣ ደሙን እንዲያፈስሱና በሚቃጠለው መስዋዕት መሰዊያ ቀንዶች ላይ እንዲያኖሩት አድርጎዋቸዋል እንዲህ በማድረግም በዚህ የስርየት መስዋዕት ያመኑ ሰዎች እንዲድኑ አስችሎዋቸዋል::

በሌላ በኩል በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሰጠው ተስፋ መሰረት ጌታችን ከ2,000 አመታት በፊት ወደዚህ ምድር መጣ በእጆች መጫን ዘዴም የሰው ዘር ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ተቀበለ በእኛ ፋንታ ሞተ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ በዚህም ሁላችንንም አዳነን እናንተና እኔ ጌታችን

እንዴት እንዳዳነን ያወቅነው በዚህ በተጻፈው ቃል አማካይነት ነው የዳንነውም በዚህ በማመን ነው እንዲህ የሚያምኑ ሰዎች «እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ» ሰዎች ናቸው ከልባችን ማመን የምንችለው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት ስናውቅ ብቻ ነው ማመናችንን በአንደበታችን መመስከር የምንችለውም ስናምን ብቻ ነው።

ወደ ዘሌዋውያን 17:15-16 እንመለስ *«የሞተውን ወይም አውሬ የሰበረውን የሚበላ ሰው ሁሉ የአገር ልጅ ወይም እንግዳ ቢሆን ልብሱን ያጥባል በውሃም ይታጠባል እስከ ማታም ርኩስ ይሆናል ከዚያም በኋላ ንጹህ ይሆናል ልብሱንና ገላውን ባያጥብ ግን ሐጢአቱን ይሸከማል»* በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ሕዝብ በስርየት ቀን ሊቀ ካህኑ የሚያደርገውን አይተው በማመናቸው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ተቀብለዋል ሊቀ ካህኑ እጆቹን በመስዋዕቱ ላይ በመጫንና ሐጢያቶቻቸውን በእርሱ ላይ በማሻገር መስዋዕቱን በእነርሱ ፋንታ አቅርቦ እስራኤሎች ከሐጢያቶቻቸው እንዲነጹ አስችሎዋቸዋል ነገር ግን ማንኛውም እስራኤላዊ እንደ ሬሳ ያለ ርኩስ ነገር ቢነካ ልብሶቹን ማጠብና ሰውነቱንም በውሃ መታጠብ ነበረበት መጽሐፍ ቅዱስ ሰውነቱን በውሃ ባይታጠብ ሐጢያቱን እንደሚሸከም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ይህ «ውሃ» በእጅጉ አስፈላጊ ነው ሰው የሐጢያቶቹን ስርየት ከተቀበለ በኋላ እንንን በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ላይ ያለውን እምነቱን ጠብቆ መቀጠል ያለበት መሆኑ አስፈላጊ ነው።

የውሃ የማጠብ ተግባር

ከውሃ ተግባራቶች አንዱ ቆሻሻን ማንጻቱ ነው ውሃ ለሰዎች ሕይወትንም ይሰጣል እኛ በሐጢያቶቻችን ስርየት ብናምንም

በዚህ ምድር ላይ ደግመን ሐጢያት አንሰራምን? በእርግጥም እንሰራለን ነገር ግን እነዚህም ሐጢያቶች ቢሆኑ በአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተካተዋል ጌታ እነርሱንም ደግሞ ደምስሶዋቸዋል ነገር ግን ሐጢያት በምንሰራበት ጊዜ ሁሉ ሕሊናችን ይጎዳል ይሰቃያል ታዲያ እነዚህን ሐጢያቶች ምን እናድርጋቸው? እንደገና በኢየሱስ ክርስቶስ ልናምን ይገባናልን? የለም እኛ ማድረግ የሚገባን ነገር ቢኖር እነዚህም ሐጢያቶች በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ ወደ እርሱ እንደተላለፉ በልቦቻችን ማጽናትና ጌታችን አስቀድሞ ደግመን ሐጢያት እንደምንሰራ ስለሚያውቅ ልክ እንደዚያ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደ በልቦቻችን ማመን ነው በሌላ አነጋገር የደህንነትን ወንጌል እንደገና በአእምሮዋችን ውስጥ ማሰላሰል ያስፈልገናል በድክመቶቻችን ምክንያት ከምንሰራቸው ሐጢያቶች በሙሉ ነጻ መውጣት የምንችለው ያን ጊዜ ነው ሙሉ በሙሉ የምንነጻው ያን ጊዜ ነው ሙሉ በሙሉ የምንድነውና ፈጽመን ጻድቃን የምንሆነው ያን ጊዜ ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወት ሕግ ማለትም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ክርስቶስ ኢየሱስ በሐጢያትና በሞት ሕግ ስር ሆነን ስናለቅስ የነበርነውን ሰዎች እንዳዳነንና በእርሱ ውስጥ እንድንኖር እንዳደረገን ይናገራል ሐዋርያው ዮሐንስም እንደዚሁ በ1ኛ ዮሐንስ 5:3-8 ላይ ኢየሱስ በውሃውና በደሙ ወንጌል በመምጣት ፈጽሞ ከሐጢያት ነጻ እንዳወጣን በግልጽ ይናገራል እርሱ ጨምሮም «ውሃው፣ ደሙና መንፈሱ» ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ከሐጢያት ያዳነን የመሆኑን እውነት ይመሰክራሉ መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክረው ምንድነው? ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ ይመሰክራል ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ዩኒቨርስ የፈጠረ አምላክ እንደሆነና እኛን ሰዎችንም

ለማዳን በሰው መልክ በድንግል ስጋ አማካይነት በዚህ ምድር ላይ የመወለዱን እውነታ ይመሰክራል ውሃውና ደሙስ ምን ይመሰክራሉ? የደህንነት አምላክ የሆነው ጌታችን በዚህ መንገድ ሰው ሆኖ እንደመጣ፣ በ30 አመቱም በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ፣ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉና የእኛን ሐጢያቶች በሙሉ እንደወሰደ፣ እነዚህንም ሐጢያቶች በመስቀል ላይ እንደተሸከመና እዚያው እንደሞተ ይመሰክራሉ።

ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም ብቻ የሚያምን ማንኛውም ሰው ምንም ያህል በኢየሱስ ክርስቶስ ለረጅም ጊዜ ቢያምንም የያዘው እምነት ፈጽሞ የማይረባ እምነት ነው በዚህ መንገድ የሚያምኑ ሰዎች ራሳቸውን ሐጢያተኞች አድርገው ይገልጣሉ ምክንያቱም ነገ እንደገና ሐጢያትን ይሰራሉና ነገር ግን እንደዚህ የሚያስቡት ለምንድነው? ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንደተቀበለ ስለማያውቁ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም ሁሌም ሐጢያተኞች ሆነው በመኖር የሚቀጥሉት ለዚህ ነው ሕሊናቸው ሐጢያት አልባ ነን ብለው እንዲናገሩ አይፈቅድላቸውም።

ለእናንተና ለእኔ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ ተላልፈዋል እኛ ጨለማ በጥልቁ ላይ ያለብን ሰዎች በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ሐጢያትን ከመስራት በቀር ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም ልቦቻችንም ቋንቋ ሊገልጠው ከሚችለው በላይ የረከሱ ናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ ተሰቅሎም ተኮነነ እስከ ሞት ድረስም ደሙን አፈሰሰ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ በዚህም ፈጽሞ ከሐጢያቶቻችን አዳነን ጌታ አሁንም እኛን ሕያው ነው እርሱ በዚህ የደህንነት ቃል ለሚያምን ሁሉ ደህንነትን በነጻ የሚሰጥ

አምላክ ነው እናንተስ ታዲያ? ታምናላችሁ? በልቦቻችሁ የምታምኑ ከሆነ እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ ልቦቻችሁን ያውቃል በመዳናችሁም ያትማችኋል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነትን ያመጣልን አምላክ ነው የእግዚአብሄር ልጆች የምንሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ነው ሐጢያት አለባችሁ ወይስ የለባችሁም? እናንተ ምንም ሐጢያት የለባችሁም ምክንያቱም ሐጢያቶቻችሁ በሙሉ ወደ ጌታ ተላልፈዋልና ታዲያ ይህ ማለት ሐጢያትን በነጻነት መስራት አለብን ማለት ነውን? በእርግጥም አይደለም! ትክክል ያልሆነ ነገር ስናደርግ ሐጢያትን እንሰራለን ይህንን የምናደርገው የሆነ ሰው እንድናደርግ ስለነገረን አይደለም የሆነ ሰው እንዳናደርገው ስለሚከለክለንም ልንተወው የምንችለው ነገር አይደለም ሰዎች ሁሉ ጉድለት ስላለባቸው እስከ ዕለተ ሞታቸው ቀን ድረስ ሐጢያትን ይስራሉ ጌታችን ወደዚህ ምድር የመጣው ከእነዚህ ሐጢያቶች ሊያድነን ነው በእርግጥም ሙሉ በሙሉ አድኖናል እኛ ማድረግ ያለብን ነገር ቢኖር ይህንን ማመን ብቻ ነው ሰው አምኖ የሚጸድቀው በልቡ ነው በአፉም መስክሮ ይድናል::

እንደገና ወደ ዘፍጥረት 1:2-5 እንመለስ *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበረ እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ እግዚአብሄርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን::»*

እግዚአብሄር በጨለማ በተሞላው ድቅድቅ አለም ውስጥ ብርሃን እንዲሆን አዘዘ ይህ የሚያመላክተው የእግዚአብሄር ልጅ ወደ ምድር የተላከ መሆኑን ነው እግዚአብሄር ልጁ በጥምቀት

ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንዲወስድና በመስቀል ላይ እንዲሞት በማድረግ ሁላችንንም ከሐጢያቶቻችን እንዳዳነን ያመላክታል።

እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ያደረገው ምንድነው? ቅርጽ አልባና ባዶ በነበሩትና ጨለማም በጥልቁ ላይ በነበረባቸው በሰዎች ልቦች ላይ ብርሃንን አበራ እንዲህ በማድረግም ጨለማና ባዶነት ሁሉ እንዲጠፋ አደረገ እውነተኛ እርካታን፣ እውነተኛ ስርአትን፣ እውነተኛ ብርሃንና እውነተኛ ሕይወትንም አመጣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ አለም የደህንነት ብርሃን ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሐጢያተኞች አዳኝ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ጌታችን ነው በዚህ የውሃና የመንፈስ ወንጌል ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን እንደሆነና በውሃውና በደሙ አማካይነት እንዳዳነን ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ የደህንነት ብርሃን ሆንዋል አጋር ምዕመናኖቼ በዚህ አለም ላይ ብቸኛው እውነተኛ ብርሃን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እግዚአብሄር አይቶት መልካም ነው ያለው ይህንን ብርሃን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ብርሃንን ከጨለማ እንደለየ ይናገራል እርሱ ሁለቱን ከለያየ በኋላ ብርሃኑን ቀን ጨለማውንም ሌሊት ብሎ ጠራው በዚህ አለም ላይ ሁለት አይነት ሰዎች አሉ እነርሱም የብርሃን ልጆችና የጨለማ ልጆች ናቸው (1ኛ ተሰሎንቄ 5:5) የብርሃን ልጆች «ኢየሱስ ክርስቶስን ከማወቁ በፊት በእርግጥም ጨለማ በጥልቁ ላይ የነበረበት የሐጢያት ክምር ነበርሁ አእምሮውም ግራ የተጋባ ነበር ባዶ ነበርሁ እርካታ አልነበረኝም ወደ ሲያል ከመጣል በቀር ምርጫ አልነበረኝም ነገር ግን አንተ በአገልጋዮችህና በቤተክርስቲያንህ አማካይነት ይህንን ቃል አስተማርኸኝ ፈጽመህም አዳንከኝ ጌታ ሆይ በአንተ አምናለሁ!» በማለት እምነታቸውን የሚመሰክሩ ሰዎች ናቸው እግዚአብሄር እንዲህ ላመኑትና እውነተኛ አዳኛ

ቸው አድርገው ለተቀበሉት ሰዎች የብርሃን ልጆች የሚል ስም ሰጥቶዋቸዋል የእርሱ ልጆች ይሆኑ ዘንድም ስልጣንን ሰጥቶዋቸዋል።

«እናንተ በአንድ ወቅት የዲያብሎስ ልጆች ነበራችሁ ከእንግዲህ ወዲያ ግን የብርሃን ልጆች እንጂ የጨለማ ልጆች አይደላችሁም» እግዚአብሄር ብርሃንን ከጨለማ የለየበት አንደምታ ይህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም ለተወለዱት ሰዎች *«ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ» (ኤፌሶን 5:8)* ያለው ለዚህ ነው።

በዚህ በውሃውና በመንፈሱ ቃል በተባረከው የደህንነት ቃል የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሄር ልጆችና የእርሱ ሕዝብ ናቸው ነገር ግን በዚህ ቃል መሰረት የማያምኑ ሰዎች የጨለማ የሌሊትና የዲያብሎስ ልጆች ናቸው በዚህ አለም ላይ በርካታ ሰዎች ቢኖሩም በዚህ በማመናቸው ወይም ባለማመናቸው አንዳንዶቹ የእግዚአብሄር ልጆች ይሆናሉ ሌሎቹ ደግሞ የዲያብሎስ ልጆች ይሆናሉ አንዳንዶቹ ወደ ሰማይ ሲሄዱ ሌሎቹ ሲያልፍ ይጣላሉ እግዚአብሄር እንዲህ አድርጎ የእምነትን ሕግ ደንግጎዋል ደህንነት በእምነት ብቻ እንዲገኝ አድርጓል ሰው ጻድቅ የሚሆነው በልቡ በማመን ነው እኛም የእግዚአብሄር እውነተኛ ሕዝብ የምንሆነው በእምነት ነው።

እግዚአብሄር ብርሃንን ከጨለማ በግልጽ በመለየት የእርሱ ሕዝብ የሆኑትን የእርሱ ሕዝብ ካልሆኑት ለይቶዋል ሐጢያተኞችም በጻድቃን ጉባኤ እንዳይቆሙ ከልክሎዋል (መዝሙረ ዳዊት 1:5) አንድ ሰው በአንድ የታወቀ የቲዎሎጂ ሴሚናሪ ውስጥ የድህረ ምረቃ ኮርሱን በሚገባ ካጠና በኋላ መጋቢ ቢሆን ነገር ግን እውነትን ባለማወቁ አሁንም በልቡ ውስጥ ሐጢያት ካለበት ይህንን የእውነት ቃል መስበክ

አይችልም ሊነግራችሁ የሚችለው ነገር ቢኖር «መልካም ሕይወትን እንኑር» የሚለውን ብቻ ነው ዕውር ዕውርን ቢመራው ሁለቱም ወደ ገደል ወድቀው ይሞታሉ። (ማቴዎስ 15:14)

ሐጢያተኛ የሆነ ሰው ቢያስተምራችሁ ፈጽሞ ከሐጢያት ነጻ መውጣት አትችሉም ሐጢያት ካለባችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ብታምኑም ወደ ሲያል ትጣላላችሁ ታዲያ ክርስቲያኖችና ክርስቲያን ያልሆኑት ሁሉ ሲያል የሚወርዱት ለምንድነው? ምክንያቱም የዘመኑ ቤተክርስቲያኖች በሙሉ ወደ ንግድ ድርጅትነት ስለተለወጡ ነው በጣም ብዙ መጋቢዎች እየተንቀሳቀሱ ያሉት ልክ እንደ ነጋዴዎች ነው እነዚህ ውሸታሞች ሰማይ ለመሄድ ለተሰበሰቡት ነፍሳቶች በረከቶችን እየለመኑላቸው እንደሆኑ ይናገራሉ ነገር ግን በተጨባጭ ሲታይ ገንዘባቸውን እየበዘበዙዋቸው ነው።

በዚህ አለም ላይ ሰናይ ሕይወትን መኖር የማይፈልግ ማን አለ? ነገር ግን ሰዎች ሕይወታቸውን የሚኖሩት ሐጢያት በመስራት ስለሆነ በሐጢያቶቻቸው ምክንያት ወደ ሲያል ይወርዳሉ የጉስቁልና ኑሮ ይኖራሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃውና በደሙ እንዳዳነን በማወጅ ይህንን ወንጌል ለእነዚህ ሰዎች መስበክ ያለብን ለዚህ ነው ለእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን የተሰጠው እውነተኛ ጥሪ ይህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን እንደሆነ የምናምነው እኛ ነን።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ንስሐ ምንድነው?

የሐዋርያት ስራ 3:19 እንዲህ ይላል «*እንግዲህ ከጌታ ዘንድ የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ...ሐጢአታችሁ ይደመሰስ*

ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም» ይህ ምንባብ «በትክክል ንስሐ የሚገባና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምነውን ሁሉ ጌታ ሐጢያት አልባ ያደርገዋል» ማለት ነው በሌላ አነጋገር ጌታችን ሐጢያቶቻችን ስላስወገደ ደህንነታችንን በእምነት እንድንቀበል እየነገረን ነው።

«እኛ ሰዎች ነን እስከ ዕለተ ሞታችን ቀን ድረስ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያትን ከመስራት መሸሽ አንችልም» በማለት መሰረታዊውን ድካማችንን ስንቀበልና ጌታ የሰጠውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በማመን ወደ እግዚአብሄር ስንመለስ እውነተኛ ንስሐ ማለት ይህ ነው ጌታ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደደመሰበት የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ስንመጣና የሐጢያቶቻችንን ስርየት በእምነት ከተቀበልን ጌታ የመጽናናትን ዘመን ይሰጠናል በእግዚአብሄር ፊት የሚደረግ እውነተኛ ንስሐ ከክፉ መንገድ መመለስና «ጌታ ሆይ አንተ ያልከው ትክክል ነው» ማለት ነው።

ነገር ግን ለእግዚአብሄር የሚደረገውን እውነተኛ ንስሐ በምናጤንበት ጊዜ የአብዛኛው ሰው የገነነ መረዳት ምንድነው? ብዙ ሰዎች ንስሐ ከመግባት ከመመለስና የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ለአንዱና ለመጨረሻ በመቀበል ፋንታ የንስሐ ጸሎቶች ከራሱ ከንስሐ ጋር ተመሳሳይ እንደሆኑ አድርገው ይመለከቱዋቸዋል ስለዚህ «ጌታ ሆይ ተሳስቻለሁ እባክህ ይቅር በለኝ» በማለት ደግመው ሐጢያት በሰሩ ጊዜ ሁሉ የንስሐ ጸሎቶችን ያቀርባሉ።

ይህ እንዴት ያለ ከንቱነት ነው! በማርቆስ 7:21-23 ላይ እንዳየነው እግዚአብሄር ከሰዎች ልቦች ውስጥ እንደ ክፉ አሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርና፣ ስርቆት፣ ምቀኝነት፣ ጥል፣ ዝሙትና የመሳሰሉ አስራ ሁለት አይነት ሐጢያቶች እንደሚወጡ ተናግሮዋል ስለዚህ እውነተኛ ንስሐ «እኔ እስከ ዕለተ ሞቱ

እስከ ስጋዬ ማብቂያ ድረስ ሐጢያትን ከመስራት ማምለጥ የማልችል ሰው ነኝ እስከ መጨረሻው ድረስም ሐጢያት እሰራለሁ» በማለት ራሳችንን መቀበል እስከ አሁን ድረስ ከያዝናቸው የተሳሳቱ እምነቶች መመለስና ጌታ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የሰራነውን እያንዳንዱን ሐጢአት ለአንዴና ለመጨረሻ በደመሰሰበት ወንጌል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርለት እውነተኛ ንስሐ ከሐሰተኛ አመኔታዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ወደ ማመን ወደ እግዚአብሄር መመለስ ነው።

ነገር ግን አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በትክክል በእውነቱ አይኖሩም ነገር ግን ከዚያ ርቀው በውሸንብር እየሞቱ ነው የተለመደው የንስሐ መረዳታቸው አንድ ጊዜ ሐጢያት ከሰሩ ሐጢያቶቻቸውን መገንዘብና «ተሳስቻለሁ ዳግመኛ ፈጽሞ ሐጢያት አልሰራም» በማለት በራሳቸው መንገድ መፍትሄ ማምጣት እንዳለባቸው ያስባሉ ንስሐ ማለት ይህ እንደሆነ ያስባሉ ምክንያቱም እስከ አሁን ድረስ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማያውቁት መጋቢዎቻቸው ያስተማሩዋቸው ይህንን ነው መጋቢዎች «በየዕለቱ የንስሐ ጸሎቶችን በመጸለይ የምትሰሩዋቸውን የግል ሐጢያቶቻችሁን አንጹ» ሲሉን ይህ ለጆሮዎቻችን የሚታመን ይመስላል።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? እንዲህ ይላል *«ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብራውያን 9:22)* እንዲህም ደግሞ ይላል *«የሐጢያት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6:23)* ጌታችን በመስቀል ላይ ከመሞቱ ከሦስት አመታት በፊት በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ በመሰቀልም የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ ደመሰሰ።

ለ70 አመታት ያህል እንደምትኖሩ በመገመት ይህንን በግላችሁ ብታስቡት ይህ ማለት ጌታችን በጥምቀቱ አማካይነት

በስጋ ከሰራችኋቸው ሐጢያቶች ጀምሮ በልብ እስከሰራሁዋቸው ሐጢያቶች፣ በአስተሳሰቦቻችሁ ከሰራችኋቸው ሐጢያቶች ጀምሮ በድካሞቻችሁ ምክንያት እስከሰራችኋቸው ሐጢያቶች፣ አውቃችሁ ከሰራችኋቸው ሐጢያቶች ጀምሮ ሳታውቁ እስከሰራችኋቸው ሐጢያቶች ድረስ እስከ ዛሬ የሰራችሁትን እንዳንዱን ሐጢያትና እስከ ሽምግልናችሁ ድረስ የምትሰሩትን ሐጢያት ወስዶዋል ማለት ነው ጌታችን እነዚህን የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ መስቀል ወስዶ ደሙን አፈሰሰ በእናንተ ቦታም ለእነዚህ ሐጢያቶች ተኮነነ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ ለሚያምኑ ሰዎችም ሁሉ አዳኝ ሆነ ጌታ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በመጣው በዚህ እውነት እንድናምን ሁላችንንም ያዘናል።

ሰው በየዕለቱ የንስሐ ጸሎቶችን በማቅረብ ሊቀደስ ይችላል የሚለው እሳቤ መሰረተ ቢስ አባባል ነው

ጌታ እንዲህ አለ *«እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም ያርነት ያወጣችኋል» (ዮሐንስ 8:32)* ጌታችን በእውነት እንድናምን ነገረን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት የዚህን አለም ሐጢያቶች ተሸከመ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ ወደ መንግስተ ሰማይም አረገ ይህንን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛችሁ አድርጋችሁ የምታምኑ ከሆነ ያን ጊዜ ከዚህ አለም ሐጢያቶቻችሁና ከጥፋትም ሁሉ ትድናላችሁ ጌታ በጥምቀቱ አማካይነት የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ ስለተሸከመና ስላስወገዳቸው በዚህ እውነት ብናምን ሁላችንም በብርሃን እንቆማለን።

ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ግራ በመጋባታቸው «የአዳም ሐጢያታችን ይቅር ተብሎዋል የግል ሐጢያቶቻችን ግን

በየዕለቱ በምናቀርባቸው የንስሐ ጸሎቶች ይቀደሳሉ» በማለት ክፉ ትምህርት አፍልቀዋል ስለዚህ አንዳንድ መጋቢዎች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ በሚናገረው መሰረት ሳይሆን በሰዎች ስነ ምግባሮች ላይ ተመስርተው ንስሐን ያብራራሉ ያስተምራሉ ይህ ዳግም ላልተወለዱ ሰዎች ጆሮ ጥሩ ቢመስልም እንዲህ የሚል ማንኛውም ሰው የዲያብሎስ አገልጋይ ነው።

በአጭሩ ቅድስና ላይ መድረስ ይገባናል የሚለው እሳቤ ፈጽሞ የማይረባ ነገር ነው በዕድሜ እየገፋን ስንሄድ ሰብአዊ ተፈጥሮዋችን ይበልጥ ደንማ ይበልጥ ግትርና ይበልጥ ደንዳና እየሆነ እንደሚሄድ እየታወቀ እንዴት ልንቀደስ እንችላለን? የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማያምኑ መጋቢዎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ባለማስተማራቸው ጉባኤያቸውን እየዋሹ ነው ጉባኤው በስራ ላይ የተመሰረተ እምነትን እንዲተገብር ያደፋፍሩታል ተከታዮቻቸውም እነርሱን እንዲያገለግሉዋቸው ይጠይቁዋቸዋል ጉባኤያቸውን ነጻ ከማውጣት ርቀው በሕግ ስራ ሊያስሩዋቸው ይሻሉ።

እኛ ልናስተውል የሚገባን ነገር ቢኖር ራሱ አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር የመምጣቱን የሰውን ዘር ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የማንጻቱን እውነት ነው ሐጢያቶቻችንንና የሚጠብቀንን የሐጢያት ኩነኔ ያስወገደው ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙና ሞቱ ነው እምነታችንን በዚህ እውነት ላይ በማኖር መዳን የቻልነው ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐጢያቶቻችንና ከፍርዳችን ስላዳነን ነው ይህንን እውነት የደህንነት ብርሃን አድርገው በተቀበሉ ሰዎች አማንይነት እግዚአብሄር ሌሎች ነፍሳቶች እውነተኛ ደህንነታቸውን እንዲያገኙና ይህንንም ለመላው አለም እንዲሰብኩ አስችሎዋቸዋል።

አሁን ሁላችንም የእግዚአብሄር ልጆች መሆን የምንችለው አሁን እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሄር ልጅ መሆን የሚችለው እግዚአብሄር የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ስላጠናቀቀልን ነው ይህንን ዩኒቨርስ፣ በአይኖቻችንን የምናየውን ይህንን አለምና ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው እግዚአብሄር እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሄር ራሱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ለሐጢያተኞች የተሰጠውን ደህንነትም እንደዚሁ ፈጽሞዋል ይህ እንዴት ያለ ድንቅ የምስራች ነው? የአለም ብርሃን መሆን በመቻላችን እግዚአብሄርን በሚገባ ልናመሰግነው የምንችለው እንዴት ነው? በዚህ ምድር ላይ እንዴት ተወልደን የሰማይ ሰዎች መሆን እንደቻልን በትክክል ስናስብ በጣም እንገረማለን በጣምም አመስጋኞች እንሆናለን::

ከሐጢያት መዳናችን በአጋጣሚ የተገኘ አይደለም ነገር ግን የተገኘው እግዚአብሄር ዳግም እንድንወለድና የራሱ ሰዎች እንድንሆን ስላደረገን ነው ይህ የደህንነት እውነት የሆነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እንዲህ ያለ ትልቅና ግሩም እውነት ነው በዚህ አለም ላይ ከዚህ ወንጌል የሚበልጥ ድንቅ ነገር ሊኖር አይችልም::

እናንተ የሰማይ ሕዝብ መሆን የቻላችሁት እንዴት ነው? እግዚአብሄር የሰውን ዘር ዕጣ ፋንታ አቅዶ የራሱ ሕዝብ አደረጋቸው እኛም በዚህ ነገር እንገረማለን ለዚህም አመስጋኞች ነን ሰዎች ዩኒቨርስን ለመፍጠር ቢያቅዱ ኖሮ ሊያደርጉት ይችሉ ነበር? እኛ ሰዎች ይህንን ማድረግ አንችልም ነገር ግን እግዚአብሄር ዩኒቨርስን ከፈጠረበት ቅጽበት ጀምሮ በዚህ ምድር ላይ ምንም ሰው ሳይወለድ በፊትም እንኳን የሰው ዘር ከሐጢያት ዳግም እንዲወለድ ለሚያደርገው አላማ ሁሉን ነገር ፈጠረ::

ይህ እንዴት ያለ ድንቅ ዕቅድ ነው? እኔ ይህንን ወንጌል

እንዳስፋፋና እርሱን እንዳገለግለው ስለፈቀደልኝ ጌታን አመሰግነዋለሁ በዚህ ምድር ላይ ምንም አዲስ ነገር የለም ከዚህ ወንጌል ውጭ ለማንኛውም ሌላ ነገር መኖር በራሱ አሰልቺ ነው ነገር ግን በዚህ ምድር ላይ መልካም የሆነውን ነገር በምናስብበት ጊዜ ይህ መልካም ነገር እግዚአብሄር የራሱ ሕዝቦች ያደረገን መሆኑ ነው ይህ በየዕለቱ የምንደሰትበት፣ ባሰብነው ጊዜ ሁሉ የሚባርከንና በየዕለቱ ብናስበውም እንኳን እንከን የማይገኝበት እጅግ የሚያጽናና የምስራች ነው።

እግዚአብሄር የሰጠን እጅግ ክቡር ስጦታ ምንድነው?

እግዚአብሄር ከሰጠን ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል የተሻለ ሌላ የምስራች የለም በዚህ ከሰአት በኋላ ከወንድሞች ጋር ወንጌልን ለመስበክ ወጣሁ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለሐጢያተኞች ከመስበክ የተሻለ ምን ሌላ የምስራች አለ? ለሐጢያተኞች እግዚአብሄር ከሐጢያት ያዳናቸው ከመሆኑ ከዚህ የተሻለና የሚበልጥ ምን ስጦታ አለ? በሆስፒታል ውስጥ ለሚገኙ ሕመማኖች አንድ ሳጥን የፍራፍሬ ጭማቂ መስጠት እኛ እየሰበክነው ካለነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል ጋር ይወዳደራልን? በዚህ ምድር ላይ ለእኛ ለሰዎች ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል የሚበልጥ ሌላ ምንም ነገር የለም።

እግዚአብሄር እኛንና ሰማያትንና ምድርን ገና ከመጀመሪያው ፈጠረን እግዚአብሄር በሰማይ የራሱ ሕዝብ ሊያደርገን በዚህ ምድር ላይ ዳግም እንድንወለድ አደረገን ኢየሱስ ክርስቶስ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰጠን በእርሱ እንድናምንና ዳግም እንድንወለድም አደረገን የእግዚአብሄር ሕዝብም አድርጎ ለወጠን በዚህ አለም ላይ ከዚህ የሚበልጥ ሌላ

ምን የላቀ በረከት አለ? ስለዚህ እውነት ባሰብን ጊዜ ሁሉ የሚያጽናናና የሚያስደስት ነው።

ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ይልቅ ይበልጥ የተባረከ ወይም ይበልጥ የሚጽናና ምንም ነገር የለም ስለ ሰው ዘር ደህንነትና ስለ እግዚአብሄር ጸጋ ስናስብ እኛ ሰዎች ልናደርገው የምንችለው ምንም ነገር የለም ነገር ግን እኛ ልናደርገው የሚገባን ነገር ቢኖር ለእግዚአብሄር ምስጋናንና ክብርን መስጠት ብቻ ነው እኛ ሰዎች ልናደርግ የሚገባን ነገር ቢኖር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን እግዚአብሄር በሰጠን የተባረከ ጸጋ መደሰት ብቻ ነው።

እግዚአብሄር የሰጠው ደህንነት በጣም የተባረከ በጣም ድንቅ በጣም ታላቅና በጣም ክቡር ነው ስለዚህ በዚህ እውነት በማመን ለእርሱ ክብርን በመስጠትና እርሱን በማመስገን እግዚአብሄርን ከማወደስ በቀር ሌላ ልናደርገው የምንችለው ምንም ነገር የለም ምክንያቱም ይህ እውነት ፈጽሞ ሊካድ ወይም ሊወገዝ አይችልም ደህንነታችንን ካገኘን ጀምሮ ብዙ ጊዜ ባለፈ ቁጥር ይህ ደህንነት ምን ያህል ድንቅና ክቡር እንደሆነ በትክክል እንለማመዳለን ከእግዚአብሄር ዘንድ የመጣ ከዚህ የሚበልጥ የላቀ በረከት እንደሌለ እናምናለን ሰዎች ከውሸቦንብር፣ ከባዶነትና ከጨለማ ነጻ መውጣት የቻሉት እግዚአብሄር በሰጠን የሚያበራ የደህንነት ወንጌል አማካይነት ነው።

በዚህ አለም ነገሮች ፈጽሞ ሊሞላ የማይችለው የልብ ባዶነት

በደህንነት ብርሃን ባይሆን ኖሮ ፈጽሞ ከሐጢያቶቻችን ማምለጥ ባልቻልን ነበር አስተሳሰቦቻቸው ፈጽሞ ግራ የተጋቡ

ሐጢያተኞች የተወታተበውን የሐጢያቶቻቸውን ድውር እንዴት ማስተካከል ይችላሉ? የወደቀ ሰው እንዴት በራሱ ጥረት ሊመለስ ይችላል? ይህ የማይቻል ነው በዚህ ምድር ላይ ከተወለዱበት ቅጽበት ጀምሮ ሐጢያተኞች ሆነው የተወለዱ ሰዎች በራሳቸው ጥረት እንዴት ጻድቃን ሆነው ዳግም ሊወለዱ ይችላሉ? ይህ ተግባር በሰው የማይቻል ነው ይህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ጌታ በሰጠን እውነተኛ የደህንነት ብርሃን በማመን ብቻ ነው::

ሰዎች በተፈጥሮዋቸው የማይረኩ ሆነው ሳሉ እንዴት በራሳቸው ጥረቶች እርካታን ሊያገኙ ይችላሉ? ሐጢያተኞች እርካታን ማግኘት የሚችሉት ከየት ነው? ሐብት ሊያካናቸው ይችላልን? የሐብት መጠን እርካታን ሊያመጣ አይችልም ባለጠጋ ብትሆኑ በእርግጥ ትደሰታላችሁን? ልቦቻችሁ በዚያ ሁሉ ገንዘብ ይሞላሉን? እኔ ፈጽሞ ባለጠጋ ሰው ሆኜ አላውቅም ሆኜ ቢሆን እንኳን ባዶ ልቤን አይሞላልኝም ነበር ማንም ሰው ፈጽሞ ባዶ የሆነን ልብ መሙላት አይችልም እርካታ ሊኖር አይችልም::

ልቦቻችንን በእርካታ መሙላት የምንችለው እንዴት ነው? ይህ የማይቻል ነው በምን ልንሞላ እንችላለን? ልንረካ የምንችለው በምንድነው? በገንዘብ፣ በጸታ ግንኙነትና በተድላ? የኮምፕዩተር ጨዋታዎችን በመጫወት? በሚያስደስቱ የጊዜ ማሳለፊያዎች? በእግር ኳስ ጨዋታ?

ይህ የእግር ኳስ ጨዋታ ትልቅ ጨዋታ እንደሆነ የታወቀ ነው በጨዋታ የማሸነፍ ደስታ ታላቅ ስሜት ነው ሰራተኞቻችን አብረው በሚሆኑበት ጊዜ አዘውትረን ኳስ እንጫወታለን ተቀናቃኞቻችሁን አታላችሁ ግብ ለማስቆጠር ስትመቱና ተቀናቃኞቻችሁ እናንተን ለማቆም ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ ቢሞክሩም ኳስዋ በርራ መረብ ላይ ስታርፍ ማየት

ከልክ ያለፈ የደስታ ስሜትን ይሰጣል ሰዎች ከሚሰሙዋቸው እጅግ ታላላቅ ደስታዎች አንዱ በስፖርት የማሸነፍ ደስታ ነው ኬስ ጨዋታን ማየት በራሱ ያስደስተናል እኛ የምንደግፈው ቡድን ነጥብ ሲያስቆጥር ሁላችንም ከመጠን በላይ ተነቃቅተን በደስታ እናብዳለን አንዳንድ የቤዝቦል ደጋፊዎች ጨዋታቸውን አብዝተው ስለሚወዱ የሕይወታቸውን ግማሽ የሚያሳልፉት በኬስ ሜዳ ውስጥ ነው።

ነገር ግን እነዚህ ነገሮችም ቢሆኑ የሰዎችን ባዶ ልቦች መሙላት አይችሉም አንድ ወንድ የሚወዳትን ሴት ቢያስደስታት አትረካናምን? አትረካም በዚህም ውስጥ እውነተኛ እርካታ የለም «ሕይወቴንም መስጠት ቢሆን እንኳን የምወዳት ሴት የምትፈልገውን እያንዳንዱን ነገር አደርጋለሁ» ብሎ ቢያስብና በእርግጥም ሁሉን ነገር ቢያደርግላት ትረካለችን? ሕይወቱን በሙሉ ለእርስዋ አሳልፎ ቢሰጥ እርስዋ በእርግጥ ትረካለችን በልብዋ ውስጥ ያለው ባዶነት ይጠፋልን በቀሪው ሕይወቷ በሐሴትና በደስታ ተሞልታ ትኖራለችን? አትኖርም ምንም ያህል አብዝቶ ቢያፈቅራት ሁሌም ደስተኛ ሆና ልትኖር አትችልም ሰዎች በየጊዜው የላቀ እርካታን ይፈልጋሉ።

በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ንጉስ ሰሎሞን እጅግ የተቀናጣና የተንደላቀቀ ሕይወትን ኖሮዋል በርካታ እነጌዎችና ቁባቶች ነበሩት መኖሪያውና ሐብቱም እጅግ ድንቅ ነበር ነገር ግን በዚህ ምድር ላይ ባዶ ልቡን የሚሞላ ምንም ነገር አልነበረም በመክብብ ውስጥ «ሁሉም ከንቱ የከንቱም ከንቱ ነው ሁሉም ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነው» በማለት ሐዘኑን የገለጠው ለዚህ ነው በሌላ አነጋገር ሰው በሌላ ሰው ቢከበርና ቢወደስ እርካታ የለውም እግዚአብሄር እንዲህ ያለውን ልብ «ውሃን መያዝ የማይችሉ የተቀደዱ ጉድጓዶች» (ኤርምያስ 2:13) በማለት የገለጠው ለዚህ ነው።

አንዳንድ ሰዎች አደንዛዥ ዕፆችን የሚጠቀሙት ለምንድነው? አደንዛዥ ዕፆችን የሚጠቀሙት ባዶ ልቦቻቸውን መሙላት ስለማይችሉ ነው በዚህ አለም ላይ ሊገኝ የሚችል ማንኛውም ነገር ቢኖራቸውም እንኳን አሁንም እርካታን ሊያገኙ አይችሉም ልቦቻቸው ባዶ ናቸው በልቦቻቸው ውስጥ ምንም ነገር የለም ሰዎች በዚህ አለም ላይ በሚገኝ በማንኛውም ነገር ባዶ ልቦቻቸውን መሙላት አይችሉም እግዚአብሄር እንዳዳነን፣ ዳግም እንድንወለድ እንዳደረገን፣ የራሱ ሕዝቦች አድርጎ እንደለወጠንና ጻድቃን እንዳደረገን እውነቱን ከተቀበሉ ሰዎች በስተቀር ሌላ ማንም ሰው እርካታን ሊያገኝ አይችልም ሰው ዳግም ካልተወለደና ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ልቡ እስካልተቀበለ ድረስ የልቡን ባዶነት ፈጽሞ መሙላት አይችልም።

ባዶ ልብ ሊረካ የሚችለው እግዚአብሄር በሰጠው በዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሞላ ብቻ ነው እግዚአብሄር ልቦቻችንን ቅርጽ አልባና ባዶ ያደረጉትንና በጥልቁ ላይም ጨለማን ያኑሩትን ሐጢያቶቻችንን አስወግዶ በእነርሱ ፋንታ ልቦቻችንን አትረፍርፎ የሚሞላውን የእውነት ስጦታ ሰጠን ይህንን ስጦታ አትረፍርፎ በመስጠትም አዳነን ዳግም የተወለዱ ሰዎች በልቦቻቸው ውስጥ እርካታና እውነተኛ ደስታ አላቸው የልብ እውነተኛ እርካታ የነፍስ እርካታ ብቻ ነው በአንጻሩ ግን ዳግም ባልተወለዱ ሰዎች ልቦች ውስጥ ፈጽሞ ምን እርካታ ሊኖር አይችልም።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም የተወለዱ ሰዎች የረካ እምነት

እውነተኛ እርካታ ማግኘት የምንችለው እውነተኛ ብርሃን

በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በማመን ዳግም ስንወለድ ብቻ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግም እንድንወለድ ባደረገን በዚህ ደህንነት ማመን አለብን ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ የነፍሶቻችንን ችግሮች በሙሉ፣ የልቦቻችንን ባዶነትና ግራ የተጋቡትን አስተሳሰቦቻችንን መፍታት አንችልም እነዚህን ነገሮች ሁሉ መፍታት የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ደስተኞች ሊያደርገን የሚችል ሌላ ማንም የለም እውነተኛ እርካታን የሚሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ይህንና ያንን እናደርግ ይሆናል ባለጠጎችም እንሆን ይሆናል ነገር ግን አሁንም እርካታ የለም እውነተኛ እርካታ ከየትም ቦታ ሊገኝ አይችልም በመጨረሻ እርካታን ማግኘት የምንችለው ጌታን ስናገለግል ነው እርካታ የሚኖረው የእግዚአብሄርን ስራ ስንሰራ ነው የምንረካው በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምንና ዳግም ስንወለድ ነው በአጭሩ እርካታ የሚኖረው ከእርሱ ጋር ስንመላለስ ነው።

እግዚአብሄር «ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ» አለ ይህም በሰዎች ልቦች ጥልቅ ውስጥ ሐጢያት እንዳለ ያመላክታል ሰዎች ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ ያውቃሉን? የለም ሐጢያቶቻቸውን አያውቁም በሐጢያት ቢወለዱም የራሳቸውን ሐጢያቶች አያውቁም እናንተስ ታዲያ? ሐጢያቶቻችሁን ያወቃችሁት መቼ ነው? ወንጌልን በሰማችሁ ብርሃኑ በበራላችሁ ጊዜ ማን እንደሆናችሁ አውቃችኋልን? ወይስ ይህንን ያወቃችሁት ቀደም ብላችሁ ነው? በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመናችሁ በፊት ምናልባት ራሳችሁን የምትቆጥሩት ጥቂት ሐጢያቶችን እንደሰራችሁ አድርጋችሁ ሊሆን ይችላል መጽሐፍ ቅዱስ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ ሲል ሐጢያቶቹን በግልጽ የሚያውቅ ሰው የለም ማለቱ ነው።

ነገር ግን ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን ባያውቅም በዚህ አለም ላይ አስደንጋጭ ሐጢያቶችን ደጋግሞ የሚሰራ ከሆነ «እኔ ማለት ለካ እንዲህ ነኝ» በሚል ግንዛቤ ቢያንስ በትንሹም ቢሆን ራሱን ወደ ማወቅ ይመጣል ሰዎች እንደዚህ የሚያስቡት አስተሳሰቦቻቸውና ልቦቻቸው ግራ ስለተጋቡ ነው ሰው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እስካልተገናኘ ድረስ በውስጡ ሐጢያት እንዳለ በትክክል ሊገነዘብ አይችልም ዳግም እስካልተወለደ ድረስ ይህንን በእርግጠኝነት ሊያውቅ አይችልም ከእውነተኛው ብርሃን ጋር እስካልተገናኘ ድረስ የሚያውቅበት መንገድ የለም።

ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ ማለት ሰዎች ምን አይነት ሐጢያተኞች እንደሆኑ አያውቁም ማለት ነው እነርሱ ራሳቸው ሐጢያተኞች እንደሆኑና ለሲያል እንደታጩ አያውቁም ሰዎች ሐጢያቶቻቸውን ማወቅ አይችሉም የእውነት ብርሃን እስካልበራ ድረስ ፈጽመው ማውቅ አይችሉም ሁሉም ሰው ጥሩ እንደሆነ ያስባል ሰዎች ከመላዕክቶች ጋር እኩል እንደሆኑ ያስባሉ እኔም የሐጢያት ስርየትን ከመቀበሌ በፊት ራሴን ጥሩ ሰው አድርጌ እቆጥር ነበር።

ልጅ በነበርሁ ጊዜ በመንደሬ በጥሩ ልጅነቴ እታወቅ ነበር ጎረቤቶቼ ፈጽሞ የማላስቸግርና ሁሌም ጥሩ ሰው በጣም ጨዋና ተግባቢ ስለመሆኔ መናገር ያዘወትሩ ነበር ለአንድ አረጋዊ ሰው ጨዋነት የተሞላ ሰላምታን ማቅረብ ትልቅ ዋጋ ያሰጥ ነበር አንድ ልጅ አንድን አረጋዊ ሰው በጨዋነት ሰላምታ ከሰጠ 90 ነጥብ ያገኛል ቆሻሻን የሚያነሳና ሻንጣቸውን የሚይዛላቸው ጎረቤቱንም የሚረዳ ከሆነ 100 ነጥብ ያስቆጥራል ያኔ እኔ እንደዚህ አይነት ልጅ ነበርሁ መጥፎ ልጅ እንደሆንሁ ሲናገር የሰማሁት ሰው ፈጽሞ የለም።

ነገር ግን እያደግሁ ስሄድ ብዙ መጥፎ ነገሮችን ስላደረግሁ ሁሉንም ላስታውሳቸው አልችልም ሌሎች ልጆችን አስፈራራ

ነበር በትምህርት ቤት ውስጥም ሁሌ እጣላ ነበር እኔ ካልተጣላሁ ሌሎቹ ልጆች ተጣልተው እንደሆን አረጋግጥ ነበር ይህንን የማደርገው ስለተሰላችሁ ነበር ስለዚህ ጠብ ከጀመርሁ በኋላ ተመልካቾችን ሰብስቤ እመለከት ነበር ለጓደኞቼም «እያንዳንዳችሁ የሚበላ ነገር ማምጣት አለባችሁ ዛሬ አንድ ትልቅ ትዕይንት ይታያል ልትመጡ ይገባል እከሌና እከሌ እርስ በርሳቸው ይጣላሉ» እላቸዋለሁ ያን ጊዜ ጓደኞቼ ሌላውን ነገር ሁሉ የቤት ስራውንና ሁሉንም ነገር ትተው ይሰበሰባሉ።

ልክ እንደዚህ የቡድን ጠብን ማነሳሳትን ጨምሮ ብዙ መጥፎ ነገሮችን አድርጌአለሁ አሁን ስለዚያ ነገር ሳስብ በየጊዜው ብዙ መጥፎ ነገሮችን አደርግ ነበር ነገር ግን በውስጤ አንዳች ጥሩ ነገር ባይኖርም ጎረቤቶቼ በሙሉ ጥሩ ሰው እንደሆንሁ አድርገው ያመሰግኑኝ ነበር እኔ ራሴም ጥሩ ሰው እንደሆንሁ አስብ ነበር «እንደ እኔ ጥሩ የሆነ ሰው አለ?» ብዬ በማሰብ ከፍተኛ የሆነ የራስ ግምት ነበረኝ በእርግጥም እጅግ ጥሩ ሰው እንደሆንሁ አስብ ነበር።

«እርግጥ አንዳንድ ጊዜ ከጓደኞቼ ጋር እጣላለሁ ታዲያ ብጣላስ? ይህ እያንዳንዱ ጎረምሳ የሚያደርገው የተለመደ ነገር ነው ይህ እንዴት ሐጢያት ይሆናል? የሚደሙ አፍንጫችና ግምባሮች የዕድገቱ ክፍል ናቸው» ብዬ አስብ ነበር ሐጢያትን የሚያዋቅሩት መግደል፣ ምቀኝነት፣ ስርቆት፣ ስንፍናና ክፉ አሳቦች ቢሆኑም ያን ጊዜ ግን ሁሉም ጥሩ ነው ብዬ አስብ ነበር ሕጉን ስለማላውቅ ሐጢያትን አላውቅም ነበር።

በሌላ አነጋገር ሰው የእውነትን ብርሃን ከመቀበሉ በፊት ሐጢያትን ማወቅ አይችልም ታዲያ ሰዎች ሐጢያትን ማወቅ የሚችሉት እንዴት ነው?

በኮርያ ሳንግቺኦል የተባለ የታወቀ የቡዲስት መነኩሴ ነበር ይህ መነኩሴ ሐጢያተኛ እንደነበር የተናዘዘው ለመሞት

ሲያጣጥር ነበር መንፈሳዊ ንቃት ላይ ለመድረስ ሲል ራሱን ከውጭው አለም አግልሎ አንዴም ሳይተኛ ሁሌም ተቀምጦ ያለ ማቋረጥ ግድግዳው ላይ እንዳፈጠጠ ለአስር አመታት ያህል አእምሮውን ገርቷል የዚህ ሁሉ ጥረት ውጤት በርካታ ሰዎችን ያታለለ መሆኑን መገንዘቡ ነበር።

ከውጪ ያሉ ሰዎች መነኩሴው ራሱን ከቀረው አለም አግልሎ በትንሽ መቅደስ ውስጥ በዚህ መልኩ ለአስር አመታት ያህል መኖሩን ሲመለከቱ ሁሉም «ዋው! ይህ ሰው በሕይወት ያለ ቡድሃ ነው! በዚህ አለም ላይ እርሱን የሚመስል ማንም ሰው የለም እርሱ የዚህ ዘመን በሕይወት ያለ ቡድሃ ነው» በማለት ይደነቁ ነበር ሳንግቹኦል ይህንን ለአስር ረጅም አመታቶች ሰምቷል ነገር ግን መነኩሴው ራሱ «እኔ በሕይወት ያለሁ ቡድሃ አይደለሁም ብዙ ሴቶችን ተመኝቻለሁ በአስተሳሰቦቼም ሁሉንም አይነት የረከሱ ምግባሮችን አድርጌአለሁ ተኝቼ የማላውቅ ብመስልም በእርግጥም ተኝቻለሁ ምግብ የበላሁ ባልመስልም በእርግጥ በልቻለሁ» በማለት አምኖዋል ነገር ግን ተከታዮቹ ይህንን ሲሰሙ «እንዴት ያለ ታላቅ መነኩሴ ነው! በጣም ትሁት ስለሆነ ራሱን እንዲህ አዋረደ» በማለት ይበልጡኑ አመሰገኑት።

እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ይሰፍፍ ነበር» (ዘፍጥረት 1:2)* ማንም ሰው ቃሉን ከመስማቱ በፊት ሐጢያቶቹን አያውቅም ቃሉ እንዲህ ይላል *«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ»* በሌላ አነጋገር እውነተኛውን ማንነታችንን በትክክል ማወቅ የቻልነው፣ በልቦቻችን ውስጥም ታላላቅ ሐጢያቶች እንዳሉ የተገነዘብነውና በእግዚአብሄርም ፊት ለሲያል የታጨን ክፉ ሐጢያተኞች መሆናችንን የተረዳነው ኢየሱስ ክርስቶስን

በማወቅ፣ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል በመስማትና እግዚአብሄር በሰጠው ብርሃን አማካይነት ነው ብርሃንና የእግዚአብሄር ሕዝብ የሆንነው እንዲህ ነው በእርግጥም ይህ የእግዚአብሄር ጸጋ ነው ለዚህ የሚበልጥ ምን የላቀ ስጦታ አለ?

ከዚህ ክስተት የበለጠ ሌላ ምን የላቀ ክስተት አለ? እግዚአብሄር ሰዎችን የራሱ ሕዝብና ልጆቹ ካደረገበት ከዚህ ሁነት የሚበልጥ ምን አቢይ ሁነት አለ? እግዚአብሄር የሰው ስጋ የለበሰውን ልጁን ወደዚህ ምድር ላከው እንዲጠመቅ አደረገው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አስተሰረየ አነጻቸው የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ተሸከመ ወደ መስቀልም ወሰዳቸው በእኛ ፋንታም የሐጢያቶቻችንን ኩነኔ ተሸከመ እኛን ጻድቃን ካደረገን ከዚህ ፍጥረት የሚበልጥ ታላቅ ፍጥረት የለም።

እግዚአብሄር እንዲህ ያለውን ታላቅ ስጦታ ስለሰጠን ምስጋናዬን ሁሉ አቀርባለሁ። ✉

በነጻ የሚታደል መጽሐፍ ለመጠየቅ www.nlmission.com

አንደኛ ቀን: በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ

« ዘፍጥረት 1:1-5 »

«ምድረም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ እግዚአብሄርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው::»

በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሄር እኛን የፈጠረበት አላማ ተብራርቷል የስነ ሕንጻ ባለሙያዎች አንድ ሕንጻ ሲነድፉ ወይም ሥዕል ሰዓሊያን ስዕል በሚሰሩበት ጊዜ ፕሮጀክታቸውን በትክክል መስራት ከመጀመራቸው በፊት መሰራት ያለበትን ስራ አስቀድመው በአእምሮዋቸው ውስጥ ይጸንሱታል ልክ እንደዚሁ አምላኳችንም ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት የእኛን የሰዎችን ደህንነት በአእምሮው ውስጥ አቅዶት ነበር ይህንን አላማ በአእምሮው ይዞ አዳምንና ሔዋንን ፈጠረ እግዚአብሄር ሁላችንም ልናየውና ልናስተውለው የምንችለውን ምድራዊ ግዛት እንደ ምሳሌ በመጠቀም በስጋ አይኖቻችን የማይታየውን የሰማይ ግዛት ሊያብራራልን ፈለገ::

እግዚአብሄር ከአለም ፍጥረት በፊት ለእያንዳንዱ ሰው ልብ

የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመስጠት የሰውን ዘር ፈጽሞ ለማዳን ፈለገ ሰዎች ሁሉ ከአፈር ቢፈጠሩም ነፍሳቸውን ለመጥቀም ሲሉ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት መማርና ማወቅ አለባቸው ሰዎች የሰማይን ግዛት ሳያውቁ በመኖር የሚቀጥሉ ከሆነ የሚያጡት ምድራዊውን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ሰማያዊውንም ነገር ሁሉ ነው።

ነገር ግን በዘመኑ ክርስትና ውስጥ የዘፍጥረት መጽሐፍ የገለጠልንን መንፈሳዊውን የሰማይ ግዛት እንድናስተውል የሚያስችለንን ትምህርት ማግኘት አዳጋች ነው ለዚህም ምክንያቱ የክርስትና መሪዎች ከጨለማ ማምለጥ አለመቻላቸው ነው ምክንያቱም እነርሱ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል አያውቁትም አያምኑትምም ስለዚህ ክርስቲያኖች ነፍሳቸው በእግዚአብሄር የፍጥረት አላማ መሰረት እንድትፋፋ የሚፈልጉ ከሆነ በመጀመሪያ ሁሉም እግዚአብሄር የሰጠን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ትክክለኛ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል እስከ አሁን ድረስ የእግዚአብሄር ሕዝብ ስላልሆኑ መንፈሳዊዎቹን የሰማይ በረከቶች እንዲቀበሉ የሚያስችላቸውን እውነተኛ እምነት ማግኘት ያስፈልጋቸዋል።

በዚህም ቅጽበት እንኳን እግዚአብሄር በመንፈሳዊው የውሃና የመንፈስ ወንጌል መንግስቱን በሰዎች ልቦች ውስጥ እየሰራ ነው አሁን ሁሉም ሰው በእግዚአብሄር ቃል በማመን የሰማይን መንፈሳዊ ግዛት ማየት መቻል አለበት ይህ የሚቻለው ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ላይ ባላቸው እምነት ብቻ ነው ስለዚህ መንፈሳዊው የሰማይ ግዛት ላይ እንዲደርሱ ለማስቻል የውሃውንና የመንፈሱን የመንፈሱን ወንጌል ለሰው ሁሉ መስበክ አለብን።

እግዚአብሄር ይህንን መላውን ዩኒቨርስና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር የፈጠረበት አላማ የመንግስቱን ስጦታ ሊሰጠን ነው ከዚህ በተጨማሪም እግዚአብሄር በወንጌሉ ስልጣን አማካይነት ይህንን መንግስቱን ሊሰጠን በችሮታው ወሰነ በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የነፍሳችንን መዳን የገዛው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን መንግስተ ሰማይ መግባት እንችል ዘንድ ነው ጌታችን እያንዳንዱን አማኝ ለአንዱና ለመጨረሻ ከሐጢያቶቹ ሁሉ ማዳን ይችላል ምክንያቱም እርሱ ወደዚህ ምድር መጥቶ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው የውሃ ጥምቀት አማካይነት የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ እነዚህን የአለም ሐጢያቶች ተሸክሞም ደሙን አፈሰሰ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ።

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን መንፈሶቻችን የሰማይ ግዛት ላይ እንዲደርሱ አስችሎዋቸዋል እግዚአብሄር ለሰዎች ሁሉ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የመሻትን ፍላጎት ሰጥቶዋቸዋል ማለትም *«በልቦቻቸው ውስጥ ዘላለማዊነትን አስቀምጦዋል።» (መክብብ 3:11)*

እግዚአብሄር በሰማያትና በምድር ፍረጥት ታሪክ አማካይነት መንግስቱን በእኛም ልቦች ውስጥ መስራት ፈለገ የዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ «ምድርም ባዶ ነበረች» ሲል በሐጢያት ምክንያት የተወሳሰበውን የሰው የልብ ሁኔታ የሚያመላክት ነው እግዚአብሄር *«ብርሃን ይሁን»* ብሎዋል ይህ ምንባብ ሰው ሁሉ በዚህ አለም ላይ ከተወለደበት ቅጽበት ጀምሮ በልቡ ውስጥ በርካታ ሐጢያቶችን ይዞ የተወለደ ቢሆንም አሁን ዳግም መወለድ እንደሚችል ያመላክታል እግዚአብሄር ትክክለኛ ውን የደህንነት እውነት ብርሃን ሐጢያት ባለበት በእያንዳንዱ ሰው ላይ በማብራት ቀድሞውን በሐጢያት የተቀባዠሩትን ልቦቻችንን ማረም ፈለገ።

የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከማወቃችን በፊት ሁላችንም በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት ነበረብን ስለዚህ በልባችን ውስጥ የተቀባዠረው ነገር ምን እንደሆነ በራሳችን መረዳት አልቻልንም በሌላ አነጋገር ሰው ሁሉ በሐጢያቶቹ ምክንያት ከእግዚአብሄር እንደተለየ ሳያውቅ ይኖር ነበር ስለዚህ ሰዎች እውነተኛ ደህንነት ምን እንደሆነ ሊያውቁ ቀርቶ እውነተኛ በጎነት ምን እንደነበረና ክፋታቸውም ምን እንደሆነ ሊያውቁ አልቻሉም ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች አሁንም በውሸንብራቸው ውስጥ ስለዳከሩ እጅግ ትልቁን ክፋት እጅግ ትልቅ በጎነት ብለው ያሳስቱታል እግዚአብሄር «ምድርም ባዶ ነበረች» ያለው ለዚህ ነው የእያንዳንዱ ሰው ልብ ልክ እንደተወታተበ ድውር መሆኑን መናገሩ ነው፡፡

እያንዳንዱ ሰው በዚህ አለም ላይ ከተወለደበት ቅጽበት ጀምሮ ከስጋ ወላጆቹ ሁሉንም ሐጢያቶች ወርሶዋል (መዝሙረ ዳዊት 51፡5....*«እነሆ በአመጻ ተጸነስሁ እናቴም በሐጢያት ወለደችኝ»* ማርቆስ 7:21....*«ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ሳሳብ ዝሙት መስረቅ መግደል»*) መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ሁሉ ሁሌም ሐጢያት የሚሰራው በተፈጥሮው በሐጢያት ስለተወለደ እንደሆነ በግልጽ ይናገራል (ሮሜ 7፡17-20) ነገር ግን ሰው ሁሉ በአንዱ ሰው በአዳም ምክንያት በሐጢያት እንደተወለደ ሁሉ አሁን ሰው ሁሉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ጻድቅ ሰው ይሆናል፡፡

ሰው ሁሉ ያልገባው ነገሮች እነዚህ ናቸው

የእግዚአብሄር ቃል እያንዳንዱ ሰው ሐጢያትን ከአባቶቹ ስለወረሰ በተፈጥሮው የሐጢያት ክምር እንደሆነ ይናገራል

በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ሰው ሁሉ ከተወለደበት ቅጽበት ጀምሮ በሐጢያት ስለተወለደ በሕይወቱ ሁሉ ሐጢያትን ከመስራት ማምለጥ እንደማይችል ይናገራል።

ነገር ግን ብዙ ሰዎች እንዲህ ባሉ የሐጢያት ጉዳዮች ላይ ያሉዋቸው አስተሳሰቦች የተሳሳቱ ናቸው በተፈጥሮ ልቦቻቸው ጥሩና ጨዋ እንደሆኑና ሳያውቁም ሐጢያት የሚሰሩት ካሉባቸው ሁኔታዎች የተነሳ እንደሆነ ሁኔታዎቻቸው ምቹ ቢሆኑ ፈጽሞ ሐጢያት እንደማይሰሩ ያስባሉ ሆኖም መገንዘብ የሚገባን ነገር ቢኖር ሰዎች ሐጢያት የሚሰሩት ባሉባቸው አሳዛኝ ሁኔታዎች ምክንያት ሳይሆን በተፈጥሮ ሁሉም በሐጢያት የተወለዱ በመሆናቸው ምክንያት መሆኑን ነው የአዳምና የሔዋን ዘሮች በዚህ አለም ላይ ከተወለዱበት ቀን ጀምረው የቅድመ አያቶቻቸውን እያንዳንዱን ሐጢያት እንደወረሱና በሕይወታቸው ውስጥ ሁሌም ሐጢያትን የሚሰሩት ለዚህ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል ሐጢያቶቻችንን መገንዘብ የምንችለውና የሐጢያቶቻችንንም መሰረታዊ ባህርይ በትክክል መገንዘብ የምንችለው በእግዚአብሄር ቃል አማካይነት ብቻ ነው።

እግዚአብሄር ሰው ሁሉ *«የክፉ አድራጊዎች ዘር» (ኢሳይያስ 1:4)* እንደሆነ ተናግሮዋል የሰው የማንነት ዘር ከመጥፎ ዛፍ ጋር ሊመሳሰል ይችላል እያንዳንዱ ዛፍ እንደ ወገኑ ፍሬን ያፈራል የአፕል ዘሮች ተዘርተው ከዚያ ውስጥ ዛፍ በበቅል ይህ ዛፍ አፕሎችን ብቻ እንደሚያፈራ አያጠራጥርም የአፕል ዛፍ አፕሎችን ማፍራት ስለማይፈልግ ብቻ ይህንን ማስወገድ አይችልም የአፕል ዛፍ አፕሎችን ማፍራቱ የጊዜ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ ሁሉ ሰውም በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ሳለ ሐጢያትን የመስራቱ ነገር የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው በዚህ አለም ላይ ከተወለደበት

ቅጽበት ጀምሮ የተወለደው የሐጢያት ቁሶችን ይዞ ነው።

እግዚአብሄር ሰዎች ሁሉ በየጊዜው ሐጢያትን የሚሰሩት እያንዳንዱ ሰው ሲወለድ ጀምሮ በሐጢያት ስለተወለደ ነው እኛ ም በዚህ እውነት ልናምንና በልባችን ውስጥም ልንቀበለው ይገባናል እናንተ ልክ እንደ መንፈሳዊ እሾህ የሐጢያት ዘር ሆናችሁ ከተወለዳችሁ ሁሌም ሐጢያትን እየሰራችሁ ትኖራላችሁ እሾህ የሚያበቅለው እሾህን እንደሆነ ሁሉ ሐጢያተኖችም በሕይወታቸው ሐጢያትን እንደሚሰሩ በጣም ግልጽ ነው ኢየሱስ *«መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል።» (ማቴዎስ 7:17)*

እዚህ ላይ እኛ መገንዘብ የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር ሐጢያተኞች ሆነው የተወለዱ ሰዎች ማፍራት የሚችሉት ክፉ ፍሬዎችን ብቻ የመሆኑን ግልጽ እውነት ነው እያንዳንዱ ሰው ሲወለድ ከወላጆቹ ሐጢያተኛ ልብን ስለወረሰ ሌላ ነገር ቢመኝም ሁሌም ሐጢያትን ይሰራል በልቦቻችን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ልናምን የሚገባን ለዚህ ነው እውነቱ በእምነት ከሐጢያቶቻችን ሁሉ መንጻት የምንችለውና የእግዚአብሄር ሕዝብ የምንሆነው ያን ጊዜ ብቻ መሆኑን ነው ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ያስፈልገዋል።

መሰረታዊውን ተፈጥሮዋችሁን ተረድታችሁታልን? ብዙ ሰዎች «እኔ ማነኝ? ከየት መጣሁ ወዴትስ እየሄድሁ ነው?» ብለው ራሳቸውን ቢጠይቁም በዚህ አለም ላይ የሚኖር ማንም ሰው በራሱ ጥረት ለእነዚህ ጥያቄዎች አርኪ መልሶችን አላገኘ ም ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሊገኝ የሚችለው የእግዚአብሄርን ቃል በማመን ብቻ ነው ነገር ግን ሰዎች በራሳቸው የተወሳሰበ አስተውሎት መልስ ለማግኘት ስለሚሞክሩ በዚህ ድርጊታቸው የአእምሮዋቸውን ውሸጉብር አቀሳስበውታል ስለዚህ በርካታ

ፈላስፎች ግራ መጋባታቸውን ግልጽ ባልሆነ «የክህደተ እግዚአብሄር» እሳቤ ሸፋፍነውታል።

በምትሰሩዋቸው ሐጢያቶች ምክንያት እየተቅበዘበዛችሁ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ጠፍታችኋልን? ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ እናንተም ሐጢያተኛ ተፈጥሮዋችሁን መረዳት ስላቃታችሁ ሐጢያትን የሚያነጻውን እውነት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መቀበል አልቻላችሁም ኢየሱስ ለሰው ሁሉ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» ይላል እንደዚያም ሆኖ የእያንዳንዱ ሰው አስተሳሰቦች አሁንም ድረስ ግራ ተጋብተዋል ትክክለኛውና መልካሙ ነገር የቱ እንደሆነ መለየት ሳይችል ቀርቶ ግራ በተጋቡ እሴቶች ውስጥ እየኖረ ነው ስለዚህ በመጀመሪያ በእግዚአብሄር ፊት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ከሐጢያቶቻችን መንጻት አለብን ያንን ለማድረግም እኛው ራሳችን ሁላችንም በሐጢያት እንደተወለድን ከተጻፈው ቃል መረዳት አለብን የደህንነት እውነት በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመንና ልቦቻችንም ከሐጢያት መንጻት የሚችሉት ያን ጊዜ ብቻ ነው።

እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችንን ለማንጻት ለእያንዳንዳችን ሁለት ሕጎችን አስተምሮናል እግዚአብሄር ከእነዚህ ከሁለቱ ሕጎች ሐጢያቶቻችንን እንድንገነዘብ የሚያደርገንን የሕጉን ቃል የመጀመሪያ አደርጎ ሰጠን ሌላው ሕግ እግዚአብሄር እያንዳንዱ ሰው ከሐጢያቶቹ ሁሉ ነጻ እንዲሆን የሰጠው የመንፈስ ሕግ ነው በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሕጉን በመስጠት ሐጢያቶቻችን ምን እንደሆኑና እነዚህንም ሐጢያቶች ምን ያህል አጥብቆ እንደሚፈርድባቸው ሊያስተምረን ፈለገ።

እንደምናውቀው በሕጉ ውስጥ 613 የእግዚአብሄር ትዕዛዛት አሉ የእነዚህ መሰረትም አስርቱ ትዕዛዛት ናቸው ከእነዚህ

ከአስሩ ትዕዛዛት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አራት ትዕዛዛት ከእግዚአብሄር ጋር ባለን ግንኙነት ልንጠብቃቸው የሚገቡንን ተግባራቶች ይዘረዝራሉ በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በእነዚህ በመጀመሪያዎቹ አራት ትዕዛዛት «እኔ እናንተንና በዚህ ምድር ላይ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ፈጥሬአለሁ ስለዚህ በዚህ ምድር ላይ ላለው ነገር መስገድና እርሱንም ማገልገል የለባችሁም» ብሎ ይነግረናል ከአምስተኛው እስከ አስረኛው ድረስ ያሉት ቀሪዎቹ ስድስት ትዕዛዛት ሰዎች እርስ በርሳቸው ባላቸው ግንኙነቶች ሊጠብቁዋቸው የሚገቡ ስርአቶች ናቸው ስለዚህ እግዚአብሄር አስርቱን ትዕዛዛት ሰጠን ነገር ግን ማንም ሰው ይህንን ሕግ ያለ እንከን መጠበቅ አልቻለም።

ብንቀበለውም ባንቀበለውም እግዚአብሄር ፈጥሮናል እግዚአብሄር ይወደናል እግዚአብሄር ጌታችንና ንጉሳችን ነው ስለዚህ እግዚአብሄር «በፊቴ ሌሎች አማልክት አይሁኑላችሁ» ቢል ትክክል ነው የፈጠረን እግዚአብሄር ስለሆነ እርሱን መታዘዛችን የግድ ነው በዚህ ቃል መሰረት ካላመንንና እርሱንም ካልታዘዝን ይህ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት ይሆናል ነገር ግን እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ፈጣሪ መሆኑን በትክክል መረዳት ተስኖናል እግዚአብሄር የሰውን ዘር እርሱን ብቻ እንዲያገለግል እርሱን ብቻ እንዲታዘዝና እንዲያምን ቢያዘውም ሰዎች ከእግዚአብሄር ይልቅ ሌላ አንዳች ነግን በማመንና በማገልገል ይህንን ማድረግ ተስኖዋቸዋል።

ስለዚህ በሐጢያት የወደቁ ሰዎች ሐጢያቶቻቸውን የሚያውቁባቸው የእግዚአብሄር ትዕዛዛቶች ያስፈልጉዋቸዋል በእግዚአብሄር ትዕዛዛት ቃል አማካይነትም በሕይወታችን በእግዚአብሄር ፊት ምን ያህል ሐጢያቶችን መገንዘብ ችለናል እንዲህ ሐጢያቶቻቸውን ያመኑ ሰዎችንም እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሊያነጻቸው ሕዝቡ

ሊያደርጋቸውና በእነርሱም መንግስቱን ሊመሰርት ፈለገ እግዚአብሄር ለእያንዳንዱ ሰው ሕጉን የደነገገው የሰውን ዘር ከሐጢያቶቹ ነጻ ለማውጣት ለመባረክና የራሱ ሕዝብ ለማድረግ ነው ሁላችንም ይህንን መገንዘባችንና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመናችን ፈጽሞ አስፈላጊ ነው።

በሌላ በኩል የእግዚአብሄርን ቃል የማናውቅ ከሆነ ለዘላለም ሐጢያቶቻችንን መቀበል አንችልም ለምን? ምክንያቱም ያለ እግዚአብሄር ሕግ ሐጢያቶቻችን ሊታወቁ አይችሉምና የበጎና የክፉ ፍጹም የሆነ መለኪያ የሆነው የእግዚአብሄር ሕግ ባይኖር መተላለፎችም አይኖሩም ነበር። (ሮሜ 4፡15፤ 7፡8)

ራሳችንን በራሳችን መንገድ ጠቢብ አድርገን እናስበዋለን እያንዳንዳችንም የራሳችን የመገምገሚያ ስርአት አለን «ይህ ጥሩ ነው ያ መጥፎ ነው ይህ ትክክል ነው ያ ስህተት ነው» የሚል የአስተሳሰብ ልማድ አለን ይህንን የምናደርገው ግን በራሳችን መንገድና ለራሳችን በሚስማማ መልኩ ነው ስለዚህ የሚጠቅመን ነገር ጥሩ የሚጎዳን ነገር ደግሞ መጥፎ እንደሆነ እንደመድማለን ነገር ግን እንዲህ ያለው ብያኔ ከራሳችንና ከራስ ወዳድነታችን የመነጨ ነው።

እኛ ሰዎች በራሳችን መንገድ ምንም ሕግ የመደንገግ ችሎታ የለንም ምክንያቱም እኛ እግዚአብሄር የደነገገውን ሕግ መታዘዝ የሚገባን ፍጡራኖች ነንና እግዚአብሄር ሕጉን ለሁላችንም ሰጥቶዋል ይህ የእግዚአብሄር ሕግ «በፊቴ ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ብሎ አዞናል ልቦቻችን የእግዚአብሄርን ሕግ መቀበልና መታዘዝ የሚገባቸው ለዚህ ነው።

የእግዚአብሄርን ሕግ የምንቀበል ከሆነ የሌሎችን ንብረት መመኘት ሐጢያት ነው ሌሎች ያሉዋቸውን ነገሮች ተመኝታችሁ አታውቁምን? ሌሎች ያላቸውንስ ለማግኘት ፈልጋችሁ አታውቁምን? ሁላችንም የባልንጀራችንን ሚስት

ወይም ባል፣ ሐብት ወይም መኪና እንመኛለን ከዚህም በላይ እነዚህን ነገሮች በልቦቻችንን መመኘት ብቻ ሳይሆን የተመኘ ናቸውን ነገሮች በሙሉ የራሳችን ለማድረግ መሳምጀታችንን በተግባር እንገልጠዋለን እነዚህ አሳቦችና ምግባሮች ሐጢያቶች እንደሆኑ እግዚአብሄር ግልጽ አድርጓል በባልንጀራችን ላይ በሐሰት መመስከርም እንደዚሁ ሐጢያት መሆኑን እግዚአብሄር ነግሮናል ስርቆትም ሐጢያት እንደሆነ ተናግሮዋል ማመንዘርም ልክ እንደ መግደል ሁሉ ሐጢያት እንደሆነ ተናግሮዋል ወላጆችን አለማክበርም ሐጢያት እንደሆነ ተናግሮዋል ከእግዚአብሄር ውጪ ለማንኛውም ሌላ ነገር መስገድም እንደዚሁ የሚያጠፋን ሐጢያት እንደሆነ ተናግሮዋል።

የእግዚአብሄርን ሕግ በልቦቻችን ውስጥ ከተቀበልንና ምግባሮቻችንን በዚህ ሕግ ላይ ተመስርተን ከመረመርን ሁላችንም በእግዚአብሄር ፊት ብዙ ሐጢያቶችን እንደሰራን እንገነዘባለን ከተወለድንበት ቅጽበት ጀምሮ ሐጢያተኞች ሆነን ተወልደናል ከመግደል ጀምሮ እስከ ምንዝርናና ስርቆት ድረስ ያሉትን በወላጆቻችን ልቦች ውስጥ የነበሩ ሐጢያቶችንም ሁሉ ወርሰናል ሁላችንም በልባችን ውስጥ መግደል፣ ማመንዘርና መስረቅ ስላለ እግዚአብሄር «እናንተ ሐጢያተኞች ናችሁ» ብል ከሚገባው በላይ ትክክል ነው ነገር ግን ሰዎች ከመጀመሪያውም እነዚህን ሐጢያቶች በልቦቻቸው ውስጥ ይዘው የተወለዱ ቢሆኑም ይህንን ራሳቸው አያውቁትም።

እኛ ሰዎች በልቦቻችን ውስጥ የመግደል ፍላጎት ያለን ብንሆንም እግዚአብሄር ይህንን እንዳልተረዳን ተመልክቷል ስለዚህ እግዚአብሄር እንዳንገድል የሚያዝዘንን ሕጉን በመስጠት ነፍሰ ገዳዮች እንደሆንን እንድናውቅ አስቻለን በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ሕግን የሰጠን እንዲህ ያለን «የሐጢያት ክምሮች» እንደሆንን ሊያስተምረን ነው ሁሉም ሰው በእግዚአብሄር ፊት

ሐጢያተኛ ነው የሰው ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ያለም ይሁን ዝቅ ያለ ሁሉም ሰው በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኛ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሁላችንም ሐጢያተኞች እንደሆንን ግልጽ አድርጓል።

እግዚአብሄር የፈጠራቸው የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት አዳምና ሔዋን ነበሩ እነርሱ ግን በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት ሰሩ በዲያብሎስ ፈተና ተታልለው እግዚአብሄርን ከዱት በዚህ ምክንያት የአዳምና የሔዋን ዘሮች ሆነው የተወለዱ ሰዎች በሙሉ አያቶቻቸው በእግዚአብሄር ፊት የነበሩዋቸውን እነዚያኑ ሐጢያተኛ ፍላጎቶችና ባህርይ ይዘው ተወልደዋል ሁሉም ሰው በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኛ የሆነው ለዚህ ነው።

እግዚአብሄር በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ «ምድርም ባዶ ነበረች» ሲል እኛ ራሳችን ሐጢያተኞች እንደነበርን አለመረዳታችንን እየጠቆመ ነበር ሰዎች ራሳቸውን ባለማወቃቸው እግዚአብሄር «እናንተ መተላለፎች ያሉባችሁ ሐጢያተኞች ናችሁ» ማለቱ ነበር ስለዚህ በመጀመሪያ ስለ እግዚአብሄር ሕግ መማር አለብን በዚህ ሕግ አማካይነትም በእግዚአብሄር ፊት ታላላቅ ሐጢያተኞች እንደነበርን መረዳት ይኖርብናል ሰዎች ሁሉ ልቦቻቸው ምን ያህል ግራ የተጋቡ እንደሆኑ መረዳት የሚችሉትና አንድ እርምጃ ወደፊት በመሄድም የደህንነት እውነት በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሚድኑት በዚህ መልክ ነው ሁላችንም «ሰዎች ሐጢያት የሚሰሩት ከመጀመሪያውም በሐጢያት ስለተወለዱ እንደሆነ» በትክክል ማወቅ አለብን አእምሮዋችንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበል እንደሚኖርብን በግልጽ መረዳት አለበት።

በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች እንደሆናችሁ ታምናላችሁን? ብዙ ሰዎች ግን ሐጢያተኛውን ተፈጥሮዋቸውንም አይገነዘቡም ፍጹም ስለሆነው የእግዚአብሄር

በጎነት የሚያስተምራቸውንም ሕግ አያውቁም ስለዚህ ታላላቅ ሐጢያተኞች መሆናቸውን ፈጽመው ሳያውቁ ትልቅ ውሸቦንብር ውስጥ ወድቀዋል ሆኖም እግዚአብሄር ሰዎች የሚሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሕሊናቸው ጽላትና በእግዚአብሄር ዙፋን ፊት ባለው የምግባሮች መጽሐፍ ላይ ጽፎዋቸዋል የፍርዱን ቀን መምጣትም እየጠበቀ ነው በሰው ወይም በእግዚአብሄር ፊት በድብቅ ወይም በግልጽ ሐጢያት ሰርታችሁ ቢሆንም እንኳን ሕሊናችሁን የሚረብሽ አንዳች ሐጢያት ሰርታችሁ ከሆነ እግዚአብሄር «እነዚህን ሐጢያቶች ሰርታችኋል» ብሎ በመመዝገብ ሁሉንም በሕሊናችሁ ጽላት ላይ ጽፎታል (ኤርምያስ 17፡1) የእግዚአብሄርን ሕግ ብናውቅም ባናውቅም እግዚአብሄር አሁንም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በልቦቻችን ጽላት ላይ ይጽፋቸዋል ከዚህም በላይ መተላለፎቻችንን ብንረሳ እንኳን ሐጢያቶቻችን በሙሉ በምግባር መጽሐፍ ላይ ስለተጻፉ ከእነዚህ ሐጢያቶች ኩነኔ የምናመልጥበት መንገድ የለም ሐጢያት ያለባቸው ሰዎች በንጹህ ሕሊና ፈጽሞ «ሐጢያት የለብኝም» ማለት የማይችሉት ለዚህ ነው በተቃራኒው ግን «እኔ ሐጢያተኛ ነኝ» ብለው በመናዘዝ ራሳቸውን ይኮንናሉ።

እግዚአብሄር ሰው ሁሉ የሰራቸውን ሐጢያቶች በሙሉ በልቡ ጽላት ላይ ስለጻፋቸው ማንም ሰው ሐጢያተኛ መሆኑን መንድ አይችልም ለምሳሌ ያህል ሳናውቅ ሰረቅን እንበል ይህንንም ፈጸሞ ረሳን እግዚአብሄር ግን ለሕሊናችን «ሰርቀሃል» ብሎ ይናገራል ይህንንም በልቦቻችን ጽላቶች ላይ ይጽፈዋል ይህ ስርቆትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ሌላውን ሁሉ ነገር ይመለከታል የመግደል ፍላጎት ከነበረን ወይም ይህንን ፍላጎት ከተገበርነው ይህ ሐጢያት በሌሎች ሰዎች ቢታይም ባይታይም እግዚአብሄር በልቦቻችን ጽላቶች ላይ ይጽፈውና በሕሊናችን ይወቅሰናል ስለዚህ ማናችንም ስለ መተላለፎቻችን ባናውቅም

እነዚህ ሐጢያቶች በሕሊናችን ላይ ስለተጻፉ «እነዚህን ሐጢያቶች ሰርቻለሁ» ብለን ለእግዚአብሄር ከመናዘዝና ከማመን በቀር ምርጫ የለንም።

እኛ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር ሐጢያተኝነታችንን ለእግዚአብሄር ማመንና የሕጉን ጥብቅነት መገንዘብ ብቻ ነው «እኔ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኛ ነኝ» ብለን መናዘዝ ብቻ ይኖርብናል እግዚአብሄር ይህንን ከእኛ የሚጠይቀው ለምንድነው? እኛ ሐጢያተኞች መሆናችንን ስናምን መስማት የሚፈልገው ለምንድነው? እግዚአብሄር አስቀድሞ «እኔ ሐጢያተኛ ነኝ» ብለን ስንናዘዝ መስማት የሚፈልገው ሐጢያቶቻችንን ለመደምሰስ ነው ይህም ለባሮቹ የምህረትን ስጦታ ከሚሰጥ ንጉስ ጋር ተመሳሳይ ነው ስጦታ ዋጋ ያለው የሚሆነው ተቀባዩ አጥብቆ የሚፈልገው ነገር ሲሆን ነው ተቀባዩ ያለዚህ ስጦታ ሌላ ነገር ማግኘት የሚችል ከሆነ ለዚህ ስጦታ አመስጋኝ አይሆንም እግዚአብሄር የደህንነት ጸጋውን መስጠት የሚፈልገው በእጅጉ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ነው።

ነገር ግን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከማወቃችን በፊት ምን አይነት ሐጢያት እንደሰራን በእግዚአብሄር ቃል አማካይነት በትክክል መገንዘብ አንችልም እኔም ራሴ ከዚህ ቀደም ልክ እንደዚህ ነበርሁ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ከማመኔና ኢየሱስ ከማወቄ በፊት ሐጢያቶቼን ያን ያህል በደምብ አላውቃቸውም ነበር እኛ ሐጢያቶቻችንን ለማጽደቅና ሐጢያተኛ ማንነታችን ለመከላከል ደመነፍሳዊ ዝንባሌ አለን ሐጢያቶቻችንንም መደበቅ እንወዳለን።

ነገር ግን ሐጢያቶቻችንን ከእግዚአብሄር ለመደበቅ ስንሞክር ልቦቻችን ይቸገራሉ በአንጻሩ እነዚህን ሐጢያቶች እንደሰራን ለእግዚአብሄር ስናምንና ሐጢያት የተሞሉትን ልቦናዎቻችንን ስንቀበል በመጨረሻ ልቦቻችን እርካታን ያገኛሉ

ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሐጢያቶቻችንን በደመሰሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ አማካይነት እውነተኛ ደህንነት ላይ መድረስ የሚችሉት በእግዚአብሄር ፊት እውነተኛ ውን ማንነታቸውን በታማኝነት የሚገነዘቡ ሰዎች ናቸው።

መላው የሰው ዘር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን ያነጻውን እውነት መገንዘብ አለባቸው

እያንዳንዳችን እግዚአብሄር የሰውን ዘር ሐጢያቶች እንዴት እንደደመሰሰ በትክክል ማወቅ አለብን ሁላችንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለብን ጌታ በመጠመቅ ሐጢያቶቻችንን ለአንዴና ለመጨረሻ እንደወሰደና በመሰቀልም በእኛ ፋንታ የእነዚህን ሐጢያቶች ኩነኔ በሙሉ እንደተሸከመ ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባናል የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ብንሰማና በልቦቻችን ብናምን ሐጢያቶቻችን በሙሉ ይነጻሉ እኛ ም እንድናለን።

ሕይወታችን በዚህ ምድር ላይ ብቻ አያቆምም እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ሳላችሁ የምትሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ሊደመስስ እናንተንም ሐጢያት አልባ ሊያደርጋችሁ መንግስተ ሰማይ ሊወስዳችሁና ከእናንተም ጋር ለዘላለም ሊኖር ፈለገ ስለዚህ ከአለም ፍጥረት በፊትም ይህንኑ አቀደ ጊዜ ሲደርስም አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመላክ በዕቅዱ መሰረት ሁሉንም ፈጸመ ነገር ግን በእኛ በኩል መዳን የምንችለው እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችንን እንደደመሰ ስናምንና ስንቀበል ብቻ ነው ሁላችንም ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን ማመን የሚገባን ለዚህ ነው ስለዚህ ሁላችንም በእግዚአብሄር ፊት

በግልጽ በሐጢያት ስለተወለድንና እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስም ሐጢያት የምንሰራ ሐጢያተኞች ስለሆንን የእግዚአብሄርን ጸጋና ፍቅር መቀበል የምንችለው ይህንን ስናምንና እምነታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስናኖር ብቻ ነው።

«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ»

እግዚአብሄር ከአለም ፍጥረት በፊት ሰዎችን ለመፍጠርና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ዳግም እንዲወለዱ ለማድረግ አቀደ እግዚአብሄር በመጀመሪያው የፍጥረት ቀኑ ሁለት ነገሮችን አደረገ በመጀመሪያ የሰማይንና የምድርን ግዛት ፈጠረ ሁለተኛ ብርሃንን ፈጠረ እግዚአብሄርን ሰውን ፈጠረ ነገር ግን እርሱን መፍጠር ብቻ አይደለም ነገር ግን እኛን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናንምነውን አማኞች የራሱ ልጆች ለማድረግ አላማ መላውን ዩኒቨርስ በመፍጠር የደህንነትንም ብርሃን ሰጠው።

አመኔታዎቻችንና እምነታችን መጀመር ያለባቸው ለሚከተለው ጥያቄ መልሱን በማወቅ ነው «እግዚአብሄር የሰውን ዘር የፈጠረበት አላማ ምንድነው?» እግዚአብሄር ከእኛ የሚፈልገው የእምነት አይነት ምን እንደሆነ ማወቅ የምንችለው ያን ጊዜ ሠቻ ነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ከእግዚአብሄር ጋር መገናኘት የምንችለውም ያን ጊዜ ብቻ ነው እግዚአብሄር ይህንን መላውን ዩኒቨርስና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ሲፈጥር አላማው የተቀመጠው እንዴት ነበር? የፍጥረት አላማው እኛን ከሐጢያት ዳግም እንድንወለድና የእርሱ ሕዝቦች እንድንሆን ማድረግ ነበር እኛን የእርሱ ሕዝብ የማድረጉንም ይህ ተግባር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጸመው እግዚአብሄር መላውን ዩኒቨርስና የሰውን ዘር የፈጠረበት

የመጀመሪያው አላማ ሰዎች በዚህ ምድር ላይ እንዲወለዱ ማድረግ በእነርሱም ላይ የደህንነት ብርሃን ማብራትና በዚህም የእግዚአብሄር ሕዝቦች አድርጎ ፍጹማን ማድረግ ነበር፡፡

እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ እግዚአብሄርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን::» (ዘፍጥረት 1:3-5)*

እግዚአብሄር ሊያደርግልን የፈለገው የመጀመሪያው ነገር እዚህ በዘፍጥረት 1:1-5 ላይ ተጽፎዋል አንድ ግንበኛ ቤትን የሚገነባው ለአላማ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሄርም መላውን ዩኒቨርስና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር የፈጠረው በራሱ ዕቅድ መሰረት ነው ይህ ዕቅድ ምን ነበር? የሰውን ዘር የራሱ ሕዝብ ለማድረግ ነበር ይህንንም አድርጓል፡፡

ወደ እግዚአብሄር ከመሄዳችን በፊት ገናም በዚህ ምድር ላይ እየኖርን ሳለን በልቦቻችን ውስጥ የደህንነትን ብርሃን መቀበል ያለብን ለዚህ ነው እግዚአብሄር ለምን ሰውን እንደፈጠረና እንዴት በኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነታችንን እንዳቀደ በትክክል ማወቃችን አስፈላጊ ነው ሁላችንም ይህንን ማመንና መቀበል አለብን እግዚአብሄር ለምን ፈጠረን? እግዚአብሄር እኛን የፈጠረበት አላማ ምንድነው? እግዚአብሄር «ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ» ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ መረዳት ያስፈልገናል ይህ እግዚአብሄር በእውነት ብርሃን ሐጢያተኞችን ፃድቃን ማድረጉ ነበር፡፡

ዘፍጥረት 1:1 እንዲህ ይላል *«በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»* ይህ ምንባብ እግዚአብሄር የስጋ አይኖቻችን የሚያዩትን መላውን ዩኒቨርስና እያንዳንዱን ነገር

እንደፈጠረ የሚያብራራ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሄር መንፈሳዊውን የሰማይ ግዛትም እንደሰጠን ያመላክታል በዚህ ዩኒቨርስ ላይ የተወለዱ ፍጥረታቶች በሙሉ የእግዚአብሄርን ዕቅድ ማወቅ አለባቸው በዩኒቨርስ ያለው እያንዳንዱ ነገር በእግዚአብሄር እንደተፈጠረ ሁሉ ሐጢያተኞችም ሁሉ እንደዚሁ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት እንደገና ተፈጥረው ጻድቃን ሆነዋል።

አሁንም እንኳን አምላካችን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ሐጢያተኞች ጻድቃን እንዲሆኑ ለመምራት እየሰራ ነው ስለዚህ እግዚአብሄር የፍጥረታቶችን ግዛት ቢፈጥርም የፍረቱ ሁሉ ዋና አላማ እኛን ልጆቹ ማድረግ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የፍጥረታቶችን ግዛት የፈጠረው የእርሱ ሕዝብ የመሆንን በረከት ሊሰጠን ነው የእግዚአብሄር ፈቃድ እናንተንና እኔን የእርሱ ሕዝብ ማድረግ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ «በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ማለቱን ስናነብ እግዚአብሄር ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ለምን እንደፈጠረ መገንዘብ አለብን እግዚአብሄር ይህንን ዩኒቨርስና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር የፈጠረው የሰውን ዘር ለመፍጠርና ሰዎችንም ብርሃን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን በማንጻትና የብርሃን ልጆች እንዲሆኑ አድርጎ በመለወጥ የራሱ ሕዝቦች ለማድረግ አላማ ነው መገንዘብና ማመን ያለብን ለዚህ ነው እግዚአብሄር መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው እኛን ለማዳን አላማ ለደህንነታችን ነው።

እግዚአብሄር ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ፈጠረ ይህ እውነት እነርሱን የፈጠራቸው ከሐጢያተኞች ስፍራ ወደ ጻድቃን ስፍራ ሊወስዳቸው እንደሆነ ይነግረናል አሁን እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመንና እርሱንም

በመቀበል ጻድቃን ሰዎች ብንሆንም እናንተና እኔ እዚህ ደረጃ ላይ እስከምንደርስ ድረስ ሁላችንም ሐጢያተኞች ነበርን ይህንን እውነት ያስተማረን የእግዚአብሄር ቃል በጣም አስገራሚና አስደናቂ ነው።

ራሳችንን ስንመረምር ሁላችንም እንዴት ዋጋ እንደሌለንና ጭብጥ አፈሮች እንደሆንን እናያለን ነገር ግን እንደ እኛ ላሉ የማይረቡ ሰዎች እግዚአብሄር ልጆቹ ሊያደርገን እነዚህን ክቡር የሆኑ የሰማይና የምድር ግዛቶች ፈጠረልን ይህንን ስናስብ እንዲህ በማለት የመሰከረውን ጳውሎስን እናስበዋለን *«የእግዚአብሄር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው ለመንገዱም ፍለጋ የለውም» (ሮሜ 11:33) «ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን።» (ሮሜ 11:36)*

ሐዋርያው ጳውሎስ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለዚህ አለም በሰበከና የእግዚአብሄርን ስራ በሰራ ጊዜ እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን የፈቃዱን ታላቅነት ተረዳ ሁሌም በዚህ ይደነቅ ነበር እግዚአብሄር ሐጢያተኞችን ጻድቃን ለማድረግና የእርሱ ልጆች አድርጎ ሊለውጣቸው የሰማይን ግዛት የፈጠረላቸው ሰዎች ምን ቢሆኑ ነው? የብርሃን መልአክ የሆነው ሉሲፈር እግዚአብሄርን በተቃወመው ጊዜ እግዚአብሄር ወደ ሲያል ጣለው እንጂ ይቅርታን አልሰጠውም ለሰዎች ግን እግዚአብሄር የአምላክ የደህንነት ስጦታ በሆነው የእውነት ቃል በማመን ልጆቹ እንዲሆኑ የሚፈቅድላቸውን ዕቅድ አቀደ ይህንንም ዕቅድ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈጸመው።

እግዚአብሄር እንዲህ ብሎናል *«እግዚአብሄር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐንስ 3:16)* ስለዚህ እግዚአብሄር ብርሃን ይሁን ሲል ብርሃን ሆነ እግዚአብሄርም ይህንን ብርሃን በዚህ አለም ላይ አበራ

እግዚአብሄር ይህንን ብርሃን ለሚታዘዙ ሰዎች የእርሱ ሕዝብ የሚሆኑበትን ጸጋ ፈቅዶላቸዋል የእግዚአብሄርን ብርሃን በማይቀበሉ ሰዎች ላይም በብያኔው መሰረት ይፈርድባቸዋል እግዚአብሄር በችሮታው ይህንን ክቡር ስራ የሰራልን በእውነት ብርሃን አማካይነት እስካላወቅነው ድረስ ልናስተውለው ስለማንችል ነው።

እኔ የሐጢያቶቼን ስርየት ከጌታ ስለተቀበልሁና ሕይወነን እየኖርሁ ስለሆነ እግዚአብሄርን ከማመስገን በቀር ሌላ የማደርገው ምንም ነገር የለም ምክንያቱም እርሱ ለእኛ ያለው ዕቅድ በጣል የላቀ ታላቅና ዕጹብ ድንቅ ነው በእግዚአብሄር ፊት የምንመካበት ምንም ነገር ስለሌለን እኛ ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር በእምነታችን አማካይነት እርሱን ማመስገን ብቻ ነው እግዚአብሄር ይህንን ዩኒቨርስ የፈጠረው ለሰው ዘር ድንቅ የሆነ ዕቅድ ስለነበረው እንደሆነ አምናለሁ እናንተም ይህንን ታምናላችሁን? በልቦቻችን ውስጥ በእግዚአብሄር ዕቅድ ማመን የምንችለው በውስጣችን መንፈስ ቅዱስ ስላለ ነው እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ደህንነታችንን አቀደ የፈጠረንም ለዚሁ አላማ ነው።

እግዚአብሄር የደህንነትን ብርሃን አብርቶልናል የደህንነትን ብርሃን ያበራልን ይህ አምላክ የሸክላ ዕቃዎቻችን በሆኑት በእናንተና በእኔ ልቦች ውስጥ መዛግብቶችን አስቀምጦዋል በእግዚአብሄር ቃል ሁሉ ማመን የምንችለውና ከእርሱ ጋር ተባብረን የምንሰራው በልቦቻችን ውስጥ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል ስላለን ነው በስጋዊ መንገድ የምናስብ ከሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልናስተውላቸው የማንችላቸው ብዙ ክፍሎች አሉ ነገር ግን በልቦቻችን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስላለ የእግዚአብሄርን ስራ መረዳትና ማመን እንችላለን።

እግዚአብሄር በዚህ የቅዱሳት መጽሐፍት ቃል አማካይነት

ሊነግረን እየሞከረ ያለውን ነገር መረዳት ያስፈልገናል እኛ በእግዚአብሄር እውነት ማመንና የእርሱ ሕዝቦች መሆን የምንፈልግ ከሆነ እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን እቅድና ያከናወነውን ስራ መገንዘብ አለብን የዘመኑ ክርስቲያኖች ብዙዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ያጠናሉ ነገር ግን የእግዚአብሄርን ቃል ማጥናትና መመርመር ስለ መጽሐፍ በዕውቀት ደረጃ ከመማርና ምንባቦቹን ከማስታወስም ይበልጣል የእግዚአብሄር ቃል የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናበት አላማ እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን ዕቅድ ለማወቅ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ብርሃን እንዳደረገን ይናገራል እኛም እውነተኛውን የደህንነት ብርሃን መቀበል አለብን እግዚአብሄር የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት የማይቀበሉትን ሰዎች የሰይጣን ልጆች ብሎ ይጠራቸዋል እግዚአብሄር ለእኛ ድንቅ የሆነ የደህንነት ዕቅድ እንዳለውና ሁሉንም እንደፈጸመ መገንዘብ አለብን ሕይወታችንን ያለ እምነት ስንኖር በፈቃዱ በተጨባጭ ማመን የምንችለው እግዚአብሄር ምን አይነት በረከቶችን እንደሰጠን ስንገነዘብና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስናምን ብቻ ነው።

በልቦቻችን ውስጥ ካለው ውጥንቅጥ ግራ መጋባት ነጻ የሚያወጣን ምንድነው?

ወደ ዘፍጥረት 1:2 እንመለስ እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር።»*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምድር የምታመላክተው የሰውን

ልብ ነው ምድር ባዶ ነበረች ማለት የሰው ልብ ግራ የተጋባና ባዶ ነው ማለት ነው በሌላ አነጋገር ሰዎች አሁን እየኖሩ ያሉት በውዥንብር ውስጥ ነው ባዶነትም አለባቸው ማለት ነው ምክንያቱም ከደህንነት እውነት ቃል ጋር አልተገናኙምና ይህንን የሰውን ዘር ውዥንብር ለማስወገድ ትክክለኛ የሆነ «የሐጢያት፣ የጽድቅና የፍርድ» (ዮሐንስ 16፡8) እውቀት ሊኖረን ይገባል በሌላ አነጋገር የሐጢያቶቻችሁን ስርየት መቀበልና በእርግጥም ግራ ከተጋቡት ልቦቻችሁ ነጻ መውጣት የምትችሉት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ስታደምጡና ስታምኑ ነው ነገር ግን በጣም ብዙ ሰዎች አሁንም ድረስ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል አለማወቃቸው የሚያሳዝን ነው ስለዚህ አስተሳሰቦቻቸውና ልቦቻቸው አሁንም በግራ መጋባት እየተቅበዘበዙ ናቸው፡፡

አሁንም ገና ብርሃንን ያልተቀበሉ ሰዎች ግራ ከተጋቡት አስተሳሰቦቻቸው ማምለጥ ስለማይችሉ እየታገሉ ነው ነገር ግን የደህንነት እውነት ብርሃን ወደ ልቦቻቸው ሲገባ ውዥንብራቸው በአንድ ጊዜ ይወገዳል፡፡

እግዚአብሄር እንዲህ ብሎናል *«ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ»* እግዚአብሄር ይህንን በድቅድቅ ጨለማ የተሞላውን አለም በብርሃን ሲያበራው ጨለማ ወዲያውኑ ተወገደ እግዚአብሄርም ለእኛ ያደረገውን አየ እነሆም መልካም ነበር እግዚአብሄርን ማወቃችን የሚጀምረው በኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውን የወንጌል እውነት ከማወቅ ነው እርሱ የደህንነትን ብርሃን በእኛ ላይ ሲያበራ ከእንግዲህ ወዲህ ጨለማ ሊቆይ አይችልም፡፡

ስለዚህ እኛ የደህንነት ብርሃን የሆንን ሰዎች ይህንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በዚህ አለም ላይ ለሚኖር ለእያንዳንዱ ሰው ማስፋፋት አለብን የውሃውንና የመንፈሱን

ወንጌል በዚህ አለም ላሉ ሰዎች በምንሰብክበት ጊዜ ውሸጉብር ከእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ይወገዳል እኛ ያመንነውና የሰበክነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል በርካታ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመራ ምንም ጥርጥር የለም እነርሱ በልቦቻቸው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሲያምኑ የልቦቻቸው ባዶነት ይወገዳል ሐጢያቶቻቸውም ደግሞ ይደመሰሳሉ ይህንን የውሃውንና የደሙን ወንጌል በልቦቻችሁ ስትቀበሉ ሐጢያቶቻችሁ ይወገዳሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደህንነት እውነት ብርሃን ይናገራል የዚህ ደህንነት መሰረት የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል ነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል በደህንነት ውስጥ የእውነት መሰረት ቢሆንም ይህ ወንጌል ራሱ የደህንነት ብርሃን ነው ሁሉ ነገራችን በዚህ ወንጌል ውስጥ ተካቷል በዚህ ወንጌል ውስጥ ጻድቅ የሆነው ሕይወታችን፣ እውነተኛው እምነታችንና እግዚአብሄር ተስፋ የሰጠንን እያንዳንዱን በረከት የምንቀበልበት ተስፋችን ይገኛል።

እግዚአብሄር በሰዎች አስተሳሰቦች በውሸጉብራቸው በባዶነታቸውና ሐጢያተኛ በሆነው አእምሮዋቸው ውስጥ የደህንነት እውነት ብርሃን ሆኖ ይሰራል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *«የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» (ዘፍጥረት 1:2)* እግዚአብሄር በተጻፈው ቃል መሰረት ይሰራል።

እኛም ደግሞ በእግዚአብሄር ቃል መሰረት በማመን ወንጌልን ማገልገልና የእምነት ሕይወታችንን መኖር አለብን የተጻፈውን ቃል ስናምንና በዚህ እምነትም ለእያንዳንዱ ሰው «የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ይህ ነው» እያልን ስንሰብክ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ቃል መሰረት ይሰራል አዳዲስ ምዕመናኖችም ወደ እግዚአብሄር ፍቅር ይመጣሉ *«የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» (ዘፍጥረት*

1:2) እግዚአብሄር በቃሉ መሰረት በእውነቱ አማካይነት ይሰራል የእግዚአብሄር መንፈስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ግራ በተጋቡ ባዶ በሆኑና በሐጢያተኛ ሰዎች ልቦች ውስጥ ይሰራል የእያንዳንዱን ሰው ሐጢያቶች በሙሉም ያነጻል።

እግዚአብሄር በግልጽ *«የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር» (ዘፍጥረት 1:2)* ይለናል እዚህ ላይ «መንፈስ» የሚያመላክተው መንፈስ ቅዱስን ነው ይህንን ምንባብ ካየን በኋላ የእግዚአብሄር መንፈስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል አማካይነት በመስራት ሰዎች ደህንነትን ይቀበሉ ዘንድ እንዳስቻለ አምነናል አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምታምኑ ሰዎች በልቦቻችሁ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አለ።

መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሄር ቃል አማንይነት በልቦቻችሁ ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ይታወቃችኋልን? መንፈስ ቅዱስ በእምነታችን መሰረት በተጻፈው የእግዚአብሄር ቃል አማካይነት ይሰራል የእግዚአብሄርን ቃል ስንሰማ፣ ስናምንበትና ስንቀበለው በልቦቻችን ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ይመሰክራል እርሱ በልቦቻችን ውስጥ «አዎ ያ ትክክል ነው እመኑና ተቀበሉ እግዚአብሄርን በመታመን ተከተሉ» በማለት ይናገራል።

የእግዚአብሄር መንፈስ በውሆች ላይ ይሰፍፍ ነበር እዚህ ላይ «ይህ ውሃ» ማለት ምን ማለት ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በዚህ ምንባብ ውስጥ ውሃ የሚያመላክተው የእግዚአብሄርን ቃል ነው ነገር ግን በጠባቡ ስንመለከተው ይህ ውሃ የሚያመላክተው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ የተቀበለውን ጥምቀት ነው 1ኛ ጴጥሮስ 3:21 እንዲህ ይላል *«ይህም ውሃ ማለትም ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል»* እግዚአብሄር ሁሉንም ነገር በትክክል የሚሰራው ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ቃል ጋር አብሮ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በቃሉ መሰረት እንደሚሰራ ስናውቅ ስናምን ስንቀበልና የእግዚአብሄርን ቃል በግልጽ ስንከተል ያን ጊዜ እግዚአብሄር እምነታችንን ለመደገፍ ይሰራል በእግዚአብሄር ቃል ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ» ይላል።

ዘፍጥረት 1:3-4 እንዲህ ይላል *«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ»* እግዚአብሄር ብርሃን ሆኖ ወደዚህ ድቅድቅ ጨለማ አለም መጣ ይህ ማለት ጌታ ሐጢያቶቻችንን ደምስሶዋል አሁን በልቦቻችን ውስጥ ይኖራል ማለት ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በዚህ የእውነት ብርሃን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ደመሰሰ የራሱ ሕዝብ አደረገን መንፈሱንም በልቦቻችን ውስጥ ተነፈሰ እንዲህ በማድረግም የኢየሱስ ክርስቶስ ወገን አደረገን እንዲህ የእግዚአብሄር ሕዝብ መሆናችን ከተአምራቶች ሁሉ እጅግ ታላቁ ተአምር ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለዚህ አለም ከመስጠቱ በፊት ሁሉም ነገር ፈጽሞ ጨለማ ነበር እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ይሰፍፍ ነበር» (ዘፍጥረት 1:2)* ይህ አለም ድቅድቅ ጨለማ ስለነበር የነበረው ነገር ውሸጉብር ባዶነትና ጨለማ ብቻ ነበር ነገር ግን እግዚአብሄር በቃሉ «ብርሃን ይሁን» ሲል በዚህ አለም ላይ ብርሃን ብቅ አለ በዚህ ምድር ላይ ብርሃን ሊኖር የቻለው እግዚአብሄር እንዲሆን ስላዘዘ ብቻ እንደሆነ

መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ስለዚህ ጌታችን በተጨባጭ ወደዚህ ምድር መጥቶ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የእግዚአብሄር ሕዝብ አደረገን በሌላ አነጋገር ሁሉም ነገር በቃሉ መሰረት የተፈጸመውና እኛም ከአለም ሐጢያቶች ድነን የእግዚአብሄር ሕዝብ የሆንነው እግዚአብሄር ቃሉን ስለተናገረ ነበር የእግዚአብሄር ሕዝብ የሆንነው እግዚአብሄር ለእኛ በተናገረው ቃል መሰረት ነው።

እግዚአብሄርን በልቦቻችን ስላላወቅነውና ሐጢያተኞች ስለነበርን ማድረግ የቻልነው ነገር ቢኖር ወደ ዘላለማዊው ሞታችን ወደ ሲዖል የምንጣልበትን ቀን መጠበቅ ብቻ ነበር ሁላችንም ከእግዚአብሄር ርቀን ነበር ምክንያቱም ሁላችንም በተፈጥሮዋችን ሐጢያተኞች ነበርንና በአዳምና በሔዋን ሐጢያት ምክንያት ከእርግማን በታች ሆነን ተወልደናል በልቦቻችን ውስጥም ፍጹም ከሆነ ባዶነትና ሐጢያት በስተቀር ምንም አይነት የብርሃን ፍንጣቂም ሆነ አንዳች ሌላ ነገር አልነበረም በግልጽ አነጋገር በልቦቻችን ውስጥ የእውነት ወንጌል አልነበረም ልቦቻችን ሁሉም በአንድ ላይ ተወሳስበው ካሉበት ከጨለማ፣ ከባዶነትና ከውሸጉብር በስተቀር ሌላ ምንም ነገር አልነበረባቸውም ነገር ግን እግዚአብሄር «ብርሃን ይሁን» ሲል በልቦቻችን ውስጥ ብርሃን መጣ መጽሐፍ ቅዱስ ብርሃን የመጣው እግዚአብሄር ብርሃን ይሁን ብሎ ስላዘዘ እንደሆነ ይናገራል።

ጌታችን ሰማያትንና ምድርን መፍጠሩ የሚናገረው ስለ ነፍሳችን ዳግም መወለድ ነው በተፈጥሮ በነፍሳችን ውስጥ ከባዶነት፣ ከጨለማና ከውሸጉብር በቀር ሌላ ምንም ነገር የለም እግዚአብሄር ግን ተናገረን እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር እንደመጣና በደህንነት ብርሃን እንዳበራን

ነግሮናል ጌታ ውሸርንብርና ባዶነት ብቻ ወዳለባቸው ሰዎች እንደመጣና ይህንን ብርሃን ወደተቀበሉት ሰዎች ውስጥ እንደገባ ይነግረናል አጋር ምዕመናኖቹ የእግዚአብሄር ልጆች መሆን የቻልነው እንዴት ነው? ይህ በእግዚአብሄር ቃል ሲታይ ራሱን የሚገልጥ እውነት ይመስል ይሆናል ነገር ግን ራሳችንን ስንመለከት አሁን እግዚአብሄርን አባታችን ብለን መጥራት መቻላችንና አሁን የእርሱ ሕዝብ መሆናችን በተባረከው የእግዚአብሄር የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ባይሆን ኖሮ የሚቻል ባልሆነም ነበር ይህ ፈጽሞ የማይቻል ነበር ነገር ግን ይህ የተቻለው ጌታ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት እኛን ለመፈለግ በመምጣቱ ነው።

እኛ ጻድቃን የሆንነው እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት በመስራቱ ነው የእርሱ ሕዝብ የሆንነውም እግዚአብሄር በዚህ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ስላዳነን ነው ደህንነታችንን ማግኘት የምንችለውም እግዚአብሄር ቀድሞውኑም ያከናወነውን እያንዳንዱን ነገር በእምነት በመቀበል ነው እናንተና እኔ «የብርሃን ልጆች የሆንነው እንዴት ነው? የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው እንዴት ነው?» ብለን ራሳችንን ስንጠይቅና እነዚህ ጥያቄዎች ስናሰላስል በእግዚአብሄር ጸጋ እንደነቃለን እግዚአብሄር በቃሉ የብርሃን ልጆች አደርጎናል።

እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር በፈጠረ ጊዜ ብርሃን ይሁን ብሎ አዘዘ ድቅድቅ ጨለማ በሆነው አለም ላይም ብርሃን ፈነጠቀ ጨለማ ከምድር ላይ የተገፈፈው በዚህ መልኩ ነው ያን ጊዜ አለም በሁሉም አይነት የሕይወት መልኮች ሕይወትን ዘራች እንስሶች ሁሉ፣ በሰማይ የሚበሩ ወፎችና በባህር ውስጥ ያሉ አሦች ሕያዋን ሆኑ ሁሉም ነገር እንዲህ ሕይወት የዘራው በእግዚአብሄር ቃል ነው ስለዚህ በዩኒቨርስ ውስጥ ያለው

እያንዳንዱ ነገር በእግዚአብሄር ትዕዛዝ በመጣው ብርሃን እንደበቀለ ሁሉ እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ልጆቹ አድርጎናል።

በዚህ አለም ላይ ያሉት ዛፎችና ሳር፣ በሰማይ የሚበሩት ወፎች ሁሉ፣ በባህር ያለው አሳ ሁሉና በዚህ ምድር ላይ ያለው ሕዝብ ሁሉ በብርሃኑ አዲስ ሕይወትን ተቀበለ በብርሃኑም ሕይወት ዘራ ይህ ብርሃን እንዲሆን ያዘዘው አምላክ ማነው? እኛን ከሐጢያት ያዳነን አዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ኢየሱስ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ አምላካችንና አዳኝ ነው

በዘፍጥረት መጽሐፍ አማካይነት ኢየሱስ ክርስቶስን መገናኘት እንችላለን እርሱ ፈጣሪ አምላክ ነው በዚህ አለም ላይ ብርሃን እንዲሆን ያዘዘው አምላክ አዳኛችን ኢየሱስ ነው ይህ መሲሃችን ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ተናግሮ የፈጠረ ራሱ አምላክ ነው በሌላ አነጋገር በቃሉ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው አምላክ ይህንን ዩኒቨርስና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ፈጥሮዋል።

የዮሐንስን ወንጌል ስንገልጥ እንዲህ ተጽፎዋል *«በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሄር ነበረ ይህም በመጀመሪያው በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» (ዮሐንስ 1:1-3)*

ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው የቃሉ አምላክ ሰው ሆነ ወደዚህ ምድር መጣ ከሐጢያትም አዳነን በዩኒቨርስ ላይ ብርሃንን የፈጠረው ይህ አምላክ ከሰዎች ልቦች ውስጥ

ሐጢያትን ደመሰሰ ሁላችንም መጀመሪያ የወደቀው የአዳም ዘሮች ስለሆንን ሐጢያትን ወርሰናል በዚህ ውርስ ምክንያት በሐጢያት በውሸንብርና በባዶነት ታስረን ከመሞት ማምለጥ አልቻልንም ነገር ግን ጌታ ወደ እኛ መጣ በልቦቻችን ውስጥም ብርሃን ሆነ ሕይወታችንንም አዳነ በአጭሩ እግዚአብሄር ከአለም ሐጢያቶች አዳነን።

ሁላችንም እግዚአብሄር የሐጢያቶቻችንን ስርየት እንድንቀበል በመፍቀድ የአለም ብርሃን አድርጎ እንደለወጠን በመገንዘብና በማመን በእምነት እውነተኛ ደህንነትን መለማመድ ይገባናል እግዚአብሄር ብርሃን ይሁን ብሎ ባዘዘ ጊዜ ብርሃን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ይህም እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ከሐጢያት እንዳዳነን ያመላክታል ጻድቃን የሆንነው በዚህ መልኩ ነው።

ብዙ ሰባኪዎች «አጋር ምዕመናኖቼ በቅድስና በመኖር የአለም ብርሃን መሆን አለብን» ብለው ይሰብካሉ ነገር ግን ጻድቃን የሆንነው ወይም ብርሃን ሆነን የተለወጥነው በራሳችን ጥረት አይደለም ይልቁንም ሁሉም ነገር በዚህ ቃል መሰረት በትክክል የሚፈጸመው የእግዚአብሄር ቃል የተናገረውን በትክክል ስናምን ነው እግዚአብሄር በውሃውና በደሙ አማካይነት ስላዳነን ብርሃን ሆነናል በሕይወታችን ውስጥ ብራና ደመናማ ቀናቶች ቢኖሩም ሁላችንም ብርሃን የመሆናችንን እውነታ መረዳት አለብን።

ሰዎች ያልተጠናቀቁ የእግዚአብሄር ስራዎች ናቸው

«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ» (ዘፍጥረት 1:3) ስለዚህ ሁሉም ነገር የተፈጸመው እግዚአብሄር

በትክክል በተናገረው መሰረት ነው።።

በእውነት ብርሃን በማመን ቀድሞውኑም ብርሃን የሆንን ሰዎች በዚህ አለም ላይ የአለም ብርሃን ሆነን እየኖርን ነው በዚህ አለም ላይ አንድ ቀን ብርሃን እየሆንን በሌላ ቀን ደግሞ ጨለማ እየሆንን በብርሃንና በጨለማ መካከል አንንጠራወዝም ምንም ያህል ጎዶሎና ደካማ ብንሆንም አሁንም ብርሃን ነን ይህ ተአምር ነው አምላካችን እንደዚህ ስለሆነ እንከን ያለብንና ውሱን የሆንነውን ሰዎች እንደገና በመፍጠር የመጨረሻ ስራው አድርጎ አጠናቀቀን።።

እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ ይህ ዩኒቨርስና በውስጡ ያለው እያንዳንዱን ነገር ሙሉ አልነበረም ይህ አለም በጨለማ፣ በውኀዥንብርና በባዶነት የጠሞላ ነበር ሕይወትም አልነበረውም መላው ዩኒቨርስ ራሱ በትልቅ ውጥንቅጥ ውስጥ ነበር ምድር፣ ሰማያትና ከዋክብቶች ሁሉም ነገር ቅርጽ አልባ ነበር።።

ነገር ግን እግዚአብሄር ብርሃን እንዲሆን ሲያዝዝ ብርሃን ሆነ በዚህ መንገድ እግዚአብሄር ሁሉንም ነገሮች ስርአት በማስያዝ ያለ እንከን ሰራቸው ከዋክብቶች ሁሉ ያለ ግጭት በዩኒቨርስ ዙሪያ እንዲሽከረከሩ ያደረገው እግዚአብሄር ነው አንዳንድ ከዋክብቶች እርስ በርሳቸው እንዲጋጩ አድርጎ አንዳንድ ከዋክብቶች እንዲጠፉና አዳዲስ ከዋክብቶች እንዲፈጠሩ የሚያደርው እግዚአብሄር ነው እግዚአብሄር ይህንን በማድረግ ተፈጥሮ ራስዋን እንድታመጣጥን አደረገ ቢሊዮን አመታቶች ቢያሳልፉም እንኳን እያንዳንዱ ነገር እንደ በፊቱ ይሰራ ዘንድ ስርአትን ደነገገ እግዚአብሄር እንከን ያለበትን አለም ከፈጠረ በኋላ ፍጹም እንዳደረገው ሁሉ እኛን ሰዎችንም እንደዚሁ ፍጹማን አድርጎናል።።

እግዚአብሄር እኛን ሰዎችን ሲፈጥር ከመጀመሪያው

የተጠናቀቀ ስራዎች አድርጎ አልፈጠረንም እርሱ ከአፈር ሲፈጥረን ያልተጠናቀቅን ነበር በሰይጣን የሚፈተን ሰው አድርጎ ፈጠረን በሰይጣን እንድንፈተንም ፈቀደ ጌታችን መጥቶ ፍጹማን ያደረገን ከዚያ በኋላ ነው እግዚአብሄር ቅርጽ አልባ በሆነው በመላው ዩኒቨርስ ግዛት ላይ ብርሃንን በማብራት ውሸጉብሩን ሁሉ አስወግዶ ትክክለኛ በሆነ ስርአት አደራጀው ልክ እንደዚሁ ብርሃን የሆነው ጌታም በሐጢያት በወደቅነውና ጥልቅ በሆነው ጨለማ ግራ በተጋባነው ሰዎች ልቦች ውስጥ ገባ።

«ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን» (ዘፍጥረት 1:5) እግዚአብሄር ከመጀመሪያው ፍጹማን አላደረገንም ይህ ዳግም እንድንወለድ የሚያስችለን የእግዚአብሄር ችሮታ ነው እግዚአብሄር ይህንን መላውን ዩኒቨርስና እኛን ሲፈጥረን በእነዚህ ነገሮች ሁሉ አላማ ነበረው ይህ አላማም እግዚአብሄር በመንግስተ ሰማይ ለዘላለም ከእናንተና ከእኔ ጋር አብሮ መኖርና አብሮን በክብር መደሰት ነበር አጋረ ምዕመናኖቼ አሁን እግዚአብሄር ለምን ይህንን ዩኒቨርስና እኛን ሰዎች እንደፈጠረ ምክንያቱ ገብቶዋችኋል? አሁን እግዚአብሄር እናንተንና እኔን የፈጠረን ከእርሱ ጋር በክብር እንድንደሰትና ለዘላለም እንድንኖር እንደሆነ ገብቶዋችኋልን? እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ እንኩን ያለብን ሆነን እንድንወለድ ያደረገው፣ ጊዜው ሲደርስም የጠራን፣ ያዳነን፣ የራሱ ሕዝቦች ያደረገን፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን የለወጠንና የእርሱ ልጆች ሆነን ለዘላለም እንድንኖር ያስቻለን ለዚህ ነው።

ይህ አምላክ ጻድቃን አድርጎናል ያ የእግዚአብሄር ዳግም ፍጥረት ነው እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ለእኛ ለሰዎች ከሰራቸው ስራዎች ሁሉ እጅግ ትልቁ ተአምር ነው እናንተ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ከሐጢያቶቻችሁ

ነጽታችሁ የእግዚአብሄር ልጆች ሆናችኋል ሐጢያተኞች ጻድቃን ሆኑ ይህ እጅግ ታላቅ ተአምር ነው እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ» (ዘፍጥረት 1:3)* እኛ ጻድቃን የሆንነው እግዚአብሄር ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ስላዳነን ነው።

አሁን እኛ በዚህ ምድር ላይ ጻድቃን ሆነን እየኖርን ነው አንዳንድ ጊዜ ራሳችሁን ጎዶሎና ደካማ ሆኖ ታገኙት ይሆናል ነገር ግን አሁንም ጻድቅ ሰዎች ናችሁ እኛ የሐጢያት ክምሮች የነበርን ሰዎች አሁን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን መኖራችን እጅግ ታላቅ ተአምር አይደለምን?

«እግዚአብሄርም ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ» (ዘፍጥረት 1:4) እግዚአብሄር እኛ ጻድቃን ሆነንና ወደ ብርሃን ተለውጠን ሲያየን በጣም በመደሰቱ ደስታው ቋንቋ ከሚገልጠው በላይ ነበር አንድ ሐጢያተኛ ሐጢያቶቹን ሲገነዘብ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን የውሃና የመንፈስ ወንጌል ሲያምንና በዚህም ድኖ የእግዚአብሄር ምሉዕ ስራ ሲሆን በመንግስተ ሰማይ ደስታ የሚሆነው ለዚህ ነው። **(ሉቃስ 15:7-10)**

ነገር ግን ችግሩ ሕይወታችንን ስንኖር ብዙውን ጊዜ እኛ ራሳችን ብርሃን የመሆናችንን እውነታ አለመገንዘባችን ነው እግዚአብሄር ብርሃን ካደረገን በኋላ እኛ በማየቱ እንደተደሰተ ይናገራል እግዚአብሄር ደስተኛ ሆኖ ሳለ እኛ ግን ብዙውን ጊዜ ብርሃን የመሆናችንን እውነታ መቀበል ያዳግተናል።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቢያምኑም የዚህ አለም ብርሃን መሆናቸውን ገና የማያውቁ ሰዎች ደግመው ቃሉን ማሰብ አለባቸው ከሐጢያቶቻቸው ድነው እንኳን «እኔ ብርሃን ለመሆን የሚጎድለኝ ነገር አለ» ብለው የሚያስቡ ሰዎች እንደገና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ደግመው ማጽናት አለባቸው አጋር ምዕመናኖቼ ሕይወታችንን ስንኖር እንዴት ብርሃን

ልንሆን እንደቻልን፣ እንዴት ብርሃን እንደሆንን መገንዘብና በዚህ እውነትም ማመን አለብን በእርግጥ የእግዚአብሄር ስራዎች እንደሆንን እናምን እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ለማየት ራሳችንን መመርመር ያስፈልገናል እግዚአብሄር ብርሃን ስላደረገንም ደግመን ልናመሰግነው ይገባናል እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የእግዚአብሄር ፍጹማን ስራዎች ሆነናል እኛ በእርግጥም የዚህ አለም ብርሃን ነን በዚህ አለም ላይ ያለ ሐጢያት እንድንኖር ስላስቻለንም ጌታችንን እናመሰግናለን፡፡

እግዚአብሄር ብርሃኑን ከጨለማው ለየ

አጋር ምዕመናኖቼ *«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ»* የሚለውን ዘፍጥረት 1:3ን ስናነብ ብርሃን መሆናችንን ማመን ይኖርብናል መጽሐፍ ቅዱስ *«እግዚአብሄርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው» (ዘፍጥረት 1:5)* በማለት እንደቀጠለ ሁሉ እግዚአብሄር ብርሃኑን ከጨለማው እንደለየ መረዳት አለብን፡፡

እግዚአብሄር ሁለቱንም በግልጽ ለይቶዋቸዋል የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎች ብርሃን ናቸው ይህንን ያልተቀበሉ ሰዎች ግን ጨለማ ናቸው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ብርሃን ናቸው በሌላ አነጋገር እነርሱ የእግዚአብሄር ልጆች ናቸው ነገር ግን የውሃውን ወንጌልና የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ያልተቀበሉ ሰዎች ጨለማ ናቸው የጨለማ ልጆች የዲያብሎስ ልጆች ናቸው፡፡

በዚህ አለም ላይ ሁለት አይነት ሰዎች አሉ ሁሉም ሰው በዚህ ምድር ላይ የተወለደው ባለመጠናቀቅ ቢሆንም

እግዚአብሄር ባበራው ብርሃን በማመን ብርሃን የሆኑ ሰዎች አሉ ለማመን እምቢተኞች በመሆናቸውም አሁንም ድረስ ጨለማ የሆኑ ሰዎችም አሉ ይህ ብርሃን ሌላ ሳይሆን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ነው በዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ፊት እያንዳንዱ ሰው በሁለት አይነት ሰዎች ተከፍሎዋል ወይ ሐጢያተኛ ነው አለበለዚያም ጻድቅ ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ያመጣልንን ይህንን ደህንነት የተቀበሉ ሰዎች ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የተቀበሉ ሰዎች የእግዚአብሄር ልጆች ሆነዋል የእግዚአብሄር ልጆች በመሆናቸውም ይህንን አለም እያበሩ ሕይወታቸውን ይኖራሉ ጊዜው ሲደርስም እግዚአብሄር አብ ወደ ዘላለም መንግስቱ ይወስዳቸዋል፡፡

ነገር ግን ይህንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት በልቦቻቸው የማይቀበሉ ሰዎች የጨለማ ልጆች ሆነው ይቀራሉ የዲያብሎስ ልጆች ይሆናሉ ሌሊት የሚሆነው ጨለማ በጥልቁ ላይ ሲሆን ነው ሌሊትን ትወዳላችሁ? ይህ ሌሊት በእጅጉ አደገኛ ነው ፈጽሞ ብርሃን ስለሌበት ድቅድቅ ጨለማ ሌሊት አስቡ የሌሊቱ ግዛት ፈጽሞ የተደበላለቀ፣ ስርአት የሌለው፣ አደገኛ፣ አስፈሪና አይንን የሚያሳውር ነው፡፡

«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ» (ዘፍጥረት 1:3) እግዚአብሄር ብሩህ የሆነውን አለም ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው እግዚአብሄር ሁለቱንም እንደለየ ማመን ይኖርብናል *«ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ» (ኤፌሶን 5:8)* እግዚአብሄር ሰዎችን ሁሉ የራሱ ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች አድርጎ ለይቷል ሁሉም ሰው ከውጪ ሲታይ ተመሳሳይ ይመስል ይሆናል ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሄር ልጆች ሲሆኑ ሌሎቹ ግን አይደሉም ስለዚህ እግዚአብሄር ለአንዱ ሕዝብ «እናንተ ልጆቼና

ሕዝቤ ናችሁ» ይላል ለሌሎቹ ግን «እናንተ ልጆቼ አይደላችሁም» ይላል።

በመጨረሻውም ቀን የእነዚህ ሁለት አይነት ሕዝቦች እጣ ፈንታ ይወሰናል ከውሃና ከመንፈስ ያልተወለዱ ሰዎች የጨለማ ልጆች በመሆናቸው በጽድቅ ብያኔ ይቀጣሉ እግዚአብሄር በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ የጨለማን ልጆች ከሐሰተኛ ነቢያቶች ጋር አብሮ በእሳትና በዲን ወደሚቃጠል ባህር እንደሚጥላቸው ተናግሮዋል ሐሰተኛ ነቢያቶችና ተከታዮቻቸውም ሁሉ ወደ ሲያል እሳት ይጣላሉ ነገር ግን በአንጻሩ ብርሃን የሆኑት ልጆች ወደ እግዚአብሄር መንግስት ይገባሉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ብርሃን የሆኑ ሰዎች ወደ ብርሃን ግዛት ይገባሉ እግዚአብሄር ቀደ ዘላለማዊው የብርሃን ግዛት ወደ እግዚአብሄር መንግስት እንዲገቡና እንዲኖሩ ያስችላቸዋል።

«ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን»

ዘፍጥረት 1:5 እንዲህ ይላል *«ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን»* በሰው አለም ውስጥ ቀን የሚጀምረው በጥዋት ሲሆን የሚያበቃውም በምሽት ነው የአለም ነገሮች ለአጭር ጊዜ ብቻ አብርተው ወደ ጨለማ የሚመለሱ ጊዜያዊ ናቸው የሰው ዘር ታሪክም ልክ እንደዚህ ነው ታሪክ ለአጭር ጊዜ ያበራና ተመልሶ ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይወረወራል ነገር ግን የእግዚአብሄር ግዛት የተለየ ነው የእግዚአብሄር ግዛት መጀመሪያ ላይ በእንከን ይጀምራል ውሎ አድርጎ ግን ፍጹም ሆኖ ይጠናቀቃል የእግዚአብሄር ግዛት ሁሌም እንዲህ ነው።

የመገናኛው ድንኳን አደባባይ በር የሚገኘው በጸሐይ መውጫ አቅጣጫ በኩል በስተ ምስራቅ ነበር ታዲያ ታቦቱ

የሚገኘው የት ነበር? በስተ ምዕራብ ነበር የእግዚአብሄር ግዛት በእንከን ይጀምርና ፍጹም ሆኖ ይጠናቀቃል እግዚአብሄር የሚሰራው እንደዚህ ነው እግዚአብሄር ሰዎች ዳግም መወለድ እንዳለባቸው የሚናገረው ለዚህ ነው እግዚአብሄር *«ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሄር መንግስት ሊገባ አይችልም» (ዮሐንስ 3:5)* ይላል ጅማሬው ጎዶሎ ቢሆንም እግዚአብሄር ፍጹም አድርጎ ይሞላዋል።

የእምነት ሕይወታችንም ልክ እንደዚህ ነው የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከተቀበልን በኋላም እንኳን መጀመሪያ ላይ ጎዶሎዎች ነን በሌላ አነጋገር ብንድንም ያን ያህል የምናውቀው ነገር የለንም ምንም የተለወጠ ነገር እንደሌለ ይሰማናል ትክክል የሆነው ነገርም ምን እንደሆነ እርግጠኞች አይደለንም ስለዚህ ከዳንን በኋላ ጉድለታችንን አብልጠን እንወደዋለን ምክንያቱም ሕይወታችን መለወጥ አለበት እኛም በእምነት መኖር አለብን ከዚህ ቀደም ለስጋችንና በስጋዊ ጉልበታችን መኖርን እናዘወትር ነበር አሁን ግን በስጋችን ጉልበት ላይ ብቻ የምንደገፍ ከሆንን እንረገማለን ስለዚህ በእግዚአብሄር ላይ መደገፍ፣ በእርሱ መታመንና በእምነት መኖር አለብን አብልጠን ጉድለቶቻችንን ወደ ማየት የምንመጣው ለዚህ ነው ደካማውን ማንነታችንን ስናይ የምንቃብዘውና የምንታገለው ለዚህ ነው ስለዚህ ጅማሬያችን ጎዶሎ ነው።

ሆኖም እግዚአብሄር ወደተናገረለት ግዛት ገብተን እዚያ መኖር ከጀመርን በኋላ በእምነት የምንኖር ከሆንን መጀመሪያ ላይ ጉድለት ያለብን ቢመስለንም ፍጹማን እንሆናለን በስጋ አይኖቻችን ጉድለት ያለብን ቢመስለንም የእግዚአብሄርን ቃል ስንከተለውና ውስጡ ስንገባ የእምነት ሕይወት በእርግጥም ፍጹምና ሙሉ እንደሆነ ራሳችን እንለማመደዋለን እግዚአብሄር

ሁሌም የሚሰራው እንደዚህ እንደሆነ እናውቃለን፡፡

እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ያደረገውን ብናጠቃልለው እናንተና እኔ ጻድቃን ሆነናል ማለትም ብርሃን ሆነናል እግዚአብሄር ብርሃን አድርጎናል ብርሃን ሆነን እንድንኖርም አድርጎናል እግዚአብሄር ብርሃን ያደረገን የመሆኑን ይህንን እምነት ደግማችሁ እንዳተጸኑት ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ፡፡

ውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምታምኑ ሰዎች ብርሃን እንደሆናችሁ ታምናላችሁን? እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ብርሃንን ከጨለማ በግልጽ ለይቷል ስለዚህ እስከ አሁን ድረስ ከሐጢያቶቹ ዳግም ያልተወለደ ማንኛውም ሰው ጨለማ ነው ምንም ያህል ራሱን ቢገራ ምንም ያህል አይኖቹ በጥበብ ቢያበሩ ምንም ያህል በራሱ ቢተማመን ጨለማ አሁንም ጨለማ ነው ልቡ ግራ እንደተጋባ አያጠራጥርም፡፡

ነገር ግን ዳግም የተወለዱ ሰዎች አሁን የአለም ብርሃን ናቸው እኛ በእምነት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የብርሃን ልጆች ስለሆንን ሁሉንም ማወቅ እንችላለን ምክንያቱም በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ ይናገረናል ያስተምረናል ይመራናል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ አማኞች በውስጣቸው መንፈስ ቅዱስ ስለሚኖር ሁሌም ፍጹማን ናቸው፡፡

ሕይወታችንን ስንኖር እኛ የዚህ አለም ብርሃን እንደሆንን ደግመን ማስታወስ ይገባናል እናንተና እኔ ብርሃን መሆናችን ከተአምሮች ሁሉ የሚልቅ ተአምር ነው ማንም ሰው በምግባሮቹ ብርሃን መሆን ይችላልን? በራሱ ምግባሮች አይችልም፡፡

ብርሃን እንድንሆን የሚያስችለን ብቸኛው ነገር የእግዚአብሄር ቃል ነው ቃል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እኛ መጥቶ *«እግዚአብሄርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ» (ዘፍጥረት 1:3)* አለን ከዚህ ቃል በቀር ሌሎች ቃሎች አያስፈልጉም ጨለማ

ወደሆነ ክፍል ገብታችሁ ማብሪያውን ስታበሩት ብርሃን በበራበት ቅጽበት ጨለማው ይጠፋና ክፍሉ በብርሃን ይሞላል ልክ እንደዚሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ ወስዶ ስለደመሰሳቸው በዚህ የእውነት ብርሃን ብናምን ልቦቻችን ወዲያውኑ ሐጢያት አልባ ይሆኑና ንጹህ ብርሃን ሆነው ይለወጣሉ።።

እግዚአብሄር በእርግጥም ብርቱና ሁሉን ቻይ ነው እግዚአብሄር ለዚህ ለጨለማው አለም ለዚህ በውሸቦንብር፣ በባዶነትና በጨለማ ለተሞላው አለም ብርሃንን ሰጠ እግዚአብሄር «ብርሃን ይሁን» ብሎ ባዘዘ ጊዜ ብርሃን ፈነጠቀ ጨለማውም ተገፈፈ።።

ሊመጣ ላለው ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይሁንለትና የተቀበልነው ደህንነት ይህንን የሚመስል ነው እርሱ በተናገረ ጊዜ ምዚህ ምድር ላይ ፍጹም ብርሃን ፈነጠቀ በእግዚአብሄር ቃል ጨለማ ለአንዱና ለመጨረሻ ተገፈፈ ብርሃን ብቻም ነገሰ እኛን ያዳነን ይህ አምላክ ሁሉን ቻይ ስለሆነ እግዚአብሄር በተናገረው የእውነት ቃል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል ሐጢያቶቻችን በሙሉ ለአንዱና ለመጨረሻ ተደመሰሱ።።

ጌታ ከሐጢያት ሊያድነን ተስፋ የሰጠው በእውነት ቃል ነው እርሱንም ፈጽሞታል እንደሚያድነን የሚናገረው ይህ የኪዳን ቃል የተሰጠው ሰይጣንን በረገመው ጊዜ ነበር እንዲህ ብሎዋል *«ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ በሆድህም ትሄዳለህ አፈርንም ትበላለህ በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።።» (ዘፍጥረት 3:14-15)*

ለሰው ዘር ይህንን ተስፋ ከሰጠ በኋላ ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሄር የሴቲቱ ዘር ሆኖ ስጋ በመልበስ ከማርያም ተወለደ

የውሃ ጥምቀትንም በመቀበል የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ እጅግ ተገቢ በሆነ መንገድ ወሰደ በመስቀል ላይም ደሙን አፈሰሰ ሰው የሆነው መለኮታዊው ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ አማካይነት ሐጢያቶቻችንንና ኩነኔን ሁሉ በመሸከም የሕጉን መጠይቆች ፈጸመ የሞትን ዋጋ በመክፈልም የዲያብሎስ ባሮች የሆንነውንና በእርሱ የታሰርነውን ሰዎች የራሱ የእግዚአብሄር ልጆች አደረገን ማለትም ጻድቃን አደረገን ክርስቶስ የእግዚአብሄር ሕዝቦች አድርጎ ለእግዚአብሄር አብ አቀረበን፡፡

ይህ ደህንነት ምንኛ ፍጹም ነው? በእግዚአብሄር ስራዎች ውስጥ ምንም እንከን የለም እርሱ ሁሉንም ነገዐር ፍጹም አድርጎ አጠናቆዋል እግዚአብሄር የእርሱ ሕዝቦች እንሆን ዘንድ ምንም እንዳይጎድለን የብርሃን ልጆች እንድንሆን አስቻለን የእግዚአብሄር ደህንነት ምን ያህል ግሩም ነው? እኛ አሁን የብርሃን ልጆች ብርሃን መሆናችን እንዴት ያለ በረከት ነው? ከሐጢያት መዳናችን የተገኘው በሚጠፋ ወርቅና ብር ሳይሆን በዘላለማዊው የእግዚአብሄር ቃል ነው፡፡ (1ኛ ጴጥሮስ 1:23)

ቃሉ ጻድቃን አድርጎናል ማለት በእግዚአብሄር ጸድቀናል ማለት ነው የእርሱ ሕዝብ የሆንነው በእግዚአብሄር ቃል በማመን ነው ፍጹም የሆነውን በረከት የተቀበልነውም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ነው፡፡

በዚህች ሰአት ብርሃን ስላደረገን አሁን ብርሃን ስለሆንንና አሁን በእግዚአብሄር ወደ ብርሃን ስለተለወጥን እንደገና እግዚአብሄርን እናመሰግነዋለን እግዚአብሄር ብርሃን እንዲሆን ያዘዘው በዚህ ስጋዊ ዩኒቨርስ ላይ ብቻ አይደለም ይልቁንም በልቦቻችን ውስጥ ያለውን ጨለማ ለመግፈፍ እግዚአብሄር ራሱ የእውነት ብርሃን ሆኖ ወደ ልቦቻችን በመግባት ጻድቃን አደረገን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ሁላችንም ደግመን እግዚአብሄርን ማመስገን ይገባናል፡፡ ✉

ከጠፈር በላይ ያለው ውሃና ከጠፈር በታች ያለው ውሃ

« ዘፍጥረት 1:6-8 »

«እግዚአብሄርም በውሆች መካከል ጠፈር ይሁን በውሃና በውሃ መካከልም ይከፈል አለ እግዚአብሄርም ጠፈርን አደረገ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትንም ውሆች ለየ እንዲህም ሆነ እግዚአብሄርም ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ሁለተኛ ቀን::»

እግዚአብሄር በፍጥረቱ የመጀመሪያ ቀን ነፍሳቶችን የማዳን ስራ ሰራ በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ሐጢያተኞችን ጻድቃን አደረጋቸው ጻድቃኖችንም በግልጽ ከሐጢያተኞች ለየ ሰማይና ምድር በተፈጠሩ በሁለተኛው ቀን እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየ በሌላ አነጋገር ይህ ማለት እግዚአብሄር ቃሉን ከሰይጣን ቃሎች ለየ ማለት ነው::

ከጠፈር በላይ ያለው ውሃና ከጠፈር በታች ያለው ውሃ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «የውሃ» መንፈሳዊ ትርጉም የሚያመላክተው «የእግዚአብሄርን ቃል» ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ዘር ሐጢያቶች የተወሰደበትን ከአጥማቂው ዮሐንስ የተቀበለውንም ጥምቀት እንዲሁ ያመላክታል በዚህ ምድር ላይ

የእግዚአብሄርን ቃል የሚያስፋፉ ሰዎች አሉ የሰይጣንንም ቃሎች የሚያስፋፉ ሰዎችም ደግሞ አሉ እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ያሉትን ውሆች በሙሉ ከጠፈር በላይ ያለ ውሃና ከጠፈር በታች ያለ ውሃ በማድረግ የለያቸው ለዚህ ነው እግዚአብሄር በሁለተኛው የፍጥረት ቀን ባደረጋቸው ነገሮች አማካይነት «በዚህ አለም ላይ ቃሌን በእምነት እየተመገቡ የሚኖሩ ሰዎችና የሰይጣንን ቃሎች በበመመገብና እነርሱንም በማስፋፋት የሚኖሩ ሌሎች ሰዎች አሉ» እያለ ነው ስለዚህ የእግዚአብሄርን ቃል እንደሚሰብኩ የሚናገሩ ሰዎች በእርግጥ የእግዚአብሄር አገልጋዮች እንደሆኑ ወይም የሰይጣን አገልጋዮች እንደሆኑ የምንለይበትን መንገድ ማወቅ ያስፈልገናል።

በጎና ፍጹም ስጦታ ሁሉ ከብርሃናት አባት ከላይ ይመጣሉ (ያዕቆብ 1:17) በአንጻሩ እያንዳንዱ ክፋት የሚፈልቀው ከሰው ልብ ውስጥ ነው ስለዚህ የእግዚአብሄር ቃል ብርሃን ሲያበራ እውነተኛው የሐጢያተኞች ባህርይ ይገለጣል ከጠፈር በታች ያለው ውሃ ማለትም ምድራዊ ቃሎች የሚያመላክቱት ከሰው ልብ የሚፈልቁ ትምህርቶችን ነው ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ የተለየው ለዚህ ነው።

በዚህ ምድር ላይ ያለው ውሃ በጠፈር ላይ ካለው ውሃ በዋናነት የተለየ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ከሰው ልብ የሚወጣ ቃል ሁሉ ከጠፈር በታች ያለ ውሃ ሲሆን እርሱ ለእኛ የተናገረው የእውነት ቃል ከጠፈር በላይ ያለ ውሃ እንደሆነ እየተናገረ ነው።

በዚህ ምድር ላይ ሐሰተኛ ነቢያቶች አሉ ነገር ግን በዚያው ጊዜ ደግሞ እውነተኛ ነቢያቶች የሆኑ የእግዚአብሄር አገልጋዮችም አሉ ሐሰተኛ ነቢያቶች የእግዚአብሄርን ቃል ሳይመለከቱ ከልቦቻቸው የሚወጣውን ሁሉ የሚናገሩ ናቸው በብሉይ ኪዳንም እንደዚሁ ሐሰተኛ ነቢያቶች ከአእምሮዋቸው

በፈለቀው በማንኛውም ነገር ላይ በመመርኮዝ ትንቢት ተናግረው ነበር ስለዚህ በመንፈሳዊ አነጋገር የእነርሱ ትምህርቶች የምድር ቃሎች ማለትም የሰይጣን ቃሎች ናቸው።

ነገር ግን የሰይጣን ቃሎች አሁንም በሰዎች ልቦች ውስጥ መስራት ይችላሉ ስለዚህ ዲያብሎስ የሚጠቀምባቸውን ሰዎች ስንመለከት ሐጢያተኞች ከቃሉ ውጭ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ወይም በልሳን እንዲናገሩ ይነግሩዋቸዋል ይህ ሌላ ሳይሆን ከአእምሮዋቸው ውስጥ የሚወጣ የማይረባ ነገር ነው እነርሱ የሚሉትን በጥንቃቄ በምናደምጥበት ጊዜ ከራሳቸው አስተሳሰቦችና ስሜት የፈለቀ ድምጽ መሆኑን በቀላሉ እንረዳለን ስለዚህ ፈጽሞ የተዘበራረቀ ነው በጣም የረከሰ ስለሆነ መስማታችንን መቀጠል እንኴን አንችልም።

በጸሎት ምሽግ የመነቃቃት ስብሰባ ወቅት የሚነገረውን በምንሰማበት ጊዜ እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎች ሰባኪው መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ የእግዚአብሄርን ቃል እየተናገረ እንደሆነ ወይም በአእምሮው ውስጥ ያለውን ማንኛውም ነገር እየተናገረ እንደሆነ በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን እንደ እነዚህ ያሉ ብዙ ሰባኪዎች የሚናገሩት ፈጽሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይገናኝ ነገር ነው ለምሳሌ ጉባኤው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል እየተናገሩ ድምጽ ማጉያው የሆነ አይነት የተለየ ድምጽ እንዲያወጣ ያደርጉትና «እሳትን ተቀበሉ!» እያሉ ይጮሃሉ ከፍተኛ ድምጽ ያለውን ባንድ በመጠቀምም የሕዝቡን ስሜት አነሳስተው በርካቶች ቀልባቸውን እንዲስቱ ያደርጉዋቸዋል በእርግጥ ሕዝቡ በዚህ መንገድ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላልን?

እግዚአብሄር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *«የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ተቀበሉ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» (የሐዋርያት ስራ 2:38)* ይላል ነገር ግን የሰይጣን አገልጋዮችን

ቃሎች በምንሰማበት ጊዜ ሰው የሐጢያቶቹን ስርየት የሚቀበለው መንፈስ ቅዱስን ከመቀበል በተነጠለ መልኩ ነው ይላሉ «በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ ሁላችሁም ቅዱሳን ናችሁ ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ ፍጹማን ለመሆን መንፈስ ቅዱስ መቀበል ይኖርባችኋል» ይላሉ።

ነገር ግን ሰው ዳግም ከተወለደ በኋላ ገና መንፈስ ቅዱስን መቀበል አለበትን? እንዲህ የሚሉት የውሸታሞች ቃሎች ናቸው የእነርሱ ትምህርቶች ከጠፈር በላይ ያለ ቃል ሳይሆን ከጠፈር በታች ያሉ ቃሎች ማለትም ከምድር የበቀሉ ቃሎች ናቸው በሌላ አነጋገር እነርሱ እግዚአብሄር ፈጽሞ ያልተናገረውን የራሳቸውን ፈጠራ ይናገራሉ።

የሰይጣን ቃሎች ሁሌም እንደዚያ ናቸው ሰዎች ከእግዚአብሄር ቃል የተለየ አንዳች ነገር በሚናገሩበት ጊዜ እነዚያ ቃሎች የሰይጣን ቃሎች ናቸው የሰይጣን ቃሎች ባህርይ ይህ ነው ሰይጣን የሚናገረው ነገር የእግዚአብሄር ቃል እንዳልሆነ ግልጽ ነው ነገር ግን ቃሎቹ የእግዚአብሄር ቃል ናቸው ይላል የሰይጣን ቃሎች ባሕርይ ሌላ ሳይሆን ይህ ነው የእግዚአብሄርን ቃል እየሰበኩ በማስመሰል በመጨረሻ ሰዎችን ማታለል ነው።

የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰብኩ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፉት ቃሎች ላይ ተመርኩዘው ሊሰብኩት ይገባል በአንጻሩ የሰይጣን አገልጋዮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ በልቦቻቸው ውስጥ የመጣውን ማንኛውንም ነገር በመናገር በርካታ ሰዎችን ወደ ጥፋት ይነዱዋቸዋል የሰይጣን ቃሎች ዳግም ባልተወለዱ ሰዎች አማካይነት ይሰራሉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቢያምኑም የሰይጣን ቃሎች እምነታቸው አሁንም ድረስ ባልበሰለ ሰዎች አማካይነት መስራት ይችላሉ።

ታዲያ የሰይጣን ቃሎች በሰዎች ላይ የሚወርዱት እንዴት

ነው? በመጀመሪያ የሰይጣን ቃሎች ዳግም ባልተወለዱ ሰዎች ውስጥ እንደሚሰሩ ተናግሬአለሁ ሰይጣን በሚገባ የሚጠቀምባቸው ዳግም ያልተወለዱ ሰዎችን ነው ስለዚህ ሰይጣን በውስጣቸው ታማኝነትን ያነሳሳል ልቦቻቸውን ይለውጣል በተጨባጭ እያገለገሉ ያሉት ውሸቶችን ሆኖ ሳለ ለእውነት እየሰሩ ያሉ ይመስል ጠንክረው እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል ሰይጣን ሰዎች የሐሰተኛ አስተማሪዎችን ውሸቶች እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል ሰይጣን የሚሰራው ዳግም ባልተወለዱ በእነዚህ ሰዎች ነው እውነትን ከመከተል ይልቅ እውነት ያልሆነውን እንዲከተሉ በእነርሱ በኩል ይሰራል።

አንድ ሰው ዳግም ባልተወለደ መጋቢ እየተመራ የእምነት ሕይወቱን ሲኖር የራሱ የሰይጣን አገልጋይ በመሆን የሚያበቃው ለዚህ ነው ይህ መጋቢ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የማያምን ከሆነ በራሱ መንገድ ጥሩ እየሰራ መሆኑን ቢያምንም በመጨረሻ አገልግሎቱ በሙሉ የሰይጣን ስራ ነው ስለዚህ መጋቢው በመጀመሪያ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም መወለድ አለበት።

የሰይጣን ስራ የሚገለጠው በእውነት በማመን ሳይሆን ለሰው በመገዛት ነው

እንደ እውነቱ ከሆነ ሳያውቁት የሰይጣንን ስራ እየሰሩ ያሉ ብዙ መጋቢዎች አሉ እነርሱ የሰይጣን አገልጋዮች ሆነው ብዙ የሐሰት ስራ እየሰሩ ነው የሰይጣን ስራቸው ሕማሞችን ቢፈውስና አጋንንቶችን ማስወጣት ቢችልም የሚያፈሩት ሐጢያተኞችን ነው ምክንያቱም ተከታዮቻቸው አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት አለባቸውና ቀጣዩ የሰይጣን

ስራቸው ሕጉን ለመጠበቅ ጠንክረው እንዲጥሩ በመለወጥ ጉባኤዎቻቸውን ሕግ አጥባቂ አማኞች ማድረግ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታን በደማስቆ መንገድ ላይ ከመገናኘቱ በፊት ፈጽሞ ለሕጉ የተሰጠ ነበር በፈሪሳውያን መካከል ፈሪሳዊ ስለነበር ከሚገባው በላይ ሐይማኖተኛ ነበር የእርሱ ሐይማኖት አጥባቂነት ክርስቲያን ቅዱሳኖችን እስከ ማሳደድና እስከ መግደል ድረስ የተዘረጋ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ ዳግም ከመወለዱ በፊት ገና ወጣት በነበረ ጊዜ የእግዚአብሄር አገልጋይ የነበረውን እስጢፋኖስን ሲወግሩት የነበሩትን ሰዎች ልብስ ይጠብቅ ነበር እርሱ «ልብሳችሁን እጠብቃለሁ ሒዱና የምትፈልጉትን ያህል ውገሩት!» ያለ ሰው ነው በዚህም ዘመን ቢሆን ሰይጣን በሚሰራባቸው ቤተክርስቲያኖች ውስጥ እንዲህ ያለ አክራሪ ሐይማኖተኝነት አለ እግዚአብሄር የእርሱ አገልጋዮች ስራውን በጸጥታ እንዲሰሩ ያደርጋል በአንጻሩ ዲያብሎስ በአገልጋዮቹ አማካይነት ለክብር ያላቸው ፍላጎት በማነሳሳት ሁሉንም አይነት ከበሮዎች እየደለቀ ስራውን ይሰራል።

ሰዎችን በስሜት ቅንአት ማነሳሳት የሰይጣን ስራ ባሕርይ ነው ሰይጣን የሚጠቀምባቸውን ሰዎች ስንመለከት ሲሰሩ የምናየው በራሳቸው የቅንአት ስሜት ብቻ ነው የማለዳ የጸሎት ስብሰባዎችን ለ70 ተከታታይ ቀናቶች የምሽት የጸሎት ስብሰባዎችንም ለ40 ቀናቶች ከመከታተል ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ ሳምንት ውስጥ አጥንቶ እስከማጠናቀቅ ድረስ ስራቸው የሚጠይቃቸው በጣም ብዙ ልዩ ልዩ መጠይቆች ስላሉ እነርሱን ማከናወን የማያቋርጥ ትግል ነው የእምነት ሕይወታቸውም በመፈክር ላይ መፈክርን እየደረበ የሚቀጥል በራሳቸው ጥረትም አንድ ነገር ለማድረግ የሚታገል ነው ነገር ግን እኛ ማድረግ የሚገባን ነገር ቢኖር እምነታችንን በእርሱ

ጽድቅ ላይ አኑረን መጸለይ፣ ልቦቻችንን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ ማስደገፍና እርሱንም መታመን ነው እግዚአብሄርን ለማስደሰት 40 ቀናቶች መጸለይ ይገባናልን? በእርግጥም አይገባንም!

ሆኖም እነርሱ እውነትን የሚያምኑና የሚከተሉ ሰዎች ስላልሆኑና በእግዚአብሄርም ቃል መታመን ስለማይችሉ ብዙውን ጊዜ አንድ የተለየ ነገር ይሻሉ በስጋ ቀናተኞች ቢሆኑ እግዚአብሄር እንደሚባርካቸው ያስባሉ በእጅጉ ቀናተኞች ለመሆን ስለሚሞክሩ እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምን አማኞች ዳግም ያልተወለዱትን የእነዚህን ሰዎች ቅንአት ልንከተል አንችልም።

እኔም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከማወቄ በፊትና በእርሱም ከማመኔ በፊት ከሚገባው በላይ ቀናተኛ ነበርሁ ወጣቶችን ሰብስቤ ቤተክርስቲያንን ከውስጥና ከውጭ እንዲያጸዱ እስበስብ፣ ምስክርነት እንዲሰጡም ወደ መንገድ እመራ፣ በምሽት ለሚሆነውም የመዘምራን ቡድን ልምምድ እንዲያደርጉ እሰበስባቸው ነበር ዳግም ከመወለዴ በፊት እንዲህ ቀናተኛ ነበርሁ በእግዚአብሄር ፊት ገና ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች በጣም የጋሉ ስለሆኑ እዚህ ላይ ስፍራውን የሳተውን መሰጠታቸውን ማጤን ያስፈልገናል።

አንድ ክርስቲያን ጥብቅ ሐይማኖተኛ ስለሆነ ይህ ማለት የግድ የእግዚአብሄርን ፈቃድ እየተከተለ ነው ማለት አይደለም በሌላ አነጋገር የእምነት ሕይወታችንን ስንኖር በመጀመሪያ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት ምን እንደሆነና እግዚአብሄርን የሚያስደስት ሕይወት ምን እንደሆነ ትክክለኛ እውቀት ሊኖረን ይገባል ለእኛ በእግዚአብሄር ቃል ላይ መደገፍ፣ ምክሩን መሻትና ወደ እግዚአብሄር መቅረብ ማለት የእግዚአብሄርን ፈቃድ መፈጸም ማለት ነው እውነትን መከተል

በእግዚአብሄር ጽድቅ በመታመን ወደፊት መገስገስ ነው ይህ በሰው መሰጠት ሊደረስበት የሚገባ ነገር አይደለም።

ዘፍጥረት 1:2 እንዲህ ይላል *«የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር»* ይህ ማለት የእግዚአብሄር መንፈስ የሚሰራው በእግዚአብሄር ቃል ነው ማለት ነው እኛ ልናደርገው የሚገባን ነገር ቢኖር የእግዚአብሄር ቃል ምን እንደሚል መረዳትና እርሱን መከተል ነው እግዚአብሄር ምክሩን ስንሻ፣ በእርሱ ስንታመንና እርሱን ስንከተለው በሕይወታችን ውስጥ ይሰራል ነገር ግን ከዚህ ከዚህ በተነጻጸረ መልክ ለሰው ዘር ራስን ማስገዛት የፍጻሜ መስመር የሌለውን የማራቶን ሩጫ ይመስላል ሰው ምንም ያህል ራሱን በማስገዛት ቢቀጥል ይህ ማለቂያ የለውም ትንሽ ጨምሮ መሞከርና ጥቂት ጠንክሮ ለመስራት መሞከር ተደጋጋሚ ማበረታቻን የያዘ ነው ነገር ግን ከዚህ የሚገኝ ውጤት ቢኖር ራስን ያስገዛ አማኝ ለመሆን ከቶውኑም ፍጻሜ የሌለው ትግል ነው።

የሰው ዘር ራስን የማስገዛት አላማው የራስን ፍላጎት ማርካት ነው አንድ ሰው ፔዳሎቹን ያለማቋረጥ እስካላሽከረከረ ድረስ ከብስክሌቱ ይወድቃል የሰውም ሐይማኖተኝነት እንደዚሁ ማለቂያ የሌለው ሩጫ ይጠይቃል ይህ ቅንአት ሰዎችን ከመጠን በላይ ያደክማል ያሰቃያልም ሆኖም ሰይጣን አሁንም ቀናተኞች እንዲሆኑ እያነሳሳቸው ነው በመጨረሻም ወደ ሲያል ይጎትታቸዋል ምክንያቱም እጅግ ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሄር ቃል ይልቅ የሰይጣንን ቃሎች በበለጠ ቅንአት ይከተላሉና።

የሰው ቅንአት ሰውየውን ነጻ አያወጣውም ነገር ግን ሰውየውን ያደክመዋል እግዚአብሄር «እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» ብሎናል በአንጻሩ ሰይጣን ለሰዎች የሚያስፈልጋችሁ ጠቅለል ያለ የእግዚአብሄር ቃል እውቀት ነው በተጨባጭ የሚያስፈልጋችሁ ሐይማኖተኝነት

ነው» ይላል የሰይጣን ስነ አመክንዮ ፈጽመን ለእግዚአብሄር ሐይማኖተኞች ከሆንን «እውነተኝነት ሰማይን እንደሚያንቀሳቅስ» ሁሉ እግዚአብሄርም ይንቀሳቀሳል የሚል ነው በዚህ የተነሳ ሰዎች «ሐጢያተኛም ብሆን በትጋት ወደ እግዚአብሄር ከጸለይሁ እግዚአብሄር ሐጢያቴን ይተወዋል» ብለው ያስባሉ ይህ እሳቤ ፈጽሞ የተሳሳተ ነው::

ወደ እግዚአብሄር በትጋት መጸለያችን ምን የሚያስገኘው ነገር አለ? በሐይማኖተኝነታችን ላይ ብቻ ማተኮር የለብንም ያ ሰይጣናዊ ነው በራሳችን ቅንአት መሰረት ከመኖር ይልቅ የእግዚአብሄርን ፈቃድ መገንዘብና በዚህ የእግዚአብሄር ፈቃድ መሰረት መኖር አለብን::

ነገር ግን የሰይጣን አገልጋዮች ለምድራዊ ስራ ቀናተኞች እንድንሆን ሊያነሳሱን ይሞክራሉ እኛን ሐይማኖተኞች ለማድረግ ከሚሰሩት ስራ ለጥቀው ምንም የማናውቅ አድርገው ወደ ሲያል ይነዱን ዘንድ ፍጹም መሐይሞች ሊያደርጉን ይሞክራሉ እግዚአብሄር በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3:6-7 ላይ *«ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ ሐጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትም የሚወሰዱትን' ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና::»*

በሌላ አነጋገር ሰይጣን ሰዎችን ወደ ድንቁርና ለመውሰድ ይሞክራል ግራ ሊያጋባቸው ይሞክራል እግዚአብሄር ሰይጣን ሰዎች ፈጽሞ መሐይማን ሆነው ይቀሩ ዘንድ ድንቁርናን በማምጣት ሁሌም የሚማሩ ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ የማይደርሱ ሰዎች እንደሚያደርጋቸው ይናገራል ሰይጣን ድንቁርናና ግትርነት ውስጥ እንዲወድቁ ያደርጋቸዋል ይህ ድንቁርናና ግትርነትም ወደ እውነት እውቀት እንዳይደርሱ ይከለክላቸዋል ሰዎችን መሐይማን ማድረግ የሰይጣን ስትራቴጂ ነው::

ብዙ ክርስቲያኖች ምስክርነትን በመስጠት ሌሎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ በመመስከር ረገድ በጣም ቀናተኞች ናቸው የሰይጣን አገልጋዮች ሰዎችን በመለወጥ ጥረታቸው በጣም ትጉሃን ናቸው ምክንያቱም ቅንአታቸው ታላቅ ነውና ደካሞች የሚመስሉትንም ያጠምዳሉ በሌላ አነጋገር ሰይጣን ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ከሆኑ ሊሳካላቸው ከሕመሞቻቸው ሊፈወሱ ወይም በስራቸውም ሊከናወንላቸው እንደሚገባ ይናገራል ሰይጣን በእነዚህ አባባሎች ፍላጎቶቻቸውን ያነሳሳና በራሱ ስትራቴጂ መሰረት ያጠምዳቸዋል ይህ የድንቁርና ውጤት ነው የእግዚአብሄር ቃል የመሃይማን ቅንአት ፈጽሞ እውነት ላይ መድረስ እንደማይችል የሚናገረው ለዚህ ነው ቃሉ የእግዚአብሄርን ጽድቅ የሚቃወሙ ሰዎች ሁልጊዜ ቢማሩም ወደ እውነት እውቀት መድረስ እንደማይችሉ ይናገራል በሌላ አነጋገር ዳግም ያልተወለዱ መሐይም ሰዎች ከሰይጣን አገልጋዮች ምንም ያህል ብዙ ቢማሩም ፈጽሞ ወደ እውነት መድረስ አይችሉም በየቀኑ ሌሎችን ያስተምሩ ይሆናል ተከታዮቻቸው ግን አሁንም የእነርሱ ትምህርቶች ካበቁ በኋላ እንኳን መጀመሪያ መማር እንደጀመሩበት ጊዜ ሐጢያተኞች ሆነው ይቀራሉ::

ጌታ በዮሐንስ 8:32 ላይ እንዲህ ብሎዋል *«እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም ሰርነት ያወጣችኋል»* ስለዚህ እግዚአብሄር እውነትን እንድናውቅ እየነገረን ነው በመሆኑም ጌታ እውነትን እንድናውቅ ሲነግረን በአንጻሩ ሰይጣን ደግሞ ቀናተኞች እንድንሆን ይነግረናል::

የእግዚአብሄር ጽድቅ ምንድነው? እርሱ እውነት ነው ትክክለኛው እውነት ምንድነው? ትክክለኛው እውነት የሰዎችን ሕይወት የሚያድነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት ነው ስለዚህ አንድ ሰው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል

ሲያውቅ የዘላለምን ሕይወት መቀበል ይችላል በአንጻሩ ሰይጣን ሰዎችን መሐይማን በማድረግ የዘላለምን ሕይወት እንዳያገኙ ይከለክላቸዋል ለዘላለም ይቀጡ ዘንድ እስከመጨረሻው ድረስ ሐጢያተኞች እንዲሆኑ ሊያስራቸው ይሞክራል የሰይጣን አገልጋዮች ሰዎች የእግዚአብሄርን ጽድቅ እውቀት እንዳያገኙ ለመከልከል የድንቁርናን ቃሎች ማስፋፋታቸውን የሚቀጥሉት ለዚህ ነው።

ሰይጣናዊ እምነት ይህ ነው *«የአምልኮት መልክ አላቸው ሐይሉን ግን ክደዋል» (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:5)* የአምልኮት ሐይል የሚያመላክተው ሰው በእግዚአብሄር ጽድቅ በማመን ጻድቅ የሚሆንበትን የወንጌል ሐይል ነው ስለዚህ ሰይጣን ሰዎች የእግዚአብሄርን ጽድቅ ሳይሆን የራሳቸውን ጽድቅ የእግዚአብሄር ጽድቅ አስመስለው እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል የሰይጣን ሰዎች በእግዚአብሄር ጽድቅ እንደሚያምኑ ቢያስመስሉም እውነተኛውን የአምልኮት ሐይል በእምነት ሊቀበሉ አይችሉም ዲያብሎስ እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ያስወገደ የመሆኑን እውነት ከማወቅ ሊከለክለን ይሞክራል አሁን ሙሉ በሙሉ ሐጢያት አልባ እንደሆንን ከመገንዘብ ሊያሰናክለን ይሞክራል ሰይጣን የሚያደርገው ነገር ቢኖር ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ እንዲመስሉ ውጫዊ የአምልኮት መልክ እንዲለብሱ ማድረግ ብቻ ነው ሰይጣን ግልጽ የሆነ አላማ ሳይኖራቸውና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ እንዲመስሉ በማድረግ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዳይቀበሉ ይከለክላቸዋል።

በሌላ አነጋገር ሰይጣን ሰዎችን ቀናተኞች እንዲሆኑ በማነሳሳት ወደ እውነት መድረስ እንዳይችሉ ያደርጋል እንዲህ በማድረግም በርካታ ክርስቲያኖች በመጨረሻ በራሳቸው ድክመቶች እንዲሞቱ ወደ ድንቁርና ይነዳቸዋል ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም በልቦቻቸው ውስጥ አሁንም

ሐጢያቶቻቸውን ይዘው እንዲቆዩ ማረጋገጥ የሰይጣን ስራ ነው አሳዛኙ ነገር እነዚህ የሰይጣን ትምህርቶች በዘመኑ ክርስትና ውስጥ በጣሙን የገነኑ መሆናቸው ነው::

በእግዚአብሄር ቃል መሰረት ውሸቱን ከእውነት መለየትይገባናል

እግዚአብሄር በሁለተኛው የፍጥረት ቀን ያደረገው በቃሉ መሰረት ጠፈርን መለየት ነበር እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ እንዲለይ አዘዘ እግዚአብሄር የተናገረው ሁሉ እንደዚያው ይፈጸማል እዚህ ላይ በእግዚአብሄር ቃል መሰረት «መለየት» ማለት ምን እንደሆነ እናስብ

እግዚአብሄር ቃሉን ከሰይጣን ቃሎች ለይቶዋል እግዚአብሄር እውነትን ከሐሰት የሚለየው በምን መስፈርት ነው? እግዚአብሄር በዘፍጥረት 1:2 ላይ *«የእግዚአብሄርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር»* እንደሚል እርሱ ሁሌም የሚሰራው በቃሉ ነው ስለዚህ በቃሉ ዳግም የተወለዱትን ዳግም ካልተወለዱት መለየት ይችላል::

በእግዚአብሄር ቃል በተሰጠ አንድ ትምህርት ላይ በምናስብበት ጊዜ ትምህርቱ በእግዚአብሄር ቃል መሰረት ትክክል እንዳልሆነ ስናውቅ የሰይጣን ቃሎች ነው ብለን መደምደም እንችላለን በሌላ አነጋገር የምንሰማው የምናምነውና በልቦቻችን ውስጥ የምንጠብቀው የእግዚአብሄርን የጽድቅ ቃል ስለሆነ ሰዎች የሚነግሩንን በእግዚአብሄር ቃል መሰረት በምናሰላስልበት ጊዜ ትክክል ካልሆነ የሰይጣን ቃል ነው ብለን ልንፈርድ እንችላለን በሌላ በኩል በእግዚአብሄር ቃል

በተንጸባረቀው መሰረት እውነት ከሆነ የእግዚአብሄርን ጽድቅ የሚገልጥ የእውነት ቃል ነው።

በሌላ አነጋገር ጻድቃን ምንም አይነት ትምህርቶች ቢገጥሙዋቸው ከጠፈር በላይ ባለ ቃልና ከጠፈር በታች ባለ ቃል ሊለዩዋቸው ይችላሉ ከሰባኪዎች አንደበት የሚወጡት ትምህርቶች ወይ የእግዚአብሄር ቃሎች ናቸው አለበለዚያም የሰይጣን ቃሎች ናቸው እነዚህ ትምህርቶች በግልጽ ከእግዚአብሄር የጽድቅ ቃል ጋር የማይስማሙ ከሆኑ ምንም ያህል የተቀነባበሩና የሚስቡ ቢሆኑና እነዚህን ትምህርቶች የሚያቀርበው ሰውም ምንም ያህል ታዋቂና የተከበረ ቢሆን እነዚህን ትምህርቶች ችላ ልንላቸው ይገባናል የእግዚአብሄርን ጽድቅ ያልያዙ ቃሎች የእግዚአብሄር ቃል ሳይሆኑ የሰይጣን ቃሎች መሆናቸው ግልጽ መሆን አለበት ክብር ባለው ቤተክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል ሆነው ቢሰበኩም ከእነርሱ ልንርቅ ይገባናል።

አንድን ትምህርት ከጠፈር በላይ ያለ ቃልና ከጠፈር በታች ያለ ቃል አድርገን በምንለይበት ጊዜ ለዚህ መለኪያ የሚሆነው የእግዚአብሄር የጽድቅ ቃል ነው የዚህ አለም ሰዎች አንድ ሰው ሲናገር ሲሰሙ የሚያደምጡት በእግዚአብሄር ቃል መለኪያ ላይ ተመስርተው አይደለም ነገር ግን የጀርባ ማንነቱን ማለትም ስልጣኑን፣ ሐብቱን፣ ዝናውን፣ ወይም ትምህርቱን በመመልከት ብቻ ነው ነገር ግን በዚህ አይነቱ መለኪያ ላይ በመመስረት ከጠፈር በላይ ያለውን ቃልና ከጠፈር በታች ያለውን ቃል ማለትም የእግዚአብሄርን ቃል ከሰይጣን ቃሎች መለየት አይቻልም የአንድን ሰው ቃሎች በምንሰማበት ጊዜ የእግዚአብሄር ቃል የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ የምንገልጥ ከሆነ የሰይጣንን ቃሎች ከእግዚአብሄር ቃል በግልጥ መለየት እንችላለን።

ስለዚህ የአለምን መለኪያ መጣል አለብን በእግዚአብሄር ቃል ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርተንም ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃና ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ መለየት ይገባናል እናንተም ደግሞ በእውነት ቃል አማካይነት ራሳችሁን ከግራ መጋባት ነጻ ማውጣት ይገባችኋል።

በሰይጣን የተሰሩ የሐሰት ትምህርቶች

አንዳንድ ሰዎች ሰው ሙሉ በሙሉ የሚድነው በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በኋላ ቅድስና ላይ ሲደርስ ብቻ ነው ይላሉ በክርስትና ውስጥ እንዲህ ያለው አባባል የሐዲት ቅድስና ትምህርት ተብሎ ይታወቃል ይህ ትምህርት ከመንጻት ትምህርት ጋር ተያይዞ እውቅና ያገኘ ክርስትና ተብሎ በሚጠራው ውስጥ በይፋ ተቀባይነትን ካገኙ ትክክለኛ ትምህርቶች አንዱ ነው ነገር ግን ይህ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተረጋገጠው የእውነት ቃል የመጣ አይደለም።

ይህንን መሰረተ ቢስ ትምህርት የሚያቀነቅኑ ሰዎች የሚያቀርቡዋቸው መከራከሪያዎች የሚከተሉት ናቸው በመጀመሪያ እነርሱም *«እግዚአብሄርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለንና ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው» (ሮሜ 8:28-30)* የሚለውን ቃል ያነበንባሉ ሰዎች በዚህ ቃል ላይ ተመስርተው «ወደ መንፈሳዊ ብስለት የሚያደርሱ ሰባት ደረጃዎች» በሚል የቅድስናን ትምህርት ፈጥረው ይናገሩለታል

ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ ውስጥ *«ልጆ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና»* የሚለውን ቁጥር 29ን በመጥቀስ ክርስቲያኖች ሲሸመግሉ በስጋ ይቀደሱና ቀስ በቀስ ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ይመስላሉ በማለት ይከራከራሉ::

ነገር ግን ይህ ምንባብ የሚለው እንደዚያ አይደለም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር የልጁን መልክ እንድንመስል ሲናገር ይህ ማለት የጌታን ውጫዊ ገጽታ መምሰል አለብን ማለት አይደለም እግዚአብሄር አስቀድሞ የወሰነንና የጠራን በእምነት በአንድ ጊዜ የእግዚአብሄርን ልጅ መልክ እንመስል ዘንድ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በልቦቻችን ውስጥ ለማኖርና በእርሱም እንድናምን ለማድረግ ነው::

አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት በተቀበሉ ሰዎች ሁሉ ልቦች ውስጥ የእግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ ይኖራል መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው በጻድቃን ልቦች ውስጥ ነው ስለዚህ የእግዚአብሄርን ልጅ መልክ የሚመስሉት በልባቸው ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች ናቸው እግዚአብሄር እንዲህ አስቀድሞ የወሰነንና ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የጠራን የሐጢያቶቻችንን ስርየት ለአንዱና ለመጨረሻ እንቀበል ዘንድ ነው::

ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉና መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች የእግዚአብሄር ልጆች ናቸው መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ሰዎች የእግዚአብሄር ልጆች አይደሉም ይህ ሆኖ ሳለ ግን ብዙ ሰዎች በሮሜ 8:29-30 ያለውን ምንባብ በተሳሳተ መንገድ ተርጉመውታል በዚህ ምክንያትም ሰው ሙሉ በሙሉ ይድን ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በኋላ መቀደስ አለበት ብለው

ወደ ማመንና መከራከር ደርሰዋል የቅድስና ትምህርት እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ራሱ ትሁትና ገር መሆን እንዳለብን በመናገር ሰዎች በስጋዊ ባህሪያቶቻቸው ላይ እንዲያተኩሩ ይመራቸዋል ስለዚህ ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች የሮሜን ምንባብ በመጥቀስ ሰባቱን የቅድስና ደረጃዎች ያብራራሉ።

ሮሜ 8:30 እንዲህ ይላል *«አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው»* አንዳንድ ሰዎች በዚህ ምንባብ ላይ ተመስርተው አስቀድሞ የመወሰንን ትምህርት ይደግፋሉ ነገር ግን የዚህ ምንባብ ትክክለኛ ትርጉም ሰው ሰራሽ አባባል ከሆነው አስቀድሞ የመወሰን ትምህርት ፈጽሞ የተለየ ነው እግዚአብሄር አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠርቶዋቸዋል ማለት እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ መላውን ሕዝብ መርጦታል ማለት ነው አዳም ሐጢያት በሰራ ጊዜ እግዚአብሄር የመስዋዕቱን እንስሳ ቁርበት አለበሰው ልክ እንደዚሁ እግዚአብሄር እኛን የሴቲቱ ዘርና የመስዋዕት ቁርባናችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ እንድንነጻ ሊያስችለን ወሰነ ስለዚህ «አስቀድሞ የወሰናቸውንም» የሚለው ሐረግ የሚያመላክተው ኢየሱስን ክርስቶስንና አዳም ዘር የሆኑትን ሐጢያተኞች ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ለመቀበል የሚመጡትን ሁሉ ነው።

ስለዚህ እዚህ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ *«አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው»* ሲል አምላካችን የዚህ አለም ሐጢያተኞች በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲጠሩና በኢየሱስ ክርስቶስ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዲቀበሉ አስቀድሞ ወስኖዋል

ማለት ነው እግዚአብሄር የሐጢያቶቻቸውን ስርየትን የተቀበሉትን ሰዎች ጻድቃን ብሎ ይጠራቸዋል የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር በሙሉ አልብሶዋቸው የራሱ ልጆች አድርጎዋቸዋል ይህ ሁሉ ሐጢያተኞችን ልጆቹ በሚያደርገው የእግዚአብሄር ዕቅድ ውስጥ ተካቷል ይህ የእግዚአብሄር ሕግ ነው።።

መጽሐፍ ቅዱስ «አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው» ሲል እግዚአብሄር እኛን ሰዎችን ጠርቶን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን ፈጽሞ ደምስሶዋል ማለት ነው እርሱ ፈጽሞ ጻድቃን አድርጎናል የጠራቸውንም ደግሞ ቀድሶዋቸዋል አሁን ይህንን አስተዋላችሁትን? ይህ ሁሉ የሆነው በአንድ ጊዜና ለአንዴና ለመጨረሻ ነው።።

ከእግዚአብሄር ዕይታ አንጻር ይህ ሰፋ ያለ ዕቅድና በረጅም ጊዜ ተግባራዊ መሆንን የሚጠይቅ ነው ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን ለራሳችን በምናውልበት ጊዜ እነዚያን በረከቶች ሁሉ ወዲያውኑ ተቀብለናል እገግዚአብሄር ስለጠራን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ደምስሶዋል የሐጢያቶቻችንን ስርየት ስለተቀበልን ጻድቃን ሆነናል የከበርነውንም በዚህ መልኩ ነው እኛ ከብረናል ማለት እግዚአብሄር የእርሱ መልክ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን በልቦቻችን ውስጥ ስለሰጠን አሁን ሐጢያተኞች የእግዚአብሄር ልጆች ይሆናሉ የእግዚአብሄር ልጆች መሆን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ከእግዚአብሄር ጋር አብሮ የመሆን ክብር ነው።።

ይህ ሁሉ የሆነው በአንድ ጊዜ ነው ይህ የሆነው በአንድ ጊዜ ስለሆነ ሰው ደህንነት ላይ የሚደርሰው በሰባቱ የቅድስና ደረጃዎች አማካይነት ነው ማለት የሰይጣንን ቃሎች መናገር ነው የዚህ ትምህርት አቀንቃኞች ሰው በዚህ አለም ላይ ሳለ

በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነና ወደ ቅድስና በሚያደርሰው መንገድ ላይ በትጋት ከተጓዘ በድንገት ይለወጥና በዚህ ምድር ላይ ልክ እንደ እግዚአብሄር ቅዱስ ይሆናል በማለት ሙጭጭ ይላሉ ይህ እሳቤ የሰው አስተሳሰብና የሰይጣን ቃል ነው የሰይጣን ቃሎች የሚያመጡት ነገር ቢኖር ውዥንብርንና ሰዎችን መሐይማን ማድረግ ነው።

እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በዕቅድ ጠርቶናል ለዚህ የእግዚአብሄር ጥሪ መልስ የሰጡትን ሰዎችም ለአንዱና ለመጨረሻ ጻድቃን አድርጎዋቸዋል በውሃውና በመንፈሱም ወንጌል በአንድ ጊዜ ቀድሶዋቸዋል እግዚአብሄር በእርሱ ጽድቅ በማመን ልጆቹ እንሆን ዘንድ አክብሮናል እግዚአብሄር ለአንዱና ለመጨረሻ የፈጸመው ደህንነትና ቅድስና ሌላ ሳይሆን ይህ ነው ስለዚህ ሰዎች ቅዱሳን የሆኑት በራሳቸው ጥረቶች አይደለም።

አጋር ምዕመናኖቼ ሰዎች የሐጢያትን ስርየት ከተቀበሉ በኋላ ቢሞክሩ በእርግጥ ይበልጥ ቅዱሳን ይሆናሉን? የለም በምንም ሁኔታ ይበልጥ ቅዱሳን አይሆኑም ልቦቻችን አስቀድመው በእግዚአብሄር ጽድቅ ቅዱሳን ቢሆኑም ስጋችን ግን እስከምንሞት ድረስ ጎዶሎ ሆኖ ይቀራል ሐዋርያው ጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት በማመን የደህንነታችንን ማረጋገጫ ማግኘታችን የስጋችን ርኩሰት ተወግዶዋል ማለት ሳይሆን የእግዚአብሄርን ጽድቅ በእምነት ለብሰናል ከአሁን ጀምሮም ፈቃዱን እንከተላለን ማለት እንደሆነ የተናገረው ለዚህ ነው። (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)

ስለዚህ መንግስተ ሰማይ የምንገባው በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ባለን እምነታችን ብቻ ነው እግዚአብሄርን ስንታመንና እርሱን ስንከተል ሕይወታችንን በመኖር የምንቀጥለው በልባችን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስላለ ነው እኛ የምንለወጠው በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያደረውን የእግዚአብሄር ቃል እውነት

በመከተል ነው እውነትን መከተል የምንችለውም እግዚአብሄር ባጠናቀቀው ደህንነት በማመን ብቻ ነው በስጋዊ ጥረቶቻችን ራሳችንን መለወጥ አንችልም በዚህ ሁሉ ለማመን እምነታችንን ስንታመን ይህ የሆነልን ራሱ አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ስለቀደሰንና ስላከበረን ነው።።

ይህ በእኛ ላይ የሆነው በዚህ ሁሉ ለማመን በእምነታችን በመታመናችን ራሱ አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ቀድሞውኑም ስለቀደሰንና ስላከበረን ነው ስለዚህ የእግዚአብሄር ልጆች ያልሆኑ ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች ከእኛ ዳግም ከተወለድነው ተለይተዋል ስለዚህ እኛ አሁን ከእነርሱ የተለየ ሕይወት እየኖርን ነው ገና ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች ሰባቱን የቅድስና ደረጃዎች ይናገራሉ አንድ ቀንም ኢየሱስን እንመስላለን ይላሉ ስለዚህ በማንኛውም መከራ ውስጥ ታግሰው ያልፋሉ የሚሹትን ሁሉ ይታገሳሉ እውነቱ ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ቅዱስ የማይሆንና ለረጅም ጊዜ ነጽተው አይቆዩም የሰው ትዕግስት ገደብ ስላለው እነርሱ ከቅድስና ርቀው ውሎ አድሮ ትዕግስታቸው ያልቅና ይፈነዳሉ በመጨረሻም ይበልጥ ግትሮችና ራስ ወዳዶች ይሆናሉ ሰው በስጋው ሊቀደስ ይችላል የሚለው እሳቤ የሰው የተሳሳተ እሳቤ ውጤት ነው።።

ስለዚህ በእውነት ቃል ላይ ተመስርተን በሐዲት የመቀደስን ትምህርት ስናስብ በትክክል የሰይጣን ትምህርት ሆኖ ይገለጣል ሰው ዳግም ሳይወለድ ለረጅም ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ ባመነ ቁጥር በራሱ ግትርነትና ግብዝነት ይበልጥ ይደነድናል እንዲህ ያሉ ሰዎች በውጭ ሲታዩ ጻድቃን ይመስሉ ይሆናል ልቦቻቸው ግን ፈጽመው የረከሱ ናቸው ሕሊናቸው ዳግም መወለድ ስለተሳነውም ሁሌም የሚሮጡት ወደ ሐጢያት ሆኖ ሳለ እንደዚያ እንዳይደሉ ያስመስላሉ ይህ ምን ያህል ክፉ ነው? እነርሱ ከውጭ ጥሩ መስለው ለመታየት በግብዝነት የተቀባቡ

መቃብር ናቸው በውስጣቸው ግን ጨለማ በጥልቁ ላይ አለ በሐጢያት ውስጥ እየሰጠሙና እየበሰበሱም ናቸው ብዙ ሰዎችን የማሳሳታቸውና የማታለላቸው ምግባሮቻቸውም ያን ያህል በጣም የረከሱና ይበልጥ የከፉ ናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እነዚህን ሰዎች የተለሰኑ መቃብሮች ብሎ የሚጠራቸው ለዚህ ነው።

ሰይጣን የተናገረው ሁሉ ውሸት ነው እነዚህን ቃሎች አብዝተን በተከተልን ቁጥር ይበልጥ እንደተታለልን እንገነዘባለን

በተሳሳተ እምነት ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው እንደሚያምኑ የሚናገሩ ሰዎች የአምልኮት መልክ ብቻ አላቸው መጽሐፍ ቅዱስ *«የአምልኮት መልክ አላቸው ሐይሉን ግን ክደዋል» (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:5)* ብሎ እንደወቀሳቸው የእምነት ሐይል የላቸውም ሐጢያተኞች በትክክል አምልኮት ሊኖራቸው አይችልም እነርሱ ያላቸው ነገር ቢኖር ውጫዊ የሆነ የእምነት ሕይወት ገጽታ ነው ሲያመልኩ ይንበረከካሉ ሲጸልዩም እጆቻቸውን ያጣምራሉ በእነዚህ ነገሮች የተካኑ ናቸው በተደጋጋሚም በአንደበቶቻቸው ቅድስናን ያነበንባሉ ልቦቻቸው ግን በስስትና በመሳምጀት የተሞሉ ስለሆኑ በሁሉም አይነት ፍትወት የሚነዱ ናቸው ጌታ ይህንን አይቶ *«የአምልኮት መልክ አላቸው ሐይሉን ግን ክደዋል»* አላቸው።

ልቦቻቸው ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች አለምን እንጂ እግዚአብሄርን አይከተሉም በአለም ተቀባይነትን ለማግኘ ትናአለማዊ ሐብቶቻቸውንም ለማብዛት ይሞክራሉ ከዚህ የተነሳም ልቦቻቸው ፈጽመው ረክሰዋል በሌላ አነጋገር ለመጀመሪያ ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑበት ጊዜ ይልቅ

የኋለኛው ዘመናቸው ይበልጥ የረከሰ ነው ጌታችን በእግዚአብሄር እናምናለን የሚሉ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ሙሉ በሙሉ ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች መጨረሻቸው ከመጀመሪያው ይልቅ የረከሰ እንደሚሆን ግልጽ አድርጓል ጌታ መጨረሻቸው ይበልጥ የተጎሳቆለ እንደሚሆንም ተናግሮዋል ስለዚህ የሰይጣን ቃሎች በቃሉ አማካይነት ሲታዩ በግልጽ ተለይተው ይታወቃሉ።

አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት ያለባቸው ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም በተጨባጭ ያመኑ በሰይጣን ቃሎች ነው አንድ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያምን እየተናገረ የእግዚአብሄርን ቃል ከልቡ የማይከተል ከሆነ የዚህ ምክንያቱ በዚህ ጊዜ ሁሉ የሰይጣንን ቃሎች መከተሉ ነው ሰው በትክክል በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል የሚያምን ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል አያዳግተውም እኛ ቃሉ የማይወድቅ መሆን አውቀን ጌታን እንከተላለን በእርግጥ ይህንን ማድረግ ለእኛ አዳጋች ነው ነገር ግን ከመከተል በቀር ምርጫ የለንም እንዲህ የጌታን ቃል በምንከተልበት ጊዜ ልቦቻችን ይበረታሉ ይደሰታሉም።

በአንጻሩ ሰው የሰይጣንን ቃሎች ሲቀተል አብዝቶ በተከተለ ቁጥር ይበልጥ ግራ ይጋባል ሕሊናውም ይበልጥ ይረክሳል እነዚህ ሰዎች በቃሎቻቸው ጌታን እንደሚከተሉ ይናገራሉ ነገር ግን የራሳቸውን ትምህርቶች በበለጠ ቅንአት ያቆማሉ እነዚህ ትምህርቶች የሰይጣን ቃሎ ናቸው ትምህርቶቹ እየጠነከሩ ሲሄዱም የተከታዮቻቸው ልቦች ይበልጥ የረከሱ ይሆናሉ እንደዚያም ሆኖ በምግባሮቻቸው መልንም ሕይወትን እንደሚኖሩ ያስመስላሉ በልቦቻቸው ውስጥ ሁሉም አይነት ርኩሰቶች ቢኖሩም ምግባሮቻቸው ጥሩ እስከሆኑ ድረስ ርኩሳን እንዳልሆኑ በመናገር ራሳቸውንም ያታልላሉ።

የእግዚአብሄር ጽድቅ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በሚያምኑ አማኞች አማካይነት ተገልጦዋል

በአንጻሩ በእውነት ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ልቦች መስመራቸውን ሲስቱ መንፈስ ቅዱስ ቀደም ብሎ ልባቸውን ይወቅሳል ዳግም ተወለድን እንኳን ልቦቻችን የሚስቱበት ወቅት አለ ልቦቻችንን ካልመለስናቸው በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ ያዝናል ስለዚህ ልቦቻችን ሰላም አይኖራቸውም ልቦቻችን ይረበሻሉ ብዙም ሳይቆይ ልቦቻችን እንደገና ይሰቃያሉ እንዲህ በቀላሉ ክፉ ምግባሮችን የማንሰራው ልቦቻችን ስለሚሰቃዩ ነው ዳግም የተወለዱ ሰዎች በአንድ መንገድ ላይ በሚጓዙበት ጊዜ በዚህ መንገድ ላይ በነጻነት መጓዛቸውን የሚቀጥሉት ልቦቻቸው ሰላም ከሆኑ ብቻ ነው በሌላ አነጋገር በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ ልቦቻችንን ስለሚወቅስ በተሳሳተ መንገድ ላይ መጓዛችንን መቀጠል አንችልም ምክንያቱም ልቦቻችን ምቾት አይሰማቸውም አይደሰቱምም ዳግም የተወለዱ ሰዎች የሚገጥማቸው ይህ ነው።

በአንጻሩ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ያልተቀበሉ በልባቸውም ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሌለባቸው ሰዎች የሰይጣንን ቃሎች መከተላቸውን ይቀጥላሉ ምክንያቱም የሰይጣንን ቃሎች ከሙሉ ልባቸው አምነው የሚወጡ ሰዎች መሄድ የሚገባቸው በስስት የተሞላው ልባቸው እንደመራቸው ነውና ስለዚህ የእግዚአብሄር ቃል ሊቆጣጠራቸው አይችልም ዳግም ያልተወለዱ ክርስቲያኖች አሁን እየጠጡ ያሉት ከጠፈር በታች ያለውን የሰይጣንን ቃሎች ውሃ በመሆኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማያምኑት ከአለም ሰዎች የተለዩ አይደሉም የዘመኑን ክርስቲያኖች ክርስቲያን ካልሆኑት መለየቱ አዳጋች የሚሆነው ለዚህ ነው።

የሰይጣንን ቃሎች የሚያምኑ ሰዎች በአለም ፍትወት መሰረት ይኖራሉ የሰይጣንን ቃሎች የሚከተሉ ሰዎች ከአለም ሰዎች በምንም የተለዩ አይደሉም በተቃራኒው እንዲያውም ከአለም ሰዎች ይበልጥ የረከሱ ሊሆኑ ይችላሉ ዳግም ሳይወለዱ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች በሰይጣን ቃሎች ስለሚያምኑ ምንም መንፈሳዊ ፍሬ አያፈሩም ሐጢያተኞች ሆነው ይቀራሉ በእነርሱ አማካይነትም የሐጢያትን ስርየት የተቀበለ ሰው የለም ወንጌል የተሰበከላቸው እነዚያው ሰዎች አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች ሆነው ቀርተዋል የሰውን ቃሎች የሚያምኑና የሰይጣንን ቃሎች የሚከተሉ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያምኑ ቢናገሩም እግዚአብሄርን የሚያስደስት ፍሬ የሌላቸው ለዚህ ነው እነዚህ ሰዎች በቃሉ አማካይነት በዚህ ሁሉ ዘመን የሰይጣንን ቃሎች እንደተከተሉ ያለ ምንም ማመንታት መገንዘብ አለባቸው።

በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ የምታምኑ ከሆነ እናንተም ደግሞ እምነታችሁን በእግዚአብሄር ቃል መመርመር አለባችሁ የእግዚአብሄርን ቃል እየተከተላችሁ ነውን? መጽሐፍ ቅዱስ የማይከተል ሰው ቢኖር እርሱ አሁን ሰይጣንን እየተከተለ ነው ለልክ እርሱ እንደተታለለ ሁሉ አስተማሪውም ደግሞ በሰይጣን ተታሎዋል እርሱ በእግዚአብሄር ቃል ፊት ይህንን እውነት መደበቅ አይችልም።

ሰው የሰይጣንን ቃሎች እንደተከተለ ካወቀ ይህ ሰው አሁን ከዚህ ነጻ መውጣት ይችላል ሰው እውነትን እንዳልተከተለ ከተገነዘበ በመጀመሪያ የሰይጣንን ትምህርቶች ከሚያሰራጭ የሐሰት ጉባኤ መውጣት አለበት እንዲህ ያሉ ሰዎች ሐሰተኛ ወደሆነ ቤተክርስቲያን መሄዳቸውን ሲያቆሙ ብዙም ሳይቆይ ወደ እግዚአብሄር ጽድቅ መመለስ ይችላሉ።

ሰው የእግዚአብሄርን ቃል ያለ ማመንታት ማወቅና ግልጽ

በሆነ መረዳት መከተል አለበት የሰይጣንን ቃሎች እየተከተሉ እንደሆኑ እውነቱን የማያውቁና ዳግም ወዳልተወለደች ቤተክርስቲያን የሚሄዱ ሰዎች የሚጠብቃቸው ነገር ቢኖር ጥፋት ብቻ ነው እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃና ከጠፈር በታችን ያለውን ውሃ በግልጽ ለይቶታል ስለዚህ እነዚያ ሰዎች የሰይጣንን ቃሎች መከተላቸውን ከቀጠሉና ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ብቻ የሚጠጡ ከሆኑ እግዚአብሄር እንደሚለያቸው አያጠራጥርም ስለዚህ ወደ እግዚአብሄር ካልተመለሱና እስከ መጨረሻውም ድረስ ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ በመጠጣት የሚቀጥሉ ከሆነ ይጠፋሉ ይህ የእግዚአብሄር ስህተት አይደለም።

ይህንን በማጤን አንድ ክርስቲያን ለረጅም ጊዜ በእግዚአብሄር ያመነ ቢሆንም እንኳን የሚያሳየው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ከሌለው በሰይጣን ቃሎች እንዳመነ ተገንዝቦ የእግዚአብሄርን ቃል መሻትና መፈለግ አለበት እግዚአብሄርን ሲሻ እግዚአብሄርም ይገናኘዋል ነገር ግን ዳግም ያልተወለደችው የሰይጣን ቤተክርስቲያን በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ስልጣን እየሰጠችው በመቀጠል ሌላ የትም ቦታ እንዳይሄድ አጥብቃ ታስረዋለች በአንዳንድ ቤተክርስቲያኖች መጋቢዎች ዳግም መወለድ ለተሳናቻው ብቻ ሳይሆን በታማኝነት ቤተክርስቲያን ለማይመጡት ሰዎች ድቁናንና ሽማግሌ የመሆን ስልጣንን ይሰጡዋቸዋል በዚህም ልቦቻቸውን በክብር ለማርንት ሲሉ እንዲህ አድርገው የቤተክርስቲያን ስልጣኖችን በማግነን ድቁናንና የሽማግሌነትን ስልጣኖች ያስረክባሉ ምክንያቱም እነርሱ ቢመሩዋቸውም ጉባኤያቸው ለውጥ ደስታና አንዳች እርካታ የለውምና ቅዱሳኖችን በመንፈሳዊ ሁኔታ በትክክል መምራት ያልቻሉ መጋቢዎች እርካ ያጣውን ጉባኤ ሲመለከቱ ለተከታዮቻቸው ሙገሳዎችን ያበዙላቸዋል ምክንያቱም

በመንፈሳዊ ሁኔታ ሊያረኩዋቸው አልቻሉምና ስለዚህ አንድ ሰው እምነታችሁ በትክክል ሳይጸና የቤተክርስቲያን ስልጣን ሊሰጣችሁ የሚፈልግ ከሆነ እርሱ ሐሰተኛ እረኛ እንደሆነ ልትገነዘቡ ይገባችኋል።

ዳግም የተወለደች ቤተክርስቲያን የስልጣን ቦታዎችዋን ስትመሰርት ይህንን የምታደርገው በሌሎች መለኪያዎች ሳይሆን ቅዱሳኖች በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ እምነትና የማገልገል ስጦታ ያላቸው በመሆናቸው ላይ ተመስርታ ነው ዳግም የተወለደች ቤተክርስቲያን ለረጅም ጊዜ ቤተክርስቲያን ስላዘወተረ ወይም እርሱን ለማስደሰት ስትል ብቻ ለማንም ሰው የቤተክርስቲያን ስልጣን አትሰጥም ይልቁንም የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ለዚህ ሰው የቤተክርስቲያንን ስልጣን በአደራ የምትሰጠው ይህ ሰው በእግዚአብሄር ጽድቅ ሲያምንና እርሱን ማገልገል የሚችል ሲሆን ብቻ ነው።

ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች ግን የሚተዳደሩት በሰይጣን ቃሎች ነው ስለዚህ የቤተክርስቲያን ስልጣኖችን በመስጠት ሰዎችን ለማርኳት ይሞክራሉ ስለዚህ አንድ መጋቢ አሁንም በልቦቻችሁ ውስጥ ሐጢያት ቢኖርባችሁም እንኳን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አንድ የስልጣን ቦታ ሊሰጣችሁና ሊያከብራሁ የሚፈልግ ከሆነ እናንተም ጉልበት አልባ ከሆናችሁና ልታደርጉት የምትችሉት ምንም ነገር ከሌለ ሰይጣን እያታለላችሁ እንደሆነ ልትገነዘቡ ይገባችኋል ይህ መጋቢ የእግዚአብሄር አገልጋይ እንደሆነ በግልጽ ልትገነዘቡ ይገባችኋል እንዲህ ካሉ ሰዎችም ልትሸሹ ይገባችኋል እናንተም ራሳችሁ መዳን የምትችሉት ያን ጊዜ ብቻ ነው ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ መለየት ሌላ ሳይሆን ይህ ነው ይህ በግልጽ መለየት አለበት።

እግዚአብሄር በፍጥረቱ በሁለተኛው ቀን ምን አደረገ?

እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየ እኛም እንደዚሁ የሰይጣንን ቃሎች ከእግዚአብሄር ቃል መለየት አለብን የምንለያቸው እንዴት ነው? ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ የምንለየው በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተመስርተን ነው።

እኛ አሁን ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ እየጠጣንና ሕይወታችንም በዲያብሎስ ቁጥጥር ስር እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ በግልጽ መገንዘብ ይኖርብናል ኢየሱስ ክርስቶስን ከልባችሁ እያመናችሁት ገናም ጻድቃኖች ካልሆናችሁ ይህ ማለት እየጠጣችሁት ያለው ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ማለትም የምድርን ውሃ ነው ማለት ነው በኢየሱስ በማመን ሐጢያት የሌለባቸው ጻድቃን የሆኑና በቃሉ መሰረት የሚኖሩ ሰዎች ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ እየጠጡ የሚኖሩ ሰዎች እንደሆኑ ልትገነዘቡ ይገባችኋል።

አንድ ሰው ለግማሽ ምዕተ አመት ያህል በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በኋላ አሁንም ሐጢያተኛ ከሆነ ይህ ማለት ይህንን ሁሉ ዘመን ያመነው በዲያብሎስ ቃሎች ነው ማለት ነው በአንጻሩ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በትክክል የሚያውቁና የቃሉን ብርሃን በመቀበል ሙሉ በሙሉ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ያገኘ ሰዎች እግዚአብሄር የመራቸው ሰዎች ናቸው እነዚህ ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማይ እየተጓዙ ያሉ የእግዚአብሄር ልጆች ናቸው ክርስቲያኖች ሐጢያተኞች ወይም ጻድቃኖች እንደሆኑ ለሲያል ወይም ለሰማይ የታጩ እንደሆኑና የእግዚአብሄር ልጆች ወይም የዲያብሎስ ልጆች እንደሆኑ በትክክል ለይተው ማወቅ አለባቸው በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተመስርተን ራሳችንን ስንመረምር ሐጢያት የሌለብን ጻድቃን ከሆንን የእግዚአብሄር

ልጆች ሆነን ሰማይ እንገባለን ነገር ግን ሐጢያት ካለብን የሰይጣን አገልጋዮች ሆነን ወደ ሲያል እንጣላለን ስለዚህ እግዚአብሄር ለይቶናል እግዚአብሄር ይህንን በግልጽ አድርጎታል እግዚአብሄር በግልጽ ለይቶናል እኛም ይህንን እናውቃለን ነገር ግን አንዳንዶቻችን አሁንም የራሳችንን ሕሊና እያታለልን ነው።

ሰው ሕሊናውን ሲመለከት ሐጢያተኛ እንደሆነ ወይም ጻድቅ እንደሆነ በግልጽ በግልጽ ይመለከታል ወንጌልን ሰምተን ዳግም ተወልደን ይሁን ወይም አይሁን፣ እኛ ቅዱሳን እንሁን ወይም ሐይማኖተኞች፣ ልቦቻችን ሐጢያት ይኑርባቸው ወይም አይኑርባቸው፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችም በግልጽ ይኖሩብን ወይም አይኑሩብን ሁላችንም ወይ ሐጢያተኞች ነን አለበለዚያም ጻድቃኖች ነን ልቦቻችንን እያታለልን እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ራሳችን በግልጽ መወሰን አለብን እኛ እግዚአብሄር ቤተክርስቲያን አባል እንደሆንን ወይም የዲያብሎስና የአለም ወገን እንደሆንን ራሳችን ለይተን ማወቅ አለብን የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰማ ሰው ሁሉ ራሱን በግልጽ ማወቅ ይችላል ስለዚህ አሁንም ድረስ ራሳቸውን በሰይጣን ቃሎች የሚያስቱ ከጠፈር በታች ባለው ውሃ የሚኖሩና ይህንን ውሃ የሚጠጡ ሰዎች በእግዚአብሄር ሊጠፉ የተገባቸው ናቸው።

ሐጢያተኛ በእውነት ፊት የከፋ ሐጢያተኛ መሆኑን መናዘዝ አለበት

እግዚአብሄር ብርሃንን ከጨለማ ከጠፈር በላ ያለውንም ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ በግልጽ እንደለየ መረዳት አለብን እግዚአብሄር እንዲህ ቢለይም ሰዎች የራሳቸውን ሕሊና በማሳት መጥፋታቸውን እየቀጠሉ እንደሆነ ታውቃላችሁን?

ሰዎች ወደ ሲያል ለመውርዳቸው እግዚአብሄርን መውቀስ አይችሉም ምክንያቱም ሕሊናቸው በልቦቻቸው ውስጥ ያሉትን ሐጢያቶች በእውነተኝነት ቢገነዘቡ፣ በእርግጥም እግዚአብሄርን ቢሹና እውነትንም ከልባቸው ቢፈልጉ እግዚአብሄር በእርግጥም እነዚህ ሰዎች እውነትን እንዲያገኙ ያስችላቸው ነበርና።

አሁን በዚህ አለም ላይ ብርሃኑ አለ እኛ በግልጽ የእውነት ቃል አለን ይህንን ቃል በትክክል የተማረ፣ ያየ፣ ያደመጠና እውነተኝነቱን ያመነ ሰው ሁሉ ዳግም መወለድ ይችላል ከጠፈር በታች ያለውም ውሃ ቢሆን ከጠፈር በላይ ወዳለው ውሃ ሊለወጥ ይችላል በባህር ውስጥ ያለው ውሃ ተኖ ወደ አየር እንደሚነሳና እንደገና ውሃ ሆኖ እንደሚወርድ ሁሉ ከታች ያለውም ውሃ እንደዚሁ ከላይ ወዳለው ውሃ ሊነሳ ይችላል ይህ የሚቻል ቢሆንም ሰዎች አሁንም ራሳቸውን ያታልላሉ ለሲያል የሚታጨትና በከንቱ የሚሰቃዩት ለዚህ ነው ሰው ወደ እግዚአብሄር መመለስና ብርሃንን ማግኘት አለበት ኑዛዜ ሌላ ሳይሆን ይህ ነው።

ጌታ «አምላክ ሆይ እኔ ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ የጠጣሁ ሐጢያተኛ ነኝ ጌታ ሆይ እባክህ አድነኝ» በማለት ወደ እግዚአብሄር የሚመጡትን ሰዎች በእርግጥ ይገናኛቸዋል አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት ያለባቸው ሰዎች በእግዚአብሄር አገልጋዮች ፊት ዳግም በተወለደችው የእርሱ ቤተክርስቲያን ፊት መቅረብና ቃሉን በማድመጥ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት መቀበል አለባቸው።

እግዚአብሄር በሰዎች ልቦች ውስጥ እውነትን ከሐሰት በግልጽ ለይቷል ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ የጠጡ ሐጢያተኞች ይህንን ፈጽሞ መርሳት የለባቸውም ያለ ምንም ማመነታት ዳግም ወደተወለዱ ሰዎች ጉባኤ መምጣት አለባቸው በዚህ መንገድም ያለ ምንም ችግር መለወጥ

አለባቸው እግዚአብሄር ይህንን ልዩነት ቢያደርግም ሰው አሁንም «በኢየሱስ ክርስቶስ ብታምን ሐጢያት ቢኖርብህም እንኳን እግዚአብሄር ጻድቅ አድርጎ ይቆጥርሃል» በሚለው የሰይጣን ትምህርት የራሱን ሕሊና የሚያታልል ከሆነና በዚህም ወደ ሲያል ከተጣለ ይህ ሙሉ በሙሉ የእርሱ ስህተት መሆኑን ልትገነዘቡ ያስፈልጋችኋል።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየው ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ እንደሆነ መረዳት አለብን እግዚአብሄር ትምህርቶችን ሁሉ በእርሱ ቃልና በሰይጣን ቃሎች ለይቶዋቸዋል አሁን ያመንነው የማንን ቃሎች እንደሆነ በተመረኮዘ መልኩ በረከቶቻችንና እርግማኖቻችን ይወሰናሉ ሰው የሚጠጣው ነገር ደስታውን ወይም ሐዘኑን ይወስናል።

ራሳችሁ ምረጡ

እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለይቶታል ወይ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ እንጠጣለን አለበለዚያም ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ እንጠጣለን የትኛውን ውሃ እንደምንጠጣ የመወሰኑ መብት ሙሉ በሙሉ የእኛ ነው ይህ በግለሰቡ ምርጫ ላይ የተመረኮዘ ነው ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ የሚመርጡ ሰዎች ይህንን ውሃ ይጠጣሉ ከዚህ የተነሳም ይጠፋሉ በአንጻሩ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ መጠጣት የሚፈልጉ ሰዎች ይህንን ውሃ ይጠጡና ዳግም ይወለዳሉ በዚም የዘላለምን ሕይወት ያገኛሉ ሁሉም ነገር የሚሆነው በትክክል በሰው ምርጫ ነው።

ሰው ወደ ሰማይ ወይም ወደ ሲያል የመሄዱ ነገር

የሚመረኮዘው በራሱ ምርጫ ላይ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያልን ያዘጋጀውን ያህል ሰማይንም አስቀድሞ አዘጋጅቷል ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁሉ ጻድቅ መሆን እንዲችል ሁሉን ነገር አዘጋጅቷል የሚቀር ነገር ቢኖር የሰው ምርጫ ነው ሰው ሐጢያተኛ ሆኖ መቅረት ከፈለገ በሰይጣን ቃሎች አምኖ ሐጢያተኛ ሆኖ ይቀራል ነገር ግን ጻድቅ መሆን የሚፈልግ ከሆነ በእግዚአብሄር ቃል አምኖ ጻድቅ ይሆናል በሌላ አነጋገር ሰማይና ሲያል የሚመረኮዙት በሰው ብያኔና ምርጫ ላይ ነው ሰማይና ሲያል የሚያርፉት በሰውየው ምርጫ ላይ ነው።

እግዚአብሄር ቀድሞውኑም ሁሉን ነገር አዘጋጅቷል የሚቀር ነገር ቢኖር ምን አይነት ምርጫ እናደርጋለን የሚለው ጥያቄ ነው ሰማይ መሄድ የምንፈልግ ከሆነ ማድረግ የሚኖርብን ነገር የእግዚአብሄርን ቃል መምረጥ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ መጠጣትና የኢየሱስ ክርስቶስን አገልጋዮች መከተል ነው በሌላ በኩል ወደ ሲያል መሄድ የምንፈልግ ከሆነ የሰይጣንን ቃሎች መምረጥ ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ መጠጣትና ቃሎቻቸውን ተማምነንም የሰይጣንን አገልጋዮች መከተል ነው በምናምነው ነገር መሰረት ሁሉም ነገር በእግዚአብሄር ፊት ያለ ምንም መሳሳት ይፈጸማል።

እግዚአብሄር በመጨረሻው ቀን በፍርድ ዙፋን ላይ ይቀመጥና ሐጢያተኞችን «ገና ከመጀመሪያው ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ እንደለየሁ ነግሬአችኋለሁ ነገር ግን እናንተ የሰይጣንን ቃሎች በመምረጥ በራሳችሁ ፈቃድ ውሸቶችን ለማመንና ወደ ሲያል ለመሄድ መረጣችሁ ስለዚህ እንደ ምርጫችሁ ይሆንላችኋል በእምነታችሁ መሰረት ሰይጣን ወደሚኖርበት ስፍራ መሄዳችሁ ተገቢ ነው» ይላቸዋል ያን ጊዜ ለሲያል የታጩት ሰዎች ምንም የሚናገሩት ነገር አይኖራቸውም አንደበት ይኖራቸው ይሆናል ነገር ግን አንዲትም ቃል ትንፍሽ አይሉም።

እግዚአብሄር ዳግም እንድንወለድ የሚያስችለንን ቃል እውነት ደህንነት የዘላለም ሕይወትና ሌሎች ሰማያዊ በረከቶችን ሁሉ የያዘውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በነጻ በግልጽ ሰጥቶናል እነዚህን ነገሮች ሁሉ ከሰጠን በኋላ እግዚአብሄር የእርሱን በረከቶችና እርግማኖች የምንወስድበትን ምርጫ ሰጠን እግዚአብሄር እውነተኛ ቃሉን ከሐሰተኛ ትምህርቶች ለየ እግዚአብሄር በዚህች ፕላኔት ላይ ቀኑን ከጨለማ እንደለየ ሁሉ እግዚአብሄር ውሃውን ሁሉ ከጠፈር በላይ ያለ ውሃና ከጠፈር በታች ያለ ውሃ አድርጎ ለይቶታል እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ከኖሩ በኋላ ወደ ዘላለም ሕይወት ግዛት ሊገቡ ላሉት ሰዎች ሁሉ ይህንን ልዩነት በማድረግ የራሳቸውን ዕጣ ፋንታ እንዲወስኑ አደረጋቸው።

እግዚአብሄር ቀኑን ከሌሊቱ የለየው ያለ ምክንያት አይደለም ይህንን ያደረገው ብሩህ የሆነውን የብርሃን ግዛት ፍጹም ከሆነው የጨለማ ግዛት ለይቶ ሊያሳየን ስለፈለገ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የጻድቃንን ግዛት ከሐጢያተኞች ግዛት በግልጽ ለይቶታል እርሱ ይህንን ልዩነት ያደረገው ወደ ሲያል መሄድ የሚፈልጉ ሰዎች በጨለማ እንዲያምኑና ሰማይ መሄድ የሚፈልጉ ሰዎችም በብርሃን እንዲያምኑ ነው እግዚአብሄር የለየውን ማንም ሰው ሊለውጠው አይችልም ሰው ምንም ያህል ችሎታ ቢኖረው ቀንን ወደ ሌሊት ሌሊትን ወደ ቀን መለወጥ አይችልም ልክ እንደዚሁ ማንም ሰው እግዚአብሄር ያደረገውን መለወጥ አይችልም።

ቅን ሕሊና ያለው ሰው እግዚአብሄር የለየውን ሙሉ በሙሉ እንዳለ ያምናል እኛ የዘላለምን ሕይወት የተቀበልነው ብርሃኑን በመቀበል ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከላይ የወረደውን የእግዚአብሄር ቃል በመቀበል ነው።

የምድር ውሃ ማለትም የሰይጣን ትምህርቶች መልካም

ለሆኑ ሰብአዊ ምግባሮች እንድንጥር ያነሳሱናል ከጠፈር በታች ያለው ውሃ በስጋዊ ጥረቶቻችን አማካይነት ጻድቃን እንድንሆንና እንድንድን ያስተምሩናል ይህ የሰይጣን ቃል ነው ሰው በራሱ ጥረቶች አማካይነት መልካም ሕይወትን በመኖርና በመቀደስ ጻድቅ እንደሚሆንና እንደሚድን ማንም ቢነግራችሁ ይህ የሰይጣን ቃል መሆኑን አስታውሱ የእግዚአብሄር ቃል እግዚአብሄር የፈጸመውን በልቦቻችን በማመንና ቃሎቹንም በልቦቻችን ውስጥ በመቀበል ጻድቃን እንደሆንን ይናገራል ጻድቃን መሆን ከምግባሮቻችን ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም ይህ የሚገኘው ከላይ የወረደውን የእግዚአብሄር ቃል በማመን ብቻ ነው የሐጢያቶቻችንን ስርየት ልንቀበል፣ ጻድቃን ልንሆንና የዘላለምን ሕይወት ልናገኝ የሚገባን ከጠፈር በላይ ባለው ቃል፣ በእግዚአብሄር የእውነት ቃል፣ በማናቸውም የሰው ምግባሮች መተካት በማያስፈልገው ፍጹም የሆነ ቃሉ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ የእግዚአብሄር ቃል ከሰማይ ወርዶ በዚህ ምድር ላይ ፍሬን በማፍራት እንደገና ተመልሶ ወደ ላይ ይሄዳል በእግዚአብሄር ቃል ብታምኑ ደስታ ታገኛላችሁ ነገር ግን ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ የምትጠጡ ከሆነ ትረገማላችሁ እግዚአብሄር እንድትሰቃዩና እንድትረገሙ አይፈልግም እግዚአብሄር ቃሉን የሰጠን በዚህም ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ የለየው ለዚህ ነው ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ የጠጣ ሰው ዳግመኛ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ በጭራሽ አይጠማም።

ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ እስከዛሬ ድረስ የጠጡ ሰዎች አሁን ወደ እግዚአብሄር ቃል ሊመለሱ ይገባቸዋል ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ብቻ የቀመሱ ሰዎች ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ መሻት ይገባቸዋል አሁኑኑ ወደ እግዚአብሄር የጽድቅ ቃል ወደ እውነተኛው እምነት ሊመለሱ ይገባቸዋል። ✉

እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ውሆችን ለየ

« ዘፍጥረት 1:6-8 »

«በውሆች መካከል ጠፈር ይሁን በውሃና በውሃ መንከልም ይከፈል አለ እግዚአብሄርም ጠፈርን አደረገ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላ ያሉትንም ውሆች ለየ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም ሰማይን ጠፈር ብሎ ጠራው ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ሁለተኛ ቀን::»

እግዚአብሄር ውሃን ከውሃ ለመለየት በውሆች መካከል ጠፈር እንዲሆን ሲያዝዝ በቃሉ መሰረት ሆነ እግዚአብሄርም ይህንን ጠፈር ሰማይ ብሎ ጠራው በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄር በሁለተኛው የፍጥረት ቀን ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ እንዴት ከጠፈር በላይ ካለው ውሃ እንደለየው ያብራራል በመጀመሪያ ፕላኔት ምድር የሚሸፍን አንድ የውሃ አካል ብቻ ነበር እግዚአብሄር ግን ጠፈርን አደረገና ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ በምድር ላይ ካለው ውሃ ለየ ዛሬ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ምን ማለት እንደሆነ ማብራራትና የእግዚአብሄርን በረከቶች ከእናንተ ጋር መጋራት እወዳለሁ::

የእግዚአብሄርን የሰማያትና የምድር ፍጥረት ስንመለከት እርሱ በመጀመሪያው ቀን እንዳደረገው በሁለተኛውም ቀን መለየቱን እንደቀጠለ መረዳት እንችላለን በዚህ በሁለተኛው ቀን እግዚአብሄር የሰራው ስራ መንፈሳዊ መልዕክት የሚከተለው

ነው የእግዚአብሄርን ቃል ከሰይጣን ክፉ ቃሎች መለየቱ በእጅጉ አስፈላጊ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ከሰማይ በላይ ያለውን ውሃ ከምድር በታች ካለው ውሃ በመንፈሳዊ መልኩ የሚለይ እምነት ሊኖረን እንደሚገባ እየተናገረ ነው።

እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየ እንዲህ ያደረገው እውነተኛ እምነት እንዲኖረን ከተፈለገ በመጀመሪያ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ መጠጣት እንዳለብን ሊነግረን ነው እግዚአብሄር እንዲህ አድርጎ ውሃውን ከለየበት ምክንያት በስተ ጀርባ ያለውን መንፈሳዊ ትርጉም መገንዘብ ያስፈልገናል ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠን የውሃና የመንፈስ ወንጌል ማመን የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው የእግዚአብሄርንም ስራ በእምነት መስራት የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው በሌላ አነጋገር የዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የእግዚአብሄርን ቃል ከሰይጣን ቃሎች ለይተን ማወቅና መለየት እስካልቻልን ድረስ ለዘላለም ወደ እግዚአብሄር ግዛት መግባት አንችልም።

እውነት ከውሸት መለየት አለበት

እውነትን ከውሸት መለየት ካልቻልን የእግዚአብሄርን ስራ መስራት የማንችል ብቻ ሳንሆን እግዚአብሄርንም እንቃወማለን እግዚአብሄር ስለዚህ ጉዳይ እየነገረን ያለው ለዚህ ነው ነገር ግን በዛሬው ክርስትና ውስጥ ሕግ አጥባቂዎችና ወንጌላውያን ተብለው የሚጠሩት ሰዎች እውነቱን ከውሸቱ መለየት ሳይችሉ ቀርተው ራሳቸው በሰሩዋቸው ሰው ሰራሽ ትምህርቶች ብቻ በተሳሳተ መንገድ ያምናሉ እነርሱ በእግዚአብሄር ቢያምኑም ወደ እግዚአብሄር ግዛት መግባት የማይችሉበት እጅግ

መሰረታዊው ምክንያት ከምድር በላይ ባለው ውሃ ማለትም ሰው ሰራሽ በሆኑት ትምህርቶች በማመናቸው መሆኑን መገንዘብ አለባቸው።።

በዛሬው የክርስትና ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉት ውሸታሞች እግዚአብሄር በቅዱሳት መጻህፍት ቃል ውስጥ በተጨባጭ ከተናገረው ነገር ይልቅ በእነዚህ ሰው ሰራሽ ትምህርቶች አብዝተው ይደገፋሉ ይታመናሉም አሁንም እንኳን የእግዚአብሄር ስራ የሚሰሩ በሚያስመስሉ ብዙ የክርስቲያን መሪዎች ትልቅ ስህተት እየተሰራ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል ምክንያቱም እነርሱ በእርግጥም ከእግዚአብሄር ቃል ጋር የተደባለቁትን ስጋዊ ትምህርቶቻቸውን እያካፈሉ ነውና።።

የእግዚአብሄርን መንፈሳዊ ቃል ከሰው ስጋ ከሚወጡ ትምህርቶች መለየት ይገባናል የእግዚአብሄርን ስራ በትክክል መስራት የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው ለእግዚአብሄር አገልጋዮች የስጋቸው አለመብቃት ወይም ድካሞች ችግር አይደሉም በተቃራኒው ለእግዚአብሄር አገልጋዮች እጅግ ትልቁ ችግር አስቀድመው መንፈሳዊውን ቃል ከስጋዊ ቃሎች ሳይለዩ የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት መሞከራቸው ነው አንድ ሰው የሰውን ቃሎች እግዚአብሄር ከተናገረው ቃል በጥንቃቄ ሳያጤንና ሳይለይ የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት ከሞከረ የራሱን የነፍስ ጥፋት ሳንጠቅስ መጨረሻው መጥፋት በማያስፈልጋቸው ነፍሳቶች ላይ መንፈሳዊ ጥፋትን ማምጣት ነው።።

እኛ የእግዚአብሄር ሰራተኞች የሆንን ሰዎች እግዚአብሄር የሚነግረንን ቃል ግልጽ በሆነ መረዳት መስበክ አለብን ለምን? ምክንያቱም ያ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነውና ከጠፈር በላይ ያለው ውሃና ከጠፈር በታች ያለው ውሃ በዋናነት የተለያዩ ናቸው ስለዚህ የእግዚአብሄር ሰራተኞች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት ማወቅ ሐሰተኛ ወንጌሎችን ከእውነተኛው

ወንጌል መለየትና የወንጌልን እውነት ብቻ መስበክ አለባቸው አሁን የእግዚአብሄር ቃል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ምን እየነገረን እንደሆነ በትክክል ማወቅ እንችላለን ስለዚህ የእግዚአብሄር ሰራተኞች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ምስጢር በትክክል ማወቅ፣ በእርሱ ማመንና እምነታቸውንም በዚህ ወንጌል ላይ በማኖር ለሰው ሁሉ መስበክ አለባቸው እያንዳንዱ ሐጢያተኛ የእግዚአብሄርን የቤዛነት እውነት ወደ ማወቅ የሚመጣው ያን ጊዜ ብቻ ነው በዚህ አማካይነትም እግዚአብሄር ይከብራል።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ውስጥ የተደበቀውን ምስጢር ብናውቅና ብንሰብክ በርካታ ሰዎች የዘላለምን ሕይወት መቀበል ይችላሉ ምክንያቱም ይድናሉና እኛ የሰበክነውን ከጠፈር በላይ ያለ ውሃ ማለትም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት ቢገነዘብና ቢያምን ከሐጢያትና ከግራ መጋባት እንደሚድን የተረጋገጠ ነው ይህ እውነት እንዲሆን የእግዚአብሄር አገልጋዮች የመንፈስን ቃል ከስጋ ቃሎች ለይተው መስበክ መቻል አለባቸው እርሱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል አማካይነት የዚህን አለም ሰዎች ሰዎች ለአንዱና ለመጨረሻ እንዳዳናቸው አልነገረንምን? እግዚአብሄር እኛ የእርሱ ልጆች መሆን የምንችለው ከሐጢያት በሚያድነን እውነት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን እንደሆነ ነግሮናል ስለዚህ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል በግልጽ ማወቅ አለብን በእምነትም ለሰው ሁሉ ልንሰብከው ይገባናል እውነተኛውን ወንጌል ከሐሰተኛ ወንጌሎች መለየት አለብን እምነታችንንም በእውነተኛው ወንጌል ላይ በማኖር የእግዚአብሄርን እውነት ለሚናፍቁ ሁሉ ልንሰብከው ይገባናል።

አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ቢያምኑ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሳያምኑ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ

ከሐጢያቶቻቸው መዳን እንደሚችሉ ይናገራሉ ይህ ግን እውነት አይደለም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት የማያውቁ ሰዎች «ሰው በድንግዝግዝ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ከሐጢያት መዳን ይችላል» ይላሉ ይህ ውሸት ነው እንደ እውነቱ ከሆነ ጉዳይ ይህ አይደለም ዲያብሎስ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑ ግድ ባይሰጠውም ፍጹም የሆነውን የሐጢያት ስርየት እንዳይቀበሉ በመከልከል ወደ ጥፋት ሊነዳቸው ይሞክራል።

ሰይጣን ከእነርሱ በሕግ ላይ የተመሰረተ እምነት በመጠየቅና ከሐጢያት በታች በማሰር ሰዎችን በእርግጠኝነት በጥፋት ጎዳና ላይ ለማስኬድ «የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን» ተብላ የምትጠራዋን እንኳን ለመጠቀም ብልህ ነው የዲያብሎስ የመጨረሻው ግብ ክርስቲያኖችም እንኳን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንዳያውቁ በክርስትናም ውስጥ ቢሆን የሐሰት ወንጌሎች እንዲሰራጩ ማድረግ ነው በመጨረሻም ሁሉም በሐጢያቶቻቸው ይጠፋሉ የሐጢያት ደመወዝ ሞት ስለሆነ የዲያብሎስም ስራ እንደዚሁ የሞት ስራ ነው ዲያብሎስ በርካታ ሰዎች የስጋቸውን ፍትወቶች የሚያረኩላቸውን የሐሰተኛ ወንጌሎች ቃሎች ብቻ እንዲሰሙ በማድረግ ከእግዚአብሄር እውነት በማራቅ ረገድ በሚገባ የተካነ ነው የዲያብሎስ ዋናው አላማ ያረፈው እዚያ ላይ ነው እኛ ሁላችን ጌታ የሰጠንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት በማወቅና በእርሱም በማመን ከሚዋሸው ዲያብሎስ ክፉ ወጥመዶች ማምለጥና መዳን አለብን።

ስለዚህ የሰይጣን አገልጋዮች የሰዎችን ነፍስ የሰይጣንን ቃሎች ከእግዚአብሄር ቃል ጋር ደባልቀው በመመገብ ወደ ሞት እየነዱዋቸው እንደነበር መገንዘብ አለብን የዲያብሎስን ትምህርቶች ከእግዚአብሄር ቃል ጋር መደባለቁ ምን ውጤት

አመጣ? የዚህ ወኪል ሐሰተኛ ወንጌሎች ናቸው በመሆኑም የሰይጣን አገልጋዮች አሁንም ሐሰተኛ ወንጌሎችን በመስበክ እየቀጠሉ ስለሆኑ መሞት የማያስፈልጋቸውን ነፍሳቶች ወደ ጥፋት በመንዳት ቀዳሚ ሆነዋል ሰይጣን የሚሰራውና ውሸታሞችም የሚያደርጉት ስራ ይህ ነው ሰይጣን ሰዎችን በማሳት የተካነ ነው ነገር ግን እግዚአብሄር እውነተኛውን ወንጌል ከሐሰጠና ወንጌሎች በመለየት ወንጌልን አስተውለው የሚያደምጡ ሰዎችን ያድናቸዋል በመሆኑም የእግዚአብሄር አገልጋዮች የእግዚአብሄርን ቃል ከዲያብሎስ ቃሎች ለመለየት ጥረቶቻቸውን ሁሉ መቀደስ አለባቸው እኛ ለእግዚአብሄር ስራ በምንለፋበት ጊዜ እግዚአብሄር በሁለተኛው የፍጥረት ቀን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለምን በዚህ መንገድ እንደለየው ሁላችንም መገንዘብ ያስፈልገናል።

ለእምነት ሕይወታችን ጠንካራ የሆነ የደህንነት መሰረት መገንባት አለብን

በእግዚአብሄር ስራ ላይ በእጅጉ ችግር የሚፈጥሩት የእግዚአብሄርን ቃል ከሰው ቃሎች እንዴት እንደሚለዩ ሳያውቁ በትጋት ነገር ግን በግብር ይውጣ የሚሰሩ ነሰዎች ናቸው ይህ እንደዚሁ በትክክል መስተዋል አለበት ራሳቸውን የእግዚአብሄር ሰራተኞች አድርገው የሚጠሩ ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል ከሰዎች ቃሎች ጋር በሚስቡበት ጊዜ እግዚአብሄር ለሚሰራው ነፍሳቶችን የማዳን ስራ እጅግ ትልቅ እንቅፋት እንደሚሆን መገንዘብ ያስፈልገናል የእግዚአብሄር አገልጋዮች ተብለው የሚጠሩ ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል ከሰይጣን ቃሎች ጋር ደባልቀው መስበካቸው የአገልግሎታቸው እጅግ ታላቁ ሕጸጽ ነው።

ለምሳሌ ኢየሱስ የጴጥሮስን እግር ያጠበበትን በዮሐንስ 13 ላይ የሚገኝ ምንባብ ሲጠቅሱ «ጌታ ሰውነታቸውን የታጠቡ ሰዎች የሚያስፈልጋቸው እግሮቻቸውን ብቻ መታጠብ እንደሆነ ለጴጥሮስ እንደነገረው ሁሉ እኛም እንደዚሁ በንስሐ ጸሎቶቻችን አማንይነት በየቀኑ ሐጢያቶቻችንን ማጠብ አለብን» ማለት ነው ብለው ይተረጉሙታል ብዙ ሐሰተኛ አገልጋዮች በዚህ ሞኝ የሆኑ ምዕመናኖችን ያታልሉ ይሆናል እኛም የሐጢያቶቻችንን ስርየት ባንቀበልና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል ዳግም ባንወለድ ኖሮ እኛም ደግሞ በዚህ ዘመን በገነኑት ውሸታሞች በተታለልንና ለጥፋት ስፍራ የታጨን ከመሆን በቀር ምርጫ ባልነበረን ነበር።

መንፈሳዊ ማስተዋል የሌላቸው ሰዎች በየቀኑ ከሐጢያት መንጻት እንዳለባቸው በተሳሳተ መንገድ ያስተምራሉ ነገር ግን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ የእግዚአብሄር አገልጋዮች እነዚያ ሐሰተኛ ሰባኪዎች እንደሚተረጉሙት ይህንን ምንባብ አይተረጉሙትም እነርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀ ጊዜ የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዱና ለመጨረሻ ተሸክሞ ወደ መስቀል በመሄድ ተሰቅሎ ደሙን አፈሰሰ በዚህም ለአንዱና ለመጨረሻ ከአለም ሁሉ ሐጢያቶች አዳነን ብለው ያስተምራሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የዚህን አለም ሐጢያቶች ለአንዱና ለመጨረሻ ያስወገደ አዳኝ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ይህ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት እንደሆነ ይናገራል ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር በመምጣት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ለአንዱና ለመጨረሻ ፈትሞ አስወገደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ አንዱ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ በዚህ

ሁኔታ የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ በመሸከም፣ በመሰቀል፣ እስከ ሞት ድረስ ደሙን በማፍሰስና ዳግመኛም ከሙታን በመነሳት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የዘላለም አዳኝ ሆነ።

ኢየሱስ በዮሐንስ 13 ላይ የደቀመዛሙርቱን እግሮች ባጠበ ጊዜ የደቀመዛሙርቱን ሐጢያቶች በሙሉ ወደፊት የሚሰሩዋቸውንም ሐጢያቶች እንኳን አስቀድሞ ስላስወገደበት የደህንነት እውነት ስለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል እየተናገረ ነበር ይህ ሆኖ እያለ በርካታ ሰዎች አሁንም የደህንነትን እውነት አልተገነዘቡም ምክንያቱም የእግዚአብሄርን እውነተኛ የውሃና የመንፈስ ወንጌል አላገኙምና።

ከጠፈር በላይ ያለውን የእግዚአብሄር ቃል ብቻ የሚመገቡ ሰዎች ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ለመጠጣት አሻፈረኝ ይላሉ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎዋል *«ለሮጌ የወይን ጠጅ ሲጠጣ ለዲሱን የሚሻ ማንም የለም ለሮጌው ይጣፍጣል ይላልና» (ሉቃስ 5:39)* በእውነተኛው አለም ለሮጌ ወይን ጠጅ የተሻለ ነው ለሮጌውን ወይን የቀመሰ ሰው ገና የተጠመቀውን አዲስ የወይን ጠጅ አይፈልግም።

መንፈሳዊው ግዛት ግን ፈጽሞ ተቃራኒ ነው የሰውን ታሪክ ስንመለከት ዘመኑ ምንም ያህል ረጅም ቢሆንም ከሰው አስተሳሰቦች የፈለቁት ፍልስፍናዊና ሐይማኖታዊ ትምህርቶች ፈጽሞ ከእግዚአብሄር ቃል ጋር የሚቃረኑ ናቸው የዚህ አለም ፍልስፍናዎችና አስተሳሰቦች ምንም ያህል በዕድሜ የሸመገሉ ወይም ጥልቅ ቢመስሉ ሰዎችን ከሐጢያት ከሚያድነው የደህንነት እውነት ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ጋር ሲወዳደሩ ያልተገሩና ከንቱ ትምህርቶች ናቸው የእግዚአብሄር ቃል የሆነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ሰዎችን ከሐጢያት የሚያድን እውነተኛ የሕይወት ቃል ነው ስለዚህ ጠቢባን የሆኑ

ሰዎች የአለም ሐይማኖቶች ከሚያስተምሩዋቸው ትውፊታዊ ትምህርቶች ይልቅ እግዚአብሄር በሰጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል የሚያምኑ ሰዎች ናቸው።።

ሰዎች ምንም ያህል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅንንት ቢያስቡና አዳኛቸው አድርገው ቢያምኑም ጌታ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ መንክል ግንኙነትን እስካልፈጠሩና እምነታቸውን በሁለቱም ላይ እስካላኖሩ ድረስ በዋሾዎች ተታለው ይጠፋሉ ይህ በእኛ ላይ ከተከሰተ እኛም ደግሞ ከእግዚአብሄር የዘላለም ሕይወት በረከት ርቀን እንባዝናለን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሳያውቁና ሳይድኑ የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት ለሚሞክሩ ሰዎች በእርግጥም እርግማን ነው እነርሱ የእግዚአብሄርን ስራ ከማገልገል ርቀው እያበላሹት ነው በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው በሚያምኑ በዘመኑ ክርስቲያኖች መካከል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እምነት ያለው ሰው ከሌለ እርሱ እየሰራ ያለው የእግዚአብሄርን ስራ ሳይሆን የሰይጣንን ስራ ነው እነዚህ መጋቢዎች የእግዚአብሄርን ስራ እየሰሩ አይደለም ነገር ግን የራሳቸውን ምኞቶች ለመሙላት ሲሉ ብቻ በትጋት እያገለገሉ ነው የእግዚአብሄርን ስራ እየሰሩ ያሉት የዚህ አለም ብዙ ውሸታሞች ሳይሆኑ የእግዚአብሄርን ስራ ከልባቸው እየሰሩ ያሉት አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች መሆናቸውን መገንዘብ አለባችሁ።።

ብዙዎቹ የዘመኑ ክርስቲያኖች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል ውሸታሞች ከሰበኩዋቸው የሰይጣን ቃሎች መለየት ባለመቻላቸው በሰይጣን ተታለው ወደ ጥፋት ተነድተዋል ስለዚህ የእግዚአብሄር ቃል የሆነውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለማድመጥ መሞከር አለባቸው ነገር ግን በርካታ የዚህ አለም ክርስቲያኖች በአሁኑ ጊዜ የሚሹት ምን

አይነት ስብከቶችን ነው? እነርሱ የሚሹት ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ የሚሰብኩትን የእግዚአብሄር አገልጋዮች ነው ወይስ ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ የሚሰብኩ አገልጋዮችን?

በጣም ብዙ ክርስቲያኖች አሁን የሚሹት ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ጋር ደባልቀው የሚሰብኩ ሰዎችን ነው እነርሱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ተቀብለው ቢሆን ኖሮ ከጠፈር በላይ ያለውን ቃል የሚሰብኩ የእግዚአብሄር አገልጋዮችን ይፈልጉ ነበር በአሁኑ ጊዜ ከሐጢያቶቻቸው ያልነጹ በርካታ ሰዎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ባለማወቃቸው በእግዚአብሄር ፊት የእምነትን ሕይወት ለመኖር እየሞከሩ ነው ነገር ግን ገና ከሐጢያቶቻቸው ነጻ መውጣት ያለባቸው ሰዎች በውሸታሞች ተታለዋል ስለዚህ እየኖሩ የሳሉት ስጋዊ የሆነውን የሐይማኖት ሕይወት ብቻ ነው።

እስከዛሬ ድረስም ራሳቸውን የእግዚአብሄር አገልጋዮች አድርገው የሚጠሩ ብዙ መጋቢዎች እንዲህ በሰይጣን ተታለዋል ከዚህ የተነሳ የተሳተፉት ከንቱ አይረቤ በሆነ አገልግሎት ውስጥ ነው በእነዚህ ሰዎች እምነትና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በሚያምኑ ሰዎች እምነት መካከል ግልጽ የሆነ የእምነት ልዩነት አለ።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሳይሆን በሐሰተኛ ወንጌል በሚያምኑ ሰዎች ልቦች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንደሌለባቸው እናያለን በአሁኑ ጊዜ ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው ቢያምኑም መንፈስ ቅዱስ ሊወርድባቸው አይችሉም ምክንያቱም በውስጣቸው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የለምና ለዚህ ምክንያቱ አሁንም በጨለማ ውስጥ ስለሚኖሩ ነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ትክክለኛ የሐጢያት ስርየት እውነት እንደሆኑ አያውቁም።

በሌላ አነጋገር ይህ የሆነበት ምክንያት አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት ስላለ ነው በአንጻሩ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ በነጹ ዳግም የተወለዱ ሰዎች ልቦች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አለ ስለዚህ በልቦቻቸው ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይድረሰውና እነርሱ የሰዎችን ቃሎች ከእግዚአብሄር ቃል መለየት ይችላሉ በዚህም የእግዚአብሄርን ቃል በትክክል መስበክ ይችላሉ በእውነት ቃል ስለሚያምኑም መንግስቱንም በትክክል መገንባት ይችላሉ ጻድቃን የሰይጣንን ቃሎች ከእግዚአብሄር ቃል መለየት ይችላሉ በዚህ እውነተኛ እምነትም ትክክለኛውን የደህንነት ወንጌል መስበክ ይችላሉ::

እስከ ዛሬ ድረስ የእግዚአብሄርን ክብር እየጋረዱ ያሉት ሰዎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት የማያውቁ ሰዎች ናቸው እነርሱ ከእግዚአብሄር ጋር የሚያገናኛቸው ምንም ነገር የላቸውም እነርሱ ከእግዚአብሄር በጣም ርቀዋል በዙሪያችን እንደዚህ ያሉ በጣም ብዙ መጋቢዎች መኖራቸው የሚያሳዝን ነው እነዚህ ሰዎች ከራሳቸው የውዴታ ፍላጎት በመነሳት የእግዚአብሄርን ስራ እየሰሩ እንደሆነ ቢናገሩም በተጨባጭ እየሰሩ ያሉት ግን የእግዚአብሄርን ስራ ሳይሆን የሰይጣንን ስራ ነው እነርሱ የእግዚአብሄርን ስራ ከመስራት በጣም ርቀው ስራውን እየተሳደቡ ነው ነገር ግን ይበልጥ ከባዱ ችግር እነርሱ ራሳቸው ይህንን አለማወቃቸው ነው::

የእነዚህ ውሸታሞች አንዱ ባህርይ እውነትን አለማወቃቸው ነገር ግን ባተሌ መሆናቸው ነው አሁን እነርሱ በመጀመሪያ የእግዚአብሄር ወንጌል በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለባቸው አሁን እነርሱ ከእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን እየፈለቀ ያለውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል ማድመጥ አለባቸው አሁን

የእግዚአብሄር ስራ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ለሚያምኑ ሰዎች በአደራ መሰጠት አለበት አሁን የእግዚአብሄርን ስራ እየሰራችሁ እንደሆነ እየተናገራችሁ ነገር ግን ገና የእውነት ወንጌል የሆነውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማታውቁ ከሆናችሁ መንፈሳዊ ዕውሮች ስለሆናችሁ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል አብልጣችሁ ልትሹት ይገባችኋል።

አንድ ቤት በሚሰራበት ጊዜ ጽኑ መሰረት መመስረቱ ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ እኛም የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት በመጀመሪያ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የእምነት መሰረታችንን በትክክል መመስረት አለብን ሰው ሌሎችን የሚያድን የእግዚአብሄር ሰራተኛ ሆኖ መውጣት የሚችለው እርሱ ራሱ ለአንዱና ለመጨረሻ ከሐጢያቶቹ ከዳነ በኋላ ብቻ ነው ሰዎች በመጀመሪያ ራሳቸው ሳይድኑ በጥረታቸው የእግዚአብሄር ሰራተኞች ለመሆን በመሞከር ሁሉንም አይነት ሁካታ ቢያስነሱ በመጨረሻ እምነታቸው ያለ ምንም እገዛ ተፈረናክሶ ይወድቃል እናንተ በእግዚአብሄር ፊት የእምነት ሰዎች መሆን የምትፈልጉ ከሆነ በመጀመሪያ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት አማካይነት የሐጢያቶቻችሁን ስርየት መቀበል ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ መዳንና በእውነተኛው የእምነትና በእውነተኛው የደህንነት መሰረት ላይ የእምነት ቤታችሁን መስራት አለባችሁ በመጀመሪያ በእግዚአብሄር ቃል የደህንነትን እውነተኛ የሐጢያት ስርየትን መሰረት መመስረትና ከዚያም በእምነት መንገድ መጓዝ አለብን በእግዚአብሄር ፊት ጠቢባን የሚባሉት እነዚህ ሰዎች ናቸው ሁላችንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነተኛውን የደህንነት ቤት ማግኘትና ከዚያም የእግዚአብሄርን መንግስት በመገንባት መሳተፍ አለብን።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት የመጣውን ኢየሱስ

ክርስቶስን አዳኛችን አድርገን ልናምነው ይገባናል ከጌታም ጋር መመላለስ አለብን የጌታን ወንጌል መስበክ የምንችለውና እስከ መጨረሻውም ድረስ ከእርሱ ጋር መጓዝ የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው ጥቂት ጊዜ ቢወስድም በመጀመሪያ በእውነት ቃል የደህንነትን መሰረት በጽኑ መመስረትና በዚህ መሰረት ላይም የእምነትን ቤት እንደ አለት አጠንክረን መስራት ያስፈልገናል የአንድን ሰው የደህንነት መሰረት መመስረትና ከዚያም የእምነት ሕይወቱን መጀመር በሰው አይኖች የተንዛዛ ይመስል ይሆናል በእምነት አይኖች ግን ይህ ብልህነት እንደሆነ ማየት እንችላለን የእምነት ቤታችንን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት መገንባት ይገባናል አሁን እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለምናምን ሁላችንም እውነተኛ ደህንነት ላይ መድረስ እንችላለን አሁን የእምነት የእውነተኛ ደህንነት ቤታችንን ስለሰራን ምንም የምንፈራው ነገር ሳይኖር በጌታ ሰላም መኖር እንችላለን።

እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምን አማኞች በዚህ አለም ላይ መኖር የሚገባን ሰው ሁሉ ከሐጢያት መዳንና የእግዚአብሄር ልጅ መሆን እንዲችል ነው ያንን ለማድረግ በመጀመሪያ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ወንጌል የእምነት መሰረትን አጽንተን መመስረትና ከዚያም የእግዚአብሄርን ስራ መስራት አለብን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ቢመለስም ከሐጢያት ፍርድ ማምለጥ የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው ነገር ግን የእምነት ሕይወታቸውን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሳያምኑ የሚጀምሩ ሰዎች ቤቱን በአሸዋ ላይ የሰራን ሰው ይመስላሉ እግዚአብሄር በፍርድ ቀን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሰራ ሰው ከአምላክ ፍርድ ማምለጥ እንደማይችልና አወዳደቁም ታላቅ እንደሚሆን ተናግሮዋል ስለዚህ ሁላችንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት በማመን እውነተኛውን የሐጢያት

ስርየት ቤት መስራት አለብን፡፡

ጌታ በሁለተኛው የፍጥረት ቀን ጠፈርን ሰርቶ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃና ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ለየ እግዚአብሄር በሰማያትና በምድር መካከል ያለውን ስፍራ ጠፈር ብሎ ጠራው እግዚአብሄር ፕላኔት ምድርን ሸፍኖዋት ከነበረው ውሃ አንዳንዱን ከጠፈር በላይ እንዲሆን አደረገው በምድር ላይ የቀረው ውሃ ደግሞ በአንድ ስፍራ እንዲሰበሰብ አደረገው የደህንነታችንና የእምነታችን መሰረት የምንመሰርተውና የእምነት ሕይወታችንን የምንኖረው ከዚህ ጠፈር በላይ ባለው ውሃ ነው ጌታችን የተናገረለት ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ የሚያመላክተው ምንድነው? የሚያመላክተው ንጹህ የሆነውን የእግዚአብሄር ቃል ነው ከእግዚአብሄር ቃል ሁሉ ከማንኛውም ሌላ ነገር ይበልጥ ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ነው፡፡

ጌታ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ክቡር ደም አማካይነት ከአለም ሐጢያቶች አድንኖን የእግዚአብሄር ልጆች አድርጎናል እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመንና ከሐጢያት ዳግም በመወለድ አሁን የእግዚአብሄር ሕዝብ ለሆንነው ለእኛ የእግዚአብሄርን ስራ በአደራ ሰጥቶናል ስለዚህ እግዚአብሄር መንግስቱን፣ በረከቶቹንና ፍቅሩን ሰጥቶናል እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ በመጠጣት ከሐጢያቶቻቸው ነጻ የወጡትንና ጻድቃን የሆኑትን ሰዎች ባርኮዋቸዋል ነገር ግን ይህ በረከት ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ካልጠጡ ሰዎች የራቀ ነው በተቃራኒው በእነርሱ ላይ የሚሆነው የተገላቢጦሽ ነው፡፡

አሁን እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ከዚህ አለም ሐጢያቶች እንዳዳነን ማመን አለብን ይህንንም መስበክ ይገባናል ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃውና

በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ከአለም ሐጢያቶች በሙሉ አድኖናል ከሐጢያቶቻችን ሁሉ የሚያድነንን የእምነት መሰረት በምንመሰርትበት ጊዜ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ልንመሰርተው ይገባናል ይህንን እውነት ለሌሎች በመስበክም በውሃውና በመንፈሱ በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑና የእግዚአብሄርን የእውነት ብርሃን እንዲያመሰግኑ ልንመራቸው ይገባናል።

በሌላ በኩል የደህንነት መሰረታቸውን ከጠፈር በላይ በሆነው ውሃ ያልመሰረቱ ሰዎች የጥፋት ልጆች ይሆናሉ ምንም ያህል ጠቢብና በእውቀት የተሞላ ቢሆንም ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ እስካልጠጣ ድረስ ማንም ሰው ሊድን አይችልም አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ብቻ ከሐጢያቶቻቸው እንደዳኑ ይናገራሉ ነገር ግን ጉዳዩ ይህ እንዳልሆነ ሕሊናቸው በሚገባ ያውቃል እነዚህ ሰዎች ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ሳይለዩ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚያምኑ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑት በከንቱ ነው በአንዳንድ የክርስቲያን ጉባኤዎች ውስጥ አንዳንድ ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እንደሚያምኑ ይናገራሉ ነገር ግን ትምህርቶቻቸውን በዝርዝር ስንመረምር ለሰዎች እየሰበኩ ያሉት ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ጋር ደባልቀው እንደሆነ ማየት እንችላለን እነዚህ ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች አይደሉም እነርሱ በእግዚአብሄር ፊት እንክርዳዶች እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም።

በዚህ አለም ላይ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ሰዎችን የሚያድኑ የእግዚአብሄር አገልጋዮች አሁንም አለ ነገር ግን በአለም ላይ የሰይጣንን ጉባኤዎች የሚያስተባብሩና የእግዚአብሄርን ስራ እየሰሩ እንደሆነ በተሳሳተ መንገድ

የሚያስቡ በርካታ ውሸታሞችም ደግሞ በዚህ አለም ላይ አሉ ይህንን ግልጽ ላድርግላችሁ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ያልተቀበሉ ሰዎች ሁሉ ውሸታሞች ናቸው ለደህንነታቸው በመስቀሉ ደም ብቻ የሚያምኑና ይህንኑም የሚሰብኩ ሰዎች በሙሉ ሰውን ሁሉ ራሳቸውንና ሌሎችንም የሚያታልሉ ውሸታሞች ናቸው በዚህ አለም ላይ የሚኖር አብዛኛው ሰው በመስቀሉ ደም ብቻ ያምናል ደህንነትም ይህ እንደሆነ ይናገራል ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በተጨባጭ አልዳኑም ስለ ራሳቸው ደህንነትም ምንም ማረጋገጫ የላቸውም ምክንያቱም በልቦቻቸው ውስጥ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የላቸውምና መጽሐፍ ቅዱስ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ብቸኛው አስተማማኝ የወንጌል እውነት እንደሆነ ይናገራል በዚህ አለም ላይ ጌታ ከሰጠው ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል በቀር የደህንነት ወንጌል ሊሆን የሚችል ሌላ ወንጌል የለም።

በአለም ሁሉ እየተስፋፋ ስላለው የገነነ ቲዎሎጂ አንድ ወይም ሁለት ነገር አውቃለሁ ነገር ግን ሰው ቲዎሎጂን ሲመረምር በውስጡ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማግኘት አይችልም በውስጡ ያለው ከጠፈር በታች ያለ ውሃ ብቻ ነው ሁሉም የቃለ እግዚአብሄር አስተምህሮቶች የተመሰረቱት «ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ደም ብቻ መዳን ይችላል» በሚለው እሳቤ ላይ ነው እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ድርጅትም በዚህ መሰረት ላይ ተመስርቶ የተለያዩ አሳቦችን ያንጸባርቃል ነገር ግን ከቃለ እግዚአብሄር ምሁራኖች ሁሉ ውስጥ «በመስቀሉ ደም በእርግጠኝነትና ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶቼ ስለነጻሁ አሁን ሐጢያት አልባ ሆኛለሁ» የሚል ሰው ማግኘት አልቻልሁም።

እንዲህ የሚሉ ጥቂቶች ያሉ ቢሆንም እነርሱ ሐጢያት አልባ ነን ያሉት ከትምህርት አንጻር ብቻ ነው ነገር ግን እነርሱ

አሁንም ቀጣይነት ባለው መንገድ በየጊዜው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ይቀበሉ ከነበሩት ሐይማኖተኞች የተለዩ አልነበሩም እነርሱ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ያወቁና ያመኑ እውነተኛ ክርስቲያኖች አልነበሩም።

በዚህ አለም ላይ ያሉ ብዙ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው የሚለያዩት በመረጡዋቸው የቤተክርስቲያን ድርጅቶች ብቻ ነው ሁሉም ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ጋር የሚያገናኛቸው ምንም ነገር የላቸውም በዚህች ቅጽበት እንኳን በርካታ ሰዎች በመስቀሉ ደም በማመን ብቻ ሐጢያቶቻቸው እንደሚደመሰሱላቸው ያስባሉ ነገሩ ግን እንደዚያ አይደለም ለእነዚህም ሰዎች ቢሆን ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ለአንዱና ለመጨረሻ የሚደመሰሱላቸው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ሲያምኑ ብቻ ነው አለበለዚያ ሐጢያቶቻቸው ፈጽመው አይወገዱም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለሁላችንም በግልጽ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት አማካይነት የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበል እንዳለብን ይናገራል እኔ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የማምነውና ከጠፈር በላይ ስላለው ውሃ ለእናንተ የምመሰክረው ለዚህ ነው እውነተኛ ደህንነት ወደ ነፍሳችሁ የሚመጣው ይህንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በጆሮዎቻችሁ ስትሰሙና ይህንን የሐጢያት ስርየት ወንጌል በልቦቻችሁ ስትቀበሉ ነው አሁን ከሐጢያቶቻችሁ የዳናችሁት በመስቀሉ ደም አማካይነት ብቻ እንደሆነ የምታምኑ ከሆነ የራሳችሁን ሕሊና ማታለላችሁን ልታቆሙ በእግዚአብሄር ፊት ልትቀርቡና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ልታምኑ ይገባችኋል።

አሁን በዚህች ፕላኔት ምድር ላይ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እየተሰበከ ያለበት ስፍራ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ብቻ ነች በዚህ አለም ላይ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል

በማመን ዳግም የተወለዱ ሰዎች ጉባኤ ከሆነችው የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን በስተቀር ሌላ ጉባኤ የለም በዚህ አለም ላይ ያሉ የእግዚአብሄር አገልጋዮች አሁን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በግልጽ እየሰበኩና ሰዎችም የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዲቀበሉ እያስቻሉዋቸው በመሆኑ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለማመን ይህ ዕድል ሊያመልጣችሁ አይገባም በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ደም ብቻ የምታምኑ ከሆናችሁ በስም ክርስቲያኖች ተብላችሁ የምትጠሩ አለማዊ ሐይማኖቶች መሆን ብትችሉም እውነተኛ ክርስቲያኖች መሆን አትችሉም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ካልተቀበላችሁ ለዘላለም ከሐጢያቶቻችሁ ፈጽሞ ማምለጥ አትችሉም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ካልሆነ በቀር ለሐጢያት ለአንዱና ለመጨረሻ የማምለጫ ሌላ መንገድ የለም ሁላችሁም ይህንን በእምነት እንድትረዱት እመክራችኋለሁ ምክንያቱም እግዚአብሄር ሐጢያተኞችን ፈጽሞ «እናንተ ጻድቅ ናችሁ እናንተ ሕዝቤ ናቸው» አይላቸውም ስሞቻቸውንም በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ አይጽፈውም::

በክርስትና ውስጥ የመናፍቃን ሁሉ የጋራ የሆነው አንዱ ባህርይ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ጋር ደባልቀው መስበካቸው ነው በአንጻሩ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የዚህ አለም ሐጢያቶች በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ለአንዱና ለመጨረሻ ወደ ራሱ እንደተላለፈ ያውጃል ሐጢያቶቻችን በሙሉ እርሱ ከአጥማቂው ዮሐኝስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት በአንድ ጊዜ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ተላልፈዋል ይህ ሆኖ እያለ ግን ሰዎች ይህንን እውነት ችላ ብለው በመስቀሉ ደም ብቻ በማመን ከሐጢያት ለመዳን ይሞክራሉ በትክክል መዳን የማይችሉት ለዚህ ነው እነርሱ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑት በከንቱ ነው::

ከዳንን በኋላ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የምንጠመቀው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለምናምን ነው እኛ አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅና ደሙን በማፍሰስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ እንዳነጻና የሐጢያትን ኩነኔ በሙሉ እንደተሸከመ በማመን የእምነታችን ምልክት እንዲሆን በውሃ እንጠመቃለን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት ተመሳሳይ መንገድ መጠመቃችን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ያለን የእምነታችን ምልክት ነው በዚህ ስርአት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ያለንን እምነታችንን እየገለጥን ነው የምናምነው እንዲህ መሆኑን ለመጠቆም የእምነታችን ምልክት ይሆን ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠመቃለን::

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች በእርሱ ከማያምኑ ሰዎች ጋር አይተባበሩም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *«ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከአመጽ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ሕብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?» (2ኛ ቆሮንቶስ 6:14-15)*

የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የቀበሉና የተቀደሱ ቅዱሳኖች ጉባኤ ናት (1ኛ ቆሮንቶስ 1:2) ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የማያምኑ ሰዎች የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን አባል መሆን አይችሉም::

የቅዱሳን የእምነት መሰረት መውደቅ የለበትም የልባችንን የደህንነት መሰረት የሚሰራው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ያለን እምነታችን ከፈረሰ ኢየሱስ ክርስቶስ በልቦቻችን ውስጥ ሊኖር አይችልም ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ጊዜ የሐጢያት

ስርየትን ደህንነት የሰጠን አዳኝ ሆንዋል ጌታ በውሃና በደም ወደ እኛ በመምጣት ሐጢያቶቻችንን በአንድ ጊዜ ደምስሶዋል ኢየሱስ ክርስቶስ በልቦቻችን ላይ በመሰረተው የሐጢያት ስርየት እውነት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የእምነት መሰረት ላይ በመቀመጥ በእምነት የምንኖረው ለዚህ ነው ነገር ግን የደህንነት መሰረት በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ያለን እምነታችን ከፈረሰ ሰውነታችንንና ልባችንን የምናኖርበት ስፍራ የለንም የጻድቃን ልቦች ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል በቀር የሚኖሩበት ሌላ ስፍራ የላቸውም ስለዚህ ያለዚህ ወንጌል መጨረሻቸው መጥፋት ይሆናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አዳኛችሁ ይሆን ዘንድ የእምነት ቤታችሁን የእግዚአብሄር ቃል በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ አጽንታችሁ መስራት አለባችሁ ያንን ማድረግ ካቃታችሁ የእምነት ሕይወታችሁ ወደ ውድቀት ይለወጣል የእምነት መሰረታችሁን በንሰሐ ጸሎቶቻችሁ ላይ ከመሰረታችሁት ይህ እምነት ሁሌም ይዋዥቃል በመስቀሉ ደም ላይ ብቻ በመተማመንና የንስሐ ጸሎቶቻችሁን በመጸለይ የእምነት ሕይወታችሁን ብትኖሩ እምነታችሁ ምሉዕ ይሆናልን? የለም እንዲህ አይነት እምነት ሁሌም ይናወጣል ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ ማለትም የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የሐጢያቶቻችሁ ስርየት ወንጌል መሆኑን ማመን ያለባችሁ ለዚህ ነው።

የሰዎችን ቃል ከእግዚአብሄር ቃል ሳይለዩ የሚያደምጡ ሰዎች ከእግዚአብሄር ርቀው ይቅበዘበዛሉ ስለዚህ እውነቱን ከውሸት መለየት አለብን የእግዚአብሄርን ቃል ከሰዎች ቃሎች ሳይለዩ የሚያምኑ ሰዎች ይጠፋሉ ስለዚህ ሁሌም የደህንነትን እውነት ከውሸት መለየት በግልጽ ለይተን ማወቅና በእውነት ብቻ ማመን አለብን።

አጋር ምዕመናኖቹ ሐጢያቶቻችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ ከተቀበለው ጥምቀት ውጭ ሊነጹ ይችላሉን? አይችሉም የዚህ አለም ሐጢያቶች ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጠን ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ውጭ ፈጽመው ሊነጹ አይችሉም የዚህ አለም ሐጢያቶች ያለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል እንዴት ሊነጹ ይችላሉ ብለን እናምናለን? ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ስለወሰደ በዚህ ምክንያትም ደሙን ስላፈሰሰና የእግዚአብሄርን ጽድቅ ሁሉ ስለፈጸመ ይህንን እውነት በልቦቻቸው የሚያምኑ ሰዎች ለአንዴና ለመጨረሻ ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ነጽተዋል እኛ አሁንም በየቀኑ ሐጢያት ብንሰራም በንስሐ ጸሎቶቻችን ሳይሆን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ስለምናምን ሐጢያቶቻችን በሙሉ ፈጽመው ነጽተዋል የዚህ አለም ሐጢያቶች ከልቦቻችሁ ውስጥ በሌላ በምን ሊነጹ ይችላሉ? በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ባለን እምነታችን ሲታዩ ሐጢያቶቻችን ለአንዴና ለመጨረሻ ነጽተዋል ስለዚህ ሐጢያቶቻችን መንጻታቸው ያለፈ ነገር ነው።

በልቦቻችን ውስጥ ያሉት እነዚያ በርንታ ሐጢያቶች በሙሉ በእምነት የነጹት በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ላይ እምነት ስላለን ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በአጥማቂው ዮሐንስ ነበር (ማቴዎስ 3:13-17) በቅድሚያ «ጥምቀት» የሚለው ቃል «ማጠብ» ማለት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት ሐጢያቶቻችን በሙሉ ነጽተዋል ጥምቀት የሚለው ቃል «መቅበር» ማለትም ነው ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ ስለተጠመቀ «ተፈጸመ» በማለት አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ሞተ ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምን ሁሉ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሞቷል በእምነትም በመንፈስ ከእርሱ ጋር ተነስቷል።

በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህኑ አሮን እጆቹን በመስዋዕቱ በግ ላይ ሲጭን የእስራኤል ሕዝብ የአመቱ ሐጢያቶች በሙሉ ወደ መስዋዕቱ በግ ይተላለፉ ነበር ልክ እንደዚሁ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ የሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዱና ለመጨረሻ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተላልፈዋል ኢየሱስ ክርስቶስም በእኛ ፋንታ የሐጢያት ኩነኔን ተሸከመ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ ጥምቀትን ባይቀበል ኖሮ ከአለም ሐጢያቶች ፈጽሞ ባልነጻን ነበር።

ስለዚህ በዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ 1 ላይ እግዚአብሄር አስቀድሞ ከጠፈር በላይ ስላለው ውሃ ስለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል መስክሮዋል ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ በግልጽ ልንለይ ይገባናል ልናምን የሚገባንም ከጠፈር በላይ ባለው ውሃ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ብቻ ነው።

ኢየሱስ በማቴዎስ 7:21-23 ላይ እንዲህ አለ *«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ ዓመጸኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ»* በመጨረሻው ዘመን አጥብቀው በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም ወደ ሲያል ሊጣሉ የሚገባቸው በርካታ ሰዎች ይኖራሉ።

በቅርቡ በደቡባዊ የኮርያ ባህር ዳርቻ ላይ በምትገኝ የቻንግዋን የወደብ ከተማ ቤተክርስቲያን ተከልሁ እዚያም አገለገልሁ በአንድ የንግድ ወረዳ አንባቢ በሚገኝ ትልቅ ሕንጻ ሦስተኛ ወለል ላይ አንድ ስፍራን ተከራይቼ አገልግሎቴን ጀመርሁ ለከተማይቱ አዲስ ስለነበርሁ እኔ ከተከልሁት

ቤተክርስቲያን ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስም የሚጠቀም ሌላ ቤተክርስቲያን እንዳለ አልተረዳሁም።

አንድ ቀን አንድ መጋቢና ሚስቱ ምሽት ላይ ሊጎበኙኝ መጡ «ዚህ ምን አመጣችሁ?» ብዬ ስጠይቃቸው መጋቢው «ይቅርታ አድርግልን እኔ የእከሌላ የእከሌ ቤተክርስቲያን መጋቢ ነኝ ከእኔ ቤተክርስቲያን ጋር ተመሳሳይ ስም ያለው አዲስ ቤተክርስቲያን በመከፈቱ የመጣሁት አንዳንድ የምክር ቃሎችን ልሰጥህ ነው» አለኝ መጋቢው በዚህ የቤተክርስቲያን ስም ለረጅም ጊዜ እንዳገለገለና ተመሳሳይ ስም የሚጠቀም ሌላ ቤተክርስቲያን ብዙ ውዥንብር እንደሚፈጥር፣ የሚላክ ደብዳቤም ወደ ተሳሳተ አድራሻ እንደሚላክ አብራራልኝ እናም የቤተክርስቲያኔን ስም እንድቀይር ጠየቀኝ።

እኔም መልሼ አድራሻውና ቤተክርስቲያኑ የተለያ እንደሆነ በመጠቆም መልስ ሰጠሁት «የቤተክርስቲያኑ ድርጅት ተመሳሳይ ቢሆን ኖሮ አንዳንድ ሰዎች ግራ ሊጋቡ እንደሚችሉ ማየት እችላለሁ ነገር ግን አድራሻውና የቤተክርስቲያኑ ድርጅት የተለያየ በመሆኑ ምንም ግራ የሚያጋባ ነገር የሌለበት ግልጽ አይደለምን? ምልክቱን ተመልከት የእኛ አድራሻና ቤተክርስቲያን ከአንተ የተለየ አይደለምን?» አልሁት ነገር ግን ይህ መጋቢ ግትርነቱን ማሳየትና «ያም ቢሆን የቤተክርስቲያንህን ስም መለወጥ ይኖርብሃል» በማለት ሙጭጭ ማለቱን ጀመረ።

ከእነዚህ ጥንዶች ጋር በቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነን ለተወሰነ ጊዜ ከተነጋገርን በኋላ ወደ ቢሮዬ ጋበዝኋቸው ሻይ ካቀረብሁላቸው በኋላም እንዲህ አልኋቸው «ይህንን ጉዳይ ደግሜ አስብበታለሁ የተሻለ ነው ብዬ ከወሰንሁ ስሙን እቀይራለሁ እንደዚያ ከሆነ ግን ከእናንተ ካሳ እጠይቃለሁ የቤተክርስቲያኔ ስም ከተለወጠ ምልክቱም መቀየርና አዳዲስ በራሪ ጽሁፎችም ደግሞ መታተም አለባቸው ቅያሬያችንን

ለሌሎች ለማሳወቅም ብዙ ስራና ትንሽ የማይባሉ ወጪዎችን ይጠይቃል ለዚህ ሁሉ ካሳ መክፈል ትችላላችሁን? ያ ግን ከተወሰነ ማሰላሰል በኋላ ልወስነው የሚገባኝ ነገር ነው የሆኖ ሆኖ መጋቢ ሆይ ሐጢያት አለብህ?»

መጋቢው ደንገተኛ በሆነው ጥያቄዬ ግራ ተጋብቶ «ሐጢያት የለብኝም» በማለት መለሰ::

ደግሜ «ሐጢያት የሌለብህ እንዴት ነው?» ብዬ ጠየቅሁት::

«በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ስለማምን ሐጢያት የለብኝም::»

«ታዲያ ደግመህ ሐጢያት አትሰራምን? ደግመህ ሐጢያት ብትሰራ እንኳን አሁንም ሐጢያት አልባ ነህን?»

«አሁንም ሐጢያት አለብኝ::»

«ታዲያ ሐጢያት ስትሰራ የንስሐ ጸሎቶችን አትጸልይምን?»

«እጸልያለሁ::»

«ሐጢያት የለብኝም ብለሃል ሆኖም ሐጢያት በምትሰራበት ጊዜ ሁሉ የንስሐ ጸሎቶችን ታቀርባለህ? ንስሐ ስትገባ የምትጸልየው እንዴት ነው? እግዚአብሄርን ሐጢያቶችህን እንዲያነጻልህ ትጠይቀዋለህ? ወይስ ሐጢያቶችን በሙሉ ስላነጻልህ ታመሰግነዋለህ?»

«በእርግጥ እንዲያነጻቸው እጠይቀዋለሁ::»

«ታዲያ ይህ በልብህ ውስጥ ሐጢያት ያለ ለመሆኑ ማስረጃ አይደለምን? አንተ የስሙን ችግር ለመወያየት ወደ ቤተክርስቲያኔ መጥተህ ይሆናል ነገር ግን እንዲህ ባዶ እጅህን ልትመለስ አይገባህም::»

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በስፋት አብራራሁላቸው የተወሰነ ጊዜ ቢወስድም መጋቢውና ባለቤቱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ወደ ማመን መጡ በዚህም

የቀድሞ አገልግሎቶቻቸውን ሁሉ በሙሉ ለማቆምና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለማገልገል ወሰኑ እንድመራቸውም ጠየቁኝ ነገር ግን አሳዛኙ ነገር መጋቢው ውሎ አድሮ በመስቀሉ ደም ከሚያምን ጉባኤ ጋር እንደተቀላቀለና በዚህ ምክንያት ትክክለኛ ው የእምነት መሰረት በሙሉ እንደፈራረሰ መስማነ ነው እኔ ለዚህ መጋቢ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ በእግዚአብሄር ቃል ብለይለትም ሰይጣን መጋቢው የተቀበለውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከሐሰተኛ ወንጌል ጋር ደባለቀው እምነቱንም ሙሉ በሙሉ አሰጠመበት፡፡

እግዚአብሄር ለማንኛውም ወንጌል ዕውቅናን አይሰጥም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየው ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ መረዳትና እርሱንም በእምነት መከተል አለብን ማንኛውም ወንጌል ትክክል ነው የምንል ከሆነ በመንፈሳዊ አነጋገር መጨረሻችን ፈጽሞ መስጠም እንደሚሆን መገንዘብ አለብን ችግሩ የእምነታችን መድከም እንጂ የእግዚአብሄር ቃል አይደለም የእግዚአብሄር የእውነት ቃል ፍጹምና የማይለወጥ ነው የእግዚአብሄር ቃል እውነተኛና ምሉዕ ነው ስለዚህ ሰዎች ደካማ ስለሆኑ ብቻ የእግዚአብሄር ቃል እርስ በርሱ የሚቃረን ነው ብለው መክሰስ አይችሉም ይልቁንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ብቻ ሊያምኑ ይገባቸዋል፡፡

ጌታ እንዲህ አለ *«እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ»* የእግዚአብሄር ቃል እውነት ነው ጌታ የተናገረው ነገር እውነት ነው ሕይወትም ነው መንገድም ነው የሁሉም ውሸታሞች አንድ የተለየ ባህርይ ከቶውኑም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማይሰብኩ መሆናቸው ነው ነገር ግን የተጠናወታቸው ነገር ቢኖር ብዙ ሰዎችን ወደ በረታቸው ማምጣት ብቻ ነው ያንን ለማድረግም ለሰዎች ስጋዊ አስተሳሰብ የሚስማማውን ብቻ

ይሰብካሉ ተከታዮቻቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ቢያምኑና ለቤተክርስቲያን ታማኝ ቢሆኑ በዚህ ምድረ ላይ ሊበለጽጉና ጤናማና ረጅም ዕድሜ ሊኖሩ እንደሚባረኩ ያስተምራሉ።

እኛ ግን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ናለው ውሃ ጋር ቀላቅለን ለሰዎች መስበክ የለብንም ይህንን የምናደርግ ከሆነ ከሐጢያቶቻቸው ነጽተው ዳግም ሊወለዱ አይችሉም ውሸታሞች አሁንም ድረስ ሐጢያቶቻቸው በልቦቻቸው ውስጥ እያሉ ራሳቸውን የእግዚአብሄር ሕዝብ አድርገው የሚጠሩት ከትምህርት አንጻር ብቻ ነው።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አማካይነት የእግዚአብሄር የጠለቀ ነገር እንኴን ማወቅ ይችላሉ ስለዚህ የሰዎች ልቦች በእውነት ቃል በግልጽ ተገልጠው ማየት ይችላሉ የሰዎችን ልቦች በእውነተኛው የውሃና የመንፈስ ወንጌል ቃል ስንመረምር በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት እንዳለ ወይም እንደሌለ ማወቅ እንችላለን እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለሚያምኑ ሰዎች እምነትን ጥበብን መንፈሳዊ መለየትን ስለሰጠ አይኖቹን በማየትና ከእርሱ ጋር ጥቂት በመነጋገር ብቻ ሰው ሐጢያተኛ እንደሆነ ወይም ጻድቅ እንደሆነ ማወቅ እንችላለን አንድ ሰው እንደዳነ ወይም እንዳልዳነ ለመለየት የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር እንዴት እንደዳነ እራሱን መጠየቅና የሚሰጠውን ማብራሪያ ማድመጥ ብቻ ነው።

ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሰዎችን መንፈሳዊ ሁኔታ እናውቃለን በአንጻሩ ግን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ያልለዩ ሰዎች እውነተኛውን ከሐሰተኛው መለየት አይችሉም።

ይህንን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ መረዳቱ፣ በእርሱ ማመኑና እርሱንም ለሌሎች መስበኩ በጣም አስፈላጊ የሆነው

ለዚህ ነው ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ ከጠፈር በላይ ያለ ውሃ ሆኑ በግልጽ መለየት አለበት ከጠፈር በታች ያለውም ውሃ ከጠፈር በታች ያለ ውሃ ሆኑ በግልጽ መለየት አለበት በዚህ መሰረትም ሊሰበኩ ይገባቸዋል የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከሌሎች ወንጌሎች ለይተን ወንጌልን በማስተዋል መስበክ አለብን የዲያብሎስን ቃሎች ከእግዚአብሄር ቃል በመለየት የእግዚአብሄርን ቃል ብቻ ልንሰብክ ይገባናል እውነት የሆነውን ፈጽሞ ከውሸቶች ጋር መቀላቀል የለብንም እግዚአብሄር እንዲህ ይላል *«በእርሻህም ሁለት ኣይነት ዘር ኣትዝራ» (ዘሌዋውያን 19:19)* እግዚአብሄር በእርሻ ለሳይ ሁለት አይነት ዘር እንዳንዘራ ስላዘዘን የምናምንበትን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ብቻ በግልጽ መስበክ አለብን እኛ መስበክ ያለብን የተጻፈውን የእግዚአብሄር ቃል ብቻ ነው።

አንዳንድ ሰዎች «ታዲያ ይህ ማለት የሐጢያቶቻችንን መንጻት የምናገኘው በጥምቀት አማካይነት ብቻ ነውን?» ብለው ይጠይቃሉ የሰው ዘር ሐጢያቶች የሚነጹት በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና በመስቀሉ ደም ብቻ ነው ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ከልቦቻቸው ውስጥ ተወግደው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የተላለፉት ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት ነው እነዚህ ሐጢያቶች የተኮነኑትም በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ አማካይነት ነው እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዲህ ብሎዋልን? እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን ውስጥም እንደዚሁ ይህንኑ እውነት ተናግሮዋል የብሉይ ኪዳን ቃል በሙሉ የአዲስ ኪዳን ቃል ጥላ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ዘመን የተቀበለው ጥምቀትም የብሉይ ኪዳን ግርዘት ጥላ ነበር በብሉይ ኪዳን ዘመን ያልተገረዙ ሰዎች የፋሲካውን ጠቦት ይበሉ ዘንድ ብቁ አልነበሩም (ዘጸአት 12:48) የፋሲካውን ጠቦት መብላት የፈለገ ማንኛውም ሰው እስራኤላዊ

ቢሆንም እንኳን መገረዝ ነበረበት በስጋ ያልተገረዙ ሰዎች በፋሲካው ለመሳተፍ ብቁ አልነበሩም።

ሕጉ አዲስ ኪዳንንም ይመለከታል ዳግም ካልተወለድን በቀር ወደ ሰማይ በአል አንገባም ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ዳግም የምንወለደው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስናምን ብቻ ነው እኛ ከሐጢያቶቻችን ዳግም መወለድና ወደ እግዚአብሄር መንግስት መግባት የምንችለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን እንደሆነ ተናግሮዋል።

ሁሉም ሰው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን ከሐጢያቶቹ መንጻትና ዳግም መወለድ የሚገባው ለዚህ ነው ጌታ በውሃውና በደሙ አማካይነት ከአለም ሐጢያቶች ባዳነን ወንጌል ማመን አለብን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል በግልጽ ከጠፈር በላይ ያለ ውሃ ነው ይህ ሆኖ እያለ የዘመኑ ክርስቲያኖች እንኳን በእርሱ ሊያምኑ ቀርቶ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማወቅ ፍላጎትም የላቸውም ክርስትና የተበላሸው ጌታ የሰጠውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለማመን እስከ ዛሬ ድረስ እምቢተኛ በመሆኑ ነው ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ንስሐ መግባትና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለበት።

በመላው አለም ያለው ክርስትና እንዲህ ቅጥ ያጣው ለምንድነው? ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ማመንና መስበክ ስለተሳነው ነው በሌላ አነጋገር ሁሉም ነፍሳቶች እንዲህ የተጨመላለቁት ሰዎች ከጠፈር በታች ባለው ውሃ ስለሚያምኑና ይህንንም ከአንዳንድ የእግዚአብሄር ቃል ጋር ደባልቀው ስለሰበኩት ነው በርካታ ሰዎች አሁንም ሐጢያት ያለባቸው ቢሆኑም እንኳን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ብለው እየተናገሩ በግትርነት ሐጢያት አልባ ነን ይላሉ ከዚህ የተነሳ ይህ አለም እምነታቸው በሕግ አጥባቂነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ

ሳለ ታማኝ አማኞች እንደሆኑ በሚያስመስሉ ብዙ ክርስቲያኖች ተሞልቷል።

እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ሐጢያተኞችን በሕይወት ብርሃን አማካይነት አዳናቸው በሁለተኛው ቀን እግዚአብሄር ከሐጢያት የዳኑትን ለየ ማለትም ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየ እግዚአብሄር በመጀመሪያ ሰማያትንና ምድርን ሲፈጥር መላው አለም በውሃ ተሸፍኖ ነበር ነገር ግን እግዚአብሄር ከዚህ ውሃ አንዳንዱን ወደ ሰማይ ወሰደው ስለዚህ በውሆች መካከል ጠፈር የሚባል ባዶ ስፍራ ተፈጠረ።

እግዚአብሄር ያደረገውን አሳንሳችሁ አትገምቱት የእርሱ ቃል እውነት ነው ሁሉም ሰው ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ጠጥቶ ቢሆን ኖሮ ምንኛ ድንቅ በሆነ? ሰው ሁሉ ይህንን ውሃ ጠጥቶ ቢሆን ኖሮ ሁሉም ጻድቅ ይሆን ነበር ከዚህም በላይ የዘመኑ ክርስትናም በእርግጥ ክርስቶስ መንግስት ይሆን ነበር እኛ ጻድቃኖች በዚህ አለም ላይ መኖራችንን ብንቀጥል አለም ትለወጣለች እኛ ጻድቃኖች ክፋትን እናደርጋለን? የለም ክፋትን አናደርግም ጻድቅ የሆነ ሰው መቼም ቢሆን ክፋትን አያደርግም።

በአንጻሩ ዳግም ያልተወለዱ ክርስቲያኖች በዚህ አለም ላይ ሲኖሩ ምን ያህል ክፋት ያደርጋሉ? እነርሱ እጅግ ብዙ ክፉ ነገር ስለሚሰሩ ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሰዎች እንኳን በእነርሱ ተሰላችተው ደክሞዋቸዋል ይህ ለምን ሆነ? ምክንያቱም እነርሱ በእምነት ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ መጠጣት ተስኖዋቸዋልና ይህ የሆነበት ምክንያት በውሸታሞች ስለተታለሉና ድብልቅ ውሃ ስለጠጡ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ከጠፈር በላይ ካለው ውሃ ጋር ቀላቅለው የሚሰብኩ ሰዎች የእግዚአብሄር

ባሮች እንዳልሆኑ በግልጽ ይናገራል ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ጋር ቀላቅሎ የሚጠጣ ማንኛውም ሰው መጨረሻው መሞት ነው እግዚአብሄር እኛን ከአለም ሐጢያቶች ያዳነው ከጠፈር በላይ ባለው ውሃ አማካይነት ብቻ ነው ከሰማይ ዝናብን በማውረድም ይንከባከበናል ሰው በእርግጥ የዘላለምን ሕይወት ማግኘት የሚፈልግ ከሆነ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ መጠጣት አለበት በፋንታው በምድር ላይ ያለውን ውሃ የሚጠጣ ከሆነ መጨረሻው በመንፈሳዊ ሁኔታው መጥፋት ይሆናል።

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ከሐጢያቶቻችን አድኖናል አሁን እኛ እየኖርን ያለነው በዚህ የደህንነት ጸጋ ነው እግዚአብሄር የዘላለምን ሕይወት ሰጥቶናል ሰማያዊ የሆኑ መንፈሳዊ በረከቶችንም ለግሶናል የእርሱ ሰራተኞች አድርጎናል የእርሱን ስራ በሚገባ መስራት እንድንችልም «የማስታረቅንም አገልግሎት» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡18) በአደራ ሰጥቶናል።

እኔ ደጋግሜ እግዚአብሄርን አመሰግናለሁ ሁላችንም ያለ መታከት ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ብቻ መስበክ አለብን ከጠፈር በታች ያለው ውሃ የዲያብሎስ ቃሎች መሆናቸውን አውቀን በግልጽ ልንኮንናቸው ይገባናል ሁላችንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ብቻ በመታመን እግዚአብሄርን እያመሰገንን ሕይወታችንን ልንኖር ይገባናል ጌታችን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ወደ እኛ መጥቶ ያዳነን አምላክ በመሆኑ በእርሱ ያመነ ሰው ሁሉ የደህንነትን ስጦታ ተቀብሎዋል ስለዚህ ሁሌም ይህንን ቃል በልቦቻችን ውስጥ ልንንከባከበው ይገባናል አሁን እምነታችንን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ በማኖር በትክክል እንኑር።

በውሃ በተሸፈነችው በዚህች ፕላኔት ላይ እግዚአብሄር

ውሃውን በሁለት የተለያዩ መለያዎች ከፈለው ስለዚህ ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ የተለየ ነው ይህም ሰዎች በሰበኩዋቸው ቃሎች መካከል የእግዚአብሄር ቃል እንዳለ እንደዚሁም የሰይታን ቃሎች እንዳሉ ያመላክታል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር መጀመሪያ እውነተኛውን የውሃውንና የመንፈሱን ቃል ተናገረን ሰይጣን ግን እየዋሸ ነው ሰዎች ከሰበኩዋቸው ቃሎች ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል የሆነውንና ያልሆነውን እንዴት እንደምንለይ ማወቃችን በጣም አስፈላጊ ነው።

«በውሃና በውሃ መካከል ይከፈል» በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ውሃ የሚያመላክተው የእግዚአብሄርን ቃል ነው የእግዚአብሄር መንፈሳዊ ቃል የሚመጣው ከላይ ነው የእግዚአብሄር ቃል የሚመጣውም ከተጻፈው የቅዱሳት መጽሐፍ ቃል ውስጥ ነው በአንጻሩ በምድር ላይ ያለው ውሃ የሚፈልቀው ከሰዎች ስጋዊ ልቦች ውስጥ ነው የምድር ቃሎች መሰረታዊ መነሻ ከሰው ልብ ውስጥ የሚፈልቀው የስጋ ፍትወት ነው መጽሐፍ ቅዱስ ከሰዎች ልቦች የሚወጡት ቃሎች የሰይጣን ቃሎች እንደሆኑ ነገር ግን ከእግዚአብሄር አንደበት የሚወጣው የሰማይ ውሃ እንደሆነ ይናገራል ስለዚህ በዚህ ምድር ላይ የሐሰተኛ ነቢያቶች ቃሎችና የእውነተኛ ነቢያቶች ቃሎች አብረው ይኖራሉ እግዚአብሄር ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ የመለየቱ አንደምታ ይህ ነው።

በብሉይ ኪዳንም ዘመን እንደዚሁ ሐሰተኛ ነቢያቶች ከራሳቸው ልብ አፍልቀው ውሸቶችን ተንብየው ነበር (ሕዝቅኤል 13፡2) የሰይጣን ቃሎች በክፋትና በውሸቶች አማካይነት በሰዎች ልቦች ውስጥ ሊሰሩ ይችላሉ የሰይጣን መሳሪያዎች ሆነው የሚያገለግሉትን ሰዎች ስንመለከት በልባቸው ውስጥ ባሉት የፍትወት ፍላጎቶች ላይ ተመስርተው እንዴት እንደሚዋሹ እንመለከታለን እነርሱ መንፈስ ቅዱስ ሆነ

ዕቃ ነገር አድርገው ይመለከቱታል ስለዚህ ተከታዮቻቸው የመንፈስ ቅዱስን እሳት እንዲቀበሉ በመጠየቅ ወይም ከልባቸው ውስጥ እንዲህ አይነት ግራ የሚያጋባ ከንቱ ነገር በማፍለቅ ውሸቶችን ይናገራሉ እነርሱ የሚናገሩትን በጥንቃቄ ስናደምጥ ሁሉም የፈለቀው ከልቦቻቸው ውስጥ ነው በጣም የተሳሳተና የረከሰ ከመሆኑ የተነሳም ታግሰን ማድመጥ እንኳን አንችልም ወደ ጸሎት ስብሰባ ስንሄድ ወይም የመነቃቃት ጉባኤ ላይ ስንገኝ ሰባኪው መጽሐፍ ቅዱሱን ቢከፍትም አብዛኛውን ጊዜ እየተናገረ ያለው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ይሁን ወይም በልቡ ውስጥ ያለውን ይሁን መናገር አንችልም እነዚህ ሰባኪዎች የሚያቀርቡዋቸው ስብከቶች ሙሉ በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይጣጣሙ ናቸው።።

ግዙፍ ከሆነ የመዘምራን ቡድን ጀምሮ እስከ ሮክ የሙዚቃ ባንድና ታላላቅ ተናጋሪዎች ጀምሮ ሁሉን አይነት መሳሪያዎች በማንቀሳቀስ በመጀመሪያ ዳግም ያልተወለዱትን ነፍሳቶች በራሳቸው ስሜት ይሞሉዋቸዋል ከዚያ በኋላ ጉባኤውን መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይነግሩታል የድምጽ ማጉያው የነፋስን ድምጽ አስመስሎ እንዲያወጣ በመጠቀም «እሳትን ተቀበሉ!» እያሉ ይጮሃሉ ይህ ግን ስሜታቸውን በማነሳሳት ሕዝቡን በጋራ ቀልብ ከመንሳት በቀር የሚፈይደው ነገር የለም በአንጻሩ እግዚአብሄር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰው መንፈስ ቅዱስን በስጦታ መልክ የሚቀበለው የሐጢያቶቹን ስርየት ሲቀበል እንደሆነ ይናገራል (የሐዋርያት ስራ 2:38) በዚህ መሰረት በመስበክ ፋንታ በዕውር ድንብር መንፈስ ቅዱስ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይገኛል ይላሉ በጣም የተሳሳቱት ለዚህ ነው ብዙ ሰዎች የሐጢያት ስርየትን ሳይቀበሉ በመለመን ብቻ መንፈስ ቅዱስን መቀበል እንደሚችሉ ያምናሉ ይህ ግን ፈጽሞ የተሳሳተ እምነት ነው የመንፈስ ቅዱስን መቀበል ያለባችሁ በውሃውና

በመንፈሱ ወንጌል በማመንና የሐጢያቶቻችሁን ስርየት በመቀበል ነው።።

ሐሰተኛ ነቢያቶች የልቦቻቸውን ፍትወቶች ለመሙላት ሲሉ ብቻ ሁሌም ይዋሻሉ ትምህርቶቻቸውም ከምድር የበቀሉ እንዲህ ያሉ ቃሎች ናቸው በሌላ አነጋገር እነዚህ ሰዎች እርሱ ፈጽሞ ያልተናገረውን ለእግዚአብሄር በመስጠት የራሳቸውን የእግዚአብሄር ቃል ያዘጋጃሉ እነርሱ የሚናገሩት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ስለሆነ ሁሉም ውሸታሞች ናቸው የሰይጣንን ቃሎች መናገር ማለት እግዚአብሄር ፈጽሞ ያልተናገረውን መናገርና ይህንንም የእርሱ ቃል አስመስሎ መቀባባት ነው የሰይጣን ቃሎች እንዲህ ናቸው እነርሱን የሚያስፋፉ ሰዎችም የሰይጣን አገልጋዮች ናቸው።።

እኛ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የተጻፈውን የእግዚአብሄር ቃል ማንበብና ይህንንም ቃል በእምነት መስበክ አለብን በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የተጻፈውን እውነት ማመንና ይህንኑም በእምነት ማሰራጨት አለብን በአንጻሩ ዳግም ያልተወለደ ሰው ከራሱ ልብ አውጥቶ በሚናገርበት ጊዜ እየተናገረ ያለው የሰይጣንን ቃሎች ነው የሰይጣን ቃሎች የሚሰሩት በማን በኩል ነው? እነርሱ የሚሰሩት የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ባላገኙ ሰዎች አማካይነት ነው ሰይጣን ከሐጢያት ዳግም የተወለዱ ቢሆኑም እንኳን ደካማ በሆኑ ሰዎች አማካይነትም ደግሞ ይሰራል በሌላ አነጋገር የሰይጣን ቃሎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ባልበሰሉት ሰዎች አማካይነት ሊሰሩ ይችላሉ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ሰይጣን ዳግም ባልተወለዱ ሰዎች አማካይነትም ይሰራል እነዚህ ሰዎችም ሰይጣን የሚጠቀምባቸው ምርጥ መሳሪያዎች መሆናቸው እርግጥ ነው።።

ስለዚህ ሰይጣን የማታለልን ስጦታ በመስጠት ዳግም

ያልተወለዱ ሰዎችን ሐይማኖተኞች ያደርጋቸዋል በዚህ አማካይነትም ብዙ ሰዎችን ግራ መጋባት ውስጥ ይወረውራቸዋል ሰይጣን በልብ ውስጥ የሆነ ስቃይን በሚፈጥርበት ጊዜ ሊሰራ የሚችለው ዳግም ባልተወለዱ ሰዎች አማካይነት ነው ሰይጣን ዳግም ባልተወለዱ ሰዎች አማንይነት ሰዎች ሰፊውን መንገድ ይከተሉ እንደሆነ በማረጋገጥ ሊሰራ ይችላል ዳግም ባልተወለዱ መጋቢዎች አመራር ስር ያሉ አማኞችን ስንመለከት ሁሉም በሰይጣን ቃሎች የተሞሉ መሆናቸውን እንመለከታለን በእነርሱ የሚመሩት ቤተክርስቲያኖች የሚያደርጉት ነገር ቢኖር የሰይጣንን ስራ መስራት ነው ስለዚህ በመጀመሪያ ዳግም መወለድ ያለባቸው መጋቢዎች ናቸው።

እውነቱ ከሐሰቱ በግልጽ መለየት አለበት

እግዚአብሄር በሁለተኛውም የፍጥረት ቀን እንደዚሁ መለየቱን ቀጠለ የለየው እንዴት ነበር? እርሱ ቃሉን ከሰይጣን ቃሎች ለየ የራሱን ፍሬዎችም ከሰይጣን ፍሬዎች ለየ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምንም አሁንም ገና በትክክል ጻድቅ ካልሆነ ይህ ሰው አሁንም የምድርን ውሃ እየጠጣ ያለና በዲያብሎስ ቁጥጥር ስር ያለ ለመሆኑ በግልጽ መረዳት ይገባናል አንድ ሰው ለ50 አመታት ያህል በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በኋላ እንኳን ገናም ሐጢያተኛ ሆኖ ካለ የዚህ ምክንያቱ የዲያብሎስን ቃሎች ማመኑ ነው በአንጻሩ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና የሐጢያቶቻቸውንም ስርየት በልቦቻቸው ውስጥ በመቀበል ጻድቃን የሆኑ እንደዚሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑ በኋላ በቃሉ መሰረት መኖራቸውን የሚቀጥሉ ሰዎች ከጠፉር

በላይ ያለውን ውሃ እየጠጡ ያሉ ሰዎች ናቸው።

እነዚህ ሁለት አይነት ሰዎች እርስ በርሳቸው በግልጽ ይለያሉ አንድ ሰው ሐጢያተኛ ወይም ጻድቅ እንደሆነ ለሲያል ወይም ለሰማይ የታጨ እንደሆነና የእግዚአብሄር ልጅ ወይም የዲያብሎስ ልጅ እንደሆነ በግልጽ መለየት አለበት ጻድቃን መንግስተ ሰማይ ይገባሉ ሐጢያተኞች ግን ወደ ሲያል ይጣላሉ።

እግዚአብሄር ሰዎችን ሁሉ በሁለት የተለያዩ ቡድኖች ከፍሎዋቸዋል እርሱ ይህንን በግልጽ አድርጓል እግዚአብሄር ይህንን በግልጽ ቢያደርግም ብዙ ሰዎች አሁንም ድረስ ሕሊናቸውን ያታልላሉ ሰው ሕሊናውን ሲመለከት ከእነዚህ ከሁለቱ እንዱ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ሰው የእግዚአብሄርን ቃል በመስማት ዳግም ተወልዶ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ፣ ቅዱስ እንደሆነ ወይም ሐይማኖተኛ እንደሆነ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እንዳሉት ወይም እንደሌሉትና የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን አባል ወይም የሰይጣን ጉባኤ አባል እንደሆነ በግልጽ መለየት አለበት።

እኛ ከሐጢያቶቻችን መዳን ከፈለገን በመጀመሪያ ራሳችንን በግልጽ መናዘዝ አለብን

ሁላችንም እግዚአብሄር እውነትን ከሐሰት በግልጽ እንደለየ መረዳት አለብን እግዚአብሄር እውነቱን እንዲህ ቢለይም ሰዎች እየጠፉ ያሉት ሕሊናቸውን በማታለላቸው ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል እግዚአብሄር ሰዎችን ወደ ሲያል የሚልካቸው በመሆኑ ሊወቀስ እንደማይችል አረጋግጠዋል ምክንያቱም ሰዎች በእርግጥ እግዚአብሄርን የሚሹና በቃሉ ፊት

እውነተኞች ከሆኑ እግዚአብሄር ያለምንም ችግር እነዚህን ሰዎች ሁሉ በእውነት ቃሉ አማካይነት ይገናኛቸዋል ሰው በእግዚአብሄር ቃል አማንይነት ልቡን በቅንንት ቢመለከት ከየትኛው ቡድን እንደሆነ በግልጽ ማወቅ ይችላል ስለዚህ በራሳቸው ተታልለው ምናቦችን የሚከተሉና በዚህ ምክንያትም የሚጠፉ ሰዎች ማማኸኛ የላቸውም።

አሁን በዚህ አለም ላይ ብርሃን አለ አሁን በዚህ አለም ላይ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት አለ እኛ የውሃና የመንፈስ ወንጌል አለን ስለዚህ ቃል በትክክል ከተማራችሁት ካያችሁትና በሙሉ እርግጠኝነትም የምታነምኑት ከሆነ እናንተም ደግሞ ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ ነጻ መውጣት ትችላላችሁ እውነቱ ያ ነው ከጠፈር በታች ያለውም ውሃ ቢሆን ከጠፈር በላይ ወዳለው ውሃ ሊለወጥ ይችላል በባህር ውስጥ ያለው ትነት ወደ ላይ እንደሚወጣና ተመልሶ ዝናብ በመሆን እንደሚወርድ ሁሉ ከታች ያለው ውሃም እንደዚሁ ከላይ ወዳለው ውሃ ሊቀየር ይችላል።

ይህ ሆኖ እያለ ሰው እንዲህ ሊለወጥ ቢችልም ሰዎች አሁንም ራሳቸውን ያታልላሉ በጨለማ ውስጥ መኖራቸውን የሚቀጥሉትና ለሐጢያቶቻቸውም የሚኮነኑት ለዚህ ነው እያንዳንዱ ሐጢያተኛ ሐጢያተኛ ሆኖ ወደ እግዚአብሄር መመለስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመንና ብርሃንን ማግኘት አለበት ሊደረግ የሚገባው ተገቢ ኑሃዜ ሌላ ሳይሆን ይህ ነው።

1ኛ ዮሐንስ 1:9 እንዲህ ይላል *«ለሐጢአታችን ብንናዘዝ ሐጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው»* እናንተም ደግሞ በዚህ ቃል ማመን አለባችሁ «ጌታ ሆይ በልቤ ውስጥ ሐጢያት አለብኝ እኔ ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ስጠጣ የነበርሁ ሐጢያተኛ ነኝ ጌታ ሆይ እባክህ አድነኝ» ብላችሁ ተናዘዙ ወደ እግዚአብሄር ባሮችና ወደ እርሱ

ቤተክርስቲያን ኑ ቃሉን ስሙ የሐጢያቶቻችሁንም ስርየት ተቀበሉ::

እግዚአብሄር በሁለተኛውም ቀን መለየቱን ቀጠለ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ በመለየት ቃሉን ከሰይጣን ቃሎች ለየ እግዚአብሄር እውነተኛውን እምነት ከሐሰተኛው እምነት የመለየቱን እውነታ በፍጹም መርሳት የለብንም እግዚአብሄር እውነቱን በሰዎች ልቦች ውስጥ ካለው ውሸት በግልጽ ለይቶታል ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ የጠጡ ሐጢያተኞች ዳግም የተወለዱ ቅዱሳኖች ወዳሉበት ጉባኤ መምጣትና መለወጥ አለባቸው እግዚአብሄር የሕይወትን መንገድ በግልጽ ቢለይና ቢከፍትም ሰዎች አሁንም የራሳቸውን ሕሊና ማታለላቸውን የሚቀጥሉና ወደ ሲያል የሚጣሉ ከሆነ ይህ ፈጽሞ የእነርሱ ስህተት መሆኑን መረዳት አለብን በረከቶቻችን ወይም እርግማኖቻችን፣ ደስታችን ወይም ሐዘናችን በሙሉ የሚወሰኑት ምን አይነት ቃል እንደምናምንና እንደምንቀበል እዚያ ላይ ተመርኩዞ ነው::

ሰው ከሐጢያት የመዳኑ ጉዳይ ያረፈው በምርጫው ላይ ነው

ሰው እግዚአብሄር በለየው ከጠፈር በላይ ባለው ውሃ ወይም ከጠፈር በታች ባለው ውሃ ሊያምን ይችላል ይህ የግለሰቡ ጉዳይ ነው ከጠፈር በታች ባለው ውሃ የተሳቡና እርሱን የሚከተሉ ሰዎች ይህንን ውሃ ይጠጣሉ በዚህ ምክንያትም በስብሰው ይጠፋሉ የሰው ዕጣ ፈንታ የሚገለጠው በራሱ ምርጫ መሰረት ነው::

ሰማይ እንሄዳለን ወይስ ወደ ሲያል እንጣላለን? ኢየሱስ

ክርስቶስ አስቀድሞ ሰማይንና ሲያልን አዘጋጅቷል እያንዳንዱ ሰው ጻድቅ ይሆን ዘንድም የትረፈረፈ ደህንነትን ፈጽሞዋል ሰው ሐጢያተኛ ሆኖ መቅረት ከመረጠ ሐጢያቶቹን መደምሰስ የማይችሉትን ቃሎች ማለትም ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ያምናል ነገር ግን ጻድቅ መሆን ከፈለገ በእግዚአብሄር ቃል ያምናል ከጠፈር በላይ ያለውንም ውሃ ይጠጣል ሰማይና ሲያል የሚመረኮዙት በሰው በራሱ ብያኔና ምርጫ ላይ ነው እግዚአብሄር አስቀድሞ ሁሉን አድርጓል በምርጫችን መሰረት ወይ ሰማይ እንገባለን አለበለዚያም ሲያል እንጣላለን ሁሉም ነገር ሰው ባመነው መሰረት ያለ ምንም መሳሳት በእግዚአብሄር ፊት በትክክል ይፈጸማል።

አጋር ምዕመናኖቼ አሁን እግዚአብሄር እንዲህ እውነትን ከሐሰት በግልጽ የለየበትን ምክንያት መገንዘብ ትችላላችሁን? እግዚአብሄር የመጨረሻውን ፍርዱን በሚሰጥበት ዙፋኑ ላይ ሆኖ አምርሮ የሚከተለውን ይናገራል «እኔ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ በግልጽ ለይቻለሁ እውነቱ ምን እንደሆነና ውሸቱም ምን እንደሆነ በግልጽ ነግሬአችኋለሁ እንዲህ በጣም ግልጽ ባደርግላችሁም እናንተ ግን አሁንም ከእኔ ቃል ይልቅ የዲያብሎስን ውሸትና ቃሎች መርጣችኋል ስለዚህ ለእናንተ የሚስማማችሁ ዲያብሎስ ወደሚኖርበት ስፍራ መሄድ ነው ለምን? ምክንያቱም እናንተ የእኔ ሕዝብ አይደላችሁምና።»

ስለዚህ ወደ ሲያል የሚጣሉ ሰዎች ለእግዚአብሄር የሚናገሩት ምንም ነገር የላቸውም አንደበቶቻቸው ቃላቶችን ይፈልጋሉ ነገር ግን የሚናገሩት ቃል አያገኙም እግዚአብሄር ወንጌልን እውነትን ደህንነትን የዘላለም ሕይወትንና በረከቶችን ሰጥቶናል እግዚአብሄር እግዚአብሄርን የሚሹትንና ቃሉንም በእምነት የተቀበሉትን ሰዎች እነዚህን በረከቶች ሁሉ እንዲቀበሉ

አስችሎዋቸዋል ነገር ግን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ የማይጠጡ ሰዎች በመጨረሻ እርግማኖች ሁሉ ይገጥማቸዋል ምክንያቱም የሐጢያቶቻቸውን ስርየት መቀበል አልቻሉምና እግዚአብሄር በረከቶቹን ከእርግማኖች ለይቶዋቸዋል እውነተኛ ቃሉንም ከሐሰተኛ ቃሎች ለይቶዋል ብርሃንን እንደፈጠረና ቀንን ከሌሊት እንደለየ ሁሉ እግዚአብሄር እነዚህንም ደግሞ ለይቶዋቸዋል።

የእያንዳንዱ ሰው ዕጣ ፋንታ የሚወሰነው በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ከእግዚአብሄር መደቦች የትኛውን ይመርጣል በሚለው መሰረት ነው እርሱ ቀንን ከሌሊት የለየው ያለ ምንም ምክንያት አይደለም ቀን ሲሆን ብሩህ ነው ሌሊት ሲሆን ግን ድቅድቅ ጨለማ ነው ጨለማና ብሩህ ግዛቶች አሉ በሌላ አነጋገር የጻድቃን ግዛትና የሐጢያተኞች ግዛት አለ።

እግዚአብሄር ልዩነቱን በግልጽ ስላስቀመጠ ሰው ሰማይ መሄድ የሚፈልግ ከሆነ ማድረግ የሚኖርበት ነገር ቢኖር በግልጽ በብርሃን ማመን ነው በሌላ በኩል ሲያልፍ መሄድ የሚፈልግ ከሆነ ማመን የሚኖርበት በጨለማ ነው ሰው ምንም ያህል የተካነና ብርቱ ቢሆን ቀኑን ወደ ጨለማ ሌሊቱን ደግሞ ወደ ቀን መለወጥ አይችልም ልክ እንደዚሁ ሰዎችም እግዚአብሄር የለየውን ደግመው ማበላሸት አይችሉም እግዚአብሄር ያደረገውን ማንም ሊለውጠው አይችልም።

የሰው ሕሊና ትክክል ከሆነ እግዚአብሄር የለየውን ሙሉ በሙሉ ከማመን በቀር ምርጫ የለውም ሰው ብርሃንን ተመልክቶ ከተቀበለው ከላይ የሚመጣውን የእግዚአብሄር ቃል ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይቀበላል ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ ማለትም የምድር ቃሎች የሚያስተዋውቁት የሰዎችን ድርጊቶች ነው ሰው በራሱ ስጋዊ መሰጠትና ጥረቶች የተቀደሰ ሕይወት በመኖር በሌላ አነጋገር ሕጉን በመጠበቅና በመቀደስ

ጻድቅ ይሆናል ማለት የሰይጣን ቃሎች መሆናቸውን በግልጽ ማስታወስ ይገባችኋል የእግዚአብሄር ቃል እንደምን ሐጢያቶቻችንን እንደመሰሰ በልቦቻችን በመገንዘብ ጻድቃን መሆን በዚህ በማመንና ይህንንም እንዳለ በትክክል መቀበል ከሰው ድርጊቶች ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም ከላይ የወረደው የእግዚአብሄር የእውነት ቃል ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ እግዚአብሄር ብቻውን ያጠናቀቀው ደህንነት ነው የወንጌል እውነት ሰብአዊ ምግባሮቻችን ለደህንነታችን አጋዥ ሐይል ሊሆኑ እንዲገባቸው አይጠይቅም።

የእግዚአብሄር ቃል ከሰማይ ወርዶ በምድር ላይ ፍሬዎችን አፍርቶ እንደገና ተመልሶ ወደ ላይ ይወጣል በእግዚአብሄር ቃል ከጠፈር በላይ ባለው ውሃ የምታምኑ ከሆናችሁ ደስታችሁን ታገኛላችሁ ነገር ግን ከጠፈር በታች ባለው ውሃ የምታምኑ ከሆናችሁ ትረገማላችሁ ለመረገም ብቻ ሊታመኑ በማይችሉ መከራዎች ውስጥም ታልፋላችሁ በሕግ ላይ በተመሰረተ የእምነት ሕይወት ስር ያሉ ሰዎች የሚያልፉባቸው መከራዎች ከተለመደው በጣም የተለዩ ናቸው ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ በመጠጣታቸው እንዲህ በብዙ ሲሰቃዩ ማየት አሳዛኝ ነው።

አንድ ጊዜ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ የጠጡ ሰዎች ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ደግመው አይጠጡም ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ብቻ የጠጡ ሰዎች ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ሊጠጡ አይችሉም አሁኑኑ መመለስ የሚገባቸው ለዚህ ነው።

እግዚአብሄር የሚደሰትባቸው የአምላክ አገልጋዮች

እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ፕላኔት ምድርን የሸፈናትን ውሃ በሁለት ከፈለው አንዱን ግማሽ ከጠፈር በላይ ሲያኖረው

ሌላውን ግማሽ በምድር ላይ ተወው እግዚአብሄርም የተነጣጠለ ስም ሰጣቸው ከጠፈር በላይ ያለ ውሃና ከጠፈር በታች ያለ ውሃ ተብለው ተጠሩ እግዚአብሄር ለምን የተጻፈ ቃል ኖረው? እርሱ ይህንን የጻፈው አንድ ቀለል ያለ እውነት እንድናውቅ ነው? አይደለም እግዚአብሄር ይህንን የጻፈው የእግዚአብሄር ቃልና የሰይጣን ቃሎች አብረው እንደሚኖሩ ሊነግረን ነው።

እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ያደረገው ይህንን ነው እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ብርሃንን ከጨለማ እንደለየ የሚናገረውን ቃል አይተናል በሁለተኛውም ቀን የሰማይን ውሃ ከምድር ውሃ ለየ እግዚአብሄር የሰማይን ውሃ ከምድር ውሃ ብርሃንን ከጨለማ በግልጽ በመለየቱ ተደሰተ ታዲያ የሰማይ ውሃ ምንድነው? የምድርስ ውሃ ምንድነው?

በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰብኩ ሁለት አይነት ሰዎች አሉ አንደኛዎቹ የሕዝብ አይነቶች የሰይጣንን ቃሎች በተጨባጭ የሚያስፋፉ ሲሆኑ ሌሎቹ የሕዝብ አይነቶች ደግሞ እውነተኛውን የእግዚአብሄር ቃል የሚሰብኩ ሰዎች ናቸው የኋለኛው ቡድን የእግዚአብሄርን የተጻፈ ቃል ያውቃል በእርሱም ያምናል እርሱንም ይሰብካል የመጀመሪያው ቡድን ግን በራሳቸው ሰው ሰራሽ አስተሳሰቦች ላይ ተመስርተው የተጻፈውን የእግዚአብሄር ቃል በመተርጎም ሰይጣንንና ሕዝቡን የሚያስደስተውን ብቻ ይሰብካሉ እነዚህ ሰዎች ለሰው ዘር የስነ ምግባር መመሪያ መጽሐፍ ይመስል መጽሐፍ ቅዱስን እንደዚያ ይተረጉሙታል ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ ጥሩ ሕይወት መኖር አለበት ብለው ይሰብካሉ ነገር ግን የእግዚአብሄርን ቃል እውነተኛ መልዕክት አያውቁትም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ የማይችሉት ለዚህ ነው።

በአጭሩ አሁን የውሃውንና የደሙን ወንጌል የማይሰብኩ ሰዎች የሰይጣንን ቃሎች የሚሰብኩ ሰዎች ናቸው እነርሱ

የእግዚአብሄርን ቃል ሰብአዊ በሆነ የስነ ምግባርና የሞራል ደርዝ ብቻ የሚያስፋፉ ሰዎች ናቸው እነርሱ የእግዚአብሄር አገልጋዮች አይደሉም እነርሱ የሰይጣን አገልጋዮች ናቸው እነርሱ ሌሎች ለኑሮዋቸው እንደሚሰሩት ሙያቸው የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል መስበክ የሆነ «ደሞዝተኞች» እንጂ ሌላ አይደሉም ሰው በእነዚህ ሰዎች አመራር ስር ሆኖ የእምነት ሕይወቱን የሚመራ ከሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከማደግ ርቆ ይሞታል::

የዚህን ምድር ውሃ ስንጠጣ ለእኛ የሚጠቅመን ውሃ አለ ሌሎች የውሃ አይነቶች ግን ቢጠጡ ጉዳት ያመጣሉ ልክ እንደዚሁ የምንሰማቸው ቃሎች ለነፍሳችን በእጅጉ ጠቃሚ ናቸው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በሚያስፋፉ ሰዎች የተሰበከውን ቃል ብቻ ብታደምጡ በስጋና በነፍስ ትባረካላችሁ አንድ ሰባኪ የእግዚአብሄርን ቃል ገልጦ እርሱን በመስበክ ፋንታ በሰው ላይ ያነጣጠሩ የስነ ምግባርና የሞራል ትምህርቶችን ብቻ አበክሮ የሚናገር ከሆነ እነዚህ ስበከቶች ጥሩ መስለው ቢታዩም አንዳች መንፈሳዊ ለውጥ ማምጣት አይችሉም በተቃራኒው እነዚህን ትምህርቶች የሚሰሙ ሰዎች ነፍሳቸው መንፈሳዊ ሞት ይገጥማታል እነዚህን መሰል ቃሎች የክርስቲያን ልቦችን ይበልጥ መከራ ውስጥ እንዲወድቁ ያደርጋቸዋል በአንጻሩ እውነተኛው የውሃና የመንፈስ ወንጌል ለምናደምጠው ሰዎች ሰላምንና ዕረፍት ያመጣልናል ስለዚህ የእግዚአብሄርን ቃል ስንሰማ ጠቃሚው ነገር የሰባኪው እውቀት፣ ገጽታ ወይም ድምጽ አይደለም ነገር ግን በትክክል ጠቃሚው ነገር ይህ ሰባኪ በእርግጥ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመኑና ይህንንም በትክክል ማስፋፋቱ ነው::

የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል አስፈላጊ ነው ኢየሱስ በማነጎስ 7:15 ላይ እንዲህ ብሎዋል *«የበግ ለምድ ለብሰው*

ከሚመጡባችሁ በውሰጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ሰሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ» ታዲያ ሐሰተኛ ነቢያቶችን ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ማወቅ የምንችለው መንፈሳዊ ፍሬዎቻቸውን በመመልከት ነው::

የአፕል ዛፍ ሙዝ ማፍራት ይችላልን? አንድ የአፕል ዛፍ በጣም የቀጨጨ በመሆኑ ምክንያት የሚያፈራቸው ፍሬዎች የቀጨጩ ይሆኑ ይሆናል ነገር ግን ሁሌም የሚያፈራው አፕሎችን ነው እሾህ ግን ምንም ያህል በእንክብካቤ ያደገ ቢሆንም በፍጹም አፕሎችን ማፍራት አይችልም በሌላ አነጋገር አንድ ሰው ቃሉን ቢሰብክና የእርሱን ቃሎች የሰሙ ሰዎችም ዳግም ቢወለዱ ይህ ሰው የእግዚአብሄር አገልጋይ ነው ነገር ግን ይህ ሰው የሰበካቸውን ቃሎች ከሰሙ በኋላ ሰዎች ከሐጢያቶቻቸው መንጻት ካልቻሉ የእግዚአብሄርን ቃል የሰበከው ሰው በእርግጥም ሐሰተኛ ነቢይ ነው ጉባኤው ሰባኪው በየጊዜው ለአንድ ቀን ለሁለት ቀን ለአንድ አመት የሰበካቸውን ቃሎች ሰምተው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት መቀበል ካልቻሉ ችግሩ ያለው ሰባኪው ላይ ነው በሌላ አነጋገር ሐሰተኛ ነቢያቶች ራሳቸው እንዴት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግም መወለድ እንደሚቻል አያውቁም በዚህም አያምኑም ስለዚህ ሰዎች የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዲቀበሉ የራሳቸውን ቃሎች ብቻ ያስተምሩዋቸዋል::

አንድን ሰው ውጫዊ ገጽታውን በማየት ብቻ ሐሰተኛ ነቢይ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መናገር አንችልም ስለ ሐሰተኛ ነቢያቶች ስናስብ ቁመናቸው ያልተገራ፣ ጨካኝና የሚያስጠላ ገጽታ ያለው እንደሆነ ወደ ማሰቡ እናዘነብላለን ይህ ግን ከጉዳዩ በጣም የራቀ ነው ውሸታሞች ራሳቸውን የሚገልጡት ልክ እንደ የዋህ በግ በብዙ ትህትና ነው መጽሐፍ

ቅዱስ ስለ እነርሱ ሲናገር እንዲህ ይላል «*ይህም ድንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና*» *(2ኛ ቆሮንቶስ 11:14)*

በጣም ብዙ ሰዎች በእነርሱ የተታለሉት ለዚህ ነው ራሱ ዳግም ሳይወለድ የሚሰብክ ስባኪ ሐሰተኛ ነቢይ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው እንደዚህ ስላሉ ሐሰተኛ ነቢያቶች ነው በአይኖቻችን የሚታየው ውጫዊ ገጽታ ፈጽሞ ከእውነቱ ጋር የማይገናኝ ነው ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች በግላቸው ቢያጠቁንም በተጻፈው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እስካመንን ድረስ ደህና ነን።

ሐሰተኛ ነቢያቶች በርካታ ሰዎችን ወደ ጥፋት ነድተዋል እነርሱ ብቻቸውን ሲያልፍ አይሄዱም ነገር ግን ሌሎች ብዙ ሰዎችን ከእነርሱ ጋር አብረው ይወስዳሉ ምክንያቱም ውሸታሞች እንደመሆናቸው ስራቸው ይህ ነውና ሐሰተኛ ነቢያቶች ሰዎችን የማታለል ስራቸውን ጥሩ አድርገው ይሰራሉ ቀሪውን ሕይወታቸውን መኖርን በሚመለከትም የሚጨነቁበት ምንም ነገር የለም ሞኝና ፈጽሞ ፍንጭ የሌለው ጉባኤያቸውም ለመጋቢዎች የሚገባውን ክብር በመለገስ ስጦታዎችን ይሰጡዋቸዋል ያገለግሉዋቸዋል ስለዚህ ውሸታሞች በተንጣለሉ ቪላ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ የቅንጦት መኪናዎችንም ይነዳሉ የተንደላቀቀ ሕይወት ይኖራሉ ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት ጉባኤያቸው በለገሳቸው ገንዘብ ነው።

ነገር ግን እነርሱን ከመውቀስ ይልቅ እኛ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር ፈጽሞ ወደ እነርሱ ጉባኤዎች አለመሄድ ነው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎች የእግዚአብሄርን ስራ ከሐሰተኞች ነቢያቶች ጋር መስራት የለባቸውም ጻድቅ የሆኑ ቅዱሳኖች እግዚአብሄርን በሚያመልኩበት ጊዜ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ከተወለዱ አጋር ቅዱሳኖች ጋር አብረው መሰብሰብ አለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ

ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች በጌታችን ስም በሚሰበሰቡበት ጊዜ እርሱም አብሮዋቸው እንደሚሆን ይናገራል እነዚህ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች የሚያመላክቱት የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ጻድቃኖችን ነው ጻድቃን አብረው ሊሰበሰቡ ቃሉን አብረው ሊያደምጡና ሊማሩ እግዚአብሄርን ሊያመሰግኑና እርሱንም በእምነት ሊከተሉ የሚገባቸው አጋሮቻቸው ከሆኑ ጻድቃን ሰዎች ጋር ብቻ ነው ያን ጊዜ ደህና ይሆናሉ ዳግም የተወለዱ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ብቻ ቢኖሩ መጀመሪያ ዳግም የተወለደው ሰው ቃሉን ቢሰብክና ሁሉም ሰው አምኖ ከእግዚአብሄር ፈቃድ ጋር ቢተባበር ያን ጊዜ በእግዚአብሄር ይባረካል ሌሎችን ከመውቀስ ይልቅ በእርግጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምን እንደሚል ማወቅና ሕይወታችንንም በእምነት መኖር አለብን እኛ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር ይህንን ነው።

ጌታ ወደፊት ሲመጣ ሐሰተኛ ነቢያቶችና እነርሱን የተከተሉ ብዙ አማኞች በጌታ ፊት ቆመው «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ አጋንንትን አስወጥቻለሁ በስምህ ትንቢትን ተናግሬአለሁ በስምህም ብዙ ድንቆችን አድርጌአለሁ» ይላሉ በዚህ ምድር ላይ በነበሩ ጊዜ ትላልቅ ቤተክርስቲያኖችን እንደሰሩና ብዙ ሰዎችን ወደ እየሱስ ክርስቶስ እንዳመጡ ይናገራሉ ነገር ግን በዚያ ጊዜ ጌታችን በግልጽ እንዲህ ይላቸዋል «ሁላችሁንም አላውቃችሁም» ጌታችን «እናንተ አጭበርባሪዎችና ሌቦች!» በማለት ይጮህባቸዋል ከዚያም «ወደ ጨለማ ጣሉዋቸው!» በማለት ያዛል የጌታችን ፍርድ ምን ያህል ቅን ነው? ግልጽ በሆኑ ብያኔዎች ላይ ልብ እስኪጠፋ ድረስ መከራከር አያስፈልግም እርሱ ለሲያል የታጨችን ወደ ሲያል ይልንቸዋል በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ደሙ በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉትን ሰዎችም ሰማይ ያስገባቸዋል በጽድቅ የሚፈርደው ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ

ዋናው አቃቤ ሕግ ነው።።

ጌታችን ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት በመጀመሪያው የፍጥረት ቀን ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት እንዲት የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንደሚቀበሉ ተናግሮዋል በሁለተኛው ቀን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉት ሰዎች ከሰይጠን ቃሎች እንዲርቁ ተናግሮዋል ለጻድቃኖች ሰይጣን ያቀረበውን ውሃ በጭራሽ እንዳይጠጡ በፋንታው የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል በመመገብ መንፈሳዊ እምነት ላይ እንዲደርሱ ነግሮዋቸዋል።።

አጋር ምዕመናኖቼ የእግዚአብሄርን ቃል ስንተረጉም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል መሰረት ልንተረጉመውና ልናምነው ይገባናል የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰብኩ ሰዎችም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት ሊሰብኩ ይገባል በሌላ በኩል ቃሉን የሚሰሙ ሰዎች ከእግዚአብሄር ባሮች የሚወጣውን ቃል መመገብና በእርሱም መኖር አለባቸው በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ ከጠፈር በታች ያለው ውሃ ማለትም በምድር ላይ ያለው ውሃ መንፈሳዊ ትርጉም የሐሰተኛ ነቢያቶች ቃሎች ነው መጽሐፍ ቅዱስ እነርሱን እንዳንሰማቸውም ሆነ ከእነርሱ እንዳንመገብ የሚነግረን ለዚህ ነው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰምተው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት በተቀበሉት መካከል እንኳን መንፈሳዊ እምነታቸው በጣም እንጭጭ ከመሆኑ የተነሳ የሐሰተኛ ነቢያቶችን ትምህርቶች መለየት ያልቻሉ፣ እነርሱን የተቀበሉና በዚህ ምክንያትም መንፈሳዊ ሙታኖች ሆነው የቀሩ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ።።

የእግዚአብሄርን ቃል ስንሰማ በመንፈሳዊ ሁኔታ ጠንቃቆች ልንሆንባቸው የሚገቡን የተወሰኑ ነገሮች አሉ በመጀመሪያ የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰብኩልን ሰዎች የእግዚአብሄር ቃል

የሆነውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንደሚያውቁ በእርሱ እንደሚያምኑና እርሱን እንደሚሰብኩት ለማየት መመርመር አለብን፡፡

የእግዚአብሄር አገልጋዮች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ፈጽመው ዳግም የተወለዱ ሰዎች መሆን አለባቸው ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እምነት ሊኖረው ይገባል በትክክል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እስካመኑ ድረስ ሁላችንም በእግዚአብሄር አገልጋዮች ልንታመንና እነርሱን ልንከተል ይገባናል የእግዚአብሄርን ፈቃድ የሚከተሉትን ሰዎች ምክር መቀበል ይገባናል በሌላ አነጋገር እነርሱ የሚናገሩት የእግዚአብሄር ቃል ነው ምክንያቱም እግዚአብሄር በባሪያዎቹ አማካይነት ለቅዱሳኑ ይናገራልና፡፡

ልንገነዘበው የሚገባን ሌላው ነገር የእግዚአብሄር ባሮችም እንደዚሁ ጉድለቶችና ድካሞች ያሉባቸው መሆኑን ነው የእግዚአብሄር አገልጋዮች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሚያምኑና የሚሰብኩ ከሆኑ ስጋዊ ማንነታቸውንም እንዳለ ልንገነዘብና ልንቀበል ይገባናል ለምሳሌ አንድ የእግዚአብሄር አገልጋይ አስቀያሚ ቢሆን «የእግዚአብሄር አገልጋይ ቆንጆ መሆን አለበት ይህ ሰው ለምን እንዲህ አስቀያሚ ሆነ?» ብለን ልናስብ አይገባንም ከዚህ ርቀን «እግዚአብሄር እንደ እረሱ ያለው ሰው አስነስቶ የእርሱ አገልጋይ አድርጎ እየተጠቀመበት ነው» በማለት ስለ እርሱ እግዚአብሄርን ልናመሰግን ይገባናል፡፡

በሌላ አነጋገር የተቀደሰውን ወንጌል እየሰበኩ ያሉትን የእግዚአብሄር አገልጋዮች በውጫዊ ገጽታቸው ላይ ተመርኩዘን ልንኮንናቸው አይገባንም የትምህርት ዳራን ወይም ዕድሜን የመሳሰሉ የማይረቡ ጉዳዮችንም ማንሳት አይገባንም ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነገር ቢኖር ልቦቻቸው የእግዚአብሄርን ቃል ይወዱ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ፣ ፈቃዱን ያውቁ እንደሆነ

ወይም እንዳልሆነና ይህንንም በእምነት ይከተሉ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ግልጽ ማድረግ ነው።

ከሌላው ሁሉ በላይ የእግዚአብሄር አገልጋዮች በእግዚአብሄር ቃል ላይ እምነት ሊኖራቸው ይገባል እኛ ልናደንቅና ልናከብር የሚገባን የእግዚአብሄርን ባሮች እምነት ነው ምን ያህል የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንደሚወዱ፣ ምን ያህል እግዚአብሄርን እንደሚያመሰግኑ፣ ምን ያህል ለወንጌል መስዋዕት እንደሆኑ፣ ሁሌም ወንጌልን ለማስፋፋት እንደምን ጠንክረው እንደሚለፉ፣ ምን ያህል ነፍሳቶችን እንደሚወዱና ለእነርሱ ደህንነትም ልቦቻቸውን ምን ያህል እንደሰጡ ልናይና ልንከታተል ይገባናል አስቀድመው የእግዚአብሄር አገልጋዮች የሆኑትን ሰዎች ልናከብራቸው ይገባናል በእምነትም ልንከተላቸው ይገባናል እግዚአብሄር የሚወድደን ያን ጊዜ ብቻ ነው።

እግዚአብሄር በመንፈሳዊ ስርአት ውስጥ ይሰራል ምክንያቱም እግዚአብሄር የውሸጉብር አምላክ አይደለምና እርሱ የስርአት አምላክ ነው አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ እምነት አላችሁን? በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን በእውነት ቃል አማካይነት ዳግም እንደተወለዳችሁ በድፍረት መናገር ትችላላችሁን? እንደዚያ ከሆነ አሁን በእርግጥም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም ተወልዳችኋል ሰው ሐጢያት እንዳለባችሁ ሲጠይቃችሁ አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለምታምኑ በግልጽ ልትመልሱለት ትችላላችሁ ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ እንደነጻችሁና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል አማካይነት ዳግም እንደተወለዳችሁ መመስከር ትችላላችሁ የእናንተ ማንነት ይህ ከሆነ እግዚአብሄር መሳሪያዎቹ አድርጎ የሚጠቀምባችሁ የእግዚአብሄር ሕዝብ ናችሁ።

አሁን በግልጽ ልታውቁት የሚገባችሁ አንድ ነገር አለ የእግዚአብሄር አገልጋዮች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሲሰብኩ በእርግጥ በእምነት ዳግም ተወልዳችሁ እንደሆነ ለማወቅ ራሳችሁን ልትመረምሩ ይገባችኋል እስከዚህች ቀን ድረስ በርካታ ሰዎች ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ውጭ አንድ ነገር ሲያስተምሩዋችሁ የነበሩ ሰዎች ገጥመዋችኋል የእግዚአብሄር አገልጋዮች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የእግዚአብሄርን ቃል በሚሰብኩበት ጊዜ ግን ራሳችሁን በጥልቀት መመልከትና በእምነት የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ተቀብላችሁ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ራሳችሁን መመርመር አለባችሁ ሁላችንም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት በግልጽ ማወቅ አለብን በእርሱም ደግሞ ማመን አለብን።

ከአሁን ጀምሮ ሕያው የሆነውን የሕይወት ቃል የሰበኩላችሁን የእነዚህን የእግዚአብሄር አገልጋዮች ቃሎች ምክርና ማደፋፈሪያ በመቀበል የእምነት ሕይወታችሁን ልትኖሩ ይገባችኋል የእምነት ሕይወታችሁን ልትኖሩ የሚገባችሁ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ነው በእግዚአብሄር አገልጋዮችም ላይ ደግሞ እምነት ሊኖራችሁ ይገባል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ይህ ለእኔ እውቅና እንድትሰጡኝ እየጠየቅኋችሁ ያስመስላል ነገር ግን ይህንን የተናገርሁት ፈጽሞ እንዲህ አስቤ አይደለም እኔ ያደረግሁት ነገር ቢኖር በእግዚአብሄር ፈቃድ መሰረት የተፈጸመውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል ለእናንተ መስበክ ብቻ ነው ከዚህ ቀደም በልቦቻችሁ ውስጥ ሐጢያት ቢኖርም አሁን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመስማታችሁ «አሃ ኢየሱስ ክርስቶስ ልክ እንደዚህ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ ሐጢያቶቼን ወስዶዋል» የሚል ግንዛቤ ላይ ደርሳችኋል።

አሁን እናንተ ሐጢያቶቻችሁ በእግዚአብሄር በተጻፈው

የውሃና የመንፈስ ወንጌል እንደተደመሰሱ ወደ ማመን ደርሳችኋል በራሳችሁን ድርጊት ላይ በተመሰረተ መልኩ ወይ እግዚአብሄርን ታደስቱታላችሁ አለበለዚያም ታሳዝኑታላችሁ የሰማይ ውሃና የምድር ውሃ በግልጽ እንደተከፈሉት ብርሃንና ጨለማም እንደተለዩ ሁሉ የእናንተም እምነት ደግሞ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል መለየት አለበት አሮጌው እምነታችሁ አሁን ካላችሁ አዲሱ እምነታችሁ መለየት አለበት አሁን «እኔ በአሁኑ ጊዜ ሐጢያተኛ ነኝ ወይስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ጻድቅ ሰው ሆኜአለሁ?» በማለት ለራሳችሁ ብያኔን መስጠት ይገባችኋል በእግዚአብሄር ፊት በግልጽ ጻድቃን ወይም ሐጢያተኞች መሆናችሁ የሚወሰነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመናችሁ ወይም ባለማመናችሁ ላይ ተመርኩዞ ነው።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ታምናላችሁን? ናመናችሁ ጻድቃን ናችሁ ወይስ ሐጢያተኞች? እናንተ ጻድቃን ሰዎች ናችሁ ጌታችን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት አድኖዋችኋል ስለዚህ በዚህ እውነት በማመን ድናችኋል።

ነገሩ ይህ ከሆነ ልታደርጉት የሚገባችሁ አንድ ተጨማሪ ነገር ይቀራል እርሱም ሁለቱን በልቦቻችሁ ውስጥ በመለየት የእግዚአብሄር አገልጋዮች ወይም የሰይጣን አገልጋዮች ሆናችሁ ለመኖር አእምሮዋችሁን ማዘጋጀት ነው ለሌሎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ የእግዚአብሄር አገልጋይ ሆኖ የመኖር መንገድ ነው እናንተም ደግሞ እንደዚህ ልትኖሩ ይገባችኋል ይህ የሚወሰነው በምታምኑት ቃል ነው።

እኛ የሐጢያቶቻችንን ስርየት የተቀበልነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ነው ከዚያ በኋላ የእምነት ሕይወታችንን የምንኖረውና ጌታን በሚገባ የምናገለግለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ነው የእምነታችን

መሰረት ሌላ ሳይሆን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ነው ዳግመኛ ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ ላለመጠጣት ከፈለጉ ትክክለኛው ነገር የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎች ከአጋር ቅዱሳኖቻቸው ጋር አብረው መሰብሰብና ማምለክ ነው እምነታችን በድርጊት ሊታጀብ ያስፈልገዋል።

በሌላ አነጋገር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ናመንን በኋላ ልንሰማው የሚገባን ከሰማይ በላይ ያለውን ቃል እንጂ የምድርን ቃሎች የሚሰብኩ ሰዎችን አይደለም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ካመናችሁ በኋላ እንደገና ራሳችሁን ዳግም ላልተወለዱ ሰዎች የምታስገዙ፣ እነርሱ የሚሰብኩዋቸውን ቃሎች የምታደምጡና በከንቱ የምታመልኩ ከሆናችሁ እንደገና ወደ ዲያብሎስ አገልጋዮች ትወድቁና ወደኋላ ትመለሳላችሁ።

እኛ እግዚአብሄር በሁለተኛው የፍጥረት ቀን የተናገረውን ልናምን ይገባናል እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ያደረገውን ልናምንና ልንከተል ይገባናል ምክንያቱም እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ያደረገው ማለትም እኛን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ማዳኑ ቀድሞውኑም በእኛ ተፈጽሞዋል ስለዚህ አሁን ንጹህ በሆነው የእግዚአብሄር ቃል በመታመን ልንኖር ይገባናል እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ያደረገውን የምታምኑና እርሱንም የምትከተሉ ከሆናችሁ አትረፍርፎ ይባርካችኋል በእግዚአብሄር መባረካችሁ ወይም አለመባረካችሁ የእግዚአብሄርን ፈቃድ የመከተላችሁ ወይም አለመከተላችሁ ውጤት ነው እኛ የእምነት ሕይወታችንን በትክክል መኖር የምንችለው ጌታ በሁለተኛው ቀን የተናገረውን ቃል ስንከተል ብቻ ነው።

ጠቢብ እንደሆናችሁ አውቃለሁ የእውነትን ቃል ከሰማችሁ በኋላ የእምነት ሕይወታችሁን እንዴት ልትኖሩ እንደሚገባችሁ ተጨንቃችሁ ይሆናል አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል

የሚያምኑ ምዕመናን ሊያደርጉት የሚገባቸው አንድ ነገር አለ የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከተቀበልን በኋላ የእግዚአብሄርን አገልጋዮች መከተል ይገባናል ዳግም ከመወለዳችሁ በፊት የምድርን ውሃ ይሰብኩ የነበሩትን ውሸታሞች አድምጣችኋል ነገር ግን የፈለጋችሁት ይህንን አይደለም ይህ የሆነው እውነትን ባለማወቃችሁ ነው ዳግም ከመወለዳችሁ በፊት ዳግም ያልተወለዱ ሰዎችን ቃሎች ከመስማት በስተቀር ምርጫ አልነበራችሁም::

ነገር ግን አሁን እናንተ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለምታምኑ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ልትመርጡ ይገባችኋል «ልንመርጥ የሚገባን የትኞቹን ቃሎች ነው?» «የእርሱን ቃል የሚሰብኩት እውነተኛ የእግዚአብሄር አገልጋዮች እነማን ናቸው?» እነዚህ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ እናንተ የምትወስኑዋቸውና የምትመልሱዋቸው ጥያቄዎች ናቸው በሌላ አነጋገር እኛ የምንሻውን ማንኛውንም ነገር ማድረግ አንችልም አሁን እኛ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ስለምናውቅ ይህንን ፈቃድ መታዘዝ ሐላፊነታችን ነው::

አሁን የእምነት ሕይወታችሁን ማደስ ይኖርባችኋል እስከ አሁን ድረስ ስትኖሩት ከነበረው በተለየ መልኩ የእምነትን ሕይወት ልትኖሩ ይገባችኋል እንዲህ ያለ የእምነት ሕይወት ለመኖር ምሪት ያስፈልጋችኋል ለምን? በእግዚአብሄር የምትባረኩበት መንገድ ይህ ነው አጋር ምዕመናኖቼ ምሪት ትፈልጋላችሁን?

ቃሉን የሚሰብኩላችሁ የእግዚአብሄር አገልጋዮች ሊኖሩ ይገባል የእግዚአብሄርን ቃል የሚሰብኩ እንዲህ ያሉ ሰራተኞች በመካከላችሁ እንዲነሱ ተስፋዬና ምኞቴ ነው የእግዚአብሄር ሰራተኛ መሆን እንዲያው በድንገት በሰው ስምምነት የሚሆን ነገር አይደለም የቃሉ አገልጋይ ለመሆን ከእናንተ በፊት

አስቀድመው አገልጋዮች የሆኑትን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል የሰበኩላችሁን ሰዎች ቃሎች ማድመጥና መማር መቀጠል አለባችሁ እኔ የእግዚአብሄርን ቃል ሰብኬላችኋለሁ ነገር ግን ልትረዱት ያልቻላችሁት አንዳች ነገር አለን? እኛ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በትክክል ሰምተናል።

ብዙዎቻችን ይህንን ቃል የሰማነው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ነገር ግን ወዳችሁታል? ለመረዳት አስቸጋሪ አልነበረምን? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰወረው የሐጢያት ስርየትን እንድንቀበል የሚያስችለን የወንጌል እውነት ብቻ ሳይሆን በርካታ ምስጢሮች ናቸው ስለ እግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ስለ አገልጋዮቹና ትክክለኛ ስለሆነ መንፈሳዊ የእምነት ሕይወት የሚናገሩ ምስጢሮች ተሰውረውበታል ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ ብዙዎቻችሁ ስትመገቡ የነበራችሁት መንፈሳዊውን የቃሉን እህል ሳይሆን እንክርዳዶችን ብቻ ነበር።

ዕቅዱ የእግዚአብሄርን ቃል የሚያብራሩትን ስብከቶቹን በትጋት አቀናብሮ ማተምና ለእናንተ ማቅረብ ነው ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ለእናንተ ማቅረቤን እቀጥላለሁ የዛሬው ቃል የእግዚአብሄር ሕያው ቃል እንደሆነ ተደርጎ ተደምጦዋልን? እንደዚያ ከሆነ ይህ የሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለምታምኑ ነው ይህ የሆነው እኔም ሕያው በሆነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል ስለማምንና እንደተጻፈውም በትክክል ስለሰበኩት ነው ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ የሰጠንን ጌታ ሁላችንም እናመሰግነዋለን። ✉

እግዚአብሄርን ፈቃድ ለመፈጸም

« ዘፍጥረት 1:9-13 »

«እግዚአብሄርም ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ቦታ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ አለ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውሃ መከማቻውንም ባህር አለው እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ሦስተኛ ቀን::»

ዛሬ ጌታችን በሦስተኛው የፍረት ቀን ያደረገውን ላንፍላችሁ እወዳለሁ እግዚአብሄር በሁለተኛው ቀን ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃ ለየው ነገር ግን ከዚህ በኋላም እንኳን የምድረ ወለል አሁንም በውሃ ተሸፍኖ ነበር ሦስተኛው ቀን ሲመጣ እግዚአብሄር እንዲህ አለ *«ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ቦታ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ»* እንዲሁም ሆነ እርሱ እንዲህም ደግሞ አለ *«ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል»* ይህም ደግሞ የሆነው እግዚአብሄር ባዘዘው መሰረት ነው::

እግዚአብሄር በሦስተኛው ቀን በቃሉ ሰራ መጽሐፍ ቅዱስ የሆነውን ካየ በኋላ «እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ» በማለት ሁለት ጊዜ ይናገራል እግዚአብሄር የብሱ በመገለጡ ተደስቶ ነበር ምድር ፍሬዎችን የሚያፈሩ ቡቃያዎችንና ዛፎችን በመመልከቱ ተደስቶ ነበር።

የምድር ወለል በውሃ ተሸፍኖ በነበረ ጊዜ የብሱ አልተገለጠም ነበር የብሱ ባይገለጥም ምድር ምንም ያህል የረከሰችና የደረቀች ብትሆንም ውብ ሆና ትታይ ነበር ምክንያቱም በውሃ ተሸፍናለችና ነገር ግን እግዚአብሄር በውሃ ተሸፍኖ የነበረው መሬት እንዲገለጥ አደረገው እርሱንም «ምድር» ብሎ ጠራው እግዚአብሄር በውሃ ተሸፍኖ የነበረውን የምድር ገጽታ ከተመለከተ በኋላ መልካም ነው አለ እግዚአብሄር የብሱ ሲገለጥ በማየቱ ለምን ተደሰተ?

እግዚአብሄር እንዲህም ደግሞ ብሎዋል *«ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል»* እዚህ ላይ ምድር የምታመላክተው የሰውን ልብ የሰውን ዘር ሐጢያተኛ ተፈጥሮ ነው የሰው ልብ እጅግ ተንኮለኛና የተበላሸ ነው ሊገለጥ ከሚችለው በላይ የረከሰና የከፋ ነው ነገር ግን በእነዚህ በርካታ ሰዎች ሁሉ መንከል ደረቁ መሬታቸው (ልብ) በተፈጥሮው ክፉ መሆኑን የሚያውቁ ያን ያህል ብዙ ሰዎች የሉም።

ታዲያ የጽድቅ ፍሬዎች ተትረፍርፈው የሚወለዱት በምን አይነት ሕዝብ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ የጽድቅ ፍሬዎች የሚወለዱት መሰረታዊው ተፈጥሮዋቸው ክፉ እንደሆነ በሚያውቁ ሰዎች እንደሆነ ይናገራል።

ይህ መርህ ከአለማዊ መርህ ጋር የሚቃረን ነው በአለም ውስጥ የሰው ልብ የሰማይን በረከቶች እንዲቀበልና ብዙ ፍሬዎችን እንዲያፈራ መልካምና ንጹህ መሆን አለበት ይባላል

ብዙ ሰዎች እንዲህ ያስተውላሉ እንዲህ ያምናሉ ይህንንም ተግባራዊ ያደርጋሉ ነገር ግን የእውነት ቃል ብዙ የእውነት ፍሬዎችን ለማፍራት ልቦቻችን በክፋት የተሞሉ መሆናቸውን ማወቅ እንዳለብን ይናገራል።

ጌታችን እንዲህ ብሎዋል *«ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል» (ማርቆስ 7:21-23)* መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው የሚድኑት ልክ እንደዚህ የተፈጥሮ ማንነታቸውን የሚያውቁ ሰዎች ናቸው።

የዚህ ምንባብ አንደምታ በመሰረታዊው የሰው ልብ ውስጥ ያለውን በትክክል ማወቅ እንደሚያስፈልግ አበክሮ ይናገራል ሰው የሐጢያቶቹን ስርየት ተቀብሎ ይሆናል ነገር ግን በማርቆስ 7:21-23 ላይ የተዘረዘሩትን ሐጢያተኛ ባህሪዎች በመቀበሉ ወይም አንድ ወይም ሁለቱን ተቀብሎ ሌሎቹን በመካድ ላይ ተመስርቶ በጎ ፍሬዎችን አፍርቶ ወይም አላፈራ ይሆናል በሌላ አነጋገር መሰረታዊውን ተፈጥሮዋችንን በሚገልጠው በዚህ ቃል ሙሉ በሙሉ አምኖ ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል።

እግዚአብሄር በዚህ በሦስተኛው ቀን በፈጸመው ስራው አማካይነት ወንጌል ተፈጥሮዋዊው ማንነታቸው የረከሰና የተበላሸ መሆኑን በሚያውቁ ሰዎች አማካይነት ወንጌል የተትረፈረፉ ፍሬዎችን እንዳፈራ በግልጽ እያሳን ነው የሰው ዘር ስጋዊ አስተሳሰቦች ሁሉም ክፉ ናቸው «እኔ የመግደል ስጋዊ ተፈጥሮ አለኝ እኔ አመንዝራ ነኝ እኔ ብልሹ ነኝ እኔ በተፈጥሮዬ እንዲህ ነኝ እግዚአብሄር መንፈሳዊ ፍሬዎችን የሚያፈራው እንዲህ በግልጽ ራሳቸውን በሚቀበሉ ሰዎች አማካይነት ነው።

የዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ እንደሚያብራራው እግዚአብሄር «የብሱም ይገለጥ» ሲል እንዲሁ ሆነ እግዚአብሄር የብሱእንዲገለጥ ያዘዘው ለምንድነው? ምድር በውሃ ተሸፍና ነበር ይህ ውሃ ከጠፈር በታች ያለ የተበከለ ውሃም ይሁን ውሃ አሁንም ውሃ ነው ስለዚህ ቆሻሻዎቹ ሁሉ ወደታች ሲዘቅጡ ውሃው ለአይን ጠርቶ ይታያል ነገር ግን እግዚአብሄር የብሱ እንዲገለጥ በማድረግ የሰው ዘር መሰረታዊ ማንነቱን እንዲያውቅ ፈለገ እዚህ ላይ አንደምታው እኛ ሁላችን ምን ያህል የረከስንና የተበላሸን ሰዎች እንደሆንን ማወቅና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንም መዳን የሚገባን መሆኑ ነው የእምነት ፍሬዎችም የሚወለዱት በእነዚህ ሰዎች አማካይነት ነው።

ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎች ተመችቶዋቸው የሚያድጉት የት ነው? ተመችቶዋቸው የሚያድጉት ብዙ ማዳበሪያ ባለበት ስፍራ ነው እዚህ ላይ ፍሬ የሚያፈራው ዛፍ የሚመላክተው የሐጢያቶቹን ስርየት የተቀበለውን ሰው ነው የወንጌል ፍሬዎች የሚወለዱት በማን አማካይነት ነው? እግዚአብሄር መንፈሳዊ ፍሬዎች የሚወለዱት እውነተኛ ማንነታቸውን እንዳለ በሚያውቁ የእግዚአብሄርን ቃል እንዳለ በሚቀበሉና «በስጋዬ ፍትወታዊ ፍላጎቶች አሉኝ እኔ ሌባ፣ አመንዝራ፣ ብልሹ፣ አስተሳሰቦቹ ክፉ የሆነ ሰው፣ ትዕቢተኛና ሞኝ ነኝ» በማለት ራሳቸውን በቃሉ መሰረት በትክክል ለእግዚአብሄር በሚያምኑ ሰዎች ነው ይህ ፈጽሞ ከአለም ትምህርቶች የሚቃረን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ «በልቦቻችሁ ውስጥ ክፉ አሳቦች፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መስረቅ፣ መጎምጀት፣ መዳራት፣ ስንፍና፣ ትዕቢትና ወ.ዘ.ተ አለ» ይላል ይህ ቢሆንም የእግዚአብሄርን ቃል በማያውቁና ሐጢያተኛ ማንነታቸውን ሙሉ በሙሉ በማይገልጡ ሰዎች አማካይነት የፍሬ ዛፎችን ማብቀልም ሆነ አንዳች ፍሬ ማፍራት አይቻልም

የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ከተቀበሉ በኋላም ቢሆን ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ በማይገልጡ በእነዚህ ሰዎች በእነርሱ አማካይነት ሌሎች መዳን ስለማይችሉ ምንም ፍሬ አይበቅልም በተቃራኒው የሚገለጠው ግብዝነታቸው ብቻ ነው።።

በመንፈሳዊ አነጋገር ሌሎች ሰዎች ምን ያህል መልንም ወይም ጥሩ ሰዎች እንደሆናችሁ ሲናገሩላችሁ መስማት ጥሩ ነገር አይደለም እውነተኛው ማንነታችሁ ከላይ ተዘርዝሮዋል ስለዚህ በጎነቶቻችሁ ውጫዊ ግብዝነት እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም እግዚአብሄር «እናንተ ክፉ ሰዎች ናችሁ እናንተ አመንዝራዎች፣ የምትጎመጁና የምትሰርቁ ሌቦች ናችሁ እናንተ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎችና የከረፋችሁ እንጂ ሌላ አይደላችሁም» ይለናል ይህ ሆኖ ሳለ ራሳችንን ስንመለከት የምናው ይህንን አይደለም አንድ ወይም ሁለት ስህተቶችን ብንቀበልም አሁንም ንጹህ ውሃ እንዳለን ድርቅ እንላለን የቆሻሻ ውሃ መተላለፊያ ቦይ እንኳን እንዳለ ከተተወ ቆሻሻው ሁሉ ዘቅጦ ከላይ ያለው ሽፋን ከጠራ ጥርት ብሎ ሊታይ ይችላል ነገር ግን ይህ ማለት ከላይ ጥርት ብሎ የሚታየው ውሃ በእርግጥ ንጹህ ውሃ ነው ማለት ነው? በአይን ሲታይ ጥርት ያለ ይመስላል ነገር ግን በሁሉም አይነት ተውሳኮች የተሞላ ቆሻሻ ውሃ ነው የሰውም ግብዝነት ልክ እንደዚህ ነው።።

የሰው ልብ ከማንኛውም ሌላ ነገር ይልቅ ክፉ ነው

እግዚአብሄር ፊጽሞ ከሰው አስተሳሰቦች ጋር የሚቃረን እውነት ተናግሮዋል «የብሱ ተገለጠ» ማለት የሰው እውነተኛ ማንነት ተገለጠ ማለት ነው እግዚአብሄር የእግዚአብሄርን ቃል በማመን «በስጋዬ የመግደል ፍላጎቶች አሉኝ የሚያመነዝር፣

የሚሰርቅ፣ የሚዘሙት፣ የሚታበይ፣ የሚሰንፍና በሐሰት የሚመሰክር ልብ አለኝ» በማለት ወደ ግንዛቤ በሚመጡና ከልባቸውም እውነተኛ ማንነታቸውን በሚቀበሉ ሰዎች አማካይነት የወንጌልን ፍሬዎች እንደሚያፈራ ይናገራል እግዚአብሄር ስለ ሰብአዊ ተፈጥሮ የተናገረውን መቀበል ይኖርብናል *«የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?» (ኤርምያስ 17:9)* እንደገናም ይህ ፈጽሞ ከአለም ትምህርቶች ጋር የሚቃረን ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ በወንጌል መኩራትና ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ማድረግ የምትችሉት ክፉ ማንነታችሁን ስታውቁ ነው በራሳችሁ ምንም የምትመጻደቁበት ወይም የምትኮሩበት ምንም ነገር ከሌላችሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ትሰብካላችሁ በኢየሱስ ክርስቶስም ብቻ ትመካላችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ካደረገው ውጭ ያለው ሌላ ነገር ሁሉ የረከሰና የተበላሸ ነው ይህንን በሚገባ የሚያውቁ ሰዎች በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ስፍራ «ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እኔ ያለውን ሰው እንኳን በዚህ መንገድ አድኖዋል እናንተም ደግሞ በማርቆስ 7 ውስጥ የተገለጣችሁ ሰዎች ናችሁ እናንም ልትድኑ ይገባችኋል» በማለት መመስከር ይችላሉ።

አጋር ምዕመናኖቼ በእርግጥ እግዚአብሄር እንደተናገረው ክፉ ሰዎች መሆናችሁን ታምናላችሁን? እያንዳንዱ ሰው እንደዚህ መሆኑን ታምናላችሁን? እግዚአብሄር እንደ እኛ ያሉ ሰዎችን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን የሚያፈሩ ሰዎች አድርጎ ለውጦናል ክፋታቸውን የማይቀበሉ ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ሁሉንም አየነት ርኩሰት በልቦቻቸው ውስጥ ደብቀው መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በጎናቸው ይዘው በጌታ ቀን ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድና አስመሳይ ፈገግታ በማሳየት መልካም ሰዎች መሆናቸውን የሚያስመስሉ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥም

በውሸት ቅድስና የሚያመልኩና የተቀደሰ ሕይወትን እንደሚኖሩ የሚያስመስሉ ሰዎች ናቸው እነርሱ የአለም ሐይማኖተኞችና የግብዝነትን ፍሬዎች የሚራቡ ሰዎች ናቸው።

አጋር ምዕመናኖቼ ሰዎች ቅዱስና ሰናይ ሕይወትን መኖር ይችላሉ? የለም በእርግጥ አይችሉም! እግዚአብሄር «እናንተ የተበላሻችሁ ሰዎች ናችሁ» ይለናል ሰዎች ከእግዚአብሄር የበለተ አለምን እየወደዱና እያገለገሉ ሳለ እንዴት በቅድስና ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን ብዙ ሐይማኖተኞች እንዲህ መኖር እንደሚቻል ያስተምራሉ ስለዚህ ሙሉ በሙሉ የተለሰኑ መቃብሮችን ይመስላሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳውያኖችን የወቀሳቸው ለዚህ ነው ክርስቲያን የሆኑ ሐይማኖተኞች ሐይማኖተኞች የሚሆኑት ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ ብቻ ነው ወደ ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ ግን ክፋታቸው በሙሉ ይገለጣል ሰዎች ሐጢያት በሚሰሩበት ጊዜ የሚገለጠው መሰረታዊው ማንነታቸው ነው እነዚህ ሐይማኖተኞች ግን ይህንን ፈጽመው አያውቁትም።

እግዚአብሄር የሚሰራው ቃሉን በሚቀበሉ ሰዎች አማካይነት ብቻ ነው

በኖህ ዘመን *«እግዚአብሄርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞቱም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ» (ዘፍጥረት 6:5)* ስለዚህ እግዚአብሄር የዚያን ዘመን ሕዝብ በፍርዱ ጠራርጎ አጠፋቸው ኖህ ግን የእግዚአብሄርን ጸጋ አገኘ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ጽፎዋል *«ኖህም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ ኖህ ኣካሄዱን ከእግዚአብሄር ጋር ኣደረገ።» (ዘፍጥረት 6:8-9)*

እግዚአብሄር ጸጋውን ለኖህ በመስጠት አዳነው እግዚአብሄር አሳቦቻቸው ክፉ የሆኑትን ሰዎች ዘርን የሚሰጡ ቡቃያዎችንና እንደ ወገናቸው ፍሬን የሚያፈሩትን የፍሬ ዛፎች እንዲያፈሩ አዘዛቸው እግዚአብሄር በውሃ ውስጥ ማለትም በአለም አይሰራም እርሱ የሚሰራው በተገለጠው ደረቅ መሬት ላይ ነው እግዚአብሄር ምድር ፍሬን እንድታፈራ አደረገ ማለት እግዚአብሄር መሰረታዊው ማንነታቸው በሌላ አነጋገር የብሱ ለተገለጠው ሰዎች የሐጢያት ስርየትን አመጣ ማለት ነው ወንጌልን የሚያገለግለውን መልካም ሥራ እንዲሰሩ የሚያደርገውም እነዚህን ሰዎች ነው።

በእኛ በክርስቲያኖች መንክል በስጋቸው መልካም የሆኑ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ በስጋው መልካም የሆነ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን አይገልጥም እርሱ የሚገልጠው የራሱን መልካምነትና በጎነቶች ብቻ ነው እግዚአብሄር በዚህ ፈጽሞ አይደሰትም ይጠላዋል የሰዎች መልካምነት እግዚአብሄርን እንደሚቃወም ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባናል።

አንዳንድ ሰዎች ጨዋ ስሆን በእርግጥም ጨዋ ነኝ ነገር ግን ሐይለኛ ስሆን በጣም ሐይለኛ ነኝ ይላሉ መልካም ሰው ነኝ ብዩ ለማስመሰል የሚያበቃኝ ምን አይነት በጎነት አለኝ? አጋር ምዕመናኖቼ ከሐጢያት በዳኑት መንክል እንኳን የእግዚአብሄር ክብር የሚገለጠው ክፋታቸውን በተቀበሉ ማለትም የእግዚአብሄርን ቃል እንዳለ በትክክል በሚያምኑ ሰዎች አማካይነት ነው በአንጻሩ በእግዚአብሄር ቃል የማያምኑ ሰዎች ምንም መልካም ፍሬ ማፍራት አይችሉም የእግዚአብሄር ጽድቅ የሚገለጠው እነርሱ ራሳቸው እጅግ የረከሱና እጅግ የተበላሹ ሰዎች መሆናቸውን በሚያውቁ ሰዎች አማካይነት ነው እኛ እንዲህ አይነት ክፉ ሰዎች መሆናችንን የምናውቀው ሁላችንም እነዚህን ሐጢያቶች በድርጊቶቻችን ስለሰራን ሳይሆን ቃሉ

በበራልን ጊዜ «ሁሉም እውነት ነው! እኔ እንዲህ ያለሁ የረከስሁና ክፉ ሰው ነኝ» ብለን በመቀበላችንና ይህንኑም በልቦቻችን በማመናችን ነው እነዚህ ሰዎች ጽድቃቸው ስለተወገደ የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ብቻ ወደ መስበክ መጥተዋል የጽድቅ መሳሪያዎች የሆኑትም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው።

በሚሽን ትምህር ቤታችን ከምትማሩት ተማሪዎች ጀምሮ እስከ አገልጋዮች የወንጌል ሰባኪዎችና በመላው አለም አስካላችሁት ወንድሞችና እህቶች ድረስ ከራሳችሁ ወይም ከሌሎች አጋር ምዕመናኖች ምንም ነገር እንዳትጠብቁ ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ ማንም ሰው ከስጋው ምንም ነገር ባይጠብቅም ብዙዎቻችን አሁንም ድረስ «እኔ ከሌላው የተለየሁ ነኝ» ብለን ወደ ማሰቡ እናዘነብላለን።

ነገር ሰዎች ሁሉ አንድ አይነት ናቸው እግዚአብሄር «ሰዎች የሐጢያት ክምሮች የክፉ አድራጊዎች ዘሮች ከማንኛውም ነገር ይልቅ የተበላሹ ናቸው» ይላል ነገር ግን በእነዚህ ሰዎች አማንይነት ፍሬዎች ሊወለዱ ይችላሉ ይህ የእግዚአብሄር የኪዳን ሐይል ነው ይህ አስገራሚ አይደለምን? እኛ ፍሬ እንድናፈራ ከፈለግን በመጀመሪያ ማን እንደሆንን መረዳት ያለብን መሆኑ ቀላል እውነት ነው እግዚአብሄር «እናንተ በበደሎች የተሞላችሁ ናችሁ» በማለት ራቁታችንን አስቀርቶን በቃሉ ውስጣችንን ስላበራው ሁላችንም በዚህ ማመንና እንዳለ በትክክል ልንቀበለው ይገባናል።

ይህንን እውነት ትቀበላላችሁን? ሁሌም ራሳችንን እንዲህ አድርገን ልንቀበል ይገባናል ከሰው ውስጥ ተጨምቆ ሊወጣ የሚችለው ነገር በሙሉ ቆሻሻ ነው እንደፈለግን ብዙ ልናስብ እንችላለን ነገር ግን ከስጋዊ አስተሳሰቦቻችን ክፉ አሳቦች፣ ቆሻሻ ፍላጎቶች፣ የመግደል አሳብና የማመንዘር ፍትወት ብቻ እንጂ

ሌላ ምንም ነገር ሊወጣ አይችልም እግዚአብሄር የገለጠው የሰው እውነተኛ ስዕላዊ መግለጫ ይህ ነው ይህ ሆኖ ሳለ ግን ብዙ ሰዎች በድርጊቶቻቸው እስካልሰሩዋቸው ድረስ እነዚህን ሐጢያቶች ለማመን ፈጽሞ ፍላጎት የላቸውም እኛን የፈጠረን ፈጣሪ ስለ እኛ ሁሉንም ስለሚያውቅ ማንነታችን ይህ እንደሆነ ቢነግረንም ልንቀበለው አንፈልግም።

ስለዚህ ሐፍረታችንን በበለስ ቅጠሎች ለመሸፈን በርትተን እንሞክራለን ነገር ግን ከበለስ ቅጠል የተሰራ ሽርጥ ምን ያህል ይቆያል? ራሳችንን በግብዝነት ምግባሮቻችን መሸፈናችን ምን ያህል ውጤታማ ነው? ከአንድ ቀን ባነሰ ወይም በግማሽ ቀን ውስጥ ሐፍረታችን በሙሉ ይገለጣል።

እግዚአብሄር የብሉ መገለጡንና ምድርም ዘር መያዝዋን ማየት መልካም እንደሆነ ሁለት ጊዜ ተናግሮዋል እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስን የሚሰብከውን የጽድቅ ፍሬዎች በእግዚአብሄር አይን ውብ የሆኑትን ፍሬዎች የሚያፈራው እውነተኛ ማንነታቸውን በተጨባጭ በሚያውቁ ሰዎች አማካይነት ነው።

የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን መቀበል አለብን

አሁን ልቦቻችሁ ከሰው ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛና እጅግም ክፉ እንደሆኑ ታምናላችሁን?

ነገር ግን እግዚአብሄር የብሉ ሲገለጥ ደስ እንደተሰኘ ሁሉ ሆነ ብለው ክፋታቸውን በድርጊት የሚገልጡ ሰዎች አሉ አንዳንድ ሰዎች የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ከተቀበሉ በኋላ ይህ ምንባብ ስላልገባቸው ሆነ ብለው በነጻነት ክፋታቸውን ይገልጣሉ እንዲህ ማድረግ የለብንም ይህ ምንባብ በቃሉ ፊት ማንነታችንን

እንድንቀበል እንጂ በድርጊታችን ሐጢያተኛውን ማንነታችንን እንድናሳይ አይነግረንም የሚነግረን ነገር ቢኖር የእግዚአብሄር ቃል መቀበል በመጀመሪያ እንዲህ ያለን ሐጢያተኛ ሰዎች መሆናችንን በእግዚአብሄር ፊት ከልባችን ማመንና መገንዘብ ጸጋውን ማግኘትና ጽድቁ ላይ መድረስ እንደሚገባን ነው ጠቢባኖቹ እነዚህ ሰዎች ናቸው።

የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ለተቀበሉ ሰዎች የሚገለጥላቸው የመጀመሪያው ክስተት ከበጎነታቸው ይልቅ ክፋታቸው መገለጡ ነው ዳግም ከመወለዳቸው በፊት አልፎ አልፎ ሲጣሉ የነበሩ ጥንዶች የሐጢያት ስርየትን ከተቀበሉ በኋላ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጣሉ ሰምቻለሁ ስለዚህ የሐጢያት ስርየትን ከተቀበሉ በኋላ «ለምን እንደዚህ እሆናለሁ? ምናልባት የሐጢያቶቼን ስርየት አልተቀበልሁም እንዴ? እንዲህ የምሆነው ለምንድነው?» በማለት ያስባሉ።

ነገር ግን በእርግጥ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምታምኑ ከሆነ ስለ ደህንነታችሁ አትጨነቁ ይህ እግዚአብሄር በቀን ተቀን ሕይወታችሁ ውስጥ ደረቁን መሬት የሚገልጥበት ነው ምክንያቱም መሰረታዊው ተፈጥሮዋችሁ ቃሉን ሙሉ በሙሉ አልተቀበለምና ቃሉን ስንቀበል የጽድቅ ፍሬዎች ይወለዳሉ ቃሉን በልቦቻችን በማንቀበልበት ጊዜ እግዚአብሄር ከእኛ ጋር መታገልና እኛን ማሸነፍ ይኖርበታል ስለዚህ ሁላችንንም በሁኔታዎቻችን ያጋልጠናል በቅርቡ ዳግም የተወለዱ ሰዎች በድካሞቻቸው የሚቃትቱት ለዚህ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ የእግዚአብሄርን ቃል በተለይም መሰረታዊ ስለሆነው ተፈጥሮዋችን የሚነግረንን በተቻለ ፍጥነት መቀበልና በእርሱም ማመን ይኖርብናል ያን ጊዜ በተጨባጭ በእግዚአብሄር ቃል ብርሃን መኖር በወንጌል መመካትና ከወንጌልና ከእግዚአብሄርም ጋር አብረን መኖር እንችላለን።

የሰውን ዘር እውነተኛ ማንነት መገንዘብ አለብን አንዳንድ ሰዎች ግን የሰውን ዘር እውነተኛ ማንነት አያወቁም ወንጌልን ቢሰሙም ገናም ጥሩ ሆነው ለመኖር ይሞክራሉ ይህ የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ደግሞ ውለው አድረው በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ያላቸውን እምነት ይተዉታል የትኛውም የእምነት ሕይወት በዚህ መንገድ ሊኖር አይችልም እኛ በቃሉ አማካይነት በመጀመሪያ በትክክል ማን እንደሆንን መረዳት አለብን፡፡

አሁን ይህ ገብቶዋችኋልን? በቃሉ ውስጥ በተገለጠው መሰረት እውነተኛ ማንነታችሁን በግልጽ ተቀብላችኋልን? የእምነት ሕይወታችንን ስንኖር ሁላችሁም ማንነታችሁን እንድትቀበሉ እመክራችኋለሁ የእኔ ማንነት በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ በትክክል የተገለጠው ነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እኔ ያሉ ሰዎችን ሐጢያቶች በዚህ አለም ላይ የሚኖረውን የእያንዳንዱን ሰው ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደው የምንመንበት ምንም ነገር ስለሌለንና በጎነት ያለው ሰውም ስለሌለ ነው እኔ ጻድቅ ሰው የሆንሁት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተሰበከና እኔም የእግዚአብሄርን ቃል ስላመንሁ ነው በውስጤ ያለው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል ብቻ እውነት እንደሆነ ይመሰክራል የእግዚአብሄርን ጽድቅ የሚያሰራጭ የጽድቅ መሳሪያ የሆንሁት ለዚህ ነው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ባይኖረኝ ኖሮ የበሰበስሁና መጥፎ ሽታ የማፈልቅ ሰው ሆኜ ከመኖር በቀር ምርጫ ባልኖረኝ ነበር፡፡

የሆኖ ሆኖ በእግዚአብሄር ፊት የሚቆሙ ሰዎች ቆሻሻዎቹን ገጽታዎቻቸውን በተቻለ መጠን ላለማጋለጥ ይሞክራሉ ግብዞች ቢያደርጉዋቸውም ሊሸፋፍኑዋቸው ይሞክራሉ በሌላ አነጋገር ሁሉም ሰው ነውሮቹንና ጉድለቶቹን ከእግዚአብሄር ለመደበቅ ይፈልጋል ነገር ግን በልቦቻችን ውስጥ ያለውን ክፋት ለመቀበልና ለማጋለጥ በምንሻበት ጊዜ ዋናው አላማው

የሐጢያቶቻችንን እውነተኛ የስርየት ስጦታ መረዳትና ማወቅ ነው እውነተኛውን የሐጢያቶቻችንን ስርት እንቀበል ዘንድ ክፋታችን ይበልጥ መጋለጥ ያለበት ለዚህ ነው።

በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለው ሐጢያት ሰው በራሱ ጥረት ሊገነዘበው የማይችለው ነገር እንደሆነ እርግጥ ነው ነገር ግን ሐጢያታቸው በእግዚአብሄር ፊት ያልተገለጠ ሰዎች ጌታ በስጦታ ያቀረበውን የሐጢያት ስርየት ሊቀበሉ አይችሉም።

በዮሐንስ ምዕራፍ 8 ውስጥ እጅ ከፍንጅ ስታመነዝር የተያዘችና ሐጢያቶችዋ በኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር የተባሉላት ሴት ታሪክ አለ ከዚህች ሴትና እርሱዋን ሲከሱዋት ከነበሩት በርካታ ሰዎች ውስጥ የሐጢያት ስርየትን በመቀበል የተባረከው ማን ነበር? ድንጋይ አንስተው ሴቲቱን ሊወግሩዋት ተዘጋጅተው ለነበሩት ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አላቸው «ከእናንተ ሐጢያት የሌለበት አስቀድሞ ይውገራት» አላቸው ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ «እናንተ ሁላችሁም ልክ እንደዚህች ሴት እንዲሁ ሐጢያተኞች ናችሁ» እያላቸው ነበር።

ነገር ግን ሕዝቡ በእግዚአብሄር ቃል ፊት ሐጢያተኞች እንደነበሩ ሙሉ በሙሉ ስላላመኑ ሁሉም ከስፍራው ሄዱ የሐጢያቶቻዋን ስርየት መቀበል የቻለችው ሴቲቱ ብቻ ነበረች ይህ ማለት ሐጢያታቸው በእግዚአብሄር ፊት ያልተገለጠባቸው ሰዎች እርሱ ያቀረበውን የሐጢያት ስርየት ለመቀበል ሊባረኩ አይችሉም ማለት ነው ሁሉም ሰው ሐጢያቱን አውልቆ በእግዚአብሄር ሕልውና ፊት ራቁቱን መቆም አለበት ጴጥሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ ጌታን ሲገናኝ *«ጌታ ሆይ እኔ ሐጢያተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ» (ሉቃስ 5:8)* በማለት ተናዞዋል።

ነገር ግን እውነተኛ ማንነታቸውን ፈጽመው የማያውቁ ብዙ ሰዎች አሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሐጢያታቸውን ማወቅ የተሳናቸውና በጥቂቱም እንኳን እንደሚጋለጥባቸው

ስጋት በገባቸው ጊዜ ሁሉ ሊደብቁት የሞከሩት ፈሪሳውያን የእነዚህ ሰዎች ምሳሌ ናቸው የእነርሱ ልቦች በእርሱ ጽድቅ ላይ እምነት አልነበራቸውም በምትኩ በራሳቸው ጽድቅ ይመጻደቃሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ጽድቅ ለመግለጥ ስለሚፈልጉ የደህንነትን እውነት የሚያዋቅረውን የእግዚአብሄር ጽድቅ ለመሸፈን ይሞክራሉ (ሮሜ 10:3) እነርሱ ከሌላው ሰው ሁሉ የተለዩ እንደሆኑ ይናገራሉ እግዚአብሄርን በራሳቸው ጽድቅ ብቻ ስለሚቀርቡት በመጨረሻ በእግዚአብሄር ጽድቅ ማመን ይሳናቸውና ፍጻሜያቸው እርሱን መቃወም ይሆናል በሌላ አነጋገር በራሳቸው ጽድቅ ስለተሞሉ፣ በእምነት ሕይወታቸው ስላማይሳካላቸውና መዳን ስለማይችሉ የእግዚአብሄርን ጽድቅ አጥብቀው መያዝ አይችሉምና በመጨረሻ ትልቅ ክስረት እንደሚደርስባቸው እርግጥ ነው።

ዛሬም ቢሆን የአለም ሐይማኖተኞች የእግዚአብሄርን ጽድቅ ከፍ ከማድረግ ይልቅ በራሳቸው ጽድቅ እየተመጻደቁና ራሳቸውን ከፍ እያደረጉ ይገኛሉ እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ሲቀርቡና እውነተኛ ማንነታቸውን ፈጽሞ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ብቻ ሲገልጡ ማየት አሳፋሪ ትዕይንት ነው።

ነገር ግን እግዚአብሄር ለእነዚህ ሰዎች ምን ያህል የረከሱና የተበላሹ እንደሆኑ ይነግራቸዋል ስለዚህ ሁላችንም አንገቶቻችንንና ልቦቻችንን በትህትና ዝቅ አድርገን በእግዚአብሄር ፊት መቅረብ የእርሱን ጽድቅ መቀበልና በምስጋናም በእርሱ ማመን አለብን በግልጽ አነጋገር እግዚአብሄርን የሚፈሩ ሰዎች ልቦቻቸውን ትሁት ያደርጋሉ የእርሱንም ጽድቅ ከፍ ያደርጋሉ በእርሱም ያምናሉ እውነተኛ ማንነታቸውን የሚያውቁና በእግዚአብሄር ፊት ትሁት እምነት ያላቸው ሰዎች ታላላቅ በረከቶችን ይቀበላሉ ምክንያቱም

በእግዚአብሄር ጽድቅ በማመን ይደሰታሉና የዘመኑ ፈሪሳውያን የዚህ ዘመን ሐይማኖተኞች ልቦቻቸውን መመልከትና ሐጢያታቸውን መቀበል አለባቸው «አቤቱ እኔ በጣም ክፉ ነኝ እባክህ ማረኝ» ብለው ሲያምኑ ያን ጊዜ ጌታ በእውነት ቃሉ አማካይነት ይገናኛቸዋል።

ምናልባት ብዙዎቻችሁ ሰዎች «አንተ ጥሩ ልጅ ነህ! በጣም ጨዋና ውብ ነህ» የሚሉዋችሁን ሰዎች እየሰማችሁ ብዙ መወድሶች እየተረጨባችሁ ያደጋችሁ ትሆኑ ይሆናል ስለዚህ እስከ ዛሬ ድረስ እናንተ ማለት እንዲህ እንደሆናችሁ አስባችሁ ይሆናል እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ቢቆሙም ራሳቸውን አያውቁም ስለዚህ በመጨረሻ እውነተኛ እምነት ላይ መድረስ አይችሉም በውስጣቸው ሁሉም አይነት ርኩሰቶች ቢኖሩባቸውም ንጹሐን ነን ብለው ስለሚያስመስሉ ቀናቶች በተቆጠሩ መጠን ራሳቸውን በግብዝነት በመለሰን ተክነው ሐይማኖተኞች ይሆናሉ።

ነገር ግን በተፈጥሮዋችን በዚህ መንገድ ልንመሰገን የሚገባን መልንምና ጻድቅ ሰዎች የአለመሆናችንን እውነታ መገንዘብ አለብን እግዚአብሄር በውስጣችን ፈጽሞ መልካም ወይም ትክክል የሆነ ነግ እንደሌለ ተናግሮዋል። (ሮሜ 3:10-12)

በእኔ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ አንድ ወንፈድም በቅርቡ ቀጣን ታሪክ ነገረኝ ይህ ወንድም ኮሌጅ ለመግባት ቤቱን ትቶ የእኔ ቤተክርስቲያን በምትገኝበት ከተማ ውስጥ ይኖር ነበር ዕረፍት አግኝቶ ወደ ቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ሁሉ ሁሌም ወላጆቹ «ልጃችን መጥቶዋል! በዚህ ምድር ላይ እንዳንተ ያለ የተሻለ ልጅ ከቶ የት ሊገኝ ይችላል?» ሲሉ ይሰማል።

ነገር ግን ከቤቱ ርቆ የተወሰነ ጊዜ ሲያሳልፍና ራሱን ሲመለከት ያን ያህል መልካም ወይም ጥሩ እንዳልሆነ ነገር ግን ቃላት ከሚገልጠው በላይ የረከሰ ሰው እንደሆነ ተገነዘበ በመሆኑም

ስለዚህ ነገር አሰበ በቅርብ የሚኖሩ ብዙ ዘመዶች ስላሉት ቤቱ በሚሆንበት ጊዜ የተለየ ትኩረት እንዳይስብ መጠንቀቅ እንደነበረበት ተረዳ ለወላጆቹ ለምን እንዲህ ጨዋ እንደመሰለ ይህ ያብራራል ነገር ግን ማንም በማያውቀው ከተማ ውስጥ ጊዜውን ሲያሳልፍ እውነተኛ ማንነቱ ይገለጥ ነበር ስለዚህ ይህ ወንድም በማርቆስ ምዕራፍ 7 ላይ እንደተገለጠው ተፈጥሮዋዊውን ክፉ ማንነቱን ከመቀበል መሸሽ እንዳልቻለ መሰከረ።

አመቺ ሁኔታዎች ላይ ስንሆን ሁላችንም ጥሩ እንደሆንን እናስባለን ነገር ግን አንድ ጊዜ ሁኔታዎቻችን ሲለወጡ ለምሳሌ ወደ አዲስ ከተማ ስንዛወርና ማንም ሰው ጣልቃ ሳይገባብን ፈጽመን ብቻችንን ስንሆን ያን ጊዜ እውነተኛ ማንነታችን በሙሉ ይገለጣል ምን ያህል ክፉና የረከሰን እንደሆንን ወደ መረዳት እንመጣለን።

ነገር ግን አስገራሚው ነገር እግዚአብሄር የአንድን ሰው ክፋት ከገለጠ በኋላ በእርሱ ልብ ውስጥ መስራት የሚጀምር መሆኑ ነው አንድ ገበሬ በእርሻ ላይ ዘሮችን ሲዘራ ያለ ምንም ዝግጅት ዝም ብሎ አይዘራቸውም በመጀመሪያ እርሻውን ያርሳል ድንጋዮችን ይለቅማል መሬቱን ያስተካክላል ከዚያም ዘሮቹን ይዘራል።

እግዚአብሄርም የሚሰራው ልክ እንደዚህ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር መስራት የሚጀምረው በልቦቻችን ውስጥ ያለውን ክፋት በመግለጥ ነው ስለዚህ ምድርን የሸፈነው ውሃ ከደረቀ በኋላ በዚያ ያለው የረከሰ ቆሻሻ እንደሚገለጥ መገንዘብ ይኖርብናል አሮጌ ጎማዎችና የፕላስቲክ ሻንጣዎች፣ የተቀዳዱ ልብሶች፣ ጫማዎች፣ የተገነጣጠሉ ጃንጥላዎችና ቡቱቱዎች፣ ሁሉም አይነት ቆሻሻ ከዚያ ይወጣል የመጠጥ ጠርሙሶችን፣ የቢራ ቆርቆሮዎችን፣ የዊስኪ ጠርሙሶችንና የዛጉ የቤት የኤሌትሪክ መሳሪያዎችንም ማየት እንችላለን።

እግዚአብሄር በመጀመሪያ የሰውን ልብ ይገፍፍና ክፋቱ እርቃኑን እንዲሆን ይገልጠዋል ከዚያ በመነሳት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የደህንነት ስራውን መስራት ይጀምራል አሁን እግዚአብሄር «የብሱም ይገልጥ» ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ መረዳት አለብን።

እግዚአብሄር በሰብአዊ በጎነታችን ፈጽሞ የእግዚአብሄርን ድጋፍ ማግኘት አንችልም ይህ ሆኖ እያለ በርካታ ሰዎች አሁንም ድረስ መልካም እንደሆኑ ስለ ራሳቸው ያስባሉ እነርሱ እውነተኛ ማንነታቸውን ሳያውቁ ራሳቸውን ንጹሐኖች እንደሆኑ ያስባሉ ቢያንስ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የተሻሉ እንደሆኑ ያስባሉ እነርሱ እጅ ከፍንጅ በምንዝር የተያዘችውን ሴት ከከሰሱት ራሳቸውንም ከዚህች ሴት የተሻሉ እንደሆኑ አድርገው ካሰቡ ሰዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው ሐይማኖተኞች ከመጠጥና ከማጨስ ይታቀባሉ ስለዚህ የሚጠጣንና የሚያጨስ ሰውን ሁሉ እንደ ሐጢያተኛ ይቆጥሩታል።

እናንተስ ግን? ወደ ዳንስ ቤት ከሚሄድ ሰው የተሻላችሁ እንደሆናችሁ ታስባላችሁን? የለም እናንተ ምንም የተሻላችሁ አይደላችሁም እናንተ የተሻላችሁ ከሆናችሁ ለዚህ ምክንያቱ አሁን በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለምትኖሩ በእግዚአብሄር ቃል ስለምታምኑና እርሱንም በሕይወታችሁ ስለምትከተሉ ነው ዳግም ባትወለዱና በዚህ አለም ላይ ሐይማኖታዊ ሕይወትን ብቻ ብትኖሩ ኖሮ ከማንኛውም የማያምን ሰው ጋር በተመሳሰላችሁ ነበር እግዚአብሄር በመጀመሪያ የብሱን ምድር የገለጠውና በዚህ በተገለጠው መሬት የሰራው ለዚህ ነው።

እግዚአብሄር በእኛ ላይ ከሰራዎች ስራዎች ሁሉ መጀመሪያ የሰራው ነገር ራሳችንን መልካምና በጎ አድርገን የምንመለከትበትን አስተሳሰብ መስበር ነው እርሱ ግራ

ከተጋቡት አስተሳሰቦቻችንና ከተሳሳቱ አመለካከቶቻችን እኛን አራቁቶናል የሰው መሰረታዊ ባህርይ ራሱ የረከሰና ክፉ ሆኖ ሳለ ይህንን ሳይገነዘቡ እንዴት ትክክለኛ የእምነት ሕይወትን መኖር ይቻላል?

እኔ ዳግም ከመወለዴ በፊት የእምነት ሕይወነን ስኖር ስለበጎነነ በጉባኤዬ ውስጥ ባሉ በብዙዎች ዘንድ ተወድሻለሁ አርአያ አማኝ በመሆንም እውቅና አግኝቻለሁ ስለዚህ እኔም ራሴ ልክ እንደዚህ አስቤአለሁ ነገር ግን እኔም ብሆን በድብቅ በሰራሁዋቸው ሐጢያቶች ሁሌም ስሰቃይ ነበር በመጨረሻ ትክክለኛ የሆነ የእምነት ሕይወትን መኖር የቻልሁት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግም ከተወለድሁና ልቤንና አስተሳሰቦቼን የሸፈነው የውሸት ማንነቴ ከተወገደ በኋላ ነው።

ውሃው ከምድር ሲወገድ ሐጢያታችሁ የሚገለጠው ያን ጊዜ ብቻ ነው የአለም ሐይማኖቶች የሚያደፋፍሩትና የሚሹት ግብዝነት በሙሉም ይገለጣል ስለዚህ የሐሰት ጽድቃችንንና የሐሰት መልካምነታችንን ወርውረን ስንጥል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሄር በቃሉ በሕይወታችን ውስጥ ይሰራል የደህንነትንም ፍሬዎች እንድናፈራ ያደርገናል በእግዚአብሄር ጽድቅ አማካይነት ፍሬዎችን ማፍራት የምንፈልግ ከሆነ በመጀመሪያ በራሳችን ከመደገፍ ይልቅ በእግዚአብሄር ቃል ላይ መደገፍ አለብን ምክንያቱም እውነተኛው ማንነታችን የረከሰና የተበላሸ ነውና በሌላ አነጋገር የራሳችንን ጽድቅ በመስበክ ፋንታ የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ ስንሰብክና የእግዚአብሄርን ጽድቅ በማመን ስንኖር ያን ጊዜ የደህንነት ፍሬዎች በልቦቻችን ውስጥ ይወለዳሉ።

አጋር ምዕመናኖቼ የእኛን ጽድቅ ከእግዚአብሄር ጽድቅ ጋር ስናነጻጽር ያን ያህል በብዙ የከፋንና የረከስን እንደሆንን መገንዘብ አለብን በውስጣችን ምንም ትክክል የሆነ ነገር ስለሌለ

በሁሉም አይነት ርኩሰቶች ስለተሞላን የእግዚአብሄርን ፍጹም ጽድቅ የሚሰጠን ይህ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ይኖረን ዘንድ ፈጽሞ አስፈላጊ ነው የእግዚአብሄር ጽድቅ መውደና ማመን አለብን አሁን አምናችኋልን? በተፈጥሮዋችን ንጹህ ብንሆን ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሊያግዘን ባላስፈለገው ነበር።

እውነተኛው ማንነታችን ክፉና የረከሰ መሆኑን አብዝተን በተረዳን ቁጥር በእግዚአብሄር ፊት አብዝተን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ እንኮራለን እግዚአብሄር የብሱ እንዲገለጥ ያዘዘው ለዚህ ነው የብሱ መገለጥ አለበት ብዙዎቻችሁ አሁንም ድረስ ደረቅ መሬታችሁ አልተገለጠም ደረቁ መሬት ሙሉ በሙሉ መገለጥ አለበት ይህ ግን ሆነ ብላችሁ ብዙ ክፉ ምግባሮችን መስራት አለባችሁ ማለት አይደለም ይልቁንም ይህ ማለት በጎዎች እንደሆናችሁ የሚነግራችሁን ሰውኛ አስተሳሰብ መጣልና በምትኩ እርሱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የገለጠውን የእግዚአብሄር ጽድቅ ማመን አለባችሁ ማለት ነው።

በስጋችንና በአስተሳሰቦቻችን ውስጥ ያለው የተሳሳተ እውቀት በሙሉ መወገድ አለበት አስመሳይ የሆነው መልካምነታችንም እንደዚሁ መወገድ አለበት የእግዚአብሄር ቃል በልቦቻችን ጽላቶች ላይ የሚሰራው ያን ጊዜ ብቻ ነው ሰዎች ኢየሱስን በእምነት መከተል አለባቸው ብዙዎች ግን ይህንን አያደርጉም ዙሪያችሁን ብትመለከቱ ምናልባት በአለም አንጻር በጣም በሳል አስተሳሰብ ያላቸውን አንዳንድ ሰዎች ማየት ትችላላችሁ እየተናገርሁ ያለሁት በአለም መንገዶች ብልጣ ብልጥና ጠንቃቃ ስለሆኑ ሰዎች ነው እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተሉ ደቀ መዛሙርት መሆን አለመቻላቸው እንግዳ ነገር ነው ይህ የሆነበት ምክንያት እነርሱ በእግዚአብሄር ከመታመን ይልቅ በራሳቸው ዕቅዶችና ስሌቶች ስለሚደገፉ ነው።

እነዚህ ሰዎች ብልጣ ብልጥነታቸውን መጣል አለባቸው በዙሪያችሁ ሰብአዊ በጎነቶች ያሉዋቸው ሰዎችም ገጥመዋችሁ ይሆናል እነዚህም ሰዎች ቢሆኑ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መሆን አይችሉም ማንም ሰው በራሱ መልካምነት ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል አይችልም ለምን? ምክንያቱም እነርሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ይበልጥ መልካም ሰዎች እንደሆኑ ያስባሉና እነርሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሻሉ እንደሆኑ እያሰቡ እንዴት እርሱን ሊከተሉት ይችላሉ? እነዚህም ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት መሆን የሚችሉት የራሳቸውን መልካምነትና ኩራት ሲጥሉ ብቻ ነው «አዎ ጌታ ሆይ አንተ ትክክል ነህ ያንተ ቃል ብቻ እውነት ነው» ብለው መመለስና ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተሉ ደቀመዛሙርት መሆን የሚችሉት የእነርሱ የሆነውን ነገር የተዉ ሰዎች ብቻ ናቸው በሰብአዊ ስሜቶች፣ በሰብአዊ ኩራትና በሰብአዊ ስሜቶች የተሞሉ ሰዎች በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባላቸው እምነት ኩራታቸውና ግንኙነቶቻቸው በሙሉ መወገድ አለባቸው።።

ጌታ *«በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ» (ማርቆስ 8:34)* ያለው ለዚህ ነው ምናልባት አሁን «እንዴት እንዲህ እኖራለሁ? ይህ አስጠሊታ ነው» ብላችሁ እያሰባችሁ ይሆናል ነገር ግን አትጨነቁ ለአምላካችን ምስጋና ይድረሰው ወደ ሕይወታችሁ አዲስ ደስታ ይመጣል በቃና ሰርግ ላይ ተገኝተው የነበሩት እንግዶች የተሻለውን ወይን ጠጅ ያጣጣሙት ባለቤቱ ያዘጋጀው ወይን ካለቀ በኋላ ብቻ አልነበረምን?

ከሰው የሆነውን ነገር በሙሉ መጣል አለባችሁ ይህ የሚያስጨንቅ ይመስላል አይደል? ነገር ግን አይደለም በተቃራኒው ሕይወታችሁን መንፈሳዊና ንጹህ ደስታ ይሞላዋል እውነተኛ መንፈሳዊ ምስጋናዎችን ትዘምራላችሁ በእምነትም

ትጸልያላችሁ ቃሉም ደግሞ በልቦቻችሁ ውስጥ በሐይል ይሰራል እኛ በሰበክነው ወንጌል አማካይነትም ብዙ ሰዎች በተጨባጭ ዳኑበትን እውነተኛውን የእምነት ሕይወታቸውን መኖር ይጀምራሉ በራሳቸው መልካምነትና ሰብአዊነት የተመኩ ሰዎች እነዚህን ነገሮች እንዲያስወግዱ ሲነገራቸው እስከዛሬ ድረስ በእነዚህ ላይ ተደግፈው ስለነበር ሁሉም ተጨንቀው ምን እንደሚያደርጉ አያውቁም ነገር ግን እነዚህን ነገሮች በድፍረት ካስወገዱ በኋላ አዲስ ደስታን ይለማመዳሉ ከእግዚአብሄር ዘንድም አዲስ ሐሴት ይበቅላል ከእንግዲህ ወዲህ በእግዚአብሄር መንፈስ እንጂ በሰብአዊ ፍልቅ ስሜታቸው አይሞሉም።

አጋር ምዕመናኖቼ አሮጌዎቹን ነገሮቻችንን መጣል አለብን እግዚአብሄር አብርሃምን *«ከአገርህ፣ ከዘመዶችህም፣ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ» (ዘፍጥረት 12:1)* አለው ልክ እንደዚሁ እግዚአብሄር አሮጌዎቹን ነገሮቻችንን እንድንጥል ይፈልግብናል።

እንደገና ወደ ዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ተመልሰን እግዚአብሄር በሦስተኛው ቀን ምን እንዳደረገልን እንመልከት *«እግዚአብሄርም ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ቦታ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ አለ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውሃ መከማቻውንም ባህር አለው እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።» (ዘፍጥረት 1:9-10)*

የእግዚአብሄር የሚለይ አገልግሎት

እግዚአብሄር በሦስተኛውም ቀን እንደዚሁ መለየቱን ቀጠለ በዚህ ቀን የብሱን ከውሃው ለየ ከሰማይ በታች ያለውን ውሃ በሙሉ በአንድ ቦታ በመሰብሰብም የብሱ እንዲገለጥ አደረገ

የብሱንም ከውሃው ለየው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በአስተሳሰቦቻችንና በልቦቻችን ውስጥ ያለ አንድ ነገር ሊለይ ፈለገ።

ሦስተኛው ቀን ከመምጣቱ በፊት ምድር በሙሉ ፈጽሞ በውሃ ተሸፍኖ ነበር መሬቱና ውሃው በሙሉ በአንድ ላይ ተቀላቅሎ ነበር ይህም ዳግም ቢወለዱም መንፈሳዊ ስርአት ባልተደነገገባቸው ልቦች ውስጥ እግዚአብሄርን የማገልገል ፍላጎትና ራሳቸውን የማገልገል ፍላጎች በአንድ ላይ እንደተቀላቀሉ ያመላክታል ስለዚህ ሰው በዚህ ሁኔታ የእምነት ሕይወቱን የሚመራ ከሆነ በመጨረሻ ወደኋላና ወደፊት ይንጠራወዛል አንዳንድ ጊዜ ለራሱ ይኖራል ሌላ ጊዜ ደግሞ ለእግዚአብሄር ይኖራል የሕይወት ዘመናቸውን ሁሉ ልክ እንደዚህ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ።

ነገር ግን በእነዚህ ሰዎች ልቦች ውስጥ እግዚአብሄር የብሱን ከውሃው ምድሩን ከባሕሮች ይለየዋል «ሕይወታችሁ ለእኔ ነው? ወይስ ለራሳችሁና ለአለም ነው?» እግዚአብሄር ይህንን ጥያቄ በግልጽ እንድንመልስ ይፈልጋል በሌላ አነጋገር እርሱ የተቀላቀሉትን ሁለቱን መነሻዎቻችንን መለየት ይፈልጋል እግዚአብሄር የራሳችንን ስጋና አለምን እንድንወድ አይፈልግም።

የሐጢያት ስርየትን በተቀበልን ሰዎች መካከልም ቢሆን የሕይወት አላማቸው በልቦቻቸው ውስጥ ተቀላቅለውባቸው እንደዚህ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ ስለዚህ ብዙ ሰዎች የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ተቀብለውም እንኳን ሁለቱንም ወገን ለማስደሰት በመሞከር በዚህ አለም ላይ ለመደሰት እየኖሩ ለእግዚአብሄር እንደሚኖሩ ያስመስላሉ።

ሙሉ በሙሉ ወንጌልን ለማገልገል የኖሩ አንዳንድ ሰራተኞች ዕቃቸውን ሸክፈው ከአለም ጋር ተቀላቅለዋል ሁሉም የተናገሩት አንድ የጋራ ነገር ቢኖር ይህ ነበር «እኔም ደግሞ

በነጻነት መኖር እፈልጋለሁ» ነገር ግን ወንጌልን እያገለገልን ብንኖር ነጻነት አይኖረንም? የላቀ ነጻነት አለን በእነርሱ ልቦች ውስጥ ለራሳቸው ያላቸው ፍቅር ለእግዚአብሄር ካላቸው ፍቅር ጋር ተቀላቅሎዋል ይህ አጥብቆ ስለያዛቸው መጨረሻቸው መንፈሳዊ ሞት ሆነ።

ዳግም በተወለዱት መካከልም ቢሆን በመንፈስና በስጋ መካከል ወደፊትና ወደኋላ የሚንዠዋዠዉ ነገር ግን አሁንም ለእግዚአብሄር እየኖሩ እንደሆነ በመናገር ራሳቸውን የሚያጽናኑ ብዙ ሰዎች አሉ እግዚአብሄር እነዚህን ሰዎች አይደግፋቸውም ምድር ከባህሮች እንደተለየች ሁሉ በውስጣችን ያለውን መንፈሳዊ ነገር ከስጋዊው በግልጽ መለየት ይፈልጋል እግዚአብሄር ግራ በተጋቡት ልቦቻችንና አስተሳሰቦቻችን ውስጥ ግልጽ የሆነ ልዩነት ማድረግ ይፈልጋል እግዚአብሄር ስጋን ስጋ፣ መንፈስን መንፈስ፣ የእግዚአብሄርን ሥራ የእግዚአብሄር ሥራ፣ የሰውን ስራ ደግሞ የሰው ስራ አድርጎ በግልጽ ለይቶታል።

እግዚአብሄር በእነዚህ አቅጣጫዎች ውስጥ ግልጽ የሆነ ልዩነት ማድረግ ፈለገ ይህንንም በሦስተኛው ቀን አደረገው አሁን በሚሸን ትምህርት ቤት ውስጥ ቃሉን እየተመገባችሁ ነው በዚህ የሚሸን ትምህርት ቤት ውስጥ የምንማረው ለምንድነው? በእኛ የሚሸን ትምህርት ቤት ውስጥ በሚሰለጥኑና በማይሰለጥኑ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? የሚሸን ትምህርት ቤቱ ስልጠና ግብ በልቦቻችሁ ውስጥ መንፈስን ከስጋ መለየት ነው ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሄር እንድትኖሩም ማድረግ ነው በዚህ አቅጣጫ የእግዚአብሄር ስራ ያልተፈጸመላቸው ሰዎች ለእግዚአብሄርና ለራሳቸው እየኖሩ እንዲህ ወደኋላና ወደፊት የሚንጠራወዙ ሰዎች ናቸው እነዚህ የሦስተኛው ቀን ስራ ሊፈጸምባቸው

የሚገባቸው ሰዎች ናቸው።

አሁን እናንተ ከእኔ ጋር እየኖራችሁ በመሰልጠን ላይ ስላላችሁ ቃሉን በእውቀት ደረጃ ብቻ መማርና መረዳት የሁሉ ነገር መጨረሻ እንዳልሆነ መገንዘብ አለባችሁ ከሁሉ በፊት በልቦቻችሁ ላይ «ለምን ልኑር?» የሚል ምልክት ልታቆሙ ይገባችኋል እናንተ «የእግዚአብሄርን ወንጌል ለማሰራጨት የሚያግዝ ከሆነ ለእግዚአብሄር እኖራለሁ ስጋዬን፣ ጊዜዬን ወይም ማንኛውንም ሌላ ነገር በነጻ እሰጣለሁ» በማለት ቆራጥ በሆነ ልብ የሚሸን ትምህርት ቤታችንን ትምህርትና ሌሎች የስልጠና ኮርሶች መከታተል ይኖርባችኋል።

እግዚአብሄር አእምሮዋችንን ለእግዚአብሄርና ለወንጌሉ ብቻ እንዲኖር ማዘጋጀት ይፈልጋል ስለዚህ በዚህ ጊዜ ለምን እንደምንኖር ግልጽ እንድናድርግ ይጠይቀናል ይህ የመለየት ስራ በውስጣችን በግልጽ መነሳት አለበት መንፈሳዊውን ነገር በውስጣችን ካሉት ስጋዊ ነገሮች መለየት አለብን ይህ ስራ ያለ ምንም ችግር ዳግም በተወለዱት ልቦች ውስጥ መነሳት አለበት።

ፍሬዎችን የማፍራት ስራ ሊጀምር የሚችለው ይህ ስራ ሲሰራ ብቻ ነው ይህ ስራ ሳይሰራ ፍሬ አይወለድም ሰው አንድ እግሩ በአለም ሌላው እግሩ በእግዚአብሄር ውስጥ ከሆነና ልክ አጥር ላይ እንደተንጠለጠለ ሆኖ የእምነት ሕይወቱን የሚኖር ከሆነ እግዚአብሄር በዚህ ሰው ልብ ውስጥ ሊሰራ አይችልም የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከተቀበልን በኋላ የምንኖረው ለእግዚአብሄር እንደሆነ ወይም ለራሳችን፣ ለአለም እንደሆነ ወይም ለእግዚአብሄር መወሰን አለብን አንዱን ወይም ሌላውን መምረጥ አለብን ምርጫው በግልጽ ከተደረገ ጻድቃን ለአለም ሊኖሩ አይችሉም።

በእግዚአብሄር ጸጋ ከእምነታችሁ ቆሻሻዎችን አስወግዱ

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል «ሉሮጌው ነገር ሉልፎዋል እነሆ ሁሉ ሉዲስ ሆኖሉል» (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17) እኛ አዲስ የሆንን ሰዎች ከአሁን ጀምሮ ለእግዚአብሄርና ጽድቅ ለሆነው ነገር ልንኖር ይገባናል ለእግዚአብሄር ብቻ መኖር መንፈሳዊ ነው የስጋን ፍላጎቶች ብቻ ለመፈጸም መሞከር ግን ከስጋ ነው *«እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሄር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሄር ሕግ ሉይገዛምና መገዛትም ተስኖታል በሥጋ ያሉትም እግዚአብሄርን ደስ ሊያሰኙት ሉይችሉም::» (ሮሜ 8:5-7)*

ይህ በልቦቻችንና በአእምሮዋችን ውስጥ ያለ ምንም አሻሚ ሁኔታ መተከል ያለበት ነገር ነው ባለፈው ጊዜ የተደሰታችሁባቸው ነገሮች እንኳን የእናንተ ከሆኑ ለእግዚአብሄርና ለወንጌል ስትሉ በድፍረት ልታስወግዱዋቸው ይገባችኋል በእርግጥ እግዚአብሄርን የማያስደስቱ ከሆኑ በድፍረትና በግልጽ ከልቦቻችሁ ውስጥ ቆርጣችሁ መጣል መቻል አለባችሁ::

ንጹህ ብር ለማግኘት ቆሻሻዎቹ ከብሩ ውስጥ መወገድ እንዳለባቸው ሁሉ በውስጣቸው የተቀላቀሉትን ቀሪዎቹን ስጋዊ ቆሻሻዎችም ከልቦቻችን ውስጥ ማስወገድ አለብን በልቦቻችሁ ውስጥ በተጨባጭ ትክክል የሆነውን በግልጽ ማወቅና መለየት አለባችሁ «ጌታ ሆይ በእርግጥ ለአንተ እኖራለሁ ሕይወቴን በሙሉ ለወንጌልና ለአንተ ቀድሼ እሰጣለሁ ራሴን ለአለምና ለከንቱ ነገሮቹ አልሰጥም» ብላችሁ በመወሰን አእምሮዋችሁን

ማዘጋጀት አለባችሁ፡፡

አጋር ምዕመናኖቼ ቀሪ ሕይወታችንን በአለም እየተደሰትን መኖር እንችላለን ነገር ግን እግዚአብሄር የሚደሰተው እንዲህ በመኖራችን ነው ወይስ እርሱ የሚደሰተው ፈጽመን ለእርሱ ስንኖር ብቻ ነው? እግዚአብሄርን ለማስደሰት ልንኖር የሚገባን ለምንድነው? በሌላ አነጋገር በእግዚአብሄር አይን መልካሙ ነገር ምንድነው? በእግዚአብሄር አይን ትክክለኛው ሕይወት ለእርሱ ለወንጌልና የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዲቀበሉ እርሱን እንዲፈሩትና እንዲከተሉት ለጠፉት ነፍሳቶች መኖር ነው እግዚአብሄር በሦስተኛውም ቀን በእያንዳንዳችሁ ውስጥ መስራት ጀምሮዋል እርሱ በሦስተኛው ቀን የጀመረው ምን አይነት ስራ ነው? እርሱ እንዲህ አለ «በውሃ ውስጥ የሰመጠው የብስ ይገለጥ» ከዚያም የብሱ ተገለጠ እግዚአብሄርም የብሱን በግልጽ ከውሃው ለየው እርሱ የአለምን ፍቅር ከእግዚአብሄር ፍቅር መንፈሳዊውን ከስጋዊው ለይቶታል፡፡

ወንጌልን ለማስፋፋት ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ይኖርብናል ለወንጌል የሚያስፈልግ ከሆነ በእኛ ላይ ስለሚደርስብን ነገር ግድ የለንም እግዚአብሄርን የሚያስደስተው ከሆነ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ፈቃደኞች ነን ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች ነን በእርግጥ ይህንን ወንጌልና እግዚአብሄርን የምንወድ ከሆነ ይህ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ነገር ለመተው ፈቃደኞች መሆን አለብን በሌላ አነጋገር በእግዚአብሄር ፊት ምንም ያህል ክቡር ነገር ቢኖረንም እንኳን ማንኛውንም ነገር ለመተው ፈቃደኞች መሆን አለብን፡፡

አጋር ምዕመናኖቼ እናንተ በዚህ የሚሸን ትምህርት ቤት ውስጥ የምትማሩት ያለ ምክንያት አይደለም ምናልባት አንዳንዶቻችሁ እዚህ የተመዘገባችሁት ምንም አይነት አላማ ሳይኖራችሁ ይሆናል ነገር ግን አጋር ምዕመናኖቼ እግዚአብሄር

ያለ መታከት በልቦቻችሁ ውስጥ እየሰራ ነው እርሱ የሕይወታችሁን መንፈሳዊ ግብ በመወሰን መንፈሳዊውን ከስጋዊ ፍላጎቶቻችሁ እየለየ ነው በሚሽን ትምህርት ቤት ውስጥ በሚኖረው የስልጠና ወቅት መንፈስና ስጋ በልቦቻችሁ ውስጥ በግልጽ መለየት አለባቸው እነዚያን አለማዊ ፍላጎቶች በሙሉ የማስወገዱም ስራ መከናወን አለበት ስለዚህ ይህ ተግባራዊ እንዲሆን ሁላችንም በትጋት መጸለይ አለብን።

በሕይወታችን እግዚአብሄርን መፍራት አለብን

እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ አናውቅ ይሆናል ነገር ግን ቀሪውን ሕይወታችንን ለእግዚአብሄርና ለወንጌል መኖር አለብን ከዘመርናቸው መዝሙሮች አንዱ የሚከተሉትን ግጥሞች ይዞዋል «ስጋችን ሁሉና ሐብታችንን በሙሉ በመስጠት ይህንን ወንጌል እናስፋፋ» በእርግጥ እግዚአብሄርን የምንወድና ወንጌል የምንወድ ከሆነ ስጋችንን ብቻ ሳይሆን ሐብታችንንም መስጠታችን ተገቢ ነው ለዚህ ወንጌል ለእርሱና ለእግዚአብሄር መንግስት መስፋፋት ሁለንተናችንን መስጠት አለብን እንዲህ አድርገን አእምሮዋችንን በሚገባ እስካላዘጋጀን ድረስ ጌታን ማገልገል አንችልም ምድርን ከውሃ በግልጽ የሚለየውም ስራ ሊሰራ አይችልም።

በእርግጥ መኖር የሚገባን ለአለምና ለራሳችን ነው ወይስ ሕይወታችንን መኖር የሚገባን ለእግዚአብሄር ነው? ለእግዚአብሄር መኖር ትክክል ነው ወይስ ስህተት? የትኛው ነው ትክክል? ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሄር መኖር ወይስ በአለም እየተደሰቱ መኖር? ዳግም ለተወለዱ ሰዎች ትክክለኛው ነገር ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሄር መኖር ነው።

አንበሳ ጥንቸልን ቢያሳድድ እንኳን ጉልበቱን በሙሉ እስንላስተባበረ ድረስ ሊይዛት አይችልም በግድግዳ ላይ ሚስማር ስንመታ አመታታችን ላይ እስካላተኮርን ድረስ በትክክል መምታት አንችልም ልክ እንደዚሁ ትንሽዋም ስራ እንኳን የእኛ ን ትኩረትና ጥረት ሁሉ ትጠይቃለች የእግዚአብሄርን ስራ ወደ መስራት ስንመጣም ይህንን ስራ ለማከናወን ልቦቻችንን፣ ጥረታችንን፣ ፈቃዳችንንና መሰጠታችንን ሁሉ ቀድሰን መስጠት ያስፈልገናል የእግዚአብሄር ቃል ይህ ትክክል መሆኑን የሚናገር ከሆነ ይህንን ቃል ልንፈራውና በዚያው መሰረት ልንከተለው ይገባናል::

አጋር ምዕመናኖቼ የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከተቀበልን በኋላ በምንፈልገው በማንኛውም መንገድ እንድንኖር እግዚአብሄር አልነገረንም ምክንያቱም አሁን ሐጢያት አልባ ነንና በተቃራኒው እግዚአብሄር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በትክክል ወደ ግባችን እንድንፈጥን ይነግረናል (ፊልጵስዩስ 3:14) የእግዚአብሄርን ሕግ ትተነዋል? የለም አልተውነውም እግዚአብሄር ስለ ሐጢያቶቻችንን ያስተማረን በሕጉ አማካይነት ነው እርሱ የሐጢያቶቻችንን ስርየት እንድናገኝ ወደ ክርስቶስ መርቶናል መጽሐፍ ቅዱስ አሁን የሐጢያቶቻችንን ስርየት ስለተቀበልን የእግዚአብሄርን ቃል መፍራታችን ትክክል እንደሆነና ይህ ቃል በሚመራን መሰረትም እግዚአብሄርን እንድንወድና ምሉዕ የሆነ ሕይወትን እንድንኖር ይነግረናል የእግዚአብሄርን ቃል በዕውቀት ደረጃ ብቻ በአእምሮዋችን ልንቀበለው አይገባንም የእግዚአብሄርን ቃል በልባችን ማመን አለብን ቅን በሆኑት ልቦቻችንም ለእግዚአብሄርና ለወንጌል ለመኖር መወሰን አለብን::

አሁን ወንጌልን ለማሰራጨት መኖራችን ተገቢ ነው

ሁላችንም «ከአሁን ጀምሮ ለእግዚአብሄር ጽድቅ እኖራለሁ» በማለት አእምሮዋችንን ማዘጋጀት አለብን ይህ አይነቱ ልብ በእርግጥም አስፈላጊ ነው አጋር ምዕመናኖቼ እንደ እኩለ ሌሊት ሕልም አጭር የሆነውን ሕይወታችንን ስንኖር በትክክል ልንኖር የሚገባን ለማነው? ትክክለኛው ነገር ለእግዚአብሄርና ለወንጌል መኖር ነው ለጌታ መኖርና ሌሎች ነፍሳቶችም የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዲያገኙ መኖር ፈጽሞ ትክክል ነው ትክክለኛው ሕይወት ለእግዚአብሄር መኖር ነው።

ብቃት ባይኖረንም በዚህ ምድር ላይ ለወንጌል መኖራችን ትክክል ነው የእርሱን መንግስት ለማስፋትና እየጠፉ ላሉት በርካታ ነፍሳቶች ሕይወታችንን መኖራችን ተገቢ ነው በስጋችን ስንኖር ብዙ የማይረቡ ነገሮችን እናደርጋለን ነገር ግን እኛ ጸድቃኖች እጆቻችንን፣ እግሮቻችንን፣ አንደበቶቻችንን፣ ጭንቅላታችን በሙሉ ለሐጢያተኞች ነፍሳት፣ የእግዚአብሄርን መንግስት ለማስፋፋትና እርሱን ለማገልገል ልናውላቸው ይገባናል ንብረቶቻችንም ለጌታ ማገልገላቸው ተገቢ ነው እንዲህ ያለ ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች ልክ እንደ ዳንኤል እግዚአብሄርን ለማገልገል አእምሮዋቸውን ያዘጋጁ ሰዎች ናቸው።

እናንተ የእግዚአብሄር ሰራተኞች ናችሁ የእግዚአብሄር ሕዝብ ምንም አይነት አጋጣሚዎች ወይም ሁኔታዎች ቢገጥሙዋቸውም እንኳን መኖር ያለባቸው ለእግዚአብሄር ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው ብዙ ሰዎች አስራትን መስጠት ብቻ በቂ ነው ብለው ያስባሉ እነርሱ የሚሰጡት ከገቢያቸው አንድ አስረኛውን ቢሆንም በጣም ብዙ ነው ብለው ይቆጫሉ።

ለእግዚአብሄር አገልጋዮች ግን አንድ አስረኛው ብቻ ሳይሆን ሁሉንም መስጠት ነው የእርሱ አገልጋዮች ሁሉን ነገር ቢሰጡ

ተገቢ ነው በሌላ አነጋገር የጌታ ሕይወት የእነርሱ ሕይወት ነው የጌታ ፈቃድም የእነርሱ ፈቃድ ነው የእርሱ አላማም አላማቸው ነው የእግዚአብሄር ሕዝብ እንደዚህ ነው አስራቶችን መስጠታችን፣ በትንሽ ቤተክርስቲያን ውስጥ ማገልገላችንና በአምልኮ ሰአት ውስጥ ተሳታፊ መሆናችን ብቻውን የእምነት ሕይወት አይደለም ነገር ግን ሁለንተናችንን ለወነጌል መስጠት አለብን የምናደርገውንም ነገር ሁሉ ለወንጌል ማድረግ አለብን የእምነት ሕይወት ማለት ይህ ነው «ይህ ሰአት የእኔ ነው ይህ ሰአት የስራዬ ነው ይህ ሰአት የቤተሰቤ ነው ቀሪው ደግሞ የጌታ ነው» ማለት አይደለም የቤተሰብ ሕይወት፣ የስራ ሕይወት፣ የትምህርት ቤት ሕይወት፣ እነዚህ ሁሉ ለጌታ መኖር ናቸው።

ያን ጊዜ እንዲህ ትሉ ይሆናል «ታዲያ እንዴት እኖራለሁ? ጌታን ብቻ የማገለግል ከሆነ ቤተሰቤን ማን ይንከባከብልኛል?» አጋር ምዕመናኖቼ አትጨነቁ ጌታን ብቻ ብናገለግል እርሱ ለእኛ ሐላፊነቱን በሙሉ ይወስዳል ይንከባከበናልም።

ጌታችን እንዲህ ብሎዋል *«ለሁለት ጌታ መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል ለእግዚአብሄርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም» (ማቴዎስ 6:24)* እንዲህ በማለትም ቀጠለ *«እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማይ አባታችሁ ያውቃልና ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሄርን መንግስት ጽድቅንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» (ማቴዎስ 6:31-33)* እኛ በዚህ ቃል እናምናለን ስለሚያስፈልጉን ነገሮችም አንጨነቅም ምክንያቱም እኛ ከሰማይ ወፎች ይበልጥ በብዙ የከበርን ነንና።

እግዚአብሄር በሦስተኛው ቀን ያከናወነው ይህንን ነው ምድርና ባህሮች መከፈል ነበረባቸው መንፈስና ስጋም በልቦቻችን ውስጥ በግልጽ መለየት አለባቸው ከልቦቻችን ጋር የተጣበቁና የተንጠለጠሉ ስጋዊ ቁርኝቶች ካሉ እነርሱን የመለየት ስራ መከናወን አለበት በሚሽን ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ መሆን አለባቸው ልቦቻችሁ ይህንን አለም መናፈቅ የለባቸውም የስጋችሁን ደስታ ብቻም መሻት የለባችሁም ከጌታ ጋር የመመላለስ ከእርሱ ጋር መከራ የመቀበልና ከእርሱ ጋር የመደሰት ባሕሪይ ሊኖራችሁ ያስፈልጋል አሁን ይህ ገብቷችኋል?

እኛ የመንግስተ ሰማይ ወታደሮች ነን

ልቦቻችን በእግዚአብሄር ፊት በትክክል መዘጋጀት አለባቸው አንድ ሰራዊት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች ቢኖሩትና ይህ ሰራዊት ለአገሩና ለንጉሱ የማይዋጋ ከሆነ እነዚህ ሁሉ በርንታ ወታደሮች ፈጸሞ የማይጠቅሙ ናቸው እነርሱ ወታደራዊ አቅርቦቶችን የሚያባክኑና የአገሪቱንም ሐብት የሚያደርቁ ናቸው::

በአንጻሩ አንድ ሰራዊት 300 ወታደሮች ብቻ ቢኖሩትና እነዚህ ሁሉ ወታደሮች አገራቸውንና ንጉሳቸውን በታማኝት ቢያገለግሉ እነዚህ 300 ወታደሮች ምርጥ የጦር ሐይል ያዋቅራሉ እነርሱ በመቶ ሺህዎች ከሚቆጠሩ ወታደሮች ጋር ቢዋጉም እነዚህ 300 ጠንካራ ወታደሮች ያሸንፋሉ እኛ ምን አይነት ሰራዊት መሆን አለብን? እኛ በእግዚአብሄር ፊት ለወንጌልና ለእርሱ ብቻ የሚኖር ምርጥ ወታደር መሆን አለብን::

ይህንን ለማብራራት እዚህ ላይ አንድ አጭር ታሪክ ልንገራችሁ ከረጅም ዘመን በፊት ሁለት አገሮች ነበሩ አንደኛው የየዋሆች አገር ሲሆን ሌላኛው አገር ብልጥ አገር ነበር በየዋሆቹ አገር ውስጥ ንጉሱም ሕዝቡም ሞኞች ነበሩ በአንጻሩ በብልሆቹ አገር ውስጥ ግን ንጉሱም በጣም ብልህ ሕዝቡም በጣም ብልጣ ብልጥ ነበር።

አንድ ቀን ሁለቱም አገሮች እርስ በርሳቸው ጦርነት ገጠሙ የብልሆቹ አገር ንጉስ «ወደፊት ግፉ!» ብሎ ሲያዝዝ ወታደሮቹ «ግርማዊ ሆይ አሁን መሰለፍ አይገባንም ትንሽ ዘለግ ብንጠብቅ ብልህነት ነው ከዚያም ወደፊት እንገፋለን» በማለት ወደፊት አልገፉም የየዋሆቹም አገር ንጉስ እንዲሁ «ወደፊት ግፉ!» በማለት ትዕዛዝ ሰጠ ወታደሮቹ ይህንን ትዕዛዝ ከሰሙ በኋላ ይሙቱ ወይም አይሙቱ ግድ ሳይሰጣቸው የጦርነት ሜዳውን ወረሩት የየዋሆቹም አገር ጦርነቱን አሸነፈ እንዴት አሸነፉት? ወታደሮቹ የራሳቸውን ትክክለኛ መንገድ በግትርተነት ሳይዙ ንጉሱ ያዘዛቸውን ስላደረጉ ነበር።

በሌላ አነጋገር ወታደሮቹ ብቁ ባይሆኑም ሕይወታቸውን ለንጉሳቸውና ለአገራቸው አሳልፈው ሰጡ የብልጦቹ አገር የየዋሆቹን አገር በቀላሉ ማሸነፍና ጦርነቱን ድል ማድረግ ይችሉ ነበር ምክንያቱም ሁሉም ብልህ ነበሩና ነገር ግን ተሸነፉ ንጉሳቸውም ተማረከ ሰራዊቱም ተደመሰሰ የየዋሆቹ አገር ወታደሮች ጥበብ ቢጎድላቸውም ልቡናቸውን ለንጉሳቸው አዘጋጅተው ነበር ንጉሱ ጦርነቱን ማሸነፍ የቻለው በእነዚህ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን በሰጡ ወታደሮች ነበር።

እናም በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ወታደሮች ነን ይህንን ጦርነት ስንዋጋ ጦርነቱን ማሸነፍ የምንችለው «ጌታ ሆይ ለአንተ ብቻ እኖራለሁ» በማለት ልቦችንን በግልጽ ስናዘጋጅ ብቻ ነው በአንጻሩ ልቡናቸውን በጌታ ላይ ያላኖሩ ሰዎች አንድ መቶ

ጦርነቶችንም እንኴን ቢዋጉ በሚዋጉት በእያንዳንዱ ጦርነት ይሸነፋሉ ታዲያ ልቦቻችን እንዴት ሊሆኑ ይገባቸዋል? ልቦቻችን በግልጽ ለእግዚአብሄር መኖር አለባቸው።

ወደ ሚሽን ትምህርት ቤት የገባነው ለምንድነው? የገባነው ጥሩ ሰባኪዎች ለመሆን ነውን? የተሳካላቸው አገልጋዮች እንሆን ዘንድ ምስጢሮቹን ለመማር ነውን? ወደ ሚሽን ትምህርት ቤት የገባነው ለዚህ ነው እዚህ የሚሽን ትምህርት ቤት ውስጥ የገባነው የሆነ የለየ ስጦታ ማለትም እንደ ልሳን ስጦታ ወይም የትንቢት ስጦታ ያሉ ነገሮችን ለመቀበል አይደለም ታዲያ ወደ ሚሽን ትምህርት ቤት የገባነው ለምንድነው? የገባነው ለጌታ ለመኖር ስለፈለግን እንደሆነ እርግጥ ነው አንድ ጊዜ ለእግዚአብሄር ለመኖር ልቦቻችንን ካዘጋጀን የምንፈልገውን ሁሉ ይፈቅድልናል ይሰጠንማል።

ወደዚህ ሚሽን ትምህርት ቤት የገባነው እንደ ቃየን ለመሆን በስጋዊ ጉዳዮች የተካንን ለመሆን አይደለም ታዲያ አሁን ልንኖር የሚገባን ለምንድነው? እኛ እንደ እንደ አቤል የማይረባ ሕይወትን ብንኖርም ለእግዚአብሄር የሚኖር ሕይወትን መኖር፣ ልቦቻችንን ማዘጋጀት፣ እርሱ ሲናገር መታዘዝና «አዎ» በማለት ልቦቻችንን ከእርሱ ጋር ማቆራኘት አለብን ልቦቻችንን ወደ እግዚአብሄር የቀኑ መሆን አለባቸው ልቦቻችን ከእርሱ ወገን መሆን አለባቸው ወደ ሚሽን ትምህርት ቤት የመጣነው ለእርሱ ለመኖር ነው አሁን እዚህ እየሰለጠንን ያለነው ለዚህ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ አሁን ቃሉን ሰምታችሁ ወደ ሚሽን ትምህርት ቤት በመምጣታችሁ ስላላችሁ አላማ ምን ታስባላችሁ? አላማችሁ በመጠኑ አልተለወጠምን? እናንተ የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ተቀብላችሁ ለእግዚአብሄር ስትሉ ወንጌልን ለነፍሳቶች ለማሰራጨትና የእግዚአብሄርን መንግስት

የሚያስፋፋውን ስራ ለመስራት ወደ ሚሽን ትምህርት ቤት ገብታችኋል አሁን ቃሉን የምትማሩት የምትጸልዩትና በተለያዩ አቅጣጫዎች እየሰለጠናችሁ ያላችሁት ለዚህ አላማ ነው።

ስለዚህ ወደዚህ የሚሽን ትምህርት ቤት የመጡ ሰዎች የራሳቸው የሆኑ ብዙ አስተሳሰቦች ሊኖሩዋቸው አይገባም አስተሳሰቦቻችን መክሰም የሚኖርባቸው እዚህ በሚሽን ትምህርት ቤት ውስጥ ነው አብዝተው የራሳቸውን አሳብ የሚያስቡ ወይም የሆነ የግል ጉዳዮችን የሚሹ ሰዎች የእግዚአብሄር ወታደሮች ለመሆን ብቁ አይደሉም እኛ በስጋችን የጎደልን ብንሆንም እውነተኛ ንጉሳችን የሆነው ጌታችን «ወደፊት ግፉ!» የሚል ትዕዛዝ በሚሰጥበት ሰራዊት ውስጥ ስለተሰለፍን ያለ ምንም ጥያቄ ወደፊት ለመግፋት መዘጋጀትና ጌታ ያዘዘንን ሁሉ ከሙሉ ልባችን መታዘዝ አለብን።

አምላካችን ሁላችንንም የእርሱ ሰራተኞች ሊያደርገን ጠርቶናል። ✉

በእግዚአብሄር ስራ ውስጥ ለመሳተፍ

« ዘፍጥረት 1:9-13 »

«እግዚአብሄርም ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ቦታ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ አለ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውሃ መከማቻውንም ባህር አለው እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ሦስተኛ ቀን::»

እግዚአብሄር በመጀመሪያ የዩኒቨርስን ፍጥረታቶች በሙሉ ፈጠረ ከዚያም ሰውን ፈጠረ ሰዎችም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግም እንዲወለዱ አድርጎዋቸዋል በሦስተኛውም ቀን እግዚአብሄር እንዲህ አለ *«ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል» (ዘፍጥረት 1:11)* ይህ ከሆነ በኋላ እግዚአብሄር መልኑም እንደሆነ አየ::

እግዚአብሄር በሦስተኛው ቀን ከሰራቸው ከእነዚህ ስራዎች መካከል ምድር የምታመላክተው ምንድነው? የምታመላክተው ልቦቻችንን ነው ስለዚህ ይህ ምንባብ የእግዚአብሄርን ቃል

በሰዎች ልቦች ውስጥ በመዝራት እግዚአብሄር ቃሉ በልቦቻችን ውስጥ እንዲበቅል፣ እንዲያብብና ፍሬን እንዲያፈራ አድርጓል ማለት ነው ይህም እግዚአብሄር ለልባችን እንደሚናገርና በዚያ ውስጥም እንደሚሰራ ይነግረናል።

ለእኛ የእምነት ሕይወትን መኖር ማለት የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ውስጥ መቀበልና በእምነት አማካይነትም የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ማፍራት ማለት ነው ነገር ግን የእውነት ቃል በልቦቻችን ውስጥ እንዳያብብና ፍሬ እንዳያፈራ እጅግ ትልቁ እንቅፋት ሰው ሰራህ የስጋ አስተሳሰቦቻችን ናቸው የሰው አስተሳሰቦች አንዲት ነፍስ ከሐጢያት እንድትድንና የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እንድታፈራ የሚጠቅሙት ምንም ጥቅም የላቸውም እግዚአብሄር ከሰማያት በታች ያለው ውሃ በአንድ ስፍራ እንዲሰበሰብ የተናገረው ለዚህ ነው ጌታ በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ እንዴት የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እንደምናፈራ ያስተምረናል።

እግዚአብሄር የእውነት ቃል በልቦቻችን ውስጥ ፍሬዎችን እንድናፈራ ይፈቅዳል

እግዚአብሄር በሦስተኛው የፍጥረት ቀን የብሱ ከውሃው እንዲገለጥ በማድረግ ምድርን ገለጣት ዘሩ ያለባቸውን ቡቃያዎችና ፍሬዎች የሚያፈሩ ዛፎችን ሁሉ አበቀለ እግዚአብሄር *«የብሱም ይገለጥ»* ሲል ምን ማለቱ ነው? ቀደም ብዬ እንደተናገርሁት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የብሱ የሚያመላክተው የሰዎችን ልቦች ነው ታዲያ እግዚአብሄር እዚህ ላይ *«የብሱም ይገለጥ»* ያለው ለምንድነው?

ይህ የሆነበት ምክንያት የእግዚአብሄር ቃል ሐይል

በልቦቻቸው ውስጥ መስራት ይችል ዘንድ ሰዎች በልቦቻቸው ውስጥ ያሉት ሐጢያቶች ምን እንደሚመስሉ ያውቁ ዘንድ ነው ጌታችን የብሱ ይገለጥ ዘንድ በግልጽ ያዘዘው የሰዎችን ሐጢያቶች ለመደምሰስ ስለፈለገና ለአንዱና ለመጨረሻ ለማስወገድ ስለፈለገ ነው።።

የሰዎች ልቦች በተፈጥሮዋቸው ጥሩ ቢሆኑ ኖሮ ደህንነት ባላስፈለገም ነበር ነገር ግን ሰዎች በተፈጥሮ ልቦቻቸው ክፉ ስለሆኑ ሁሉም ከእነዚህ ሐጢያቶች መዳን ያስፈልጋቸዋል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር እዚህ ላይ የሰው ሐጢያቶች በዋናነት መገለጥ እንዳለባቸው ይናገራል ሰዎች ሁሉ ሲወለዱ ጀምረው የተወለዱት ሐጢያተኞች ሆነው ነው እስከ ዕለተ ሞታቸውም ድረስ ሐጢያትን ይሰራሉ ስለዚህ ሰዎች ምን ያህል ሐጢያተኞች እንደደሆኑና በተፈጥሮዋቸውም ምን ያህል ያልተገሩና ክፉዎች እንደሆኑ ማየት መቻል አለባቸው።።

ሰው በልቡ ውስጥ ምን አይነት መሰረታዊ ሐጢያቶች አሉበት?

በሰዎች ልቦች ውስጥ አስራ ሁለት አይነት ሐጢያቶች አሉ እነርሱም ክፉ አሳቦች፣ ምንዝርና፣ ስርቆት፣ መግደል፣ ዝሙት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ምቀኝነት፣ ተንኮል፣ ትዕቢት፣ ስድብ፣ ስንፍና ናቸው እነዚህ ሁሉ ሐጢያቶች በሰዎች ልቦች ውስጥ በመኖር መተላለፎችን እንዲሰሩና በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች እንዲሆኑ ያደርጉዋቸዋል ይህ ማለት ሰዎች በእነዚህ ሐጢያቶች ምክንያት በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ሐጢያት በመስራት ከመቀጠል በቀር ምርጫ የላቸውም ማለት ነው ይህ ማለት ሰው ሁሉ የእግዚአብሄርን ፍርድና ጥፋት

ከመቀበል በቀር ምርጫ የለውም ማለት ነው ስለዚህ የሚያረክሱዋቸው ሰዎች የሚሰሩዋቸው ሐጢያቶች ናቸው ኢየሱስ ራሱ እንዲህ ብሎዋል «*ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክሰው ያ ነው ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል::*» *(ማርቆስ 7:20-23)*

ስለዚህ ሰዎች በልቦቻቸው ውስጥ በዋናነት ምን አይነት ክፋት እንዳለ ማወቅና ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን የደህንነት እውነት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በልቦቻችን ውስጥ መቀበል አለባቸው በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ውስጥ የተዘረዘረው ሐጢያተኛ ተፈጥሮ የሐጢያቶቻችን ስርየት ከተቀበልንም በኋላ እንኳን በስጋችን ውስጥ እንዳለ መቀበል አለብን ጌታ የሰጠንን የእውነት ቃል በእምነት መከተል የምንችለው እንዲህ ሐጢያተኛውን ተፈጥሮዋችንን ስንቀበል ነው ሁላችንም የጌታን ቃል በልቦቻችን ውስጥ መቀበል አለብን በእኛ ውስጥ ምንም መልካም ነገር እንደሌለና መልካም የሆነው እግዚአብሄር ብቻ የመሆኑን እውነታም መገንዘብ አለብን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ መዳን የምንፈልግ ከሆንን ሐጢያታችንን ማወቅና ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን የሐጢያት ስርየት ወንጌል መቀበል አለብን እነዚህ ሁለቱ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች እስካልተሟሉ ድረስ ማንም ሰው የሐጢያቶቹን ስርየት መቀበል አይችልም::

ኢየሱስ ክርስቶስ በሐጢያቶቻቸው ምክንያት ወደ ሲያል የሚወርዱትን ሰዎች ለማዳን ወደዚህ ምደር መጣ ኢየሱስ ክርስቶስ «*ሐጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም*» *(ሉቃስ 5:32)* እንዳለ ኢየሱስ ክርስቶስ እነርሱ

ራሳቸው ሐጢያተኞች መሆናቸውን ሙሉ በሙሉ የተቀበሉትንና በዚህ ምድር ላይ በሐጢያተኞች መካከል የሚኖሩትን ሰዎች ከሐጢያቶች ሁሉ ለማዳን ፈለገ።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ራሳቸው ሐጢያተኞች መሆናቸውን ካልገለጡ ጌታ በሰጠው የውሃና የመንፈስ ወንጌል በማመን የደህንነትን ፍሬ ማፍራት እንደማይችሉ ይናገራል እግዚአብሄር እውነተኛውን የሐጢያት ስርየት እንዲቀበሉ የሚፈቅድላቸው ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ሐጢያተኞች አድርገው የሚቀበሉትን ሰዎች ብቻ ነው ሰው የእግዚአብሄርን የደህንነት ጸጋ ለመቀበል ከፈለገ ሐጢያተኛ መሆኑን መቀበል አለበት ይህ ግን ያለ ምንም መለኪያዎች «እኔ ሐጢያተኛ ነኝ» በማለት ብቻ የሚደረግ አይደለም ይልቁንም ይህ የሚደረገው የእግዚአብሄርን ቃል በማወቅ ነው የእግዚአብሄርን ቃል በማወቃችን ወይን ባለማወቃችን ላይ ተመርኩዞ ወይ ሐጢያተኞች ሆነን እንቀራለን አለበለዚያም ጻድቃን እንሆናለን።

ጌታ በማርቆስ 7:21-23 ላይ እንዳለው ሰዎች ሁሉ ፈጽመው የሐጢያት ክምር እንደሆኑ ማመን አለባቸው በጌታ በማመንም ከሐጢያቶች ሁሉ ደህንነትን መቀበል ያስፈልጋቸዋል የሰው ልብ ከውልደቱ ጀምሮ በተፈጥሮው እንደ መግደል፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መዳራት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና፣ በሐሰት መመስከርና ወዘተ ያሉትን ሐጢያቶች ለመስራት ያዘነበለ ነው ስለዚህ ሁላችንም የእግዚአብሄርን ጽድቅ የፈጸመውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማመንና መከተል አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ የብሉ ይገለጥ ሲል ይህ የሚያመላክተው የራሱ የሰው ክፋት መገለጡን ነው ይህ ማለት እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የራሱን ሐጢያተኝነት በግልጽ የሚቀበለውን ሰው ያድነዋል ማለት ነው በዚያ ሰው

አማካይነትም ብዙ የደህንነት ፍሬዎችን ያፈራል።

ነገር ግን ሐጢያታቸውን የማያምኑ ነገር ግን የራሳቸውን በጎነት የሚናገሩ ሰዎች እግዚአብሄር የሰጠው ደህንነት አይጠቅማቸውም ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄርን ጽድቅ ከመከተል ይልቅ የሚከተሉት የራሳቸውን ጽድቅ ነውና ሰው «አንተ ጥሩ ሰው ነህ አንተ ደግ ነህ» የሚሉትን ሌሎች ሰዎች መስማቱ ስህተት ነው በጣም ደግና ጥሩ ሰው ሆናችሁ ከተመሰገናችሁ እናንተም በመልካምነታችሁ ምናልባት የእግዚአብሄረን ጽድቅ የሚቃወም ሰው እንደምትሆኑ ትገነዘባላችሁ ብዩ ተስፋ አደርጋለሁ የሰው መልካምነት በሰዎች ብቻ ተቀባይነት ያገኘ ግብዝነት ነው ቀደም ተብሎ እንደተነገረው የሰው መሰረታዊ ገጽታ ክፉ የሚያስብና የሚገድል አይነት ሰው ገጽታ ነው እንደ ዝሙት፣ ስርቆት፣ ምንዝርና፣ መዳራት፣ በሐሰት መመስከር፣ ትዕቢት፣ ስንፍናና ወዘተ ባሉ ሐጢያቶችም የተሞላ ነው ስለዚህ ሰዎች ልክ እንደ ቆሻሻ መጣያ ገንዳዎች ናቸው እንደዚያ ባይሆኑ ኖሮ እግዚአብሄር *«የሰው ልብ ከነገር ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?» (ኤርምያስ 17:9)* ያለው ለምንድነው?

ችግሩ ሰዎች እነርሱ ራሳቸው ምን እንደሚመስሉ በትክክል አለማወቃቸው ነው ሰዎች ራሳቸውን እንኳን ያታልላሉ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚቀራረቡት የግብዝነትን ጭምብል አጥልቀው ስለሆነ የሚያዩት እርስ በርሳቸው ያሉዋቸውን የሐሰት መልኮች ነው በዚህም እውነተኛውን ክፉ ተፈጥሮዋቸውን ሳይቀበሉ እስከ መጨረሻው ድረስ ራሳቸውን በመደበቅ ይቀጥላሉ እግዚአብሄርንና ራሳቸውንም በማታለል እስከ መጨረሻው ድረስ ሐጢያተኛውን ማንነታቸውን የማይቀበሉ ብዙ ሰዎች አሉ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄር ልጅ

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ያዳናቸው የመሆኑን የወንጌል እውነት በእምነት የማይቀበሉ ሰዎች ናቸው ስለዚህ ክፋታቸውን በግብዝነት ለመደበቅ የሚሞክሩ ሰዎች እጅግ ክፉዎች ናቸው እነዚህ ሰዎች በዚህ አለም ላይ እጅግ ታላቅ የእግዚአብሄር ጠላቶች ሆነው አብዝተው እርሱን ይቃወሙታል።

ማንም ሰው በተፈጥሮው መልካም አይደለም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ የተባለው ለዚህ ነው *«ዳድቅ የለም አንድ ስንኳ አስተዋይም የለም እግዚአብሄርንም የሚፈልግ የለም ሁሉ ተሳስተዋል በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል ቸርነትን የሚያደርግ የለም አንድስ ስንኳ የለም።» (ሮሜ 3:10-12)*

እግዚአብሄር ለሰዎች ሁሉ «አንተ መዳራትን የምትወድ ሰው ነህ» ይላቸዋል ሰዎች በራሳቸው መንገድ የተቀደሰ ሕይወትን መኖር የሚችሉ ይመስላችኋልን? ይህ ትልቅ የሆነ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው እንደዚያም ሆኖ አለም ሰዎችን መልካም ሕይወትን መኖር እንደሚችሉ እያስተማራቸው ነው የዚህ የሐሰት ትምህርት ውጤትም ሰዎች ጥሩ ሰዎች እንደሆኑ እያስመሰሉ ግብዞች መሆናቸው ነው።

በዘመኑ ክርስትና ውስጥ ያሉ አታላዮች የግብዝነትን አመዶች በቤተክርስቲያን አባሎች ላይ ረጭተዋል ግብዞች መልካም ሰዎች እየመሰሉ በየቀኑ ስለሚኖሩ በእግዚአብሄር ፊት ክፉ ሰዎች መሆናቸውን አያውቁም ክፉ ሰዎች መሆናቸውን የማያውቁት ለምንድነው? መሰረታዊ ማንነታቸውን ስለማያውቁ ነው ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮዋቸው ከውልደታቸው ጀምረው ሐጢያተኞች ሆነው ተወልደዋል ነገር ግን ሰይጣን ዲያብሎስ የግብዝነትን አመዶች በአስተሳሰቦቻችንና በልቦቻችን ላይ ደጋግሞ በመርጨቱ እውነተኛ ማንነታችንን እንዳናውቅ የሰው ዘር ከእግዚአብሄር ዘንድ የሐጢያት ስርየትን እንዲቀበል ይከለክላል።

ዘፍጥረት 6፡5 እንዲህ ይላል «*እግዚአብሄርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ*» በዚህ ምክንያት እግዚአብሄር ፍርዱን በዚህ አለም ላይ አወረደ በዚያን ዘመን የዳኑት የኖህ ስምንት ቤተሰቦች ብቻ ነበሩ የቀረው ክፉ አለም በሙሉ ጠፋ ኖህ ከእግዚአብሄር ዘንድ የደህንነትን ጸጋ በማግኘቱ ከጥፋት ውሃ ዳነ።

እግዚአብሄር የማይወዳቸው ምን አይነት ሰዎችን ነው?

እግዚአብሄር አብዝቶ የማይወዳቸው ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ግብዝነትን የሚያቀነቅኑ ሰዎች ናቸው ክፉ ሐጢያተኞች መሆናቸውን የማይቀበሉ ሰዎች በሙሉ ግብዞች ናቸው ግብዞች በሐጢያቶቻቸው ምክንያት ለሲያል የታጩ መሆናቸውን የሚነግራቸውን የራሳቸውን ሕሊና የማይሰሙና በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን የሐጢያት ስርየት ጥምቀትና የደሙን የደህንነት ወንጌል ችላ የሚሉ ሰዎች ናቸው ግብዞች ታላቅ ሐጢያተኞች ሆነው ሳለ ጻድቅ ሰዎች እንደሆኑ የሚያስመስሉና ገና በተጨባጭ ያልተቀበሉ ሆነው ሳለ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ተቀብለናል የሚሉ ሰዎች ናቸው በእግዚአብሄር ፊት በግብዝነት የሚመላለሱ ሰዎች ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን እውነት ሳያውቁ በእግዚአብሄር የሚያምኑ ሰዎች ናቸው እነርሱ ክፋታቸውን ለመደበቅ ራሳቸውን በግብዝነት ምግባሮች ውስጥ ያሰጠሙ ሰዎች ናቸው።

እግዚአብሄር የሰዎችን ግብዝነት ማለትም የውሸት መልካምነታቸውን አብዝቶ ይጠላል ምክንያቱም ግብዝነታቸው እውነተኛውን የእግዚአብሄር መልካምነት የሚቃወም ነውና ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሄርን ጽድቅ በማክበራችንና

የሰዎችን መልካምነት በማውገዛችን ብቻ ይነቅፉናል በአያሌው እንደተሳሳትንም ይናገራሉ ይህ ከእነርሱ አመለካከት አንጻር ስህተት ሊሆን ይችላል ነገር ግን ከእግዚአብሄር አመለካከት አንጻር ስንመለከተው የዚያኛው ተቃራኒ ነው።።

ሰዎች በተፈጥሮዋቸው ክፉ ናቸው ነገር ግን አሁንም ራሳቸውን ለመደበቅ ሲሉ ሰናይ ምግባሮችን ለማድረግ ይሞክራሉ ሆኖም ክፋቶቻቸውን በትንሽ መልካምነት ለመሸፈን መሞከር ሰማይን በእጅ መዳፍ ለመሸፈን እንደ መሞከር ነው ሰዎች ራሳቸው የረከሱና የተበላሹ ናቸው ታዲያ ሰዎች እንዴት መልካም ናቸው እንላለን? በሰዎች ውስጥ ምን መልካምነት አለ? በተቃራኒው ሰዎች ሐጢያታቸውን መናዘዝና የእግዚአብሄር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በማመን ፍጹም የሆነውን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት መቀበል ይኖርባቸዋል ከዚያም የሐጢያቶቻቸውን ስርየት በመቀበል ጻድቃን ከሆኑ በኋላ መከተል የሚኖርባቸው የእግዚአብሄርን እውነተኛ በጎነት እንጂ የሰዎችን ግብዝነት አይደለም ግብዝነቶቻቸውንና ክፋቶቻቸውን በሙሉ መጣል ይኖርባቸዋል ከዚያም የእግዚአብሄርን እውነተኛ መልካምነት መከተል አለባቸው።።

እኛ የረከስንና የተበላሸን ሰዎች መሆናችንን የምናውቀው እንዴት ነው? ይህንን የምንገነዘበው እነዚህን ሐጢያቶች በምግባሮቻችን በመስራታችን ሳይሆን ራሳችንን በእግዚአብሄር ቃል ስንመለከት እነዚያ ክፋቶች ሁሉ በእርግጥም በልቦቻችን ውስጥ እንደሚገኙ በመቀበል ነው በቃሉ ፊት ሐጢያተኛ የመሆኛው መንገድ ማለትም ራሳችንን ሐጢያተኞች አድርገን የምንቀበልበት መንገድ ይህ ነው የእግዚአብሄርን የደህንነት ጸጋ ለመቀበል በመጀመሪያ በእግዚአብሄር ቃል ፊት ቢያንስ አንድ ጊዜ ሐጢያተኞች መሆን አለብን ሁላችንም ክፉ ሰዎች

ብንሆንም የሐጢያት ስርየትን የሚያስገኘውን የደህንነት ወንጌል በመቀበል ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ ድነን አሁን ጻድቃን ሰዎች ሆነን ሕይወታችንን እየኖርን ነው ከዚህም በላይ በዚህ ሁኔታ ደህንነታቸውን የተቀበሉ ሰዎች በሙሉ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግብዝነታቸውን ጥለው በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ብቻ በማመን ሕይወታቸውን ይኖራሉ።

እግዚአብሄር በሰው ግብዝነት ተስፋ አያደርግም ሁሉም ሰው በተፈጥሮው ግብዝ ስለሆነ እግዚአብሄር በሰዎች ተስፋ ሊያደርግ አይችልም የአለም ሐይማኖቶች በሙሉ ግብዝነትን ስለሚከተሉ እግዚአብሄር ተስፋዎቹን የሚያኖረው በሐይማኖት ላይ ሳይሆን በቃሉ በሚያምኑ ሰዎች ላይ ነው ግብዝነት ሰውን ወደ ውድቀት የሚመራ ብቻ ሳይሆን ሰውን ሁሉ ወደ ክፉ መንገዶች ይነዳል ከዚህም በላይ ግብዝነት የእግዚአብሄርን በረከቶች የሚያግድ ነው በሰዎች ላይም እርግማንን የሚያመጣ መንገድ ነው ስለዚህ ማንም ይሁን ሰው ሁሉ በእግዚአብሄርና በሰዎች ፊት የግብዝነትን ጭምብል ማውለቅና ወደ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል መመለስ አለበት ግብዝነት የሰውን ነፍስ የሚያፈራርስ ነገር ስለሆነ ሰዎች እውነቱን መከተል አለባቸው።

ታዲያ እግዚአብሄር የሰጠው የደህንነት እውነት ምንድነው? ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ነው አሁን ሁላችንም ዳግም መወለድ እንችላለን ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ ጥምቀትን በመቀበልና በመስቀል ላይ በመሞት ከሐጢያቶቻችንንና ከበደሎቻችን ሁሉ አድኖናል።

ከዚህም በላይ በዚህ እውነት አማካይነት በሰዎች ውስጥ ምንም በጎነት እንደሌለ ግልጽ ሆንዋል ማንም ብትሆኑ ራሳችሁን አታታልሉ በሌላ በማንኛውም ሰው ግብዝነትም አትታለሉ ማንም ሰው ራሱን ማስታበይ አይገባውም።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ከማመናችሁ በፊት በጌታ ፊት ክፉ የመሆናችሁን እውነታ ትቀበላላችሁን? እኛ ራሳችን ክፉ ሰዎች የመሆናችንን እውነታ ከሙሉ ልባችን መቀበል አለብን ሰው ምንም ያህል ጥረቶችን ቢያደርግ ከሰዎች የሚወጣው ነገር ክፋት ብቻ ነው ከሰዎች ልቦች ውስጥ የሚወጣው የስርቆት አሳብ፣ ምንዝርና፣ መዳራት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ታይታና እንቅፋት ብቻ ነው እግዚአብሄር የሰዎች መሰረታዊ ክፉ ገጽታ አድርጎ የጠቆመው እነዚህን ክፉ ገጽታቸዎች ነው።።

ይህ ሆኖ ሳለ በዚህ አለም ላይ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች መሰረታዊ ክፋቶቻቸውን ሳይቀበሉ እየኖሩ ነው ክፉ ድርጊቶቻቸው እስካልተገለጡ ድረስ ክፉ እንደሆኑና ወደ ሲያል እየተንደረደሩ እንዳሉ እውነቱን አይቀበሉም ብዙ ሰዎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማይቀበሉበት ምክንያቱ ይህ ነው ነገር ግን የፈጠረን እግዚአብሄር እኛ በተፈጥሮዋችን ክፉ ሰዎች መሆናችንን ስለሚያውቅ «እናንተ ክፉ ሰዎች ናችሁ» ይለናል እግዚአብሄር ክፉ የሆነውን ማንነታችንን እንድንገነዘብ ሕጉን ቢደንግግም ብዙዎች አሁንም ድረስ ክፋታቸውን አለመቀበላቸውን ቀጥለዋል በምትኩ ነውሮቻቸውን በበለስ ቅጠሎች ማለትም በሐይማኖት ሕይወታቸው ለመሸፈን ይሞክራሉ ይህ የሰዎች እጅግ ክፉ ምስል ነው።።

ነገር ግን ማንም ሰው አሳፋሪ ሐጢያቶቹን በዚህ አለም ላይ በሚገኝ በማንኛውም አይነት ሐይማኖት መሸፈን አይችልም ሐጢያቶቹን ማንጻት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር እንደመጣለት፣ በመስቀል ላይም በይፋ እንደሞተለትና ለእርሱም እንደተነሳለት ማመን አለበት የሰው ሐጢያቶች ሊወገዱ የሚችሉት እንዲህ በማመን ብቻ ነው እናንተም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው የውሃና

የመንፈሱ ወንጌል በማመን ከሐጢያቶቻችሁ እንደምትድኑ ተስፋ አደርጋለሁ ጌታ ሰዎች ክፋቶቻቸውን ጥለው የእርሱን እውነት በመሻት የጽድቅ ስራዎችን የሚሰሩ ሰዎች እንዲሆኑ ይሻል ውድ አጋር ምዕመናኖቼ ሰው የእግዚአብሄርን ጽድቅ መከተል ከፈለገ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ብቻ ማመንና ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል አለበት።

በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ እግዚአብሄር የብሉንና ምድርም ዘሮች ያሉባቸውን የፍሬ ዛፎችና ቡቃያዎች ስታበቅል ሲመለከት «መልካም እንደሆነ» ማየቱን ይናገራል እግዚአብሄር ክፉ የሆኑትን ምስሎቻቸውን ለተቀበሉ ሰዎች ሁሉ የሐጢያት ስርየትን የሚያስገኘውን ደህንነት ሰጥቶዋቸዋል ኢየሱስ ክርስቶስን በመስበክም በእግዚአብሄር አይኖች ፊት ውብ የሆነውን የጽድቅ ፍሬ እንዲያፈሩ አድርጎዋቸዋል።

በውሃና በደም በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነት ታምናላችሁን?

ዳግም የተወለዱ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ የተቀበለውን የጥምቀት እውነት በልቦቻቸው ውስጥ ይቀበላሉ ያምኑማል ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ አለም ላይ የተወለደው እኛን ከሐጢያቶቻችን ለማዳን ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በመውሰዱ የሐጢያቶቻችንን ኩነኔ ለመሸከም ሲል ተሰቅሎ ሞተ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ እኛን በእርሱ የምናምነውን አማኞች ዳግመኛ ወደ ሕይወት ለማምጣት በሦስተኛው ቀን ተነሳ እርሱ አሁን በእግዚአብሄር አብ ቀኝ ተቀምጦዋል።

ውድ አጋር ምዕመናን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አምላክ

እንደሆነና እርሱ በሰጠው የውሃውና የመንፈሱም ወንጌል ታምናላችሁን? ነፍሳችሁ የሐጢያቶቻችሁን ስርየት እንድትቀበል የሚፈቅድላት ይህ እምነት ነው ይህ እምነት ከሌላችሁ የሚያስጠላ ሽታ ይዛችሁ የምትጓዙ ሰዎች ትሆናላችሁ ምክንያቱም በግብዝነት ትበሰብሳላችሁና አሁን ግን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ወደ እኛ በመጣው በጌታ ጽድቅ በማመን ሰማይ መግባትና ለዘላለም መኖር እንችላለን።

አሁን ሁላችሁም ክፋታችሁን እንድትቀበሉና በእውነት ቃል በማመንም ከሐጢያቶቻችሁ እንድትድኑ እመክራችኋለሁ ቀደም ብለው በወንጌል በማመን ጻድቃን የሆኑ ሰዎችም የእውነትን ቃል በመቀበልና በማመን ቀሪውን ዘመናቸውን በሙሉ የጽድቅ አገልጋዮች ሆነው እንዲኖሩ እጠይቃቸዋለሁ የእግዚአብሄር እውነተኛ ደህንነት የሚደርሳቸው ግብዝነታቸውን ጥለው ክፉ ኑባሬያቸውን የሚቀበሉ ሰዎች ናቸው እውነተኛ ማንነታቸውን ለሚቀበሉ ሰዎች እግዚአብሄር የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የሚቀበሉበትን በረከትና መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶዋቸዋል።

እግዚአብሄር በስጋዊ አስተሳሰቦቻችን አይሰራም እርሱ በልቦቻችን ውስጥ የሚሰራው በእውነት ቃል አማካይነት ነው እግዚአብሄር በሰዎች ልቦች ውስጥ የቃሉን ዘሮች ዘርቷል በልብ ውስጥም እንዲበቅሉ፣ እንዲያብቡና ፍሬዎችንም እንዲያፈሩ አድርጓል።

ጌታ በዮሐንስ 1:12 ላይ እንዲህ ብሎዋል *«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሄር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው»* ጌታ «እኔ የሰማይ በር ነኝ በሰማያዊው፣ በሐምራዊውና በቀዩ የመገናኛው ድንኳን የመጋረጃ በር በኩል አድኜአችኋለሁ» ይለናል እግዚአብሄር ሕዝቡና ልጆቹ አድርጎናል «እኔ ራሴ አባታችሁና እረኛችሁ እሆናለሁ» ብሎናል የደህንነት አበባ በልቦቻችን ውስጥ

የሚያብበውና የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ የምናፈራው እግዚአብሄር የነገረንን የእውነት ቃል በልቦቻችን ውስጥ ስንቀበል ብቻ ነው።

እውነተኛ የእምነት ሕይወት ሊገኝ የሚችለው የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ስናምን ብቻ ነው የደህንነትን ፍሬ ማፍራት የምንችለው የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ውስጥ ስናምን ብቻ ነው እግዚአብሄርን ከጥልቅ ልባችን ልናመሰግነው ልናገለግለውና የሰማይን በረከቶች ሁሉ ልንቀበል የምንችለው በዚህ ቃል ስናምን ነው እግዚአብሄር እዚህ በዛሬው ምንባብ ውስጥ የተናገረውን በአእምሮዋችን ውስጥ መያዝ አለብን *«እግዚአብሄርም ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል» (ዘፍጥረት 1:11)* እዚህ ላይ ምድር የምታመላክተው የእናንተንና የእኔን ልቦች እንደሆነና እግዚአብሄርም በቃሉ አማካይነት የሚሰራው በልቦቻችን ውስጥ እንደሆነ ታስታውሱ ዘንድ ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በልቦቻችን ውስጥ ባይኖር ኖሮ ልቦቻችን አንዳች ነገርን መስጠት ባልቻሉም ነበር እንዲህ ባሉ ልቦች ውስጥ አንዳች የሚጠቅም ነገር የለም እነዚህ ልቦች ባዶ ናቸው ምንም የሌላቸው ልቦች ናቸው በስጋ ውስጥ ሰው ሰራሽ አስተሳሰቦች አሉ ልብ ግን በተናጥል የሚኖረው በመንፈስ ውስጥ ነው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል የሌለበት ልብ ባዶ ነው በውስጡም ምንም ነገር የለም ዘርን የሚያበቅል ሳርና ፍሬን የሚያፈራ ዛፍ በልቦቻችን ውስጥ ማደግ የሚጀምረው ልቦቻችን እግዚአብሄር በተናገረው ቃል ሲያምኑ ነው።

እኛ በልቦቻችን ቃሉን በማመን ደህንነትን ተቀብለን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነናል በእውነተኛው ሰማይ ባለው በዚህ የእግዚአብሄር ቃል በማመንም የዘላለምን ሕይወት አግኝተናል በልቦቻችንም የእግዚአብሄርን በረከቶች ሁሉ ተቀብለናል

የእናንተና የእኔ ጉዳይ ይህ አይደለምን? በራሳችን አስተሳሰቦች ብንደገፍ ብዙውን ጊዜ እንግዳ የሆኑ ብዙ ጥያቄዎች ብቅ ይላሉ ነገር ግን እነዚህን የስጋ አስተሳሰቦች በሙሉ ማራገፍና በእግዚአብሄር የእውነት ቃል ብቻ ማመን አለብን በእግዚአብሄር ስራውን የሰራው የት ነው? እርሱ በቃሉ አማካይነት በልቦቻችን ውስጥ ሰርቷል እግዚአብሄር በእናንተና በእኔ ልብ ውስጥ «እኔ በውሃ በደምና በመንፈስ ቅዱስ አድኛችኋለሁ ልጆቼም አድርጌአችኋለሁ እናንተ የእኔ ልጆች ናችሁ እናንተ የእኔ ዘር ናችሁ እናንተ ጻድቃን ናችሁ::»

የእግዚአብሄር ቃል ወደ ደህንነት የሚመራን የወንጌል ዘር ነው

እግዚአብሄር ለልቦቻችን ይናገራል እርሱ «እኔ አምላካችሁ ነኝ» ይላል የእግዚአብሄር ቃል የሚያርፈው የት ነው? የእግዚአብሄርን የውሃና የመንፈስ ወንጌል ቃል በሚያምኑ ሰዎች ውስጥ ያርፋል እዚህ ላይ ከሰማያት በላይ ያለው ውሃ በምድር ላይ ይወርዳል ምድርን ያረሰርሳል ከዚያችም ምድር ሕይወት እንዲበቅል ያደርጋል የእግዚአብሄር ቃል ማለትም ከሰማያት በላይ ያለው ውሃ የሕይወት ዘር ነው የእግዚአብሄር የሕይወት ዘር የሚኖረው በምድር ላይ ሳይሆን በቃሉ ውስጥ እንደሆነ ተነግሮዋል ዘሮች ሁሉ በምድር ላይ ይወድቃሉ በመሬት ውስጥ በመቀበርና በመሬት ውስጥ የሕይወትን ቡቃያ በማብቀል ሳር፣ ቡቃያዎች ወይም ዛፎች ሆነው ያድጋሉ እነዚህ ዘሮች ጎመኖች፣ የአፕል ዛፎች ወይም የፒር ዛፎች ሆነው ያድጉና ፍሬዎችን ያፈራሉ::

በሌላ አነጋገር ምድር በራሱዋ ምንም ነገር ልታደርግ

አትችልም የእግዚአብሄር ስራ የሚታወቀው እርሱ በምድር ላይ ስለሚሰራ ነው የተለያየ ሳር፣ ዘርን የሚያበቅሉ ቡቃያዎችና ፍሬን የሚያፈሩ ዛፎች ከምድር የበቀሉት የእግዚአብሄር ቃል በምድር ላይ ስለወረደና ምድርም ቃሉን የሕይወት ዘር አድርጋ ስለተቀበለች ነው በእግዚአብሄር ስናምን ልናምን የሚገባን እንዴት ነው? በእግዚአብሄር ቃል ማመን በእግዚአብሄር ማመን ነው እግዚአብሄር ምን ይለናል?

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ሐጢያቶቻችንን እንደደመሰሰና መለኮታዊ የሆኑ ሰማያዊ በረከቶችን እንደሰጠን ተናግሮዋል እግዚአብሄር በመገናኛው ድንኳን የመግቢያ በር ላይ በተንጠለጠሉት በጥሩው በፍታ፣ በሰማያዊው፣ በሐምራዊውና በቀዩ ማግ ልጆቹ እንዳደረገን ተናግሮዋል ስለዚህ እኛ አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት የምናምን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነናል።

ታዲያ ከእግዚአብሄር ጋር ያለን ግንኙነት ምንድነው? እግዚአብሄርን አባታችን ብለን ልንጠራው እንችላለን ጌታችንም ብለን እንጠራዋለን ምክንያቱም እግዚአብሄር ጌታችንና አዳኛችን ነውና አሁን እኛ እውነተኛ የእምነት ሕይወትን እየኖርን ያለነው እግዚአብሄር ለልቦቻችን በተናገረው በዚህ የእውነት ቃል ባለን እምነታችን አማካይነት ነው የራሳችንን አስተሳሰቦች በመከተል ትክክለኛ የእምነት ሕይወትን መምራት አንችልም እውነተኛ ሕይወትን መኖር የሚቻለው የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ውስጥ ስናምን ብቻ ነው እግዚአብሄርን ማመሰገንም እንደዚሁ በልቦቻችን የምናደርገው ነገር ነው እግዚአብሄር የሚሰራው በእናንተና በእኔ ልቦች ውስጥ መሆኑን ማወቅ አለባችሁ እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል አማካይነት ቀድሞውኑም በልቦቻችሁ ውስጥ እንደሰራ ታምኑ ዘንድ ሁላችሁንም እጠይቃችኋለሁ።

ከሰማያት የመጣው የእግዚአብሄር ወንጌል

በእስራኤል የሙት ባህር ተብሎ የሚጠራ አንድ የተለየ ሐይቅ አለ በዚያ ስፍራ ሕይወት ያለው ነገር ሊኖር አይችልም ከገሊላ ባህር የሚነሳው የዮርዳኖስ ወንዝ ወደዚያ ይፈስሳል ከእስራኤል ሸለቆዎች የሚወርደው ውሃ በሙሉ ወደዚያ ይገባል የሙት ባህር ወለል ብቻውን ከባህር ጠለል በታች በግምት 400 ሜትር ይሆናል ከሙት ባህር የሚበልጥ ዝቅትኛ ስፍራ ስለሌለ ወደ ባህሩ የሚፈስሰው ውሃ በሙሉ ወደሌላ ወደማንኛውም ስፍራ ሊሰርግ አይችልም አካባቢው ካለው ሞቃታማ የአየር ንብረት ምክንያት ውሃው በፍጥነት ሲተን በሙት ባህር ውስጥ ያለው የጨው መጠን በጣም ከፍተኛ ነው ስለዚህ በሙት ባህር ውስጥ አሳ የለም በዚያ ቦታ ሕይወት ሊኖር አይችልም በሙት ባህር ዳርቻዎች አካባቢም ሳር ወይም ዛፎች መብቀል አይችሉም::

የሰው አስተሳሰቦች አለምም ልክ እንደ ሙት ባህር ነው የእግዚአብሄር ቃል በሰው አስተሳሰቦች ውስጥ አይሰራም የእግዚአብሄር ቃል በባህር ውሃ ላይ ቢወድቅ ኖሮ እግዚአብሄር ስራ ባልተሰራም ነበር የእግዚአብሄር ቃል በስጋዊ አስተሳሰቦቻችን ባህር ላይ ወድቆ ቢሆን ሕይወት መብቀልና ማደግ ባልቻለም ነበር በዚህ ምክንያት የእምነት ሕወይታችንን መኖር የሚገባን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ነው በእግዚአብሄር ላይ እምነት እንዳለን የሚታወቀውም በእግዚአብሄር ቃል በማመናችን ነው በልቦቻችን በእግዚአብሄር ቃል ማመን አለብን::

ሰዎች ዕብራውያን ምዕራፍ 11ን የእምነት መጽሐፍ የሚል ስያሜ ሰጥተውታል ዕብራውያን 11:24-31ን ብንመለከት እንዲህ ተጽፎዋል «ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ

እንዲይባል በእምነት እምቢ አለ ከግብጽም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በሐጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሄር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና የንጉሡን ቁጣ ሳይፈራ የግብጽን አገር የተወ በእምነት ነበር የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና አጥፊው የበኩሮችን ልጆች እንዲይነካ ፋሲካንና ደምን መርጨትን በእምነት አደረገ በደረቅ ምድር እንደሚያልፉ በኤርትራ ባሕር በእምነት ተሻገሩ የግብጽ ሰዎች ግን ሲሞክሩ ተዋጡ የኢያሪኮ ቅጥር ሰባት ቀን ከዞሩበት በኋላ በእምነት ወደቀ ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮችን በሰላም ስለተቀበለቻቸው ከማይታዘዙ ጋር በእምነት አልጠፋችም::»

ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ ውስጥ ከተጠቀሱት ሙሴና ረዓብ ባሻገር በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ላይ በርካታ የእምነት ሰዎች ተጠቅሰዋል የእነርሱ እምነት ምን አይነት እምነት ነበር? የእነርሱ እምነት የእግዚአብሄር አገልጋዮች ያቀረቡላቸውን ቃል በልቦቻቸው ያመኑበት እምነት ነበር ሙሴና ረዓብ በእግዚአብሄር ቃል በማመናቸው በሕይወት መኖር የእግዚአብሄርን ታላቅ ስራ ማጣጣምና ደህንነትን ማግኘት ቻሉ እኛም ደግሞ በእግዚአብሄር ቃል በልቦቻችን በማመን እውነተኛ ደህንነታችንን አግኝተናል አሁን የእግዚአብሄርን ቃል ከሙሉ ልባችን በመታመን የእምነት ሕይወታችንን በመኖር መቀጠል አለብን::

በእግዚአብሄር ቃል ላይ ባለን እምነታችን ክርስቶስን መከተል አለብን ምንም ያህል በራሳችን አስተሳሰቦች ላይ ብንደገፍም የምናተርፈው ነገር የለም አሳብ አሳብ ነው ከዚያ ያለፈ ነገር አይደለም የእምነት አበባ እንዲያብብ ማድረግ የምንችለው ከሰማያት በላይ ባለው ውሃ ማለትም በእግዚአብሄር

ቃል ስናምን ብቻ ነው እውነተኛው የእምነት ሕይወት ይህ ነው።

ባለፉት ዘመናት በእምነት የኖሩ የእምነት ቀደምቶች ከሰማያት በላይ ባለው በዚህ ውሃ በእግዚአብሄር ቃል በማመን በእግዚአብሄር ቃል መሰረት በእምነት ተመላለሱ ዮሴፍ የእስራኤል ሕዝብ ወደፊት ወደ ከንአን አገር እንደሚገቡ እርግጠኛ የነበረው በእምነት አባቶች የተሰጠውን የእግዚአብሄር ተስፋ በማመኑ ነበር በሞት አልጋ ላይ ሆኖ እነዚህን የመጨረሻ ቃሎች የተናገረው ለዚህ ነው «እኔ ብሞትም እንኳን እግዚአብሄር ወደፊት ወደ ከንአን ምድር እንድትገቡ ይፈቅድላችኋል ጊዜው ሲደርስና ከግብጽ ስትወጡ አጥንቶቼን ቆፍራችሁ በማውጣት ወደ ተስፋይቱ ምድር ይዛችሁት እንድትገቡ እርግጠኞች ሁኑ» ዮሴፍ እንዲህ የመጨረሻ ቃሎቹን የተናገረው እግዚአብሄር ለአብርሃም የተናገረውን ቃል በማመኑ ነበር ያም ቃል እግዚአብሄር ከ400 የባርነት አመታት በኋላ የእስራኤልን ሕዝብ የሚያድንና እንደገና ወደ ከንአን ምድር የሚያስገባቸው የመሆኑ ቃል ነው የእስራኤል ሕዝብም ከግብጽ ምድር ሲወጡ የዮሴፍን አጥንቶች ቆፍረው በማውጣት ከእነርሱ ጋር አብረው በመውሰድ በከንዓን ምድር ቀበሩት እምነት ማለት ይህ ነው እግዚአብሄር ስራውን የሰራው የት ነው? እርሱ ስራውን የሰራው በምድር ላይ ነው ይህ ማለት እግዚአብሄር በልቦቻችን ውስጥ ሰርቷል ማለት ነው።

በልቦቻችን ውስጥ ያለው ምንድነው? እዚያ ያለው እምነት ነው የእምነት እውነተኛ ባህርይ ምንድነው? ከሰማያት በላይ ባለው ቃል ማለትም በእግዚአብሄር ቃል ማመን ነው እምነት ማለት በግልጽ ያ ነው እምነት ማለት በሰማይ ባለው የእግዚአብሄር ቃል፣ በልቦቻችን ላይ በወረደው ቃል፣ በተሰጠን የእግዚአብሄር ቃል ከልባችን ማመን ማለት ነው ሁላችንም እምነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ማወቅ አለብን።

በልቦቻችን ውስጥ አንድ እውነተኛ ክቡር መዝገብ እንዳለ ብንናገር ያ በእግዚአብሄር ቃል ላይ ያለን ሙሉ እምነት ነው እምነት ያለው ልብ የከበረ ነው እምነት የሌለው ልብ በስጋዊ አስተሳሰቦች ብቻ የተሞላ ነው ከሰው ስጋ የወጣ ማንኛውም አሳብ አሳብ ብቻ ነው ከእውነት ቃል የወጣ ነገር አይደለም ባህር ወይም ምድር በራሳቸው ሕይወት የላቸውም ይህች ምድር ውብ አበቦችን እንድታብብ፣ ቡቃያዎችን እንድታበቅልና ፍሬዎችን የሚያፈሩ ዛፎችን እንድታወጣ የሚያደርጋት ከሰማያት በላይ ያለው ውሃ ማለትም የእውነት ቃልና የሕይወት ዘር ብቻ ነው እነዚህ ሁሉ ውብ ቡቃያዎች፣ አበቦችና ፍሬዎች የመጡት በሰማያት ባለው የእግዚአብሄር ቃል ነው።

አፈር የተሰጠውን ማንኛውንም ነገር ከመቀበል በቀር ሌላ ስራ የለውም ምድር የተዘራውን ዘር ከመቀበል በቀር ሌላ ያደረገቸወው ምንም ነገር የለም ላስተላልፍላችሁ እየሞከርሁ ያለሁት ቁምነገር በራሳችን አስተሳሰቦችና ሎጂክ የፈጠርናቸውንና በልቦቻችን ውስጥ መቀበልና በእነርሱ ማመን ትክክለኛ እምነት አለመሆኑን ነው በሰዎች አስተሳሰቦች ላይ የተገነባ እምነት በባህር ዳርቻ ላይ እንዳለ ማዕበል ወደፈትና ወደኋላ ይንጠራወዛል የጥርጥር አረፋዎችንም ይፈጥራል ይህ በሰዎች አስተሳሰቦች የተፈጠረው አንዳንድ ጊዜ አስተማማኝ ቢመስልም በሌሎች ጊዜያቶች ግን አስተማማኝ ስለማይሆን አዳላጭ ነው ሰዎች ስለሆንን ሰው ሰራሽ አስተሳሰቦቻችን ሁሌም ልክ እንደዚህ ወደኋላና ወደፊት ይዋዥቃል እንደዚያ አይደለምን? ስጋዊ አስተሳሰቦች እንደዚያ አይደሉምን? ነገር ግን ሁሉንም ነገር በእግዚአብሄር ቃል ብንመረምረው ሁሉም ነገር ግልጽ ይሆናል።

እውነተኛ እምነት ከሰው ዘር ስጋ ከሚወጡ አስተሳሰቦች ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም የእግዚአብሄር የእውነት

ቃል በምድር ላይ ሲወድቅ ሕይወትን የሚያፈራው የእውነት ዘር ያብብና ፍሬ ያፈራል ባህርና ምድር አበቦችን እንዲያወጡና ፍሬ እንዲያፈሩ የሚደርጋቸው ሐይል ምንድነው? የእግዚአብሄር የእውነት ቃል ነው።

አሁን ሁላችሁም የእግዚአብሄር ቃል በምድር ላይ እንዳበበና እንደሰራ እንደምትረዱ ተስፋ አደርጋለሁ የእግዚአብሄር የሕይወት ስራ የተገለጠው በስጋዊ አስተሳሰቦቻችን ሳይሆን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ብቻ በሚያምኑ ልቦች ውስጥ ነው እግዚአብሄር እምነታችንን የሚደግፈው ቃሉን ከእውነተኛ ልባችን ስናምን ነው ይህ ሆኖ ሳለ የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻቸው የሚያምኑ ሰዎች ያን ያህል ብዙ አይደሉም የእግዚአብሄር ቃል እውነት ነው ሐይልም አለው ቃሉ እንዲህ ይላል *«የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሄር ፊት ብርቱ ነው» (2ኛ ቆሮንቶስ 10:4)* በእግዚአብሄር ቃል የሚያምን እምነት የሰይጣንን ምሽጎች የሚያፈርስ ብርቱ መሳርያ ሆንዋል እንዲህ ያለ እምነት ያላቸው ሰዎች ከእግዚአብሄር ዘንድ የተትረፈረፉ በረከቶችን ይቀበላሉ።

ትክክለኛ እምነት የእግዚአብሄርን ቃል በስጋዊ አስተሳሰቦቻችን ለመረዳትና ለመቀበል ስንል በራሳችን ሙከራ ባጠራቀምናቸው የተሳሳቱ እምነቶች ሊበቅል አይችልም እንዲህ አይነት እምነት አንድ ጊዜ የሚያምን በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ እምነት የሌለው ሆኖ ሁሌም ልክ እንደ ማዕበል ይወዛወዛል እምነታችን ፈጽሞ ሐይማኖታዊ እምነት መሆን ብቻ የለበትም ሰው በራሱ አስተሳሰቦች ላይ በመደገፍ ፈጽሞ የእውነተኛ እምነትን አበባ ማብቀል አይችልም እግዚአብሄር በእኛ በሰዎች ስጋዊ አስተሳሰቦች እንደማይሰራ ሁላችሁም እንድትገነዘቡ እፈልጋለሁ ታዲያ እግዚአብሄር ስራውን

የሚሰራው የት ነው? እርሱ ስራውን የሚሰራው የእግዚአብሄር ቃል በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በሚያምን እምነት ነው የእግዚአብሄር ስራ በእርግጥ የሚከናወነው ከልባችን በእግዚአብሄር ስናምን ብቻ ነው እግዚአብሄር ደህንነትን የሚሰጠን፣ ልጆቹ የሚያደርገንና፣ ብዙ መንፈሳዊ ፍሬዎችን እንድናፈራ የሚፈቅድልን የእግዚአብሄር ቃል በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ባመንን ጊዜ ብቻ ነው።

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት በልቦቻችሁ ውስጥ ሰርቷል አሁንም እንኳን በዚህ የውሃና የመንፈስ ወንጌል አማካይነት በእናንተና በእኔ ልቦች ውስጥ መስራቱን ቀጥሎዋል አጋር ምዕመናኖቼ በእግዚአብሄር የምታምኑት በስጋ አስተሳሰቦቻችሁ ነው ወይስ በልባችሁ በእግዚአብሄር የምታምኑት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ነው? በውስጣችሁ በእውነት ቃል የሚያምን እምነት አለ? ሰው በእግዚአብሄር ሲያምን ሰብአዊ አስተሳሰቦቹን መተው አለበት በቀን ተቀን ሕይወታችን ስንኖር የምናስባቸውን አስተሳሰቦች መጠቀማችንን እንተው እምነታችንን በቃሉ ላይ በማኖር በእግዚአብሄር እንመን።

ከሙሉ ልባችን በእርሱ የምናምነው፣ ከልባችን እርሱን የምናመሰግነው፣ ከልባችን እርሱን የምንከተለው፣ ከሙሉ ልባችን ተማምነን ወደ እርሱ የምንጸልየውና ከልባችን የእርሱ ሰራተኞች ሆነን የምንለፋው እግዚአብሄር በልቦቻችን ውስጥ ስለሚሰራ ነው እግዚአብሄር አባቴ እንደሆነ ስለማምን በመተማመን የእምነት ጸሎቴን ማቅረብና «አባት ሆይ እባክህ ይህንን ስጠኝ» ማለት እችላለሁ።

የእግዚአብሄር ቃል በውስጣችን ይሰራል

እግዚአብሄር ራሱ እንዲህ ብሎዋል *«ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ፍሬ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል» (ዘፍጥረት 1:11)* እግዚአብሄር ራሱ የተናገረው ይህ የእውነት ቃል በምድር ላይ እንደወደቀ ማለትም ዘሩ እንደተዘራ ሁሉ ምድር ዘሩን ተቀብላ ፍሬ አፈራች ምድር ያደረገቸው ምንም ነገር የለም ምድር በራስዋ አልፈነጠዘችም ውሃ ለማጠጣትም ራስዋን መስዋዕት አላደረገችም እርስዋ ያደረገችው ነገር ቢኖር ከላይ የወረደውን ዘር መቀበልና በዙሪያው ባለው መሬት ውስጥ ያሉትን ንጥረ ነገሮች በመሰብሰብ የእውነት ዘር እንዲበቅልና እንዲያብብ ማድረግ ነው ካስተዋልን ምድርም እግዚአብሄር የፈጠራት ነች እኛ በራሳችን ያደረግነው ምንም ነገር የለም።

ስለዚህ ሰው ጥሩ ነው ብሎ ባሰበው መሰረት የእምነት ሕይወቱን ከኖረ ሁሉም ከንቱ ይሆናል «የእምነት ሕይወቱን ልክ እንደዚህ ብኖር ኖሮ አሁንም በሌሎች መገራት ይኖርብኛ ልን? ቤተክርስቲያኔን ለማስተዳደር ቀላሉ መንገድ ምንድነው? ይህ የእግዚአብሄር ቃል ከሰው መርሆዎች ጋር እንዲስማማ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት?» በማሰብ የእምነት ሕይወቱን ከኖረ እንዲህ ያለው የእምነት ሕይወት ምንም ትሩፋት አይኖረውም እንዲህ አይነት ሰዎች የእምነትን ሕይወት አልኖሩም ነገር ግን የሕይወት መንገዳቸውን በብልጣ ብልጥነት ሲመሩ ቆይተዋል በጥሩ አባባል የእነርሱ መጠይቅ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ነው እነዚህ ሰዎች የሚስማማቸውን ፍልስፍና ሲከተሉ ነበር ማንም ሰው ከልቡ በእግዚአብሄር ቃል በማመን ፋንታ በራሱ አስተሳሰቦች መሰረት መልካም የሆነውን ነገር በመከተል የእምነት ሕይወቱን ከኖረ ይህ ማለት በትክክል

የእምነት ሕይወቱን አልኖረም ነገር ግን የኖረው የሐይማኖት ሕይወትን ብቻ ነው ማለት ነው።

እግዚአብሄር በልቦቻችን ውስጥ ሰርቷል እግዚአብሄር በእናንተና በእኔ ልብ ውስጥ በመስራት የራሱ ልጆች አድርጎናል ይህ እውነት ነው ወይስ አይደለም? በእርግጥም እውነት ነው! አሁን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነናል የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው በአስተሳሰቦቻችን ነውን? የለም አይደለም ለመዳን በራሳችን አስተሳሰቦች ላይ ተደግፈን ቢሆን ኖሮ ፈጽሞ ሐጢያት አልባ ባልሆንን ነበር ምክንያቱም ይህ ልክ ነፋስን እንደ መጨበጥ ይሆን ነበር።

ታዲያ የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው እንዴት ነው? የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በደመሰሰው የእግዚአብሄር የወንጌል ቃል በማመን ነው በአስተሳሰቦቻችን ሐጢያቶችን በምንሰራበት ጊዜ ይህ ተወግዶ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ፈጽሞ እርግጠኞች አይደለንም በስጋዊ አስተሳሰቦቻችን እንዋልላለን ልቦቻችን ግን በግልጽ «ሐጢያት የለም» ብለው ይመሰክሩልናል ሙሴ፣ ኢያሱ ወይም ጋለሞታይቱም ረዓብ ቢሆኑ የእምነት ሰዎች በሙሉ ችግሮቻቸውን የፈቱት በእምነት ነው።

እኛ የእግዚአብሄርን ቃል በልባችን በማመን ትክክለኛ የእምነት ሕይወትን መኖር እንችላለን የእግዚአብሄርን ቃል በልባችን ካመንን በቃሉ ውስጥ ያለው የሕይወት ዘር ወደ ውስጣችን ገብቶ በውስጣችን ይሰራል የሕይወትንም እንቡጥ ያበቅላል ይህ ፈጽሞ ራሳችን ልናደርገው የማንችለው ነገር ነው በልቦቻችን ውስጥ እንዲህ ያለ ውበት ባይኖርም እግዚአብሄር ግን አሁንም የሚበቅሉ ውብ እንቡጦችን፣ የሚያብቡ አበቦችንና የሚያፈሩ ፍሬዎችን ያበቅላል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ውብ ስራዎችን እንድንሰራ ያደርገናል ማን በምን ይሰራል?

እግዚአብሄር በእውነት ቃል ይሰራል ያን ጊዜ የእውነት ዘር ወደ ውስጣችን ይገባል ይህ ዘር በውስጣችን ውብ ስራዎችን ይሰራል።

እውነቱ ወንጌልን ለሌሎች ነፍሳቶች እንድናሰራጭ፣ እግዚአብሄርን የማገልገል ስራ እንድንሰራ፣ በእምነትም ጌታን የመከተል ስራ እንድንሰራና ዲያብሎስን ተዋግቶ የማሸነፍን ስራ እንድንሰራ ያደርገናል እነዚህን ነገሮች እንድናደርግ የሚያስችለን እውነት ነው እኛ ብቻችንን እነዚህን ነገሮች ማድረግ አንችልም ምንም ያህል በተቃጠለ መንፈስ ብንሞክርም ፈጽሞ ልንሰራቸው አንችልም በሌላ አነጋገር በራሳችን አስተሳሰቦች ላይ ተመስርተን የእምነት ሕይወትን መኖር አንችልም ልቦቻችን እንደሚከተለው ተቃኝተው ከሆነ ፈጽሞ የደህንነትን ወንጌል መቀበል አትችሉም «በኋላ አስብበታለሁ ላስተውለው የምችል ከሆነ አምናለሁ ነገር ግን ቃሉን ከተመለከትሁና ደጋግሜ ከሰማሁት በኋላ ላስተውለው ካልቻልሁ በጭራሽ አላምንበትም ላስተውለው የምችለውን ብቻ አምናለሁ ማለቴ ነው» እንዲህ ባለ አስተሳሰብ ከታሰራችሁ በፍጥነት ልትጥሉት ይገባል።

እምነት ቀላል ነገር ነው ሰው ሊያደርገው የሚገባው ነገር ቢኖር በልቡ የእግዚአብሄርን ቃል ማሰላሰልና በቃሉ ማመን ብቻ ነው እውነትም እንደዚሁ ቀላል ነገር ነው እውነት እውነት ነው እንደዚያ ስላሰብን ብቻ ውሸት አይሆንም ዋጋውም በአስተሳሰቦቻችን አይደገፍም እውነት ስለተቀበልነው ብቻ እውነት አይሆንም ስላልተቀበልነውም ውሸት አይሆንም እውነት እውነት ነው እውነት ፈጽሞ የማይለወጥ ነገር ነው።

ሰብአዊ አስተሳሰቦች፡ የእምነት ሕይወት እንቅፋቶች

እግዚአብሄር በፍጥረት ስራ አማካይነት በእኛ በሰዎች ላይ

ሊሰራው የፈለገውን ስራ ገልጦዋል እግዚአብሄር በመጀመሪያው ቀን ስለ ደህንነት ስራ ተናገረ በሁለተኛው ቀን ስለ መለየት ስራ ተናገረ በሶስተኛው ቀን ሰው እንዴት የእምነት ሰው እንደሚሆን ተናገረ ሆኖም እምነታቸው ሦስተኛው ቀን ላይ ያልደረሰ ብዙ ሰዎች አሉ እነርሱ የእግዚአብሄር አገልጋዮች ይሆኑ ዘንድ በሦስተኛው የፍጥረት ቀን የተሰራውን ይህንን የእግዚአብሄር ስራ መቀበል ይኖርባቸዋል እግዚአብሄር በአራተኛው ቀን የሰማይ ክዋክብቶችን ፈጠረ ከዚያም በአምስተኛው ቀን በእርካታ መብረር፣ በእምነት ከውሃ በታች መዋኘት፣ በእምነት በሁሉም ላይ መንገስና፣ ሁሉንም ነገር በሙላቱ ማጣጣም ታወቀ::

የሶስተኛው ቀን ስራ በልቦቻችን ውስጥ እንዳይተገበር እጅግ ትልቁ እንቅፋት ምንድነው? ስጋዊ አስተሳሰቦቻችን ናቸው ብዙ ሰዎች የእምነት ሕይወታቸውን እየኖሩ ያሉት በራሳቸው የስጋ አስተሳሰቦች ነው ነገሩ እንደዚያ ስለሆነ የሰው የእምነት ሕይወት የአስተሳሰቦቹ ውጤት ነው በሰው አስተሳሰቦች ላይ ያልተመሰረተ የእምነት ሕይወት አይደፋፈርም ሰው «ወዮ! ይህ ትክክል ይመስላል ስለዚህ እንመንበት እኔ አምናለሁ» ብሎ በማሰብ ምንም ያህል ቃል ቢገባ ይህ እምነት በእግዚአብሄር ቃል ላይ ካልተመሰረተ የሆነ መከራ ሲመጣ ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ በንኖ ይጠፋል እምነቱም ይሞታል::

ለምሳሌ ማዕበል የቀላቀለ አውሎ ነፋስ በባህር ዳርቻ ላይ ሲከሰት በባህሩ ዳርቻ አካባቢዎች ጥፋትን ያመጣል በአንድ ጊዜ ሁሉንም እንደሚጠራርግ አውሎ ነፋስ በባህሩ ዳርቻ ያሉትን ቤቶች በጎርፍ ያጥለቀልቃቸዋል የባህር ዳርቻውንና የውሃ መከላከያውንም ዱካ ሳይተው ጠራርጎ ይወስደዋል እምነትን የሚበሉት የስጋ አስተሳሰቦች ናቸው ሰው ስለስጋው አብዝቶ ባሰበ ቁጥር እምነቱም እንደዚያው ይከስማል በጊዜ ሒደት

ውስጥም እምነቱ አንድም ፍንጭ ሳይተው ሙሉ በሙሉ ይከስማል ሰው አብዝቶ ወደ ራሱ የስጋ አስተሳሰቦች ሲሳብ አስቀድሞ ያመነባቸውንም ነገሮች ይተዋቸዋል ውሎ አድሮም የቀረች ትንሽ እምነት ብትኖርም ሙሉ በሙሉ ተጠርጋ ትጠፋለች።

ሁለት አይነት ሰዎች አሉ እነርሱም ቃሉን ከልባቸው የሚያምኑ ሰዎችና ጥሩ መስሎ በሚታያቸው መልኩ መሰረት የእምነት ሕይወታቸውን የሚመሩ ሰዎች ናቸው የእምነት ሕይወታቸውን በራሳቸው አስተሳሰቦች በመምራት የሚቀጥሉ ሰዎች እግዚአብሄር በሦስተኛው ቀን የት እንደሰራ አያውቁም አጋር ምዕመናኖቼ የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ማመን አለብን በልባችንም ልናሰላስለውና በልባችንም ልናምነው ይገባናል ማመን የሚገባን በልቦቻችን ነው መከተል የሚገባንም እንዲሁ በልቦቻችን ነው የእግዚአብሄር ስራ የሚገለጠው ያን ጊዜ ብቻ ነው።

የእግዚአብሄርን ቃል በራሳቸው አስተሳሰቦች ደረጃ ብቻ የሚወስዱና በልቦቻቸው የማያምኑት ሰዎች ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ «የዚያ ምንባብ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ያ አይደለም...ዛሬ እየተናገረ ያለው ስለ እምነት ነው ምንባቡ ልክ እንደዚያ ሊተረጎም ይችላል» ብለው ለራሳቸው በማሰብ አንድ የታሪክ ንግግር የሚያደምጡ ይመስል ያደምጡታል።

እኔ አሁን እየተናገርሁ ያለሁት ስለ ታሪክ አይደለም «የሙሴ ዘመን በሆኑ የአመተ አለም ዘመናቶች ውስጥ ነበርበዚያ ዘመን የነበረው ባህልም እንዲህና እንዲያ ነበር በዚያ ባህል ውስጥ ሙሴ እንዲህና እንዲያ ባሉ መንገዶች የእስራኤል ሕዝብ መሪ ሆነ ያም ታላቅ ነገር ነበር ሁላችንም ሙሴን እንምሰል» እያልሁ አይደለም ይልቁኑ ለእናንተ እየተናገርሁ ያለሁት የእግዚአብሄር ሕዝቦች እምነት ሙሴ የነበረው እምነት

ቢሆን፣ ረዓብ የነበራት እምነት ቢሆን ወይም ኢያሱ የነበረው እምነት ቢሆን የተመሰረተው የየሖዉን ቃል በልባቸው በማመናቸው ላይ ነበር እግዚአብሄር የእምነት ክልል ይህ ነው ይላል::

ይህንን ስብከት ስትሰሙ ካስተዋላችሁት በኋላ ልትቀበሉት የምትሞክሩ ከሆነ ልታደርጉ የሚኖርባችሁ ነገር ቢኖር መመርመር ነው የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ካስተዋላችሁት በኋላ የምትቀበሉበት የላቀ እውቀት አላችሁን? ቃሉን ለማስተዋል ለግላችሁ ለመገምገምና ከዚያም በራሳችሁ አስተሳሰቦች ከመቀበል ሞክራችሁ ቢሆን ኖሮ በጣም ይረፍድባችሁ ነበር አሁን የተነገረውን ነገር ማስተዋል የምትችሉት ከ10 አመታት በኋላ ምናልባትም ከ20 አመታት በኋላ ብቻ ሊሆን ይችላል «ወይ ጉድ ያን ጊዜ መጋቢ ቻንግ እንዲህ ያለው ለካ ለዚህ ነው» ብላችሁ ለመናገር 20 አመታቶች ይወስድባችሁ ይሆናል ምናልባትም የእምነት ሕይወታችሁን በራሳችሁ አስተሳሰቦች ላይ ተመስርታችሁ በመኖር ቀጥላችሁት ከሆነ ይህ ግንዛቤ 20 አመታቶች ካለፉ በኋላም እንኳን ላይመጣ ይችላል ምናልባትም እንዲህ ላለው መረዳት ከመንቃታችሁ በፊት ሞታችሁ ሊሆን ይችላል አስተሳሰቦቻችሁ ጠላቶቻችሁ ናቸው::

የእምነት ሕይወታችንን ስንኖር በልባችን ውስጥ ባለው እምነት ስለ እግዚአብሄር ቃል ማሰቡ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በራሳችን ስጋዊ አስተሳሰቦች የእግዚአብሄርን ቃል የምንኮንን፣ እምነታችንን የምንንከባከብና ዕጣ ፈንታችንን የምናቅድ ከሆነ የራሳችን አስተሳሰቦች ጠላት ይሆኑብናል የእምነት ሕይወታችንን በራሳችን አስተሳሰቦች መኖር የለብንም እግዚአብሄር በነገረን ማመን አለብን ሰው በራሱ አስተሳሰቦች ቃሉን ለመረዳትና አርቆ ለማቀድ በመሞከር የሚሞክርበት በአስተሳሰቦቹ የተመራ የእምነት ሕይወት የእምነት ሕይወት አይደለም::

እግዚአብሄር የሚሰራው የት ነው?

እግዚአብሄር በሦስተኛው ቀን ምድር ዘርን የሚሰጥ ቡቃያና እንደ ወገኑም ፍሬን የሚያፈራ የፍሬ ዛፍ እንድትሰጥ አዘዘ እግዚአብሄር ይህንን የተናገረው ለባህር አይደለም ለእኛ ሁለተኛው የእግዚአብሄር ፍጥረት ቀን አልፎዋል ሁለተኛውም ቀን እንደዚሁ አልፎዋል ከጠፈር በላይ ያለው ውሃም በዚህ ምድር ላይ ካለው ውሃ ተለይቷል አሁን የእግዚአብሄር ቃል ምን እንደሆነና የዲያብሎስ ቃሎች ምን እንደሆኑ ታውቃላችሁን?

አሁን ከሦስተኛው ቀን ጋር ተገናኝተናል ሁለተኛው ቀን ሲያልፍ ሦስተኛው ቀን በእርግጠኝነት ይመጣል በእርግጥም ሦስተኛው ቀን አስቀድሞ መጥቶልናል በሦስተኛው ቀን ሁለት ክስተቶች ሆነዋል እግዚአብሄር ምድርን የሸፈኑትን ውሃዎች በአንድ ስፍራ ሰብስቦ ባህሮች ብሎ ጠራቸው የብሱንም ምድር ብሎ ጠራው ይህም እግዚአብሄር ባህሮችን ከምድር ፈጽሞ ለይቶዋቸዋል ማለት ነው በተከፈሉት በሁለቱ መካከል እግዚአብሄር ስራውን የሰራው በየትኛው ነው የሰራው በምድር ነው እግዚአብሄር *«ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል» (ዘፍጥረት 1:11)* ብሎ የተናገረው ለምድር ነው እግዚአብሄር በምድር ላይ ዘርን ዘራ በምድር አማካይነትም ፍሬዎችን አበቀለ እንዲህ በማድረግም ክብሩን ገለጠ እግዚአብሄር ያ መልካም እንደሆነ አየ የተባለው ለዚህ ነበር።

ታዲያ እግዚአብሄር በእኛ የሰራው እንዴት ነው? እርሱ በልቦቻችን ውስጥ ሰራ እርሱ በሚያምኑ ሰዎች ልቦች ውስጥ ስራውን ሰራ እኛም በእምነት ደህንነታችንን ተቀበልን በእምነትም የእግዚአብሄር ልጆች ሆንን በእምነትም ከፍርድ

ዳንን እግዚአብሄርንም በእምነት አባታችን ብለን እንጠራዋለን በእምነትም የእምነት ሕይወታችንን በመኖር እንቀጥላለን ሁሉም ነገር የሚከናወነው በእምነት ነው።

ነገር ግን እኛ ልናውቀው የሚገባን ነገር ቢኖር እስከ አሁን ድረስ ገና ሶስተኛውን ቀን ያላለፉ አንዳንድ ወንድሞችና እህቶች አንዳንድ የእግዚአብሄር አገልጋዮችም ያሉ መሆናቸውን ነው እነርሱ አሁንም እንኳን በራሳቸው አስተሳሰቦች የእግዚአብሄርን ቃል ይዳኛሉ የእግዚአብሄር ቃል የእምነትና የእውነት መሳሪያ እንጂ የእኛ ብያኔና ትንተና መሳሪያ አይደለም የእግዚአብሄርን ቃል በራሳችን ሰብአዊ አእምሮ ምንም ያህል ብንተነትነው በውስጡ ምንም ስህተት ልናገኝበት አንችልም ስለዚህ ይህንን ከንቱ የሆነ ሙከራ ለራሳችን መረዳት ትተን በልባችን ማመን መጀመር አለብን እኛ እግዚአብሄር ተስፋ በሰጠንና ባጠናቀቀው ቃል ሁሉ ማመን አለብን የቀሩትንም ተስፋዎች በሙሉ ያለ ጥርጥር እንደሚፈጽምልንም ማመን አለብን።

እስከ አሁን ድረስ የእምነት ሕይወታችሁን ኖራችኋልን? የእግዚአብሄርን ቃል ስትሰሙ ወይም መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ ልታስተውሉት፣ ልታምኑትና ልትቀበሉት ስላልቻላችሁ በመጨረሻ እስክታስተውሉት ድረስ ይዛችሁት ትቆያላችሁን?

ቢሮ ስንገባ «የተወሰኑ» «ያልተወሰኑ» እና «ውሳኔ የሚጠብቁ» የሚሉ የፋይል ማስቀመጫዎች ከፍተኛ ስልጣን ባለው ሰው ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠው እናያለን «የተወሰነ» የሚለው የፋይል ማቀመጫ የያዘው ምንድነው? የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጣቸውን ሰነዶች የያዘ ነው «ያልተወሰነ» የሚለው የፋይል ማስቀመጫስ? ገና ምንም ውሳኔ ያልተሰጣቸውን ሰነዶች የያዘ ነው «ውሳኔ የሚጠብቅ» የሚሉ ፋይሎችን የያዘው ማስቀመጫ በሚገባ የተመረመሩ ነገር ግን ገና የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጣቸውን ጉዳዮች የያዘ ነው።

የሰውን እምነትም የተወሰነ ያልተወሰነና ውሳኔ የሚጠብቅ ብለን ልንገልጠው እንችላለን ከእነዚህ የተለያዩ የእምነት አይነቶች መካከል እግዚአብሄር አብዝቶ የሚጠለሳው ውሳኔ የሚጠብቀውን እምነት ነው ውሳኔ የሚጠብቅ እምነት ትኩስም ሆነ በራድ ያልሆነ ነገር ግን ለብ ያለና የሚዋልል እምነት ነው ቃሉ እውነት ቢሆንም ሰው ግን ከአስተሳሰቦቹ ጋር ባለመስማማቱ ምክንያት ለጊዜው ያስቀምጠውና ከአስተሳሰቦቹ ጋር በሚስማማበት ጊዜ ወደ በኋላ ያምንበታል ሰው የእምነት ሕይወቱን እንዲህ ላልተወሰነ ጊዜ የሚያስቀምጠው ከሆነ ይህ በእግዚአብሄር አመለካከት ግራ የሚያጋባና ፈጽሞ የማይጨበጥ አይመስልምን?

ምናልባት እግዚአብሄር «ሄይ! ቃሌን በራስህ መንገድ ለመበየን ልታስተውለው ከቻልህ ልታምንበት ካልቻልህ ደግሞ ላታምንበት ያን ያህል ብልህ ነህ እንዴ? ታዲያ እንዴት ነው ያዳንሁህ? ደህንነትን የተቀበልከው ስላስተዋልከው ነውን? ሔይ! ደህንነትን በጸጋ ብትቀበልም ሕይወትህን ፈጽመህ በራስህ አስተሳሰቦች ለመኖር እየሞከርህ ነው የእምነት ሕይወትህን በራስህ መረዳት ብቻ ለመኖር እየሞከርህ ነው» ይል ይሆናል።

ይህ እምነት ተብሎ የሚጠራው ነገር ማስተዋልን አይቀበልም እምነት ተስፋ የሚደረገውን ነገር የሚያስረግጥ የማይታየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ባለፉት ዘመናት የእምነት ሽማግሌዎች እግዚአብሄር ይህንን መላውን አለም እንደፈጠረ ያወቁት የእግዚአብሄርን ፍጥረት እያንዳንዱን ገጽታ ስለተረዱ ሳይሆን በእግዚአብሄር ቃል ስላመኑ እንደሆነ ይናገራል። (ዕብራውያን 11:1-3)

አጋር ምዕመናኖቹ እግዚአብሄር ይህንን አለም በቃሉ በፈጠረ ጊዜ እዚያ ነበርን? አይተነዋል? እግዚአብሄር ባህሮችን ሲፈጥር ተመልክተናል? እግዚአብሄር ምድርን ሰውን

አያቶቻችንንና አባቶቻችንን ሲፈጥር አይተናል? የለም ማናቸውንም አላየንም ታዲያ እግዚአብሄር መላውን ዩኒቨርስና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር እንደፈጠረ የምናውቀው እንዴት ነው? ይህንን የምናውቀው በእምነት ነው እያልሁ ነው::

እግዚአብሄር በመጀመሪያ መላውን ዩኒቨርስ ፈጠረ ይህንን እውነታ የምናውቀው እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ በሚለው የእግዚአብሄር ቃል በማመን ነው ደህንነትንም የተቀበልነው በእምነት ነው እግዚአብሄር እረኛችን መሆኑን ያወቅነውም እንዲሁ በእምነት ነው ሁሉም ነገር የሆነው በእምነት ነው ሰማይ መሄድም እንደዚሁ በእምነት የሚከናወን ነገር ነው::

ውሳኔ የሚጠብቅ እምነት አስፈሪ ጠላት ነው

ውሳኔ የሚጠብቅ እምነት ለእምነታችን እጅግ አስፈሪው ጠላት ነው ያልወሰነ እምነት በእርግጥም ያሉት ችግሮች በጣም ጥቂቶች ናቸው ይህ ገና ከቃሉ ጋር ባልተገናኙ ሰዎች የተያዘ እምነት ስለሆነ ሰው ማድረግ የሚገባው ነገር ቢኖር የእውነትን ቃል ለእነርሱ መናገርና እነርሱን መምራት ነው ነገር ግን ውሳኔ የሚጠብቅ እምነትን በሚመለከት የመጨረሻው ውሳኔ መቼ እንደሚሰጥ ማንም አያውቅም የአለምን ነገሮች ልናዘገያቸው እንችላለን ነገር ግን ውሳኔ ያልተሰጠውን እምነት በግትርነት በመቀበል መክሰር አያስፈልገንም በእግዚአብሄር ቃል በማመን ብሩክ በሆነው ብርሃን ውስጥ መግባት ለእኛ በእጅጉ የተሻለና በእጅጉም ብልህነት ነው ሰው የእግዚአብሄርን ቃል የእውቀት ጉዳይ አድርጎ ተቀብሎት ከሆነና በተጋረዱት

አስተሳሰቦቹ ውስጥ ቀብሮት ከሆነ በእርግጥም ሞኝነት ይሆናል ትበሉት ዘንድ የሚጣፍጥ ምግብ ቀርቦላችሁ ተርባችሁ ሳለ ዝም ብላችሁ ብትመለከቱትና ባትበሉት ነገሩ ሁሉ ሰማይ ላይ የተንጠለጠለ ዳቦ ሆኖ ይቀራል ውሳኔ ያላገኘ እምነትም ልክ እንደዚያ ነው።

ዳግም ለተወለዱ ሰዎች እጅግ ትልቁ እንቅፋት እግዚአብሄር በሶስተኛው የፍጥረት ቀን በምድር ላይ እንደሰራ የሚሰራው በእኛ ልቦች ውስጥ የመሆኑን እውነታ ሳያምኑ እግዚአብሄር በአስተሳሰቦቻቸው ውስጥ እንዲሰራ መፈለጋቸው ነው ይህ ስህተት ነው እግዚአብሄር ሲሰራ የሚሰራው በምድር ላይ በሰዎች ልቦች ውስጥ መሆኑ ተጽፎዋል እርሱ «ለዘላለም በልቦቻችሁ ውስጥ መስራቴን እቀጥላለሁ» በማለት የሚሰራበትን ሕግ ደንግጎዋል።

ነገር ግን ብዙ ሰዎች አሁንም ድረስ የሆነ የማይታመን ነገር ይጠብቃሉ የእምነት ሕይወታቸውን በራሳቸው አስተሳሰቦች መሰረት ለመምራት የሚሞክሩ ሰዎች «ባህርም ውሃ ነው እግዚአብሄር በባህር ላይም ደግሞ መስራት አለበት ጭንቅላቱ የተዘጋ ይመስላል ይህንን መረዳቱ በጣም አስቸጋሪ ነው» ብለው ስለሚያስቡ አስተሳሰቦቻቸው በሙሉ ግራ ተጋብተዋል የባህር ማዕበሎች ሁሌም በባህሩ ዳርቻ ላይ እንደሚረጩ ሁሉ እነርሱም በቃሉ ፊት ሲቆሙ ፈጥነው በራሳቸው እሳቤ አስቀድመው ለመረዳት ይሞክራሉ የእግዚአብሄር ቃል በቀላሉ ሊታመን የሚገባ ነገር ነው።

እግር ኳስ በምንጫወትበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ግልጽ ነው የማን ቡድን ተጫዋች እንደሆንን ካወቀን በኋላ የእኛ ወገን ለሆኑ ተጫዋቾች ኳሱን ማቀበልና ኳሱን ወደ ሌላው ቡድን ግብ መምታት እንደሚገባን በደመ ነፍስ እናውቃለን ኳሱን ስንመታ «ኳሱን ለማን ላቀብል» ብለን

በማሰብ ጊዜ አናባክንም ለየትኛው ወገን እንደምጫወት በግልጽ ስለማውቅ ጨዋታውን በላቀ ጽናት መጫወት እችላለሁ ነገር ግን ይህንን መሰረታዊ ሕግ ባላውቅ ማለትም በዚህ ቡድን ውስጥ ወይም በዚያ ቡድን ውስጥ ስለመሆኔ እርግጠኛ ባልሆን በእርግጠኝነት በራሴ ቡድን ላይ ጎል አስቆጥራለሁ።

የእግዚአብሄር ቃል ሰው ልክ እንደ ሕጻን ልጅ ሊያምነው የሚገባው ነገር ነው እምነታችንን በእግዚአብሄር ቃል ከማኖር ብናነሳ ይህ የእግዚአብሄር ቃል የእኛ አይሆንም ነገር ግን በእምነት ብንቀበለው የእግዚአብሄር ቃል የእኛ ይሆናል ይህ ሆኖ እያለ ብዙዎቻችሁ እምነታችሁን በሙሉ በእግዚአብሄር ቃል ላይ የማኖር የመጨረሻ ውሳኔያችሁን ለማዘግየት በምታደርጉት ቁጥብነት ምክንያት ብዙ ኪሳራ እንደሚገጥማችሁ አትገነዘቡም አጋር ምዕመናኖቼ እኔም ባለፈው ዘመን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሄር ቃል ላይ የመታመንን የእምነት ከፍታ ለመውጣት ፈቃደኛ ባለመሆኔ ልክ እንደ እናንተ ነበርሁ።

ሰዎች የእግዚአብሄርን ቃል ደግመው ደጋግመው በአስተሳሰቦቻቸው ለመረዳት ይሞክራሉ በዮሐንስ ምዕራፍ 13 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የጴጥሮስን እግሮች ሲያጥብ የተመለከተ ሰው «በዚያን ዘመን ሰዎች የሰንደል ጫማዎችን ያደርጉ ነበር እግሮቻቸው አቧራን ስለሚቅሙ በየቀኑ መታጠብ ነበረባቸው ይህ ክስተት የሆነው ለዚህ ይመስለኛል» ብሎ ያስብ ይሆናል በእርግጥ ይህ እሳቤ 100 በመቶ ከእውነት የራቀ አይደለም ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የጴጥሮስን እግሮች ያጠበው ለዚያ አይደለም እነዚህ ሰዎች ቃሉን ሲሰሙ ብዙ ስለሚያስቡ «ያንን የእግዚአብሄር አገልጋይ ላምነው እችላለሁ? አሁን ያ ሰው ምን እያለ ነው? አሁን እሰማዋለው የምሰማው ግን አንድ ጊዜ ብቻ ነው» የሚሉ ይመስል እጆቻቸውን አጣምረው መስማታቸውን ይቀጥላሉ።

እግዚአብሄር አገልጋይ የሚሰብከው የራሱን ቃሎች ሳይሆን የእግዚአብሄርን ቃል መሆኑን ካወቅን በኋላ ቃሉን በልቦቻችን ማድመጥ አለብን ነገር ግን በብዙ ሰዎች ልቦች ውስጥ በእምነት የሚኖር ምንም ነገር የሌለው እየሰሙት ያለው ነገር በእርግጥ የእግዚአብሄር ቃል መሆናቸውን ወይም የሌላ ሰው ቃሎች መሆናቸውን ሳይለዩ ስለሚያደምጡ ነው እነዚህ ሰዎች ስብከቶቹን አዳምጠው ቢሆን ኖሮ «ስለ እግር ኳስ ጨዋታ ሲናገር ተመልከቱት! የሚናገረው ሁሉ ስለራሱ ነው?» ይሉ ይሆናል።

በዚህ ሰዓት የተነገረውም የእግር ኳስ ጨዋታ ታሪክም ቢሆን ከእግዚአብሄር ቃል የተነገረ መሆኑ እውነት ነው እንደዚያ አይደለምን? ነገር ግን በራሳቸው አስተሳሰቦች ላይ ተመስርተው የእምነት ሕይወታቸውን የሚኖሩ ሰዎች ቃሉን በሚሰሙበት ጊዜ አቃቂር ማውጣትና መምረጥ ይወዳሉ በራሳቸው መንገድም አንዳንዱ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነና ሌላው የእግዚአብሄር ቃል እንዳልሆነ ይወስናሉ ብዙዎቹ ቃሉን ሙሉ በሙሉ ለማመን እምቢተኛ በመሆን የሚዘገዩት ቃሉን ልክ እንደዚህ አቃቂር ስለሚያወጡለት ነው ውሳኔያቸውን ስለሚያዘገዩትም እምነት በውስጣቸው ስር ሰድዶ አያድግም ሌሎች ሰዎች ሁሌም ፈጥነው በእምነት ያድጋሉ ነገር ግን ስለ እድገታቸው ብዙ አሳቦች ያሉባቸው ሰዎች ፈጽሞ ምንም እድገት አያዩም እንደዚያም ቢሆን ልክ ገንፎን ከሳህን ውስጥ ለመጨለፍ የመሞከርን ያህል እምነታቸው እንዲህ ከፍተኛ ችግር ከደረሰበት በኋላ ትንሽ ያድጋል።

የእግዚአብሄር ቃል በሰዎች ልቦች ውስጥ ይሰራል እኛ በዚህ እውነት ማመን አለብን «ውድ አምላክ መንገዱ ይህ ይመስለኛል እግዚአብሄር ሆይ ምን ይመስልሃል?» ብላችሁት ከሆነ «ኦ እንደዚያ ነው? እንግዲያውስ እኔን እርሳኝ! ሁሉንም

አውቃለሁ ብለህ ስለምታስብ ማድረግ የምትፈልገውን ሁሉ አድርግ አሁን ሁሉን አድራጊው አንተ ነህ» ብሎ ይመልስላችኋል።

እግዚአብሄር በልባችን አማካይነት ከእኛ ጋር መገናኘት ይፈልጋል በልባችን ውስጥም ፍቅርን መጋራትና አብሮን መጫወት ይሻል አበባው እንዲያብብ ይፈልጋል እግዚአብሄር መሬት ውስጥ ገብቶ በዚህ ደረቅ መሬት ላይ አበቦችን፣ ቡቃዮችንና የፍሬ ዛፎችን ሊተክልና ምስጢራዊ የሆኑትን መንገዶቹን ሊያሳየን ይፈልጋል።

እግዚአብሄር በልቦቻችን ውስጥ እውነተኛውን ወንጌል መትከልና በእኛ አማካይነትም የወንጌልን አበቦች እንዲያብቡና መንፈሳዊ ፍሬዎችም እንዲበቅሉ ማድረግ ይፈልጋል ይህንን ማወቅ አለባችሁ ገባችሁ? በራሳችሁ አስተሳሰቦች የኖራችሁበትን ያለፈውን የእምነት ሕይወታችሁን ማውገዝ አለባችሁ ለመቶ ቀናቶች ያህል እንኳን ብታስቡ ከእርሱ የሚወጣ ምንም ነገር የለም ጊዜንና ጉልበትን ከማባከን በቀር የሚተርፍ ምንም ነገር የለም።

በእግዚአብሄር ቃል የሚያምኑ የእምነት ሰዎች

የእምነት ሕይወታችንን በሚያምን ልብ ልንኖር ይገባናል በዕብራውያን ውስጥ በእምነት የኖሩትን እነዚህን ሰዎች ሁሉ ተመልከቱ ከእነርሱ አንዱዋ የሆነችው ጋለሞታይቱ ረዓብ «ቀይባህርን የተሻገሩት የእስራኤል ሕዝቦች የሆዋ ተብሎ የሚጠራ መለኮታዊ አምላክ አላቸው እግዚአብሄር ከእነርሱ ጋር በመሆኑ በአስር ሺህዎች ከሚቆጠረው የግብጻውያን ሰራዊት ዳኑ ይህ የሆዋ ተብሎ የሚጠራው አምላክ ሁሉንም ባህር

ውስጥ በማስጠም የግብጻውያንን ሰራዊት በሙሉ አጠፋቸው እንዲህ ያለ ታላቅ መለኮታዊ አምላክ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር አብሮ አለ» የሚል ወሬ ሰማች።

ጋለሞታይቱ መጻተኛ ብትሆንም «በእርግጥ እንዲህ ያለ መለኮታዊ አምላክ ካለ እኔም አምናለሁ የእስራኤልን ሕዝብ ያዳነውን መለኮታዊ አምላክ የራሴ አምላክ አድርጌ አምነዋለሁ» በማለት በልብዋ አመነች ውሎ አድሮም ጊዜው ሲደርስ የእስራኤል ሕዝብ ሰላዮች ረዓብ ወደ ምትኖርበት በከንዓን ምድር ወዳለችው ወደ ኢያሪኮ መጡ።

የታሪክ ምሁራኖች የኢያሪኮ ከተማ ቅጥሮች በጣም ሰፊና ጠንካራ ስለነበሩ ሁለት 8 ቶን የሚመዝኑ ከባድ የጭነት መኪናዎች በቅጥሮቹ ላይ ሊመላለሱ ይችሉ እንደነበር ይናገራሉ ቅጥሮቹ በውስጥና በውጭ በሁለት መደቦች የተሰሩ ስለነበሩ በጣም ሰፊ እንደነበሩ ይነገራል ስለዚህ ቅጥሮቹ ለመከላከያነት የተመቹ ነበሩ በሰው አስተሳሰብ እነዚህ ቅጥሮች ፈጽሞ ሊፈርሱ አይችሉም በዚያን ዘመን አንዲት ከተማ ስትጠቃ ወራሪው ሰራዊት የከተማይቱን በሮች ሰብረው ወደ ከተማይቱ ከመግባት ትላልቅ የሚያፈርሱ ግንዶችን ይጠቀሙ ነበር ነገር ግን የኢያሪኮ በሮች በጣም ጠንካራ ቅጥሮቹም በጣም ብርቱዎች ስለነበሩ የኢያሪኮ ከተማ ልትደፈር አትችልም የትኛውም ጦር ጥሶ ሊገባባት አይችልም ተብሎ በስፋት ይታመን ነበር በቅጥሮቹ ላይ ረዓብ የምትባል ጋለሞታ ሴት መሸታ ቤት ነበራት ረዓብ በእነዚያ ቅጥሮች ጫፍ ላይ መሸታ ቤት ሰርታ ነበር ቤተሰብዋም የወይን ጠጅ እየሸጠ ኑሮውን ይገፋ ነበር።

ሆኖም የእስራኤል ሕዝብ አምላክ ስለሆነው የሆዋ የሰማችው ይህች ረዓብ «እግዚአብሄር እንደዚያ ከሆነ እኔም ደግሞ በእግዚአብሄር አምናለሁ» በማለት በልብዋ በእግዚአብሄር አመነች ሰላዮች ሲመጡም በዚህ እምነት ደበቀቻቸው እነዚህ

ሰላዮች ወደ እርስዋ መሸታ ቤት መጡ ለመሰለል ሲሉም እየጠጡ ሳለ ሰዎች ምን ይሉ እንደነበር ሲያዳምጡ ነበር ጋለሞታይቱ ረዓብ ግን እስራኤሎች እንደነበሩ አውቃለች በረዓብ መሸታ ቤት ውስጥ የነበረ ሌላ ሰውም እንደዚሁ ወደ ከተማው ፀጉረ ልውጥ ሰዎች እንደገቡ አውቆ ይህንን ለንጉሱ ሊያስታውቅ ሄደ በመሐል ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮቹን ወስዳ ደበቀቻቸው::

እየደበቀቻቸው ሳለ «እናንተ የእስራኤል ሕዝብ ናችሁ?» ብላ ጠየቀቻቸው::

«አዎ ነን::»

«ስለ አምላካችሁ የሆዋ ወሬ ሰምቻለሁ ይህ አምላክ ሕዝቡን ከቀይ ባህር ያዳነ አምላክ እንደሆነ ሰምቻለሁ ይህ እውነት ነውን?»

«እውነት ነው::»

«ያ እውነት ከሆነና እግዚአብሄር ይህችን ከተማ ለመውሰድ የሚፈልግ ከሆነ ይህች ከተማ ትወድቃለች እንደዚያ ከሆነ አንድ ቅድመ ሁኔታ አለኝ እኔ እደብቃችኋለሁ ነገር ግን ሕዝባችሁ ይህችን ከተማ ሲወስድ እኔንና ቤተሰቤን እንድታድኑ እፈልጋለሁ» ያን ጊዜ ሰላዮቹ ቤተሰቦችዋን እንደሚያድኑላት ከእርስዋ ጋር ስምምነት አደረጉ::

ረዓብ በጣሪያ ላይ ካሰቀመጠችው የተልባ እግር ስር ደበቀቻቸውና እንዴት በሰላም ማምለጥ እንደሚችሉ በዝርዝር ነገረቻቸው ጋለሞታይቱ ረዓብ በየሆዋ አምላክ በመታመን ሰላዮቹን ሸኘቻቸው የእስራኤል ሕዝብ ለወረራ ሲመጣ ጋለሞታይቱ ረዓብ በስምምነቱ መሰረት ከመስኮትዋ በስተ ውጭ ቀይ ጥብጣብ አሰረች መጽሐፍ ቅዱስ ኢያሱ «ቀይ ጥብጣብ በለበት ቤት ውስጥ ካለው ቤት አንድም ሰው እንዳትገድሉ» ብሎ ባወጣው ትዕዛዝ መሰረት የረዓብ ቤተሰቦች በሙሉ ተረፉ::

የረዓብ ድርጊት ምን አይነት ድርጊት ነበር? በራስዋ አስተሳሰብ ያደረገችው አንዳች ነገር ነበር? የለም አልነበረም በእምነት የተደረገ ነገር ነበር የረዓብ አስተሳሰቦች ልክ እንደ ማዕበል ተረጭተው ምን ማድረግ እንደሚገባት እርግጠኛ ሳትሆን ቀርታ ቢሆንም እምነት ግን ነበራት የእስራኤልን ሕዝብ ከቀይ ባህር ያዳነው እውነተኛው መለኮታዊ አምላክ የሆዋ እግዚአብሄር እንደሆነ የሚያምን እምነት ባይኖራት ኖሮ ማለትም በልብዋ በእግዚአብሄር አምና ባይሆን ኖሮ እነዚህን ድርጊቶች ማድረግ ባልቻለችም ነበር።

ጋለሞታይቱ ረዓብ የዳነችበት እምነት እያንዳንዱ ሰው ሐጢያቶቻችንን ለመውሰድ ሲል በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም (ቀይ ማግ) በማመን ደህንነቱን እንዲያገኝ የሚፈቅድለት ያው አይነት እምነት ነው እኛም ብንሆን ደህንነታችንን ያገኘነው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በሚያምነው እምነት ነው።

ሙሴም እንኳን የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ያወጣው በእምነት ነበር እርሱም ከእግዚአብሄር ሕዝቦች አንዱ የሆነው በዚህ እምነት ነበር ሙሴ ንጉስ የሚያደርጉትን መብቶች እንደማይረቡ ነገሮች ቆጥሮ ጣላቸው «እኔ የአንዲት አገር መስፍን አይደለሁም በፋንታው እኔ የእግዚአብሄር ሕዝብ ወገንና የነገስታት ንጉስ ልጅ ነኝ እኔ የዚህ አለም መስፍን አይደለሁም በፋንታው የእግዚአብሄር መንግስት መስፍን ነኝ» ብሎ አመነ እርሱ እንዲህ አይነት እምነት ስለነበረው የንጉስነትን ስልጣንና ክብር መጣል ቻለ።

አጋር ምዕመናኖቼ ይህ ሙሴ በልቡ በእግዚአብሄር ቃል ስላመነና ለአባቶቹ በተነገረው የእግዚአብሄር ቃል ስላመነ የእስራኤልን ሕዝብ ደስታና ሐዘን መካፈልና ከእነርሱም ጋር አብሮ መኖር ቻለ ይህ ሁሉ የሆነው በልቡ በማመኑ ነበር

እግዚአብሄር በእምነት ሰዎች ውስጥ ስራውን የሚሰራው የት ነው? እግዚአብሄር ስራውን የሚሰራው በልቦቻቸው ውስጥ ነው።

እግዚአብሄር በእኛ በቅዱሳኖች የሚሰራው የት ነው? እርሱ የሚሰራው በምድር ላይ ነው እርሱ በእናንተና በእኔ ልቦች ውስጥ ይሰራል ነገር ግን የተሳሳተ አድራሻ የያዘ ስፍራ ለማግኘ ት የምንሞክር ይመስል የእግዚአብሄርን ስራ በባህር ላይ ለመስራት የምንሞክርባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ አሁንም እንኳን በአስተሳሰቦቻቸው ቃሉን ለመረዳት የሚሞክሩ አንዳንድ ሰዎች አሉ እግዚአብሄር ግን አስቀድሞ በልቦቻችን ውስጥ ስራውን ሰርቷል።

የራሳችንን አስተሳሰቦች መጣል አለብን በልባችንም የተጻፈውን የእግዚአብሄር ቃል በማመን ደህንነትን መቀበልና የእምነትን ሕይወት መኖር አለብን የእምነት ሕይወት ይህ ነው አጋር ምዕመናኖቼ በዚህ ታምናላችሁን? የምስጋና ዝማሬዎችን ስንዘምር እግዚአብሄርን በልቦቻችን በማመን ልንዘምር ይገባናል የእምነት ሕይወታችንንም ስንኖር የእግዚአብሄርን ቃል ከልባችን በማመን ልንኖር ይገባናል እምነት ማለት ይህ ነው።

ሁላችሁም የእግዚአብሄርን ቃል በልባችሁ በማመን የእምነት ሕይወታችሁን እንድትኖሩና እግዚአብሄርም የሰጣችሁን በረከቶች በሙሉ እንድትቀበሉ ተስፋዬና ጸሎቴ ነው። ✉

ከሐጢያታችን ሁሉ መዳን የምንችለው ሐጢያታችንን በሙሉ ስናውቅ ብቻ ነው

« ዘፍጥረት 1:9-13 »

«እግዚአብሄርም ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ቦታ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ አለ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውሃ መከማቻውንም ባህር አለው እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ሦስተኛ ቀን::»

ከዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የተወሰደው መልዕክት እያንዳንዱ ሰው ሐጢያቱን ማወቅና የደህንነትን ፍሬ ማፍራት እንዳለበት የሚናገር ነው::

እያንዳንዱ ሰው በዚህ አለም ላይ ከተወለደበት ቅጽበት ጀምሮ በሐጢያት ተወልዶዋል ስለዚህ ሰዎች ሁሉ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ በርካታ መተላለፎች ከመፈጸም ማምለጥ አይችልም ስለዚህ እግዚአብሄር የራሳችንን ሐጢያተኝነት ተገንዝበን እንድናውቅና የሰጠንን የውሃውንና

የመንፈሱን ወንጌል እውነት እንድናስተውል ፈለገ እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደተሰጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እምነት ላይ ለመድረስ ከፈለግን በመጀመሪያ ሐጢያታችንን መገንዘብ አለብን።

እውነቱ ግን ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን የሚኖሩት ሐጢያታቸውን ፈጽሞ ሳያውቁ ነው እኛ ከእግዚአብሄር የራቅነው በራሳችን ጽድቅ ምክንያት ነው እኛ ሐጢያተኛውን ማንነታችንን አናውቀውም ምክንያቱም በጣም ራሳችንን ያጸደቅን ሰዎች ነን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ መዳን የምንፈልግ ከሆነ በመጀመሪያ የራሳችንን ሐጢያት ማየት መቻል አለብን የእግዚአብሄርንም ጽድቅ ማወቅና በእርሱም ማመን አለብን።

በሌላ አነጋገር ሰዎች ክፋቶቻቸውንና ሐጢያቶቻቸውን ማንጻት ከፈለጉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ላይ ማነጣጠርና በእርሱም ማመን አለባቸው ሰው ሁሉ የተደበቀውን ማንነትና ሐጢያት መረዳት በእግዚአብሄር ፊት መስገድ የእርሱን እርዳታ መለመንና ጌታ በሰጠን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለበት ሊድን የሚችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው ያንን ለማድረግ በመጀመሪያ ክፉ ማንነታችንን መረዳት አለብን የእግዚአብሄር ቃል እኛን ከሐጢያት የሚያድን የእውነት ቃል ነው ጌታ ደህንነትን የሚሰጠውና ብዙ የእምነት ፍሬዎችን እንዲያፈሩ የሚያስችላቸው የእግዚአብሄርን እውነት ለተቀበሉ ሰዎች ነው።

ጌታችን በሦስተኛው የፍጥረት ቀን የተናገረውን እውነት መገንዘብ አለብን መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ በሦስተኛው የፍጥረት ቀን ሁለት ጊዜ *«እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ» (ዘፍጥረት 1:10-12)* ይላል መጀመሪያ እግዚአብሄር የብሱ መገለጡን በማየት እንደተደሰተ ተናገረ ለሁለተኛ ጊዜ ዘርን የሚያበቅሉ ቡቃያዎችና ፍሬ የሚያፈራ ዛፍን ማየት መልካም እንደሆነ ተናገረ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምድር የምታመላክተው የሰውን ልብ ነው እግዚአብሄር ይህንን ምድር የሸፈነውን ውሃ በአንድ ስፍራ ሲሰበስበው የብሱ ተገልጦ አየ ይህ የሚያመላክተው የእግዚአብሄር ቃል ልቦቻችንን የሸፈኑትን ብዙ ግብዝነቶች ሊያሳየን የሚችል መሆኑ ነው።።

እግዚአብሄር የብሱ ሲገለጥ በማየቱ ለምን ተደሰተ?

ይህ የሆነበት ምክንያት ሰው መዳን የሚችለው ክፉ የሆነው ባህሪው ሲገለጥ ብቻ ስለሆነ ነው ሰው ሰራሽ ሐይማኖቶች የግብዝነት ስርአቶች ብቻ ናቸው በሌላ አነጋገር ሰዎች መሰረታዊውን ሐጢያታቸውን ሐይማኖት ተብሎ በሚጠራ የግብዝነት መሸፈኛ ስለጠቀለሉት እነርሱ ራሳቸው ክፉ ሰዎች መሆናቸውን አያውቁም ስለዚህ ሰዎች በሐጢያት የተሞላውን እውነተኛ ማንነታቸውን ማየት ስለማይችሉ ራሳቸውን መልካም ሰዎች አድርገው በመቁጠራቸው ትልቅ መታለል ውስጥ ወድቀዋል።።

እግዚአብሄር ሐጢያቶቻቸው እንዳይገለጥ ለመከለስከል ከሚሞክሩ ሰዎች በተቃራኒ ሐጢያቶቻቸው እንዲገለት የሚፈልገው ለዚህ ነው የሰዎች ሐጢያቶች ከእግዚአብሄር ሊደበቁ አይችሉም እግዚአብሄር የሰዎችን ሐጢያቶች ማጋለጥና መፈወስ ይሻል እግዚአብሄር ለእያንዳንዱ ሐጢያተኛ የሐጢያት ስርየትን መስጠት የሚችለው የሰው ክፋቶች ከተገለጡ በኋላ ብቻ ነው እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችን ሙሉ በሙሉ ተገልጠው ሲመለከት የሚደሰተው ለዚህ ነው።።

ሰዎች በጥቅሉ ሌሎች ጥሩና መልንም ሰዎች እንደሆኑ አድርገው እንዲመለከቱዋቸው ይፈልጋሉ ስለዚህ ሁሌም ጥሩ

ሰዎች እንደሆኑ ያስመስላሉ በራሳቸው ግብዝነት ተሞኝተውም አብዛኞቹ በእርግጥም መልካም ሰዎች እንደሆኑ አምነዋል ነገር ግን እውነቱ በልቦቻቸው ውስጥ በጣም ብዙ ክፋቶች የተደበቁ መሆናቸው ነው ሁሉም ይህንን መገንዘብ ያስፈልጋቸዋል።

እግዚአብሄር የሰጠው ደህንነት የሚፈጸመው ለማነው? ደህንነት የሚመታው ራሳቸውን ፈጽመው ሐጢያተኞች እንደሆኑ አድርገው ለሚያውቁና ጌታ በሰጠው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለሚያምኑ ሰዎች መሆኑ አያጠራጥርም በሌላ አነጋገር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት መቀበል የሚችሉት በመንገዳቸው ቢቀጥሉ ሲያል መውረዳቸው እንደማይቀር የሚያምኑ ሰዎች ብቻ ናቸው እናንተስ ታዲያ? አንዳንዶቻችሁ ልቦቻችሁ ጥሩ እንደሆኑ አታስቡምን? እንዲህ ያሉ ሰዎች ከሐጢያቶቻቸው መዳን ይችላሉ? ወይስ ሰው ከሐጢያቶቹ ሊድን የሚችለው የልቡን ክፋት ሲገነዘብና የእግዚአብሄርን ጸጋ ሲጠይቅ ነው? ከሐጢያት ማዳን የሚችለው የፊተኛው ሳይሆን የኋለኛው ነው ሆኖም የልቦቻቸውን መሰረታዊ ክፋት የሚያውቁና የሚያምኑ ሰዎች ያን ያህል ብዙ አለመሆናቸው ያሳዝናል።

እግዚአብሄር እንዲህ ብሎዋል *«የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?» (ኤርምያስ 17:9)* በማርቆስ 7:21-23 ላይም እንዲህ ብሎዋል *«ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኰል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል።»*

የሰው ስጋዊ አስተሳሰቦች ክፉ ናቸው ሰዎች በተፈጥሮዋቸው ነፍስ ገዳዮች አመንዝሮችና አባካኞች ናቸው ሁሉም በዋናነት የተወለዱት ክፉ ሰዎች ሆነው ነው

እግዚአብሄር የደህንነት ጸጋውን የሚሰጠው እንዲህ ያሉ ሐጢያተኞች መሆናቸውን ለሚያውቁ ሰዎች ነው እግዚአብሄር የሐጢያት ስርየትን ፍሬዎችና የወንጌል ስርጭትን ፍሬዎች የሚያፈራው በእነዚህ ሰዎች አማካይነት ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የደህንነት በረከቱን የሚሰጠው በእርግጥም እነዚህን ሐጢያቶች በልቦቻቸው ውስጥ እያስተናገዱና በሕይወት ዘመናቸውም ሁሉ እነዚህን ሐጢያቶች እያፈለቁ የሚኖሩ ክፉ ሐጢያተኞች መሆናቸውን ለሚገነዘቡና ለሚያምኑ ሰዎች ብቻ ነው።

ይህ ከአለም ትምህርቶች ጋር ፈጽሞ የሚቃረን ነው ራሳችንን መልንም ሰዎች እንድናደርግ ከወላጆቻችንና ከስነ ትምህርት ስርአታችን ተምረናል በወጣቶች የስነ ትምህርት መስክ የተስፋፋ «የመፈረጅ ቲዮሪ» የሚባል የገነነ ጽንሰ አሳብ አለ ይህ ጽንሰ አሳብ አንድ ልጅ በወላጆቹ ወይም በመምህሮቹ «ውሸታም» ተብሎ ከተፈረጀ ልጁ ውሸታም ይሆናል ልጁ «ጥሩ ልጅ» ተብሎ ከተፈረጀ ጥሩ ባህርይ ያለው ሰው ሆኖ ያድጋል ነገር ግን ይህ ጽንሰ አሳብ የሚያብራራው የሰውን ግብዝ ባህሪዎች ብቻ ስለሆነ የሰዎችን መሰረታዊ ተፈጥሮ ሊመለከት አይችልም።

ሐይማኖትም ከዚህ የተለየ አይደለም ሁሉም ሐይማኖቶች የሚያስተጋቡት የሰውን ዘር መልካምነትና ጽድቁን ነው በዚህ አለም ላይ እጅግ ክፉዎቹ ሰዎች ክፋቶቻቸውን በውሸት በጎነቶች (ግብዝነት) የሚሸፍኑ ሰዎች ናቸው ክርስትናን እንደ ሐይማኖት አድርገው የሚያምኑትም እነዚሁ ሰዎች ናቸው እነርሱ መሰረታዊ ማንነታቸውን ስለማያውቁ ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ የሚያድናቸውን የእግዚአብሄርን ወንጌል አይቀበሉም ይህንን እውነተኛ ወንጌል ከመቀበል ርቀው በሰው የጽድቅ ምግባሮች ላይ ብቻ የሚያተኩሩ የሐሰት ወንጌሎችን ይሰብካሉ።

ስለዚህ በዚህ አለም ላይ እርሱን አብዝተው የሚቃወሙት የእግዚአብሄር አደገኛ ጠላቶች ዳግም ያልተወለዱ እነዚህ ክርስቲያኖች ናቸው እነርሱ «ነገር ግን አሁንም ቢሆን ሰው ቢያን አንድ ወይም ሁለት በጎነቶች የሉትምን?» በማለት ይከራከራሉ የመጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ቃል ግን ሰው ፈጽሞ ምንም መልካምነት እንደሌለው ይናገራል (ሮሜ 3:10-12) ስለዚህ በመጀመሪያ ልቦቻችን ምን ያህል በብዙ ስጋዊ አስተሳሰቦች እንደተሞሉ በመገንዘብ እውነተኛ ማንነታችንን መረዳት አለብን::

ሰማያትና ምድር የተፈጠሩበት ሦስተኛው የፍጥረት ቀን ሲጀምር ይህች ምድር በውሃ ተሸፍና እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ጽፎዋል እዚህ ላይ ይህ ውሃ የሚያመላክተው ከጠፈር በታች የነበረውን ውሃ ነው አንዳንድ ጊዜ ከጠፈር በታች ያለውም ውሃ ቢሆን ጥርት ብሎ ሊታይ ይችላል ነገር ግን በውሃ የተሸፈነው ከታች ያለው መሬት በጣም የቆሸሸ መሆኑ እውነት ነው እግዚአብሄር ይህንን መሬት ሊያነጻው የሚችለው ከታች ያለው የቆሸሸው መሬት ሲገለጥ ብቻ ነው እርሱ በሦስተኛው ቀን «የብሱም ይገለጥ» ያለው ለዚህ ነው ይህም የሰው ዘር መሰረታዊ ተፈጥሮ በዋናነት ክፉ ስለሆነ እግዚአብሄር መተላለፎቻችንን እንድንገነዘብና እንድናምን እንደሚፈልግብን ያመላክታል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያተኞችን ሁሉ ሊጠራና ከእያንዳንዱ ሐጢያት ሊያድናቸው መጣ ጌታችን እንዲህ ብሎዋል *«ሐጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» (ሉቃስ 5:32)* እግዚአብሄር ክፉ አሳቦች፣ ምንዝርናዎች፣ ዝሙቶች፣ ስርቆቶች፣ መሳምጅት፣ መዳራት፣ ስንፍና፣ ትዕቢትና ወዘተ በሙሉ በሰው ውስጥ እንዳሉና እኛ ሰዎች ሁላችንም እንዲህ ያሉ የረከሱ ልቦች እንዳለን ተናግሮዋል እግዚአብሄር

ሐጢያተኝነቱን በአምላክ ቃል ፊት ሙሉ በሙሉ በማይገለጥ ሰው አማካይነት አንዳች ፍሬ ማፍራት አይችልም ነገር ግን ሰው በራሱ ምንም አይነት ትሩፋት እንደሌለውና ሐጢያተኛ ሰው መሆኑን የሚያውቅ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስን መገናኘትና ዳግም መወለድ ይችላል::

እግዚአብሄር የሰጠው ደህንነት የመጣው ለማነው?

እግዚአብሄር የሰጠው የሐጢያት ስርየት ደህንነት የሚሰጠው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለሚያምኑ ሰዎች ብቻ ነው እኛ በጸጋው የዳንነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እኛ ላሉ ሐጢያተኞች በሰራው ስራ በማመን ነው:: (ኤፌሶን 2:8)

መጽሐፍ ቅዱስ *«እግዚአበሄርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ክፉ እንደሆነ አየ» (ዘፍጥረት 6:5)* ብሎ ስለጻፈ እርሱ ይህችን ምድር ለመዳኘት ወሰነ የእግዚአብሄር ፍርድም በዚህች ምድር ላይ ወረደ ሐጢያተኞችም በሙሉ ጠፉ የዳኑት የኖህ ስምንቱ ቤተሰቦች ብቻ ነበሩ::

ኖህ የዳነው የእግዚአብሄርን ጸጋ ስላገኘ ነበር እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ኖህ ግን በእግዚአብሄር ፊት ሞገስን አገኘ የኖህ ትውልድ እንዲህ ነው ኖህም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ ኖህ አካሄዱን ከእግዚአብሄር ጋር አደረገ» (ዘፍጥረት 6:8-9)* «ሞገስ» የሚለው ቃል ከስጦታ ጋር ተመሳሳይ ነው ኖህም ቢሆን ሐጢያተኛ ነበር ምክንያቱም እርሱ እንደ ማንኛ ውም ሰው ደንማና ጉድለት ያለበት ሰው ነበር ነገር ግን ከእግዚአብሄር ፍርድ ተርፎ ዳነ ይህ የተቻለው እንዴት ነበር? ይህ የተቻለው ኖህና ቤተሰቡ ከእግዚአብሄር ዘንድ የሐጢያት

ስርየትን ጸጋ በማግኘታቸውና ጻድቃን በመሆናቸው ነው በሌላ አነጋገር ኖህ ጻድቅ ሰው የሆነው በእግዚአብሄር የደህንነት ጸጋ በማመኑ ነበር።

እግዚአብሄር ለኖህ ጸጋውን በማልበስ አዳነው እግዚአብሄር ልክ እንደ ኖህ ለእኛም ደግሞ ያንኑ ጸጋ ሰጥቶናል አስተሳሰቦቻችንና ድርጊቶቻችን ክፉ ቢሆኑም እንኳን እግዚአብሄር የእርሱ ሕዝብ እንድንሆን ባርኮናል እግዚአብሄር ይህችን ምድር ከገለጣትና ካደረቃት በኋላ ዘሩ ያለበትን ቡቃያና እንደ ወገኑም ፍሬን የሚያፈራ የፍሬ ዛፍን እንድታበቅል ባረካት ምድር በእግዚአብሄር ፊት ፍሬ ማፍራት የጀመረችው የብሱ በተገለጠ ጊዜ ነው።

በሌላ አነጋገር ሰዎች ከሐጢያቶቻቸው ዳግም የሚወለዱት በመጀመሪያ ለሲያል የታጩ ሐጢያተኞች መሆናቸውን ሲያምኑና ሁለተኛም በውሃውና በመንፈሱ እውነት በመጣውና ሐጢያተኞችን ከሐጢያት ባዳነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው ሐጢያተኛ ሁኔታችንን ብንገነዘብና ልቦቻችንን የሸፈነውን የግብዝነት ጭምብል ብናወልቅ እኛም ደግሞ የእግዚአብሄርን ቃል በመቀበልና በእርሱም በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበልና መልካም ፍሬ ሁሉ ማፍራት እንችላለን።

እግዚአብሄር ግብዞችን ይጠላል

በእግዚአብሄር ፊት መልካም ሰዎች እንደሆኑ የሚያስመስሉ ከውሃውና ከመንፈሱ ዳግም የመወለድን እውነት አያውቁም ክፋቶቻቸውን መልኝም በሚመስል ፈገግታዎቻቸው የሚደብቁ ሐይማኖተኞች የተለመዱ ግብዞች ናቸው ሁሌም እንዲህ ግብዝ የሚሆኑት ለምንድነው? እነርሱ ራሳቸው ለሲያል

የታጩ ሐጢያተኞች የመሆናቸውን እውነታ መደበቅ ስለሚፈልጉ ነው እነርሱ የእግዚአብሄርን ቃል አይሰሙም የራሳቸውን የሕሊና ድምጽም አይቀበሉም ሐጢያተኞች ሆነው ሳሉ ጻድቅ ሰዎች እንደሆኑ ያስመስላሉ ለሐጢያቶቻቸው ወደ ሲያል የሚጣሉ የመሆናቸውን እውነታ ስለማይቀበሉና የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ለማግኘት ምንም ፍላጎት የላቸውም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሚያጥላሉት ለዚህ ነው።

በዚህ አለም ላይ በእርግጠኝነት ጥሩ ሰዎች መሆናቸውን በማመን የተታለሉ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ በእግዚአብሄር ፊት ጥሩ ሰዎች እንደሆኑ በማሰብ እዚህ ምናብ ውስጥ ያሉ ማለትም ክፉ ሐጢያተኞች መሆናቸውን ለእግዚአብሄር የማያምኑ ሰዎች በሙሉ ግብዞች ናቸው በግብዝነታቸው የሚመጻደቁና በስራዎች የተቃኘ እምነት የሚሹ ሰዎች እግዚአብሄርን የሚያስደስተውን ዳግም የመወለድ እውነት የማይከተሉ ነገር ግን የራሳቸውን ትክክለኛነት ብቻ የሚከተሉ ግብዞች ናቸው እግዚአብሄር የሰውን ግብዝነት ይጠላል ማለትም እርሱ ሐሰተኛ መልካምነቶችን ይጠላል።

ስለዚህ የሰው ሀሰተኛ መልንምነት እውነተኛውን የእግዚአብሄር መልካምነት የሚቃወምና ሰውን ወደ ሲያል የሚነዳ ገዳይ ሐጢያት መሆኑን ልትገነዘቡ ይገባል ክፉ ሰዎች በግብዝነታቸው ሐጢያታቸውን በሙሉ በግብዝነታቸው ለመሸፈን መሞከራቸው ክፉትን ላለማየት አይኖቻቸውን ከመሸፈን ጋር የሚመሳሰል ነው የሱፍ ሾርባ የያዘ ጠርሙስ ብትከፍቱ የሚፈስሰው የሱፍ ሾርባ ነው በሱፍ ሾርባ ከተሞላ ጠርሙስ ውስጥ ንጹህ ውሃ አይፈስስም ልክ እንደዚሁ ሰው ራሱ የረከሰና የተበላሸ ሆኖ ሳለ እንዴት አንዳች መልንምነት ከእርሱ ሊወጣ ይችላል?

ስለዚህ ሰዎች በመጀመሪያ ሐጢያታቸውን ለእግዚአብሄር

መናዘዝ የእግዚአብሄር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ማመንና ሙሉ በሙሉም ልክ እንደ አመዳይ ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ መንጻት አለባቸው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ከተቀበሉና ጻድቃን ከሆኑ በኋላ ከእንግዲህ ወዲህ የሰውን ግብዝነት መከተል የለባቸውም ነገር ግን የእግዚአብሄርን ቃል በእምነት መከተል አለባቸው እያንዳንዱን የሰው ግብዝነት መጣልና የእግዚአብሄርን ጽድቅ የሚያለብሰንን ትክክለኛ የወንጌል እውነት ብቻ መከተል የምንችለው እስከ ዕለተ ሞታችን ቀን ድረስ ሐጢያት እንደምንሰራ ስናምን ብቻ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ከሐጢያቶቻቸው የዳኑ ሰዎችም ቢሆኑ ስጋቸውን በሚመለከት አሁንም ድረስ ክፉና የረከሰ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው እግዚአብሄር ክብሩን የሚገልጠውና የጽድቅን ፍሬ የሚያፈራው ክፉ ማንነታቸውን በሚቀበሉ ሰዎች አማካይነት ነው በአንጻሩ የእግዚአብሄርን ቃል እንዳለ የማይቀበሉ ሐጢያተኞች እውነተኛ ውን የእግዚአብሄር መልካምነት የጽድቅ ፍሬ አያፈሩም ራሳችንን ብልሹ ቆሻሻና አስጠሊታ ሰዎች አድርገን እንድንመለከት የተገደድነው እነዚህን ሁሉ መተላለፎች በድርጊቶቻችን በተጨባጭ ስለሰራን አይደለም ይልቁንም ራሳችንን ሐጢያተኛ ሰዎች አድርገን ለመቀበል የምንገደደው ይህንን ቃል በራሳችን ላይ ለማብራት በእግዚአብሄር ቃል ስለምናምን ነው።

የእግዚአብሄር ጽድቅ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ውስጥ አለ ሁላችንም በተፈጥሮዋችን ክፉ ሰዎች ነን ነገር ግን የሐጢያት ስርየት ወንጌል የሆነውን የደህንነት ወንጌል ስለተቀበልን ድነናል አሁን ጻድቅ ሰዎች ሆነን ሕይወታችንን እየኖርን ነው የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከተቀበልን በኋላ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሄር የጽድቅ ስራዎች የጽድቅ መሳሪያዎች

የሆንነው ገናም ክፉ ሰዎች መሆናችንን ስለምናምን ነው።

እግዚአብሄር በሰው ግብዝነት አይተማመንም ግብዝነት ማጭበርበር ነው ስለዚህ እምነት ሊጣልበት የሚችል አይደለም ሐይማኖትም እንደዚሁ የግብዝነት ክምር ነው ስለዚህ እግዚአብሄር ከሐይማኖት የሚጠብቀው ምንም ነገር የለም።

ግብዝነት ራስን ወደ ማጥፋት ይነዳል ግብዝነት ሐጢያት ነው የእግዚአብሄርን በረከቶች የሚያግድ እንቅፋት ነው ግብዝነት እርግማን ነው ግብዝነት የእግዚአብሄርን እርግማን የመቀበያ መንገድ ነው የእግዚአብሄርን በረከቶች መቀበል የሚፈልግ ሰው ካለ ከግብዝነት መጽዳት አለበት ግብዝነት መወገድ አለበት ምክንያቱም የሰውን ነፍስ ያጠፋልና እውነተኛ መልካምነት በእግዚአብሄር ማመንና ራስን ማወቅ ነው።

እግዚአብሄር በግብዞች አይተማመንም እርሱ የሚተማመነው በቃሉ በሚያምኑ ሰዎች ነው የእግዚአብሄርም ቤተክርስቲያን እንደዚሁ በሰው ግብዝነት አትተማመንም ማንም ቢሆን በሌላ ሰው አንተማመንም ምክንያቱም የሰው ስጋ በግብዝነት የተሞላ ነውና የሁሉም ሰው ስጋ ተመሳሳይ ስለሆነ «እኔ እንደዚያ ሰው አይደለሁም እኔ ከሌላው ሰው ሁሉ የተለየሁ ነኝ» ብሎ ማሰብ መታለል ነው ሁሉም ሰው ያው የሐጢያት ክምር ነው ጌታ ግን የሐጢያተኞች አዳን በመሆን የእግዚአብሄርን ጽድቅ ገለጠልን እርሱ ማንም ሰው ፈጽሞ ጽድቅ እንደሌለው በእግዚአብሄር ፊት ሙሉ በሙሉ አጋልጦዋል።

ራሳችሁን አታታልሉ በራሳችሁ ግብዝነት አትሞኙ እግዚአብሄር ራሱ የሰው ዘር የክፉ አድራጊዎች ዘር እንደሆነና የሰውም ልብ ከማንኛውም ሌላ ነገር ይልቅ ክፉ እንደሆነ ተናግሮዋል።

ነገር ግን የእግዚአብሄር ሐይል አስደናቂ ስለሆነ እንዲህ

ባሉ ሰዎች አማካይነት አሁንም የጽድቅ ፍሬውን ያፈራል በእውነት አማካይነት ከሐጢያቶቻችን ያዳነን የእግዚአብሄር መልካምነትና ጽድቅ ነው ይህ የእግዚአብሄር ሐይል ነው ይህ ድንቅ አይደለምን? የደህንነት ወንጌል እግዚአብሄር ያለው ብቸኛ ው እውነት ነው እኛ የእውነትን ፍሬ ማፍራት የምንፈልግ ከሆነ ፈጽሞ ሐጢያተኞችና ፈጽሞ ግብዞች እንደሆንን መረዳትና እንደዚያ ማመን አለብን::

በውስጣችሁ የተገለጡትን ሐጢያቶች በሙሉ ታምናላችሁን?

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም ለተወለዱትም ሰዎች ቢሆን መጀመሪያ የሚታየው ክስተት የስጋቸው ሐጢያት አብዝቶ መገለጡ ነው በሌላ አነጋገር ክፉው ማንነታቸው ከዚህ ቀደም ከተገለጠው በላይ ይገለጣል::

በእኔም የሆነው ይኸው ነው ከዚህ ቀደም ከባለቤቱ ጋር ተጋጭቼ አላውቅም ነገር ግን የሐጢያቶቼን ስርየት ከተቀበልሁ በኋላ ከባለቤቱ ጋር ወደ መጋጨቱ አዘነበልሁ የተማርሁትን ትክክለኛ ትምህርት ሁሉ እስክረሳ ድረስም ቃላቶቼ የሚያበሳጩ ሆኑ ስለዚህ የሐጢያቶቼን ስርየት ከተቀበልሁ በኋላ አንዳንድ ጊዜ «ለምን እንደዚህ እሆናለሁ? ይህ ማለት ምናልባት ከሐጢያቶቼ ሁሉ አልነጻሁም ማለት ነውን? እንዴት እንዲህ ያለ ነገር አደርጋለሁ?» በማለት ግራ እጋባለሁ::

እኛ በእርግጥም በግብዝነት የተሸፋፈንን ክፉ ሰዎች ስለመሆናችን የእግዚአብሄር የእውነት ቃል ያለ አንዳች ጥርጣሬ ግልጽ አድርጎዋል ነገር ግን የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ባለመቀበላችን ምክንያት በሕይወታችን ውስጥ ደረቁ መሬት

እንዲገለጥ አደረገ የተጻፈውን የእግዚአብሄር ቃል ማለትም ትክክለኛውን የመልካምነት ቃል ካልተገነዘብን የእግዚአብሄር ቃል ሊዋጋንና ሊያሸንፈን ይገባል ስለዚህ እግዚአብሄር በሚገጥሙን ሁኔታዎች አማካይነት የሰውን ዘር ክፋቶች በሙሉ ይገልጣል።

ነገር ግን ክፉ የሆነውን ማንነታቸውን ከተቀበሉና በእግዚአብሄር የእውነት ቃል ካመኑ በኋላ የሐጢያት ስርየትን ፍሬ ማፍራት ይችላሉ በውስጣችን እንዲህ ያሉ ክፋቶች እንዳሉ በራሳችን አላቅንም ነገር ግን እግዚአብሄር እነዚህን ክፋቶች እንድናይና እንድንገነዘብ ክፋታችንን ገለጠ ጌታ ይህንን ካደረገ በኋላ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ቃል አማካይነት አዳነን ስለዚህ ክፋቶቻችንን አብዝተው በተገለጡ ቁጥር ጌታን አብዝተን እናመሰግነዋለን።

ስለዚህ ሁሉም ሰው በተቻለ ፍጥነት የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል መቀበልና በግብዝነት የተሞላ የክፉ አድራጊዎች ዘር መሆኑን አውቆ ወደ እግዚአብሄር በመመለስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው በውሃውና በደሙ ወንጌል በማመን ዳግም መወለድ አለበት በእርግጥ በወንጌል ልትመኩና ከዚህ ወንጌልና ከእግዚአብሄር ጋር በብርሃን ውስጥ ለመኖር የምትፈልጉ ከሆነ ሙሉ በሙሉ በእርሱ የእውነት ቃል ማመን አለባችሁ።

ሕይወታቸው በግብዝነት የተታለ ሰዎች የእግዚአብሄር ቃል የሚያስተምረውን እውነት አያውቁም ስለዚህ ሕይወታቸው ይበልጥ ግብዝ እየሆነ ሔደ ምንም ያህል ጠንክረው ቢሞክሩም በትክክል ጥሩ ሰዎች ሆነው መኖር እንደማይችሉ ሲያውቁ የእምነት ሕይወታቸውን ፈጽመው ይተዉታል በሌላ አነጋገር በግብዝነታቸው ስለተታለሉ የእምነት ሕይወታቸውን እስከ መጨረሻው ድረስ መኖር አይችሉም እነርሱ በእውነት ቃል አማካይነት ምን አይነት ሰዎች እንደሆኑ

ሊገነዘቡና ግብዝነታቸውን ሊጥሉ ይገባቸው ነበር ሰዎች መዳን የሚችሉት ሐጢያታቸውን ሲያውቁና ክፋቶቻቸው ሲጋለጡ ብቻ ነው።

እናንተስ ታዲያ? ክፉ እንደሆናችሁ ትቀበላላችሁን? ሰው ሙሉ በሙሉ 100 በመቶ ክፉ እንደሆነ ታውቃላችሁን? እኔ ራሴ በእግዚአብሄር ቃል ላይ እንደተገለጠው በእርግጥም ፈጽሞ ሐጢያተኛ እንደነበርሁ ከሙሉ ልቤ እቀበላለሁ እንደዚያም አምናለሁ እኔ የምመጻደቅበት ምንም ነገር ስለሌለና ማንም ሰው ምንም መልካምነት ስለሌለው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው የተጠመቀውና ደሙን ያፈሰሰው ክፉ የሆነውን የሰው ዘር ሐጢያቶች እያንዳንዱን የአለም ሐጢያት ለመውሰድ ነው ሁላችንም ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን መሆኑን በማመን ማለትም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ድነናል።

በእርግጥም ትክክለኛው እውነት የእግዚአብሄር ቃል ብቻ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ይመሰክራል የሰው ዘርም በዚህ አውነት በማመን አሁን ከሐጢያቶቹ ሁሉ ነጽቶ የጽድቅ መሳሪያ ሆንዋል በእግዚአብሄር ባይሆን ኖሮ መልካም በሆነውም የኢየሱስ ክርስቶስ የእውነት ቃል ባይሆን ኖሮ የሰው ዘር ሙሉ በሙሉ በግብዝነቱ ተበላሽቶ መቋቋም በማይቻል ጥምባት ውስጥ በኖረ ነበረ አሁን በዚህ አለም ላይ የሚኖር ሰው ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበለው ጥምቀቱ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ባዳነን የደህንነት እውነት ማመንና ደህንነትን ማግኘት አለበት።

ከግብዝነት ሐጢያቶቻችሁ ሁሉ ትድኑና ጻድቃን ሰዎች ሆናችሁ ትኖሩ ዘንድ ክፋቶቻችሁን እንድትቀበሉ፣ በእግዚአብሄር የእውነት ቃል እንድትተማመኑ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እንድታምኑ ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ አንድ ጊዜ ጻድቃን ከሆናችሁ የእርሱን የእውነት ቃል

በመቀበልና በእርሱ ጽድቅ በማመን ቀሪውን ዘመናችሁን የጽድቅ መሳሪያዎች ሆናችሁ እንድትኖሩ እጠይቃችኋለሁ።

እግዚአብሄር የሰጠው እውነተኛ ደህንነት የሚሰጠው ግብዝነታቸውን ለሚቀበሉና ለሚጥሉት ሰዎች ነው እግዚአብሄር ይህንን ደህንነት ያመጣው እውነተኛውን ማንነታቸውን ለሚቀበሉ ለእነዚህ ሰዎች ነው ምስጋናዩን ሁሉ ለአምላካችን አቀርባለሁ አሜን! ✉

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ የእግዚአብሄር አገልጋዮች ሊያደርጉት የሚገባቸው ነገር

« ዘፍጥረት 1:14-19 »

«እግዚአብሄርም አለ ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች፣ ለዘመኖች፣ ለዕለታት፣ ለዓመታትም ይሁኑ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ እግዚአብሄርም በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው በቀንም በሌሊትም እንዲሰለጥኑ ብርሃንና ጨለማንም እንዲለዩ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አራተኛ ቀን::»

የሰዎችን ነፍስ ጠልቆ ማወቅና መለየት የእግዚአብሄር ስራ መጀመሪያ ነው

እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት በአራተኛው የፍጥረት ቀን በባሪያዎቹ በኩል ምን አደረገ? የራሱን ሕዝብ ከቀሩት ሕዝቦች እንዲለዩ አደረጋቸው እግዚአብሄር አብ ሰውን ሁሉ ከሐጢያቶቹ ለማዳን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ምድር

ላከው እግዚአብሄር የሰዎችን ሐጢያቶች ለመደምሰስ መሳሪያው አድርጎ ሊጠቀምባቸው አገልጋዮቹን አስነሳ እግዚአብሄር የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሰጠውና ይህንን ወንጌል የሚሰብኩ አገልጋዮቹን ያስነሳው ነፍሳቶችን ለማዳን ነው ስለዚህ እግዚአብሄር አገልጋዮቹን ይንከባከባቸዋል በትክክልም ይቀርጻቸዋል ከዚያም ይጠቀምባቸዋል።

የእግዚአብሄር አገልጋዮች በዚህ ምድር ላይ የብርሃንን ልጆች ከጨለማ ልጆች እንዲለዩና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለእነርሱ እንዲሰብኩ በሐላፊነት የተሰጣቸውን ጥሪ ይዘው ማገልገል አለባቸው የእግዚአብሄር አገልጋዮች የእርሱን ስራ ሲሰሩ ሰዎች የሐጢያት ስርየትን ተቀብለው እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መመርመርና መለየት አለባቸው።

በዚህ አለም ላይ የወንጌል ሰባኪዎች ጥሪ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ ከሆነ ይህንን ስራ እንዴት እንደሚፈጽሙት ሊያውቁ ይገባል ስለዚህ የአንድ ወንጌላዊ አገልግሎት አስቀድሞ መጀመር ያለበት በፊቱ ያሉት ነፍሳቶች ከሐጢያት ድነው እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ በመለየት ነው ነፍሳቶችን መለየት የማይችል ከሆነ ስራው ሁሉ ከንቱ ይሆናል ስለዚህ በመጀመሪያ ነፍስ ድኖ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መወሰን አለበት ከዚያም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ቃል ለሐጢያተኞች መስበክ አለበት ከዚህ በኋላ እነዚህን ነፍሳቶች መንከባከብና እምነታቸውን ማሳደግ አለበት አንድ ወንጌላዊ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለሚያምኑ ሰዎች የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል ደረጃ በደረጃ የመስበክ ሐላፊነትም አለበት ይህንን ወንጌል ለሌሎች ነፍሳቶችም ደግሞ ማሰራጨት የሚችሉት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በትክክል ከሰለጠኑ ወንጌላውያኖች የሰሙ ሰዎች ብቻ ናቸው።

አንድ ወንጌላዊ ከሰዎች ጋር ሲገናኝ ሊያደርገው የሚገባው

የመጀመሪያው ነገር የእግዚአብሄር ሕዝብ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ መወሰንና ይህንንም እንዲያውቁ ማድረግ ነው በዚህ አለም ላይ ያሉ ብዙዎች ራሳቸውን ወንጌላውያኖች አድርገው ቢጠሩም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሚያውቁ ግን በእርግጥም ጥቂቶች ናቸው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል አስቀድሞ በኢየሱስ እናምናለን ለሚሉ ክርስቲያኖች ሊሰበክ የሚገባው ለዚህ ነው።

አንዳንድ ሰባኪዎች አንድ ነፍስ ድኖ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ለይተው ማወቅ እንደማይችሉ እናያለን ምክንያቱም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል አያውቁምና ስለዚህ እያንዳንዱ ሰባኪ በመጀመሪያ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለራሱ ማወቅ አለበት እርሱ ራሱም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምን አማን መሆን አለበት የዳኑትን ካልዳኑት መለየትን በሚመለከት የትኛውም ወንጌላዊ ግራ መጋባት አይኖርበትም።

መንፈሳዊ ዕውራኖች ሰው ድኖ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መለየት አይችሉም በሌላ አነጋገር እውነተኛ ምስክር ይህ ነፍስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እንደሚያምን ወይም እንደማያምን መለየት መቻል አለበት የእግዚአብሄር አገልጋዮች ወንጌልን ማስፋፋት ከተሳናቸው ምክንያቱ በዚህ አገልግሎት ሰዎችን የመለየት ችሎታ ስለጎደላቸው ነው እውነተኛ የወንጌል ምስክር በመጀመሪያ ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ያምኑ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መመርመርና ከዚያም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ዘሮች መዝራት አለበት ይህ ሆኖ እያለ በጣም ብዙ ምስክሮች አስቀድመው የነፍስን ሁኔታ በትክክል ሳይመረምሩ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ይሰብካሉ የብዙ ውድቀቶች ምክንያት ይህ ነው።

ስለዚህ አንድ ወንጌላዊ ሊያደርግ የሚገባው የመጀመሪያው ነገር ሰው ጻድቅ እንደሆነ ወይም ሐጢያተኛ እንደሆነ

በመንፈሳዊ መንገድ መለየት ነው ይህ ሰው አሁንም ገና ሐጢያተኛ እንደሆነ የማያውቅ ከሆነ ወንጌላዊው እግዚአብሄር በሐጢያቱቹ ምክንያት እንደሚኮንነው ሊያስተምረው ይገባል በእግዚአብሄር ፊት ትክክለኛ የሆኑ ምስክሮች የሰዎች ነፍስ በብርሃን ወይም በጨለማ ውስጥ እንዳለች እንዴት እንደሚወስን ማወቅና ከዚያም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መመስከር አለበት አንዳንድ ጊዜ ስንመሰክር አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ለምን እንደተጠመቀ ምክንያቱን ባያውቁም ሐጢያት አልባ እንደሆኑ ይናገራሉ።።

ራሳቸውን ወንጌላውያን ብለው የሚጠሩ ሰዎች የእነዚህ ሰዎች ወኪል ናቸው እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ከዮሐንስ የተቀበለውን ጥምቀት ምስጢር ማለትም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እውነት በትክክል ሳያውቁ በዕውር ድንብር ሐጢያት እንደሌለባቸው ይናገራሉ አጋር ምዕመናኖቹ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሳያውቁ «እኔ በኢየሱስ ስለመምን ሐጢያት አልባ ነኝ» ቢሉም ይህ በእርግጥ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት የለም ማለት አይደለም ሰዎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ባያውቁም ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው እስካመኑ ድረስ ሐጢያት እንደሌለባቸው በዕውር ድንብር ሲናገሩ ራሳቸውን እያታለሉ ነው ሰው ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ እንደሚያምን ሊናገር ይችላል ነገር ግን በልቡ ውስጥ ሐጢያት ካለ አሁንም ሐጢያተኛ ነው ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ሐጢያት የለብኝም ብሎ መናገር እግዚአብሄርንና ሰዎችን ማታለል ነው ነገሩ እንደዚያ አይደለምን?

እያንዳንዱ ክርስቲያን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ያውቃል? የለም ሁሉም ክርስቲያን ይህንን ወንጌል አያውቅም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ባያውቁም በኢየሱስ እንደሚያምኑ የሚናገሩ እጅግ በጣም ብዙ ክርስቲያኖች አሉ

ነገሩ እንዲህ ከሆነ በመጀመሪያ በመንፈሳዊ አነጋገር እነዚህ ክርስቲያኖች አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች መሆናቸውን መወሰን አለብን ወንጌላውያን አማኞች ተብለው የሚጠሩትም እንደዚሁ የዚህ አይነት ሰዎች ናቸው ወንጌላውያን አማኞችም እንደዚሁ መንፈሳዊ ንቃት የሚያስፈልጋቸው ለዚህ ነው።

በእግዚአብሄር ፊት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምን ምስክር እንዴት በእምነት እንደሚኖር ያውቃል አንድ ሰባኪ ጉባኤውን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት በትክክል ካልመራ አገልግሎቱ በሙሉ አይሳካም እግዚአብሄር ብርሃንን ከጨለማ የሚለየው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በሚያምኑ ምስክሮች አማካይነት ነው በትክክል ማገልገል የምንችለው የውሃንና የመንፈሱን ወንጌል በማመን ስለምናገለግል ነው በእግዚአብሄር ፊት ትክክለኛው አይነት አገልግሎት ጻድቃንን ከሐጢያተኞች የሚለይና የደህንነት እውነት የሆነውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሚሰብክ አገልግሎት ነው።

አሁን እናንተ እውነተኛ ምስክሮች ሆነው አገልግሎታቸውን መፈጸም የሚችሉት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ አማኞች ብቻ እንደሆኑ መረዳት መቻል አለብን ምክንያቱም በፊቱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ጻድቃን የሆኑ ሰዎች ናቸውና ሐጢያተኞች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የማያምኑ ሰዎች ናቸው ሰባኪው ጻድቃኖችን ከሐጢያተኞች መለየቱንና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበኩን በጭራሽ ችላ ማለት የለበትም።

ስለዚህ አንድ ሰባኪ ከሰው ጋር ሲገናኝ የአገልግሎቱ የመጀመሪያ ደረጃ ይህ ሰው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን በግልጽ ዳግም ተወልዶ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ በትክክል ማወቅ ነው ወደ አውደ ውጊያ ብንሄድና ብንዋጋ

በአይኖቻችን ፊት የቆመው ሰው የእኛ ወታደር ይሁን ወይም ጠላት መለየት ካልቻልን ይህንን ጦርነት እንዴት መዋጋት እንችላለን? እኛ በእውነት ቃል ማጥቃትና እርሱን ማዳን እንድንችል በመጀመሪያ በፊታችን የቆመው ይህ ሰው ገና የሐጢያቶቹን ስርየት ያልተቀበለ መንፈሳዊ ጠላት መሆኑን በግልጽ ማወቅ አለብን።

አንድ ሰባኪ መንፈሳዊ ጦርነትን ሲዋጋ የደህንነትን እውነት ሊያውቅ ይገባዋል በዚህ መንገድ ሐጢያተኛውን ከሐጢያት ወጥመድ ነጻ ሲያወጣውና ሲታደገው ያን ጊዜ ብቻ እውነተኛ የእግዚአብሄር አገልጋይ ይሆናል በሌላ አነጋገር በእግዚአብሄር ፊት እውነተኛዎቹ ምስክሮች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ለሐጢያተኞች እውነተኛውን ደህንነት ማምጣት አለባቸው።

እግዚአብሄር በፍጥረት ቃል አማካይነት ዕቅዱን አሳይቶናል በፍጥረቱ መጀመሪያ ላይ በግልጽ የተወሰኑ ነገሮችን የመለየትን ስራ ሰርቷል ሰማያትን ከምድር፣ ብርሃንን ከጨለማ፣ ከጠፈር በላይ ያለውን ውሃ ከጠፈር በታች ካለው ውሃና የብሱን ከባህሩ ለይቶዋል እንደገናም በአራተኛው የፍጥረት ቀኑ በጠፈር ላይ ሁለት ብርሃናትን በማኖር ቀኑን ከሌሊቱ ለይቶዋል።

ስለዚህ አንድ ሰባኪ ከነፍሳቶች ጋር ሲገናኝ እነዚህ ነፍሳቶች ድነው እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ይለይ ዘንድ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው አንድ ወንጌላዊ ነፍሳቶችን በሚለይበት ጊዜ በራሱ ስጋዊ መለኪያ ላይ ተመስርቶ መለየት አይገባውም ነገር ግን መለየት ያለበት ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት ላይ ተመስርቶ ነው።

እግዚአብሄር በሰጠው የደህንነት እውነት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ተመስርተን ዳግም የተወለዱትን ዳግም

ካልተወለዱት መለየቱ ለእኛ በረከት ነው የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን የዳኑትን ካልዳኑት በትክክል የመለየቱን ስራ ማከናወን አለባት የእግዚአብሄር ስራ ሊጀመር የሚገባው በዚህ የመለየት ስራ ነው የእግዚአብሄር መንግስት ሊገነባ የሚችለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰባኪዎች ብርሃንን ከጨለማ የሚለየውን መንፈሳዊ መለየት ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነው እነዚህ ሰባኪዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ሰራተኞች ሆነው የእግዚአብሄርን አገለግሎት መፈጸም ይችላሉ ስለዚህ አንድ ሰባኪ ብርሃኑን ከጨለማው መለየት የማይችል ከሆነ በትክክል ሊያገለግል አይችልም::

የሐጢያቶቻቸውን ስርየት በተቀበሉት ሰዎች መካከል ደግ ልብ ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉ እነርሱ «ብዙ ሰዎች ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው አምነው ሳለ እንዴት ዳግም አልተወለዱም ማለት እችላለሁ?» ይላሉ በተለይም የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን አማኞች የሚያምኑት ወንጌል ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ጋር ይቀራረባል ነገር ግን ፍጹም ወንጌል አይደለም ስለዚህ ራሳቸውን ጻድቃን ብለው ለመጥራት ምኞት አይሰማቸወወም ምክንያቱም አሁንም ገና በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት አለና በሌላ አነጋገር እኛ የምናምነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ከእነርሱ እምነት የተለየ ነው::

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ምስክሮች እንደዚያ ሊያደርጉ ቢሞክሩ እንኳን ዳግም ያልተወለዱ ሰዎችን ማስተዋልና መቀበል እንደማይቻላቸው ግልጽ ነው በመጨረሻም ጻድቃን ከሐጢያተኞች ይለያሉ እውነተኛ ምስክሮች የአለም ዕውቅና ባላቸው የሚሲዮናውያን ድርጅቶች ውስጥ ካሉት ጋር ለመግባባትና አብረው ለመስራት አጥብቀው ቢፍጨረጨሩም እነዚህ ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች

ስላልሆኑ ተቀባይነት ሊኖራቸው አይችልም እነርሱ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ስለማይቀበሉ ውለው አድረው ከእኛ ይለያሉ::

በመጨረሻ ብርሃንና ጨለማ አብረው ሊኖሩ አይችሉም በቤታችሁ ውስጥ ያለውን መብራት ስታበሩት ጨለማ ወዲያውኑ ይጠፋል መብራቱን ስታጠፉት ደግሞ ጨለማው ይመለሳል በአንድ ክፍል ውስጥ ብርሃንና ጨለማ አብረው ሊኖሩ አይችሉም በቤት ውስጥ ያለው መብራት ሲበራ ጨለማው ወዲያውኑ ይጠፋል ስለዚህ እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምን አማኞች ለሆነ አላማ ከወንጌላውያን ቤተክርስቲያን አማኞች ጋር አብረን ለመስራት ብንሞክር በመጨረሻ ከእነርሱ መለየታችንን ከማወጅ በቀር ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም::

አንዳንድ ሰዎች «የሐጢያቶቼን ስርየት ተቀብዬአለሁ አሁንም እየተቀበልሁ ነው ወደፊትም እቀበላለሁ» ይላሉ

በቅርቡ የአንድ አለም አቀፍ የሚሽን ድርጅት አባል ከሆነ ሚሲዮናዊ ጋር ተገናኝሁና አብረን ሕብረት አደረግን ነገር ግን እርሱ ያመነው ወንጌል እኔ ካመንሁት ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ፈጽሞ የተለየ ነበር::

በውሃውና በመንፈሱ ወነወንጌል በማመን የሐጢያት ስርየት በአንድ ጊዜ እንደተገኘ ነገርሁት እርሱ ግን ነገሩ እንደዚህ እንዳልሆነ ተናገረ ይህ ሚሲዮናዊ እንዲህ አለ «እኔ የሐጢያቶቼን ስርየት ተቀብያለሁ አሁንም እየተቀበልሁ ነው ወደፊትም ደግሞ እቀበላለሁ» አብዛኞቹ ክርስቲያኖች

የሚገባቸውና የሚያምኑት እንደዚህ ነው ነገር ግን ይህንን ጉዳይ ጥቂት ጠለቅ ብለን ብናስበው ተቃርኖ እንዳለበት ማየት እንችላለን እንዲህ ያለው እምነት የዘመኑ ክርስትና በሒደት የሚገኝ ቅድስና ውጤት ነው በዚህ ዘመን በመላው አለም የሚገኙ የክርስቲያን መሪዎች በዚህ መንገድ ያምናሉ ታዲያ እነዚህ መሪዎች የሚሰብኩት ምንድነው?

እኔ ራሴ ሐጢያት እንደሌለባቸው ከሚናገሩ ብዙ የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን አማኞች ጋር ተገናኝቻለሁ ነገር ግን እነርሱ ሐጢያቶቻችን ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት አማንይነት ወደ ኢየሱስ እንዳልተላለፉ ተናግረዋል እኔም እንዲህ አልኋቸው «እንግዲያውስ የአለም ሐጢያቶች ኢየሱስ ከዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት ወደ እርሱ መተላለፋቸው እውነት ላለመሆኑ መረጃውን አሳዩኝ እኔ ሐጢያቶቻችን በጥምቀቱ አማካይነት በእርግጥ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ በእግዚአብሄር ቃል አረጋግጥላችኋለሁ» ሁሉም አንዲት ቃል ሳይናገሩ ተመልሰው ሄዱ በመጨረሻም ከእኛ ጋር በመንገድ የተለያዩ ሰዎች ራሳቸውን ለውሃውና ለመንፈሱ ወንጌል እስካላስገዙ ድረስ ሁሉም ከእኛ ይነጠላሉ።

ስለዚህ የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን አማኞች ሐጢያት አልባ እንደሆኑ ብቻ አምነዋል ኢየሱስ ከዮሐንስ የተቀበለውን ጥምቀት እውነት አላመኑበትም ስለዚህ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች መሆናቸው ግልጽ ነው ለጥቂት ጊዜ ለእነርሱ ተግባቢና ተወዳጅ ለመሆን ሞክርሁ ነገር ግን እስከ መጨረሻው ድረስ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለማመን እምቢተኞች እንደሆኑ አየሁ ይህም ብቻ አይደለም እኛንም ደግሞ ተቃወሙን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የእውነትን ብርሃን ስላበራን ጠሉን።

አጋር ምዕመናኖቼ በብሉይ ኪዳን ለመስዋዕት በሚቀርበው

እንስሳ ራስ እጆች መጫኑ በአዲስ ኪዳን ዘመን ኢየሱስ ከተቀበለው ጥምቀት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ መረዳት አለባችሁ በዚህም ማመን ይገባችኋል በአጭሩ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መረዳትና እርሱንም በልቦቻችሁ ማመን አለባችሁ የሐጢያቶቻችሁን ስርየት መቀበል የምትችሉት በኢየሱስ ደም ብቻ አይደለም የሐጢያቶቻችሁን ስርየት የምታገኙት በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ በእነዚህ በሁለቱ መንፈሳዊ እውነቶች ነው::

በብሉይ ኪዳን ዘመንም እንደዚሁ ግርዘትና የፋሲካው ጠቦት ደም ነበሩ:: (ዘጸአት 12:3-7, 43-49)

ኢየሱስ በውሃ ብቻ አልመጣም እርሱ የመጣው በውሃ በደምና በመንፈስ ነው መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ይመሰክራል ውሃውና ደሙም የኢየሱስን ጥምቀትና መስቀሉን ይመሰክራሉ ደህንነታችንን ያገኘነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር ሲመጣ በቃሉ ተስፋ እንደሰጠው በጥምቀቱ አማንይነት ሐጢያቶቻችንን ወሰደ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሐጢያት መንጻት ኢየሱስ የተቀበለውን ጥምቀት ይመሰክራል ኢየሱስ ያፈሰሰው ክቡር ደም ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ የተሸከመውን የሐጢያት ኩነኔ ይነግረናል::

የኢየሱስ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን የመስዋዕት ስርአት ውስጥ ተስፋ የተሰጠ ነው ኢየሱስ የተቀበለው ይህ ጥምቀት ድንገተኛና በአጋጣሚ የሆነ ክስተት ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በተገለጠው የእግዚአብሄር ተስፋ መሰረት የተፈጸመ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ የተቀበለው ጥምቀት የደህንነት ማረጋገጫ አለመሆኑን የሚያሳይ አንዳች መረጃ ማቅረብ የሚችል ሰው የለም ስለዚህ

እኛ ከእነርሱ መለየታችን የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው ከእነርሱ የተለየነው እምነታችን ከእነርሱ ስለሚለይ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰጥቶን አሁን ብርሃን ስለሆንን ከእነርሱ ተለይተናል።

በዚህች ምድር ላይ ሌሊቱ የሚመጣው እንዴት ነው? ሌሊቱ የሚመጣው ጸሐይ ወደ ሌላው የፕላኔቷ አቅጣጫ ስለምትዞር ነው አይደል? ቀኑ ሲነጋ የሚነጋው በጸሐይ ምክንያት ነው ስለዚህ ቀንና ሌሊትን የሚወስነው ምንድነው? ሙሉ በሙሉ የጸሐይ ብርሃን ነው አጋር ምዕመናኖቼ እኛ በኢየሱስ ብናምንም ዳግም ካልተወለዱ ሰዎች መለየት የምንሻው በራሳችን ፈቃድ አይደለም ነገር ግን ከእነርሱ የለየን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በእውነት ምክንያት መልካም የሆኑ የሰው ግንኙነቶች በሚፈርሱበት ጊዜ ያንን መሸከሙ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ግልጽ ነው ነገር ግን በእግዚአብሄር ቃል መሰረት መለየት ያለበት በግልጽ መለየት አለበት።

ልጆች ካሬ የሚባል ጨዋታ በሚጫወቱበት ጊዜ በመሬት ላይ መስመሮችን ያሰምራሉ ለጥቂት ጊዜ ከተጫወቱ በኋላ መስመሮቹ ይጠፋሉ ያን ጊዜ ልጆቹ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ሲሉ መስመሮቹን ደግመው ያሰምራሉ በጨዋታው ሁሉ ውስጥ መስመሮቹ ሲደበዝዙ እንደገና መስመሮቹን ደጋግመው ያሰምራሉ።

ልክ እንደዚሁ እኛም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ናመንን በኋላ የመለያውን መስመር ደግመን ደጋግመን ማስመር አለብን በውሃወቅና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከተቀበልንም በኋላ እንኳን በየጊዜው የሚለያውን መስመር ማስመር አለብን አለበለዚያ ግራ እንጋባለን ጥቂት ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት መቀበላቸውን የሚያረጋግጠውን የደህንነት መስመር

ለማስመር ብዙ አመታቶች ይወስድባቸዋል።

እናንተስ? የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ከተቀበላችሁ በኋላ አንድ ጊዜ ብቻ መስመሩን ለማስመር ምን ያህል አመታቶች ወሰዱባችሁ? የእግዚአብሄርን ስራ በትክክል መስራት የሚችሉት ይህንን የደህንነት መስመር በግልጽ ያስመሩ ሰዎች ናቸው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የሚስፋፋው ይህንን ስራ መስራት በሚችሉት በእነዚህ ሰዎች አማካይነት ነው።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን በየጊዜው የደህንነትን መስመር ማስመር እንችላለን

ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጣችን ሲኖርና እኛም ብርሃኑን ስናበራ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ቀኑ ከሌሊቱ ይለያል በሌላ አነጋገር የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በልቦቻቸው ውስጥ የተቀበሉ ሰዎች አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች ሆነው ከቀሩትና ይህንን ለመቀበል እምቢተኞች ከሆኑት ተለይተው ጻድቃን ናቸው እኛ የእግዚአብሄር አገልጋዮች የሆንን ሰዎች ልዩነቱን በግልጽ ማድረግ ያለብን ለዚህ ነው አሁን ይህ ገባችሁ? ሰው እንዴት እንደሚያምን ግድ የማይሰጠን ጥሩ ልብ ያለን ጎረቤታሞች የሆንን ይመስል ልበ ሰፊ ታጋሾች መሆን አንችልም ሌሎች ሰዎች ስለ እኛ የሚናገሩትን ቢናገሩም በዳኑትና ባልዳኑት መካከል የመለያ መስመር ማስመር አለብን እግዚአብሄር *«አባቶችህ የሰሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት ኣታፍልስ» (ምሳሌ 22:28)* ይላል ነገር ግን የክርስትናን ታሪክ ስንመለከት የድንበር ምልክቱ ቀድሞውኑም ፈልሶዋል ድንበሩም ጠፍቷል።

የደህንነትን ድንበር የምናጸናው በምንድነው? ይህ

የሚወሰነው ሰው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ወይም አለማመኑ ነው ነገር ግን በ313 ኤ.ም ከወጣው የሚላን ድንጋጌ ጀምሮ ብሄራዊና አለማዊ የሆነው ክርስትና «በኢየሱስ ለማመን እግሩን ወደ ቤተክርስቲያን ያስገባ ማንኛውም ሰው መጠመቅ አለበት» የሚል ስርአት ደነገገ እግዚአብሄር ለእምነት አባቶች ያጸናውንም የድንበር ምልክት አስወገደ በዚህ ምክንያት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክርስትና ታሪክ በስሙ እግዚአብሄርን መቃወሙን ቀጠለ።

የዚያ ዘመን ሰዎች የደህንነትን ድንበር በወንጌል እውነት አቁመው በግልጽ ጠብቀውት ቢሆን ኖሮ የዘመኑ ክርስቲያኖች በሙሉ ፍጹም በሆነው እውነት ውስጥ ይገኙ ነበር ይህ ቢሆን ኖሮ ምንኛ ድንቅ በሆነ? ነገር ግን ንጉሰ ነገስት ቆስጠንጢኖስ ስልጣንን ለመጨበጥና አገዛዙን ለማጽናት ሲል ክርስትና ሊጠቀም ፈለገ ስለዚህ የሚለየውን የቤተክርስቲያን ስልጣን አስወግዶ እምነቱ ምንም ይሁን ማንኛውንም ሰው እንድትቀበል አደረገ።

አጋር ምዕመናኖቼ ልዩነትን ካላደረግን እንበላሻለን እውነት ቀስ በቀስ ሲደንዝ መበላሸቱን ለመከላከል ምንም ማድረግ አይቻልም በልቦቻችሁ ውስጥ ግልጽ መስመር ማስመር ያለባችሁ ለዚህ ነው ይህንን መስመር ለሌሎችም ደግሞ ማስመር አለባችሁ እኛ የእግዚአብሄር አገልጋዮች በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት ከተቀበልን በኋላ በየቀኑ ይህንን የደህንነት መስመር አስምረናል።

ያለፉትን ስብከቶቼን ለማደራጀትና በመጽሐፍ መልክ ለማሳተም ሳዘጋጅ የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀትና ደሙን ያላወራ አንድም ስብከት እንደሌለ ተረዳሁ በስብከቶቼ ሁሉ ላይ የተለመደው አንዱ ነገር ሁሉም የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀትና ደሙን የሚናገሩ መሆናቸው ነው ይህ ሆኖ እያለ እኔ በኢየሱስ

ክርስቶስ ጥምቀት በተደጋጋሚ የደህንነትን መስመር ባሰምርም አንዳንድ ሰዎች አሁንም ድረስ የደህንነትን መስመር በግልጽ አላስመሩም ስለዚህ አልፎ አልፎ የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን ትተው የወጡ አንዳንዶች ነበሩ እኔ በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ የደህንነትን መስመር ብዙ ጊዜ ያሰመርሁ ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች አሁንም ድረስ የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት በልቦቻቸው ውስጥ አልተቀበሉም።

እነዚህ ሰዎች መሪዎቻቸው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የደህንነትን መስመር በግልጽ ቢያሰምሩና ይህም መስመር የተሰመረው በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተመስርቶ ቢሆንም በራሳቸው አስተሳሰቦች ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ የተቀበለው ጥምቀት ለደህንነታቸው አስፈላጊ ክፍል እንደሆነ አያምኑም እነዚህ ሰዎች «እንዲህ ያለ ትንሽ የሚሸን ድርጅት በሁሉም ነገር እንዴት ትክክል ሊሆን ይችላል?» ይላሉ ይህም ብቻ አይደለም ወንጌልን በግልጽ ሲቃወሙም አይቻለሁ ትክክለኛውን እውነት መለየት አይችሉም መንፈስን ከስጋ መለየት የማይችሉት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለማያምኑ ነው።

ብዙ ሰዎች የወንጌልን እውነት ከሰሙ በኋላ «ሰው የሚድነው በውሃና በደም በማመኑ ብቻ አይመስለኝም ሰው በኢየሱስ ደም ብቻ ቢያምን እንደሚድን አምናለሁ» ይላሉ ይህ የሆነበት ምክንያት ብዙ የክርስቲያን ቤተክርስቲያኖች በዚህ ሁሉ ዘመን ደህንነት የሚገኘው የመስቀሉን ደም በማመን ብቻ ብለው በተሳሳተ መንገድ በመረዳታቸውና በተሳሳተ መንገድ በማመናቸው ነው እግዚአብሄር በአገልጋዮቹ አማካይነት በልቦቻችን ውስጥ ያሰመረውን የደህንነት መስመር መጠበቅ ያለብን ለዚህ ነው መደብዘዝ ሲጀምርም ደግመን ደጋግመን ልናሰምረው ይገባናል።

ነገር ግን ስጋችሁ በጣም ሲደክም ወይም ልቦቻችሁ በማናቸውም አጋጣሚ ሲያዝኑና በዚህ ምክንያት ሐጢያትን ስትሰሩ እምነታችሁን እርሱ በተቀበለው ጥምቀት ላይ በማኖር ሐጢያቶቻችሁ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተላለፉ መገንዘብ አለባችሁ እነዚህ ሁሉ ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የተላለፉት መቼ ነበር? የተላለፉት ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ አልነበረምን? ኢየሱስ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት ባይሆን ኖሮ የዚህ አለም ሐጢያቶች መደምሰስ ባልቻሉም ነበር ሐጢያቶቻችን በሙሉ የተደመሰሱትና የእግዚአብሄር ጽድቅ በሙሉ የተፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ባይጠመቅ ኖሮ ምንም ያህል ይህንን ከልቡ ቢፈልግም ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ሐጢያቶች የሚወስድበት ምንም መንገድ ባልኖረም ነበር እኛ ይህንን የደህንነት መስመር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በግልጽ ማስመር አለብን፡፡

አጋር ምዕመናኖቼ «ክርስቶስ» የሚለው ስም «ቅቡዕ» ማለት ነው (ዮሐንስ 1:14 ፤ዳንኤል 9:25) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ነገስታቶች፣ ካህናቶችና ነቢያቶች ይቀቡ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን ሐጢያቶቻችንን የደመሰሰ ሊቀ ካህንና ትክክለኛውን እውነት የሚያስተምረን ነቢይ ነው ከእነዚህ ከሦስቱ አንዱን እንኳን አውጥቶ መጣል እግዚአብሄርን መዳፈር ነው፡፡

«ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን ነው እርሱ በጥምቀቱና በደሙ አድኖናል ብለን ስንሰብክ አንዳንድ ሰዎች «ያ ምንም የጠለቀ ነገር የለውም የእምነት መሰረታዊ ትምህርት ነው ይህንን የመጀመሪያ እውቀት ከምታስተምረን ይልቅ ይበልጥ መንፈሳዊ የሆነ ነገር አስተምረን» ይላሉ፡፡

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በትክክል እግዚአብሄርን

እየተቃወሙትና የኢየሱስ ክርስቶስ አካል የሆነችውንን ቤተክርስቲያን እየናቁ ነው እግዚአብሄርን ይበልጥ በጥልቀት ማወቅ አስፈላጊ መሆኑ እርግጥ ነው ሆኖም ይህ ሊሆን የሚችለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስናድግ ብቻ ነው ነቢያቶች ሆነን ሚናችንን መፈጸምና ስለ እግዚአብሄርም እውነት ብዙ መማር የምንችለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ብቻ ነው እግዚአብሄር በዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወነጌል አማካይነት ስለተገናኘንና አሁን እግዚአብሄር በዚህ ወንጌል አማካይነት አምላካችን ስለሆነ ሊሆኑ ስላሉት ነገሮችም ደግሞ ያስተምረናል።

መንፈሳዊ ጦርነታችንን ለመዋጋት መጀመሪያ ምን ማድረግ ይገባናል?

በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄር እንዲህ ብሎዋል *«ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች፣ ለዘመኖች፣ ለዕለታት፣ ለአመታትም ይሁኑ»* በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ጻድቃንን ከሐጢያተኞች በግልጽ እንደሚለይ እየተናገረ ነው ይህ ቁም ነገር አስፈላጊ ነው።

እዚህ ላይ ጦርነት ፈነዳ እንበል የጠላት ወታደሮች ገና ሩቅ ሳሉ ጠመንጃዎቻችንን ተኮስንባቸው ነገር ግን ጠመንጃዎቻችን ይበልጥ ጥቅም ላይ እስኪውሉ ድረስ በጣም ከተጠጉ በኋላ የጨበጣ ውጊያ ውስጥ እንገባለን ሳንጃችንን አስገብተን ወደ ጠላት ወታደሮች እንሄዳለን ምንም ነገር ቢሆን ትኩረታችንን ጦርነቱን በማሸነፍ ላይ አድርገን በሳንጃ እንወጋቸዋለን በጠመንጃም እንገድላቸዋለን።

ነገር ግን የጠላት ወታደሮች ከእኛ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ወታደራዊ ልብሶችን ቢለብሱስ? እነርሱን ከእኛ ወታደሮች ልንለያቸው የምንችለው እንዴት ነው? ጠላት ይሁን ወይም የእኛ ሰው ሳናውቅ እንዴት ማንንም ሰው እንወጋለን? ይህንን ማድረግ አንችልም የወታደር ልብሶቻችን ከጠላት ወታደሮች ልብስ በግልጽ መለየት ያለበት ለዚያ ነው በአውደ ውጊያ ላይ ወታደሮች የሚመለከቱት ልብስን ነው ልቡ የተለየ ከሆነ ምንም ጥያቄ ሳይጠይቁ ሳንጃቸውን ይወድራሉ ከበላይ ለመጣ ትዕዛዝ እንኳን ግድ የላቸውም ልብሱ የተለየ ከሆነ በሳንጃቸው ይወጋሉ በዚህ ጊዜ የእኛ ወታደር የጠላትን ልብስ ከለበሰ የራሳችንን ሰው ከመውጋት አንመለሰም በሌላ አነጋገር መንፈሳዊ ጦርነታችንን መዋጋት ያለብን እግዚአብሄር የዳኑና ያልዳኑ ሰዎች ብሎ በለየው ግልጽ የሆነ ሁኔታ አማካይነት ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ብቸኛው እውነት ነው የእርሱ ቃል ለዚህ ምድር ብርሃንና እውነት ነው የሰው አስተሳሰቦች ወይም ቃሎች እውነት አይደሉም እውነቱ ምን ይነግረናል? ቀኑን ከሌሊቱ ለመለየት በጠፈር ላይ ብርሃን ይሁን ይላል ቀኑ ከሌሊቱ እንዲለይ አዞዋል የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎችን ካልተቀበሉ ሰዎች መለየቱ ተገቢ ነው በዚህ አለም ላይ ቀንና ሌሊት እንዳለ ሁሉ እነዚህን ሰዎች ሁሉ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉና ያልተቀበሉ አድርገን በግልጽ እንድንለይ አዞናል በሌላ አነጋገር እኛ በእርግጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ከሆንን እግዚአብሄር ይህንን የሚለይ የእግዚአብሄር ስራ እንድንሰራ እያዘዘን ነው።

ልንገነዘበው የሚገባን አንድ ተጨማሪ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ የታሪክ ባለቤት መሆኑን ነው የዚህ አለም ታሪክ በእርሱ ይደመደማል እግዚአብሄር «ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች፣ ለዘመኖች፣

ለዕለታት፣ ለአመታትም ይሁኑ» ብሎዋል የዚህ አለም ሳይንሳዊ ዕድገት ምንም ያህል የተራቀቀ ቢሆንና በዕብሪት የተሞላው የሰው ዘርም ምንም ያህል እግዚአብሄርን ቢገዳደር ይህ አለም ሰማያትንና ምድርን በፈጠረው በኢየሱስ ወደ ፍጻሜ ይመጣል ይህ እግዚአብሄር የተናገረው እውነት ነው።

የነገር ሁሉ ጅማሬና ፍጻሜ፣ ምልክቶች፣ ዘመኖች፣ ዕለታትና አመታቶች የዚህ አለም እያንዳንዱ ነገር የሚጠናቀቀው በማነው? እያንዳንዱ ነገር የሚጀምረው፣ የሚቀጥለውና የሚፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ተመላሽ ጌታ ሆኖ ወደዚህ ምድር ሲመጣ ይህ አለም ያበቃል።

ጌታ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደዚህ ምድር ሲመጣ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ደምስሶ ወደ ሰማይ አረገ ነገር ግን እርሱ በቅርቡ እንደገና ይመጣል እርሱ ሲመጣ የመጀመሪያው ያበቃና ሁለተኛው አለም ይጀምራል ይህ ገብቶዋችኋል? በዚያን ጊዜ የሺህው አመት መንግስት ይመሰረታል በታሪክ ጅማሬና ፍጻሜ ሁሉ ላይ የሚሰለጥነው ማነው? በዚህ ሁሉ ላይ ለመሰልጠን ስልጣን ያለው ማነው? ይህ ስልጣን ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የእግዚአብሄር ቃል በግልጽ የሚናገረው ይህንን ነው።

ይህ አለም ይለወጥ ይሆናል የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ግን አይለወጥም ኢየሱስ ክርስቶስ የነገረን ቃል መቼም ቢሆን አይከስምም ነገር ግን ሁሉም ይፈጸማል እግዚአብሄር *«ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ» (ማቴዎስ 5:18)* ይላል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በተናገረው ቃሉ ሁሉን ይፈጽማል እያንዳንዱን ነጥብና እያንዳንዱን ፊደል ይፈጽማል።

አጋር ምዕመናኖቼ እያንዳንዱ ሰው ወደ አፈር ከመመለሱ

በፊት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለበት ሁላችንም ከአፈር ስለተፈጠርን ሁሉላችንም ወደ አፈር እንመለሳለን ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሄር ሲፈጥረን ከእፍኝ አፈርና ከቃሉ ስለፈጠረን ነው ለዘላለም የማይለወጠው እውነት ፈጽሞ አይከስምም ሳይንስ ምንም ያህል ቢራቀቅም፣ ምንም ያህል አመጋገባችንን በጥንቃቄ ብንቆጣጠርና ምንም ያህል ሳይንስ አዳዲስና አስገራሚ መድሃኒቶችን ቢያመርትም ስንሞት አፈር ሆነን እንቀራለን።

እግዚአብሄር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያደረገውን መለወጥ አንችልም ጌታ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ያዳነን የመሆኑን እውነታ ማመን አለብን የእርሱ ምስክሮችም በዚህ ምድር ላይ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ማወቅ አለባቸው ይህንንም ስራ በእምነት መፈጸም አለባቸው አሜን! ✉

እግዚአብሄር የክብር ዕቃዎች አድርጎናል

« ዘፍጥረት 1:16-19 »

«እግዚአብሄርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ እግዚአብሄርም በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው በቀንም በሌሊትም እንዲሰለጥኑ ብርሃንና ጨለማንም እንዲለዩ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አራተኛ ቀን::»

እግዚአብሄር ለዚህች ምድር ብርሃንን ለመስጠት በሰማይ ላይ ከዋክብቶችን ፈጠረ ዛሬ እግዚአብሄር የፈጠራቸው ከዋክብቶች ስለሚጫወቱት ሚና ልነግራችሁ እወዳለሁ እግዚአብሄር ከዋክብቶችን ፈጠረ ማለት እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ሰራተኞቹን ፈጠረ ማለት ነው::

በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ሕዝብ የመገናኛውን ድንኳን ለመስራት ወርቅ አምጥተው ለእግዚአብሄር አቀረቡ ከዚህ ወርቅ ውስጥ አንዳንዱ ተቀጥቅጦ መቅረዝ ተሰራበት ሌላው ደግሞ የወርቅ ዕቃዎችና ማንኪያዎች ተሰሩበት የእግዚአብሄር ሕዝብ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚያገለግሉትን ዕቃዎች እንደሰሩ ሁሉ እግዚአብሄር አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለምናምነው ለእናንተና ለእኔ እውነተኛ እምነትን ሰጥቶናል የእርሱ አገልጋዮች ሆነን ለማገልገልም አንዳች ነገር እንዳይጎድለን ልቦቻችንን አንጽቶዋቸዋል እኛ አሁን

በእግዚአብሄር ቃል ስለሰለጠንን የእምነት ሰዎች የእግዚአብሄር ሰራተኞች ሆነን ተቀርጸናል።

እግዚአብሄር ለመንግስቱ የምናገለግል ጠቃሚ ሰራተኞቹ እንድንሆን ልጆቹን ሊቀርጸን ይሻል ስለዚህ እግዚአብሄር በሕዝቡ ላይ የተለያዩ ሁኔታዎች እንዲከሰቱ ሲፈቅድ እናያለን በእነዚህ የተለያ ሁኔታዎች አማካይነት እግዚአብሄር ለእርሱ ትክክለኛ መጠቀሚያ መሳሪያዎች ሆነን እስክንቀረጽ ድረስ እናንተንና እኔን ያተራናል።

አንድ ቀራጺ ሐውልት ሲቀርጽ ሐውልቱን በመቅረጫ ሴንጢ ይቀርጸዋል ወይም በመሮ ይፈረፍረዋል አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ ቁርጥራጮችን አንድ ላይ ይለጥፋቸዋል ሌላ ጊዜ ደግሞ ይሰባብራቸዋል በዚህ ሁሉ ሒደት ውስጥ ሐውልቱን እርሱ በሚፈልገው መንገድ ይቀርጸዋል እግዚአብሄርም እንደዚሁ ቅዱሳኖችን በዚህ መንገድ ይርቀጻቸዋል እግዚአብሄር ጠቃሚ መሳሪያዎቹ አድርጎ ይቀርጻቸው ዘንድ አስፈላጊ በሆኑ ሒደቶች አማካይነት ያሰለጥናቸዋል እግዚአብሄር ራሳቸውን መካድ የማይችሉ ሰዎችን ራሳቸውን መካድ በሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ በማሳለፍ ያንን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል አብዝቶ እንዲጠቀምባቸውም ያድሳቸዋል እግዚአብሄር ቃሉን ስለሰጠን ቃሉን እንዴት በእምነት እንደምንከተልም ያሳየናል እግዚአብሄር እርስ በርሳችን እንድንጣጣም እያሰለጠነን ነው።

እያንዳንዳችን በእግዚአብሄር ፊት ስጋዊ አስተሳሰቦቻችንን መጣልና ቃሉን ማመን አለብን አሮጌውን ነገሮቻችንን ለማቆየት የምንፈልገው የራሳችን አስተሳሰቦች ስላሉን ነው እግዚአብሄር ግን ስጋዊ አስተሳሰቦቻችንን መለወጥ ይፈልጋል እግዚአብሄር በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ራሳችንን እንድናገኝና የተለያዩ ሁኔታዎችን እንድንጋፈጥ የሚፈቅድልን ለዚህ ነው በዚህም እንከን ያለባቸውን አስተሳሰቦቻችንን ይሰባብርና የእግዚአብሄርን

ቃል እንዴት እንደምናምንና እንደምንከተል ያሳየናል እግዚአብሄር አሮጌውን ማንነታችሁን መጠቀም አይፈልግም ነገር ግን እርሱ የሚፈልገው አይነት ዕቃዎች አድርጎ ሊቀርጻችሁና የታደሰውን ማንነታችሁን ሊጠቀምበት ይሻል።

በሌላ አነጋገር የእኛ አስተሳሰቦች ከእግዚአብሄር አስተሳሰቦች የተለዩ ናቸው ከስጋዊ አስተሳሰቦቻችን የቀሩልን ነገሮች ቢኖር እስከ አሁን ድረስ የተለማመድናቸው ነገሮች ናቸው እግዚአብሄርን በራሳችን ስጋዊ አስተሳሰቦች ልንቀርበው እንሞክራለን በእምነት ለመለወጥ እግዚአብሄርን በእውነተኛው ማንነታችሁ ከመቅረብ ይልቅ በደመ ነፍስ ራሳችሁን ለመከላከል ትሞክራላችሁ ነገር ግን እግዚአብሄር ከእኛ የሚፈልገው ይህንን አይደለም።

እግዚአብሄር እንዲህ አለ «ከሰማይ በታች ያለው ውሃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ» እግዚአብሄር በየብሱ ላይ ዘሮችን ዘራ እነዚህ ዘሮች እንዲበቅሉ፣ እንዲያድጉና እርሱ የሚፈልገውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እንዲያፈሩ ፈለገ እግዚአብሄር ክፉው ተፈጥሮዋችን በሙሉ እንዳለ እንዲገለጥ ይፈልጋል ክፉውን ማንነታችንንም እንድናይ፣ እንደ እኛ ላሉ ክፉ ሰዎች የሰጠውን ጸጋ እንድናምንና የጽድቅ ሕይወትን እንድንኖር ይፈልግብናል።

ስለዚህ እግዚአብሄር በቃሉ ሊያድሰን ይፈልጋል በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄር ከዋክብቶችን ፈጠረ ማለት እኛን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምነውን አማኞች የእርሱ አገልጋዮች ሊያደርገንና መሳሪያዎቹ አድርጎ ሊጠቀምብን ይፈልጋል ማለት ነው ራሳችሁን በማናቸውም ሁኔታዎች ውስጥ ብታገኙ እግዚአብሄር የሚናገረውን በጥንቃቄ ማድመጥና እርሱንም በእምነት መከተል የሚገባችሁ ለዚህ ነው ምክንያቱም እግዚአብሄር በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ

የሚችሉ አገልጋዮቹ አድርጎ እየቀረጸን ያለው ለዚህ ነው ጌታ እንዲህ ይላል *«በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል» (ምሳሌ 3:6)*

እግዚአብሄር ፈቃዱን በቃሉ ገልጦዋል

እግዚአብሄር በምንም አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ቢመራን ይህ ሐ.ደት እግዚአብሄር እኛን የከበሩ ዕቃዎቹ አድርጎ ሊለውጠን እንደ ፈቃዱ የሚሰራበት ነው ስለዚህ እናንተና እኔ ልናደርገው የሚገባን መልካም የሆነው ነገር በተቻለ ፍጥነት የእግዚአብሄርን ቃል በእምነት መከተል ነው በተፈጥሮ እናንተና እኔ የስጋችንን መሰበርና በእምነት አዲስ መሆን አንወደውም ነገር ግን እግዚአብሄር ከእኛ ትዕግስትን ሲጠብቅና ራሳችንን እንድንክድ ሲጠብቀን በእምነት እንደዚያው መታዘዝ አለብን ያንን ለማድረግ እግዚአብሄር በቃሉ ጉድለቶቻችንን ይሞላል የስጋችንንም ጽድቅ ይሰብራል የእርሱን ስራ በእምነት የሚሰሩ ሰዎች አድርጎም ይቀርጸናል ስለዚህ ፈጥነን «እግዚአብሄር ሆይ እኔ እንደዚህ ክፉና ጎዶሎ ነኝ» ብለን በመናዘዝና እንደ እኛ ላሉ ሰዎች ጸጋውን የለገሰንን የእግዚአብሄር ቃል በማመን የእምነት ሰዎች መሆን አለብን በእግዚአብሄር ቃል ላይ ባለን እምነት ጸንተን መቆም አለብን::

እግዚአብሄር ፈቃዱ እስኪፈጸም ድረስ ሳይታክት እኛን በመቅረጽ ይቀጥላል በልቦቻችን ውስጥ ስጋዊ ቆሻሻዎች ካሉ ያስወግዳቸዋል ሰብአዊ ጽድቃችንንም ይሰብራል እግዚአብሄር ጽድቃችንን ሲሰብር «አሁን መኖሬ አበቃ» ብለን ወደ ማሰብ እናዘነብላለን ነገር ግን የስጋ ጽድቅ ከተሰበረ በኋላ በእግዚአብሄር ጽድቅ ብቻ ተማምነን እንኖር ዘንድ እግዚአብሄር ሐይልን

የተሞላ እምነት ሰጥቶናል ይህ በእግዚአብሄር ቃል ላይ የተመሰረተ ብርቱ እምነት ነው።

በራሳችን ጽድቅ የእምነት ሕይወታችንን ለመኖር መሞከር በጣም አስቸጋሪ ነው ነገር ግን የስጋችን ጽድቅ ከተሰበረ በኋላ የምንኖረው በእግዚአብሄር ጽድቅ እንደሆነ ራሳችን መለማመድ እንችላለን በመጨረሻም እንደ እግዚአብሄር ፍላጎት እንበጃለን እርሱም መሳሪያዎቹ አድርጎ ይጠቀምብናል በእግዚአብሄር ፊት መቀረጻችን ለእኛ በረከት ነው በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ እምነት ሳይኖረን መኖራችንን እግዚአብሄር ለሁላችንም አዳጋች አድርጎታል ልክ እንደ መስተዋት ዕቃዎች የከበሩ እንደሆኑ የሚያስመስሉ ሰዎችን እግዚአብሄር ክቡርነታቸውን ይሰብረዋል ፈቃዳቸው ልክ እንደ አለት ግትርና ጠንካራ የሆኑትን ሰዎችም ግትርነታቸውን እንዲያስወግዱ ያለሰልሳቸዋል በእግዚአብሄር ቢያምኑም አሁንም ድረስ ከዚህ አለም ጋር ብዙ ቁርኝቶች ካሉዋቸው ሰዎች የዚህን አለም ውሃ ያደርቃል።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሄር የጋለ ሙቀትን መቋቋም የማይችልን ሰው ሚሲዮናዊ አድርጎ ወደ አፍሪካ ይልከዋል ራሳችንን በምናገኝበት በማንኛውም ስፍራና በማንኛውም ጊዜ በቀዝቃዛ ስፍራም ሆነ በሙቀት ስፍራ የእግዚአብሄርን ስራ መስራት መቻል አለብን ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎዋል *«መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ» (ፊልጵስዩስ 4:12)* ከዚህም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ለመሆን ምን ያህል በታማኝነት በእግዚአብሄር እንደሰለጠነ ማየት እንችላለን።

ሁላችንም ልናስታውሰው የሚገባን ነገር ቢኖር ምንም አይነት ሁኔታዎች ቢገጥሙን በእግዚአብሄር ቃል ማመንና እርሱንም መታዘዝ አለብን በእግዚአብሄር ፊት ትክክለኛ

መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የምንፈልግ ከሆነ የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን መቀበል አለብን የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን የማንቀበል ከሆንንና በራሳችን ስጋዊ ጥበብ ወይም ጽድቅ ለመኖር የምንሞክር ከሆንን እግዚአብሄር ሁሌም ይሰብረናል እግዚአብሄር ልቦቻችን የእኛ የሆነ ምንም ነገር እንዳይኖራቸው ነገር ግን የእርሱ ቃል ብቻ በእነርሱ ውስጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ ይፈልጋል በእርሱ ቃል ብቻ ተሞልተን እርሱን ከልባችን የምናገለግለው አይነት ሰራተኞች እንድንሆን ይፈልጋል ዛሬም ቢሆን እግዚአብሄር ለራሱ እየቀረጸን ያለው ለዚህ ነው ስለዚህ የስጋችን ጽድቅ ስለመሰበሩ መፍራት አያስፈልገንም።

እግዚአብሄር የሚደሰትበትን ስራ መስራት እንድንችል የስጋ ጽድቃችን በእግዚአብሄር ፊት መሰበር አለበት በእግዚአብሄር ፊት በስጋዊ ግትርነታችን መጽናት አያስፈልገንም በፋንታው በእግዚአብሄር ቃል ልናምን ልቦቻችንን በእርሱ እውነት ልንሞላና ወንጌሉን በምድር ሁሉ የሚሰብኩ የታመኑ ሰራተኞች ሆነን ልንለወጥ ይገባናል ይህንን ለማድረግ የእግዚአብሄርን ቃል በእምነት በልቦቻችን ውስጥ መቀበል ይገባናል የእግዚአብሄርን ቃል ካልተቀበልን በስተቀር ልቦቻችን ሊለወጡ አይችሉም መንፈሳዊ ለውጥ የምናገኘው የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ስንቀበልና ይህንን የእግዚአብሄር ቃል ስንይዝ ብቻ ነው እግዚአብሄር በነጻነት ሊጠቀምብንና ስራውን በአደራ ሊሰጠን የሚችለው የእምነት ሰዎች ስንሆን ብቻ ነው።

እስከ ዛሬ ድረስ የእምነት ሕይወቴን ስኖርና በዚህ ሁሉ ጊዜ ጌታን ስከተል እግዚአብሄር ያደረገልንን በማየት ብዙ ጊዜ ተገርሜአለሁ እግዚአብሄር ምን ያህል በሚገባ እንደሚያውቀኝና እንዴት በሚገባ እንዳሰለጠነኝ ሙሉ በሙሉ ተረድቻለሁ

እግዚአብሄር ልቤን ያውቀዋል የሚመራኝም በተሟላው በዚህ መረዳት ነው ልቤ ስፍራውን በለቀቀ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሄር እኔን የወቀሰባቸውና ውድቀቶቼን የጠቆመባቸው ብዙ ልምምዶችም አሉኝ።

አጋር ምዕመናኖቼ እግዚአብሄር አገልጋዮቹ አድርጎ እየቀረጻችሁ ነው እግዚአብሄር የራሱ ሕዝብና አገልጋዮቹ ሊያደርጋችሁ ሲፈልግ አንዳች ተቃውሞ ሊኖር ይችላልን? በእርግጥ አይችልም! በሚሽን ትምህርት ቤት ውስጥ ባሉት ተማሪዎቻችን መካከል አንዳንድ ባለትዳር ጥንዶችም ደግሞ አሉ ባለትዳር ጥንዶች አንድ ልብና አንድ አካል ቢሆኑም እግዚአብሄር ባልንና ሚስትን የሚቀርጻቸው ለያይቶ ነው።

እናንተ እዚህ ሚሽን ትምህርተ ቤት ውስጥ የመጣችሁት በእግዚአብሄር እንድትታደሱ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋችኋል የእግዚአብሄር ሰዎች የእርሱን ስራ ጠንክረው እንደሚሰሩ እርግጥ ነው እኛ ሁሌም ቀንና ሌሊት እንሰራለን ስለ ነገውም ስራ እናስባለን በዝርዝር ስናቅድና ስንሰራም በአእምሮዋችን ውስጥ የእግዚአብሄርን ፈቃድ የማገልገል ጠቅለል ያለ አላማ አለን ስለዚህ የሚያስፈልጉት ምን ያህል ሰራተኞች ናቸው? እኛ እዚህ የመጣነው እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ መጠቀሚያ የሚሆኑ ዕቃዎች ለመሆን ነው ለእግዚአብሄር ስራና ለመንግስቱ ግንባታ መጠቀሚያ ለመሆን የምንሻው ለዚህ ነው።

የእርሱ አገልጋዮች ስትሆኑ በመጀመሪያ አሮጌው ማንነታችሁ እንደሞተ በማመን ቃሉን ማመንና መያዝ አለባችሁ እግዚአብሄር የእርሱ ሰራተኞች እንዲያደርገን የምንፈልግ ከሆነ ከሁሉም በላይ በቃሉ ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል የእግዚአብሄርን ቃል አጥብቀን መያዝ እምነታችንን በእርሱ ላይ ማኖርና ለእግዚአብሄር ጥቅም የሚመቹ ሰራተኞች ለመሆን መናፈቅ ይገባናል ጌታችንና እኛ መርካት የምንችለው

በእግዚአብሄር የእምነት ሰዎች ለመሆን ራሳችንን በፈቃደኝነት አሳልፈን ስንሰጥ ብቻ ነው ጌታችን ሊጠቀምብን ሲቀርጸን ተረጋግተን መቀረጽ ይገባናል አለበለዚያ ይህ ረጅም ጊዜ ይወስዳል ጌታም አይደሰትም እኛ በእግዚአብሄር ፈቃድ መሰረት መቀረጽ ስላለብን መታዘዝ ያስፈልገናል።

አንድ ቀራጺ አንዲት የወርቅ ቁራጭን ማንኪያ አድርጎ ሊሰራት ሲፈልግ ቁራጭዋ «ዋይ! ያማል!» ብላ ብትጮህና በተቀጠቀጠች ቁጥር ቱር ብላ ብትበር ቀራጺው እንደማይደሰት ግልጽ ነው የወርቅ ቁራጭዋ መቀረጽ እምቢ ብላ ቀራጺው በአእምሮው ባሰበው መሰረት በአንድ ቅርጽ ሊሰራት በቀጠቀጣት ጊዜ ሁሉ ቱር ብላ የምትፈናጠር ከሆነ ሁሉም ተቀጥቅጦ እስከሚስተካከል ድረስ አብዝቶ ከመቀጥቀጥ በቀር ምርጫ አይኖረውም ይህ ወርቅ በቀራጺው መቀረጽ አለበት ጉዳት ስለሚደርስበት እንዴት ቱር ብሎ ሊፈናጠር ይችላል? አንድ የወርቅ ቁራጭ ለባለቤቱ ጥቅም የማይስማማ ከሆነ ሕይወቱ ያከትማል።

ስለዚህ ስቃይ ቢኖርም ጌታችን ሲቀርጸን የእርሱን ፈቃድ አብዝተን በማሰላሰል ልንቋቋመውና ጌታን ልንከተል ይገባናል በጌታ ፊት «እንዲህ የምሰቃየው፣ የምቸገረውና የምሳቀቀው ለምንድነው?» ብለን ስናሰላስል በጌታ መሰልጠን ማለት ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ስለምንችል ችግሮቻችንን በሙሉ መቋቋም እንችላለን በአሁኑ ጊዜ በሚሸን ትምህርት ቤት እየሰለጠኑ ያሉት ወንድሞችና እህቶች ከተራ ምዕመናኖች የተለዩ ናቸው።

የቤተክርስቲያን መሪዎች ምዕመናኖችን ኢምንት በሆነ ክንዋኔ ሊያመሰግኑዋቸው ያዘነብላሉ ነገር ግን ይህ የሆነበት ምክንያት እነዚህ ምዕመናኖች የእግዚአብሄር ሰራተኞች ባለመሆናቸው ነው ሆኖም ባደረጉዋቸው በጥቃቅን ነገሮች

እንኳን ይመሰገናሉ ሆኖም አሁን የእግዚአብሄር ሰራተኞች ሆነው እየሰለጠናችሁ ያላችሁ ሰዎች መመስገንን መጠበቅ አይገባንም የእግዚአብሄር የእግዚአብሄር ሰራተኞች እንድንሆን ባንደረግ ኖሮ አንዳች መልካም ነገር አለ? ምንም መልካም ነገር ነገር የለም ቅዱሳኖች በዚህ ምድር ላይ ያሉ ቅዱሳኖች እንጂ በሰማይ ላይ ያሉ ከዋክብቶች አይደሉም ከዋክብቶች በሰማይ ላይ ሆነው ቀንና ሌሊት ያበራሉ።

እግዚአብሄር ከዋክብቶችን በሰማይ ላይ እንደፈጠረ ሁሉ አሁን እኛም የእርሱ ሰራተኞች ለመሆን በእግዚአብሄር አዲስ ሆነን መፈጠር እንደሚገባን እናውቃለን አሁን እናንተና እኔ በሰማይ እንዳሉ ከዋክብቶች ሆነናል እግዚአብሄር በቃሉ ላይ እምነት የሌላቸውን ሰዎች እምነት እንዲኖራቸው ያስተምራቸዋል ስለዚህ እግዚአብሄር የተዋረደውን ያከብረዋል የከበረውንም ያዋርደዋል እግዚአብሄር የሚያደርገው ያንን ነው ለዚህ ምክንያቱ የከበሩትና የተዋረዱት ሁለቱም ባሉበት ከቀሩ መጠቀሚያ ለመሆን በጣም ያስቸግራሉ እግዚአብሄር ሊጠቀምባቸው ባሰበው መሰረት የሚቀርጻቸው ለዚህ ነው የተዋረዱ ሰዎች ባሉበት ሁኔታቸው ለከበሩ ሰዎች ወንጌል መስበክ ስለሚያዳግታቸው ክቡር ሆነው መለወጥ አለባቸው የከበሩ ሰዎችም እግዚአብሄር በነጻነት ይጠቀምባቸው ዘንድ ከመጠን በላይ የሚመጻደቁ በመሆናቸው ያዋርዳቸውና ወንጌልን እንዲሰብኩ ያደርጋቸዋል።

እግዚአብሄር በስልጣን ቃሉ እናንተንና እኔን እየቀረጸን ነው እኛ ይህንን ሁሉ አናውቅ ይሆናል እግዚአብሄር ግን ሁላችንንም እየቀረጸን ነው ነገር ግን የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ከተቀበላችሁ ጀምሮ ምን ያህል እንደተለወጣችሁ ወደኋላ መለስ ብላችሁ ስትመለከቱ እግዚአብሄር በእርግጥም በብዙ መንገዶች እንደለወጠን እንቀበላለን።

እግዚአብሄር ያለ ማቋረጥ የእርሱ ሰራተኞች አድርጎ እየቀረጸን ነው «እግዚአብሄር ያለ ፍላጎቴ ለምን እንደዚህ እንደሚያደርገኝ መረዳት አልቻልሁም እርሱ ፈጽሞ አያውቀኝም?» በማለት በእግዚአብሄር ላይ እያጉረመረማችሁ በዚህ ደስተኞች አይደላችሁምን? ነገር ግን እንደዚህ ያሉ አስተሳሰቦች በሙሉ የራሳችን ስጋዊ አስተሳሰቦች ናቸው።

እግዚአብሄር እኛን የማያውቅ አምላክ አይደለም በተቃራኒው እርሱ ሁሉን የሚያውቅ አምላክ ነው እርሱ ስለ እኛ እያንዳንዱን ነገር ያውቃል መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ በራሳችን ላይ ያሉትን ጠጉሮች እንኳን እንደሚቆጥር ይናገራል (ማቴዎስ 10:30) እንዲህ ያለ ሁሉን አዋቂ የእርሱ ሰራተኞች አድርጎ ሊቀርጸን እያጠራን ነው።

አሁን አስቸጋሪ ሁኔታዎች እየገጠሙዋችሁና እየተቸገራችሁ ነውን? እንደዚያ ከሆነ ይህ ሁሉ እግዚአብሄር በፈቃዱ መሰረት የእርሱ ሰራተኞች እንድንሆን የሚያደርግበት የሐደቱ ሁሉ ክፍል እንደሆነ እመኑ ጌታ አሁን ያለ ማቋረጥ እያጠራችሁ ያለው በመጨረሻ እናንተን የእርሱ አገልጋዮች ለማድረግ ነው እግዚአብሄር እኛን በተለያዩ አቅጣጫዎች ስለሚያሰለጥነን ጌታ በጊዜው የሰራቸው ዕቃዎች ሆነው በክብር ያገለግላሉ እርሱ ድህነትን እንድንቋቋም ያስተምረናል ሐብትንም እንድንቋቋም ያስተምረናል ሐብትን እንዴት እንደምንጠቀምበት የማናውቅ ከሆነ ባለጠጋ እንደሆንን ወዲያውኑ እምነታችን ያበቃለታል ስለዚህ ሐብትን እንዴት መቋቋም እንዳለብን ማወቅ ይገባናል የጌታን ስራ በመስራታችን ቁሳዊ የሐብት ብልጥግናዎችን ስናገኝ ከአለም ጋር የምንቀላቀል አይነት ሰዎች መሆን የለብንም በአንጻሩ ፈጥነው ከግትርነታቸው የማይመለሱ ሰዎች ነገር ግን በድንዳኔያቸው ድርቅ የሚሉ ሰዎች ይሰቃያሉ።

እያንዳንዱ ሰው ጌታን ሲያገለግል በብዙ መከራ ውስጥ እያለ ያለ ብቸኛ ሰው እርሱ እንደሆነ ያስባል ነገር ግን ሁሉም ሰው ችግሮች ይገጥሙታል እናንተና እኔም የእግዚአብሄርን ስራ ስንሰራ አስቸጋሪ በሆኑ ችግሮች ውስጥ እናልፋለን በችኮላ ስንመለከት አንዳንድ ሰዎች ጌታን በብዙ ምኞት በማገልገላቸው ዕድለኞች እንደሆኑ ያስባሉ ነገር ግን ጠጋ ብለን ስንመለከት ሁሉም በራሳቸው መንገድ እየታገሉ ነው አገልጋዮቻችንን ራሳቸውን ዝምተኞች ያደርጋሉ ነገር ግን በዚህ ብርሃን ስንመለከታቸው በሆኑ ጉዳዮች እየተንገላቱና በትልቅ ችግር ውስጥ እያለፉ እንደሆኑ እናያለን በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ውስጥ እግዚአብሄር እነዚህን አገልጋዮች ለሆነ አላማ እየቀረጻቸው ነው።

አሁን እናንተ በሚሽን ትምህርት ቤት ውስጥ እየሰለጠናችሁ ነው ነገር ግን የራሳችሁ የሆኑ ብዙ ነገሮች ያሉዋችሁ ሰዎች የእግዚአብሄር ሰራተኞች መሆን ያዳግታችኋል በዚህ የሚሽን ትምህርት ቤት እያላችሁ የእርሱ አገልጋዮች የሰበኩትን የእግዚአብሄር ቃል ከሙሉ ልባችሁ ማመንና በልቦቻችሁምውስጥ መቀበል አለባችሁ መከራዎቻችሁን በሙሉ መቋቋም የምትችሉትና በትክክል የምትሰለጥኑት ያን ጊዜ ብቻ ነው እኛ ሁሉን ነገር መቋቋምና የእግዚአብሄርን ስራ መስራት የምንችለው በቃሉ ላይ ባለን እምነታችን አማካይነት ነው።

በመጀመሪያ ቃሉን በልቦቻችን ሳንቀበል በስጋችን ጉልበት ወይም ሐይል ወይም ዳግም ከመወለዳችን በፊት በነበሩን ልምምዶች የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት መሞከር የለብንም እግዚአብሄርን በራሳችን ስጋዊ አስተሳሰቦች ወይም ጉልበት ለመከተል ብንሞክር እስከ መጨረሻው ድረስ ፈጽሞ እርሱን መከተል አንችልም እኛ እስከ መጨረሻው ድረስ የእርሱን ስራ መስራት የምንችለው ጌታን ሁሌም በእግዚአብሄር ጸጋ ስንከተለው ብቻ ነው።

አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሄር አገልጋዮች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ሆነ ብለው ያስቸግሩዋችኋል ከረጅም ጊዜ በፊት በአንድ ወቅት የኔን ጉባኤ 230 ሜትር ካሬ (2,500 ስኩዌር ሜትር) መጠን ላለው ቻፕል ግድግዳዎችንና ማሞቂያ እንዲሰሩ ጠየቅኋቸው በቤተክርስቲያኔ ውስጥ ያሉት ወንድሞች የዚህ ባለሙያዎች እንዳልሆኑ በሚገባ አውቃለሁ ነገር ግን ሁሉንም ጠርቼ እንዲሰሩ ጠየቅኋቸው ምሽት አካባቢ ሲሚንቶ እንዲገዙ ስጠይቃቸው በዚህ ምሽት ከየት ሊገዙ እንደሚችሉ ግራ ገባቸው ሲሚንቶውን ለማግኘት የመሸጫ መደብሩን ማንኳኳት ቢያስፈልጋቸውም እንኳን አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ እንዲያደርጉ ነገርኋቸው።

የእነዚህን ቅዱሳኖች ልብ ስመለከት ስጋዊ አስተሳሰቦቻቸውን ሳይጥሉ ያለ ማቋረጥ እንደለፉ ማየት ቻልሁ አስተሳሰቦቻችን መስበር አስፈለገኝ በአንድ ወቅት ለቅዱሳን ያስገቡትን የማሞቂያ መሳሪያ ነቅለው በአዲስ የማሞቂያ መሳርያ እንዲተኩ ነግሬአቸው ነበር ስለዚህ የእሁድ የአምልኮ አገልግሎት ሲጠናቀቅ ሁሉንም በአንድ ላይ ሰብስቤ የቻፕሉን ወለል እንደገና እንዲያፈርሱ ነገርኋቸው የጠዋቱ የአምልኮ አገልግሎት ካበቃ በኋላ ባለው ተሲያት ሌላ የግንባታ ዙር ተጀመረ ከእነርሱ አንዳንዶቹ «ለምን ልታፈርሰው ፈለግህ? ጥሩ ሆኖ ተሰርቷል ምን ማድረግ እንደፈለግህ ከመጀመሪያው ልትነግረን ይገባ ነበር ብዙ ጥረት ካደረግን በኋላ እንዴት ይህንን ታደርጋለህ?» በማለት ተቃውሞዋቸውን ለማሰማት ወደ እኔ መጡ።

የሰው ስልጣን በአለም ላይ ምንም ያህል ከፍ ያለ ወይም ዝቅ ያለ ቢሆን ሰራተኛ ሆኖ እንዲያገለግል ከተፈለገ በእግዚአብሄር ፊት አስተሳሰቦቹ መሰበር አለባቸው ጉባኤውን ለአንድ አመት ያህል ልክ እንደዚህ ካሰለጠንሁ በኋላ ከዚያን ጊዜ

ጀምሮ በተናገርሁ ቁጥር ሁሉም ታዘዙኝ ሁሉም በሚገባ ሰልጥነው ነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንዲያደርጉ የጠየቁዋቸውን ሁሉ ሳያጉረመርሙ ታዘዙ ከዚያ በኋላ እኔም ደግሞ በጥያቄዎቼ ይበልጥ ምክንያታዊ ሆንሁ።

አገልጋዮቻችንን አንዳንድ ጊዜ እግር ኬስ ለመጫወት ይሰበሰባሉ አንዳንድ ጊዜ አንድ ተጫዋች ኬሱዋን ሲያንከባልል ለጥቂት ከመስመሩ ትወጣለች ተቃራኒው ቡድንም ኬስዋ ከጨዋታው ውጭ ነች በማለት ድርቅ ይላል ሌላው ቡድን ግን ያ እንዳልሆነ አበክሮ ይናገራል ሁሉም ስለሚንጫጫ ጨዋታው ለጥቂት ጊዜ ይቆማል ልክ እንደዚሁ ሰው ልቡን ካልሰበረና ራሱን ካልካደ እግዚአብሄር ስራውን በአደራ ሊሰጠው አይችልም በእግዚአብሄር ፊት «እኔነት» ካለ የእርሱን ስራ መስራት አንችልም።

በቤተክርስቲያናችን ያሉ ቅዱሳኖች በውስጣቸው «እኔነት» አለባቸው? የለባቸውም እግዚአብሄር ምዕመናኖችንም ሰራተኞችንም በአንድ ላይ አሰልጥኖዋቸዋል እግዚአብሄር መርቶዋቸው ሳለ ከእነርሱ አንዳቸውም የእርሱን ፈቃድ ባይታዘዙ እግዚአብሄር ይበልጥ ያሰለጥናቸዋል እግዚአብሄር በቤተክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ ልምምዶች ውስጥ እንድናልፍ በማድረግ በዚህ መልኩ ይቀርጸናል በአደራ የተሰጠንን በእምነት ስንፈጽም እግዚአብሄር የበለጠ ስራ በአደራ ይሰጠናል።

እግዚአብሄር ለአንድ ሰው የስራውን አንዱን ተግባር ብቻ መመደብ አይፈልግም የእግዚአብሄርን ስራ በእምነት በሚገባ ስንሰራ ተጨማሪ ስራ በአደራ ይሰጠናል ለእኔ በአደራ የተሰጠኝን ስራ መፈጸም የማልችል ከሆነ እግዚአብሄር ሌላ ሰው ይመድብበታል እኔንም ወደ ሌላ ስራ ያዛውረኛል ማናችንም ጌታን በስጋችን ጉልበትና ሐይል ማስደሰት አንችልም እርሱን ማገልገል የምንችለው እግዚአብሄር በሰጠው መንፈሳዊ

ሐይልና በቃሉ ላይ ባለን የእምነታችን ሐይል ነው እውነተኛ እምነት ይህ ነው።።

በጥቅሉ ባለ ትዳሮች በመንፈሳዊ ሁኔታቸው አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ ሚስት በባልዋ ላይ ትጮሃለት ባልም በሚስቱ ይበሳጫል ባል ለገጠሙት ችግሮች ሁሉ ሚስትን ይወቅሳል ሚስትም ለገጠሙዋት ችግሮች ባልዋን ትወቅሳለች ብዙዎቹ ባለ ትዳሮች የሚያስቡት እንደዚያ ነው ስለዚህ ሚስት «ይህ ሁሉ ችግር የገጠመኝ በባለቤቴ ምክንያት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ ማንም አያከብረኝም» ብላ ታስባለች ባልም በበኩሉ «እንዲህ የሆንሁት በሚስቴ ምክንያት ነው» ነው ብሎ ያስባል አብዛኞቹ ሰዎች መጀመሪያ የሚያስቡት እንዲህ እንደሆነ ግልጽ ነው።።

ነገር ግን በጊዜ ሒደት ውስጥ ምንም አይነት ሁኔታ ቢገጥማቸው የገጠማቸው በባል ወይም በሚስት ምክንያት ሳይሆን በራሳቸው ምክንያት እንደሆነ ወደ መረዳት ይመጣሉ መጀመሪያ ላይ ግን ሰዎች በጣም በሚቀርባቸው አጋራቸው ላይ ይበሳጫሉ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አይደላችሁምን? ጓደኞችሁን ከመውቀስና «በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ያለፍሁት ባንተ ምክንያት ነው» ብላችሁ ከማጉረምረም ይልቅ እነዚህ ሁሉ ነገሮች እግዚአብሄር እኛን እየቀረጸበት ያለው ሒደት ክፍል መሆናቸውን እንድታምኑ እመክራችኋለሁ።።

እግዚአብሄር የእርሱ ሰራተኞች አድርጎ ከቀረጸን በኋላ በትክክለኛው ስፍራ ትክክለኛ መሳሪያዎች አድርጎ ይጠቀምብናል በአንድ ሚና ውስጥ ታማኝ ከሆናችሁ እግዚአብሄር ለሌላ ሚና ይጠቀምባችኋል በዚህ መንገድ እግዚአብሄር ሁሉንም ነገሮች ማድረግ ትችሉ ዘንድ ይፈልጋል እግዚአብሄር በኤድን ገነት ሁሉ ውስጥ እንድትሰለጥኑ ይፈልግባችኋል መሄድ ወደማትፈልጉበት ስፍራ ብትላኩ ምን

ይሰማችኋል? «እግዚአብሄር ለምን እዚህ ላከኝ? ከእኔ ያነሰ ችሎታ ያለው ሰው እዚያ እያለ ለምን እኔ እዚህ መገኘት አስፈለገኝ?» በራሳችሁ መንገድ እንዲህ ደምድማችገሁ እግዚአብሄር ያዳላል ብላችሁ አታስቡምን?

እግዚአብሄር ግን ሁሌም ተስማሚ በሆነ መንገድ ይሰራል አሁን ወዳላችሁበት ስፍራ የተላካችሁት የሚያስፈልጋችሁ ይህ ስለሆነ ነው ከራሳችሁ አስተሳሰቦች ጋር ስላልተሰማ ወይም እናንተ ከምትጠብቁት ነገር ጋር ስላልተገጣጠመ አጋጣሚዎቹና ሁኔታዎቹ መጥፎ ናቸው ማለት አይደለም እግዚአብሄር እነዚህን ሁኔታዎች የፈቀደው የእርሱ ሰራተኞች አድርጎ ሊጠቀምባችሁ እንደሆነ እንድትገነዘቡ ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ እግዚአብሄር ምዕመናኖችን በዚህ መልኩ እንዴት እንደሚያሰለጥናቸው ማት እንችላለን::

እግዚአብሄር ከዋክብቶችን ፈጠረ እግዚአብሄር አገልጋዮቹን የእምነት ሰዎች አደረጋቸው እግዚአብሄር ከዋክብቶችን በሰማይ ላይ የፈጠረው ለዚህ አላማ ነው በቁሳዊ ነገሮች ላይ እምነት የሌላቸውን ሰዎች እግዚአብሄር እምነታቸውን በእርሱ ላይ በማኖር የገንዘብ ችግሮቻቸው እንዲፈቱላቸው ያደፋፍራቸዋል ቤተክርስቲያንን ለመትከል ወይም ወንጌልን ለነፍሳቶች ለመስበክ እምነት የሌላቸውን ሰዎች እግዚአብሄር በእርሱ ላይ በመደገፍና በእርሱ በመታመን ይህንን ስራ በእምነት እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል እግዚአብሄር ለችግሮች ሁሉ በእምነት እንድንጸልይና መፍትሄ እንድናገኝ ያሰለጥነናል እግዚአብሄር የእምነት ሰዎቹ አድርጎ ይቀርጸናል ጠቃሚ መሳሪያዎቹና የተባረኩ አገልጋዮቹ አድርጎ ይቀርጸናል በራሳችን ጥረት ራሳችንን የእግዚአብሄር አገልጋዮች አድርገን ማሰልጠን አንችልም የሚቀርጸን እግዚአብሄር ነው በዚህ ቅጽበት እንኳን ሁላችንንም እየቀረጸን ነው የእርሱ መሳሪያዎች አድርጎም

እየተጠቀመብን ነው እግዚአብሄር የእርሱ ሰራተኞች አድርጎ እየሰወጣችሁ ነው።።

እግዚአብሄር አገልጋዮቻችንን እንደዚሁም ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን እርሱ ሰራተኞች አድርጎ እየቀረጻቸው እንደሆነ አምናለሁ በጣም ደካሞች ስንሆን ዕረፍት የምናገኝበትን መንገድ ይከፍትልናል በጣም ብርቱዎች ስንሆን ደግሞ ይሰብረናል እግዚአብሄር በስልጣኑ እንዲህ ይሰራል ይህንን ሁሌም አንገነዘበው ይሆናል አሁን ግን በእግዚአብሄር እንደተበጀን እናውቃለን በዚህ ሒደት ውስጥ ካለፍን በኋላ እግዚአብሄር እንደቀረጸን ወደ መረዳት እንመጣለን በእግዚአብሄር ከተቀረጽን በኋላ አሁን መስራቱ ምን ያህል ቀላል እንደሆነ መረዳት እንችላለን በእግዚአብሄር ላይ ያለን እምነት ትንሽ ከሆነ እምነት አልባነታችንን ይነግረንና እንዴት እምነት እንደሚኖረን ያሳየናል።።

ወደፊት ጌታን በማገልገል ከመቀጠል ጋር መጣጣም የምንችለው በሚሽን ትምህርት ቤት በሚኖረን ቆይታ በትክክል ስንሰለጥን ብቻ ነው በእምነት ያልሰለጠኑ አገልጋዮች ካሉ እግዚአብሄር እንደገና ያሰለጥናቸዋል ምክንያቱም እኔም ደግሞ በአንድ ወቅት እንዲህ ነበርሁ በዚህች ቅጽበትም እንኳን ገናም ያለ ማቋረጥ እየሰለጠንሁ ነው አሁንም ችግሮች በመንገዳችሁ ላይ እየመጡ ከሆነ እነዚህ ነገሮች የተፈቀዱት እንዲህ ያለ ስልጠና ስለሚያስፈልጋችሁ መሆኑን እንድታምኑ እመክራችኋለሁ የእግዚአብሄርን ስራ መስራት አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን ሁላችንም በዚህ ሒደት ውስጥ ማለፍ አለብን እየተንገላታን ሊሆን ይችላል ነገር ግን የእግዚአብሄርን ቃል መቀበልና ስራችንንም በእምነት ማከናወን አለብን አሁን በሚሽን ትምህርት ቤት እየሰለጠናችሁ ያላችሁት ለዚህ ነው።።

እኛም ብንሆን ይህንን የሚሽን ትምህርት ቤት በ1991 ኤ.ም

ለመጀመሪያ ጊዜ ስንከፍት በጣም ተቸግረን ነበር ለዕለት እንጀራችንም እንኳን ስንጸልይ ነበር ቤተክርስቲያን የተወሰኑ መባዎችን ከሰበሰበች በዚያ ቀን ምግብ መብላት እንችል ነበር የተሰበሰበ መባ ከሌለ ግን አንበላም ነበር ወቅቱ በጣም አስቸጋሪ ስለነበር በጉባኤው ውስጥ ያለ አንድ ሰው እራት እንድንበላ ሲጋብዘን በዚያ ቀን እኔና ሰልጣኞቼ ብዙ እንበላ ነበር ብዙ እንበላ ነበር ምክንያቱም አሁን ራሳችንን ካላጠገብን ነገ ረሃብ ተመልሶ ሲመጣ እንጸጸታለን አሁን ግን ከመጠን በላይ በልተን እንዳንጠግብ በአመጋገብ ልምዶቻችን ተገርተናል።

አዲስ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ስንተክል ያ በመንፈሳዊ ሁኔታ ለመሰልጠን ምርጡ ወቅት ነው የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን በአደራ የሰጠችንን በታማኝነት ለመተግበር እምነት በጣም አስፈላጊ ነው አዲስ ቤተክርስቲያን ምን ያህል ገንዘብ እንደሚወስድ ሁላችሁም ታውቃላችሁ ትክክል አይደል? በልጆች መጠበቂያ ክፍል ውስጥ መስኮት ለመግጠም እንኳን ገንዘብ ያስፈልጋል ስለዚህ እኛ ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር እግዚአብሄር እንዲረዳን መጸለይ ብቻ ነው ስለዚህ መክፈል የምንችለው በቂ ገንዘብ ሲኖረን መስኮቱን አንድ በአንድ እንገጥማለን ጌታ ስናገለግል የገጠሙንን ችግሮች ሁሉ መግለጥ የሚችሉ ቃላቶች የሉም።

በመጀመሪያ በበቤተክርስቲያኔ ውስጥ ባገለገልሁ ጊዜ ሠዙ ችግሮች ገጥመውኛል ነገር ግን እግዚአብሄር በእነዚህ ችግሮች አማካይነት የእርሱ ሰራተኛ አደረገኝ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንዴት እንደማገለግልና የዚህን ወንጌል ስራ እንዴት እንደምሰራ አሳየኝ በዚህ መልኩ የእግዚአብሄርን ስራ እንደምንሰራ ማን ያውቅ ነበር?

የጌታ አገልጋይ ሆኜ ማገልገል ከጀመርሁበት ጊዜ ጀምሮ ይህንን የውሃና የመንፈስ ወንጌል ሰብኬአለሁ ነገር ግን በወቅቱ

ከእኔ ጋር ሲሰሩ የነበሩት አገልጋዮች ከእኔ የተለየ እምነት ነበራቸው ወንጌልን ለሰዎች ስሰብክ የተናገርሁትን ከሰሙ በኋላ «ምን? እርሱ ከእኔ የተለየ ነው አይደለምን?» ማለት ያዘወትሩ ነበር በዚህ አለም ላይ የሚኖሩ በርካታ መጋቢዎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል አያውቁም በእርሱም አያምኑም በሌላ አነጋገር አገልግሎታቸው ከእግዚአብሄር የውሃና የመንፈስ ወንጌል ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

ነገር ግን እኔ ነፍሳቶችን ሰብስቤ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመስበክ ውስጥ ፈጽሞ ተውጬ ነበር ከሚስቴ ጋር ተጨቃጭቄ በምበሳጭበት ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ቦርሳዬን አንስቼ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለመስበክ እወጣ ነበር።

ባለ ትዳሮች ፈጽሞ ሳይጣሉ መኖር አይችሉም በችግር ጊዜ መናቆራቸው የተለመደ ነው ይህ እኔንም ደግሞ የሚመለከት ነው ከባለቤነ ጋር ስጣላ ወደ ሆስፒታል እሄድና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለበሽተኞች እሰብካለሁ አንድ ነፍስ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከሰማ በኋላ የሐጢያቶቹን ስርየት በሚቀበልበት ጊዜ ሁሉ በጣም እደሰታለሁ ስለዚህ ወንጌልን ከሰበክሁ በኋላ በመንፈስ ተሞልቼ ወደ ቤቴ እገባለሁ ስለሆነውም ነገር ከሚስቴ ጋር አወራለሁ በዚህ መልኩ የእግዚአብሄርን በረከቶች ከሚስቴ ጋር ከተጋራሁ በኋላ ሁለታችንም በምስጋና እንሞላለን በዚህም ጥላችንን ሁሉ ረስተን ወዲያውኑ እንታረቃለን ከዚያም ለነፍሳቶች አብረን ጸለይን።

ወንጌልን ማገልገል ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም ይልቁንም የእግዚአብሄርን ቃል ከተቀበልሁ በኋላ ይህንን ስራ የምሰራው ይህ ወንጌል በጣም ክቡር ስለሆነና ነፍሳቶችን የሚያድነውም የሕይወት ስራ ይህ ስለሆነ ነው ስራው ከባድና አስቸጋሪ ቢሆንም ሁሌም ጉድለቶቻቸውን ተቀብለን

በደስታ እንሰራለን በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም አሁንም ድረስ እየሰራን ያለነው የእግዚአብሄር ስራ በጣም ክቡር ስለሆነ ነው።

የእግዚአብሄር አገልጋዮች በሰው አይን ሲታዩ ቀዝቃዛ ልብ ያላቸው ይመስሉ ይሆናል ከዚህ ቀደም ያውቁኝ የነበሩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ተቀይረሃል ይሉኛል ምክንያቱም በጣም ሩሁሩህ ነበርሁ ደሃና ምስኪን አይቼ አላልፍም ነበር በቻልሁት መጠን ልንከባከባቸው እሞክር ነበር ከዚህ በፊት ለሌላው ሰው ሁሉ እንክብካቤን እያደረግሁ መኖር የለመድሁት እንዲህ ነበር አሁን ግን ይህንን ማድረግ አልችልም ለምን? ነፍሳቶችን ማዳን እነርሱን በቁሳዊ ጉዳዮች ከመርዳት የበለጠ ክቡር ነገር እንደሆነ አውቄአለሁ ማንኛውንም ነፍስ የሚያድነው ይህ ስራ በጣም ክቡር ስለሆነ ለውሃውና ለመንፈሱ ወንጌል የሚጠቅም ከሆነ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ።

አምላካችን የእርሱ ሰራተኞች አድርጎ ጠርቶናል የእርሱ ሰራተኞች አድርጎ ስለጠራን አመሰግነዋለሁ አንዳንድ ጊዜ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ስንሰብክ ችግሮችና መከራዎች ይገጥሙናል ነገር ግን የእግዚአብሄር ሰራተኞች ሆኖ መኖር አሁንም ለእኛ በረከት ነው።

ጌታን ስትከተሉ የምትንገታገቱ ከሆናችሁ የእግዚአብሄርን ቃል አብልጣችሁ እንድትቀበሉ እመክራችኋለሁ በትግል ጊዜ መከራዎቻችንን እንድናሸንፍ የሚያስችለን እግዚአብሄር የሰጠው ቃል ነው የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ውስጥ ስንቀበል እምነት ይበቅላል እግዚአብሄር ችግሮቻችንን እንድናሸንፍ ያስችለናል ለእኛ የእግዚአብሄር ቃል ሕይወታችን ነው የእግዚአብሄር ቃል ካለን በሕይወት እንኖራለን ቃሉ ከሌለን ግን እንሞታለን።

ሐሌሉያ! እግዚአብሄር ጉልበታችንና እረኛችን ሆንዋል እግዚአብሄር ሰራተኞቹ አድርጎ ቀርጾናል። ✉

በነጻ የሚታደል መጽሐፍ ለመጠየቅ www.nlmission.com

ጻድቅ በእምነት ብቻ ይኖራል

« ዘፍጥረት 1:20-23 »

«እግዚአብሄርም አለ ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ እግዚአብሄርም ታላላቆች አንበሪዎችን ውሃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው ብዙ ተባዙም የባሕርንም ውሃ ሙሉአት ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አምስተኛ ቀን::»

እግዚአብሄር በአምስተኛው ቀን ባደረገው የፍጥረት ስራ አማካይነት ጻድቃን በእግዚአብሄርና በቃሉ ላይ ባላቸው እምነት እንዴት እንደሚኖሩ እየነገረን ነው::

እግዚአብሄር «ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ይብረሩ» ያለው ለምንድነው? ይህ የአሦችና የወፎች ጉዳይ ብቻ ነውን? በዚህ ምንባብ ላይ ስናተኩር በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ለማን እንደተሰጠ ማሰብ ያስፈልገናል ያን ጊዜ ይህ ምንባብ የተነገረው በእምነት ይኖሩ ዘንድ የሐጢያት ስርየትን ለተቀበሉ ሰዎች እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን::

በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄር ወፎች በሰማይ ላይ እንዲበሩ አደረገ በዚህም እግዚአብሄር

«ጻድቅ የሚኖረው በእምነት ብቻ ነው» ማለቱ ነው ስለዚህ እኛ ጻድቃኖች በእርግጥም በእምነት እየኖርን እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ራሳችንን መመርመር አለብን።

እግዚአብሄር *«ጻድቅ በእምነት ይኖራል» (ሮሜ 1:17)* ብሎዋል እምነት ምንድነው? «አምናለሁ» የምንልበት እምነት ነውን? ሁሌም በሕይወታችን ውስጥ ችግር አለ ነገር ግን ምንም ያህል የበዙ ችግሮች ቢገጥሙንም እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምን አማኞች የእግዚአብሄርን ቃል በልቦቻችን ካልያዝንና በእምነት ካልኖርን በስተቀር የሐጢያቶቻችንን ስርየት እንድንቀበል የፈቀደልን የመጀመሪያው እምነታችንም እንኳን ይጠፋል የእኛም መጨረሻ ከእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን መራቅ ይሆናል ይህ ብዙውን ጊዜ ሲከሰት አይቻለሁ በሌላ በኩል በእግዚአብሄር ቃል በእምነት መኖር ማለት ምን እንደሆነ የምናውቅ ከሆነና በኑሮዋችንም የእግዚአብሄርን ቃል በእምነት የምንጠቀም ከሆነ ይህ በአያሌው ይረዳናል እኛም እንባረካለን ጻድቃን በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ባላቸው እምነታቸው መኖር አለባቸው በእግዚአብሄርና በቃሉ ላይ ባላቸው እምነትም ሊኖሩ ይገባል።

እናንተና እኔ በጌታ በመታመን የእምነት ሕይወታችንን እየኖርን ነው ነገር ግን ትክክለኛው እምነት ምን አይነት እምነት እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባናል በእምነት መኖራችን ወሳኝ የሆነው ለምንድነው?

አብዛኞቻችሁ የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ከተቀበላችሁ በኋላ እንኳን እምነታችሁን ሁሉ በእግዚአብሄር ላይ በማኖር አልኖራችሁም ሁላችሁም የኖራችሁት በሥጋችሁ ጉልበት ነው እግዚአብሄርን በማመን እንደኖራችሁ መናገር አትችሉም ዳግም ከመወለዳችን በፊት በገንዘብ ወይም በስልጣን አለበለዚያም በስጋችን ጉልበት ተማምነን ኖረናል።

ነገር ግን ዳግም ከተወለድን በኋላ እግዚአብሄር በእርሱ በመታመን ልንኖር እንደሚገባንና ቃሉን በማመንም ልንከተለው እንደሚገባን ነገረን ትክክለኛው ነገር ሁላችንም እምነታችንን በእግዚአብሄርና በጽድቁ ላይ በማስቀመጥ መኖራችን ስለሆነ መኖር የሚገባን እንደዚህ ነው ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጻፈ ይህ ትክክል እንደሆነ እናስባለን ነገር ግን ቃሉ ትክክል ቢሆንም እንደዚህ መኖር ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑንም ወደ መረዳት መጥተናል ነገር ግን ችግር ሲገጥመን ያንን ማድረግ እንደማንችል እናያለን፡፡

ለምሳሌ መሰረታዊ የሆነውን የልብስ የምግብና የመጠለያ ፍላጎቶች ችግር እንመልከት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግም ከመወለዳችን በፊት ገንዘብ ለማግኘት በቀን ውስጥ 24 ሰአታትን እናሳልፍ ነበር ነገር ግን ዳግም ከተወለድን በኋላ ወደ እግዚአብሄር ቤተክርስያን ጉባኤ መጥተን በእምነት መኖር፣ ወንጌልን ማገልገል፣ መባዎችን መስጠት፣ ለጌታ መኖርና ከቤተክርስቲያን ጋር መተባበር እንደሚገባን የሚነግረንን ቃል ሰማን እነዚህ ሁሉ ትክክል ናቸው አሁን እግዚአብሄር ከእኛ እየጠየቀ ያለው ከአሮጌው ፈጽሞ የተለየ ሕይወትን ነው፡፡

ከዚህ ቀደም ልክ እንደ ሰጎን በራሳችን ጉልበት የመኖር ልምድ ነበረን አሁን ግን በእምነት እንድንኖር ስለተነገረን እምነታችን ትንሽ ስለሆነች እንደዚህ መኖሩ ያሰቅቀናል ሰጎን አቧራውን እያቦነነች በሁለት እግሮች በሰአት 80 ኪሎ ሜትር የመሮች ችሎታ አላት ክንፎችወን ሳትጠቀም በሁለት እግሮችዋ ብቻ በመጠቀም ከአዳኞችዋ ማምለጥና ምግብዋን ማግኘት ትችላለች እኛም ከዚህ በፊት የኖርነው እንደዚህ ነው አሁን ግን በጉልበታችን በመደገፍ ብቻ እንደዚህ መኖር ከቶውኑም አይቻልም ከዚህ በፊት የስጋ ጉልበት ነበረን ነገር ግን በእምነት ወደ እግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ከመጣን በኋላ የስጋ

ጉልበታችን ፈጽሞ ጎዶሎ እንደሆነ ተገነዘብን በሌላ አነጋገር ማናችንም በስጋችን ጉልበት ብቻ መኖር አንችልም ለምን? ምክንያቱም በአቅማችንና በጉልበታችን ብቻ የእግዚአብሄር መጠይቆች በሙሉ መመለስ አንችልም እምነታችንን በእግዚአብሄር ጽድቅና በቃሉ ላይ በማኖር መኖር የሚገባንና በዚህ ምክንያትም አሮጌውን የሕይወት መንገዳችንን መቀየር የሚገባን ለዚህ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ «ጻድቅ በእምነት ብቻ ይኖራል» ይላል ጻድቃን የሚኖሩበት አንድ መንገድ ብቻ አለ እርሱም በእግዚአብሄር ጽድቅና በቃሉ ላይ ባላቸው እምነታቸው መኖር ነው ስጋዊ አስተሳሰቦቻችንን መጣል የሚገባን ለዚህ ነው ስለዚህ እንዴት በእምነት መኖር እንደሚገባን እናስላስል።

በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄር «ወፎችም ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ» ብሎዋል ይህ ምንባብ የሚያመላክተው ጻድቃን በእርግጥም በእምነት መኖር እንደሚችሉ ነው ጻድቃን በጌታ በመታመን መኖር እንዳለባቸው ሲናገር ይህንን ማለቱ ነው እነርሱ ወደ ጌታ ይጸልያሉ የሚያስፈልጋቸውንም ይጠይቃሉ ጌታን ምንም ነገር ቢጠይቁት ጌታ እንደሚመልስላቸውም ያምናሉ ጌታ እረኛችን፣ አምላካችን፣ አዳኛችንና ጌታችን እንደሆነ ስናምን በእምነት መኖር እንችላለን በሌላ አነጋገር ይህ ማለት ሁላችንም ወደ እርሱ በምንጸልይበት ጊዜ ጌታ በሕይወታችን ውስጥ እንደሚሰራ በማመን ልንኖር ይገባናል ማለት ነው እምነታችንን በእግዚአብሄር ላይ ማኖር ማለት በሕይወታችን ውስጥ አንዳች ችግር በሚገጥመን ጊዜ ሕያው ወደሆነ ጌታ ለመጸለይ እምነታችንን በእግዚአብሄር ላይ ማኖርና የጸሎቶቻችንን መልስ ከእረሱ ማግኘት ነው።

እየታገልን ከሆነ ወደ እግዚአብሄር መጸለይና የእርሱን እርዳታ

መጠየቅ አለብን ጌታም የእርዳታ ጥያቄያችንን እንደሚመልስልን ልናምን ይገባናል እግዚአብሄር ጥበብንና ጸጋን እንደሚሰጠን፣ ችግሮቻችንን እንደሚፈታና ጸሎቶቻችንንም በተለያዩ መልኮች እንደሚመለስ የሚያምነው ይህ እምነት አስፈላጊ ነው በጌታ ጽድቅ ላይ ታምነን መኖር የምንችለው እንደዚህ ነው ይበልጥ ግልጽ ለመሆን ወደ እርሱ በመጸለይ የእርሱን እርዳታ እናገኛለን በጌታ በማመን መኖር ማለት ይህ ነው።

በእግዚአብሄር የምናምነው የአለም ሐይማኖቶችን የመሰረቱ አንዳንድ መስራቾችን እንደምናምነው አይደለም ነገር ግን አሁንም ለዘላለምም በሚኖረውና እናንተንና እኔን ከሐጢያቶቻችን ባዳነን ጌታ ፊት እንሳነበሳለን የእርሱን እርዳታ በመጠየቅም ወደ እርሱ እንጸልያለን ጌታን በእነዚህ ጸሎቶች የምንገናኘውና በሕይወታችንም በእርሱ የምንባረከው ያን ጊዜ ነው ወደ ጌታ ስንጸልይ በእምነታችን አማካይነት ከጌታ ጋር ሕብረት ሊኖረን ይችላል በእምነትም ልንኖር እንችላለን ትግሎቻችንን እንዲያውቅ ልናደርግ፣ የእርሱን እርዳታ ልንጠይቅ፣ ቃሉን ልናምን፣ ጌታ እንደሚረዳንና ችግሮቻችንን እንደሚፈታ ልናምን ይገባናል ለንኖር የሚገባን በዚህ እምነት ነው ይህ በእምነት ሕይወታችን ውስጥ መደረግ አለበት በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ባለው እምነታቸው የሚኖሩ ሰዎች ወደ ጌታ ይጸልያሉ ከእርሱም ጋር ሕብረት ያደርጋሉ ስለዚህ እርሱ በለገሳቸው ሐይልና ጸጋ መኖር ይችላሉ ከጌታ ጋር ሕብረት እያደረጉና በእምነታቸው አማካይነትም መልስን እያገኙ በእርሱ ላይ እየተደገፉና በእርሱ እየታመኑ መኖር ያለባቸው ለዚህ ነው።

በዚህ አለም ላይ የሚኖሩ በርንታ ሰዎች በእግዚአብሄር ታምነው እንደሚኖሩ ይናገራሉ ያ ግን እውነት አይደለም የእግዚአብሄር አገልጋዮች ችግሮች በገጥሙዋቸው ጊዜ ሁሉ

መጀመሪያ በጸሎቶቻቸው አማካይነት የእግዚአብሄርን እርዳታ ጠይቀዋል ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሌም ወደ ጌታ አልጸለየምን? የሐዋርያው ጳውሎስ እምነት እግዚአብሄር ቃል የገባውን ሳያዛንፍ እንደሚፈጽም ማመንን ያካተተ ነበር ስለዚህ እኛንም እንዲህ ሲል መከረን «በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ::» (ኤፌሶን 6:18)

ትግል ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ ሁሉ የጌታን እርዳታ ብንጠይቅ ጌታ ሁሌም ጸሎቶቻችንን በተለያዩ መልኮች ይመልስልናል የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለዚህ አለም በምንሰብክበት ጊዜ እግዚአብሄር እንደሚደግፈንና እንደሚረዳን በማመን በእምነት መኖር አለብን::

እስከዛሬ ድረስ በእግዚአብሄርና በጽድቁ በማመን ኖረናል ሐዋርያው ጳውሎስም እንደዚሁ በእግዚአብሄርና በጽድቁ ላይ ባለው እምነቱ ኖሮዋል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉት የእምነት ሰዎች በሙሉ በእግዚአብሄር ላይ ባላቸው በዚህ እምነት ኖረዋል አሁን እየመሩዋችሁ ያሉት የእምነት ቀደምቶችም እንደዚሁ እስከ አሁን ድረስ በእምነት ኖረዋል::

የእምነት ቀደምቶቻችሁ ከችግር ነጻ አልነበሩም ነገር ግን እነርሱም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ካመኑበት ቅጽበት ጀምሮ በተከታታይ ችግሮች ገጥመዋቸዋል እነርሱ ጠላትን መቋቋምና መዋጋት ነበረባቸው ተላግጦባቸዋል ተሰድደዋል ሁሉም አይነት ስድቦች ገጥመዋቸዋል የነበራቸውንም ቁሳዊ ሐብት በሙሉ አጥተዋል::

እኔም ራሴ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመኔ ብዙ ነገር አጥቻለሁ ነገር ግን ካጣሁት በላይ ደግሞ አግኝቻለሁ ጌታን ከተገናኘሁት በኋላ ከውጭና ከራሴም ቤተሰብ ሳይቀር ክፉኛ ተሰድጃለሁ ምንም ቁሳዊ ሐብት አልነበረኝም ያን ጊዜ ጤናማ ነበርሁ? የለም ጤናማ አልነበርሁም ሁሌም እታመም

ነበር አንዳንድ ጊዜ የጀርባ አጥንቱ ይቆስል ነበር የወፈረው ደሜን ሰውነቴን ማድረቁ የተለመደ ነበር ብዙ ጊዜ ወደ ሞት አፋፍ ቀርቤአለሁ እምነታችንን በጌታ ላይ በማኖር ለመኖር ስንሞክር በርካታ እንቅፋቶች ይገጥሙናል ነገር ግን በእያንዳንዱ ጊዜ ወደ ጌታ ጸልየን ጸሎቶቻችን መልስን አግኝተዋል እስከ ዛሬ ድረስ የኖርነው እንዲህ ነው ጻድቃን በእምነት ብቻ ሊኖሩ የሚገባቸው ለዚህ ነው።

እግዚአብሄር በአምስተኛው ቀን እንዲህ አለ «ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ።»

የእምነትን ጠፈር አቋርጠን መብረር የምንችለው እንዴት ነው? ዳግም ከተወለድን በኋላ የጻድቃንን ሕይወት መኖር የምንችለው እንዴት ነው? ስጋችን አሁንም እየሰራ በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ሕይወታችንን ጻድቃን ሆነን መኖር የምንችለው እንዴት ነው? ይህ የሚቻለው በጌታ ጽድቅ ላይ ባለን እምነታችን ስንኖር ብቻ ነው ጻድቃን ማንነታቸውን ማወቅ እንደሚገባቸው ሆነው በእግዚአብሄር ቃል ሁሉ በማመን መኖር አለባቸው።

ሁላችንም ብዙ መከራዎች እየጠበቁንና ስጋዊ ሞትም እንኳን ሳይቀር እየገጠመን እንዴት የእምነት ሕይወታችንን መኖር ቻልን? ይህ የተቻለው በጌታ ጽድቅ ብቻ በማመን በመኖራችን ነው በየጊዜው ወደ ጌታ እየጸለይን ጌታ ጸሎቶቻችንን እንደሚመልስና እርሱ እረኛችን፣ አባታችንና አዳኛ ችን እንደሆነ በማመን እምነታችንን ኖረናል ይህ እውነተኛ እምነት ነው።

ሕይወታችን በየጊዜው ችግር ይገጥመዋል አሁንም እንኳን ከችግር ነጻ አይደለንም ነገር ግን ከዚህ የባሱ ችግሮች ቢገጥሙንም እምነታችንን በጌታ ጽድቅ ላይ በማኖር

መኖራችንን እንደምንቀጥል እናውቃለን እንዲህ አይነት ሰዎች ስለሆንን በጌታ ጽድቅ በመታመን እስካልኖርን ድረስ በስጋና በመንፈስ ከመሞት በቀር ምርጫ የለንም።

ከእኛ የቀደሙት የእምነት ሰዎች ከአጥማቂው ዮሐንስ እስከ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ጳውሎስ፣ ማርቆስና ማቴዎስ ያሉ በሙሉ የኖሩት በእምነት ነበር እነርሱ ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ በመታመን በእምነት ኖሩ በስጋ ጉልበታቸው ወይም በቁሳዊ ሐብታቸው በመደገፍ አልኖሩም እኛም እስከዚህች ቀን ድረስ የጌታን ሐይል ተማምነን ኖረናል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሄር በአራተኛው የፍጥረት ቀን አገልገዮቹን እንዴት እንደፈጠራቸው ተናገረ በአምስተኛውም ቀን እነዚህ አገልጋዮች እምነታቸውን በጌታ ላይ በማኖር እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ተናገረ።

ችግር በሚገጥማችሁ ጊዜ ልትፈቱት የሚገባችሁ እንዴት ነው? በሰው ሰራሽ መንገድ ልትፈቱት ትሞክራላችሁን? ይህም ቢሆን እንኳን የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎችንና ገንዘብን ይጠይቃል ታዲያ ምንም ነገር ከሌላችሁ ምን ልታደርጉ ትችላላችሁ?

ልትኖሩ የሚገባችሁ ጌታን በመታመን ጽድቁን በመደገፍ የእርሱን እርዳታ በመጠየቅና በእርሱ በማመን ብቻ ነው በእግዚአብሄር ላይ የሚደገፈውን በእርሱ ጽድቅ የሚታመነውንና እርዳታውን የሚሻውን ይህንን ሕይወት ለመኖር መማር አለባችሁ ኢምንት በሆኑ ጉዳዮችም ቢሆን «እግዚአብሄር ሆይ እባክህ በዚህ እርዳኝ» በማለት ጌታን በእምነት ልንጠይቀው ይገባናል ጌታን በእምነት መጠየቅ አለብን እርሱ የጠየቅነውን እንደሚሰጠን በማመንም ልንኖር ይገባናል ችግሮቻችንን ወደ ጌታ ይዘን በመምጣት «እግዚአብሄር ሆይ እባክህ ይህንን ችግር ፍታልኝ እኔንም እርዳኝ እንድትረዳኝ

እይቅሃለሁ መልስ እንደምትሰጠኝ አምናለሁ» ብለን ልንጠይቀው ይገባናል የጌታን እርዳታ እየጠየቅንና በእርሱ እየታመንን መኖር እንችላለን።

ጌታን በእምነት ብንጠይቀውና ጸሎቶቻችንም ተገቢ ከሆነ ጌታ መልሱን ይሰጠናል እግዚአብሄር በሐይሉ በሕይወታችንነ በሁኔታዎቻችን ውስጥ ይሰራል ስለዚህ የምንኖረው በጌታ እርዳታ ነው አሁን በጌታ እየታመናችሁ መኖርን ልትማሩ ይገባችኋል አብዛኞቹ ሰዎች በራሳቸው የእውቀትና የቁሳዊ ሐብቶች ክልል ውስጥ ለመኖር ይሞክራሉ ዳግም የተወለዱ ጻድቃኖች ግን ምዕመናኖችም ሆኑ አገልጋዮች ሙሉ በሙሉ በጌታ ቢታመኑና በእምነት ቢኖሩ ችግሮችን ሁሉ ማሸነፍ ይችላሉ ችግሩ ምንም ይሁን በጌታ ፊት የሚያቀርቡት በእርሱ የሚያምኑና የእርሱን እርዳታ የሚጠይቁ ከሆኑ እርሱ በእርግጥም መልስን ይሰጣቸዋል እምነት ሌላ ሳይሆን ይህ ነው አሁን በእምነት መኖርን መማር ይገባችኋል በእርግጥም በእምነት ልትኖሩ ይገባል።

እግዚአብሄር እምነቴን አጥርቶታል

ትልቅ ችግር ገጥሞኝ የነበረበት ወቅት ነበር ነገር ግን በጌታ ታምኜ ኖርሁ በዚያን ወቀት አሁን አብረውኝ የሚሰሩት አገልጋዮችም ሆኑ የእምነት ወንድሞችና እህቶች አጠገቤ አልነበሩም ቁሳዊ ሐብቴም በጣም ጥቂት ነበር ሶክኛ ተብላ ወደምትጠራ የወደብ ከተማ በሄድሁበት ወቅት ያመንሁት ብቸኛ ው ነገር እግዚአብሄር አምላኩ እንደሆነ እኔም የእርሱ አገልጋይ እንደሆንሁና በዚህም ስጸልይ እንደሚሰማኝ ነበር የኖርሁበት እምነት ይህ ነበር።

በእግዚአብሄር ታምኜ ወደ እርሱ ጸለይሁ በስጋ አይኖቹ ምንም ተስፋ ያለው ነገር አልነበረም ነገር ግን «ያለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል ይህች ከተማ ምድረ በዳ ነች ነገር ግን እግዚአብሄር በዚህ ስፍራ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በእርግኝጠነት እንድሰብክ ያደርገኛል በዚህ አማካይነትም ብዙ ሰዎችን ከሐጢያት ያድናል የራሱንም ቤተክርስቲያን ይመሰርታል» ብሎ የሚያምን እምነት ነበረኝ የእግዚአብሄር ፈቃድ በእኔ በኩል ሊፈጽመው የፈለገውንም አውቄአለሁ ነገር ግን ምንም አልነበረኝም የማውቀውም ሰው አልነበረም ባዶ ነበርሁ::

በመጀመሪያ ደረጃ ለሦስቱ ቤተሰቦቼ ለሚስቱ ለልጅና ለራሴ የሚሆን ቡት ማግኘት ነበረብኝ የሚከራይ ስፍራ ፈለግሁ በአንድ የተጎሳቆለ መንደር ውስጥ አንድ መኝታና ትንሽ ምግብ ማብሰያ ማድቤት ያለው ጥሩ ሁኔታ ላይ ያልነበረ ቤት አገኘሁ ኪራዩ በወር $30 አካባቢ ነበር እኔ ግን ያን ያህል ገንዘብ እንኳን አልነበረኝም ምንም አስተማማኝ ተቀማጭም አልነበረብኝም::

ስለዚህ ወደ እግዚአብሄር ጸለይሁ በዚህ ጉዳይ እግዚአብሄር ስለረዳኝ ቤት ተከራይቼ እዚያ መኖር ቻልሁ ወደዚያ ከመጣን በኋላ የቤት ዕቃዎች አስፈለጉን ይህ አንድ የቤተሰብ መሪ የሚገጥመው በጣም አሳፋሪ ሁኔታ ነበር ተስፋ ቆርጬ ከተማይቱን መዞር ጀመርሁ እግዚአብሄርም ስራ እንዲያገኝልኝ ጸለይሁ «እግዚአብሄር ሆይ እኔ አገልጋይህ አይደለሁምን? እንደሆንሁ አምናለሁ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት አማካይነት ከሐጢያቶቹ አድነኸኛል እኔም እስከ ዛሬ ድረስ አገልግዬሃለሁ አሁን ግን በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ እየገጠመኝ ነው::»

በመጀመሪያ የእግዚአብሄር አገልጋይ መሆኔን ወይም አለመሆኔን በእምነት አጸናሁ በልቤ በእርግጥም የእግዚአብሄር አገልጋይ መሆኔን በልቤ ካመንሁ በኋላ እግዚአብሄርን በድፍረት

«እግዚአብሄር ሆይ እኔ የአንተ አገልጋይ ከሆንሁ ልትረዳኝ ይገባሃል እኔ የአንተ አገልጋይ ካልሆንሁ ብቻዬን ልትተወኝ ትችላለህ እኔ ግን የአንተ አገልጋይ ነኝ አሁን የአንተን ስራ መስራት እፈልጋለሁ ነገር ግን በመጀመሪያ የቤተሰቤ መሰረታዊ ፍላጎቶች መሟላት ያስፈልጋቸዋል ጌታ ሆይ ምን ላድርግ?» ብዬ ጠየቅሁት::

በስጋዬ ላደርገው የምችለው ምንም ነገር አልነበረም የጉልበት ስራ ለመስራት በገበያ ስፍራ ቆምሁ ነገር ግን መስራት አልቻልሁም የአንድ ቀን ስራ ከማገኘው ደመወዝ በላይ ለመድሃኒት መግዣ ብዙ ያስከፍለኛል ሰው ስራ ለማግኘት በማህበረሰቡ ዘንድ ተፈላጊነት ያለው አንዳች አይነት ክህሎት ወይም ችሎታ ሊኖረው ይገባል እኔ ግን እንዲህ አይነት ክህሎቶች አልነበሩኝም::

እኔ ይህንን ሁሉ ዘመን የኖርሁት ጸሎት በሚጸለይበት የተገለለ ማዕከል ውስጥ ስለነበር መሰረታዊ ስለሆኑት የልብስ፣ የምግብና የመጠለያ ፍላጎቶች መጨነቅ አላስፈልገኝም ነበር የምናገርለት የስራ ልምድ ስላልነበረኝ በዚህ አለም ላይ ብቻዬን ከቀረሁ በኋላ ምንም ላደርገው የምችለው ነገር አልነበረም ስለዚህ መጸለይ ጀመርሁ «እግዚአብሄር ሆይ ምን ላድርግ? ጌታ ሆይ እባክህ ደግፈኝ ሚስቴንና ልጄን የምድግፍበትን መንገድ እንዳገኝ እርዳኝ ይህ በጣም ከበድ ያለ ችግር ነው እኔ የአንተ አገልጋይ ነኝ ነገር ግን በእኔ ላይ እየሆነ ያለው ይህ ነገር ምንድነው? እንዲህ የምታገለው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ባለመስበኬ አይደለም ትልቅ ችግር ውስጥ ገብቻለሁ እግዚአብሄር ሆይ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ እፈልጋለሁ እባክህ እርዳኝ» እንዲህ መጸለይ ነበረብኝ::

በከተማይቱ መንገዶች ላይ ያለ አላማ ስዞር ጸለይሁ «ለኑሮ የሚያስፈልገኝን ለማግኘት በእርግጥ ምን ላደርግ እችላለሁ?»

በማለት አጥብቄ አሰብሁ በዚያች ቅጽበት ወደ አእምሮዬ ጸጉር ቤት መጣልኝ ከረጅም ጊዜ በፊት ገና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እየተማርሁ ሳለሁ የአጎቴ ልጅ ጸጉር ቤት ነበረው ስለዚህ ከትምህርት ቤት ከተመለስሁ በኋላ በአጎቴ ልጅ የጸጉር ቤት ውስጥ የደንበኛውን ጸጉር የማጠብ ስራዎችን በመስራት ከዚህ ስራ የኪስ ገንዘብ አገኝ ነበር ነገር ግን ጸጉር የመቁረጥ ክህሎት ኖሮኝ አይደለም ስለዚህ በመሰረቱ ምንም አይነት ክህሎት አልነበረኝም ያም ቢሆን ግን በጸጉር ቤት ውስጥ ስራ ለመፈለግ ወሰንሁ።

በከተማይቱ ውስጥ ከሚገኘው የሰርግ አዳራሽ ትይዩ አንዲት አነስ ያለች ጸጉር ቤት ነበረች አሁንም በእግዚአብሄር ላይ ካለኝ እምነት በቀር ምንም ነገር የለኝም ሌላ መንገድ ወይም ሊወሰድ የሚችል እርምጃ አልነበረም ወደ ውስጥ ስገባ ባለቤቱ ብቻውን እየሰራ እንደሆነ አየሁ።

ስለዚህ «አንዳች እርዳታ ያስፈልገሃልን?» ብዬ ጠየቅሁት እንደሚያስፈልገው ሲነግረኝ ለእርሱ መስራት እንደምወድ ነገርሁት ባለቤቱ ይህንን ስራ ለምን ያህል ጊዜ ስሰራ እንደነበር ጠየቀኝ አፌ አምልጦኝ «ለ20 አመታት ስሰራ ነበር» አልሁት ይህንን የተናገርሁት በእምነት ነበር።

ከዚያም «የመጣኸው ከየት ነው?» ብሎ ጠየቀኝ።

እኔም «የመጣሁት ከቡሳን ነው» አልሁ ቡሳን በኮርያ ሁለተኛዋ እጅግ ትልቅ ከተማ ነች።

እንደገናም «በቡሳን የሰራኸው የት ነው?» ብሎ ጠየቀኝ እኔም «ከተማ ውስጥ መስራት አዘወትር ነበር» ብዬ መለስሁለት የመጣሁት ከቡሳን ነበር ስለዚህ በከተማይቱ ውስጥ እጅግ ባደገው ክፍል ለ20 አመታቶች እንደሰራሁ ተናገርሁ ባለቤቱ ይህንን ከሰማ በኋላ ከሚቀጥለው ቀን ጀምሮ ስራ እንድጀምር ጠየቀኝ።

ስለዚህ በማግስቱ ጠዋት ስራ ለመስራት ወደ ጸጉር ቤቱ ሄድሁ ነገር ግን ባለቤቱ ማልዶ አልከፈተም ቤቱን ከፍቼ ስፍራውን ሳጸዳ የመጀመሪያ ሰው ገባ ለመጀመሪያ ጊዜ መቀሶችን በመያዜ እጄ ተንቀጠቀጠ ከረጅም ጊዜ በፊት የአጎቴ ልጅ የደምበኞቹን ጸጉር ሲቆርጥ አይቼ ስለነበር ጸጉሩን የምቆርጥ ማስመሰል ቻልሁ ነገር ግን ምንም ትክክለኛ የሆነ ክህሎት ስላልነበረኝ እጄ መንቀጥቀጡን ቀጠለ እዚያ ላይ ባቆም ኖሮ እባረር ነበር ስለዚህ «ጌታ ሆይ ጉልበትን ስጠኝ» በማለት በልቤ እየጸለይሁ ጸጉሩን መቁረጥ ጀመርሁ።

መቀሶቹም የተቆራጩን ጸጉር በመቁረጥ ፋንታ ጆሮውን ለመቁረጥ በመሞከር የራሳቸው የሆነ አሳብ ያላቸው ይመስል ነበር ነገር ግን ብንቀጠቀጥም ተሳክቶልኝ የሰውዬውን ጸጉር ቆርጬ ጨረስሁ ጢሙንም ደግሞ ላጨሁለት ያን ጊዜ ግን ከመጠን በላይ እንቀጠቀጥ ነበር በእጅጉ ከመጸለይ በቀር ላደርገው የምችለው ነገር አልነበረም ምክንያቱም ብባረር ሁሉም ነገር ያበቃ ነበርና «ጌታ ሆይ ከእንግዲህ ወዲህ የምጸልይበት ጉልበት እንንን የለኝም እባክህ ጠብቀኝ ጌታ ሆይ አሁን እየሰራሁ ያለሁትን ስራ እንደሰራ እባክህ እርዳኝ።»

እምነቴን በጌታ ላይ አድርጌ ሰውዬውን ላጨሁት ፊቱ ደም በደም ሆነ በተደጋጋሚም በሚደሙት ቦታዎች ላይ ቁራጭ የፊት መጥረጊያ ሶፍት አስቀመጥሁ ሰውየው ግን ተረጋግቶ ተቀምጦ አንዳች ነገር አልተናገረም ባለቤቱም ይህንን አይቶ እንዳላየ ያስመስል ነበር ምንም የተናገረው ነገርም አልነበረም ሰውየው ምን ያህል ዕዳ እንዳለበት ጠየቀ እኔም ክፍያውን ተቀበልሁ በዚያ ክህሎት ይህንን ስራ በመስራት መቀጠል እንደማልችል ግልጽ ነበር።

እኔ ግን «አሁን ማድረግ የምችለው ነገር ቢኖር በእግዚአብሄር ማመን ነው ማድረግ የምችለው ብቸኛው ነገር

ይህ ነው አሁን ነገሩ የመስራት ወይም የመሞት ሁኔታ ነው» ብዬ በማሰቤ በውስጤ ጠንንራ ጽናት ነበረኝ እንደገና «ጌታ ሆይ እባክህ ከዚህ ቦታ እንድባረር አትፍቀድ» ብዬ ጸለይሁ ሆኖም ከሁለት ሰአታት በኋላ ያው ሰውዬ ከቤቱ ተመልሶ በመምጣት ሚስቱ የግብር ይውጣ በሆነው ስራ እንዳጉረመረመች በመናገር እንደገና እንደ አዲስ ጸጉሩን መቆረጥ ፈለገ በዚህ ጊዜ ባለቤቱ ራሱ ጸጉሩን ቆረጠለት ነገር ግን እንግዳ የሆነው ነገር የጸጉር ቤቱ ባለቤት አንዳች ነገር ያልተናገረኝና በመስሪያ ቤቱ ውስጥ በመስራት እንድቀጥል የፈቀደልኝ መሆኑ ነው::

በዚያን ጊዜ 8 ሰአት ሰርቼ ያገኘሁት ገንዘብ ብዙ አልነበረም በኋላ ግን ትንሽ ጭማሪ ተደረገልኝ በኋላ በቀን ወደ $50 አካባቢ አገኘሁ ከዚህ ውስጥ $20 የቤተሰቤን የኑሮ ወጪ በመሸፈኑ ቀሪውን ተቀማጭ እንድታደርገው ለባለቤቴ ሰጠሁዋት በዚያን ጊዜ የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን ለመመስረት እየጸለይሁና ያንንም ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ ምንጮችን እያዘጋጀሁ ነበር በዚያ ጊዜ ስጦታዎችን የሚሰጠን ሰው ስላልነበረ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ እንድችል የአምልኮ ስፍራ ለማግኘት ገንዘብ ማጠራቀም ሞከርሁ::

ጊዜ ሳገኝ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምን ሰው እፈልግ ነበር በስራ ቦታዬ ላይ ስራ ቢኖረኝም ትርፍ ጊዜ ሲኖረኝ ወጣ ብ «የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስማት የምትወዱ ከሆነ እባካችሁ በዚህ የስልክ ቁጥር አግኙን» የሚሉና በእጅ የተጻፉ ማስታወቂያዎችን እለጥፍ ነበር::

ሰዎች ማስታወቂያዎቹን አንብበው በየጊዜው ይደውሉ ነበር አንድ ጊዜ ትምህርቱን በሴሚናሪ ውስጥ የሚከታተል አንድ ሰው ደውሎ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንደማያውቅ ነገረኝ ስለዚህ አገኘሁትና የውሃውንና የመንፈሱን

ወንጌል ሰበኩለት ከዚህ የተነሳ የሐጢያቶቹን ስርየት ተቀበለ የተወሰኑ ሰዎችም የሐጢያቶቻቸውን ስርየት በደስታ ተቀበሉ ነገር ግን ስብሰባ የምናደርግበት ስፍራም ሆነ ክፍል እንኳን አልነበረም ሰዎች የአምልኮ ስፍራ አለመኖሩን ሲሰሙ አዘኑ ወንጌልን ቢሰሙም ትክክለኛ የአምልኮ ስፍራ እንኳን ሳይኖር ወንጌልን መስበኬ ምን ያህል አሳዛኝ ሁኔታ እንደሆነ ከተመለከቱ በኋላ ሁሉም ትተውኝ ሄዱ።

ስለዚህ እንዲህ ስል ጸለይሁ «ጌታ ሆይ ወንጌልን አብሬ ማገልገል እንድችል አጋር ሰራተኞችን ላክልኝ» ለእግዚአብሄር በጸለይሁት መሰረትም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለአንድ የሚሽን ድርጅት መስበክ ቻልሁ አባሎቹም ወንጌልን ከሰሙ በኋላ አሮጌውንና የተሳሳተውን እምነታቸውን ጥለው የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን አብረውኝ መሰረቱ።

በወቅቱ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በምትሰብክ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ ማገልገል ስጀምር የእግዚአብሄር ሰራተኞች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመላው አለም ይሰብኩ ዘንድ የሚሰለጥኑበትን የሚሽን ትምህርት ቤት ከፈትሁ ትምህርቱን ለመስማትም አንዳንድ ያገቡ ሴቶች ወደ መማሪያው ክፍል መጡ ወደ አስር የሚሆኑ ወጣት ወንዶችና ሴቶችም የመጀመሪያ ተርም ተማሪዎች ሆነው በሚሽን ትምህርት ቤት ውስጥ ተመዘገቡ የሚሽን ትምህርት ቤቱን መጀመር የቻልሁት በዚህ መንገድ ነበር።

«እግዚአብሄር ሆይ ወንጌልን ለአለም እሰብንለሁ በኮርያ በእያንዳንዱ ክልል የአንተን ቤተክርስቲያን እተክላለሁ ጌታ ሆይ እባክህ እርዳኝ የአንተን ቤተክርስቲያን እንድተክል እንደምትረዳኝ አምናለሁ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እሰብክ ዘንድም ትፈቅድልኛለህ» በጌታም አመንሁ በዚህም እምነት ጸለይሁ ስለ ድካሞቼም ጸለይሁ እግዚአብሄርን በመታመንም ሁሉን ነገር

አደረግሁ ሁሉን ነገር በእምነት አደረግሁ ማለት ችግር በገጠመኝ ጊዜ ሁሉ ሁሌም በጌታ ፊት ተንበርክኬ የእርሱን እርዳታ ለማግኘት ጸለይሁ ማለት ነው ያደረግሁትንም ሁሉ ያደረግሁት ጌታ በእርግጥም እንደሚረዳን ተማምኜ ነው።

ልክ እንዳመንሁ እግዚአብሄር እነዚህን ነገሮች ሁሉ እንዳከናውን ፈቀደልኝ።

የጌታን ሰራተኞች ያሰለጠንሁትም በጌታ ላይ ባለኝ በዚህ እምነት ነበር የእምነት ወንድሞቼና እህቶቼ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ቢቀበሉም በልቦቻቸው ውስጥ ብዙ የቀሩ የአለም ነገሮች ነበሩ በሌላ አነጋገር ልቦቻቸው በማንኛውም ጊዜ በቀላሉ ወደ ስጋዊ አስተሳሰቦች ሊቀለበሱ ይችላሉ እነዚህ ልቦች የራሴን ቃሎች በማስነማር ብቻ ሊለወጡ ስለማይችሉ በጌታ ላይ ባለኝ እምነት የልቦቻቸውን ክፋት ማስወገድ ነበረበኝ ወደ ጌታም ልመራቸው ይገባኝ ነበር።

የእግዚአብሄርን ቃል በምመሰክርበትም ጊዜ ሁሉ በእምነት መሰክርሁ እነርሱ ስለ እግዚአብሄር ቃልና ስለ እኔ ብዙ ጥያቄዎች ስለነበሩዋቸው የእምነትን ቃል በሚመለከት ብዙ ጉዳዮችን ማስተማር ነበረብኝ የእግዚአብሄርን ቃል ስመሰክርላቸው በልቦቻቸው ውስጥ ያሉት አለማመኖች አንድ በአንድ ይወገዱ ነበር ስለዚህ በሚሽን ትምህርት ቤት አማካይነት የጌታን ሰራተኞች አፈራሁ ሰባኪዎች አድርጌም አሳደግኋቸው የእግዚአብሄርም ቤተክርስቲያን በዚህ መንገድ ተመሰረተች።

በጌታ ማመን ማለት እንደሚከተለው ማመን ነው «እግዚአብሄር አምላኬ ነው ጌታ ሐጢያቶቼን በሙሉ ለአንዱና ለመጨረሻ የደመሰሰ አዳኜ ነው እርሱ የሚረዳኝ እረኛዬ ነው እንደ ጌታ ፈቃድ ብኖርና እርሱንም በእምነት ብከተለው ምንም አይነት ሁኔታዎች ቢገጥሙኝም ለሞት ብቃረብም እንኳን ጌታ

በእርግጠኝነት ይረዳኛል ምክንያቱም እርሱ እረኛዩና አዳኜ ነውና ጌታ ከእርሱ የምጠይቀውን ሁሉ እንደሚሰጠን አምናለሁ አሁንም እንኳን የጌታን ስራ እየሰራሁ ያለሁት በጌታ ላይ ባለኝ እምነት ነው።»

በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንንን በእምነት እኖራለሁ እግዚአብሄርን በመተማመንም እሰራለሁ በእርሱ ሳምን ጌታ ያድነኛል ያሳድገኛልም ችግሮች ሲገጥሙዋችሁ ጌታ እንዲፈታላችሁ ልትጠይቁት ይገባችኋል ብትጠይቁና ጌታ መልስ እንደሚሰጣችሁ በእርግጠኝነት ብታምኑ እርሱ ጸሎታችሁን እንደሚመልስ የተረጋገጠ ነው ጌታን በዚህ መንገድ ስታገለግሉ የሚገጥሙዋችሁን ችግሮች በሙሉ አንድ በአንድ መፍታት ትችላላችሁ በርካታ ችግሮችን ማሸነፍ የምትችሉት በጌታ ላይ ባላችሁ እምነት ነው።

በፊታችሁ ችግሮችና መከራዎች አሉ? በእርግጥም አሉ ማንም ከችግር ነጻ አይደለም ታዲያ ልትፈቱዋቸው የሚገባችሁ እንዴት ነው? እምነታችሁን በጌታ ላይ በማኖር ልትፈቱዋቸው ይገባችኋል በእምነት ወደ ጌታ በመጸለይና የእርሱን እርዳታ በማግኘት ልትፈቱዋቸው ይገባችኋል እምነት ማለት በግልጽ ይህ ነው ስለ ችግሮቻችሁ ብትጸልዩ፣ በእግዚአብሄር ብትታመኑ፣ በእርሱ ላይ ብትደገፉና በእምነት ብትኖሩ ያን ጊዜ እግዚአብሄር ችግሮቻችሁን በሙሉ ይፈታል እውነተኛው እምነት ይህ ነው ይህ መላ ምታዊ እሳቤ አይደለም።

በአንድ የሚሽን ድርጅት ውስጥ መሪ የሆነ አንድ ሰው በየጊዜው በእምነት እንደሚኖር ይናገራል «በኪስ ቦርሳዬ ውስጥ ያለኝ ገንዘብ ቢኖር ለክፉ ጊዜ የምትሆን $10 ብቻ ናት የቤተሰቤን የቤት ወጪዎች ለመሸፈን በወር የሚከፈለኝ $300 ብቻ ቢሆንም በእምነት ስለምጸልይ እግዚአብሄር ይሰጠኛል ስለዚህ የምፈልገውን ለማድረግ ምንም የሚጎድለኝ ነገር የለም»

ይላል እርሱ ግን ራሱን ጉባኤ እያታለለ ነው እኔ እስከማውቀው ድረስ በርካታ የዱቤ ካርዶች አሉት ስለዚህ በካርዶቹ የሚያወጣቸው ማናቸውም ወጪዎች በሚሸን ድርጅቱ መዋዕለ ንዋይ ይሸፈናል ስለዚህ ይህ መጋቢ ለኑሮው ወጪዎች $300 ብቻ እንደሚያወጣ ሲናገር በእግዚአብሄር ፊት የራሱን ጽድቅ ብቻ እያወራ ነው።

በአንጻሩ የእኔ የኑሪ ወጪዎች በወር ከ$1,000 በላይ ነው ሰው እንዴት በወር በ$300 ብቻ መኖር ይችላል? በቤቱ ለ2-3 ቀናት አንዳንድ እንግዶችን ባስተናግድ ከ$300 በላይ አወጣለሁ ገንዘብን አለማባከን እምነት ነውን? ለጌታ ከሆነና አስፈላጊ ከሆነ መባከን የሚገባውን ገንዘብ ሁሉ አባክናለሁ ነገር ግን ገንዘብ በለሌለኝ ጊዜ ወደ ጌታ እጸልያለሁ ምናልባት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ያስፈልግ ይሆናል ለጌታ ከሆነ ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

በጌታ ፊት መኖር እምነትን በእርሱ ላይ በማኖር መኖር ነው ጻድቅ የሆነ ሰው ሁሉ በእምነት መኖር አለበት ጻድቃን የሚሰናከሉት እምነት ስለሚጎድላቸው ነው ሕይወታቸው የሚጎሳቆለውም በእምነታቸው መጉደል ምክንያት ነው በእምነት ቢኖሩ ግን ድክመቶቻቸውን በሙሉ ማሸነፍ ይችላሉ ሁሉንም ነገር ማድረግም ይችላሉ ገንዘብ ለማግኘትም ቢሆን በጌታ መታመን ያስፈልገናል ገንዘብ የምናገኘው ጌታን በማገልገል ነው እዚህ ላይ ምንም የሚያሳፍር ነገር የለም ምክንያቱም ገንዘብ የምንቀበለው ለራሳችን ሳይሆን ለጌታ ነውና አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲሰጠን ጌታን የምንጠይቀው ለዚህ ነው።

ጌታ ውሎ አድሮ ወደሚሰቀልባት ወደ ኢየሩሳሌም ሲቀርብ በደብረ ዘይት ተራራ ወደምትገነው ወደ ቤተፋጌ ደረሰ *«በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ ፈትታችሁ*

ሰምጠልኝ» (ማቴምሰ 21:2) ብሎ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ላከ።

የሆነ እንግዳ ሰው መጥቶ ውርንጫውን ሲወስድበት ባለቤቱ ምን ይላል? «ውርንጫዬን የምትወስዱት ለምንድነው?» ብሎ እንደ ሌባ አይቆጥረውምን? ነገር ግን ጌታ ለደቀመዛሙርቱ ባለቤቱ ይህንን ቢጠይቃቸው «ለጌታ ያስፈልጉታል» ብለው መመለስ እንደሚገባቸው ነግሮዋቸዋል ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ውርንጫይቱን ለማምጣት ችግር አልገጠማቸውም በቃሉ ውስጥ በትክክል እንደተተነበየው ጌታ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ። (ዘካርያስ 9:9)

የጌታ ፈቃድ የሆነው ማንኛውም ነገር ያለ ጥርጥር እንደሚፈጸም የሚያምን እምነት ሊኖረን ይገባል በጌታ ፊት መስራታችንና ለኑሮዋችን የሚያስፈልገንን ማግኘት፣ የእግዚአብሄርንም ወንጌል የማሰራጨቱን ተግዳሮች ለማሸነፍ እንዲህ መኖር በእምነት መኖር ነው እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ጻድቅ በእምነት ይኖራል» (ሮሜ 1:17)* የምንኖረው በእምነት ነው።

በአስተሳሰቦቻችሁ ውስጥ ስለ ጌታ ብዙ አለማመን አለ ሰይጣን በውስጣችን አለማመንን ሊዘራና በእምነት እንዳንኖር ሊከለክለን ይሞክራል እንዲህ በሚሆንበት ወቅት «ሰይጣን ሆይ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዛለሁ ከእኔ ራቅ!» በማለት ዲያብሎስን በእምነት ልናሸንፈው ይገባናል።

በቅርቡ አዲስ ቤተክርስቲያን ለመትከል ወደ አንዲት ከተማ ሔጄ ነበር የአምልኮ ስፍራ ለመፈለግ ከበርካታ አጋር አገልጋዮች ጋር ወደዚያ ሄድሁ ሌሊቱን በአንድ ሞቴል ውስጥ ተኝቼ ሳለሁ ድንገት በሆዴ ውስጥ ስቃይ የተሞላበት ሕመም ተሰማኝ ስለዚህ «ጌታ ሆይ እራቴን የበላሁት አንዳች መጥፎ ነገር አይደለም ታዲያ ሆዴ እንዲህ የሚያሰቃየን ለምንድነው?» በማለት ግራ ተጋባሁ በዚያን ጊዜ በማግስቱ ከቤቱ ባለቤት ጋር

የኪራይ ውል ስለምፈራረምና ይህ ደግሞ ወንጌልን ለዚያ አካባቢ ለመስበክ ወሳኝ የሆነ የመጀመሪያ እርምጃ ስለሆነ ሰይጣን ፈቃዴን ለመደቆስ እየሞከረ እንደሆነ ገባኝ።

ዲያብሎስ ሊገባብን አይችልም ነገር ግን ከውጭ ሆኖ ሊያስጨንቀን ይችላል ስለዚህ በአእምሮዬ «ዲያብሎስ ሆይ! አንተ ሰይጣን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ ከእኔ ራቅ!» ብዬ ጮህሁ ስለዚህ ሰይጣን እንዲርቀኝ አዘዝሁት ወደ እግዚአብሄርም ጸለይሁ በሆዴ ውስጥ የሚሰማኝ ሕመም ከፍተኛ ስለነበር ወደ ጭንቅላቴም አልፎ ነበር ነገር ግብ በዚህ ሌሊት አምቡላንስ ጠርቼ ቢሆን ኖሮ በማግስቱ ከቤቱ ባለቤት ጋር የኪራይ ውል እንፈራረም ስለነበር ብዙ ችግሮች ይገጥሙን ነበር ስለዚህ ሌሊቱን በሙሉ ወደ እግዚአብሄር ጸለይሁ ሰይጣንንም በእምነት አሸነፍሁት ንጋት ሲቃረብ ሕመሜ ሁሉ ለቀቀኝ በማለዳም ተነሳሁ ቁርስ ከበላሁ በኋላ ከቤቱ ባለቤት ጋር ተገናኝቼ የኪራዩን ውል ፈረምሁ።

የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመከተሌ ምክንያት ከወላጆቼና ከወንድሞቼም ተነጥዬ ነበር ይህም ብቻ አይደለም ጌታን እያገለገልሁ ሳለሁ ልጄን አጥቻለሁ በዚያን ወቅት በሌላ ቦታ በአንድ የቤተክርስቲያን ስብሰባ ላይ ተገኝቼ ነበር ትንሹን ልጄን እንዲጠብቅልኝ ለአንድ አብሮኝ ለሚሰራ ወዳጄ በአደራ ሰጥቼው ነበር መስኮቶቹን በሙሉ መዝጋት ረስቶ ስለነበር ሁለተኛው ልጄ በተከፈተው መስኮት ከአራተኛው ፎቅ ላይ ተፈጥፍጦ ሞተ አሁን በሚሸናችን ውስጥ የሚገኘው እያንዳንዱ መስኮት መከላከያ ሽፋን አለው የመከላከያ ሽፋኑን ያደረግሁት በዚህ አሰቃቂ ትዝታና ሁልጊዜም ጥንቃቄ መቅደም ስላለበት ነው ልጆቼን ሲጠብቅልኝ የነበረውን አጋር ሰራተኛም አልወቀስሁትም «ለዚህ አደጋ ማንንም አልቃወምም ማንንም በሐላፊነት አልጠይቅም» የሚል የጽሁፍ ማስታወሻም ለፖሊስ

ሰጥቻለሁ በዚህ ምክንያት የተከሰቱትንም ማናቸውንም ኪሳራዎች በሙሉ ወዲያውኑ ከፍያለሁ ባለቤቴና እኔም ተቃጥሎ አመድ የሆነውን ልጄን ቅሪተ አመድ በወንዙ ላይ በትነነዋል።

ልጄ ከመሞቱ በፊት ጌታ መቼ እንደሚወስደው ስለማላውቅ ሁሌም በእቅፌ ውስጥ አድርጌ ወንጌልን አስተምሬዋለሁ ብዙ ጊዜም «ልጄ ሆይ እንደምወድህ ታውቃለህ አይደል? እግዚአብሄርም ደግሞ በዚህ መንገድ ይወድሃል ስህተቶችህ ሐጢያቶች ናቸው ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መጣ በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅም እነዚህን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ ተሸከማቸው በመስቀል ላይ በመሰቀልም ደመሰሳቸው» በማለት ነግሬዋለሁ።

በቻልሁት መጠን ብዙ ጊዜ ስለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል ነግሬዋለሁ አንዳንድ ሰዎች እንዴት አንድ ትንሽ ልጅ ይህንን ሁሉ መረዳት ይችላል ብለው ግራ ይጋቡ ይሆናል እኔ ግን ልጅ የወላጁን ልብ መረዳት ይችላል ብዬ አምናለሁ ወላጆች በእምነት ለልጆቻቸው ወንጌልን ሲያስተምሩ ልጆችም ያንን ይቀበላሉ እኔም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለልጄ አስተማርሁት ልጄ ግን ወደ እግዚአብሄር ሄደ «ልጄ ሆይ ደህና ሁን» ቅሪተ አመዱንም ወንዝ ላይ በተንሁት።

በዚያ ምሽት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰበክሁ በዚያ ቀን በስብሰባው ላይ የተገኙ ሰዎችም የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ተቀብለዋል እኔ የራሴን ልጅ አጣሁ ጌታ ግን በዚያ ቀን ሌላ መንፈሳዊ ልጅ ሰጠኝ።

ባለቤቴን «ልጆቻችን ሲያድጉና ሲከናወንላቸው ተስፋችንን በእነርሱ ላይ አናኖርም? እግዚአብሄር አስቀድሞ ልጃችንን የወሰደው ተስፋዬን በዚህ ምድር ላይ ባለ በማንኛውም ነገር ላይ እንዳላደርግ ነው ስለዚህ ውዴ ሆይ ያጣነውን ነገር እኔ

እንደተቀበልሁት ልትቀበይው ይገባል ከእንግዲህ ወዲያም አናልቅስ ይህ ሁሉ የሆነው እኔ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለመስበክ በመሄዴ ነበር ይህ በእግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ነገር ነው» አልኋት እምነቴንም በእግዚአብሄር ላይ አድርጌ ተንበረከክሁ።

እኔም ራሴ ሰው ስለሆንሁ ልጆቼ በዚህ አለም ላይ ቢሳካላቸው እኔም በእነርሱ ላይ እደገፍ ነበር ነገር ግን ሁሉንም ነገር በጌታ ላይ ባለኝ እምነት አሸንፈዋለሁ ያደረጉትን ሁሉ ያደረግሁት በእምነት ነው እናንተም እንደዚሁ ምንም አይነት ችግሮች ቢገጥሙዋችሁና እግዚአብሄርን የሚያስደስተውን ነገር ምን ቢሆን ሁሉንም ነገር በእምነት መፍታት አለባችሁ በጌታ ላይ እምነት ሳይኖረን ወደፊት መግፋት አንችልም የእግዚአብሄርንም ስራ መስራት አንችልም።

የሚሽን ድርጅታችን መስራች አባሎች የሆኑትን የምዕመናኖች ቡድን ሳገኝ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ከቤት ውጭ ባለ ስፍራ ሰባኪ እንድሆን ጋበዙኝ ነገር ግን የተመደበልኝ ሰዓት ከሌሊቱ 11 ሰዓት (በኢትዮጵያ ከሌሊቱ 5 ሰዓት አካባቢ) ነበር በጣም መሸቶ ነበር እኔ ግን ግድ አልነበረኝም እንደ ሁልጊዜው በዚህ ጊዜም በእምነት ሰበክሁ ከመስበኬ በፊት ወደ ድንኳኔ ሔጀ «እግዚአብሄር ሆይ በዚህ ጉባኤ ላይ በዚህ ስፍራ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የሐጢያቶቹን ስርየት የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ወንጌል በዚህ ጉባኤ ላይ መሰበኩ የተሳካ አይሆንም ስለዚህ እግዚአብሄር ሆይ ይህ ስብሰባ በጣም አስፈላጊ ነው ይህንን ጉባኤ ትጠቀምበት ወይም አትጠቀምበት እንደሆነ የሚታወቀው በዚህ አጋጣሚ ነው ነፍሳቶች መዳን አለባቸው» ብዬ ወደ እግዚአብሄር ጸለይሁ።

በዚያ ስፍራ የከሰት በኋላው ሰአታቶች ለቡድን ሕብረት የተመደቡ ነበሩ አንዳንድ ሰዎች ዋና ለከመዋኘት ሲሄዱ ሌሎች

ደግሞ አሳ ለማጥመድ ሄዱ ይህ የሕብረት ስብሰባው የታወቀ ክፍል ነበር ስለዚህ ወንጌልን በመሸ ሰአት ስሰብክ አድማጩ በቀኑ ፕሮግራም በጣም ተዳክሞ ስለነበር ብዙዎቹ ያንጎላጁ ነበር ይህም የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል በትክክል የመሰበኩን ነገር አዳጋች አደረገው።

ከፊት ለፊቴ ያለው መንገድ ረጅም ነበር ብዙ የምናገረው ነገርም ነበረኝ ነገር ግን ስብሰባውን የመምራት ስልጣን ስላልነበረኝ እንደምፈልገው ልመራቸው አልቻልሁም ስለዚህ ከቀትር በኋላ በየጊዜው ብቻዬን ወደ ተራራ እወጣ ነበር ከጸሎት በኋላም ወደ ካምፑ ተመልሼ ለማታ እራት ያጠመዱዋቸውን አሶች እመለከት ነበር መናገር የምችለው ነገር ቢኖር «ለጥረታችሁ ሁሉ አመሰግናለሁ እንብላ» የሚል ብቻ ነበር።

የሕብረት ስብሰባው ናበቃ በኋላ የምትወስደኝን አውቶቡስ እየጠበቅሁ ሳለሁ ከአንዳንድ አማኞች ጋር ትንሽ ንግግር ብጤ አደረግሁ ከዚያም ጥቂት ወጣቶች ቀረቡኝ እግዚአብሄር ጊዜውን አዘጋጀልኝ በዚያን ወቅት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንደገና ለእነርሱ መስበክ ቻልሁ «የሰው ሐጢያት ምንድነው? ልክ እንደ ማዕበል ነው ማዕበሉ ሲንቀሳቀስ መምጣቱን ይቀጥላል ሰዎች እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ሐጢያት በመስራት ይቀጥላሉ ምንም ያህል ሊከላከሉት ቢሞክሩም ማዕበሉ በየጊዜው መጋጨቱን ይቀጥላል የሐጢያት ባህሪይ ይህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመጠመቅ እነዚህን ሐጢያቶች በሙሉ ተቀብሎዋል።»

አሁን መጋቢ የሆነው ወንድማችን ዎንኪ ቾይ ወንጌል የተቀበለው ያን ጊዜ ነበር ሌሎች በርካታ ወጠት ወንድሞችና እህቶችም እንደዚሁ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ተቀብለዋል የወንጌል ስራ የተነሳው እንዲህ ነበር።

የዚያ ጉባኤ መሪ ለነበረው ለሚሲዮናዊው ዮንጋዋ ሊ በሰበኩለት ጊዜ ያንን ያደረግሁት በእምነት ነበር በዚያን ጊዜ በቤቱ ተጋብዤ ነበር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ በሶፋ ላይ ተቀመጥሁ እርሱም እንዲህ አለኝ «አንድ ነገር ብቻ ልጠይቅህ::»

እኔም «ምንድነው?» አልሁት::

እርሱም «እግዚአብሄር ያዕቆብን ሲወድ ኤሳውን የጠላው ለምንድነው? ይህ ሊገባኝ አልቻለም» አለኝ እኔም «መጽሐፍ ቅዱስህን አምጣ» አልሁትና የሮሜን መጽሐፍ ምዕራፍ 9ን ከፍቼ መናገር ጀመርሁ::

«ዚህ ላይ 'ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሄር አሳብ ይጸና ዘንድ' ይላል እግዚአብሄር ማንን ጠራ? እርሱ የጠራው እንደ ያዕቆብ ያሉ ሰዎችን ነው እርሱ የጠራው ምስኪኖችን፣ ፈሪዎችንና የተዋረዱትን በእግዚአብሄር ቢያምኑም የሚመኩበት ምንም ነገር የሌላቸውን ሰዎች ነው እግዚአብሄር የሚጠራቸውና የሚያድናቸው እነዚህን ነው እግዚአብሄር ያዕቆብን የወደደው ኤሳውን ግን የጠላው እንደ ኤሳው ያሉ ሰዎች በእርሱ ላይ ከመደገፍ ይልቅ እግዚአብሄርን ስለሚቃወሙት በራሳቸው መልካምነት በጣም የበረቱ ስለሆኑ ነው::»

ያን ጊዜ ሚሲዮናዊው ሊ እንዲህ አለኝ «በዚህ ሁሉ ጊዜ ብዙ አንብቤአለሁ ብዙም ተምሬአለሁ ነገር ግን ይህንን ጉዳይ እንዲህ ጥርት ባለ መንገድ በማብራራት በኩል የመጀመሪያው ሰው አንተ ነህ::»

የንባብ ልምዱን ስመለከት ብዙ መጽሐፎች እንዳሉት አየሁ ነገር ግን «እነዚህን መጽሐፎች በሙሉ ወደ መገልገያ ማጠራቀሚያ ልትወስዳቸው ይገባሃል እኔ ከአስር አመታት በፊት አንብቤ ጨርሻቸዋለሁ ነገር ግን በውስጣቸው ነፍስን

የሚያበላሽ እርሾ እንጂ ምንም እውነት የለም ልትጥላቸው እስከማትችል ድረስ ከእነርሱ ጋር ቁርኝት ካለህ ለአሁን አስቀምቸው ነገር ግን ምን ያህል ዋጋ እንደሌላቸው ስትገነዘብ አስወግዳቸው::»

በዚያን ጊዜ የቤተክርስቲያን ሁኔታ እንደዚህ ስለነበር ሚሲዮናዊውን ሊን መጋቢ አድርገን መሾም ነበረብን ያን ጊዜ የቤተክርስቲያን ስርአት ስርአት ተመሰረተ ነገር ግን ዳግም ያልተወለደን ሰው የእግዚአብሄር አገልጋይ አድርገን መሾም እንችላለን? ስለዚህ «እግዚአብሄር ሆይ ይህንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለእርሱ ስሰብክ ቢያንስ በዚህ ወንጌል ማመን ይኖርበታል በፊት ሐጢያት ከመስራት ማምለጥ የምችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው የአንተም ስራ በትክክል የሚከናወነው ያን ጊዜ ብቻ ነው» ብዬ ጸለይሁ::

እንዲህ ብዬ ወደ እግዚአብሄር ከጸለይሁ በኋላ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በእምነት ሰበክሁ ሚሲዮናዊው ሊ በዚያን ቀን በወንጌል አልተፈወሰም ነገር ግን አሁንም ጥቂት ጊዜ ወስጄ ለመጠበቅ ወሰንሁ ስለዚህ ወንጌልን ደረጃ በደረጃ ማብራራት ቀጠልሁ ስለዚህ ቃሉን በቀጥታ ለሚሲዮናዊው ሊ ሰበክሁ በጣም ብዙ ሌሎች ጥያቄዎች ስለነበሩት የእግዚአብሄርን ቃል በእምነት በጥልቀት መፍታትና ማብራራት ነበረብኝ በመጨረሻ ሬቨረንድ ሊ ዳነ የእግዚአብሄርም አገልጋይ ሆነ ከእኛ ም ጋር አብሮ በእምነት ወንጌል አገለገለ ከእኛ በፊትም ወደ ጌታ ሄደ::

ከእናንተ በፊት ባሉት አገልጋዮች ለመታመንና እነርሱን ለመከተል እምነት ያስፈልጋችኋል በጻድቃን ሕይወት ውስጥ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምን እምነት የማይጠይቅ ምንም ነገር የለም የእምነት ቀደምቶቻችንን ያዘዙትን መታዘዝም እንደዚሁ እምነትን ይጠይቃል እነርሱን መከተልም

እንደዚሁ እምነትን ይጠይቃል ሁሉም ነገር እምነትን እንደሚጠይቅ የታወቀ ነው የእምነት ቀደምቶች አንድ ነገር እንድታደርጉ ቢጠይቁዋችሁ እግዚአብሄር በመሰረተው ስርአት ላይ እምነት ከሌላችሁ ቃሎቻቸውን መታዘዝ የማይቻላችሁ አይሆንምን?

እምነታችንን በእግዚአብሄር ቃልና በጌታችን ላይ በማኖር መኖር አለብን «ወንጌል በመላው አለም ይሰበክ ዘንድ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው ስለዚህ ወንጌልን መስበክ አለብን በእርግጥም ወንጌል ያለ ችግር ይስፋፋል» እንዲህ ስናምን እንዲህ ያሉት የእምነት ምግባሮች ከውስጣችን ይፈልቃሉ የእምነት ቀደምቶቻችን እንድናደርግ የሚጠይቁንን ማስተዋል ባንችልም እምነት ካለን ልቦቻችንን ከእነርሱ ጋር እናስተባብርና «አዎ» ብለን እንታዘዛለን ከእኛ መለኪያዎች ጋር ባይስማማና የራስ ማንነታችንን የሚጎዳ ቢሆንም የወንጌልን ጥቅም የሚያስቀድመውን ማንኛውንም ነገር እንድናደርግ የሚያስችለን እምነት ነው።

ክርስቲያኖች ወንጌልን ለአለም መስበክ እንዳለባቸው አሳምረው ያውቃሉ ነገር ግን ይህንን በተጨባጭ ለማድረግ ራሳቸውን አያዘጋጁም ምንም ያህል ጠንክረው ቢሞክሩም የተለመደው ወንጌልን የመስበክ ዘዴ በሙሉ ከንቱ ነው አንድ ሚሲዮናዊ ወደ አንድ አገር ቢሄድ፣ የአካባቢውን ባህል ቢለምድ፣ ቤተክርስቲያን ቢሰራ፣ እንደ ሆስፒታል ወይም ትምህርት ቤት ያለ የማህበራዊ አገልግሎት ማዕከል ቢከፍትና የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን አባሎች ቢያገኝ ይህ ሚሲዮናዊ አስደናቂ ስኬት አግኝቷል ወደ ሕንድ ሔዶ በዚያ ወንጌልን የሰበከው የዊሊያም ኬሪ ስራዎች ወደ ቻይና ሄዶ ወንጌልን የሰበከው የሐድሰን ቴይለር ስራዎች በክርስቲያን ሚሽን ታሪክ ውስጥ አስደናቂ እመረታዎች ሆነው ቀርተዋል።

ነገር ግን እኛስ? እኛ በጽሁፎቻችን አማንይነት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመላው አለም እየሰበክን ነው ኢየሱስ ለመመለስ ትንሽ ጊዜ ቢወስድ በታሪክ ውስጥ እውነተኛውን ወንጌል በመስበክ ወሳኝ አገልግሎትን የፈሰሙ ሰዎች ሆነን እንቆጠር ነበር ሰዎች አሳንሰው ቢመለከቱንም እኛ ትልቅ እምነት የነበረን ሰዎች እንደሆን ወደ መረዳት ይመጣሉ አሁን እኛ የምንኖረው በእምነት ነው እስከ ዛሬ ድረስም ጌታን በእምነት አገልግለናል በመጪዎቹም ቀናት ይህንን ማድረጋችንን እንቀጥላለን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *«እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።» (ዕብራውያን 11:1)*

የእግዚአብሄር ስራ ሊሰራ የሚችለው በእምነት ብቻ ነው ዲያብሎስም የሚሸነፈው በእምነት ነው ጠላቶቻችንም ድል የሚመቱት በእምነት ነው ሁሉም ነገር የሚከናወነው በእምነት ነው መኖርም እንዲሁ በእምነት የሚደረግ ነው ጌታን በማመን ልንኖር ይገባናል በእምነትም ከጌታ ጋር መተባበር አለብን እርሱንም በእምነት ልንከተለው ይገባናል ጉልበት ስታጡ መኖር የምትችሉት በእምነት ብቻ ነው የራሳቸሁ ብርታት እስንላችሁ ድረስ በእምነታችሁ ላይ አትደገፉም።

ሰጎኖች ግዙፍ ክንፎች አሉዋቸው በእነዚህ ክንፎች መብረር ቢፈልጉ ከንስርም እንኳን በልጠው በፍጥነት መብረር ይችሉ ነበር እነርሱ ብርቱዎች ናቸው ሰው በጀርባቸው ላይ ተቀምጦ እንኳን ልክ እንደ ፈረስ መሮጥ ይችላሉ ሰጎኖች ይህን ያህል ትልቅና ብርቱዎች ናቸው በሰዓት 80 ኪሎ ሜትር (50 ማይሎች) መሮጥ ይችላሉ ነገር ግን ቅልጥሞቻቸው በጣም ጠንንሮች ስለሆኑ ፈጽመው ለመብረር አይሞክሩም ምክንያቱም የመብረሩ አስፈላጊነት አይታያቸውምና።

ነገር ግን ሰጎን ቅልጥሞችዋ ከተቆረጡ በኋላ ክንፎችዋን

ትጠቀማለች እንደ አንበሳ የሳለ አዳኝ ሲያሳድዳት ክንፎችዋን ዘርግታ ሞትን ለማምለጥ ትሞክራለች ሰውነቷም ይበራል «ዋው እንዲህ አይነት ምርጥ ክንፎች እንዳሉኝ አላውቅም ነበር» ሰጎን ንስርን ማሸነፍ የምትችለው ስትበር ብቻ ነው ሰጎን እንድትበር ለማድረግ ቅልጥሞችዋን መቁረጥ አለብን ስትተኛ ቅልጥሞችዋን መቁረጥ አለብን ያን ጊዜ ከመገብናትና ቁስሎችዋን ለጥቂት ጊዜ ከጠገንላት በወር ውስጥ ትበራለች ዶሮም ቅልጥሞችዋ ከተቆረጡ መብረር ትችላለች ዶሮዎች ብዙ ሳይዘገዩ እንዲበሩ ማድረግ ይቻላል ልክ እንደተወለዱ ቅልጥሞቻቸው ቢቆረጡና ከቁስሎቻቸው ቢድኑ መራመድ ስለማይችሉ ይበራሉ።።

ጌታን በመታመን መኖር ያትችሉት ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁን? በእምነት ልትኖሩ የማትችሉት ጉልበታችሁ በጣም ጠንካራ ስለሆነ ነው ሌላ የምትደገፉበት ነገር ስላላችሁ ነው እኔ ልደገፍበት የምችለው ሌላ ምንም ነገር የለኝም ከቤቴ፣ ከጓደኞቼና ከቀድሞ ቤተክርስቲያኔ ተሰድጃለሁ።።

ጠባያችሁ እንከን የለሽ ከሆነ፣ የሰላ አእምሮ ካላችሁ ወይም በራሳችሁ ብርቱዎች ከሆናችሁ በእነዚህ ነገሮች ላይ ትደገፋላችሁ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ምንም እንዳልሆኑ ከተገነዘባችሁ በኋላ ግን በጌታ ቃል ብቻ ወደ መታመንና በእምነት ወደ መኖር ትመጣላችሁ ጻድቅ በእምነት ብቻ ይኖራል በእምነት የምንኖረው ሁሉም ነገር ሲሳካልን ብቻ አይደለም ችግሮች ሲገጥሙንም በእምነት እንኖራለን ወደ እግዚአብሄር የምንጸልየውም ያን ጊዜ ነው።።

እግዚአብሄር አስቸጋሪ ሁኔታዎችን መፍቀዱ እምነትን ሊሰጣችሁ ስለፈለገ እንደሆነ ልታምኑ ይገባችኋል ጸሎቶቻችሁን በሙሉ እንደሚመልስ በማመንም ወደ እግዚአብሄር ልትጸልዩና እርሱን ልትከተሉ ይገባችኋል እኔ ከራሴ የምጠብቀው ምንም

ነገር የለም እኔ ተሳዳቢና ቁጡ ነኝ ምሁር አይደለሁም ብርቱም አይደለሁም ሁሉም አይነት የጤና ችግሮች አሉብኝ አጭርና ወፍራም ነኝ እንደ እኔ ያለውን ሰው ማን ይወደዋል? ምንስ የምደገፍበት ነገር አለኝ? ምንም የምደገፍበት ነገር የለኝም።

አሁንም የራሳችሁ በሆነ ነገር ላይ እየተደገፋችሁ ነውን? የስጋ ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ልትገነዘቡ ይገባችኋል አሁን የምንበላው በቂ እንጀራ ካለን ለዕለት እንጀራችን አንጸልይም ነገር ግን እንጀራ ከሌለ ለእርሱ እንጸልያለን ወደ እግዚአብሄር የምንጸልየውና የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት እርሱን የምንጠይቀው ጉድለቶቻችንን ስንገነዘብ ነው የምንጸልየው የእግዚአብሄር ስራ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ስንገነዘብ ነው እምነት ይህ ነው።

አጋር ምዕመናኖቼ ጌታን ማገልገል ምን ያህል የከበረ እንደሆነ ስትገነዘቡ ሁላችሁም በእምነት ትኖራላችሁ። ✉

ልቦቻችሁን በእግዚአብሄር ፊት አጽኑ

« ዘፍጥረት 1:20-23 »

«እግዚአብሄርም አለ ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ እግዚአብሄርም ታላላቆች አንበሪዎችን ውሃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው ብዙ ተባዙም የባሕርንም ውሃ ሙሉአት ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አምስተኛ ቀን::»

እግዚአብሄር ወፎች በሰማያት ጠፈር ላይ እንዲበሩና አሶችም በውሃ ውስጥ እንዲበዙ ወፎችና አሦችም ፍሬያማ እንዲሆኑና እንዲበዙ አዘዘ ይህም ጻድቃን የተትረፈረፉ ፍሬዎችን ለማፍራት በእምነት መኖር እንደሚገባቸው ያመላክታል ጻድቃን በእግዚአብሄርና በቃሉ በቤተክርስቲያኑና እግዚአብሄር በራሱ ቤተክርስቲያን አማካይነት የሚመራቸው በመሆኑ እውነታ ማመን አለባቸው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ የእግዚአብሄር ፈቃድ እንደሆነ ሲገነዘቡና ሲያምኑ በስጋና በመንፈስ ድል ማድረግ የሚችሉ በመሆኑ የተስፋ ቃል ላይ እምነት ሊኖራቸው ይገባል::

በሌላ አነጋገር ጻድቃን ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ላይ

ማጽናት አለባቸው ፈቃዱን እየታዘዝን በእግዚአብሄር ፊት እንድንኖር አእምሮዋችንን ማዘጋጀት አለብን እምነታችንንም በእግዚአብሄር ላይ በማኖር መኖር አለብን እግዚአብሄር አሳ በውሃ ውስጥ እንዲበላ አዘዘ እግዚአብሄር በእምነት እንድንኖር አእምሮዋአችንን እናዘጋጅ ዘንድ ነግሮናል ይህንን የተናገረበትም ምክንያት ልንኖር የሚገባን በእግዚአብሄር ፈቃድ መሰረት በመሆኑ ነው።

ልቦቻችን በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት አለባቸው

በብሉይ ኪዳን የዘሌዋውያን መጽሀፍ ምዕራፍ 11 የሚበሉትንና የማይበሉትን የወፎችና የአሦች አይነት ይዘረዝራል ከእነዚህ ውስጥ በተለምዶ የምናያቸው አሳ አውጪ ወፎች የማይበሉ ርኩሳን ወፎች ናቸው አሳ አውጭዎች ብዙውን ጊዜ ጥልቀት በሌለው ውሃ ውስጥ ቆመው የሚያልፍ አሳን ይጠብቃሉ ዝም ብለው ስለሚቆሙ የተተከሉ ይመስላሉ ነገር ግን አንድ አሳ በአጠገባቸው እየዋኘ ሲያልፍ እነዚህ አሳ አውጭዎች ወዲያውኑ ለቀም ያደርጉታል መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ወፎች ርኩስ ወፎች እንደሆኑ ይናገራል በመንፈሳዊ አነጋገር እነዚህ ወፎች ልክ እንደ ሰይጣን አገልጋዮች ናቸው።

የእግዚአብሄር ቃል ወፎችንና አሳን በሁለት አይነት አንዱ የሚበላ ሌላውን የማይበላ አድርጎ ቢለያቸውም እኛ ይህንን ቃል በቃል በስጋዊ መንገድ በመተርጎም ለምንኖረው ሕይወታችን ልናውቀለው አንችልም እግዚአብሄር ወፎችን ንጹህና ርኩስ አድርጎ የከፈላቸው የተወሰኑ መንፈሳዊ እውነቶችን ሊያስተምረን እንደነበር አሳምረን ልናውቅ ይገባናል።

እግዚአብሄር አሳንም ንጹህና ርኩስ አድርጎ ለይቶታል ከእነዚህም ውስጥ ክንፎችና ቅርፊቶች ያሉዋቸው እንዲበሉ ፈቅዶዋል በሌላ በኩል ክንፎችና ቅርፊቶች የሌሉዋቸው እንዳይበሉ ተከልክለዋል ይህ የሚያመላክተው የእምነት ሕይወታችንን በሚመለከት እምነት አልባ ሕይወታችንን መጣልና እግዚአብሄርን በመታመን ብቻ መኖር እንደሚገባን ነው በውሃ ውስጥ ክንፎች የሌሉዋቸው አሦችን ማግኘት እንደምንችል እናውቃለን ክንፎችና ቅርፊቶች የሌሉዋቸው አሦች የሚያመላክቱት እምነት የሌለውን ሕይወት የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ነው።

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ወንዞች ስለተበላሹ ይህንን ማድረግ ያዳግታል በፊት ወንዞቹ ንጹህ በነበሩ ጊዜ ግን በሚሸን ትምህርት ቤት ውስጥ ካሉ ተማሪዎች ጋር ለመዝናናት አዘውትሬ እሄድ ነበር በአንዲት ትንሽ ከተማ ውስጥ በአንድ አዲስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስናገለግል በነበርንበት ጊዜ የምንበላው በማይኖረን ጊዜ መረብ ይዘን ወደ ወንዝ በመሄድ አሳ እናጠምድ ነበር ወንዙ ውስጥ እንገባና መረቡን ከወንዙ በታች እንዘረጋለን ከዚያም እንደ አምባዛና ቆሮሶ ያሉ አሶችን እናጠምድ ነበር አምባዛና ቆሮሶ ብዙውን ጊዜ የሚመገቡት ትናንሽ አሦችን ነው ስለዚህ በአብዛኛው የሚከማቹት ብዙ ሊጠመዱ የሚችሉ ትናንሽ አሦች ባሉባቸው አካባቢዎች ነው።

እግዚአብሄር ቅርፊቶች ያሉዋቸውን አሦች እንድንበላ ቅርፊቶችና አሦች ያሉዋቸውን አሦች እንዳንበላ ነግሮናል ክንፎች የሌሉዋቸው አሦች ጠንካራ የውሃ ግፊት ባለበት አካባቢ አይኖሩም በአንጻሩ ክንፎችና ቅርፊቶች ያሉዋቸው አሦች በማንኛውም ስፍራ ጠንካራ የውሃ ግፊቶች ባሉበት ስፍራም ቢሆን መዋኘት ይችላሉ ክንፍ ያለው አሳ የውሃ ግፊቱን ተቋቁሞ መዋኘት ይችላል።

እንደምናውቀው ሳልሞን የሚባሉ አሶች ቤታቸውን የሚያውቁበት ደመ ነፍስ አላቸው ወደተወለዱበት ስፍራ ለመመለስ ከውሃው በላይ ይዋኙና ሕይወታቸውን አደጋ ላይ በመጣልና ሁሉንም አይነት እንቅፋቶች በመቋቋም እዚያ እንቁላላቸውን ይጥላሉ እንቁላላቸውን የሚጥሉት ወደተወለዱበት ስፍራ ከተመለሱ በኋላ ብቻ ነው አሳ ክንፎች አሉት ማለት ወደሚፈልገው ቦታ መሄድና መኖር ይችላል ማለት ነው።።

በሌላ በኩል ክንፎች የሌሉዋቸው አሦች የውሃውን ግፊት ተቋቁመው መዋኘት አይችሉም እነዚህ አሦች ወደተሻለ ስፍራ ለመሄድ በጣም የጠበበ ተግዳሮት ይገጥማቸዋል በአካባቢያቸውም እንኳን ብዙ መንቀሳቀስ አይፈልጉም ዘመናቸውን በሙሉ በአንድ ስፍራ በመዋለድና በመሞት በተወለዱበት ስፍራ ይኖራሉ።።

ከዚህ የምናገኘው መንፈሳዊ ትምህርት ቢኖር እኛ ጻድቃኖች ልክ ክንፍ እንዳለው አሳ ነን ነገር ግን እኛ ለጌታ መኖር የምንፈልግ ከሆነ ማድረግ የሚገባን የመጀመሪያው ነገር ልቦቻችንን በእግዚአብሄር ላይ ማጽናት ነው እምነታችን ይህ ነው እኛ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ብቸኛው እውነት እንደሆነ እናምናለን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመንም ድነናል ከእግዚአብሄር ሕዝብ ጋር አብረን አለን ከአሁን ጀምሮ ለወንጌል መኖር አለብን ስለዚህ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን የእኛ ናት አሁን የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ቤታችን ነች ያዕቆብ የድንጋይ ትራስ ተንተርሶ በሜዳ ባንቀላፋ ጊዜ የእግዚአብሄር መላዕክቶች በመሰላል ላይ ሲወጡና ሲወርዱ አይቶ «ይህ የእግዚአብሄር ቤት ነው» በማለት መሰከረ ልክ እንደዚሁ እኛም የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን አሁን ቤታችን እንደሆነች እንመሰክራለን።።

እኛ ከሐጢያቶቻችን ከዳንን በኋላ አሁን ወደ እግዚአብሄር ቤተክርስቲያን መጥተናል አሁን በውስጥዋ እየኖርን ነው ነገር ግን አንዳንዶቻችን ነጻ ስንወጣ አንዳንዶቻችን ገና ልቦቻችንን ነጻ አላወጣንም ዳግም በተወለዱ ክርስቲያኖች መካከል ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ያጸኑ ሰዎች አሁን የእግዚአብሄር ወገን ናቸው ሁላችንም አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ ወገን እንደሆንን የሚያምኑና ይህንን እምነት የሚጠብቁ ሰዎች ነን።

እነዚህ ሰዎች «ሁላችንም የእግዚአብሄር ሕዝብ ነን እነዚህ ሁሉ የእኔ ወገን ናቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ የእግዚአብሄር ሰዎች የእኔ ወገን ናቸው እኛ በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ መስራታችን ጌታን ማገልገል ነው» ስለዚህ ልቦቻችን እንዲህ መዘጋጀት አለባቸው።

በሌላ አነጋገር ጻድቃን በኤዞፕ ልብ ወለድ ውስጥ እንዳለው የሌሊት ወፍ ቀን አይጥ ሌሊት ደግሞ ወፍ ነን እያሉ ወደኋላና ወደፊት አይንጠራወዙም የሌሊት ወፍ በአእዋፋትም ሆነ በእንስሶች ዘንድ ተቀባይነት የለውም ስለዚህ የሚኖረው በጨለማ ጫካ ውስጥ ነው ሌሎቹ አእዋፋት በሙሉ ተስማምተው ሲኖሩ የሌሊት ወፍ ግን ከቀሩት ተለይቶ ብቻውን ይኖራል።

ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ላይ ያላጸኑ ሰዎች የሚጠሉት በእግዚአብሄር ብቻ አይደለም የዚህ አለም ሰዎችም ሊጠሉዋቸው ይችላሉ ልቦቻችን የእግዚአብሄርን ፈቃድ መታዘዝና ለእርሱም መገዛት አለባቸው ልቦቻችን ለእግዚአብሄር ጽድቅ የመኖር ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል «የእግዚአብሄር አገልጋይ ስለሆንሁ ከእንግዲህ ወዲህ ለእግዚአብሄር ጽድቅ ብቻ እንጂ ለዚህ አለም አይደለም» ብለን በመወሰን ልቦቻችንን ማጽናት አለብን በሌላ አነጋገር ልቦቻችን በመጀመሪያ በእግዚአብሄር ጽድቅ የማመን፣ እርሱን የመከተልና የመታዘዝ

ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ያለ ቆራጥ ልብ ነበረው *«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሄር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» (ገላትያ 2:20)* ያለው ለዚህ ነው።

ስለዚህ ክርስቶስን በሕይወታችን አማንይነት በክብር እንድናገለግለው ከፈለግን ለእርሱ ለመኖር ልቦቻችንን ማጽናት አለብን እግዚአብሄር ልባቸው ለአምላክ ጽድቅ ፍላጎት የሌላቸውን ሰዎች አይባርካቸውም እግዚአብሄር የሚሰራው በእርሱ ጽድቅ በሚያምኑና በእርሱ በጸኑ ልቦች ውስጥ ነው እግዚአብሄር በቃሉ ከሚያምኑ የእምነት ሰዎች ጋር አብሮ አለ ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ላይ ባጸኑ ሰዎች ይደሰታል እግዚአብሄር የሚረዳቸውም እነዚህን ሰዎች ነው እግዚአብሄር የእነዚህን ሰዎች ልቦች ያበረታል መንፈሳዊ አይኖቻቸውንም ይከፍታል እንዲህ በማድረግም በእርሱ ስራ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

በአንጻሩ እግዚአብሄር ልቦቻቸውን ያላጸኑ ሰዎችን አይባርክም ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ላይ ያላጸኑ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄርን ስራ መስራት እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው ግራ ይጋባሉ።

ለእግዚአብሄር ጽድቅ መኖር የምንችለው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማገልገል ጻድቃን ሊኖሩበት የሚገባው ትክክለኛ ሕይወት መሆኑን ሲያምኑ ብቻ ነው በሌላ አነጋገር «አሁን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለዚህ አለም አሰራጫለሁ ነገር ግን የሆነ ነገር ቢሳሳት ወደ አለም እገባለሁ» ብሎ በማሰብ ተጠራጣሪ መሆን የለብንም ልቦቻቸው

በእግዚአብሄር ያላጸኑ ሰዎች ከእርሱ አንዳች ነገር ሊቀበሉ መጠበቅ አለባቸው መጽሐፍ ቅዱስም በያዕቆብ ውስጥ የሚለው ይህንኑ ነው *«ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚዋላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው::» (1ኛ ዮሐንስ 1:6-8)*

ሁሌም ከጌታ ጋር ለመኖር ልቦቻችንን ማጽናት ምንም ነገር ቢፈጠር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለመኖር መወሰን ይገባናል እግዚአብሄር በሕይወታችን ውስጥ የሚሰራው የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመከተል እንዲህ ልቦቻችንን ስናጸና ነው ልቦቻችን በእግዚአብሄር ላይ ካልጸኑ አንድ ቀን ከአለም ጋር ሌላ ቀን ደግሞ ከእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ጋር እንወግናለን በሌላ አነጋገር የሰው ልብ ጽኑ ካልሆነ ከአንዱ ወደ ሌላው እየተንጠራወዘ ወደኋላና ወደፊት ይባዝናል::

ጀርመን ወደ ምስራቅ ጀርመንና ወደ ምዕራብ ጀርመን በተከፋፈለች ጊዜ እርስ በርሳቸው ሰላዮችን ይልኩ ነበር ከእነዚህ ሰላዮች አንዳንዶቹ ለሁለቱም የሚሰልሉ ነበሩ እነዚህ ሰላዮች የአንዱን ወገን ምስጢር ለሌላው የሌላውን ምስጢር ደግሞ ለቀድሞው አሳልፈው ይሰጣሉ ከሁለቱም ይከፈላቸው ስለነበር እስከሚታወቅባቸው ድረስ ተሳክቶላቸው ነበር ነገር ግን ውለው አድረው ተቀላቀሉ በተቀላቀለችው ጀርመን ውስጥ በጣም የተለጡ ሰዎች ቢኖሩ እነዚህ ለሁለቱም ሲሰልሉ የነበሩት ሰላዮች ናቸው ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ብቻ የገዛ አገራቸውን የከዱ ሰዎች አሁን ታድነው ከተያዙ በኋላ ለፍርድ ቀርበው ተቀጥተዋል በአንጻሩ ለአንድ አገር ብቻ ለምሰራቅ ጀርመንም ይሁን ወይም ለምዕራብ ጀርመን የሰለሉት ሰላዮች ለሰሩዋቸው የስለላ ተግባራቶች ይቅርታን አግኝተዋል እነዚህ ሰላዮች

በተከፋፈለችው ጀርመን ውስጥ እያንዳንዳቸው ላገለገሉት መንግስታቸው ሲሉ ሊያመልጡዋቸው በማይችሉባቸው ሁኔታዎች ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው ከለላ አግኝተዋል ነገር ግን ወላዋይ የሆኑት ሰላዮች ግን ለፍርድ መቅረብ ነበረባቸው እነዚህ ወላዋይ ሰላዮች በምስራቅና በምዕራብ ጀርመን ሰዎች የተጠሉ ነበር ከቅልቅሉ ከአስርተ አመታት በኋላ አሁን እንኳን ወላዋይ ሰላዮች ታድነው ተይዘው ለፍርድ እየቀረቡ ነው።

በስጋዊው አለም ውስጥ እንኳን የሚሆነው ይህ ከሆነ እኛስ ልቦቻችንን ማጽናታችን ምንኛ በእጅጉ ወሳኝ ነው? በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ እየሰራን ያለነው እናንተና እኔ አንድ ቀን ልቦቻችንን በዚህ አለም ላይ በቀጣዩ ቀን ደግሞ በእግዚአብሄር መንግስት ላይ በማጽናት ወደኋላ ወደፊት እንዴት እንጠራወዛለን? ይህንን የምናደርግ ከሆነ በሁለቱም ወገኖች እንደምትጠሉና እንደምትናቁ የተረጋገጠ ነው በሕይወታችን ውስጥ ልቦቻችንን በእግዚአብሄር መንግስትና በወንጌሉ ላይ ማጽናት አለብን ልቦቻችንን በቀናው መንገድ ላይ ማኖር የእንዳንዳችን ሐላፊነት ነው ይህ የእግዚአብሄር ስራ አይደለም እግዚአብሄር ከፈቃዳችን ውጭ ይህንን እንድናደርግ አያስገድደንም ጻድቃን አንዳንድ ጊዜ ችግር ይገጥማቸዋል ነገር ግን ከእነርሱ አንዳንዳቸው የእግዚአብሄርን ፈቃድ ባለመከተላቸው ምክንያት በከንቱ መከራን ይቀበላሉ።

አጋር ምዕመናኖቼ በእግዚአብሄር ፊት ልቦቻችሁን አጽኑ አእምሮዋችሁ በእግዚአብሄር ላይ መጽናት አለበት አሁን እኛ ያለነው በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ በመሆኑ ልቦቻችንን አንድ ጊዜም እንኳን በፍጹም ያላኖርን ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት በትክክል መኖር አንችልም እነዚህ ሰዎች እግዚአብሄርን በብዙ ያስቸግሩታል ከእነርሱ ጋር ስራ በሚሰራበት ጊዜ ምንም አይነት መንፈሳዊ ስራ ማከናወን

አይቻልም ጌታን መከተል አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ይሸሻሉ የእግዚአብሄር ስራ በደንብ ሲሰራ ይከተሉታል ይህ አይነቱ ልብ በእግዚአብሄር ፊት የቀና ልብ ነውን? አእምሮዋችንን በእግዚአብሄር ላይ ካጸነን በኋላ እንቅፋቶችን ሁሉ በእምነት እያረስን ወደፊት መገስገስ አለብን እኛ ቀድሞውኑም የእግዚአብሄር ሕዝቦችና የመንግስቱ ሰራዊት ስለሆንን እግዚአብሄርን መታመን የእርሱን ቤተክርስቲያን ችግሮችም የራሳችን ችግሮች አድርገን መውሰድ የእግዚአብሄርን እርዳታ መጠየቅና የእርሱን ስራም በሙሉ ሐይላችን መስራት አለብን ነገር ግን ልቦቻቸውን ያላጸኑ ሰዎች የእግዚአብሄርን ስራ እየሰሩ ሳሉ ችግር ውስጥ ቢገቡ ልቦቻቸው ከዚህ አለም ሰዎች ጋር ይወግናሉ፡፡

አሁን እኛ የእርሱ መንፈሳዊ ወታደሮች ሆነን ለዚህ አላማ ወደ ሚሸን ትምህርት ቤት ከመጣን በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ ለመኖር የምንሻ ከሆነ ልቦቻችንን በእግዚአብሄር ላይ ማጽናት አለብን እዚህ ከመምጣታችሁ አስቀድማችሁ አእምሮዋችሁን በእግዚአብሄር ላይ አጽንታችሁ ከሆነ ያ በጣም የተሸለ ነው ነገር ግን ወደዚህ ከመጣችሁ በኋላም እንኳን ገና አእምሮዋችሁን ያላጸናችሁ ከሆነ አታዘግዩት በተቻለ ፍጥነት ልቦቻችሁን አዘጋጁ፡፡

እግዚአብሄር ልቦቻችንን በእርሱ ላይ አጽንታችሁ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ሁሉንም ያውቃል ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ላይ ያላጸኑ ሰዎች እግዚአብሄር መቼ እንደሚረዳቸው እንኳን አያውቁም በእግዚአብሄርም ላይ እምነት የላቸውም እየተዋጋነው ያለነውን መንፈሳዊ ውጊያ መዋጋት የምንችለው የእኛ ወገን በግልጽ ከጠላት ወገን ከተለየ ብቻ ነው ጠላት መሸነፍና በሰይፍ መቆረጥ አለበት አእምሮዋችን የዚህ አይነት ሰዎችና የዚያ አይነት ሰዎች መሆን እንደምንችል የሚያስብ

ከሆነ እንዴት መንፈሳዊ ጦርነትን መዋጋት እንችላለን? ልቦቻችንን እንደሚከተለው ማጽናት አለብን «እኔ የእግዚአብሄር ሕዝብ ወገን ነኝ እኔ የክርስቶስ ነኝ እኔ ወታደር ነኝ የምኖረው ለእግዚአብሄር መንግስትና ለእርሱ ሕዝብ ነው» አሁን ልቦቻችንን እናጽና፡፡

እኛ በእርሱ የተጠራን የጌታ ሰራዊት ነን

በደቡብ ኮርያ ሰራዊቱ የተዋቀረው ለዚህ አገልግሎት በተመለመሉ ወጣቶች ነው ልክ እንደዚሁ እግዚአብሄርም እኛን የመንግስቱ መንፈሳዊ ወታደሮች አድርጎ መልምሎናል ወታደሮች ሆነው የሚመላለሱ ሰዎች ትክክለኛው ነገር የጠራቸውን ማለትም ጌታችንን መከተልና የእርሱን መንግስት በታማኝነት መከላከልና ማስፋፋት ብቻ ነው (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4) እዚህ ላይ መወላወል ሊኖር አይችልም ስለዚህ ጉዳይ ፈጽመን እርግጠኞች እስካልሆንን ድረስ መንፈሳዊ ሞት ይገጥመናል፡፡

በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ስንሆን ወታደሮቻችንን ከውጊያው ቢሸሹና ቢደበቁ እንዴት መቋቋም እንችላለን? ጠላት ያድነናል? ያለው ምርጫ አንድ ብቻ ነው ወይ ለጠላት እንማረናለን አለበለዚያም በእምነት ድል እንመታቸውና እናሸንፋቸዋለን በእምነታችን መንፈሳዊ ሐይል አማካይነት መንፈሳዊ ድላችንን ማረጋገጥ አለብን ያንን ለማድረግ ልቦቻችንን በግልጽ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

እኔ ልቤን ያለ ማወላወል በእግዚአብሄር ላይ አጽንቼአለሁ አእምሮዩን ከረጅም ጊዜ በፊት እንደ እናንተ ከመጸለዩም በፊት እንኳን በእግዚአብሄር ላይ አጽንቼአለሁ ጌታ በውሃውና

በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት እንደተገናኘሁት ወዲያውኑ ልቤን በእግዚአብሄር ላይ በማጽናት ቀሪ ሕይወቴን ለስራው ለመኖር ወስኛለሁ።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ ሰዎች ለእግዚአብሄር የከበሩ ናቸው ነገር ግን እግዚአብሄር ዳግም ያልተወለዱ ሰዎችን የሚያያቸው እንደዚህ አይደለም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ምዕመናኖች ሲሰናከሉ እግዚአብሄር «ይህ አሳሳቢ አይደለም ሰዎች ሁሉ እንደዚያ ናቸው» ይላል የእርሱ ሕዝብ ያልሆኑትን ግን አይታገሳቸውም።

ግልጽ የሆነ የእምነት ማንነት ሊኖረን ይገባል የእስራኤል ሕዝብ የራሳቸው ሕዝብ ያልሆኑትን አሕዛቦች ከእንስሳ ያልተሻሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርገው ይቆጥሩዋቸው ነበር ምክንያቱን ታውቃላችሁን? እስራኤሎች የእግዚአብሄር ምርጥ ሕዝብ እንደነበሩ ስላሰቡ ነው አሁንም እንኳን ከፍልጤማውያን ጋር እየተዋጉ ነው ሁለቱም በስጋ የአንድ ቅድመ አያት የአብርሃም ዘሮች ናቸው አብርሃም በመጀመሪያ ከአጋር እስማኤልን ወለደ በኋላም በእግዚአብሄር የተስፋ ቃል መሰረት ይስሐቅን አገኘ አንዱ ልጅ ከእግዚአብሄር የተስፋ ቃል የተወለደ ሰው ነበር ሌላው ልጅ አብርሃም ከገረዲቱ ጋር ባለው ግንኙነት የተወለደ ነበር።

ስለዚህ እግዚአብሄር በመንፈሳዊ ሁኔታ የእርሱ ሕዝብ የሆኑትን የእርሱ ሕዝብ ካልሆኑት በግልጽ ለይቶዋቸዋል እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑትን ሰዎች የራሱ መንፈሳዊ ሰዎች አድርጎ አጽንቶዋቸዋል በዚህ ወንጌል የማያምኑትንም ሰዎች የእርሱ ሕዝቦች እንዳልሆኑ አድርጎ ለይቶዋቸዋል የእግዚአብሄርን ሕዝብ የእርሱ ካልሆኑት ሕዝብ መለየት ካልቻልንና አሁንም ገና አእምሮዋችንን በእግዚአብሄር

መንግስት ላይ ካላጸናን እንዴት መንፈሳዊውን ጦርነት መዋጋት እንችላለን? የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማስፋፋቱን አገልግሎትስ እንዴት እንፈጽማለን? ሌሎችን ከሐጢያት መታደግ የምንችለው በትክክል የማን ወገን እንደሆንን ስናውቅ ብቻ ነው ይህንን በሌላ መንገድ ልናከናውነው የምንችለው እንዴት ነው?

አጋር ምዕመናኖቼ እስከ አሁን ድረስ ልቦቻችሁን ካላጸናችሁ በዚህች ቅጽበት እንኳን አእምሮዋችሁን በእግዚአብሄር ላይ እንድታጸኑ ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ ሕይወታችሁ የእግዚአብሄርን መንግስት ለመገንባት እንዲኖር ወስናችሁ ልባችሁን በትክክል አጽኑ ያን ጊዜ እግዚአብሄር ይባርካችኋል ከእናንተ ጋር በመስራትም ይደሰታል እግዚአብሄር የሚደሰተውና የሚባርካችሁ ለጌታ ለመኖር ስትወስኑ ነው እግዚአብሄር ገና ልቦቻቸውን ላላጸኑ ሰዎች አይሰራላቸውም እግዚአብሄር በውስጣችን እስካልሰራ ድረስ የእግዚአብሄርን ስራ መስራት እንችላለን? የለም እንደማንችል የታወቀ ነው።

አእምሮዋችንን ማዘጋጀት አለብን የእኛው መንግስት ለሆነው ለእግዚአብሄር መንግስት መኖር አለብን ስለ ራሳችን ብቻ በማሰብ ፋንታ ለዚህ መንግስትና አሁን ወገናቸው ለሆንነው ለእነዚህ ሰዎች ልንኖር ይገባናል አጋር ምዕመናኖቼ አእምሮዋችሁን አዘጋጅታችኋልን? እንደዚያ ከሆነ ስልጠናችሁን አላገባደዳችሁም በቀሪው ስልጠናችሁ ልታደርጉት የሚገባችሁ ነገር ቢኖር በእምነት መከተልና መማር ከቤተክርስቲያንም ጋር መተባበር ነው አእምሮ ከተዘጋጀ በኋላ ስጋ እርሱን ይከተላል።

በመጀመሪያ ደረጃ ልቦቻችሁ በእምነት ለመኖር መዘጋጀት አለባቸው እግዚአብሄር የሚበሉትን ወፎች ከማይበሉት ወፎች የለየው የሚበላውን አሳም ከማይበላው የለየው ለዚህ ነው ክንፎችና ቅርፊቶች ያሉዋቸው አሦች የውሃውን ግፊት

ተቋቁመው ይዋኛሉ በሌላ አነጋገር ልቦቻቸውን ያጸኑ ሰዎች ጌታ እንዲኖሩ የሚፈልግባቸውን የሕይወት አይነት ይኖራሉ እነርሱ የዘመኑንና የአለምን ግፊት ይቋቋማሉ የራሳቸውን ፍላጎት አይፈጽሙም ነገር ግን ምንም ነገር ቢያደርጉ ለጌታ ያደርጉታል እምነታቸው ትንሽ ብትሆንም በእምነት ይኖራሉ የሰው ልብ ካልተዘጋጀ የእግዚአብሄርን ስራ መስራት አይችሉም ነገር ግን ልቡን ያዘጋጀ ሰው የእግዚአብሄር ወታደር ሆኖ የእምነትን ስራ መስራት ይችላል እግዚአብሄር በአምስተኛው የፍጥረት ስራው አማካይነት ሊናገር እየሞከረ ያለው ይህንን ነው::

እግዚአብሄር ይህንን ዩኒቨርስ እንደፈጠረ ታምናላችሁን? እግዚአብሄር ሕይወትን ሁሉ እንደ ወገኑ እንደፈጠረ ታምናላችሁን? እርሱ እንደፈጠረ የታወቀ ነው እግዚአብሄር ወፎችን እንደ ወገናቸው ፈጥሮዋል አሳውንም እንደ ወገኑ ፈጥሮዋል የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ አሳብ የሰዎችን አይኖች አሳውሮዋል ከዚህ የተነሳ ብዙዎቹ እግዚአብሄር በእውነቱ መሰረት የፈጸመውን አይገነዘቡም ነገር ግን አይኖቻቸው የተከፈተላቸው ሰዎች እግዚአብሄር ይህንን ዩኒቨርስና በውስጡ ያሉትን ነገሮች በሙሉ እንደፈጠረ በግልጽ መገንዘብ ይችላሉ እያንዳንዳቸውን እንደ ወገናቸው ፈጥሮዋል::

አጋር ምዕመናኖቼ ይህንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሚያስፋፋው ይህ ጉባኤ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን እንደሆነ ታምናላችሁን? የእግዚአብሄር ሰራተኞች ሌሎች ሳይሆኑ እናንተ ናቸው የእርሱ ሰራዊት ሆናችሁ የተመለመላችሁትም እናንተው ናችሁ እያንዳንዳችን በየግላችን ልቦቻችንን ማጽናት አለብን ሕይወታችን የሚለወጠው ልቦቻችንን በእግዚአብሄር ላይ በማጽናታችን ላይ ተመርኩዞ ነው የምናደርገው ነገር ከውጪ ሲታይ ተመሳሳይ ይመስል ይሆናል ነገር ግን ጌታን ለማገልገል

ልቦቻቸውን ባጸኑ ሰዎች የተሰራው ስራ የተለየ ነው።

አእምሮዋቸውን ያዘጋጁ ሰዎች ለእግዚአብሄር ይሰራሉ በአንጻሩ አእምሮዋቸውን ያላዘጋጁ ሰዎች ለራሳቸው ይኖራሉ የእግዚአብሄርን ስራ ስንሰራ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሄርን ስራ በግብር ይውጣ የሚሉ ከሚመስሉ ነገር ግን ለራሳቸው እየሰሩ ካሉ ሰዎች ጋር እንገናኛለን።

ጌታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል ተናግሮዋል ይህ ወንጌል እንዲስፋፋም ይናፍቃል ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሄር ወንጌል አይደሰቱም ነገር ግን የራሳቸውን ክብር ብቻ ለመሻት ልቦቻቸውን በሙሉ አዘጋጅተዋል እነዚህ ሰዎች አሁንም ገና የሐጢያቶቻቸውን ስርየት መቀበል አልቻሉም ምክንያቱም ልቦቻቸውን በወንጌል እውነት ላይ አላጸኑምና በሌላ አነጋገር ለእግዚአብሄር የሚሆን ልብ የላቸውም አንድ ጊዜ የአንድ የወንጌላውያን ሚሽን መሪ በእርሱ የሚሸን ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ለአራት አመት ያህል እንደተማሩ በመናገር ጉራውን ነዛብኝ ስለዚህ እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት «በእነዚያ አራት አመታቶች ሁሉ ምን አስተማርህ?» ከንግግር ስነ ምግባር ጀምሮ እስከ ማዕድ ስርአቶች ድረስ ሁሉንም ነገር እንዳስተማረ ነገረኝ ይህ ሰው ሐሰተኛ አስተማሪ ነው።

መጋቢዎች እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ ማገልገል አለባቸው ብዙ ሰዎች ምንም ነገር አያውቁም ከስነ መለኮት ሴሚናሪ ተመርቀው እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ አንድ ጥቅስ እንኳን አያውቁም ታዲያ በሲሜናሪ ውስጥ የሚማሩት ምንድነው? የሚማሩት ቲዎሎጂ ተብሎ ስለሚጠራ የትምህርት መስክ ነው ያም ማለት የሚማሩት ስለ ተለያዩ የቃለ እግዚአብሄር ምሁራን አስተሳሰቦች ነው።

ከእነዚህ ሴሚናሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ በሚሸን ትምህርት

ቤታችንን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ጥልቅ የሆነውን የእውነት ቃል እያንዳንዱን ጥቅስ እየተማሩ ነው ሌላው ሰው ሁሉ ለራሱ ቲዎሎጂን ሲማር፣ ለራሱ ቤተክርስቲያን ሲተክል፣ ለራሱ መባዎችን ሲሰበስብና ለራሱ ሲያገለግል ይህንን እያደረገ ያለው ልቡን በትክክል በእግዚአብሄር ላይ ባለማጽናቱ ነው ስለዚህ ልቦቻችሁን በእግዚአብሄር ላይ ካላጸናችሁ በስተቀር በመጨረሻ ለራሳችሁ ብቻ እየኖራችሁ እነዚህን ሐሰተኛ ነቢያቶች ከመመስል አታመልጡም።

«እኔ እዚህ በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ እቆያለሁ እኖራለሁ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የምሰብከውም እዚሁ ነው ስለዚህ የእግዚአብሄር ሕዝብ ከሞተ ያን ጊዜ እኔም ደግሞ እሞታለሁ የእግዚአብሄር ሕዝብ ሲከናወንለት እኔም ይከናወንልኛል የእምነት ጉልበቴን ሁሉ በመሰብሰብ ጌታ እስከሚመለስበት ቀን ድረስ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እሰብካለሁ።»

ልቤ በእግዚአብሄር ላይ የጸናው እንዲህ ነው «ዚህ የተሰበሰቡት ሰዎች ሕዝቤ ናቸው ይህ መንግስቴ ነው የጌታ መንግስት መንግስቴ ነው የጌታን መንግስት ማስፋፋት ማለት መንግስቴን ማስፋፋት ማለት ነው» ስፍራዬና ሐላፊነት እንዲህ በግልጽ ተብራርቷል።

ሙሴ የእግዚአብሄር መንግስት አገልጋይ ሆኖ ሰርቷል ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወደዚህ ምድር መጥቶ መምህር ሆኖ ሰራ ጌታ ሕዝቡን ለማዳን መምህር ሆኖ መጣ ሙሴ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ቢሰብክም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ስለ ሁላችንም በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ የሕዝቡን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ ለእነርሱም ሞተ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ በዚህም አዳናቸው እኛ የእግዚአብሄር መንግስት ባለቤቶች መሆናችንን በግልጽ ተረድተን በመንግስቱ ውስጥ መኖር አለብን

ይህ ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ላይ ካላጸኑ ሰዎች ሕይወት የተለየ ሕይወትን መኖር ነው።

አብረውኝ የሚያገለግሉ አገልጋዮች እንዴት እየታገሉ እንደሆነ ሲያማክሩኝ «አዎ ሁላችንም እየታገልን ነው መከራችን ሁሉ ለጌታ ሲሆን ምን ማድረግ እንችላለን? እየታገልን ያለነው ለራሳችን ሳይሆን ለእግዚአብሄር መንግስት በመሆኑ ይህ ሁሉ ዋጋ ያለው አይደለምን? ስለዚህ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ብታልፍም እንኳን አሁንም ለጌታ ስራ ራስህን ልትሰጥ ይገባሃል ዋናው ነገር የእግዚአብሄር ስራ ነው ሌላ ምን እንጠብቃለን? በጣም ደካማ እንደሆንህና ጌታን መከተልም አዳጋች እንደሆነ ትናገራለህ ነገር ግን አለም ሁሉ የተቀበለን ጥሩ ሰዎች ሆነን ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ መሳሪያዎች አድርጎ ይጠቀምብን ነበር?»

አጋር ምዕመናኖቼ ኢየሱስ ክርስቶስ ኮንፊሺየስን ወይም ሶቅራጥስን መጠቀም ይመርጣል ወይስ እኔን ሊጠቀም ይመርጣል? እባካችሁ ይህንን ልቦቻችሁ በሚያምኑት መሰረት በቅንንት አስቡት እናንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ብትሆኑ ኖሮ ማንን ትጠቀማላችሁ ኮንፊሺየስን ወይስ እኔን? እናንተ ባስተማራችሁት መሰረት የሚያምነውንና ልቡን ያጸናውን ሰው ትጠቀሙበታላችሁ ማንነቱ ቢጎዳም እንኳን ግድ ሳይሰጠው ጌታው የሆናችሁትን የእናንተን ፈቃድ ብቻ የሚያደርገውን ሰው ትመርጣላችሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለኮንፊሺየስ ወይም ለሶቅራጥስ አንዳች ነገር ነግሮዋቸው ቢሆን ኖሮ ቀድሞውኑም የያዙዋቸው እሳቤዎች ስላሉ «ጌታ ሆይ ያንን መናገር አይገባህም» ይሉት ነበር በሌላ አነጋገር ሰው አንዳንድ ጊዜ በሰዎች ወገን ሌላ ጊዜ ደግሞ በክርስቶስ ወገን በመቆም ወደኋላና ወደፊት የሚንጠራወዘው ልቡን ስላላዘጋጀ ነው የስነምግባርና የመልካም

ምግባር አስተማሪ በኢየሱስ መንግስት ውስጥ ሰራተኛ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ መሳሪያዎች አድርጎ ሊጠቀምባቸው ተስማሚ የሆኑ ሰዎች የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከሚያምኑ ምዕመናኖች መንከል ልቦቻቸውን በእግዚአብሄር ላይ ያጸኑ ሰዎች ናቸው እርሱ ሊጠቀምባቸው ተስማሚ የሆኑ ሰዎች ልቦቻቸውን ያለ ማወላወል በእግዚአብሄር ላይ ያኖሩ ሰዎች ብቻ ነው ሰው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እኩል ሆኖ ለመቆም የሚሞክር ከሆነ እግዚአብሄር የእርሱ ሰራተኛ አድርጎ ሊጠቀምበት አይችልም እግዚአብሄር የሚጠቀምባቸው ራሳቸውን በፊቱ የሚያዋርዱትንና አስቀድመው የጌታን ስራ የሚሹትን ነው ጌታችን የሚጠቀምባቸው በነጻነት ወደ ስራ ሊያሰማራቸው የሚችላቸውን ሰዎች ነው።

ኢየሱስ እዚህ ቢሆን ኖሮ ወንጌልን የሚቃወሙ ሰዎችን ምን ይላቸው ነበር? «እናንተ የማትረቡ ዲቃላዎች እናንተ የእፉኝት ዘሮች ሁላችሁንም እረግማችኋለሁ» አይላቸውምን? እንደዚያ ከሆነ እኛም የእኛ ርህራሄ ለሚያስፈልጋቸው ምስኪኖች ርህራሄን እያሳየን የእግዚአብሄርን ጠላቶች መቃወም አለብን የእርሱ አገልጋዮች መሆን ማለት ልቦቻችን ከእግዚአብሄር ልብ ጋር ተቆራኝተዋል ማለት ነው ልቦቻችን መጽናት አለባቸው።

እግዚአብሄር ዳዊትን አስመልክቶ እንዲህ ብሎዋል «እርሱ እንደ ልቤ የሆነ ሰው ነው» ዳዊት ጌታ ባዘዘው መሰረት የፍልስጤምን ሰራዊት ጠራርጎ አጠፋ በአንጻሩ ሳኦል የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ስላልታዘዘ አንዳንድ ፍልስጤሞችን አዳነ በራሱ አስተሳሰቦች ላይም ተመስርቶ ለእግዚአብሄር ለማቅረብ ሲል ከምርኮው አንዳንድ የሰቡ ከብቶችን አተረፈ ዳዊት ግን የእግዚአብሄርን ቃል ሙሉ በሙሉ ታዘዘ

እግዚአብሄር በአውደ ውጊያው ላይ ጠላቶች የሆኑትን በሙሉ እንዲገድል በነገረው ጊዜ ዳዊት ሁሉንም ገደለ አጠፋቸው ዳዊት እንዲገድል የተነገረውን ሁሉ እንስሶችንም ጨምሮ ገደለ።

ዳዊት ሳኦልን ተክቶ የእስራኤል ንጉስ ሆነ እነዚህ ሁለት ሰዎች ግን በመንፈሳዊ መልኩ በጣም የተለያዩ ነበሩ ሳኦል በውጭ ገጽታው የሚማርክ ሰው ነበር በአካላዊ ብቃቱም በእስራኤል ሕዝብ የተከበረ ነበር ነገር ግን ከዳዊት በተቃራኒ ልቡ እግዚአብሄርን ለማክበርና በመንግስቱ ውስጥ ያለውን ሕዝብ በመንፈሳዊ ሁኔታ ለመንከባከብ የተዘጋጀ አልነበረም የዳዊት ልጅ ሰሎሞንም እንደዚሁ ልቡን አላጸናም ስለዚህ ከጎረቤት መንግስታት ብዙ እቴጌዎችን ወስዶ ቁባቶቹ አደረጋቸው በጎረቤት ያሉ አህዛብ መንግስታቶች «ግርማዊ ሆይ ይህች የእኔ ሴት ልጅ ነች» በማለት ሴት ልጆቻቸውን ሲያቀርቡለት ንጉስ ሰሎሞን «ሴት ልጅህ በጣም ውብ ነች» ብሎ ቁባቱ አድርጎ ይወስዳት ነበር ይህንን ያደረገው ልቡ በእግዚአብሄር ላይ ስላልጸና ነበር።

የዚህ አለም ሴቶች ማለትም ዳግም ያልተወለዱ ሴቶች ልክ እንደ እባቦች ናቸው ጻድቃኖችን ያጠፉዋቸዋል ምናልባት ሳምሶን እንደ'ት በደሊላ እንደተታለለ በመሳፍንት ውስጥ ሳታነቡ አትቀሩም መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ሴቶች «ጋለሞታዎች» ብሎ የሚጠራቸው ለዚህ ነው ስለዚህ ሰሎሞን የአህዛብ እቴጌዎች ሲቀርቡለት «እነዚህን ሴቶች ለምን እዚህ አመታችሁ? በጣም ያስጠላሉ ፍላጎቴን የሚያበላሹ የረከሱ ጋለሞታዎችን ይመስላሉ አስወጡዋቸው» ማለት ይገባው ነበር እንደዚያ ቢል ኖሮ በዙሪያው ያሉት ሌሎቹ ነገስታቶች ሴት ልጆቻቸውን አያመጡለትም ነበር እግዚአብሄር ሰሎሞንን ከአሕዛብ ሴቶች ጋር እንዳያገባ አዞት ነበር እንደዚያ ሆኖ ሳለ የሰሎሞን ልብ ስላልጸና በስጋው ፍትወቶች መሰረት ለማግባት

ሲል የፈለገውን አገባ ከዚህ የተነሳም መጨረሻው በመንፈሳዊ ሁኔታው መጥፋት ሆነ።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ጻፈ *«ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች ሦስት መቶም ቁባቶች ነበሩት ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉት» (2ኛ ነገስት 11:3)* በዚህ ምክንያት ወደ በኋላ እንዲህ ሲል ተናዘዘ *«ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው» (መክብብ 1:2)* እንዲህ ያለ የጸጸት ሕይወት ከኖረ በኋላም ሞተ በልጁ የአገዛዝ ዘመንም የእግዚአብሄር መንግስት ለሁለት ተከፈለ መውደቅም ጀመረ።

ምንም ነገር ብንሰራ ልቦቻችንን በእግዚአብሄር ፊት መጻናት አለብን ይህ እንደሚያስፈልግ ታውቃላችሁን? ልቦቻችን የእግዚአብሄር መሆን አለባቸው ልቦቻችን እግዚአብሄር አምላካችን እንደሆነ፣ የእርሱም ቤተክርስቲያን ቤተክርስቲያናችን እንደሆነችና የእርሱም ሕዝብ ሕዝባችን እንደሆነ ሊያምኑ ይገባል።

እስከ አሁን ድረስ የነበሩን እሴቶቻችንና የብያኔ መለኪያዎቻችን በሙሉ መለወጥ አለባቸው *«የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው መልበስ» (ቆላስያስ 3:10)* አለብን በቤቴ ሳለሁ ልጄን «አንተ በስጋ ልጄ ብትሆንም በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሌሎቹ የእግዚአብሄር ሰዎች ጋር ሁሉ ትመሳሰላለህ ከእነርሱ የምትለይበት ብቸኛው ልዩነት በስጋ ልጄ መሆንህ ነው ከዚህ ሌላ በመንፈሳዊ ሁኔታ ልዩነቱ ምንድነው? ምንም ልዩነት የለም በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ እንሁን» እለዋለሁ በመንፈሳዊ አነጋገር እርሱን የምመለከተው ሌሎች ቅዱሳኖችን በምመለከትበት ተመሳሳይ መንገድ ነው ስለዚህ መጀመሪያ ላይ ልጄ ይህንን መቀበል አዳግቶት ነበር ምክንያቱም እርሱም በውስጡ መንፈስ ቅዱስ ስላለው ውሎ አድሮ ግን ተስማማ።

የመሪው የቤተሰብ አባሎችና ዘመዶች ቁልፍ የስልጣን

ቦታዎች የያዙበትና በጎሳ መሰረት ላይ ተመስርቶ የሚንቀሳቀስ አንድ የሚሽን ድርጅት አይቻለሁ ስለዚህ መሪው በዚህ ድርጅት አገልጋዮች ላይ ጥብቅ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ያደርግ ነበር እነዚህ ሰዎች የሚያገለግሉት የእግዚአብሄርን መንግስት አይደለም ነገር ግን ለራሳቸው ክብር ሲሉ የኢያሪኮን ከተማ እንደገና ለመገንባት እየሞከሩ ነው እግዚአብሄር እነዚህን ሰዎች እንዲህ በማለት አስጠንቅቆዋቸዋል *«ይህችን ከተማ ኢያሪኮን ለመሰራት የሚነሳ ሰው በእግዚአብሄር ፊት ርጉም ይሁን መሰረተዋን ሲጀምር በኩር ልጁ ይጥፋ በርዋንም ሲያቆም ታናሹ ልጁ ይጥፋ::» (ኢያሱ 6:26)*

ይህንን አናደርግም በእኔ ቤተክርስቲያን ውስጥ ልጄ የተለዩ መብቶች የሉትም እንደ ማንኛውም ሌላ ሰው ከእግዚአብሄር ሕዝብ እንደ አንዱ ሆኖ እግዚአብሄርን እንዲያገለግል እጠብቃለሁ ይህንን እስካላደረግሁ ድረስ እርሱ ይጠፋል ይህንን የማደርገው ስለምወደው ነው በእምነት የሚያድገውና በእምነቱ የሚቆመው ያን ጊዜ ብቻ ነው ስጋዊ ድክመቶቹን በሚመለከት ለልጄ እንክብካቤን ባደርግም በመንፈሳዊ ሁኔታ መተከል የሚገባው ግን በግልጽ መተከል አለበት ይህ ሁሉ ልቤን ከማጽናቴ የመነጨ ጉልበት ነው ልቦቻችንን ማጽናት በኢየሱስ ክርስቶስና በቃሉ ማመን በእምነት መዋጋትና የእግዚአብሄርንም መንግስት በእምነት መገንባት አለብን::

አጋር ምዕመናኖቼ አእምሮዋችሁን በእግዚአብሄር ላይ እንድታጸኑ ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ ልቦቻችንን በየጊዜው ስናጸና በሰማይ እንደሚበሩ ወፎች በእምነት እንኖራለን ክንፍ እንዳለውም አሳ ልባችንን የሚያረካ የእግዚአብሄር ስራ መስራት እንችላለን::

ልቦቻችንን ካጸናን በኋላ ጠላትን ማሸነፍና በእምነት ድል ማድረግ እንችላለን በእግዚአብሄር በማመን የሐጢያተኞችን ነፍስ ከሐጢያት ማዳን የሚችል ስራ መስራት እንችላለን:: ✉

ከልባቸው በእግዚአብሄር ቃል የሚያምኑ የእምነት ሰዎች ሕይወት

« ዘፍጥረት 1:20-23 »

«እግዚአብሄርም አለ ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ እግዚአብሄርም ታላላቆች አንበሪዎችን ውሃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኝቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው ብዙ ተባዙም የባሕርንም ውሃ ሙሉአት ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አምስተኛ ቀን::»

በዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሄር *«ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ»* ብሎዋል ውሃ በአሳ እንደተሞላ ሁሉ አሀንም እንኳን በእግዚአብሄር ቃል የሚያምኑ በርንታ ጻድቃን ሰዎች የእርሱን ስራ በታማኝነት መስራታቸውን ቀጥለዋል በዚህች ቅጽበት እንኳን የእግዚአብሄር ቃል ሕያው ነው በእምነት በሚመላለሱ ሰዎችም ይሰራል የእግዚአብሄር ቃል በዚህ ምድር ላይ እስከኖረ ድረስ ጻድቃን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመስበክ እንደሚቀጥሉ ልባዊ ተስፋዬ ነው::

የእግዚአብሄር ቃል እንድናድግና በእምነትም እንድንበረታ ነፍሳችንን እየመገበ ነው የእግዚአብሄር ቃል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ምዕመናኖችን መመገቡን ቀጥሎዋል ይህ አለም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በሚያምኑ ምዕመናኖች እየተሞላ ነው ነገር ግን በዚሁ ጊዜም ደግሞ ሰይጣን ሊበጠብጠን እየሞከረ ነው ቢሆንም በእምነታችን ጸንተን ልንቆም ይገባናል ሰይጣን እንቅፋት ቢፈጥርም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማስፋፋታችንን ማቆም አንችልም።

ነገር ግን ሰይጣን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እየሰራ ነው የእግዚአብሄር ቃል እንዳይስፋፋ ሁሉንም አይነት ዘዴዎች ይጠቀማል በኤድን ገነት በተንኮለኛው እባብ አማካይነት የእግዚአብሄረን ቃል ለማበላሸት ሞከረ አሁንም እንኳን ሰይጣን የእግዚአብሄር ሕዝቦች የሆዋን እንዳያገለግሉ ለመከላከል በመሞከር እንቅፋት መሆኑን ቀጥሎዋል ሁሉም ሰው ጣዖት አምልኮን እንዲፈጽም ለማድረግ በመሞከር ሁሉንም ወደ ጣዖታት ይነዳቸዋል።

በአዲስ ኪዳንም ዘመን ቢሆን ዲያብሎስ ሳይታክት የእግዚአብሄርን ቃል ለማበላሸት ሞክሮዋል ሆኖም ሰይጣን የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል ለማበላሸት ምንም ያህል ቢሞክርም እግዚአብሄር እስከ አሁን ድረስ ቃሉን ጠብቆ አቆይቶታል ለሌሎች እንደሚተላለፍም አረጋግጦዋል እግዚአብሄር በየጊዜው ጥሩ የሆኑ እንሳ ኪንግ ጀምስ ቨርዝን ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን በማቅረብ ሰዎች በቃሉ አማካይነት የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዲቀበሉ እያስቻላቸው ነው።

ስለዚህ አሁን እያነበብነው ያለነው ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር ከረጅም ጊዜ በፊት በነቢያቶቹ አማካይነት በትክክል እንደተናገረው ፈጽሞ ሳይበላሽ ቆይቶዋል አሁን በዚህ አለም ላይ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው መዳንና የዘላለም ሕይወትን

መቀበል የሚስችለውና ምንም የማይጎድለው የተጻፈ የእግዚአብሄር ቃል አለው በሌላ አነጋገር የሐጢያቶችን ስርየት እንድንቀበል የሚያደርገን የእግዚአብሄር ቃል አሁን በእጆቻችን ውስጥ በያዝነው በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎዋል።

በሌላ በኩል ሰይጣንም ስራውን ቀጥሎዋል የተሳሳቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንደምን በስፋት እንደሚያጣምሙ መገንዘብ አለባችሁ የዛሬዎቹ እንኸን የሞላባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የእግዚአብሄርን ቃል ስልጣን እየተጫኑት ነው።

የዛሬው ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በዚህ ምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ሐጢያተኛ ከሐጢያት እንደሚድንና የዳኑ ነፍሳቶችም ደግሞ እንደሚሳካላቸው ይነግረናል ነገር ግን ሰይጣን አሁንም እንንን የእግዚአብሄርን ቃል ለማጣመም እየሞከረ ስለሆነ ክርስቲያኖችም እንኳን ሰማይ ከመግባት ይታቀባሉ ሰይጣን በጥንቷ ቤተክርስቲያን ዘመንና ዛሬም ብዙ እንቅፋቶችን እያስቀመጠ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል።

ነገር ግን ዲያብሎስ እኛን ለማደናቀፍ ምንም ያህል ጠንክሮ ቢሞክርም የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል በዚህች ምድር ላይ ሲያብብ የሰይጣን እንቅፋቶች ደግመው አይሳካላቸውም እግዚአብሄር አሳ በውሃ ውስጥ እንዲኖር እንደፈጠረው ሁሉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ቅዱሳኖችም የእግዚአብሄርን ቃል በመታመን በእምነታቸው ማደጋቸውን ይቀጥላሉ።

ስለዚህ እምነታችን መሰረቱን በእግዚአብሄር ቃል ላይ በማኖር እንደ አዲስ መጀመር አለበት

የእግዚአብሄር ቃል ነፍሳቶችን ሁሉ ከዚህ አለም

ሐጢያቶች የሚያድንና እንዲሳካላቸው የሚያደርግ ነው እኛ በእግዚአብሄር ቃል በመታመን ለብዙ ነፍሳቶች ልንሰብከው ይገባናል ያን ጊዜ በእኛ አማካይነት ብዙ ነፍሳቶች ከአለም ሐጢያቶች ይድኑና ይለወጣሉ በእግዚአብሄር ቃል ምክንያት ውሃው እንዴት በአሳ እንደተሞላ አይተናል አሁን በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች በተጻፈው የእግዚአብሄር ቃል ላይ ባላቸው እምነት አማካይነት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሚሰብኩ ሰራተኞች ሆነው እየተነሱ ነው ዛሬ ጻድቅ ሰዎች ሆነን የምንኖረው እግዚአብሄር ቃሉን ስለነገረን ነው ሁላችሁም ይህንን እንድትገነዘቡና በእርሱም እንድታምኑ እመክራችኋለሁ።

የእግዚአብሄር ቃል ሐጢያተኞችን ከሐጢያቶቻቸው እንዲድኑ የሚያስችላቸው የእውነት ቃል ነው ይህ እንደዚህ ከሆነና እኛም ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ለመዳን በእርግጥ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም ተወልደን ከሆነ ልንኖረው የሚገባን የእምነት ሕይወት ምንድነው? ወንጌልን በመላው አለም የሚያስፋፋ የእምነት ሕይወት መኖር እንደሚኖርብን የታወቀ ነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ባለን እምነት አማካይነት በሰማይ ግዛት ውስጥ ልንኖር ይገባናል እምነታችንን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ በማኖር ከእግዚአብሄር ጋር አንድ ቤተሰብ ልንሆን ይገባናል በዚህ እምነትም ደግሞ መኖር አለብን።

እግዚአብሄር በሰማይ እንደሚበሩ ወፎች እንድንኖር ነግሮናል ጻድቃን እምነታቸውን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ በማኖር ወደፊት ከመገስገስና የእግዚአብሄርን ፈቃድ ከመፈጸም እየከለከሉዋቸው የእምነት መንገዳቸውን የሚያደናቅፉት ስጋዊ አስተሳሰቦቻቸውና ስሜቶቻቸው መሆናቸውን መገንዘብ አለባቸው እግዚአብሄር ከእኛ የሚፈልገው ብቸኛው ነገር በቃሉ ማመን፣ በእምነት ክልል ውስጥ መብረርና

በዚያም መኖር መሆኑን የሚነግረን ለዚህ ነው።

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት በማመን ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ዳግም የተወለዱ ሰዎች እምነታቸውን በቃሉ ላይ በማኖር እንዲኖሩ ይጠይቃቸዋል በእርግጥ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የእግዚአብሄር ሕዝብ ከሆንን አሁን እግዚአብሄር ከእኛ የሚፈልገው ቃሉን በመታመን እንድንኖር ነው እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ባለው ነገር እንዳንደገፍ ይልቁንም በቃሉ ላይ እንድንደገፍና በቃሉ ላይ ባኖርነው በዚህ እምነት እንድንኖር እየነገረን ነው።

በሌላ አነጋገር በእርግጥ እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምን አማኞች ከሆንን እግዚአብሄር «በእኔና በጽድቄ ላይ ባላችሁ እምነት ኑሩ» ይለናል እኛ ከአለም ሐጢያቶች የዳንን የእግዚአብሄር ሕዝብ ከሆንን በእግዚአብሄር ቃል በመታመን በእምነት ክንፎች መብረር ይኖርብናል እግዚአብሄር ደስ ከተሰኘ ሁሉንም ነገር እንደሚፈቅድና ሁሉንም እንደሚፈጽም በማመን በእምነት መኖር አለብን እግዚአብሄር ሁሌም በእርሱ ላይ የሚያነጣጥር ሕይወትን እንድንኖር እየነገረን ነው።

በፊታችን ሁለት የተለያዩ አለሞች አሉ አንደኛው የስጋ አይኖቻችን የሚያዩት ክልል ይህ የአሁኑ አለም ነው ነገር ግን የስጋ አይኖቻችን የማያዩት የእግዚአብሄር ግዛት አለ ይህ ግዛት ዘላለማዊና ከአሁኑ አለም የበለጠ አስተማማኝ እንደሆነ ማስታወስ አለብን።

እግዚአብሄር *«ወፎችም ከምድር በላይ ከጠፈርም በታች ይብረሩ»* አለ እዚህ ላይ የጠፈር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም በሰማይ ያለ ሕዋ ማለት ነው የእግዚአብሄር ቃል ስለ እርሱ ግዛት ይናገራል ይህ ማለት ጻድቃን የሚኖሩት በምድራዊ ግዛት ላይ አይደለም ማለት ነው ነገር ግን በጌታ ባላቸው እምነት በሰማይ ግዛት ላይ መብረር ይኖርባቸዋል በሌላ አነጋገር

እግዚአብሄር የእርሱ ፈቃድ በነጻነት የሚፈጸመው የእግዚአብሄርን ቃል በምንታመንበት በእምነት ክልል ውስጥ ስንኖር እንደሆነ ይናገራል፡፡

እግዚአብሄር በእርሱ በማመን በዚህ የእምነት ግዛት ውስጥ ብንኖር ተስፋ ከምናደርገውና ከምንፈልገው በላይ ብዙ ነፍሳቶችን እንደሚያድን ተናግሮዋል እኛ ልንኖር የሚገባን በእግዚአብሄር ቃል በማመን ነው እግዚአብሄር በቃሉ የምናምነውን ሰዎች ለዘላለም እንድንኖር ያስችለናል፡፡.

እግዚአብሄር በራሳችን የስጋ ሰብአዊ ጉልበት በመታመን እንድንኖር አልነገረንም ይልቁንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ አማኞች በእግዚአብሄር ቃል ላይ ባላቸው እምነት እንዲኖሩና ወደ እግዚአብሄር መንግስት እንዲገቡ ነግሮዋቸዋል በእግዚአብሄር የጽድቅ ቃል ውስጥ እምነታችንን በዚህ ቃል ላይ በማኖር በነጻነት መኖር እንችላለን፡፡

ሆኖም ከእግዚአብሄር ቃል ይልቅ ብዙ ምድራዊ ነገሮች አስቀድመው በልቦቻችን ውስጥ ገብተዋል ስለዚህ በመንፈሳዊ ሁኔታ በትክክለኛ እምነት መኖር ቀላል አይደለም በጣም ብዙ ምድራዊ ፍላጎቶች ስላሉን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሄር ቃል በመታመን መኖር በጣም አስቸጋሪ ነው «በዚህ መንገድ ልኑር ወይስ በዚያ መንገድ ልኑር?» ብለን ግራ ስንጋባ ይህንን ጥያቄ በእግዚአብሄር ጽድቅ ክልል ውስጥ ሆነን ከማሰብ ይልቅ ብዙውን ጊዜ በአእምሮዋችን ውስጥ ባሉት ስጋዊ ፍላጎቶቻችን ሕይወታችንን እንቀርጸዋለን፡፡

እግዚአብሄር ሕይወታችንን በስጋዊ ነገሮች እንዳናቅድ ይነግረናል ከዚህ ርቀን ከምድር በላይ ከጠፈርም በታች እንደሚበሩ ወፎች በእርሱ ላይ ባለን እምነት እንድንኖር ነግሮናል እኛም ጻድቃኖች በተወሰነ መጠን ምድራዊ ፍላጎቶች አሉን ነገር ግን ጌታ የሌለበት ሕይወት ትርጉም የለውም በሌላ

አነጋገር የሰማይ ግዛት በስጋ አይኖች ባይታይም ከማናቸውም ምድራዊ ሐብቶች እጅግ ጠቃሚና ዋጋ ያለው ነው፡፡

እግዚአብሄር የስጋ አይኖቻችን የሚያዩት ምድራዊው ግዛት ብቸኛው ግዛት እንዳልሆነ እየነገረን ያለው ለዚህ ነው እዚህ እግዚአብሄር ለእኛ ለጻድቃኖች በስጋ አይኖች የማይታየውን መንፈሳዊውን ግዛት ለምን እንዳሳየን መረዳት ያስፈልገናል ይህንን በማድረጉ እምነታችንን በእግዚአብሄር ላይ በማኖር እርሱ ባዘጋጀልን መንፈሳዊ ግዛት ውስጥ እንድንኖር እየነገረን ነው፡፡

እግዚአብሄር በስጋ አይኖቻችን በሚታየው ነገር ሳይሆን በተጻፈው ቃሉ ላይ ባለን እምነታችን እንድንኖር እየነገረን ነው ከእግዚአብሄር የምንይቀው የምንሻው ወይም የምንፈልገው አንዳች ነገር ከሌለ ፍላጎቶቻንን በሙሉ በእርግጠኝነት ይሞላልናል የልቦቻችንን ፍላጎቶችና አሳቦች በሙሉ ማስተዋልን ሁሉ ለሚያልፈው ለእግዚአብሄር ማስታወቅና መልስ እንደሚሰጠንም ማመን አለብን፡፡

እኛ ጻድቃን በእግዚአብሄር ቃል ላይ ባለን እምነታችን ልንኖር ይገባናል እግዚአብሄር «ጌታን ለማገልገል ካለኝ ጥቂቱን ብጠቀምና የቀረውን በሙሉ ለራሴ ጉዳይ ባውለው ምንም አይደለም» ብለን ራሳችንን ለማሳመን የምንሞክርባቸውን ጠባብ አስተሳሰቦችና ስጋዊ ሕይወት እንድንጥል እየነገረን ነው እግዚአብሄር በእርሱ ጽድቅ እንድንኖር በሚያስችለን አዲስ ሕይወት ለእርሱ ጽድቅ እንድንኖር እየነገረን ነው፡፡

አምላንችን በጌታ እንድንኖር ያስችለናል

ጌታ እንዲህ ብሎናል *«ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሄር አመኑ በእኔም ደግሞ አመኑ» (ዮሐንስ 14፡1)* በሌላ አነጋገር

እግዚአብሄር ጸሎቶቻችንን ይሰማል በራሱ ጊዜ የሚያስፈልጉንን ያቀርብልናል የእርሱን መልካም ስራ እንድንሰራም ያግዘናል እግዚአብሄር በአእምሮዋችሁ ውስጥ ያቀዳችሁትንና በቃሉ ክልል ውስጥ ሆናችሁ እግዚአብሄርን የጠየቃችሁትን በመመለስ ፈቃዱን በእናንተ አማካይነት ይፈጽማል እርሱ ፍላጎቶቻችንን ሁሉ የሚያሟላልን በእግዚአብሄር ቃል መሰረት ስንኖር ነው፡፡

በዚህ አመትም እንደዚሁ እግዚአብሄር በራሱ ቤተክርስቲያን አማካይነት በርካታ ነፍሳቶችን በማዳን እንደሚቀጥል አምናለሁ አጋር ምዕመናኖቼ በመጀመሪያ በአገራችን ቤተክርስቲያኖችን መትከልና ወንጌልን ማስፋፋት አለብን በመላው አለም ሁሉ የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያኖች በመትከልም እንደዚሁ በሌሎች አገሮች የሚገኙ በርካታ ነፍሳቶችን ወደ ደህንነት መምራት አለብን የእግዚአብሄርን ቤተክርስቲያን በመላው አለም መትከልና የውሃውነና የመንፈሱን ወንጌል ማስፋፋት የሚቻለው እምነታችንን በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ በማኖር ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሄር በአምላክ ጽድቅ ያመንበትን እምነታችንን በማየት የእርሱ አገልጋዮች አድርጎ አስነስቶናል ስራችንን ባርኮዋል ከእኛም ጋር ሰርቷል የራሱን ሰራተኞች የጠራቸው፣ ያሳደጋቸውና የተንከባከባቸው እግዚአብሄር ነው እግዚአብሄር አገልጋዮቹ አድርጎ ስላጸናቸው በእነዚህ የእግዚአብሄር አገልጋዮች አማካይነት በርካታ ነፍሳቶችን አድኖዋል እግዚአብሄር የእርሱ ቤተክርስቲያን አባሎች የሆንነውን እኛን የመንግስቱ ሰራተኞች አድርጎ ሊጠቀምብን ፈለጎዋል፡፡

በምድራዊ ነገሮች ብቻ ለመኖር የምንሞክር ከሆነ በመጨረሻ አንድ ወሰን ላይ እንደርሳለን ስለዚህ መንፈሳዊ ሕይወትን መኖር የምንችለው በእግዚአብሄር በማመን ብቻ ነው እግዚአብሄር በሰማይ ላይ እንድንበር እየነገረን ነው

እግዚአብሄርን የሚያስደስተው እምነት በእግዚአብሄርና በቃሉ ላይ የተመቻቸ እምነት ነው ስለዚህ ሁላችሁም በእምነታችሁ እንድትበሩ እመክራችኋለሁ በሰማይ ላይ እንድትበሩና እግዚአብሄር እንዴት በዚህ አለም ላይ እንደሚሰራ በራሳችሁ ልምምድ ለራሳችሁ እንድታዩ እመክራችኋለሁ፡፡

አሁንም ድረስ የሐጢያቶቻቸወን ስርየት ያልተቀበሉ ሰዎች በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ የተቀመጠውን የእምነት ክልል ሊያውቁት አይችሉም ሐጢያተኞች እንዴት በእምነት ሊኖሩ ይችላሉ? እነርሱ እየኖሩ ያሉት የእግዚአብሄርን ጽድቅ በሚያምኑበት የእምነት ክልል ውስጥ አይደለም ነገር ግን በራሳቸው የስጋ ምኞት ክልል ውስጥ እየኖሩ ነው ጻድቃን በእግዚአብሄር ጽድቅ መታመን አለባቸው እግዚአብሄርን በተጨባጭ የሚያስደስተው ምን እንደሆነ ማወቅና ማመን አለባቸው በዚያ መሰረትም መኖር አለባቸው፡፡

እግዚአብሄር ፈቃዱን በሙሉ እንደሚፈጽም ማመን ማለት እውነተኛ እምነት መያዝ ማለት ነው ነገር ግን እናንተስ? እግዚአብሄር በቸርነቱ እንደሚመራችሁ በእርግጥ ታምናላችሁን? በዚህ የእምነት ክልል ውስጥ ብንኖር በሐይል ተሞልተን ሕይወታችንን እንደምንኖርና እንዲህ ያሉ ታላላቅ ሰማያዊ በረከቶችን እንደምንቀበል የተረጋገጠ ነው፡፡

እናንተም ደግሞ በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ተመቻችቶ በተቀመጠ እምነት ትኖሩ ዘንድ እጅግ ልባዊ ተስፋዬ ነው እግዚአብሄር በእርሱ ጽድቅ ስታምኑ ምን ያህል እንደሚደሰት መገንዘብ ያስፈልጋችኋል መጽሐፍ ቅዱስ ጻድቃንን አስመልክቶ እንዲህ ጽፎዋል፡፡

«አምላክሽ እግዚአብሄር በመካከልሽ
ታዳጊ ሐያል ነው በደስታ በአንቺ
ደስ ይለዋል በፍቅሩም ያርፋል

በእልልታም በአንቺ ደስ ይለዋል» (ሰፎንያስ 3:17)

በእርሱ ጽድቅ ላይ ባለን እምነታችን ብንኖር እግዚአብሄር ይደሰታል ስለዚህ ምድራዊ ነገሮችን እንጠጣለን እንበላለን እንዲህ በከንቱ ኖረን እንሞታለን ከማለት ይልቅ ልቦቻችንን በእግዚአብሄር ላይ ማጽናት አለብን እግዚአብሄር *«ጻድቅ በእምነት ይኖራል»* ብሎዋል እግዚአብሄር ወደ ቤቱ እስከሚጠራችሁ ድረስ የእግዚአብሄርን ጽድቅ እንድትሰብኩ ሁላችሁንም እመክራችኋለሁ፡፡

አብርሃም ሊንከን በአሜሪካ የነበረውን ባርነት አስወገደ በዚህ ክነውኑም በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ እጅግ አድናቆትን ካተረፉ ሰዎች መካከል አንዱ ሆነ ጻድቃን ሐጢያተኞች ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ነጻ እንዲወጡ ለሚያስችላቸው የእግዚአብሄር ጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው ይህ በዚህ አለም ላይ እጅግ የሚደነቅ ሕይወት ነው በዚህ ምድር ላይ የሚኖሩ የእግዚአብሄር ሕዝቦች በእምነት ለእግዚአብሄርና አብረዋቸው ላሉት ሰዎች ቢኖሩ ማለትም ብዙ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማምጣት ሕይወታቸውን ቀድሰው ቢሰጡ በዚህ ምድርና በሚመጣው አዲስ ሰማይና ምድር ላይ ለዘላለም እንደ ጻሐይ ያበራሉ ይከብራሉም እግዚአብሄር እንዲህ ብሎዋል *«ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ጸዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ» (ዳንኤል 12:3) «በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግስት እንደ ጻሐይ ይበራሉ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይሰማ::» (ማቴዎስ 13:43)*

ሁላችሁም ይህንን ሕይወት እንድትኖሩ እመክራችኋለሁ እውነተኛ የእምነት ሕይወት ሌላ ሳይሆን ይህ ነው በዚህ ምድር ላይም ቢሆን የሚያበሩት መልካም የሰሩ ሰዎች ስሞች ናቸው ልክ እንደዚሁ በሰማይ ለዘላለም የሚያበሩት በጌታ መንግስት ውስጥ በእውነተኛ እምነት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌልና

በእውነት መሰረት የሚየሰምኑ ሰዎች ናቸው እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም ለተወለዱ ሰዎች ያለ ምንም ማመንታት በእምነት እንዲኖሩ ነግሮዋቸዋል።

እግዚአብሄር በአምስተኛው የፍጥረት ቀን በእምነት እንድንኖር ነገረን ስድስተኛው ቀን ሲመጣ እግዚአብሄር ሰውን ፈጠረ በሰባተኛውም ቀን አረፈ እግዚአብሄር በዚህ ዕቅዱ መሰረት ሁላችንንም በእምነት እንድንኖር እያዘዘን ነው በእግዚአብሄር ማመን በሰማያትና በምድር የፍጥረት ዕቅዱ ውስጥ እንደተካተተ ማወቅ አለባችሁ እግዚአብሄር ለእናንተ ያለው ዕቅድ በእምነት እንድትኖሩ እንደሆነ ታውቁ ዘንድ እያንዳንዳችሁን እለምናችኋለሁ።

ወደ ዘፍጥረት 1:21 እንመለስ «እግዚአብሄርም ታላላቆች አንበሪዎችን ውሃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኝቻቸውንም ተንቀሳቃሾችን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።»

እግዚአብሄር ሰሪ ነው እርሱ ፈጣሪ ነው እገዚአብሄር የሰራው ምንድነው? እግዚአብሄር ታላላቆችን አንበሪዎችና ሕያዋን ፍጥረታቶችን መፍጠሩ እንደዚሁም እያንዳንዱን ወፍ እንደ ወገኑ መፍጠሩ በችሮታው የእምነት ሰዎችን መፍጠሩን የሚያሳይ ነው በውስጣችን እምነትን የሚፈጥረው እግዚአብሄር ነው እርሱ እምነትን ይሰጠናል በውስጣችንም እምነትን ያበቅላል በእምነት እንድንከተለውም ይፈልግብናል።

በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ውስጥ ብትኖሩ እግዚአብሄር በጽድቁ የምታምኑበትን ተጨማሪ እምነት ይሰጣችኋል በመጀመሪያ የራሳችሁን ሰብአዊ ጥረት ከንቱነት ይገልጣል ዳግም የተወለዱ ሰዎች ወደ እምነት ክልል መግባትና በእምነት መኖርን መማር የሚችሉት ጌታን በምድራዊ ሐብቶቻቸው

ለመከተል ያላቸው ጥረት ፈጽሞ ሲከስም ብቻ ነው ያን ጊዜ የእምነታቸው መጠን አብዝቶ ይጨምርና ሙሉ በሙሉ ጌታን ወደ መታመን ይመጣሉ በሌላ አነጋገር ከዚህ ቀደም እምነቱን የተጠቀመበት ሰው የላቀ እምነትን በመጠቀም መቀጠል ይችላል የላቀ እምነት ሲኖረውም እምነቱ ቀስ በቀስ ያድጋል።

በአንድ ወቅት በእምነት በጌታ የኖሩ ሰዎች መጀመሪያ ላ እምነታቸው እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ትንሽ ልትሆን ትችላለች ነገር ግን በሒደት ይህ እምነት ያድጋል ልቦቻቸውም መንፈሳውያን ይሆናሉ ስለዚህ በእግዚአብሄር ላይ በቂ እምነት የለንም ብላችሁ ልትጨነቁ አይገባችሁም እግዚአብሄር ይህንን እምነት በእናንተና በእኔ ውስጥ ያሳድጋል እምነታችን እንዲያድግም ይንከባከበዋል።

አሁንም እንኳን እግዚአብሄር እኛን በማበጀት ቀጥሎዋል እግዚአብሄር ከዋክብቶችን እንዳበጀ ሁሉ እኛንም የእምነት ሰዎች እንድንሆን እየቀረጸን መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋችኋል እናንተንና እኔ የእግዚአብሄር ሕዝብ አድርጎ እየሰራን ነው አሁን በስጋቸው ላይ እየተደገፉ ያሉ ሰዎችን እግዚአብሄር ስጋዊ ነገሮቻቸውን እያወደመ ነው እግዚአብሄር በእርሱ ሳናምን መኖር እንዳንችል እያደረገን ነው የእግዚአብሄር ፈቃድ ይህ ነው።

የተወሰኑ ችግሮች ሲገጥሙን በሆነ ሰውኛ መንገድ ልንፈታቸው ብንሞክር ተጨማሪ ችግሮች ይገጥሙናል እንዲህ ባሉ ጊዜያት በእግዚአብሄር ብናምን፣ በእርሱ ላይ ብንደገፍና እርሱን ብንከተል እግዚአብሄር ጉዳዮቻችንን በሙሉ ይፈታል እንዲህ በማድረግም ስለ እውነተኛ እምነት ያስተምረናል እግዚአብሄር እምነታችን እንዲያድግ ይፈልጋል በእርሱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁሉን የሚያደርገው እግዚአብሄር ራሱ ነው አምላካችን ወላጅ ልጁን እንደሚንከባከብ የሚንከባከበን ለዚህ ነው።

እኛ አሁን በእግዚአብሄር ጽድቅ ወደምናምንበት የእምነት ግዛት ገብተናል በእግዚአብሄር ጽድቅ ብታምኑና በእምነት ብትኖሩ መንፈሳዊ በረከቶችን እንዳገኙ እንደሌሎች ትቀረጻላችሁ ነገር ግን በእግዚአብሄር ሳታምኑ ሕይወታችሁን ብትኖሩ በዚህ ምድር ላይ ትሰቃያላችሁ አሁን በጭራሽ አልረፈደም አሁንም ቢሆን እምነታችሁን በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ በማኖር ልትኖሩ ይገባችኋል።

እምነታችን እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ትንሽ ልትሆን ትችላለች ነገር ግን በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ያለን ይህ እምነት አብዝቶ ሲያድግ በመላው ሰማያዊ ግዛት ላይ እንድንበር፣ ውብ የሆነውን የሰማይ ግዛት በሙሉ እንድናይ፣ ለዘላለምም በሰማያዊ ነገሮች ሁሉ እንድንደሰትና በደስታና በሐሴት እንድንኖር ያስችለናል በእግዚአብሄር አገልግሎት ውስጥ በነጻነት እንድንሳተፍ፣ የእርሱን በረከቶች በነጻነት እንድናጣጥምና የእርሱን ክብር ሁሉ እንድናይ የተደረግነው በእምነት ግዛት ውስጥ ስላለን ነው ያ ለእኛ ከተሰጡን የእግዚአብሄር የተባረኩ ችሮታዎች አንዱ ነው።

እግዚአብሄር በአምስተኛው ቀን በእምነት እንድንኖር ፈለገ እግዚአብሄር በእርሱ ላይ እምነት እንዲኖረን እየነገረን ነው እምነታችን የሚያድገውም ይህ እምነት ሲኖረን እንደሆነ እየነገረን ነው በእግዚአብሄር የውሃና የመንፈስ ወንጌል ብታምኑ በእርግጠኝነት የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ታገኛላችሁ ካላመናችሁ ግን ለዘላለም የሐጢያቶቻችሁን ስርየት አታገኙትም።

መንፈሳዊ የሆኑ ወይም ሌሎች ችግሮቻችሁንና ጭንቀቶቻችሁን ለመፍታት ወደ እግዚአብሄር ትጸልያላችሁን? በእግዚአብሄር ብታምኑ እነዚህን ችግሮች በሙሉ በሚያስገርም ሁኔታ በእርግጠኝነት እንደሚፈታላችሁ አምናለሁ በሌላ በኩል ግን በእግዚአብሄር የማታምኑና በእርሱ ላይ የምትደገፉ ከሆናችሁ

በፋንታው በሰው ሰራሽ አስተሳሰቦች፣ ዘዴዎች ወይም መንገዶች የምትደገፉ ከሆናችሁ የእግዚአብሄር የጸጋ እጆች ከእናንተ ይርቃሉ እርሱም «በራሳችሁ ጥረት ማድረግ እንደምትችሉ ስለምታስቡ የምትፈልጉትን ሁሉ ሞክሩ» ይላል በእግዚአብሄር በመታመን ተስፋዎቻችንን ሁሉ በእርሱ ላይ ማኖርና እግዚአብሄር ሁኔታዎቻችንን እንዴት እንደሚለውጥና በሕይወታችን ውስጥም እንዴት እንደሚሰራ ለራሳችን ማየት አለብን።

በእግዚአብሄር ላይ መደገፍ አለብን

እግዚአብሄር በእረሱ ላይ በመታመን ፋንታ በራሳቸው ሰብአዊ ጉልበት የሚደገፉ ሰዎች በሙሉ ክፉዎች እንደሆኑ ተናግሮዋል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ኔፊሊም» (ዘፍጥረት 6፡4) እንዲህ ያሉ ሰዎች ነበሩ እነዚህ የሚያመላክቱት የላቀ ጉልበት ያላቸውን ወይም ግዙፋን የሆኑ ሰዎችን ነው እግዚአብሄር እንደ ኔፊልም እንደ ጎልያድ ያሉ ሰዎችን ያዋርዳል ነገር ግን እግዚአብሄር እንደ ዳዊት በእርሱ የሚደገፉትን ሰዎች የእርሱ አገልጋዮች አድርጎ ያስነሳቸውና በእነርሱ በኩል ይሰራል።

ማንም ሰው ምንም አይነት ክብር ይኑረው እግዚአብሄር ያንን ክብር ልክ እንደ ማለዳ ጤዛ የማድረቅ ጉልበት አለው እርሱ ምድራዊ ነገሮችን በሙሉ በአንድ ሌሊት ማውደም ይችላል ነገር ግን በእግዚአብሄር ላይ የሚደገፉ ሰዎችን ለዘላለም በሰማይ ግዛት ውስጥ ጸንተው እንዲቆሙ ይፈቅድላቸዋል የእርሱን ብርሃን እንዴት ለዘላለም እንደሚያበሩ ያሳያቸዋል።

በስጋዊ ነገሮች ላይ እተደገፋችሁ ነውን? ወይስ በእውነት

አምላክ ላይ እየተደገፋችሁ ነው? ሁላችሁም በእግዚአብሄር ላይ እንድትደገፉ እመክራችኋለሁ ማንኛውም አይነት ችግሮች ሲገጥሙዋችሁ በእግዚአብሄር ላይ እንድትደገፉ እመክራችኋለሁ ሁላችንም የጌታን እርዳታ እንድንጠይቅ፣ በእርሱ እንድንታመን እርሱን ተስፋ እንድናደርግና የእርሱን ፈቃድ እንድናውቅ እፈልጋለሁ ጌታን መከተል ተስፋችንን ሁሉ በስራው ላይ ማኖርና ጌታን መሻት አለብን እግዚአብሄር እነዚህን ሰዎች በመንገዳቸው ላይ እንደሚያበለጽጋቸውና እንደሚባርካቸው አምናለሁ ማናችሁም በምድራዊ ነገሮች ላይ እንዳትደገፉ እፈልጋለሁ ምድራዊ ነገሮች ያጠፉናል ያስቱናል ከዚህም በላይ ወዲያውኑ ያጠፉናል ስለዚህ ሁላችሁም በዘላለማዊው አምላክ ላይ እንድትደገፉ እመክራችኋለሁ፡፡

በርካታ ሰዎች በዚህ ምድር ላይ ኖረዋል ነገር ግን ከእነዚህ ሁሉ ሰዎች ዘላለማዊው ብርሃን የሚፈነጥቀው በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ በሚደገፉ ሰዎች ልቦች ውስጥ ነው ነገር ግን በእግዚአብሄር ጽድቅ የማይደገፉ ሰዎች ፈጽሞ በመንግስቱ ውስጥ አይገኙም ምንም ያህል መልካም ሰዎች ቢሆኑ እግዚአብሄር በእርሱ ጽድቅ የማይታመኑ ሰዎችን መልካም ምግባሮች በሙሉ ከንቱ አድርጎ ይቆጥራቸዋል፡፡

በምዕራባውያን ታሪክ ውስጥ ከሮማውያን መንግስት ጀምሮ ቅዱሱን የሮማውያን መንግስት ይዞ እንደ ስፔን መንግስት፣ የብሪቲሽ መንግስትና አሜሪካ ያሉ ታላላቅ ሐይሎች ተነስተው ወድቀዋል ብሪታንያ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ብዙ ቅኝ ግዛቶች የነበሩዋት ትልቅ ሐይል ስለነበረች «ጸሐይ ፈጽሞ የማትጠልቅባት መንግስት» ተብላ ተጠርታ ነበር በምዕራባውያን ታሪክ ውስጥ የታላላቅ መንግስታት መነሳትና መውደቅ ከክርስቲያን እምነት መነሳትና መውደቅ ጋር ተዛምዶዋል በሌላ አነጋገር አንድ አገር በእግዚአብሄር ላይ ሲደገፍና እርሱን ሲፈራ

ይበልጥ እየበለጸገ ይሄዳል ነገር ግን አንድ ጊዜ በመንግስቱ ስልጣን፣ በጡንቻውና በጦር መርከቦቹ ወታደራዊ ጉልበት ላይ ከተደገፈ ክብሩ ለዘላለም ሊቆይ አይችልም፡፡

በአንጻሩ በእውነት በእግዚአብሄር ላይ የሚደገፉ አገሮችና በእግዚአብሄር ላይ የሚደገፉ ሰዎች የእግዚአብሄር ጸጋ አይርቃቸውም ጻድቃን በእምነት በእግዚአብሄር ብርሃን ይበልጥ ብሩህ እየሆኑ ይሄዳሉ እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል፡፡

«የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት
ብርሃን ነው ሙሉ ቀን እስኪሆንም
ድረስ እየጨመረ ይበራል፡፡» (ምሳሌ 4:18)

ጻድቃን የእርሱን የእውነት ብርሃን እንዲገልጡ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም ከተወለድን በኋላ በጌታ ላይ ባለን እምነታችን ወየም በአለም ላይ ባለው ነገር በመደገፍ መኖር እንቀጥል እንደሆነ ለመወሰን በመስቀለኛ መንገዶች ላይ ስንቆም በእግዚአብሄር ጽድቅ የሚያምነውን የእምነት መንገድ በግልጽ መምረጥ አለብን፡፡

በእግዚአብሄር ጽድቅ የሚያምኑ የእምነት ሰዎች እንንን በዚህ አለም ላይ እኖሩ ሊሳሳቱ ይችላሉ በአንድ ወቅት ዳዊት የእስራኤሎችን ቁጥር ለመቁጠር ሞከረ ነገር ግን እግዚአብሄር ሕዝቡን እንዲቆጥር አልፈለገም እግዚአብሄር በስጋ መደገፍን አብዝቶ ይጠላል እግዚአብሄር ሰው በጉልበቱ ላይ ሲደገፍ ማለትም ልቡ በምድራዊ ነገሮች ላይ ሲደገፍ አይወድም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሄር ዳዊትን እንደቀጣውና በእስራኤልም በርካታ ሰዎች በዚህ ምክንያት እንደሞቱ ተጽፎዋል ስለዚህ የእምነት ሰዎች በምድራዊ ነገሮች ላይ ለመደገፍ ሲሞክሩ እግዚአብሄር በዚህ የተሳሳተ መንገድ ላይ እንዳይጓዙ ያግዳቸዋል ይከለክላቸውማል፡፡

አጋር ምዕመናኖቼ በልባችን ውስጥ ጌታችን ሊኖር ልንከተለውና በእምነትም እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኘውን እያደረግን ሕይወታችንን ልንኖር ይገባናል የእግዚአብሄርን እውነት ካወቅን በኋላ ነገም በእርሱ ላይ እንደምንደገፍና እንደምታመን ዛሬም በጌታ ላይ ልንደገፍና ልንታመን ይገባናል በቀሪው ዘመናችንም በጌታ ላይ ብቻ በመታመን መቀጠል እንደሚገባን እርግጥ ነው ስለዚህ ፈጽመን አንሰናከል ነገር ግን ወደ ዘላለም መንግስት እስክንደርስ ድረስ ሁሌም በጌታ ላይ እንታመን፡፡

በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ብቻ እምነት ቢበኖራችሁ እግዚአብሄር በእርግጠንነት ይባርካችኋል እኛ በእግዚአብሄር ጽድቅ ስለምናምን እያንዳንዱ እግዚአብሄር በረከት ሊኖረን ይችላል እግዚአብሄር ሁሉን በጊዜው ይፈጽመዋል በጊዜውም ከፍ ያደርጋችኋል፡፡

ስለዚህ እምነት ይኑራችሁ በእግዚአብሄር እመኑ በጌታ ጽድቅ እመኑ በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ምሪትም ታመኑ እግዚአብሄር ራሱ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በገለጣቸው የእግዚአብሄር ጽድቅ ስራዎች እመኑ በልቦቻችሁ ውስጥ በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ሁሉ ልቦች ውስጥ በጌታ የሚያምን እምነት ካለ ያን ጊዜ እግዚአብሄር ይበልጥ ክቡር ወደሆነ ስፍራ ከፍ ያደርጋችኋል እግዚአብሄርም ዕቅዱን የምትፈጽሙ መሳሪያዎቹ አድርጎ እንደሚጠቀምባችሁ አምናለሁ፡፡

ስለዚህ በጌታ ላይ በመታመን እምነታችንን ሁሌም መጠቀም ያስፈልገናል በችግር ጊዜ በጌታ ላይ ጥቂት ብቻ ከምትደገፉ ይልቅ ችግሩ ሲወገድ እንደገና በአለም ላይ ትደገፋላችሁ ምንም ቢሆን በጌታ ላይ መደገፍ አለባችሁ ልቦቻችሁም ሁሌም በእግዚአብሄር ላይ ብቻ መጽናት አለባቸው

ልቦቻችን ወደ አለም እንዲሄዱ ልንፈቅድ አይገባንም ከሁሉም በላይ ልቦቻችንን መጠበቅ አለብን እምነታችንንም መከላከል አለብን ሕይወታችንን ስንኖር የጌታን ፈቃድ መታዘዝ፣ በእርሱ ማመንና ልቦቻችንን መጠበቅ አለብን።

እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ እርሱን የሚሻ ሰው እንዳለ ማየት ይፈልጋል እግዚአብሄር በእርሱ የሚያምንና ጌታ በውስጡ የሚያድርበት ሰው ሲያይ በዚህ ሰው በኩል ይሰራል መጽሐፍ ቅዱስ «*እግዚአብሄርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው ብዙ ተባዙም የባሕርንም ውሃ ሙሉአት ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ*» እንደሚል እግዚአብሄር በእርሱ ላይ የሚደገፉትን እንዲህ ያሉ ሰዎች ይባርካቸዋል።

እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ የሚባርከው ማንን ነው? በእግዚአብሄር ጽድቅ የሚያምኑትን በእግዚአብሄር ሕጎችና ቃል መሰረት የሚመላለሱትን ሰዎች ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የሚባርካቸው የእምነት ሰዎችን ነው እግዚአብሄር ከልባቸው በእርሱ የሚያምኑ ሰዎችን ይባርካል በውጫዊ ገጽታ ብቻ በቅንአት የሚቃጠሉ ሰዎችን አይባርካቸውም።

እግዚአብሄር በእርሱ ጽድቅ በሚያምኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ይገባል እርሱ ይንከባከበናል ያደምጠናል በሕይወታችን ውስጥም ይሰራል በዚህ ታምናላችሁን? እግዚአብሄር እናንተንና እኔን በባረከበት በዚህ ፍቅር ታምናላችሁን? እናንተና እኔ በእግዚአብሄር ላይ ባለን እምነት ካልሆነ በቀር መኖር እንደማንችል ታምናላችሁን? በእግዚአብሄር ብናምን እኛን ሊባርከን እንደሚደሰት ታምናላችሁን? አዎ እባካችሁ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ እመኑ።

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም የተወለዱትንና ከዚያን ጊዜም ጀምሮ በእግዚአብሄር ጽድቅ እየታመኑ የሚኖሩትን ሰዎች ይባርካቸዋል በእግዚአብሄር

ጽድቅ ስንታመንና እርሱን ስንከተል እግዚአብሄር በማይነገሩ ክቡር በረከቶች ይሞላናል የእግዚአብሄርን ፈቃድ የምንታዘዝ ከሆነ ሺህ እጥፍና ሚሊዮን እጥፍ ይባርከናል ምክንያቱም እግዚአብሄር ስማያትንና ምድርን ከፈጠረበት መጀመሪያ ጀምሮ ሁላችንንም ሊባርከን ፈልጎዋል።

ስለዚህ ከጌታ ጋር አንድ ልብ ሆነን በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሄርን መንግስት ለማስፋፋት መትጋትና በእምነትም የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማገልገል አለብን የእግዚአብሄርን ታላላቅ በረከቶች ለመቀበል አቋራጩ መንገድ ሌላ ሳይሆን ይህ ነው ጅማሬያችን ታናሽ ቢሆንና ብዙ ሰዎችም በእኛ ባይማረኩም ልቦቻችን በእግዚአብሄር ላይ እምነት ካላቸው ያ ከበቂም በላይ ነው ያን ጊዜ እግዚአብሄር በእኛ አማካይነት ማድረግ የሚፈልገውን ሁሉ በክብር ይፈጽማል አሜን! ✉

እግዚአብሄር እኛን በአምሳሉ የፈጠረበት ምክንያት

« ዘፍጥረት 1:24-31 »

«እግዚአብሄርም አለ ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ እንስሳውንም እንደ ወገኑ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባህርን ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ እግዚአብሄርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሄር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው እግዚአብሄርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባህርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው እግዚአብሄርም አለ እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩ በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ ለምድርም አራዊት ሁሉ ለሰማይም ወፎች ሁሉ ሕያው ነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾችንም ሁሉ የሚበቅለው ሐመልማል ሁሉ መብል ይሁንላቸው እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን::»

እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ እያንዳንዱን ነገር ከፈጠረ በኋላ የፈጠረው የመጨረሻው ነገር የሰውን ዘር ነበር መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር የሰውን ዘር በፈጠረ ጊዜ በራሱ መልክና አምሳል እንደፈጠረው ይናገራል በዘፍጥረት ውስጥ ከሚገኘው ከዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ስላሴ አምላክን ማግኘት እንችላለን::

የምናምነው አምላክ እግዚአብሄር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን ሲፈጥር እነዚህ ሦስት ስብዕናዎች -- አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ - በእግዚአብሄር አምሳል መሰረት የሰውን ዘር ፈጠሩ እዚህ ላይ እግዚአብሄር «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» አለ እኛም ስላሴ አምላክን ማወቅ መቻል አለብን እግዚአብሄር የሰውን ዘር በራሱ መልክ ፈጠረው ይህንን አለምና የሰውን ዘር የፈጠረውም ስላሴ አምላክ እግዚአብሄር አብ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ ነው ሰማያትንና ምድርን በእነርሱ መካከል ያለውን እያንዳንዱን ነገርና ሰውንም ራሱን የፈጠረው ይህ አምላክ ነው::

በፍጥረቱ የመጨረሻው ቀን ማለትም በስድስተኛው ቀን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስራ የሰውን ዘር በመልኩ ፈጠረው እግዚአብሄርም *«ሰውን በመልካችን እንፍጥር»* አለ በዚያ መሰረትም ፈጠረው::

ታዲያ ሰው ምንድነው? ሰዎች ምንድናቸው? በእግዚአብሄር መልክ አምሳል የተፈጠሩ ናቸው ታዲያ ይህ ማለት እግዚአብሄር የሰውን ዘር በራሱ መልክ በፈጠረው ጊዜ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ የራሱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አድርጎ ሊፈጥረን ፈልጎ ነበር ማለት ነውን? አሥ እግዚአብሄር የሰውን ዘር በራሱ መልክ አምሳል የፈጠረበትን ዕቅድ መረዳትና በትክክል ማስተዋል ያስፈልገናል እግዚአብሄር ገና

ከመጀመሪያው ሰዎችን በመልኩ አምሳል የፈጠራቸው በስልጣኑና በክብሩ እንዲደሰቱ ነው።።

እግዚአብሄር ወንድንና ሴትን የፈጠረበት አላማ የራሱን ቤተክርስቲያን ለመመስረት እንደነበር መረዳት ይገባናል እግዚአብሄር ሴትን ከወንድ የጎን አጥንት መፍጠሩ እግዚአብሄር አብ ፈቃዱን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሚፈጽም የመሆኑን እውነታ የሚተነብይ ነው ይህም በቤተክርስቲያኑ አማካይነት የሚገለጠውን የእግዚአብሄር ዕቅድ ያሳያል ይህንን ዕቅድ ያቀደውና የሚፈጽመውም ስላሴ አምላክ ነው።።

እግዚአብሄር እያንዳንዱን ሰው በራሱ መልክ ፈጠረው ይህም አላማውን ለመፈጸም ሲል በእግዚአብሄር ታቀደ ነው አለም ከመፈጠሩ ከረጅም ጊዜ በፊት እግዚአብሄር አብ እኛን ልጆቹ ለማድረግ አስቀድሞ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አቀደ ይህንን የእግዚአብሄር አብ ዕቅድ ለመፈጸምም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መጣ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ የአለምን ሐጢያቶች ተሸከመ በመስቀል ላይ ሞተ ዳግመኛም ከሞት ተነሳ በዚህም የአብን ፈቃድ ፈጸመ በሌላ በኩል መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሄር አብና ኢየሱስ ክርስቶስ ለፈጸሙት ደህንነት ዋስትናን ይሰጣል ኢየሱስ ክርስቶስ በመታዘዝ የእግዚአብሄር አብን ፈቃድ ፈጸመ።።

የእግዚአብሄር አብ ፈቃድ የተፈጸመው እንዴት ነበር?

አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ለእኛ አንድ አምላክ ናቸው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር አብ ከአለም ፍጥረት በፊት በኢየሱስ ክርስቶስ እንደመረጠንና አስቀድሞ እንደወሰነን

ይናገራል ያቀደውንም ፈቃዱን በኢየሱስ ክርስቶስ ፈጸመው (ኤፌሶን 1:3-5) በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር አብ ለእኛ ያለውን ፈቃድ አስቀድሞ ወሰነ ፈጸመውም ይህ ሁሉ እግዚአብሄር አብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ መልክ አምሳል ልጆቹ አድርጎ ፈጥሮናል ማለት ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ይህንን የፈጸመው ከአብ ከልጁ ኢየሱስ ክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተማክሮ ነው ስለዚህ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በክብር ሊፈጥሩን አቀዱ እርሱንም ፈጸሙት::

እግዚአብሄር አብ ልጆቹ አድርጎ ሊፈጥረን አቀደ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስም የአባቱን ፈቃድ በመታዘዝ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ሞተ ዳግመኛም ከሙታን ተነሳ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅና የአለምን ሐጢያቶች በመውሰድ ሐጢያቶቻችንንም ተሸክሞ በመስቀል ላይ በመሞትና ዳግመኛም ከሙታን በመነሳት የሰውን ዘር ሐጢያቶች ደመሰሰ በዚህም የእግዚአብሄርን ፈቃድ ፈጸመ እግዚአብሄር አብ ልጆቹ አድርጎ ሊፈጥረን ፈለገ ስለዚህ በልጁ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የእርሱ ልጅ የሚሆኑበትን መብት ሰጣቸው::

ታዲያ እግዚአብሄር እኛን ሰዎችን ልጆቹ አድርጎ የመለሰንና በመልኩ አምሳል የፈጠረን እንዴት ነው? ይህንን ያከናወነው በአንድ ጊዜ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ነው እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ ፈቃዱንም ፈጸመ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እኛን በማዳንና በመፍጠርም ፈቀዱን ፈጸመ የሰውን ዘር በመልኩ የፈጠረው ለዚህ ነው::

እግዚአብሄር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ በመልኩ ፈጠረው እንዲህም አለ *«ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ»* (ዘፍጥረት

2:24) ፈቃዱ ይህ ነው እኛ ሰዎችም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ከእርሱ ጋር አንድ እንድንሆን ይፈልጋል እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን የሰውንም ዘር ሲፈጥር ወንድና ሴት አድርጎ የፈጠረው ለዚህ ነው እግዚአብሄር እነርሱን በፈጠራቸው ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሊያድናቸው ያቀዳቸው የዳኑና ጻድቃን የሆኑ ሰዎች በአእምሮው ውስጥ ነበሩ።

ለፈቃዱ ምስጋና ይግባውና ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑ ሰዎች የመኖራቸውን አላማ መከወን የሚችሉት በእምነት ነው እኛ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን ዳግመኛ ተወልደናል በሌላ አነጋገር የዚህ አለም ሐጢያተኞች የእግዚአብሄር ልጆች መሆን የሚችሉት ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ስናምንና በዚህም የሐጢያቶቻችንን ስርየት ስንቀበል ብቻ ነው የእርሱ ልጆች የምንሆንበትን መብት የምንቀበለው ከእግዚአብሄር ነው።

በእርሱ የውሃና የመንፈስ ወንጌል በማመን የእግዚአብሄር ልጆች ከሆንን በኋላ እግዚአብሄር የሰማይ የሆነውን ሌላውን ነገር ይሰጠናል ጌታ ራሱም የሁላችንም ጌታ ይሆናል ስለዚህ የእግዚአብሄርን መልክ ከሚመስሉ ሰዎች አንዱ ለመሆናችን ምንም አይነት ጥርጣሬ የለንም።

የእግዚአብሄርን መልክ የምንመስለው እንዴት ነው? እግዚአብሄር ገና ከመጀመሪያው የሰውን ዘር በአምሳሉ ለመፍጠር ያቀደው አላማ የተፈጸመው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ነው እግዚአብሄር ገና ከመጀመሪያው እኛን ሰዎችን ልጆቹ አድርጎ ሊፈጥረን አቀደ ይህ የእግዚአብሄር አብ ፈቃድም በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጸመ።

እግዚአብሄር ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ምንም ቅድመ

ሁኔታ ልጆቹን ፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ሌሎቹ ፍጥረታት በሙሉ ያምጹ ነበር ይህ ማለት እግዚአብሄር የፍጥረታቶቹን አመጽ ይፈራል ማለት እንዳልሆነ የታወቀ ነው ነገር ግን ይህ ማለት እግዚአብሄር ፍርደ ገምድል አምላክ መሆን አልፈለገም ማለት ነው የእግዚአብሄር ስም መጥፋት ስለሌለበት እግዚአብሄር ገና ከመጀመሪያው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለደህንነታችን የሚሆን ዕቅድ ነበረው በዚህ ብርሃን መጀመሪያ በዚህ ምድር ላይ ፍጥረታቶች ሆነን መወለዳችን በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ያለ የእግዚአብሄር በረከት ነው።

እግዚአብሄር ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የምንገኝ ልጆቹ አድርጎናል እግዚአብሄር አብ የእርሱ ወንድሞችና እህቶች ሆነን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዴት አስቀመጠን? እግዚአብሄር አብ ኢየሱስ ባጠናቀቀው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ክልል ልጆቹ እንድንሆን መንገዱን ከፍቶልናል ስለዚህ የእግዚአብሄር ፍቅር መግለጫ የሆነውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በትክክል ማወቅ አለብን።

በመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሄር ዕቅድ ምን እንደሆነ መገንዘብ አለብን እግዚአብሄር አብ ከአለም ፍጥረት በፊት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደህንነታችንን አቀደ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እውነት ውስጥም ለአንዴና ለመጨረሻ ፈጸመው ይህ በኤፌሶን 1:4-5 ውስጥ በግልጽ ተመስክሮዋል *«ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን»* ደህንነታችን የተከናወነው በእግዚአብሄር ዕቅድ ነው በኤፌሶን ምዕራፍ አንድ ላይ የተገለጠው የእግዚአብሄር ዕቅድ ይህ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሄርን መልክ ወደ

መምሰል የደረስነው ለዚህ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር አብ የሰውን ዘር በዚህ አለም ላይ የፈጠረው የእርሱን መልክ እንድንመስል ነው።

በጥቅሉ የአለማዊ ሐይማኖቶች መስራቾች ተብዬዎች ራሳቸውን ለማመጻደቅ ይሞክራሉ በርካታ ሰዎች በራሳቸው ጥረት መለኮታዊ ሁኔታ ላይ ለመድረስ ሲሞክሩ እናያለን ነገር ግን ሁሉም ከንቱ ነው ነገር ግን ሰው የሐጢያቶቹን ስርየት ጸጋ መቀበልና ከእግዚአብሄር ሕዝብ አንዱ መሆን የሚችለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ኢየሱስ ክርስቶስን ሲገናኝ ብቻ ነው እግዚአብሄር ሰዎች በዚህ አለም ላይ እንዲወለዱ የፈጠረበት አላማና በእግዚአብሄር ለሚያምኑና ቃሉን ለሚከተሉ ሰዎች ሁሉ በሙላቱ የተፈጸመው እውነት ያ ነው።

እኛ በዚህ አለም ላይ መወለዳችንና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ከመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መገናኘታችን ታላቅ በረከት ስለሆነ የምንሻው ምንም ነገር የለም ይህ ማለት በዚህ አለም ላይ የተወለድንበት አላማ ተፈጽሞዋል የእግዚአብሄርም ፈቃድ እንደዚሁ ተጠናቋል ማለት ነው በእግዚአብሄር ዕቅድ ውስጥ ያለውን እውነተኛ ዕረፍት ከልባችን የምናጣጥመውና የመወለዳችንን እውነተኛ ትርጉም የምናውቀው በዚህ መልኩ ነው በዚህ አለም ላይ የተወለድንበትን አላማና የመኖራችንን ትርጉም ያገኘነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ነው።

እግዚአብሄር የሰውን ዘር በመጀመሪያ ሲፈጥር ለምን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው?

እግዚአብሄር በመጀመሪያ አዳምን ፈጠረ እንዲያንቀላፋ ካደረገው በኋላም ከጎድን አጥንቶቹ አንዱን ወስዶ ከዚህ የጎድን

አጥንት ሴትን ፈጠረ በዚህም እግዚአብሄር የሰውን ዘር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ለምን አላማ ፈጠራቸው? በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሊባርካቸው ነበር እግዚአብሄር አብ እኛን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምነውን አማኞች በአብ በኩል በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ወንድ ልጆቹና ሴት ልጆቹ አደረገን እግዚአብሄር አብ ለሚወዳቸው ሰዎች አንድያ ልጁን በመስጠቱ የእግዚአብሄር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መጥቶ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ በዚህ ምክንያት የዚህን አለም ሐጢያቶች ተሸከመ ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህን አለም ሐጢያቶች ስለተሸከመ ደሙን ማፍሰስና በመስቀል ላይ መሞት ነበረበት ዳግመኛም ከሙታን በመነሳት የአብን ፈቃድ ፈጸመ በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር አብ ልጆቹ አድርጎ የፈጠረን በልጁ አማካይነት ነው።

በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር አብ ከዚህ ሰው ማለትም ከልጁ አውጥቶ ፈጠረን እግዚአብሄር ከአዳም በወሰዳት አጥንት ሴትን ፈጠረ ይህ ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ ፈጠረን ማለት ነው ወንዱም (ኢየሱስ ክርስቶስ) ሴቲቱን (እኛን) አብዝቶ ወደዳት ስለዚህ አዳም ሔዋን ስትመጣለት እንዲህ አለ።

«ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት
ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ
ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።» (ዘፍጥረት 2:23)

ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛችን አድርገን ስናምንና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት ስንቀበል የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን ደግም መወለድ እንችላለን ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ እግዚአብሄር አብ እንዲህ አለ *«በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» (ማቴዎስ 3:17)* በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር አብ ኢየሱስ ክርስቶስን በዚህ አለም ላይ ካሉት ሌሎች ፍጥረታቶች ሁሉ

አብዝቶ ወደደው::

እኛ የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት ነው ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ አለም የላከው ማነው? አንድያ ልጁን የላከልን እግዚአብሄር አብ ነው እርሱ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማንይነት አድኖናል እግዚአብሄር አለሙን አብዝቶ ስለወደደ አንድያ ልጁን ሰጠ ይህ ማለት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምነውን አማኞች ሊያድነን ወሰነ ማለት ነው እግዚአብሄር አብ ከሐጢያቶቻችን ሊያድነን እጅግ የሚወደውን ልጁን አንድያ ልጁን ፍጡር አድርጎ ላከው::

እግዚአብሄር የእርሱን መልክ እንድንመስል ሊፈቅድልን ልጁን ወደዚህ ምድር ላከ ልጁ በፈጸመው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነትም እግዚአብሄር የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ አነጻ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑትን ሁሉ ሊያድን ወሰነ እግዚአብሄር አብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ያከናወነው የሰው ዘር ደህንነት ይህ ነው ይህም በቤተክርስቲያኑ አማካይነት የገለጠው የደህንነት ምስጢር ይህ ነው::

አሁንም ገና የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ያልተቀበሉ ሰዎች የእግዚአብሄርን ዕቅድ መረዳት አይችሉም

እግዚአብሄር ስለ እኛ ሁሉን ያውቃል ልጁን ወደዚህ ምድር በመላክም ከአለም ሐጢያቶች የማዳን ስራን ፈጸመ በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር አብ ሰይጣን በኋላ ምን እንደሚያደርግ አስቀድሞ ስላወቀ በዕቅዱ መሰረት ፈጠረን እግዚአብሄር አብ ከአለም ፍጥረት በፊት በኢየሱስ ክርስቶስ መረጠን በዚህ አለም ላይ ከመወለዳችን ከረጅም ጊዜ ምፊት ይህ ዩኒቨርስም

ከመፈጠሩ በፊት ደህንነታችንን አስቀድሞ ሲያቅድ ነበር እግዚአብሄር ያሰበውን የደህንነት ዕቅድ በኢየሱስ ክርስቶስ በተጨባጭ ፈጸመ በሌላ አነጋገር እርሱ ይህንን ዕቅድ ፈጸመ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነትም ደህንነታችንን ለአንዴና ለመጨረሻ አጠናቀቀ።

እግዚአብሄር በአምሳሉ የሰውን ዘር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ ይህ ማለት እግዚአብሄር በዚህ አለም ላይ ባስቀመጣቸው ወንድ (ኢየሱስ) እና ሴት (እኛ) አማካይነት ፈቃዱን መግለጥ ፈለገ እግዚአብሄር አብ የዚህ አለም ሐጢያተኞች በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የእርሱ ልጆች መሆን የሚችሉበት ዕቅድ ነበረው እኛ ቅዱስ ስላሴን መረዳት የምንችለው ለእኛ የሆነውን የእግዚአብሄር ፈቃድ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ስንገነዘብ ብቻ ነው።

እግዚአብሄር *«ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር»* አለ ከዚያም ወንድንና ሴትን ፈጠረ በሁሉም ነገር ላይ እንዲሰለጥኑ ፍጥረትን ሁሉ በአደራ ሰጣቸው።

በእርግጥ እግዚአብሄር በመልኩ ፈጥሮናልን? የእግዚአብሄር መልክ እንደ ሰው መልክ ነውን? ሐዋርያው ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ አይቶ *«እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖችና በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች»* እንዳሉት አድርጎ ገልጦታል «የእግዚአብሄር መልክ» የሚለው ሐረግ የእግዚአብሄር ፊት ወይም ገጽታ ማለት አይደለም ምክንያቱም እግዚአብሄር መንፈስ ነውና ይልቁንም ይህ ሐረግ የሚያመላክተው የእርሱን መለኮታዊ ባህሪያት ነው ይህም እግዚአብሄር ሕዝቡን ከመለኮት ባህሪው ተካፋይ እንዲሆኑ እንዳደረጋቸው የሚጠቁም ነው። (2ኛ ጴጥሮስ 1:4)

የእግዚአብሄር ሕዝቦች በሰዎች መካከል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉ

ናቸው አሁን እነርሱ የመለኮት ባህርይ ተካፋዮች ሆነዋል።

የእግዚአብሄር ተፈጥሮ ምንድነው? በመጀመሪያ ደረጃ እርሱ ፍቅር ነው አምላካችን የተትረፈረፈ ፍቅሩን የሰጠን መሐሪ አምላክ ነው እግዚአብሄር ለሐጢያተኞች ይራራል ሐይል የሌላቸውንም ይምራቸዋል የጻድቃን ልቦችም ደግሞ የእግዚአብሄርን መልክ ይመስላሉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ የሐጢያቶቻቸውንም ስርየት የተቀበሉ ሰዎችም የእግዚአብሄር ባህሪዎች ይኖራቸዋል።

እግዚአብሄር ክፉ አይደለም እግዚአብሄር ከሰው የሚለይበት አንዱ ገጽታ መዋሸት የማይችል መሆኑ ነው እግዚአብሄር ጻድቅ ነው ዳግም በተወለዱ ሰዎች ልቦች ውስጥ የእግዚአብሄር ጽድቅ አለ እግዚአብሄር ፍጹም ነው እርሱ ምንም ነውሮች የሉበትም ሰው ልክ እንደ እግዚአብሄር ፍጹም የሆነው በእምነት ነው እግዚአብሄር ለአብርሃም *«በፊቴ ተመላለስ ፍጹምም ሁን» (ዘፍጥረት 17:1)* ያለው ለዚህ ነው ጻድቃን ፍጹም የሆኑ ልቦች አሉዋቸው።

እግዚአብሄር አብ እነዚህን ሁሉ ነገሮች አቀደ ዕቅዱንም በልጁ አማካይነት ሊፈጽም ፈለገ ስለዚህ እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ከሐጢያቶቻችን አዳነን ኢየሱስ ደህንነታችንን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ወደ እግዚአብሄር ዙፋን ቀኝ አረገ ዳግም ሲመጣም ጌታ ሆኖ ይመጣል እግዚአብሄር አብ ደህንነታችንን አቀደ ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃውና በደሙ አማካይነት ከሐጢያቶቻችን አዳነን ይህንን የደህንነት እውነት በልቦቻችን ስንቀበል እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ «ትክክል ናችሁ እኔ አምላካችሁ ነኝ እናንተም ልጆቼ ናችሁ» በማለት እምነታችንን ያጸናል ያትመንማል ስለዚህ ስላሴ አምላክ -- አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ -- አለ እነዚህ ሦስቱም የእግዚአብሄር ስብዕናዎች በሙሉ በእርሱ

መልክ ለተፈጠርነው ለእኛ አንድ ናቸው።

የስላሴ ትምህርት እጅግ ጠቃሚ የሆነ የቃለ እግዚአብሄር ርዕሰ ጉዳይ ነው ነገር ግን ልቦቻቸው ከሐጢያቶቻቸው ያልነጹላቸው ሐጢያተኞች የቅዱስ ስላሴን እሳቤ አያስተውሉም መንፈስ ቅዱስ ማስተዋልን እስካልሰጠን ድረስ ይህንን መንፈሳዊ እሳቤ መረዳት አንችልም ኢየሱስ ክርስቶስንም አዳኛችን አድርገን ልንገነዘበው አንችልም በመንፈስ ቅዱስ በኩል ባይሆን ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ በልቦቻችን ውስጥ አዳኛችን መሆን ባልቻለም ነበር እግዚአብሄር አብንም «አባ አባት» ብለን መጥራት አንችልም ስለዚህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ እምነት ከሌለን ትክክለኛ ወደ ሆነ የመንፈስ ቅዱስ መረዳት ላይ ፈጽሞ መድረስ አንችልም።

በቃሎቻችሁ ሁሌም ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ እንደሆነ ልትናገሩ እንደምትችሉ የታወቀ ነው ነገር ግን ያለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ የመሆኑን እውነተኛ የእምነታችሁን ኑዛዜ መናዘዝ አትችሉም በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ስለ አብ ፈቃድና ስላዳነን የኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነት እየነገረን ያለው በቅዱሳት መጽሐፍት ቃል አማካይነት ነው እግዚአብሄር በመንፈስ ቅዱስ ያተመን ጻድቃን እንዳደረገን ለማረጋገጥ ነው።

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማንይነት ካዳነንና ጻድቃን ካደረገን በኋላ «ሐጢያት የለባችሁም እናንተ ልጆቼ ናችሁ እናንተ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁ» ይላል ስለዚህ እግዚአብሄር እኛን ከአለም ሐጢያቶች በማዳን ይህንን የስላሴ አምላክ ዕቅድ መሆኑን እንድንገነዘብ አስችሎናል እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ደህንነታችንን እንዳቀደ በኢየሱስ ክርስቶስም ደህንነታችንን ያለ እንከን እንደፈጸመና እርሱ ራሱም በዚህ የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ

በመንፈስ ቅዱስ እንዳተማቸው ተናግሮዋል እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት በኢየሱስ ክርስቶስ የዳንነውን ሰዎች ፈጽሞ እንደማይተወን ተናግሮዋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አለ *«ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላዕክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ሐይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሄር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቻለሁ» (ሮሜ 8:38-39)* እግዚአብሄር አድኖናል ፈሞም ልጆቹ አድርጎናል እኛ ን ከሐጢያት በማዳን የተከናወነው የእግዚአብሄር ፈቃድ ይህ ነው በሌላ አነጋገር ደህንነታችን የተከናወነውና እኛም የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው በእግዚአብሄር ፍጹም የእውነት ቃል ነው።

ይህ የደህንነት እውነት ከሰው የተገኘ ትምህርት አይደለም ከሰውም በሰውም አይደለም ሰው ደህንነትን ማግኘት የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ቃል በማመን ብቻ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እኛ የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው በእግዚአብሄር አብ ችሮታ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነትና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንደሆነ ይናገራል።

እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነታችንን ባያቅድ ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ባልመጣም ነበር በአጥማቂው ዮሐንስም ባልተጠመቀ ነበር ዳግመኛ ከሙታን መነሳት ቀርቶ የአለምን ሐጢያቶች ተሸክሞ መሰቀል፣ ደሙን ማፍሰስና እስከ ሞት ድረስ መድማት ባላስፈለገው ነበር ወደ እግዚአብሄር አብ ዙፋን ቀኝ ማረግ ባላስፈለገው ነበር መመለስም አያስፈልገውም የእግዚአብሄር አብ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከአለም ሐጢያቶች ለማዳን በግልጽ ወደዚህ ምድር መጣ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌልም እኛን ከአለም ሐጢያቶች በመታደግ

በእርግጥም የእግዚአብሄር ሕዝብ አደረገን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ አለም ሐጢያቶች ቢያድነንና በዚህ እንድናምን ቢጠይቀንም እኛ ራሳችን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ካላመንን መንፈስ ቅዱስ የመጨረሻ ማረጋገጫ በመስጠት አያትመንም ስለዚህ እምነታችን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ፍጹም ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ነገር ከንቱ ነው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለሌሎች ስንሰብክ ካመኑ መንፈስ ቅዱስ ወዲያውኑ ልቦቻቸውን ያትማል ስለዚህ እነርሱም የእግዚአብሄር ልጆች መሆናቸው ይመሰክርላቸዋል በሌላ አነጋገር መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሄር ቃል «ትክክል ናችሁ! ሐጢያት የለባችሁም!» በማለት የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የተቀበሉትን ሰዎች ይደግፋዋቸዋል።

እኛ ያደረግነው ነገር ቢኖር የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መቀበል ብቻ ቢሆንም አሁን መንፈስ ቅዱስ በልቦቻችን ውስጥ ይኖራል ደህንነታችን የተከናወነው በስላሴ አምላክ ነው አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አምላክ ናቸው ይህ አምላክም ለእኛ ተመሳሳይ አንድ አምላክ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሄር አብ ለእኛ ባቀደው ዕቅድ መሰረት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት እንዳዳነን በልቦቻችንን መቀበል አለብን ያን ጊዜ የእግዚአብሄር ልጆች እንሆናለን እግዚአብሄር ስላሴ እንደሆነ ስለምናውቅና ስለምናምን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት አባታችን ነው እርሱ እረኛችንም ነው እግዚአብሄር አብ ኢየሱስ ክርስቶስን በሰው ስጋ ወደዚህ ምድር ሊልከው እንዳቀደና ኢየሱስ ክርስቶስም በውሃውና በደሙ አማካይነት ከሐጢያቶቻችን እንዳዳነን ስናምን ያን ጊዜ የእግዚአብሄር ልጆች እንሆናለን።

እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የምናምን አማኞች ስለ ስላሴ አምላክ የምንናገረው በቀላሉ ነው በእርሱ የምናምነውን

ያለ ችግር ነው ለጻድቃን ስለ እግዚአብሄር የሚነገረው እውነት ያን ያህል አስቸጋሪ አይደለም «እግዚአብሄር ወደደን ልጁን የላከልን ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሳ ነው እግዚአብሄር እጅግ በሚወደው አንድያ ልጁ አማካይነት ከሐጢያት አዳነን ስለዚህ በዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ውሃና ደም በማመን ድነናል ከሐጢያት መዳን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሄርም ልጆች ሆነናል::»

የደህንነታችን መርህ ልክ እንደ ጋብቻ መርህ ነው በዚህ አለም አንድ ወንድና አንዲት ሴት ሲዋደዱ ልጅ እንደሚወለድ ሁሉ እግዚአብሄር አብም በልጁ አማካይነት ልጆቹ አድርጎናል ሐዋርያው ጳውሎስ በጋብቻ ላይ ሲናገር እንዲህ ያለው ለዚህ ነው *«ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ይህ ምስጢር ታላቅ ነው እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ» (ኤፌሶን 5:31-32)* ደህንነታችን ልክ እንደ ጋብቻ ነው የወንድና የሴት መጋባት እግዚአብሄር እኛን የማግባቱ ያህል ነው እግዚአብሄር ልጆቹ ስላደረገን እርሱና እኛ አንድ አንል ሆነናል::

ነገር ግን ሐጢያተኞች ስላሴ አምላክን የሚያብራሩበት መንገድ የላቸውም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት እስካልተቀበልን ድረስ ቅዱስ ስላሴን ማስተዋል አንችልም ሰው የሐጢያቶቹን ስርየት ቢቀበልም እንኳን የመንፈስ ቅዱስ እሳቤ ምጣም ውስብስብ ሆኖ ከተብራራ የሚፈጥረው ራስ ምታትን ብቻ ነው ሰው ይህንን እሳቤ መረዳት የሚችለው ቀለል ባለ መንገድ ከተብራራለት ብቻ ነው አለበለዚያ በጣም በተወሳሰበ መልክ ከተብራራ ለማስተዋል አዳጋች ነው::

የሰው ልብ አንዳንድ ጊዜ ጨካኝ ወደ መሆን ያዘነብላል ዳግም የተወለዱ ሰዎችም እንኳን በየጊዜው ርህራሄ ቢሶች የሚሆኑ ይመስላሉ ነገር ግን በጣም ገሮች ናቸው ጻድቃን

ማንኛውንም ሰው የመጉዳት ፍላጎት የላቸውም ምክንያቱም በእርሱ መልክ መሰረት በእግዚአብሄር ምሳሌ አዲስ ፍጥረታት ሆነን ዳግም ወልደናልና (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17) እኛ የሐጢያቶቻችንን ስርየት በሙሉ የተቀበልን ሰዎች የእግዚአብሄር ልብ አለን።

በስድስተኛው የፍጥረት ቀን በዚህ በመጨረሻው ቀን እግዚአብሄር የሰውን ዘር ፈጠረ በመልኩም ፈጠረን እግዚአብሄር ለስድስት ቀናት ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገረ ፈጠረ በሰባተኛውም ቀን አረፈ እግዚአብሄር በሰባተኛው ቀን ማረፉ ደህንነታችንን ለአንዱና ለመጨረሻ ማጠናቀቁን ይገልጣል ሰባት ቁጥር የእግዚአብሄርን ፍጽምና ይገልጣል እግዚአብሄር ደህንነታችንን እንዳቀደና የደህንነት ንድፉንም ልክ እንደ አለት አጠንክሮ ተግባራዊ እንዳደረገው ያመላክታል ስለዚህ እግዚአብሄር በዚህ መንገድ የሰውን ዘር በመልኩ ፈጠረው እኛ እግዚአብሄር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተባብረው የፈጠሩን የስራቸው ውጤቶች ነን።

በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች በስላሴ አምላክ በትክክል አያምኑም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነና እርሱ ራሱም አምላክ እንደሆነ አያምኑም ይህንን መንፈሳዊ እሳቤ እንኳን መረዳት አይችሉም ከዚህ የተነሳ የቅዱስ ስላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት የት እንደሚገኝ ለማወቅ ይጠይቃሉ።

ነገር ግን የስላሴ አምላክ ጭብጥ በዘፍጥረት 1:26 ላይ ይገኛል *«እግዚአብሄርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር»* እዚህ ላይ የሆዋ እግዚአብሄር አብ «ሰውን በራሴ መልክ እንደ ራሴ ምሳሌ ብቻዬን ልፍጠር» ብሎዋልን? አላለም እርሱ ያለው «ሰውን በመልካችን እንፍጠር» ነው እነዚህ የብዙ ቁጥር ቃሎች እግዚአብሄር ስላሴ እንደሆነ ያሳያሉ።

ለመድገም ያህል እግዚአብሄር እንዲህ አለ *«ሰውን በመልካችን እንፍጠር»* ይህ የሚያመላክተው ስላሴ አምላክን ማለትም አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ነው ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታቸው እንደሆነ ይናገራሉ ጌታ እነርሱን የፈጠራቸውና ከሐጢያት ያዳናቸው አምላክ እንደሆነ ይናገራሉ ስለ መንፈስ ቅዱስስ? እርሱንም ቅዱስ አምላክ አድርገው ይጠሩታል መንፈስ ቅዱስ ሁሌም በውስጣችን ስለሚኖር ይጠብቀናል ይመራናል ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ የእግዚአብሄር ልጆች እንዳልሆንን ይናገራል።

አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ለእኛ አንድ አምላክ ናቸው የምንለው ለዚህ ነው እነዚህ ሦስቱ የእግዚአብሄር ስብዕናዎች ፈጽመው አድነውናል ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን ደህንነታችንን አልፈጸመም ነገር ግን በአብ ፈቃድ መሰረት አዳነን ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ በአብ ፈቃድ መሰረት ተመላለሰ እርሱ እንዲህ አለ *«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሄር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው።»*

እግዚአብሄር ልጆቹ አድርጎ የፈጠረን በዚህ መልኩ ነው እግዚአብሄር አብ ሐጢያቶቻችንን ለመደምሰስና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ልጆቹ ሊያደርገን አቀደ ይህንንም ዕቅድ ለመፈጸም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መጣ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ሞተ በሦስት ቀናት ውስጥም ከሙታን ተነሳ በዚህም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ፈጽሞ ደመሰሰ አሁን ይህንን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑ ሰዎችን እግዚአብሄር «እናንተ ልጆቼ ናችሁ ሌሎቹ ፍጥረታት በሙሉ ፍጡራን ብቻ ናቸው እናንተ ግን ልጆቼ ናችሁ» በማለት ይቀበላቸዋል።

እግዚአብሄር እያንዳንዱን ሰው ልጁ አድርጎ ሊቀበል እንደሚፈልግ የታወቀ ነው (1ኛ ጢሞቴዎስ 2:4) ነገር ግን ብዙ ሰዎች የዲያብሎስን ቃሎች ስለሚያደምጡ፣ የእግዚአብሄርን ደህንነት ስለማይቀበሉና ፈጽመው ሐጢያት አልባ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሄር በልጁ አማካይነት እንዳዳናቸው ለማመን እምቢተኞች ስለሆኑ የእግዚአብሄር ልጆች መሆን ካለመቻላቸውም በላይ የዲያብሎስ ልጆች ሆነው ቀርተዋል።

አሁን ስላሴ አምላክን መረዳት መቻል አለባችሁ ከሐጢያት መዳናችን በድንገት የመጣ ነገር እንዳይደለ እርግጥ ነው ደህንነታችን የታቀደውና የተከናወነው በስላሴ አምላክ አማካይነት ነው ስለዚህ እኛ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር በዚህ እውነት ማመን ብቻ ነው መንፈስ ቅዱስ «እናንተ ልጆቼ ናችሁ» በማለት ለደህንነታችን ዋስትናን ስለሰጠን ረዳታችን አጋዣችን ብለን እንጠራዋለን።

ሰው ሲከስር ዕዳውን ሊከፍልለት ዋስትና የሰጠው ሰው ዕዳውን በሙሉ መክፈል አለበት ነገር ግን እኛን በሚመለከት ለደህንነታችን ዋስትናን የሚሰጠን ሌላ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ነው ምንም አይነት ጉድለቶች ቢኖሩብንም ምንም ያህል ሰይጣን ሐጢያት እንዳለብን ቢከሰንም መንፈስ ቅዱስ «እኔ ዋስትናችሁ እሆናለሁ እናንተ በእርግጥም የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁ ሐጢያት የለባችሁም» በማለት ለደህንነታችን ዋስትናን ሰጥቶናል እግዚአብሄር ጻድቃን እንድንሆን አቀደ ይህንንም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ፈጸመው እግዚአብሄር በስድስተኛው የፍጥረት ቀን የሰራው ስራ ይህ ነው።

እግዚአብሄር «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው» ብሎ ነግሮናል የምናፈራውና የምንበዛው እንዴት ነው? መብዛት የምንችለው

ኢየሱስ ክርስቶስን ስናገባው ብቻ ነው።

እግዚአብሄር «ምድርን ሙሉአት» ብሎ ነግሮናል አሁን ሰዎች ምድርን ይሞላሉን? አዎ አሁን የአለም የሕዝብ ቁጥር ከ6 ቢሊዮን በላይ መሆኑን ስናጤን ምድር አሁን በሰው ዘር እንደተሞላች ግልጽ አይደለምን? የእግዚአብሄር ቃል ሳይፈጸም ይቀራልን? አይቀርም በእግዚአብሄር ቃል መሰረት ይፈጸማል።

እግዚአብሄር «በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዙአቸው» ብሎዋል ሰዎች ሕያዋን ፍጥረታቶችን ሁሉ አይገዙምን? አንድ አውሬ ምንም ያህል ብርቱ ቢሆንም እንኳን ከሰው አገዛዝ ስር ነው የሰውን ዘር ማሸነፍ የሚችል አውሬ የለም አውሬ ብርቱ በሆነው ጉልበቱ ሰዎችን ለጊዜው ያሸንፍ ይሆናል ነገር ግን የትኛውም አውሬ ጠቢብ የሆነውንና መሳሪያዎችንም እንዴት መጠቀም እንደሚችል የሚያውቀውን የሰው ዘር ፈጽሞ ማሸነፍ አይችልም ከሰው ይበልጥ ብልህ የሆነ አውሬ የለም እግዚአብሄር በመልኩ እንደፈጠረን የተናገረው ለዚህ ነው።

በዚህ ምድር ላይ ያለው ነገር ሁሉ የሰማይ ጥላ ነው እግዚአብሄር እኛን ከፈጠረን በኋላ በፍጥረቱ ላይ እንድንሰለጥን ነገረን በዚህ የከበረ፣ ውብ፣ ዘላለማዊ ክልልና ቋንቋ ከሚገልጠው በላይ ድንቅ በሆነው በመንግስተ ሰማይ ላይ እንድንገዛ ያደርገናል እግዚአብሄር በአንድያ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሰዎችን በራሱ መልክ ፈጠራቸው የራሱ ልጆችም አድርጎ ወሰዳቸው እነዚህ ልጆች ሁሉንም ነገር እንዲያጣጥሙ መንግስተ ሰማይን በእነርሱ ይሞላል ይህ የእግዚአብሄር ዕቅድ ነው ይህ ዘላለማዊ ዕቅዱ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ «አሁን እኔ ወደ አባቴ መንግስት እሄዳለሁ ተመልሼም እመጣለሁ» (ዮሐንስ 14:1-3) ያለው ለዚህ ነው።

እግዚአብሄር እንድንወለድ የፈጠረንና ያዳነን በመንግስተ

ሰማይ ውስጥ የዘላለምን ሕይወት በረከት እንድናጣጥም ሊያስችለን ነው ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን የከበሩ በረከቶችን መቀበል ነው።

እኛን ለማዳን የሚያቅድ ሊታደገን ራሱን መስዋዕት የሚያደርግ የክብር ዙፋኑን ትቶ በውሃውና በደሙ አማካይነት የሚያድነን የራሱን ያንኑ ክብርና ስልጣን ማነው? ይህንን ምን አይነት አማልክት ወይም ፍጡር ያደርገው ነበር? ይህንን ያደረገው እግዚአብሄር ብቻ ነው ምክንያቱም ወዶናልና የሐጢያቶቻችንን ስርየት በመቀበላችን በጣም የተደሰትነው ለዚህ ነው የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንደተቀበሉ ሰዎች የሚደሰት ማንም የለም እግዚአብሄር ሰማያዊ ሐብቶችን በሙሉ ካጠራቀመልን በኋላ አሁን እኛን እየጠበቀን ነው እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ እንድንወለድ ያደረገን የሰማይን ብልጥግናዎች ሁሉ፣ መላውንም መንግስት ሊሰጠን ነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነትም ልጆቹ አድርጎናል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት መባረክ ማለት ነው በዚህ አለም ላይ እስከኖርን ድረስ የተለያዩ ወቅቶች፤ ጸደይና በጋ፣ በልግና ክረምት አሉን ሆኖም እግዚአብሄር በሁሉም የሕይወት ገጽታዎቻችን ባርኮናል እኛ ሰማያዊ በረከቶችን ሁሉ ተቀብለናል እግዚአብሄር ቋንቋ የማይገልጣቸውን መንፈሳዊ የሆኑትን የሰማይ በረከቶች ሁሉ ሰጥቶናል እናንተም ተቀብላችኋቸዋል አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ድንቅ የሆኑ በረከቶችን ተቀብለዋል።

በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ የጸታ ልዩነት የለም እኛ ወንዶችና ሴቶች የሆንን የእግዚአብሄር ልጆች ለዘላለም እንነግሳለን ለዘላለምም የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን እንቀራለን በመላዕክቶች ላይም እንኳን እንሰለጥናለን መላዕክቶች «ጌታዬ እንኳን ደህና መጣህ» ይሉናል እኛም «ተሸከመኝና እንጓዝ»

እንላቸዋለን እኛ እነዚህን በረከቶች ተቀብለናል።

ከዚህም በላይ እግዚአብሄር ምስክሮቹ እንድንሆን ጠርቶናል እኛ ዘላለማዊ በረከቶችን ለመቀበልና በዚህ ምድር ላይም የእግዚአብሄርን ክቡር ስራ ለመስራት በእግዚአብሄር የተጠራን የወንጌል ምስክሮች ነን።

እኛ በእግዚአብሄር ጽድቅ እናምናለን ምስጋናችንንም ለእርሱ እንሰጣለን እግዚአብሄር በፈጠረን ጊዜ የፈጠረን የእርሱ ልጆች ሊያደርገን ነው እግዚአብሄር ተራ ፍጡራኖች አድርጎ ቢፈጥረንና እዚያ ላይ ቢያቆም ኖሮ ለምንም የምንጠቅም ባንሆን ነበር እግዚአብሄር ለእኛ ትልቅ ዕቅድ አለው እርሱ ታላላቅ ነገሮችን ያደርጋል እርሱ ሁሉን ነገር በአደራ ሰጥቶናል በሁሉም ላይ የምንሰለጥንበትንም ስልጣንና መብት ሰጥቶናል ይህንን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስና በቤተክርስቲያን በኩል ሰጥቶናል እግዚአብሄር በቤተክርስቲያን አማካይነት እነዚህን በረከቶች ሰጥቶናል ማለት እግዚአብሄር እያንዳንዱን መንፈሳዊ የሆነ የሰማይ በረከት እያካፈለ ያለው በኢየሱስና በኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምኑ የእግዚአብሄር አገልጋዮች አማካይነት ነው ማለት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልጦናል *«ያልታወቁ ስንባል የታወቅን ነን የምንሞት ስንመስል እነሆ ሕያዋን ነን የተቀጣን ስንሆን አንገደልም ሐዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።»* *(2ኛ ቆሮንቶስ 6:9-10)*

እኛ እንዲህ አይነት ሰዎች ነን ምንም የሌለን እንመስላለን ነገር ግን ድንቆች ነን የአለም ጉዳዮች ቢረብሹዋችሁም አትዘኑ እናንተ የምትኖሩት ሕይወት የከበረ ሕይወት ነው በዚህች ፕላኔት ላይ ከእኛ በስተቀር የሐጢያት ስርየትን የተቀበለ ሌላ ሰው የለም ይህ ድንቅ በረከት ወደ እኛ የመጣው በራሳችን

ትሩፋት ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ነው።

እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስለምናምንና ወንጌልንም እያስፋፋን ስለሆነ የዳንነው እኛ ነን በእግዚአብሄር የተወደድነው እኛ ነን የእርሱ ክቡር አገልጋዮችም እኛ ነን እኛ የእግዚአብሄር ተወዳጅ ሕዝቦች ነን።

ከሐጢያቶቻችን ላዳነን ስላሴ አምላክ ምስጋናዬን ሁሉ አቀርባለሁ። ✉

በእግዚአብሄር መልክ ተፈጥረናል

« ዘፍጥረት 1:24-31 »

«እግዚአብሄርም አለ ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ እንስሳውንም እንደ ወገኑ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ እግዚአብሄርም ያ መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሄርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባህርን ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ እግዚአብሄርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሄር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው እግዚአብሄርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባህርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው እግዚአብሄርም አለ እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩ በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ ለምድርም አራዊት ሁሉ ለሰማይም ወፎች ሁሉ ሕያው ነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾችንም ሁሉ የሚበቅለው ሐመልማል ሁሉ መብል ይሁንላቸው እንዲሁም ሆነ እግዚአብሄርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ስድስተኛ ቀን::»

የዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ሰማያትና ምድር የተፈጠሩበትን ስድስተኛውን የፍጥረት ቀን ያብራራል የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ዕቅዱን በሙላቱ እንድናይ የሚፈቅድልንን የእግዚአብሄር ሰፊ ዕቅድ ንድፍ ያቀርብለናል እግዚአብሄር ይህንን ዕቅድ እንደሚፈጽምም ይተነብያል።

አምላካችን የሰውን ዘር የፈጠረው ለክብሩ ነው የክብሩ ምስጋና ልንሆን ይገባናል ዘፍጥረት 2:1 «ሰማይና ምድር ሰራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ» እንደሚል እግዚአብሄር በስድስተኛው ቀን በሰራው ስራ ማድረግ የፈለገውን ሁሉ አጠናቀቀ።

እግዚአብሄር በስድስተኛው ቀን *«ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ»* በማለቱ እርሱ ያዘዘው ሆነ እግዚአብሄር በምድር ላይ እንስሶችን ከፈጠረ በኋላ ያ መልካም እንደሆነ አየ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትን እንደወገኑ ከፈጠረ በኋላ እግዚአብሄር *«ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር»* አለ።

የሰው ዘር በእግዚአብሄር መልክ ተፈጠረ

የእግዚአብሄር መልክ ምንድነው? እግዚአብሄር በመጨረሻው የፍጥረት ቀን እንዲህ አለ *«ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር»* ይህም እግዚአብሄር እንዴት ልጆቹ እንሆን ዘንድ እንደፈጠረን ያመላክታል።

ሰማያትና ምድር እስከተፈጠሩበት እስከ አምስተኛው የፍጥረት ቀን ድረስ እግዚአብሄር በሰማያት ላይ ጸሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብቶችን እንደዚሁም እንደ አሳ ያሉ በውሃ

ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታቶችና በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎችን ፈጥሮዋል በስድስተኛው የፍጥረት ቀን እግዚአብሄር ከከብቶች ጀምሮ እስከ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታቶችና የምድር አራዊቶች ድረስ በምድር ላይ የሚኖሩ እንስሶችን ሁሉ ፈጥሮዋል ከዚህ በኋላ አምላካችን ልጆቹ በኤድን ገነት ውስጥ እንዲኖሩ ፈለገ።

እግዚአብሄር *«ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር»* ሲል የሰውን ዘር በራሱ መልክና ምሳሌ ለመፍጠር መፈለጉ እውነት ነው ይህ የእግዚአብሄር መልክ በፊቱ ፈጽመው ሐጢያት አልባ የሆኑትን የእግዚአብሄር ልጆች ያመላክታል ስለዚህ በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ቅዱሳን ሰዎችን ማለትም ጻድቃንን ሊፈጥር ፈለገ።

አጋር ምዕመናኖቼ እግዚአብሄር እኛን ሰዎች የፈጠረው ለምን አላማ ነው? እግዚአብሄር አዳኛችንን አስቀድሞ አዘጋጀ ከዚያም በመጨረሻው ቀን የራሱ ልጆች አድርጎ ሊፈጥረን ፈለገ በእርግጥም ፈጠረን እግዚአብሄርም «እግዚአብሄርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሄርም መልክ ፈጠረው» አለ እግዚአብሄር እኛን የፈጠረበት ዋናው አላማ በኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነት በኩል የእግዚአብሄርን መልክ እንድንመስል ነው ስለዚህ እኛ በእርሱ አምሳል የተፈጠርን የእግዚአብሄር እጅ ስራዎች ነን።

እግዚአብሄር ከፈጠራቸው ፍጥረታቶች ሁሉ ድንቅ የሆነው ስራ በእግዚአብሄር መልክ የተፈጠረው የሰው ዘር ነው እግዚአብሄር ተራ ፍጥረታቶች የሆኑትን ሰዎች በራሱ መለኮታዊ ባህርያት ምሳሌ ልጆቹ ማድረጉ የአምላክ ችሮታ ነው እግዚአብሄር በመጀመሪያ መላውን ዩኒቨርስ ፈጠረ ከዚያም በመጨረሻው የፍጥረት ቀን አዳምን ፈጠረ በዚህ በመጨረሻው ቀን የድንቅ ስራዎችን ሁሉ ድንቅ የሆነ ስራ ፈጠረ ይህም እግዚአብሄር በመልኩና በምሳሌው ጻድቅና ሐጢያት አልባ

ያደረገውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በኩልም የእግዚአብሄር ልጅ ወደ መሆን የተለወጠው የሰው ዘር ነበር እውነቱ ይህ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ «ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸመ» ሲል ይህ የሚጠቁመው እግዚአበሄር በመጨረሻው ቀን የፈጠረን የመሆኑን እውነታ ነው እግዚአብሄር ሰማያትና ምድር በተፈጠሩ በስድስተኛው የፍጥረት ቀን የሰውን ዘር ፈጠረ ነገር ግን ይህንን ያደረገው ሌላውን ነገር ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ብቻ ነበር ከዚህም በላይ እግዚአብሄር የሰውን ዘር የፈጠረው ልክ እንደ ሌሎቹ ፍጥረታቶች አይደለም ነገር ግን እግዚአብሄር ሰውን የፈጠረው በራሱ መልክ «በምሳሌያችን» ነበር::

ታዲያ እግዚአብር ሰዎችን በመልኩ ፈጠረ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት እግዚአብሄር ሐጢያት ስለሌለበት የሰውን ዘር ሐጢያት አልባ አድርጎ ፈጠረው እግዚአብሄር ጻድቅ ስለሆነ የሰውን ዘር ጻድቅ አድርጎ ፈጠረው እግዚአብሄር ንጉሥ ስለሆነ የንጉስነቱን ስልጣን እንዲረከቡ ሰዎችን ሐጢያት አልባና ጻድቅ ልጆቹ አድርጎ ፈጠራቸው ማለት ነው::

እኛ የእግዚአብሄር ፍጥረት ድንቅ ስራ ነን

የእግዚአብሄር ጽድቅ ወንጌል በሆነው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት ተቀብለናል እኛ የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበላችን በመልኩና በምሳሌው መሰረት በእግዚአብሄር የመፈጠራችን ነጸብራቅ ነው እግዚአብሄር በመጨረሻው የፍጥረት ቀን በስድስተኛው ቀን የሰውን ዘር በመልኩ ምሳሌ ፈጠረው::

ራሳችንን በጥንቃቄ ስንመለከት እኛ እግዚአብሄር ከሰራቸው ድንቅ ስራዎች ሁሉ የምንበልጥ ድንቅ ስራ እንደሆንን መገንዘብ ይገባናል እግዚአብሄርን መላውን ዩኒቨርስና የዚህን አለም ፍጥረቶች ሁሉ ፈጠረ ዳግም የተወለድነውን እናንተንና እኔንም መረጠን ዩኒቨርስን እንድናስተዳድርም የራሱ ልጆች አደረገን እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም ከተወለድን በኋላ አሁን በራሱ በእግዚአብሄር የአምላክ ልጆች ሆነን ተፈጥረናል።

የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብ እንደሚለው እኛ በዝግመተ ለውጥ አማካይነት በድንገት በዚህች ፕላኔት ላይ መምጣታችን ፈጽሞ እውነት አይደለም ይህ ሰው ሰራሽ መላ ምት ነው ከሌሎች ፍጥረታቶች ጋር ተስማምተን መኖራችንና እነርሱን ለማስተዳደርም መብትን አግኝተን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን መወለዳችን ተራ የሆነ ግጥምጥሞሽ ሆኖ በጭራሽ ሊገለጥ አይችልም ይህ ገና ከመጀመሪያው በእግዚአብሄር ዕቅድ መሰረት የተከናወነ አንዳች ነገር ነው እግዚአብሄር በመልኩ ፈጠረን ሐጢያት አልባና ቅዱስም አደረገን።

የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው በራሳችን ጥረትና ለውጥ አይደለም ነገር ግን ዳግም የተወለድን ጻድቃን ሆነን የተለወጥነው በአለም ላይ ባለው ነገር ሁሉ ላይ የምንሰለጥነውና የምንገዛው እግዚአብሄር አስቀድሞ በአንድያ ልጁ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ባቀደው መሰረት ነው እግዚአብሄር በመልኩ ፈጠረን ማለት ይህ ነው።

እግዚአብሄር ልጆቹ አድርጎ ሊፈጥረን ፈለገ በመጨረሻው ቀን የፈጠረንም በዚህ ፈቃድ መሰረት ነው እግዚአብሄር እኛን ሰዎችን ሲፈጥረን ምን አይነት ዕቅድ አቀደ? እግዚአብሄር ዩኒቨርስንና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ያለ አንዳች ዕቅድ አልፈጠረም እግዚአብሄር በዩኒቨርስ ውስጥ ያለውን እንዳንዱን ነገር የፈጠረው ለልጆቹ ለመስጠት ነው እግዚአብሄር

ሰዎችን በራሱ መልክ የፈጠረው ልጆቹ አድርጎ ሊቀበላቸው ነው ሰዎች ተራ ፍጥረታቶች ቢሆኑም እግዚአብሄር ሐጢያት አልባ አድርጎ ፈጠራቸው በዚህም እውነተኛ ሉአላዊ ስልጣን ያላቸው ልጆቹ አድርጎ ለወጣቸው ስለዚህ እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎች የእግዚአብሄር ፍጥረት ሁሉ እጅግ ታላቁ ድንቅ ስራ ሆነን ልንገለጥ እንችላለን፡፡

ሰው ሌላ ሰው መፍጠር ይችላል? በእርግጥም አይችልም ፍጡራኖች በመሆናችን የእግዚአብሄር ፍጥረት ክፍል ነን ነገር ግን የእግዚአብሄር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ስለሆንን ያለነው በዩኒቨርስ ውስጥ አይደለም ነገር ግን በዩኒቨርስ ላይ ቆመናል ስለዚህ እግዚአብሄር ከፈጠራቸው ፍጥረታቶቹ ሁሉ ውስጥ እኛ ን የእርሱ ልጆች አድርጎ ሊፈጥረን መምረጡ እንዴት ያለ አስገራሚና ታላቅ ጸጋ እንደሆነ ልንገነዘብ ያስፈልገናል፡፡

የተፈጠርነው እንዴት ነበር? እግዚአብሄር እንዲህ አለ *«ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር»* እግዚአብሄር ሰውን በመፍጠሩ ተደሰተ የፈጠረን እግዚአብሄር ነው፡፡

እግዚአብሄር የፈጠረን ምን አይነት ፍጡራኖች አድርጎ ነው? የፈጠረን ልጆቹ አድርጎን ነው እግዚአብሄር ራሱ ሰዎችን የራሱ ልጆች አድርጎ እንደፈጠራቸው ስለተናገረ ይህ ማለት እናንተም ደግሞ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁ ማለት ነውን? በትክክል! እናንተ ተራ ሰዎች አይደላችሁም ነገር ግን የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁ ሰዎች በተለምዶ የሰው ዘር «የፍጥረት ሁሉ ባለቤት» ነው ይላሉ ነገር ግን እኛ የእርሱን መለኮታዊ ባህሪያቶች የምንንፈል የእግዚአብሄር ልጆች ነን፡፡

«ተራ የሆኑ ፍጡራኖች ከፈጣሪ ጋር ተመሳሳይ በሆነ የስልጣን ቦታ ላይ ሊቀመጡ ይችላሉን?» አንዳንዶች ይህንን ይጠራጠሩ ይሆናል ይህ ማለት እኛ ተራ ፍጡራኖች የእግዚአብሄርን ስፍራ የምንመኝ ዕብሪተኛና ደፋሮች መሆን

ይገባናል ማለት አይደለም ይልቁንም እኛ የእግዚአብሄር ልጆች የሆንነው እግዚአብሄር ገና ከመጀመሪያው የሰውን ዘር እንዲህ አድርጎ በመልኩ ሲፈጥር ስለፈጠረንና በዚህም ስለምናምን ነው ይህ ሁሉ የተቻለው ሁሉን የሚችለው አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሆነው የአለም ፍጥረት ክፍል እንዲሆን እኛን ልጆቹን አስቀድሞ ስለፈጠረንና ይህንን ለሚያውቁና ለሚያምኑ ሰዎችም የእርሱን ስልጣንና ክብር በመስጠቱ ነው::

እኛ የእግዚአብሄር ክብር ምስጋናዎች ልንሆን ይገባናል

የእግዚአብሄር ስራ በእርግጥም አስገራሚ ነው እግዚአብሄር በመልኩ እንደፈጠረን የምንገነዘብ ከሆነ ሰይጣን ለምን እግዚአብሄርን በዚህ ምድር ላይ ሊገዳደረውና ክብሩን ሊሸፍን እንደሚሞክር መገንዘብ እንችላለን በየቀኑ ለምን ለእግዚአብሄር ምስጋናን ልንሰጠውና ከሙሉ ልባችን ልናወድሰው እንደሚገባን ምክንያቱን መረዳት እንችላለን::

እግዚአብሄር እኛን የፈጠረበት አላማ በኤፌሶን 1:12 ላይ ተብራርቷል *«ይኸውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው»* እግዚአብሄር እኛን የፈጠረበት ዋናው አላማ እዚህ ላይ ተገልጦዋል *«ይኸውም...ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው::»*

ታዲያ እግዚአብሄር የፈጠረን «ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው» ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት እግዚአብሄር ፍጡራኖች እንጂ ሌላ ያልሆንነው እኛ የእግዚአብሄርን ልጅ መልክ እንድንለብስ ፈቅዶልናል ማለት ነው የእግዚአብሄር ክብር ሌላ ሳይሆን ይህ ነው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር የራሱን ክብር አልብሶናል እኛ እርሱን የምናመሰግነው ይህንን ክብር

እንደገና ለእርሱ መልሰን እንሰጥ ዘንድ ክብሩን ስላለበሰን ነው ለእግዚአብሄር ምስጋናን የምንሰጠው ክብሩን እንድንለብስ ለፈቀደልን ጸጋ እግዚአብሄርን ለማወደስ ነው።

የእርሱ የፍጥረት አላማ *«ይሽውም በክርስቶስ አስቀድመን ተሰፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው»* እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ በስድስተኛው ቀን በራሱ መልክና ምሳሌ ፈጠረን እግዚአብሄር ተራ ፍጡራኖች የሆንነውን ልጆቹ አድርጎ ስለለወጠን ይህ ማለት እግዚአብሄር ወሰን የሌለውን ክብሩን አልብሶናል ማለት ነው እናንተና እኔ ይህንን ክብር ለብሰናል የእግዚአብሄርን ክብር የለበስንና የእርሱ ምስጋና ልንሆን የሚገባን እግዚአብሄር ልክ እንደ ራሱ መልክ ለክብሩ በፍቅሩና በጸጋው የፈጠረን መሆኑን የምናውቀው እናንተና እኔ ነን።

እግዚአብሄር ራሱን በመስጠት ፈጠረን የዚህን ጸጋ ክብር የለበስነው ለዚህ ነው እኛም የእርሱ መለኮታዊ ባህሪያት ተካፋዮች የሆንን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነናል (2ኛ ጴጥሮስ 1:4) ከእንግዲህ ወዲህ ተራ ፍጥረታቶች አይደለንም ኤፌሶን 1:12 *«ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ»* የሚለው እግዚአብሄር እንዲህ ግርማውንና ክብሩን ስላለበሰን ነው አሁን ከእግዚአብሄር ዘንድ የሐጢያቶቻችንን ስርየት ስለተቀበልን ምን ያህል የከበርንና ያማርን እንደሆንን ልንገነዘብ ያስፈልገናል።

ባለ መዝሙሩ ዳዊት እንዲህ ብሎዋል *«ሰእምሮ የሌለው ክቡር ሰው እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ» (መዝሙረ ዳዊት 49:20)* ነገሩ ለምን እንዲህ ሆነ? እግዚአብሄር ከእናቶቻችን ማህጸን እንድንወጣና በዚህ አለም ላይ ሕይወታችንን እንድንኖር የላከን በከንቱ እንድንኖር አይደለም።

ይህ ሆኖ እያለ ሰዎች የቀድሞውን ማንነታቸውን ስለማይገነዘቡ በየጊዜው ሕይወታቸው ምን ያህል ጎስቋላ

እንደሆነ እያሰቡ ያለቅሳሉ «ሕይወቱ ከእንስሳም የባሰ ነው! በዚህ ምድር ላይ ለምን ተወለድሁ?» እያሉ በማላዘን አምርረው ያጉረመርማሉ ነገር ግን አምላካችን እንደዚህ እንድንኖር ያለ ምንም አላማ ወደ አፈር እንድንመለስ ብቻ በከንቱ እንድንወለድ ፈጽሞ አልፈጠረንም።

እግዚአብሄር ክብሩን በማልበስ የራሱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አድርጎናል የእግዚአብሄር አብን ክብር ለዘላለም እናመሰግን ዘንድ እግዚአብሄር በራሱ መልክ ፈጠረን ክብሩንም አለበሰን እግዚአብሄር የፈጠረን ለዚህ ነው እግዚአብሄር የፈጠረንና በዚህ ምድር ላይ እንድንወለድ የፈቀደልን በፈጠረው ዩኒቨርስ ሁሉ ላይ ያለውን ሉአላዊነቱንና ክብሩን እናመሰግን ዘንድ ነው።

ይህ ምንኛ አስገራሚ ነው! እኛ ምንም አናውቅም ነበር ተራ ረዳተ ቢስና ሐይል አልባ ፍጡራኖች ነበርን አሁን ግን በጌታ ስለሆንን ምንኛ ተለወጥን? የጌታን ክብር ለብሰናል አሁን በእርሱ እየኖርን ነው የእግዚአብሄርን ክብር እንድናመሰግን ተደርገናል እግዚአብሄር እርሱን እንድናከብረው ጠርቶናል አምላክ ከፈጠራቸው በርካታ ፍጥረታቶች እግዚአብሄር ዳግም ተወልደን ሲያየን ይደሰታል እኛም እግዚአብሄርን ለጸጋው እናወድሰዋለን እናመሰግነውማለን።

ክብራችን እንዲህ ስለሆነ መላዕክቶች እንኳን ይመኙታል መላዕክቶች እንኳን «ሰዎች እንዴት የእግዚአብሄር ልጆች ሆኑ? እንዴት የእግዚአብሄርን መልክ ይመስላሉ?» ብለው በመገረም ለእኛ የተሰጠንን የእግዚአብሄር ጸጋ ይመኛሉ እግዚአብሄር በመጀመሪያ ከመላዕክቶች በጥቂት አሳንሶ ፈጠረን የእርሱ ዕቅድ ግን በራሱ መልክና ምሳሌ ዳግመኛ ሊፈጥረን ነበር።

የአምልኮ አገልግሎትን ስንጀምር ሁሌም እግዚአብሄርን የሚያመሰግኑ ዝማሬዎችን እንዘምራለን የእኛ ምስጋና የአለም

ሐይማኖተኞች ከሚያቀርቡት አሰልቺ ምስጋና የተለየ ነው እግዚአብሄር ክብሩን ስላለበሰንና በከበረው ብርሃኑ አማካይነትም ፍቅሩንና ጸጋውን ስለለገሰን በከንፈሮቻችን እግዚአብሄርን እናመሰግናለን ክብራችን የሆነውን እግዚአብሄርን ለማመስገንና ይህንን ክብሩን ስላለበሰን እርሱን ለማወደስ አንደበቶቻችንን ከፍተን ላደረገው ለእያንዳንዱ ነገር ከፍ እናደርገዋለን ምስጋና ማለት ይህ ነው እኛ ለእርሱ የምናቀርበው ትክክለኛ ምስጋና ይህ ነው እግዚአብሄርን ጮክ ብለው የሚያመሰግኑት ልቦቻችን ናቸው ስላደረገልን ነገር አምላካችንን የምናመሰግነው በአንድ ልብ በተቆራኙ ልቦቻችን ነው።

ስለዚህ ስናመሰግን ዝም ብለን በከንቱ ልንዘምር አይገባንም አምላካችን ምን አይነት ክብር እንደሰጠን ማስታወስ ይገባናል እግዚአብሄር ልጆቹ እንዳደረገን፣ በክብርና በግርማ እንዳለበሰንና በዘላለም ሕይወት ውስጥ እንድንኖር እንዳዘጋጀልን ማስታወስ አለብን ስናመሰግን እግዚአብሄር ያለበሰንን ክብር እያስታወስን ሊሆን ይገባል።

እግዚአብሄር ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ታድጎናል

እግዚአብሄር በስድስተኛው ቀን ያደረገው ነገር በጣም አስገራሚ ነው! እግዚአብሄር ሰማያትንና ምድርን በዚህ አለም ላይም ያለውን እያንዳንዱን ነገር ከፈጠረ በኋላ ድንቅ የሆነ ነገር አደረገ ለዚህ ስራውም እናመሰግነዋለን።

እግዚአብሄር በአምስተኛው ቀን ለሕዝቡ ምን አይነት አስገራሚ ስራ ሰራ? አጋር ምዕመናኖቼ እግዚአብሄር በአምስተኛው ቀን እንዴት በእምነት መኖር እንደምንችል ነግሮናል እምነታችን እንዲያድግና በእምነት መኖር እንድንችል

እንዳደረገም ነግሮናል እግዚአብሄር በአምስተኛው ቀን ያደረገው ነገር በጣም አስገራሚ ነው! እግዚአብሄር ዳግም ከተወለድን በኋላ በእምነት እንኖር ዘንድ እንደ ክንፎች ያለ ትልቅ እምነት ሰጥቶናል እግዚአብሄር ጻድቃን ከዚህ አለም ምድር ከፍ እንዲሉና በሰማያት ጠፈር ላጠይ እንዲበሩ አድርጎዋቸዋል።

ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች በእምነት የሚኖሩበት መንገድ የለም አንድ ጊዜ ከዚህ ምድር ላይ ከለቀቁ አይተርፉም በአንጻሩ እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎች በዚህ ምድር ላይ ብንኖርም ምድራዊው ሕይወታችን ትክክለኛው ሕይወታችን አይደለም ነገር ግን ሰማያዊ ሕይወትን እንኖራለን በእምነትም ሰማያዊ ስራዎችን እንሰራለን በሌላ አነጋገር እኛ ዳግም የተወለድን ጻድቃን ሰዎች የምንኖረው ምድራዊ ሕይወትን ሳይሆን ሰማያዊ ሕይወትን ነው።

ይህ ማለት አሁን ዳግም የተወለዱ ሰዎች ዳግመኛ ለምድራዊ ነገሮች ሊኖሩ አይገባቸውም ነገር ግን የዘላለምን ሕይወት ተስፋ እያደረጉ በእምነት መንፈሳዊ ሕይወትን ሊኖሩ ይገባል ማለት ነው በእግዚአብሄር በመታመን በልጁ ግዛት ውስጥ በነጻነት እንድንደሰትና የእርሱን የጽድቅ ስራ እንድንሰራ እግዚአብሄር የእምነት ሰዎች አድርጎናል።

ኤፌሶን 1:14 እንዲህ ይላል *«እርሱም የርስታችን መያዣ ነው ለእግዚአብሄር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል»* እግዚአብሄር በዋጋ የገዛቸውን ዋጅቶዋቸዋል! አጋር ምዕመናኖቼ እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ልጆቹ አድርጎ ዋጅቶናል እግዚአብሄር አብ በመልኩ ፈጠረን እግዚአብሄር እኛን በመዋጀት የራሱ ልጆች አድርጎ ወሰደን።

በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ካዳነን በኋላ ሙሉ በሙሉ በእኛ ላይ መንገስ ጀመረ እኛ ፈጽሞ ከቤዛነት እጆቹ ማምለጥ አንችልም እኛ ፈጽሞ ከእግዚአብሄር ክብር መለየት አንችልም

እግዚአብሄር ዳግም የተወለዱ ሰዎቹን ይመራቸዋል ዳግመኛ ፈጽሞ ለዲያብሎስ እንዳንሆን ሙሉ በሙሉ በእነርሱ ላይ ይነግሳል::

ኤፌሶን 1:5-6 እግዚአብሄር እኛን የፈጠረበትን አላማ አብራርቷል እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል «በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ» እግዚአብሄር ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ አድርጎ የፈጠረን «በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ» ነው::

እግዚአብሄር ልጆቹ አድርጎ ፈጥሮናል እግዚአብሄር በጸጋው ከሐጢያቶቻችን አንጽቶናል እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደ አመዳይ አንጽቶዋቸዋል ዳግመኛ ለሐጢያት መስዋዕት እንዳይኖርና ዳግመኛ የሐጢያት ስርየትን የመቀበል ምክንያት እንዳይኖር እግዚአብሄር ሙሉ በሙሉ ፈጽሞ አዳነን እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ሐጢአት ማቅረብ የለም» (ዕብራውያን 10:18)* ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋው አድኖናል ማለለት ኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ አድርጎናል ማለት ነው::

«የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ» አምላኝችን የፍቅርና የምህረት አምላክ ስለሆነ እናመሰግነዋለን እርሱ የጸጋ አምላክ ስለሆነ እጅግ የተትረፈረፈ ጸጋውን ሰጥቶናል ፈጽሞ ወዶናል ጸጋውንም ፈጽሞ አልብሶናል ያለ እንከንም ክብሩን ሰጥቶናል እኛም ለዚህ ሁሉ እናመሰግነዋለን እግዚአብሄር ከፍ እንናደርገው ዘንድ ያዳነን እርሱን -- ጸጋውን፣ ክብሩንና ፍቅሩን -- እንድናመሰግን ፈቅዶልን ነው ስለዚህ የእግዚአብሄርን ክብር ለማመስገን ድምጻችንን ከፍ ስናደርግ እግዚአብሄር እኛን

በመፍጠሩና በማዳኑ በጣም ደስ ይለዋል።

በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሄርን ክብር መግለጥ ያለብን እናንተና እኔ ነን የእግዚአብሄርን ክብር ማወጅ ያለባቸው ዳግም የተወለዱት ናቸው አምላካችን በመጨረሻው የፍጥረት ቀን የሰውን ዘር ፈጠረ ወንድና ሴት አድርጎም ፈጠራቸው አምላንችንም ባረካቸው «በምድር ላይ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ግዙ» በማለትም በፍጥረት ሁሉ ላይ ስልጣንን ሰጣቸው እግዚአብሄር ሲፈጥረን እንደ ሌላው ነገር ተራ ፍጥረታቶች አድርጎ አልፈጠረንም በጥቅል አነጋገር እግዚአብሄር ሰዎችን በራሱ መልክ ምሳሌ የእርሱ መለኮታዊ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አድርጎ ፈጠራቸው ክብሩንም አለበሳቸው ነገር ግን በርካታ ሰዎች ይህንን አሁንም ድረስ ባለማወቃቸው ተጎሳቁለው ለመጥፋት ብቻ በዚህ አለም ላይ በከንቱ መኖራቸው የሚያሳዝን ነው።

መንፈሳዊ ሕይወት ምንድነው?

አጋር ምዕመናኖቼ መንፈሳዊ ሕይወትን ኖራችኋልን? መንፈሳዊ ሕይወትን ስንኖር እግዚአብሄር እንዴት እንዳከበረን መገንዘብ እንችላለን መንፈሳዊ ሕይወትን መኖር የምንጀምረው ዳግም ከተወለድን በኋላ ነው ታዲያ መንፈሳዊ ሕይወት ምንድነው? ለእግዚአብሄር ለወንጌልና ለእውነት በእምነት መኖርና በምድር ነገሮች ላይ መግዛት ነው ዳግም የተወለድን እናንተና እኔ «እግዚአብሄር ለጽድቅ ስራው እንድንኖር እያደረገን ነው» የሚል እምነት ካለን የጽድቅን ስራ እንድንሰራና መንፈሳዊ አገለግሎቶችን እንድንፈጽም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልቦቻችን ይበረታሉ በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር መንፈሳዊ የሆኑ የጽደቅ ስራዎችን በአደራ ሰጥቶናል የጌታን ስራ ስንሰራና

ሕይወታችንንም ለጌታ ስንኖር የእግዚአብሄር ጸጋ ክብር የሚገለጠው በዚህ ነው እግዚአብሄር ራሱም በእኛ ይከብራል።

አምላካችን ምስጋናችንን ሲሰማ ይከብራል እግዚአብሄር በምንሰራው በዚህ ወንጌልን የማስፋፋት ስራ፣ በምንኖረው ሕይወትና በምናደርገው በእያንዳንዱ ነገርም እንደዚሁ ይከብራል የእግዚአብሄር ክብርና ስልጣን የሚታየው፣ ስልጣኑ የሚገለጠውና መለኮታዊነቱ የሚታወጀው በእምነታችን አማካይነት ነው።

ሰይጣን ዕብሪቱ ለውደቀት የዳረገው የወደቀ መልአክ ነው ዲያብሎስ እግዚአብሄርን በመገዳደር እንዲህ አለ *«ከዳመናዎች ከፍታ በላይ አርጋለሁ በልዑልም እመሰላለሁ» (ኢሳይያስ 14:14)* እግዚአብሄር ግን ይህንን መልአክ ከመንግስቱ አባረረው እርሱን የተከተሉትንም ሌሎች መላዕክቶች እንደዚሁ አባረራቸው ከዚያም ሰውን በመልኩ አምሳል ፈጠረው መላዕክቶችም እንኳን በእግዚአብሄር መልክ የተፈጠሩትን ሰዎች ሲመለከቱ የሚቀኑባቸው ለዚህ ነው ምክንያቱም እግዚአብሄር ሰዎችን ያከበራቸው ልጆቹ እንዲሆኑ ነው መላዕክቶች ይህንን ክብር መልበስ እንዲችሉ ቢመኙም እግዚአብሄር የፈጠራቸው አገልጋዮቹ እንዲሆኑ ነው ሰዎችን ግን ልጆቹ አደረጋቸው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚለው ለዚህ ነው *«እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሰራ እንደ እርሱ አሳብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን።» (ኤፌሶን 1:11)*

እግዚአብሄር በፍላጎቱ መሰረት ፈጠረን በፈቃዱም መሰረት ፈጠረን ስለዚህ ፍጥረት እግዚአብሄርን መቃወም አይችልም እግዚአብሄር ከወንድ አንድ አጥንት ወስዶ ሴትን ሰራት እግዚአብሄር የአካሉን ክፋይ በመስጠት ዳግም እንድንወለድ ፈጠረን እግዚአብሄር ምንም ምላሽ ሳይጠብቅ ሰዎችን በመልኩ ፈጠራቸው የአካሉንም ክፋይ በነጻነት ሰጣቸው ሕይወቱን

በውስጣቸው ተነፈሰባቸው ልጆቹም አድርጎ ወሰዳቸው የስጋ ወላጆችም እንኳን ልጆቻቸውን ሲጸንሱዋቸው የራሳቸውን ክፋይ ለእነርሱ ይሰጣሉ ልክ እንደዚሁ የእግዚአብሄርን መንፈሳዊ ሕይወት ለዘላለም እንዲኖሩ እግዚአብሄር ክብሩን ለሰዎች ለገሰ ሕይወትንም ሰጣቸው በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ሕይወቱን ለሰው ዘር በመስጠትና በመቀደስ ልክ እንደ እርሱ ቅዱሳን እንድንሆን ፈጠረን የእግዚአብሄር ክብር ሌላ ሳይሆን ይህ ነው።

«ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸመ» (ዘፍጥረት 2:1) አምላካችን በዘፍጥረት ውስጥ እየነገረን ያለው ነገር ምንኛ ድንቅ ነው! እግዚአብሄር እናንተንና እኔን ዳግም እንድንወለድ በመፍጠር ማድረግ የፈለገውን ሁሉ አጠናቀቀ።

እግዚአብሄር የሰው ዘር ዳግም እንዲወለድ ከፈጠረው በኋላ ያረፈው ለዚህ ነው ዳግም የተወለዱትንም ለዘላለም በኤድን ገነት እንዲኖሩ ፈጠራቸው ከዚህም በላይ እግዚአብሄር ልጆቹ በመላው ላይ ላይ ባለው በእያንዳንዱ ነገር ላይ እንዲሰለጥኑ ፈቅዶዋል ስለዚህ የእርሱ ልጆች ሆነን በእግዚአብሄር ግዛት ላይ መሰልጠን ያለብን እናንተና እኔ ነን።

አጋር ምዕመናኖቼ ሕይወታችን የሚመራው በማንኛውም ሰው ነውን? አይደለም በዚህ ምድር ላይ ብንኖርም አለም አይገዛንም ታዲያ ዝም ብለን በዚህ አለም ላይ የምንኖር ሰዎች ነን? አይደለንም እኛ እንደዚህ አይነት ሰዎች አይደለንም ማን እንደሆንን ታውቃላችሁን? ከእግዚአብሄር ውጪ በእኛ ላይ የሚሰለጥን ሌላ ማንም የለም በስራ ቦታችሁ ላይ ምናልባት በአለቃችሁ የተገለላችሁ መስሎ ይሰማችሁ ይሆናል አይደል? ነገር ግን አለቃችሁ ልቦቻችሁን ያዛልን? የለም በእርግጥ አያዝም! በልቦቻችን ላይ ስልጣን ያለው እግዚአብሄር እንጂ ማንም አይደለም።

እኛ በማንም ሰው የማንተዳደር የእግዚአብሄር ሕዝብ ነን

ንጉሳችን ራሱ እግዚአብሄር ነው እኛም የእርሱ ልጆች ነን የእርሱ ልጆች በመሆናችንም በዚህ አለም ላይ ለመሰልጠን እንኖራለን::

የእግዚአብሄርን ክብር እናመሰግናለን

አጋር ምዕመናኖቼ ጌታችን መንፈሳዊ ሕይወትን እንድንኖር አስችሎናል እግዚአብሄር በእምነት እንድንኖር አስችሎናል የጽድቁንም ባለጠግነት አትረፍረፎ ለግሶናል እምነታችን እንዲያድግም መግቦናል ሁላችንንም ባርኮናል አምላካችን ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ብርሃንን ከጨለማ የእርሱን ሕዝብ ከቀሩት ሕዝቦች ከጎኑ የሚቆሙትንም ከጎኑ ከማይቆሙት ሰዎች ለይቶዋል::

ዳግም ከተወለድንና እግዚአብሄር ከፍጡራኖቹ ሁሉ ለምን እንደወደደንና እንዳዳነን ከተገነዘብን በኋላ አሁን ከእግዚአብሄር ወገን መቆም እንችላለን የእርሱን ቃልና ክብር በመቀበል በእግዚአብሄር ወገን የቆሙ ሰዎች የእግዚአብሄርን ክብር ይለብሳሉ ያ የእግዚአብሄር ጽድቅ ነው ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የእግዚአብሄር ልጆች ሲሆኑ ሌሎች ግን የኢየሱስ ክርስቶስን ግርማዊ ክብርና ጸጋውን አልተቀበሉም እነዚህ ሰዎች ከሰይጣን ጎን ይቆማሉ ስለዚህ እግዚአብሄር ክብሩን ሊያለብሳቸው አይችልም::

የእግዚአብሄር ክብር መላውን ዩኒቨርስ ይህንን ጠፈርና እኛን አትረፍርፎ ሞልቶዋል እግዚአብሄር በጽድቁ አጽድቆናል እግዚአብሄር እኛን በመልኩና በምሳሌው መፍጠሩ እግዚአብሄር በኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን ከሁሉ የሚበልጥ እጅግ ታላቅ ክብር ነው::

ነገር ግን በርካታ ሰዎች በአየር ላይ ስልጣን ያለውን አለቃ የሰይጣን ዲያብሎስን ቃሎች ያምናሉ በእርሱ ቃሎችም ተታለዋል የእግዚአብሄርንም ክብር መልበስ አልቻሉም በርካታ ሰዎች እግዚአብሄርን እየተቃወሙ በዚህ ምድር ላይ የተረገመ ሕይወትን ሲኖሩ እናያለን።

አሁን የእግዚአብሄርን መልዕክት አጠቃለን ወደ ድምዳሜ እንድረስ አሁን እኛ በእግዚአብሄር ፊት የዚህ ምድርና የመንግስተ ሰማይ ባለቤቶች መሆን የምንችለው እንዴት ነው? የእግዚአብሄርን መንግስትና የጌታችንን ክብር በሁሉም ስፍራ የምናውጅበትን የእግዚአብሄር ጸጋ የለበስነው እንዴት ነው? እኛ ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር እንዲህ ባሉ ታላላቅ በረከቶች ውስጥ እንድንኖር ስለፈቀደልን፣ የራሱ የእግዚአብሄር ልጆች እንድንሆን ስላከበረንና መንፈሳዊ ሕይወትን እንድንኖር ስለፈጠረን ለእግዚአብሄር ምስጋናን ማቅረብ ብቻ ነው።

እናንተና እኔ የመንግስተ ሰማይ ንጉሶች ነን እግዚአብሄር ይህንን ጸጋ ሰጥቶናል እግዚአብሄር ወሰን የሌለውን ፍቅሩን አልብሶናል እግዚአብሄር የእርሱ ልጆች እንድንሆን እንዲህ ያለ ክብር ሰጥቶናል እግዚአብሄር በጸጋው አማካይነት የእርሱ ልጆች አድርጎ በመፍጠር መለኮታዊ ባህሪያቶቹን እንድንካፈል አስችሎናል ልክ እንደ እርሱ ቅዱሳን የሆንን ሰዎች አድርጎም ፈጥሮናል ለዚህም እግዚአብሄርን ለዘላለም ልናመሰግነው፣ ልናወድሰው፣ የእርሱን ጽድቅ ልናስፋፋና ለዚህ ጽድቅም መንፈሳዊ ሕይወታችንን ልንኖር ይገባናል።

እግዚአብሄር ጻድቃንን በዚህ ምድር ላይ ያስቀመጣቸው በከንቱ እንዲኖሩ አይደለም እግዚአብሄር ያዳነን ክብሩን እንድናመሰግን ነው ኢየሱስ ክርስቶስ አድኖናል እግዚአብሄር ልጆቹ አድርጎናል እኛ በፍጡራኖች መካከል ብንኖርም እግዚአብሄር እኛ ፍጡራኖች ብቻ ሳንሆን የእርሱ ልጆችና

የመንግስተ ሰማይ ንጉሶች እንደሆንን እየነገረን ነው።።

አሁን የእግዚአብሄር ንጉሶች ስለሆንን የእግዚአብሄርም ፍቅር ወሰን ስለሌለውና እግዚአብሄርም ይህንን ጸጋ ስለሰጠን እነዚህን ሁሉ ድንቆች መመስከር እግዚአብሄርንም ለጸጋው፣ ለፍቅሩና ለበረከቶቹ ሁሉ ልናመሰግነው ይገባናል ጸጋውን ላለበሰን አምላኳችን ክብርን ሁሉ እሰጣለሁ! እንዲህ የእግዚአብሄር ልጆች ስላደረገንም ምስጋናዬን ሁሉ ለእርሱ አቀርባለሁ አከብረውማለሁ!

እኛ አሁን እግዚአብሄር በሕይወታችን የሰጠንን እያንዳንዱን ነገር እያጣጣምን ነው የእግዚአብሄር ልጆች ስለሆንን አብ በሰጠን እንደሰታለን የእርሱ ሕዝቦች ስለሆንን ጌታ ንጉሳችን መሆኑን ለሁሉም እንመሰክራለን የእርሱ አገልጋዮች ስለሆንን ፈጣሪ ጌታችንን እናገለግላለን የመንግስቱ ንጉሶች ስለሆንን በሁሉም ላይ እንነግሳለን ቀሪውን ሕይወታችንን የምንኖረው እንዲህ ነው የቀን ተቀን ሕይወታችንን የምንኖረው በበረከቶች በተሞሉ ልቦች ነው ወደ ጌታችን መንግስት ስንሄድም በግርማው፣ በክብሩ፣ በበረከቶቹና በጸጋው ሁሉ እየተደሰትን ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንኖራለን።። ✉

This **eBook** was created to preach the gospel of the Water and the Spirit all over the world through **Paul C. Jong's Christian Book Series .**

For more information on
Paul C. Jong's Christian Book Series,
visit us on the Web at "**www.bjnewlife.org**" **&**
"**www.nlmission.com**"

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) **በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።**